# ስንክሳር ዘወርኀ ታኅሣሥ

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ ወርኀ ፡ ታኅሣሥ ፡ ቡሩክ ፡ መዓልቱ፡ ፱ቲ ፡ ሰዓት ፡ ወእምዝ ፡ ይትዌሰክ፡ ወአመ ፡ ፩ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ አስተርእዮተ ፡ ኤልያስ ፡ ነቢይ ፡ ቅድመ ፡ እስራኤል ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ኤልያስ ፡ ቀናኢ ፡ እምዘመደ ፡ ሌዊ ፡ ውእቱ ፡ ወስመ ፡ አቡሁ፡ኢያስኑዩ፡ወስማ፡ለእሙ፡ቶና።

፪፡ ወተብህለ ፡ በእንቲአሁ ፡ እስመ ፡ በዕለተ ፡ ተወልደ ፡ ርእየ ፡ አቡሁ ፡ ፬ተ ፡ ዕደወ ፡ ብርሃና ውያነ ፡ እንዘ ፡ ይሰግዱ ፡ ሎቱ፡ ወጠብለልዎ ፡ በእሳት፡ህየንተ፡አጽርቅት፡ዘይጠበለሉ፡ቦቱ፡ ሕፃናት፡ወውእቱ፡መጽአ፡ኀበ፡ኢየሩሳሌም፡ ወነገሮሙ፡ለካህናት፡ዘንተ፡ወተበሀሉ፡እሙ ንቱ፡ቦኑ፡ይከውንኑ፡ማኅደሩ፡ውስተ፡ብርሃን፡ ወይከውንኑ፡መታሬ፡በቃሉ፡ወይኴንኖሙ፡ ለእስራኤል፡በሰይፍ፡ወበእሳት።

፫፡ ወዜና ፡ ተአምራቲሁሰ ፡ ዘገብረ ፡ በመዋዕለ ፡ አክዓብ ፡ ንጉሠ ፡ እስራኤል ፡ ወብእሲቱ ፡ ኤል ዛቤል ፡ ወበወልዱ ፡ አካዝያስ ፡ ሀሎ ፡ ጽሑፈ ፡ ውስተ ፡ መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ወዜና ፡ ዕርገቱሰ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ ሀሎ ፡ ጽሑፈ ፡ አመ ፡ ፮ለወርኀ ፡ ጥር።

፬፡ ወበእንተ ፡ ሞቱሰ ፡ ዘይከውን ፡ ድኅረ ፡ ይነግር ፡ ዮሐንስ ፡ አቡቀለምሲስ ፡ ከመ ፡ ይመጽእ ፡ ምስለ፡ ሄኖክ ፡ ወይትቃወምዎ ፡ ለሐሳዊ ፡ መሲሕ ፡ ወይገብሩ ፡ ተአምራተ ። ወሰመዮሙ፡ ክልኤ ፡ ዕፀ ፡ ዘይት ፡ ወክልኤ ፡ መኃትወ ፡ እለ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ እለ ፡ ሥዩማን ፡ ላዕለ ፡ ምድር።

፭፡ ወለዘፈቀደ ፡ ይሥሐጦሙ ፡ እምውስተ ፡ ጸላ እቶሙ ፡ ትወጽእ ፡ እሳት ፡ እምነ ፡ አፉሆሙ ፡ ወታጠፍአሙ ፡ ለጸላእቶሙ ፡ ወከመዝ ፡ ይመ ውቱ፡እለ፡ይስሕጥዎሙ፡

፮፡እስመ፡እሙንቱ፡ሥሉጣን፡ላዕለ፡ሰማይ፡ከመ፡ ይዕጽውዋ ፡ ከመ ፡ ኢይዝንም ፡ ዝናም ፡ ላዕለ ፡ ምድር ፡ በመዋዕለ ፡ ትንቢቶሙ ። ወዓዲ ፡ ሥሉ ጣን ፡ እሙንቱ ፡ ላዕለ ፡ ማይ ፡ ከመ፡ ይረ

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ፡ በወልድ፡ በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡የተባረከ፡የታኅሣሥ፡ ወር ፡ የቀኑ ፡ ሰዓት ፡ ዘጠኝ ፡ ሲሆን ፡ ከእንግ ዲህም ፡ ይጨመራል ፡ በዚችም ፡ በታኅሣሥ ፡ አንድ፡ቀን፡በእስራኤል፡ፊት፡ነቢይ፡ኤልያስ፡ የተገለጠበት ፡ ነው ። ይህ ፡ ቀናኢ ፡ ኤልያስ ፡ ከሌዊ ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ የአባቱ ፡ ስም ፡ ኢያስኑዩ፡ የእናቱም፡ስሟ፡ቶና፡ነው።

፪፡ ስለርሱም ፡ እንዲህ ፡ ተነገረ ፡ በተወለደ ፡ ጊዜ ፡ ብርሃንን ፡ የለበሱ፡ አራት ፡ ሰዎች ፡ ሲሰግዱ ለትና ፡ ሕፃናት ፡ በሚጠቀለሉበት ፡ ጨርቅ ፡ ፈንታ ፡ በእሳት ፡ ሲጠቀልሉት ፡ አባቱ ፡ አየ ። እርሱም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጥቶ ፡ ይህን ፡ ለካህናቱ ፡ ነገራቸው ፡ እነርሱም ፡ ማደሪያው ፡ በብርሃን፡ውስጥ፡ይሆን፡በቃሉም፡የሚቆርጥ፡ ይሆን ፡ ወይም ፡ እስራኤልን ፡ በሰይፍና ፡ በእሳት፡እየቀጣ፡ይገዛቸው፡ይሆን፡ተባባሉ።

፫፡በእስራኤል፡ንጉሥ፡በአክዓብና፡በሚስቱ፡በኤ ልዛቤል ፡ በልጁም ፡ በአካዝያስም ፡ ዘመን ፡ ያደረገው ፡ የተአምራቱ ፡ ዜና ፡ በመጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ተጽፎአል ። ወደ ፡ ሰማይ ፡ ያረገበት ፡ ዜናው ፡ ግን፡በጥር፡ወር፡ በስድስት ፡ ቀን ፡ ተጽፎአል።

፬፡ በኋላ ፡ ጊዜም ፡ ስለሚሆነው ፡ ሞቱ ፡ ራእይን፡ በሕይወቱ ፡ ያየ ፡ ዮሐንስ ፡ ከሄኖክ ፡ ጋር ፡ እንደ ሚመጣና ፡ ሐሳዊ ፡ መሲሕን ፡ እንደሚቃ ወሙት፡ተአምራትንም፡እንደሚያደርጉ፡ተና ግሮአል ። ሁለቱ ፡ የዘይት ፡ ዕንጨቶች ፡ በምድር፡ ላይም ፡ የተሾሙ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የሚያበሩ ፡ ሁለት ፡ መብራቶች ፡ ናቸው ፡ አለ።

፭፡ ከጠላቶቻቸውም ፡ ወገን ፡ ሊጣላቸው ፡ የወደ ደውን ፡ እሳት ፡ ከአፋቸው ፡ ወጥታ ፡ ታጠፋቸ ዋለች፡የሚጣሏቸው፡እንዲህ፡ይጠፋሉ።

፮፡ትንቢት፡በሚናገሩበት፡ወራት፡በምድር፡ላይ፡ ዝናም፡እንዳይዘንም፡ይዘጓት፡ዘንድ፡በሰማይ፡ ላይ፡ሥልጣን፡አላቸውና፡ዳግመኛም፡ደምን፡ ያደርጉት ፡ ዘንድ ፡ በውኃው ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡

www.ethiopianorthodox.org

፲፭፡ ወበዛቲ፡ዕለት፡አዕረፈ፡ናቡቴ፡እስራኤላዊ።
እስመ፡ለዝንቱ፡ናቡቴ፡ቦቱ፡ዐፀደ፡ወይን፡
ውስተ ፡ ጥቃ ፡ ቤቱ ፡ ለአክዓብ ፡ ንጉሠ ፡
ሰማርያ።

፲፮፡ ወይቤሎ ፡ አክዓብ ፡ ለናቡቴ ፡ ሀበኒ ፡ ዘንተ ፡
ዐፀደ፡ ወይንከ ፡ ይኩነኒ ፡ ዐፀደ ፡ ሐምል ፡
እስመ፡ ቅሩብ ፡ ውእቱ ፡ ለቤትየ ፡ ወእሁበከ ፡
ዐፀደ ፡ ወይን ፡ ካልዐ ፡ ዘይኄይስ ፡ እምኔሁ ፡
ወእመ፡ትፈቅድ፡እሁበከ፡ወርቀ፡ሤጠ፡ለዝ፡
ዐፀደ፡ወይንከ፡ወይኩነኒ፡ዐፀደ፡ሐምል።

፲፯፡ ወይቤሎ፡ናቡቴ፡ለአክዓብ፡ኢያምጽእ፡ሊተ፡
እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ አሀብከ ፡ ርስተ ፡
አበውየ።

፲፰፡ ወተከዘ ፡ አክዓብ ፡ ወሖረ ፡ ወሰከበ ፡ ውስተ ፡
ምስካቢሁ ፡ ወተከድነ ፡ ገጾ ፡ ወኢበልዐ ፡
እክለ።

፲፱፡ ወቦአት ፡ ኤልዛቤል ፡ ብእሲቱ ፡ ኀቤሁ ፡
ወትቤሎ፡ምንተ፡ኮንከ፡ዘኢትበልዕ፡እክለ፡
ወምንት፡ያቴክዘከ።

፳፡ ወይቤላ፡እስመ፡ተናገርክዎ፡ለናቡቴ፡ኢይዝራ
ኤላዊ፡ወእቤሎ፡ሀበኒ፡ዐፀደ፡ወይንከ፡በሤጠ፡
ወርቅ ፡ ወእመኒ ፡ ትፈቅድ፡ እሁበከ ፡ ዐፀደ ፡
ወይን ፡ ካልዐ ፡ ህየንቴሁ ፡ ወይቤለኒ ፡
ኢይሁበከ፡ርስተ፡አበውየ።

፳፩፡ ወትቤሎ ፡ ኤልዛቤል ፡ ብእሲቱ ፡ አንተኑ ፡
እንከ፡ይእዜ፡ከመዝ፡ትሬሲ፡ንጉሦሙ፡ለእስ
ራኤል፡አንተ፡ተንሥእ፡ወብላዕ፡ወአጽንዕ፡
ርእሰከ፡ወይትፌሣሕከ፡ልብከ፡እሁበከ፡አነ፡
ዐፀደ፡ወይኑ፡ለናቡቴ፡ኢይዝራኤላዊ።

፳፪፡ ወጸሐፈት ፡ በስመ ፡ አክዓብ ፡ ወኀተመት ፡
በማኅተሙ ፡ ወፈነወታ ፡ ለይእቲ ፡ መጽሐፍ፡
ኀበ፡ሊቃናት፡ይእቲ፡ሀገር፡ወኀበ፡ዐበይት፡
ውእቱ፡ብሔር፡እለ፡ይነብሩ፡ምስለ፡ናቡቴ።

፳፫፡ ወከመዝ ፡ ይብል ፡ ቃላ ፡ ለይእቲ ፡ መጽሐፍ ፡
ጹሙ ፡ ጾመ ፡ ወአንብርዎ ፡ ለናቡቴ ፡ ቅድመ ፡
ሕዝብ ፡ ወአቅሙ ፡ ሎቱ ፡ ቅድሜሁ ፡ ፪ተ ፡
ዕደወ ፡ ውሉደ ፡ ዐመፃ ፡ ይኩኑ ፡ ስምዐ ፡
ላዕሌሁ፡ ወይበልዎ ፡ ባረካሁ ፡ ለእግዚአ
ብሔር ፡ ወለንጉሥ ፡ ወአውጽእዎ ፡ አፍአ ፡
ወገርዎ፡ወይሙት።

፲፭፡ በዚቺም ፡ ዕለት ፡ የእስራኤላዊ ፡ ናቡቴ ፡
ዕርፍቱ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ናቡቴ ፡ በሰማርያው ፡
ንጉሥ ፡ በአክዓብ ፡ ቤት ፡ አጠገብ ፡ የወይን፡
አትክልት፡ቦታ፡ነበረው።

፲፮፡ አክዓብም ፡ ናቡቴን ፡ ለቤቴ ፡ ቅርብ ፡ ነውና ፡
የተክል፡ቦታ፡ይሆነኝ፡ዘንድ፡ይህን፡የወይን፡
ቦታህን፡ስጠኝ፡ከሱ፡የሚሻል፡ሌላ፡የወይን፡
ቦታ ፡ እሰጥሃለሁ ፡ ዋጋውንም ፡ ትሻ ፡
እንደሆነ፡የዚህን፡የውይን፡ቦታህን፡ሽያጭ፡
ወርቅ፡እሰጥሃለሁ፡የተክል፡ቦታ፡ይሁነኝ፡
አለው።

፲፯፡ ናቡቴም ፡ አክዓብን ፡ የአባቶቼን ፡ ርስት ፡
እሰጥህ፡ዘንድ፡እንዲህ፡ያለ፡ነገር፡እግዚአ
ብሔር፡አያምጣብኝ፡አለው።

፲፰፡ አክዓብም፡አዝኖ፡ሔደ፡ፊቱንም፡ተከናንቦ፡
በመኝታው፡ተኛ፡እህልንም፡አልበላም።

፲፱፡ሚስቱ፡ኤልዛቤልም፡ወደርሱ፡ገብታ፡እህል፡
የማትበላ ፡ ምን ፡ ሆንክ ፡ የሚያሳዝንህስ ፡
ምንድን፡ነው፡አለችው።

፳፡ የኢይዝራኤል ፡ ሰው ፡ ናቡቴን ፡ የውይንህን ፡
ቦታ ፡ በዋጋ ፡ ሽጥልኝ ፡ ትወድም ፡ እንደሆነ ፡
ስለርሱ ፡ ፈንታ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ እሰጥሃለሁ ፡ ብዬ፡
ብናገረው ፡ የአባቶቼን ፡ ርስት ፡ አልሰጥህም ፡
ብሎኛልና፡ስለዚህ፡ነው፡ያዘንሁት፡አላት።

፳፩፡ ሚስቱ ፡ ኤልዛቤልም ፡ ዛሬ ፡ እንዲህ ፡ የምታ
ደርግ፡አንተ፡የእስራኤል፡ንጉሣቸው፡ነህን፡
አሁንም፡ ተነሥተህ፡እህል፡ብላ፡ራስህንም፡
አፅና ፡ ልቡናህም ፡ ደስ ፡ ይበለው ፡ የኢይዝ
ራኤል ፡ ሰው ፡ የናቡቴን፡ ቦታ ፡ እኔ ፡ እሰጥ
ሃለሁ፡አለቸው።

፳፪፡በአክዓብ፡ስም፡ደብዳቤ፡ጽፋ፡በማኅተሙም፡
አትማ ፡ ያቺን ፡ ደብዳቤ ፡ ከናቡቴ ፡ ጋር ፡
ወደሚኖሩ ፡ ወደዚያ ፡ አገር፡ አለቆችና ፡
ወደዚያች፡አገር፡ሽማግሌዎች፡ላከቻት።

፳፫፡ የዚያቺም ፡ ደብዳቤ ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡
ነው ፡ ጾምን ፡ ጹሙ ፡ ናቡቴንም ፡ በሕዝቡ ፡
ፊት ፡ አስቀምጡት ፡ የሐሰት ፡ ምስክሮችንም፡
ሁለት ፡ ሰዎችን ፡ አስነሡበት ፡ እግዚአብ
ሔርን ፡ ሰደብከው ፡ ንጉሥንም ፡ ረገምከው ፡
ብለው ፡ ይመስክሩበት ፡ ከከተማም ፡ ወደ
ውጭ ፡ አውጥታችሁ ፡ በደንጊያ ፡ ውገሩትና ፡
ይሙት፡የሚል፡ነው።

www.ethiopianorthodox.org

፳፪፤ ወከመዝ ፡ አቅተለቶ ፡ ኤልዛቤል ፡ በግፍዕ ። ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም፡አሜን።

፳፪፤እንዲህም፡በግፍ፡ኤልዛቤል፡አስገደለችው፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን፡ ለዘላለሙ፡አሜን።

<u>አርኬ</u>

ሰላም፡ለናቡቴ፡በፍቅረ፡አሐቲ፡ዐፀዱ።ለንጉሥ፡አክዓብ፡ሶበ፡ኢተአዘዘ፡ለፈቃዱ።እስከ፡አቅተሎ በግፍዕ፡እስመ፡ከመዝ፡ልማዱ።አጽርዓት፡ግፍዐ፡ደሙ፡በፍትሐ፡ፈጣሪ፡አሐዱ።መንግሥተ፡ምልክና፡ እምኵሉ፡ትዝምዱ።

፳፫፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ፡ኤጲስቆጶስ፡ዘሀገረ፡ጋዛ።ወዝንቱ፡ እምሀገረ ፡ ሮሀ ፡ እምዘመደ ፡ ክቡራን ፡ ወወሀብዎ፡አበዊሁ፡ለቴዎዶስዮስ፡ንጉሥ፡ ከመ፡ይሢሞ፡መኰንነ፡ውእቱሰ፡ይሜንን፡ ሢመተ ፡ ወክብረ ፡ ወይጸመድ ፡ በጾም ፡ ወበጸሎት፡ወሰጊድ፡ውስተ፡ጽርሐ፡ንጉሥ፡ ወሀሎ፡ምስሌሁ፡እምነ፡ሥጋሆሙ፡ለሰማ ዕታት፡እለ፡እምሀገረ፡ፋርስ፡ወመዋዕሊሁኒ፡ በውእቱ፡ጊዜ፡፳ራ፡ዓመት።

፳፬፤ወእምዝ፡ወጽአ፡ወመንኰሰ፡ኀበ፩ደብር፡ እምነ ፡ አድባራት ፡ ወተጋደለ ፡ ተጋድሎ ፡ ዐቢየ ፡ ወሶበ ፡ ተሰምዐ ፡ ቅድስናሁ ፡ ወተጋ ድሎቱ ፡ ነሥእዎ ፡ ዘእንበለ ፡ ፈቃዱ ፡ ወሤምዎ፡ ኤጲስቆጶሰ ፡ ላዕለ ፡ ሀገረ ፡ ጋዛ ፡ ወበኵሉ፡ደወላ።

፳፭፤ወተብህለ፡በእንቲአሁ፡ከመ፡ውእቱ፡ሶበ፡ ይቄድስ፡ቅዳሴ፡ቍርባን፡ይውኅዝ፡ደም፡ ብዙኀ ፡ እስከ ፡ ይመልዕ ፡ ጻሕለ ፡ እንዘ ፡ ይፌትቶ፡ለኅብስት።

፳፮፤ወሶበ፡አምጽኡ፡ሥጋሁ፡ለቅዱስ፡ያዕቆብ፡ ዘግሙድ፡ነሥአ፡ኀቤሁ፡ወነበረ፡ውስተ፡፩ ደብር፡እምአድባራተ፡ኢየሩሳሌም፡ወበመ ዋዕሊሁ፡ለመርቅያን፡ንጉሥ፡ዓላዊ፡ጐየ፡ ኀበ፡ምድረ፡ግብጽ፡ወምስሌሁ፡ሥጋሁ፡ ለቅዱስ፡ያዕቆብ፡ወነበረ፡በህየ፡ኀዳጠ፡ መዋዕለ።

፳፯፤ ወበአሐቲ፡ዕለት፡ሠርዐ፡ቅዳሴ፡ቍርባን፡ ወእንዘ፡ይቄድስ፡ውእቱ፡እለ፡ይቀውሙ፡ ሕዝብ፡ይትናገሩ፡በበይናቲሆሙ፡በጊዜ፡ ቅዳሴ፡ቍርባን፡ወኢኮነ፡ቅዱስ፡ጴጥሮስ፡ ዘይጌሥጾሙ ፡ ወርእዮ ፡ መልአከ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ አኀዞ ፡ እማከዕሎሙ ፡ ወፈቀደ ፡ ይንጽሖ፡ኀበ፡መትሕት፡ዳዕሙ፡ተዓገሦ፡

፳፫፤ በዚችም፡ቀን፡ቅዱስ፡አባት፡የጋዛ፡ኤጲስ ቆጶስ፡ጴጥሮስ፡አረፈ።ይህም፡ሮሃ፡ከሚባል፡ አገር ፡ ክብር ፡ ካላቸው ፡ ወገን ፡ ነው፡ ይሾመውም፡ዘንድ፡ወላጆቹ፡ለንጉሥ፡ቴዎ ዶስዮስ፡ሰጡት፡እርሱ፡ግን፡ሹመትንና፡ ክብርን፡ይጠላ፡ነበር፡በንጉሡም፡አዳራሽ፡ ውስጥ፡በጾም፡በጸሎት፡በሰጊድ፡ተጠምዶ፡ ኖረ ፡ ከርሱም፡ ጋር ፡ የፋርስ ፡ አገር ፡ ሰማዕታት፡ሥጋ፡አብሮት፡አለ፡በዚያንም፡ ጊዜ፡ዕድሜው፡ሃያ፡ዓመት፡ነው።

፳፬፤ከዚህም፡በኋላ፡ከገዳማት፡ወደ፡አንዱ፡ገዳም፡ ሔዶ ፡ መነኰሰና ፡ ጽኑ ፡ ተጋድሎንም፡ ተጋደለ፡የቅድስናውና፡የተጋድሎው፡ዜና፡ በተሰማ፡ጊዜ፡ያለ፡ፈቃድ፡ወስደው፡ጋዛ፡ በምትባል፡አገር፡በአውራጃዋም፡ሁሉ፡ላይ፡ ኤጲስቆጶስነት፡ሾሙት።

፳፭፤ ስለርሱም፡የቍርባንን፡ቅዳሴ፡በሚቀድስ፡ ጊዜ፡ኅብስቱን፡ሲፈትት፡ጻሕሉን፡እስቲ መላው፡ድረስ፡ብዙ፡ደም፡እንደሚፈስ፡ ተነገረ።

፳፮፤ የቅዱስ፡ያዕቆብ፡ዘግሙድን፡ሥጋ፡ወደ፡ ርሱ፡ ወስዶ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ገዳማት ፡ በአንዱ፡ገዳም፡ኖረ፡በከሀዲው፡መርቅያን፡ ዘመንም፡ወደ፡ግብጽ፡አገር፡ሸሸ፡የቅዱስ፡ ያዕቆብም፡ሥጋ፡ከእርሱ፡ጋር፡አብሮ፡ነበር፡ በዚያም፡ጥቂት፡ጊዜ፡ኖረ።

፳፯፤በአንዲትም፡ዕለት፡መሥዋዕት፡አዘጋጅቶ፡ እርሱ፡ሲቀድስ፡ቆመው፡የነበሩ፡ሕዝብ፡ እርስ፡በርሳቸው፡ይነጋገሩ፡ነበር፡በቅዳሴ፡ ቍርባን፡ጊዜ፡ቅዱስ፡ጴጥሮስም፡አልገሠጻ ቸውም ፡ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ አይቶ፡ወደታች፡ሊወረውረው፡ወዶ፡ከመካ ከላቸው፡አንሥቶ፡ያዘው፡ግን፡ታገሠ፡

www.ethiopianorthodox.org

እስመ ፡ ውእቱ ፡ አክበሮሙ ፡ ወኀፈረ ፡ ገሥጾቶሙ።

፴፤ ወሶበ ፡ ተፈጸመ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ለመርቅያን ፡ ዐላዊ ፡ ተመይጠ ፡ ኀበ ፡ ምድረ ፡ ፍልስጥኤም፡ ወአጽንዐ፡ አብያተ፡ ክርስቲያናት፡ ወተራከበ፡ ምስለ ፡ አባ ፡ ኢሳይያስ ፡ ግብጻዊ፡ ወተሰምዐ ፡ ዜናሁ፡ኀበ፡ዘይኑን፡ንጉሥ፡ወፈተወ፡ንጉሥ፡ ከመ፡ ይርአዮ፡ ወኢሠምረ፡ ውእቱሰ፡እስመ፡ ይጐይይ ፡ ጥቀ ፡ እምክብረ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ኃላፊ።

፴፩፤ ወእምዝ፡በጽሐ፡ኀበ፡ጽንፈ፡ብሔረ፡ጋውር፡ ወነበረ ፡ ህየ ፡ ወበጺሐ ፡ በዓሉ ፡ ለብፁዕ፡ ጴጥሮስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ተፍጻሜተ፡ሰማዕት፡ ወሠርዐ ፡ ቅዳሴ ፡ ቍርባን ፡ ወአስተርአዮ ፡ ቅዱስ፡ ጴጥሮስ ፡ ወይቤሎ ፡ እስመ ፡ ናሁ፡ እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት፡ ይጼውዓከ ፡ ትምጻእ ፡ ኀቤሁ ፡ ወእምይእቲ ፡ ዕለት፡አእመረ፡ከመ፡በጽሐ፡ጊዜ፡ዕረፍቱ፡ ጸውዖሙ ፡ ወአዘዞሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ከመይ ጽንዑ፡ ውስተ ፡ ሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ወእምዝ፡ሰፍሐ፡እደዊሁ፡ወመጠወ፡ነፍሶ፡ ውስተ፡እዴሁ፡ ለእግዚአብሔር።ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፡ኪያነኒ፡ይምሐረነ፡በጸሎቱ፡ ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡ አሜን።

ተወው፡እርሱ፡እነርሱን፡መገሠጽ፡አፍሮ፡ አክብሮአቸዋልና።

፴፤ የከሀዲው፡መርቅያን፡ዘመን፡በተፈጸመ፡ጊዜ፡ ወደ፡ፍልስጥኤም፡ምድር፡ተመልሶ፡አብያተ፡ ክርስቲያናትን፡አጠናከረ፡ከግብጻዊ፡አባ፡ኢሳ ይያስም ፡ ጋር ፡ ተገናኘ ፡ ዜናውም ፡ በንጉሥ ፡ ዘይኑን ፡ ዘንድ ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡም ፡ ሊያየው ፡ ወደደ ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ አልወደደም ፡ ከዚህ ፡ ከኃላፊው ፡ ክብር ፡ እጅግ፡ ይሸሽ ፡ ነበርና።

፴፩፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ጋውር ፡ ከሚባል ፡ አገር ፡ ዳርቻ፡ ደርሶ፡ በዚያ፡ ተቀመጠ፡ የተመሰገነ፡ የሰማዕታት፡ ፍጻሜ፡ የሆነ፡ የሊቀ፡ጳጳሳት፡ ጴጥሮስ፡በዓሉ፡በደረሰ፡ጊዜ፡የቍርባንን፡ ቅዳሴ ፡ ሠራ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስም ፡ ተገለጸ ለትና፡ክብር፡ይግባውና፡ ጌታችን፡ኢየሱስ፡ ክርስቶስ ፡ ወደርሱ ፡ ትመጣ ፡ ዘንድ ፡ ይጠራሃል፡አለው።ከዚያችም፡ቀን፡ወዲህ፡ የዕረፍቱ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ አውቆ ፡ ሕዝቡን፡ ጠራቸውና ፡ በቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ እንዲጸኑ ፡ አዘዛቸው ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እጆቹን፡ ዘርግቶ ፡ ነፍሱን ፡ በእግዚአብሔር፡ እጅ፡ሰጠ። ለእግዚአብሔር፡ምስጋና፡ይሁን፡ እኛንም ፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለጴጥሮስ፡በዐፀደ፡ክህነት፡ዘበቈለ።ወበቤተ፡አምላክ፡ዘተተክለ።እንዘ፡ይቄድስ፡ቅዳሴ፡ዘበእ ንቲአሁ፡ተብህለ።በጊዜ፡ፈትቶ፡እምነቅዐ፡ኀብስት፡ፈልፈለ።ደመ፡መለኮት፡እስከ፡መልዐ፡ጻህለ።

፴፪ ወበዛቲ፡ዕለት፡አዕረፈ፡አብ፡ቅዱስ፡ዮሐንስ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሀገረ ፡ እስክንድርያ፡ ወው እቱ፡ እምኍልቆሙ ፡ ለአበው ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት፡፴።

፴፫፤ ወውእቱ ፡ ቅዱስ ፡ ኮነ ፡ ቀሲሰ ፡ ወውእቱ ፡ እምሀገረ ፡ ገምኑዲ ፡ ወበመዋዕሊሁ ፡ ተሐ ንፀት፡ቤተ፡ክርስቲያኖሙ፡ለቅዱሳን፡ሰማ ዕት፡ሰርጊስ፡ወባኮስ፡ወዓዲ፡ቤተ፡ክርስቲ ያኖሙ ፡ ለአቡቂር ፡ ወዮሐንስ ፡ በቅጽረ ፡ ጉባኤ፡ዘምስር፡ዘሐነፃን፡፩ብእሲ፡ፈራሂ፡ እግዚአብሔር፡ግብጻዊ፡ያዕቆባዊ፡ዘስሙ፡ እንድርያስ፡ ወውእቱ ፡ ጸሐፊሁ ፡ ለንጉሥ ፡ አብደል፡አዚዝ፡ወልደ፡መርዋን።

፴፪፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ የእስክንድርያ ፡ አገር ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ቅዱስ ፡ አባት ፡ ዮሐንስ ፡ አረፈ ፡ እርሱም፡ለአባቶች፡ሊቃነ፡ጳጳሳት፡ሠላሳኛ፡ ነው።

፴፫፤ ይህም፡የከበረ፡ቀሲስ፡የሆነ፡የገምኑዲ፡አገር፡ ሰው፡ነው፡በዘመኑም፡የቅዱሳን፡ሰማዕታት፡ የሰርጊስና፡ የባኮስ፡ ቤተ፡ ክርስቲያናቸው፡ ተሠራች፡ዳግመኛም፡የአቡቂርና፡የዮሐንስ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በምስር ፡ መሰብሰቢያ ፡ ቅጽር ፡ አጠገብ ፡ ተሠራች ፡ ያነፃቸውም ፡ ስሙ፡እንድርያስ፡የሚባል፡ እግዚአብሔርን፡ የሚፈራ ፡ ያዕቆባዊ ፡ አንድ ፡ የግብጽ ፡ ሰው ፡ ነው ።እርሱም ፡ ለመርዋን ፡ ልጅ ፡ ለገዢው ፡ ለንጉሥ፡አብደል፡ጸሐፊው፡ነው።

www.ethiopianorthodox.org

፴፬፤ ወዝንቱ፡ አባ፡ ዮሐንስ፡ ዘሐነፀ፡ ቤተ፡ ክርስቲያኑ፡ለቅዱስ፡ማርቆስ፡ ወንጌላዊ፡ በሀገረ፡ እስክንድርያ፡ዘዕውቅት፡በቃምስ።

፴፭፤ ወበመዋዕሊሁ፡ ለዝንቱ፡ ንጉሥ፡ አብደል፡ ኮነ፡ረኃብ፡ዐቢይ፡መጠነ፡ሠለስቱ፡ዓመት፡ ወኮነ፡ዝንቱ፡አብ፡ዘይሔሊ፡ለነዳያን፡ወለምስኪናን፡ ወለጽኑሳን፡ ወይሁቦሙ፡ ወርቀ፡ ወብሩረ፡ ወኅብስተ፡ ፬ተ፡ ጊዜ፡ ለለሰሙን፡ እስመ፡ ኮነ፡ ብዙኀ፡ ምሕረት፡ ወመፍቀሬ፡ ምጽዋት፡ወገባሬ፡ሠናያት።

፴፮፤ ወበመዋዕሊሁ፡ ሞተ፡ ንጉሥ፡ ይዜድ፡ ወነግሠ፡ህየንቴሁ፡መርዋን፡ወነበረ፡ዝንቱ፡ አብ፡ ዲበ፡ መንበረ፡ማርቆስ፡፱ተ፡ ዓመተ፡ ወአዕረፈ፡በሰላም።

፴፯፤ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፡ ኪያነኒ፡ ይምሐረነ፡ በጸሎቱ፡ ወበረከቱ፡ ተሀሉ፡ ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፴፬፤ ይህም፡ አባ፡ ዮሐንስ፡የወንጌላዊ፡ ቅዱስ፡ ማርቆስን፡ ቤተ፡ክርስቲያን፡በእስክንድርያ፡ አገር፡ በታወቀ፡ ቃምስ፡ በሚባል፡ ቦታ፡ የሠራ፡ነው።

፴፭፤ በዚህ፡በንጉሥ፡አብደል፡ዘመንም፡ሦስት፡ ዓመት፡ ያህል፡ ጽኑ፡ ረኃብ፡ ሆነ፡ ይህም፡ አባት፡ለድኆች፡ለጦም፡አዳሪዎችና፡ለችግረኞች፡ የሚያስብ፡ ሆነ፡ በየሳምንቱም፡ አራት፡ጊዜ፡ወርቅና፡ብር፡እንጀራም፡ይሰጣቸዋል፡ አብዝቶ፡ የሚራራ፡ መመጽወትን፡ የሚወድ፡በጎ፡ሥራዎችን፡የሚሠራ፡ነውና።

፴፮፤ በዘመኑም፡ ንጉሥ፡ ይዜድ፡ ሙቶ፡ በርሱ፡ ፈንታ፡ መርዋን፡ ነገሠ፡ ይህም፡ አባት፡ በማርቆስ፡ ወንበር፡ ዘጠኝ፡ ዓመት፡ ኖረ። በሰላምም፡አረፈ።

፴፯፤ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡ በጸሎቱ፡ ይማረን፡ በረከቱም፡ ከእኛ፡ ጋር፡ ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

አርኬ፡

ሰላም፡ ለዮሐንስ። ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ በሢመቱ። ወርቱዕ፡ በሃይማኖቱ። በስመ፡ማርቆስ፡ ሐነፀ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡አመ፡ዕብሬቱ።በዕለተ፡ፈለሰ፡እምዓለም፡ዝንቱ።ለበትረያርክ፡አትናቴዎስ፡ኀቡር፡ዕረፍቱ።

፴፰፤ ወበዛቲ፡ ዕለት፡ አዕረፈ፡ አብ፡ ቅዱስ፡ አትናቴዎስ፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ ዘሀገረ፡ እስክንድርያ፡ ዘውእቱ፡ ጳውሎስ፡ ወልደ፡ ቂስ፡ መክረም፡ ወልደ፡ ከሊል፡ ወውእቱ፡ እምኍልቆሙ፡ ለአበው፡ ሊቃነ፡ ጳጳሳት፡ ፸ወ፮ቱ፡ ወዓዲ፡ ተዝካሮሙ፡ ለጴጥሮስ፡ ወያዕቆብ፡ ወኤልያስ፡ መነኰስ፡ ወቤርሳቤህ፡ እሙ፡ ለሰሎሞን፡ ንጉሥ። ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፡ ወበረከቶሙ፡ ለእሉ፡ ቅዱሳን፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

***

፩፤ በስመ፡ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ፩ አምላክ፡ አመ፡ ፪ ለታኅሣሥ፡ በዛቲ፡ ዕለት፡ ገብረ፡ ሎሙ፡እግዚአብሔር፡ ኃይለ፡ ለ፫ቱ፡ ደቂቅ፡ እሉ፡ እሙንቱ፡ አናንያ፡ ወአዛርያ፡ ወሚሳኤል፡ ውሉዱ፡ ለኢዮአቄም፡ ንጉሠ፡ ይሁዳ፡ እለ፡ ዔወዎሙ፡ ናቡከደነፆር፡ ምስለ፡ አቡሆሙ፡ ወአልሐቆሙ፡ ውስተ፡ ቤቱ፡ ወሤሞሙ፡ውስተ፡በሐውርተ፡ባቢሎን።

፴፰፤ በዚችም፡ ቀን፡ የእስክንድርያ፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ ቅዱስ፡ አባት፡ አትናቴዎስ፡ አረፈ፡ እርሱም፡ጳውሎስ፡የተባለ፡የቂስ፡መክረም፡ ልጅ፡ የከሊል፡ ልጅ፡ ነው፡ እርሱም፡ ለአባቶች፡ ሊቃነ፡ ጳጳሳት፡ ሰባ፡ ስድስተኛ፡ ነው። ዳግመኛም፡ የጴጥሮስ፡ የያዕቆብ፡ የመነኰስ፡ ኤልያስ፡ የንጉሥ፡ ሰሎሞን፡ እናት፡ የቤርሳቤህ፡ መታሰቢያቸው፡ ነው። ለእግዚአብሔርም፡ ምስጋና፡ ይሁን፡ የእሊህም፡ ቅዱሳን፡ በረከት፡ ከእኛ፡ ጋር፡ ትኑር፡ለዘላለሙ። አሜን።

***

፩፤ አንድ፡ አምላክ፡ በሚሆን፡ በአብ፡ በወልድ፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ስም፡ ታኅሣሥ፡ ሁለት፡ በዚች፡ቀን፡ናቡከደነፆር፡ከአባታቸው፡ጋር፡ ለማረካቸው፡ሦስት፡ለሆኑ፡ለይሁዳ፡ንጉሥ፡ ለኢዮአቄም፡ ልጆች፡እግዚአብሔር፡ ኃይልን፡ አደረገላቸው። እሊህም፡ አናንያ፡ አዛርያ፡ ሚሳኤል፡ ናቸው፡ በቤቱም፡ ውስጥ፡ አሳድጎ፡ በባቢሎን፡ ሀገሮች፡ ውስጥ፡ ሾማቸው።

www.ethiopianorthodox.org

ይእቲ ፡ ብፅዓት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወኢይረትዕ፡ሎሙ፡ከመ፡ያትርፍዋ፡ውስተ፡ቤተ፡መቅደስ ፡ ከመ ፡ ኢይብጽሓ ፡ ዘይበጽሖን ፡ ለአንስት ፡ ወበእንተዝ ፡ ሠምሩ ፡ ይስምዩ ላዕሌሃ፡ተፍኀሮ፡ለዘይደልዎ፡ይርዓያ።

፲፰፤ ወእምቅድመ ፡ ዝኒ ፡ ጸውዓ ፡ ዘካርያስ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ወይቤላ ፡ አእምሪ ፡ ኦ ፡ ወለትየ ፡ ማርያም ፡ ከመ፡ አንቲ ፡ ልሕቂ ፡ ወኮንኪ ፡ ፍጽምተ፡ከመ፡ኵሎን፡አንስት፡ትፈቅዲኑ፡ትትፈኀሪ፡ወንኅሥሥ፡ለኪ፡ወሬዛ፡ሠናየ፡ወቡሩከ፡ወፈራኄ፡እግዚአብሔር፡ወሚመ፡ትፈቅዲ፡ትንበሪ፡ውስተ፡ቤተ፡መቅደስ፡ወትትለአኪዮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በኵሉ ፡ መዋዕለ ፡ ሕይወትኪ ፡ ወንግበር፡ ላዕሌኪ ፡ መርገመ ፡ ዘጽሑፍ ፡ ውስተ ፡ ኦሪት፡ ከመ ፡ ትትዓቀቢ፡አንቲ፡እምበዊዐ፡አንቀጸ፡ቤተ፡መቅደስ ፡ በመዋዕለ ፡ ዘይበጽሐኪ፡ ዘይበጽሖን፡ለአንስት።

፲፱፤ወአውሥአት፡እግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡ማርያም፡ወትቤሎሙ፡ናሁ፡አነ፡አመቱ፡ለእግዚአብሔር፡ቅድሜክሙ፡ወአልብየ፡አብ፡ወእም፡ወአንትሙ፡ህንየተ፡አቡየ፡ወእምየ፡እምታሕተ፡እግዚአብሔር፡ቅዱስ፡ወቡሩክ፡ስሙ፡በከመ፡አንትሙ፡ተአምሩ፡ትእዛዘ፡እግዚአብሔር፡ግበሩ።

፳፤ ወይቤልዎ ፡ ካህናት ፡ ወኵሉ ፡ ማኅበር ፡ ለዘካርያስ፡ ባእ ፡ ውስተ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ወጸሊ ፡ ኀበ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ዛቲ ፡ ወለት ፡ ማርያም ፡ ወበዊአ ፡ ጸለየ ፡ ዘካርያስ ፡ ወሶቤሃ፡ አስተርአዮ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይቤሎ፡ኦ፡ዘካርያስ፡ጻእ፡ወአስተጋብኦሙ፡ለኵሎሙ፡ዕደው፡እለ፡ሞታ፡አንስቲያሆሙ፡ዘእምቤተ፡ ዳዊት ፡ ወንሣእ ፡ አብትሪሆሙ ፡ ለለ፩ ፩ ምስለ፡ ስሙ ፡ ወአብእ ፡ ውስተ፡ ቤተ ፡ መቅደስ፡በጊዜ፡ሠርክ፡ወጸሊ፡ኀበ፡እግዚአብሔር ፡ ወበጊዜ ፡ ጽባሕ ፡ አውጽእ ፡ አብትሪሆሙ ፡ ወበዘከሠተ ፡ ለከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትእምርተ ፡ ውስተ ፡ በትሩ፡ ለውእቱ ፡ ይደልዎ፡ ከመ፡ ይትመጠዋ፡ ለማርያም፡

ለሚጠብቃት፡ይሰጧት፡ዘንድ፡ካህናት፡እርስበርሳቸው ፡ ተማከሩ ፡ በሴቶች ፡ ላይ ፡ የሚደርስ ፡ በርሷ ፡ ላይም ፡ ይደርስባታል ፡ ብለው ፡ ስለፈሩ ፡ በቤተ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ ይተዋት ፡ ዘንድ ፡ ለእርሱ ፡ ትክክል ፡ መስሎ ፡ አልታያቸውም ፡ ስለዚህም ፡ ሊጠብቃት ፡ ለሚገባው ፡ በእርሷ ፡ ላይ ፡ እጮኛ ፡ ሊአኖሩ ፡ ወደዱ።

፲፰፤ከዚህም፡አስቀድሞ፡ሊቀ፡ካህናት፡ዘካርያስ፡እመቤታችን፡ቅድስት፡ድንግል፡ማርያምን፡ልጄ ፡ ማርያም ፡ ሆይ፡ አንቺ ፡ እንዳደግሽና ፡ ለአካለ ፡ መጠን ፡ እንደደረስሽ ፡ ዕወቂ ፡ ልትታጪ ፡ ትወጃለሽን ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ፡ መልካም ፡ የሆነ ፡ የተባረከ ፡ ጐልማሳ፡እንፈልግልሽን፡ወይም፡በሕይወትሽ፡ከመን፡ሁሉ፡በቤተ፡መቅደስ፡ተቀምጠሽ፡እግዚአብሔርን ፡ ልታገለግዪው፡ የምትሺ ፡ ከሆነ ፡ በሴቶች ፡ ላይ ፡ የሚደርሰው ፡ በሚደርስብሽ ፡ ወራት ፡ ወደ ፡ ቤተ፡ መቅደስ ፡ ደጅ ፡ ከመግባት ፡ ትጠበቂ ፡ ዘንድ ፡ በኦሪቱ ፡ የተጻፈውን፡የርግማን፡ሥርዓት፡በአንቺ፡ላይ፡እንሠራለን፡አላት።

፲፱፤ቅድስት፡ድንግል፡እመቤታችን፡ማርያምም እነሆ ፡ እኔ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋዩ ፡ በፊታችሁ ፡ ነኝ ፡ አባትና ፡ እናት ፡ የሉኝም ፡ ስሙ ፡ ቡሩክ ፡ ምስጉን ፡ ከሆነ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በታች ፡ በእናትና ፡ አባት ፡ ፈንታ ፡ እናንተ፡ናችሁና፡የእግዚአብሔርን፡ትእዛዝ፡እንደምታውቁ፡አድርጉ፡ብላ፡መለሰች።

፳፤ካህናቱና፡ማኅበሩም፡ሁሉ፡ዘካርያስን፡ወደ፡ቤተ፡መቅደስ፡ገብተህ፡ስለዚች፡ብላቴና፡ማርያም፡ወደ፡እግዚአብሔር፡ጸልይ፡አሉት፡ዘካርያስም ፡ ገብቶ ፡ ሲጸልይ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ተገለጠለትና ፡ እንዲህ ፡ አለው ። ዘካርያስ ፡ ሆይ ፡ ወጥተህ ፡ ከዳዊት ፡ ወገን ፡ ሚስቶቻቸው ፡ የሞቱባቸውን፡ ሁሉ ፡ ወንዶች ፡ ሰብስብ ፡ የየአንዳንዱንም ፡ በትር ፡ ከስሙ ፡ ጋር ፡ ውሰድ ፡ ወደ ፡ ቤተ፡መቅደስም፡በምሽት፡አግብተህ፡ወደ፡እግዚአብሔር፡ጸልይበት፡በነጋ፡ጊዜም፡በትሮቻቸውን ፡ አውጣ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በበትሩ፡ላይ፡ ምልክት ፡ ለገለጠልህ ፡ ለዚያ ፡ ሰው ፡ ማርያምን ፡ ተቀብሎ ፡ ሊጠብቃት ፡

www.ethiopianorthodox.org

፲፫ ፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካረ ፡ በዓሉ ፡ ለሊቀ ፡ መላእክት፡ፋኑኤል።
፲፬፡ ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ኪያነኒ፡ይምሐረነ፡በትንብልናሁ፡ለፋኑኤል፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፲፫፡ በዚችም፡ቀን፡የሊቀ፡መላእክት፡ፋኑኤል፡የበዓሉ፡መታሰቢያ፡ነው።
፲፬፡ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡በፋኑኤል፡አማላጅነት፡ይማረን፡በረከቱም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለሢመትከ፡እምእግዚአብሔር፡በዴዴ።መዓርገ፡ጸሎት፡ትኩን፡ወሰይጣነ፡ውዴት፡ሰዳዴ። ፋኑኤል ፡ ንሥአኒ ፡ ዘማኅሌትየ ፡ ቡዓዴ። ፡ ከመ ፡ ይነሥኡ ፡ ረባሐ ፡ መካልይ ፡ መፍዴ ። እለ ፡ ይለቅሑ ፡ ወርቆሙ፡በርዴ።

***

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፬ ለታኅሣሥ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ ብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ እንድርያስ ፡ ሐዋርያ ፡ እኁሁ ፡ ለቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሊቀ ፡ ሐዋርያት።
፪፡ ወለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ወጽአ ፡ እፃሁ ፡ ውስተ ፡ ሀገረ፡ ልዳ ፡ ከመ ፡ ይስብክ ፡ ወኮኑ ፡ ብዙኃን ፡ እምኔሃ ፡ አምኑ ፡ በእዴሁ ፡ ለቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወሀሎ ፡ ምስሌሁ ፡ ፊልሞና ፡ ረድኡ ፡ ዘኮነ ፡ ጥዑመ ፡ ቃል ፡ ወሠናይ ፡ በኵሉ ፡ ምግባሩ ፡ ወበአምልኮቱ፡ወአዘዞ፡ሐዋርያ፡እንድርያስ፡ለፊልሞና፡ከመ፡ይዕርግ፡ዲበ፡መዓርግ፡ወያንብብ፡በጥዑም፡ቃሉ፡እምነ፡ቅዱሳት፡መጻሕፍት።
፫፡ ወሰሚዖሙ ፡ ገነውተ ፡ አማልክት ፡ ምጽአቶ ፡ ለሐዋርያ ፡ እንድርያስ ፡ ተነሥኡ ፡ ወነሥኡ ፡ ንዋየ ፡ ሐቅሎሙ ፡ ወመጽኡ ፡ ከመ ፡ ይጽብዕዎሙ፡ለእመ፡ይረግሙ፡አማልክቲሆሙ።
፬፡ ወሶቤሃ፡ሰምዕዎ፡ለፊልሞና፡እንዘ፡ያነብብ፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ወይብል፡አማልክቲሆሙ፡ለአሕዛብ፡ዘወርቅ፡ወዘብሩር፡ግብረ፡እደ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡አፍ፡ቦሙ፡ወኢይነቡ፡ዐይን፡ቦሙ፡ወኢይሬእዩ፡ዕዝን፡ቦሙ፡ወኢይሰምዑ ፡ አንፍ ፡ ቦሙ፡ ወኢያጼንዉ ፡ እድ ፡ ቦሙ ፡ ወኢይገሡ ፡ እግር ፡ ቦሙ ፡ ወኢየሐውሩ፡ ወኢይነቡ ፡ በጕራዒቶሙ ፡ ወአልቦ ፡ መንፈስ ፡ ውስተ ፡ አፉሆሙ ፡ ከማሆሙ ፡ ለይኩኑ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ፡ ገብርዎሙ ፡ ወኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይትአመኑ ፡ ቦሙ። ወበእንተ ፡ ጣዕመ፡ቃሉ፡ወሐዋዝ፡ንባቡ፡ተፈትሐ፡አልባቢሆሙ፡ወቦኡ፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ወሰገዱ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ፡ ለቅዱስ ፡ እንድርያስ ፡ ሐዋርያ ፡ ወአምኑ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየ

***

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ታኅሣሥ ፡ አራት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ የሊቀ ፡ ሐዋርያት ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወንድም ፡ የተመሰገነ ፡ ቅዱስ ፡ ሐዋርያ ፡ እንድርያስ፡በምስክርነት፡አረፈ።
፪፡ ለዚህም፡ቅዱስ፡ይሰብክ፡ዘንድ፡ዕጣው፡በልዳ ሀገር ፡ ወጣ ፡ ከእርሷም ፡ ብዙዎች ፡ በቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ትምህርት ፡ አምነው ፡ ነበር ፡ እንደ በቱ ፡ የሚጥም ፡ በሥራው ፡ ሁሉና ፡ በአምልኮቱ ፡ የተወደደ ፡ ያማረ ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ፊልሞና ፡ አብሮት ፡ ነበር ፡ ሐዋርያ ፡ እንድርያስም ፡ ከፍ ፡ ካለ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ ጣዕም ፡ ባለው፡እንደበቱ፡ከቅዱሳት፡መጻሕፍት፡እንዲአነብ፡አዘዘው።
፫፡ የጣዖታት ፡ ካህናትም ፡ የሐዋርያ ፡ እንድርያስን፡ መምጣት ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ አማልክቶቻቸውን ፡ ይረግሙ ፡ እንደሆነ ፡ ሊጣሏቸው ፡ ሽተው፡የጦር፡መሳሪያቸውን፡ይዘው፡መጡ።
፬፡ በዚያንም፡ጊዜ፡ፊልሞና፡በቤተ፡ክርስቲያን፡ውስጥ፡ከወርቅና፡ከብር፡የሰው፡እጅ፡ሥራ፡የሆኑ፡የአሕዛብ፡አማልክቶቻቸው፡አፍ፡አላቸው፡አይናገሩም። ዐይን፡አላቸው፡አያዩም፡ጆሮ ፡ አላቸው ፡ አይሰሙም ፡ አፍንጫ ፡ አላቸው፡አያሸቱም፡እጅ፡አላቸው፡አይዳስሱም፡እግር ፡ አላቸው ፡ አይሔዱም ፡ በጕሮሮአቸውም፡አይናገሩም፡የሚሠሩአቸውና፡የሚአምኑባቸው ፡ ሁሉ ፡ እንደእነርሱ ፡ ይሁኑ ፡ እያለ፡ሲያነብ፡ሰሙት። ስለ፡ቃሉ፡ጣዕምና፡ስለ ፡ ንባቡ ፡ ማማር ፡ ልባቸው ፡ ከክህደት ፡ ማሠሪያ፡ተፈታ፡ወደ፡ቤተ፡ክርስቲያንም፡ገብተው ፡ ከሐዋርያ ፡ እንድርያስ ፡ እግር ፡ በታች፡ሰገዱ፡ክብር፡ይግባውና፡በጌታችን፡በኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ አመኑ ፡ እርሱም ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ውእቱኒ ፡ መሀሮሙ፡ትምህርተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ወአ ጥመቆሙ ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ ወምስሌ ሆሙ ፡ አምኑ ፡ ብዙኃን ፡ ወተጠምቁ ፡ እም እለ፡ያመልኩ፡ጣዖተ።

፭፥ ወኮነ፡በውእቱ፡መዋዕል፡ወሀሎ፡፩፡ቀሲስ፡ በቅሩበ፡ሀገረ፡ልዳ፡ዘስሙ፡ዮሐንስ፡ወቦቱ፡ አሐዱ፡ወልድ፡ወውእቱ፡እንዘ፡ይትዋነይ፡ ምስለ፡ካልኡ፡ቀተሎ፡በግብት፡አቡሁሰ፡ ለዘሞተ ፡ አኀዞ ፡ ለዮሐንስ ፡ ቀሲስ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ አግብእ ፡ ሊተ ፡ ወልደከ ፡ ዘቀተለ ፡ ወልድየ፡ወዮሐንስ፡ቀሲስ፡ሰአሎሙ፡ለሰ ብአ፡ሀገር፡ወይቤሎሙ፡ተኀበዩኒ፡እስከ፡ አሐውር፡ወአመጽአ፡ለሐዋርያ፡እንድርያስ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ያነሥእ ፡ ሊተ ፡ ለዘሞተ ፡ ወእሙንቱ፡ሶበ፡ተኀበይዎ፡ሖረ፡ዮሐንስ፡ ቀሲስ፡ኀበ፡ሐዋርያ፡እንድርያስ፡ወነገሮ፡ ኵሎ፡ትካዞ።

፮፥ ወይቤሎ፡ሐዋርያ፡እንድርያስ፡ለቀሲስ፡ዮሐ ንስ፡ኢይትከሀለኒ፡እሑር፡ምስሌከ፡እስመ፡ ብዙኃን፡ሕዝብ፡እለ፡ይጠመቁ፡እምኀቤየ፡ ባሕቱ፡ይሑር፡ምስሌከ፡ፊልሞና፡ረድእየ፡ ወውእቱ፡ያነሥእ፡ለከ፡ለዘሞተ።

፯፥ ወአዘዞ፡ሐዋርያ፡እንድርያስ፡ለፊልሞና፡ከመ፡ ይሑር ፡ ምስለ ፡ ቀሲስ ፡ ወያንሥእ ፡ ሎቱ ፡ ዘሞተ፡ወሶበ፡ቀርቡ፡ውስተ፡ሀገር፡ይቤል ዎሙ፡ሰብእ፡ለቀሲስ፡ወፊልሞና፡ኢትባኡ፡ ውስተ፡ሀገር፡ከመ፡ኢይቅትልክሙ፡መኰ ንነ፡ሀገር፡እስመ፡ተንሥአ፡ሁከት፡ውስተ፡ ሀገር ፡ ወይቤ ፡ ፊልሞና ፡ አንሰ ፡ ኢይክል ፡ እትዓዶ ፡ ትእዛዘ ፡ መምህርየ ፡ ዳዕሙ ፡ አሐ ውር፡አንሥእ፡ለዘሞተ፡ወለእመ፡ቀተለኒ፡ መኰንን፡ይመጽእ፡መምህርየ፡እንድርያስ፡ ወያነሥአኒ፡ሊተኒ፡ወለዘሞተ፡ቀዳሚ።

፰፥ ወበዊአ፡ውስተ፡ሀገር፡ተራከቦ፡ፊልሞና፡ ለኒቆሮስ፡መኰንን፡ይቤሎ፡ለምንት፡ታማ ስን፡ሀገረ፡አኮኑ፡ዘሤሙከ፡ከመ፡ትዕቀብ፡ ሀገረ፡እምኵሉ፡እኩይ፡መኰንንኒ፡ይቤ፡ ዝንቱ፡ብእሲ፡ቀታሌ፡ነፍስ፡ይመስል፡ ወይቤሎሙ፡ለሐራ፡ንሥእዎ፡ወስቅልዎ፡ወቀ ሥፍዎ፡ወአኀዝዎ፡ሐራ፡ወሰቀልዎ፡ከመ፡ ይቅሥፍዎ።

የቤተ፡ክርስቲያንን፡ትምህርት፡አስተምሮ፡ የክርስትና፡ጥምቀትን፡አጠመቃቸው፡ከእሳ ቸውም፡ጋር፡ጣዖትን፡ከሚያመልኩ፡ውስጥ፡ ብዙዎች፡አምነው፡ተጠመቁ።

፭፥ በዚያ፡ወራትም፡እንዲህ፡ሆነ፡በልዳ፡አገር፡ አቅራቢያ፡ስሙ፡ዮሐንስ፡የሚባል፡አንድ፡ ቄስ፡ነበረ፡ለእርሱም፡አንድ፡ልጅ፡አለው፡ እርሱም ፡ ከባልንጀራው ፡ ጋር ፡ ሲጫወት ፡ በድንገት፡ገደለው፡የሟች፡አባትም፡ልጄን፡ የገደለ ፡ ልጅህን ፡ አሳልፈህ ፡ ስጠኝ ፡ ሲል ፡ ቀሲስ፡ዮሐንስን፡ያዘው፡ቀሲስ፡ዮሐንስም፡ የሀገር ፡ ሰዎችን ፡ ሔጄ ፡ ሐዋርያ ፡ እንድር ያስን፡ እስከማመጣው፡ዋስ፡ሁኑኝ፡እርሱ፡ የሞተውን፡ያነሣልኛልና፡ብሎ፡ለመናቸው፡ እነርሱም፡በተዋሱት፡ጊዜ፡ቀሲስ፡ዮሐንስ፡ ወደ፡ሐዋርያ፡እንድርያስ፡ሒዶ፡ችግሩን፡ ሁሉ፡ነገረው።

፮፥ ሐዋርያ ፡ እንድርያስም ፡ ቀሲስ ፡ ዮሐንስን ፡ እንዲህ፡አለው፡ከእኔ፡ዘንድ፡የሚጠመቁ፡ ብዙ፡ሕዝቦች፡ስላሉ፡ከአንተ፡ጋር፡እሔድ፡ ዘንድ፡አይቻለኝም፡ግን፡ደቀ፡መዝሙሬ፡ ፊልሞና፡አብሮህ፡ይሒድ፡እርሱ፡የሞተውን፡ ያስነሣልሃል፡አለው።

፯፥ ሐዋርያ፡እንድርያስም፡ከቄሱ፡ጋር፡ሒዶ፡ የሞተውን፡ያስነሣለት፡ዘንድ፡ፊልሞናን፡ አዘዘው፡ወደ፡ከተማውም፡ሲቀርቡ፡ቄሱንና፡ ፊልሞናን፡ሰዎች፡በከተማው፡ውስጥ፡ሁከት፡ ሁኗልና፡አገረ፡ገዥው፡እንዳይገድላችሁ፡ ወደ፡ከተማ፡አትግቡ፡አሏቸው።ፊልሞናም፡ እንዲህ፡አለ፡እኔ፡የመምህሬን፡ትእዛዝ፡ መተላለፍ፡አልችልም፡የሞተውን፡ለማን ሣት፡እሔዳለሁ፡እንጂ፡መኰንኑ፡ቢገድ ለኝም፡መምህሬ፡እንድርያስ፡መጥቶ፡እኔ ንም፡አስቀድሞ፡የሞተውንም፡ያስነሣናል።

፰፥ ሲገባም፡መኰንኑን፡ኒቆሮስን፡ተገናኘውና፡ ፊልሞና፡እንዲህ፡አለው፡ሀገርን፡ለምን፡ ታጠፋለህ፡የሾሙህ፡ከክፉ፡ነገር፡ሁሉ፡ ሀገርን፡ልትጠብቅ፡አይደለምን፡መኰንኑም፡ ይህ፡ሰው፡ነፍሰ፡ገዳይ፡ይመስላል፡አለ፡ወታ ደሮችንም፡ይዛችሁ፡ሰቅላችሁ፡ግረፉት፡ አላቸው፡ወታደሮችም፡ይገርፉት፡ዘንድ፡ ይዘው፡ሰቀሉት።

www.ethiopianorthodox.org

፱፤ ወይቤሎ፡ፊልሞና፡ለኒቆሮስ፡መኰንን፡ለም ንት፡ትሰቅለኒ፡ወለምንት፡ትቀሥፈኒ፡እንዘ፡ አልቦ፡ዘአበስኩ፡ወአንሰ፡ንኡስ፡መኑ፡እም ዜነዎ፡ለመምህርየ፡እንድርያስ፡ከመ፡ይነጽር፡ ረድኦ ፡ እንዘ ፡ ይሰቅልዎ ፡ ወይቀሥፍዎ ፡ ወሜጠ ፡ ገጾ ፡ መንገለ ፡ ሐራ ፡ ወይቤሎሙ ፡ አልቦኑ፡እምውስቴትክሙ፡ዘይምህር፡ወይሣ ሃል፡ላዕሌየ፡ከመ፡ይሑር፡ኀበ፡መምህርየ፡ እንድርያስ ፡ ወይንግሮ ፡ በእንቲአየ ፡ ከመ ፡ ሀሎኩ፡በተሰቅሎ፡ወበተቀሥፎ፡ወመጽኡ፡ ሰገራት፡ወበከዩ፡እምጣዕመ፡ቃሉ።

፲፤ ወሶቤሃ፡መጽኡ፡አዕዋፍ፡ኵሎሙ፡ተናገርዎ፡ ወይቤልዎ፡ፈንወነ፡ለነ፡ወቀርበት፡ኀቤሁ፡ ነአስ፡ዖፍ፡ወትቤሎ፡እስመ፡ቀሊለ፡ሥጋ፡ አነ፡ፈንወኒ። ወይቤላ፡አንቲሰ፡ዘማዊት፡ እምከመ፡ረከብኪ፡በፍና፡አሐደ፡እምአዝ ማድኪ፡ትትዋነዪ፡ምስሌሁ፡ወኢታፈጥኒ፡ ገቢአ ፡ ወእምዝ ፡ ቀርበ ፡ ቋዕ ፡ ወይቤሎ ፡ ፈንወኒ፡ሊተ፡ወይቤሎ፡ፊልሞና፡አንተሰ፡ በቀዳሚ ፡ መዋዕል ፡ አመ ፡ ተፈኖከ ፡ ኢያግ ባእከ፡መልእክቶ፡ለአቡነ፡ኖኅ።

፲፩፤ ፊልሞናሰ፡ጸውዓ፡ለርግብ፡ወይቤ፡ነገድ፡ ኀሪት፡እንተ፡ሰመያ፡እግዚአብሔር፡የዋ ሂተ፡እምኵሉ፡አዕዋፍ፡እስመ፡አንቲ፡ አብጻሕኪ፡ሠናየ፡ዜና፡ለአቡነ፡ኖኅ፡አመ፡ ፈነወኪ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ ውስተ ፡ ታቦት ፡ ወባረከ ፡ ላዕሌኪ ፡ ጸድቅ ፡ ኖኅ ፡ አቡነ ። ወይእዜኒ፡ሑሪ፡ኀበ፡ሀገረ፡ልድያ፡ኀበ፡ መምህርየ ፡ እንድርያስ ፡ ወንግሪዮ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይምጻእ ፡ ኀበ ፡ ረድኡ ፡ ፊልሞና ፡ እስመ፡ ሰቀሉኒ ፡ ወይቀሥፉኒ። ወሶቤሃ ፡ ሖረት ፡ ርግብ ፡ ወነገረቶ ፡ ለእንድርያስ ፡ ሐዋርያ ፡ ወተመይጠት ፡ ምስለ ፡ ስጣዌ ፡ መልእክቱ፡ወትቤሎ፡ቡርክት፡ርግብ፡ለፊ ልሞና፡ጽናዕ፡ወኢትፍራህ፡እስመ፡አነ፡ እመጽእ፡ይቤለከ፡መምህርከ፡እንድርያስ።

፲፪፤ ወሶቤሃ፡ሰምዓ፡ለርግብ፡ኒቆሮስ፡መኰንን፡ እንዘ፡ትነግሮ፡ለፊልሞና፡በቃል፡ሰብአዊ፡ አንከረ፡ጥቀ፡ወተንሥአ፡ፍጡነ፡ወፈትሖ፡ ወአውረዶ፡እምተሰቅሎ፡ለፊልሞና፡ለሊሁ፡

፱፤ ፊልሞናም፡ኒቆሮስ፡የተባለውን፡መኰንን፡ እንዲህ፡አለው፡የበደልኩት፡በደል፡ሳይኖር፡ ለምን፡ሰቅለህ፡ትገርፈኛለህ፡እኔ፡ታናሽ፡ ብላቴና፡ስሆን፡ደቀ፡መዝሙሩን፡እኔን፡ ሰቅለው፡ሲገርፉኝ፡ይመለከት፡ዘንድ፡ ለመምህሬ፡እንድርያስ፡ማን፡በነገረው፡አለ። ወደ፡ወታደሮችም፡ፊቱን፡መልሶ፡እንዲህ፡ አላቸው፡ከውስጣችሁ፡የሚራራና፡የሚያዝ ንልኝ፡የለምን፡በመሰቀልና፡በመገረፍ፡ እንዳለሁ፡ሒዶ፡ለመምህሬ፡እንድርያስ፡ ስለ፡እኔ፡ይነግረው፡ዘንድ፡አለ፡ከቃሉ፡ ጣዕም፡የተነሣ፡ወታደሮች፡ተሰብስበው፡ መጥተው፡አለቀሱ።

፲፤ በዚያንም፡ጊዜ፡አዕዋፍ፡ሁሉ፡መጥተው፡ እኛን፡ላከን፡ብለው፡ተናገሩት፡ድምቢጥ፡ ቀርባ፡እኔ፡በአካሌ፡ቀላል፡ነኝና፡እኔን፡ ላከኝ፡አለችው፡አንቺስ፡አመንዝራ፡ነሽ፡ ከወገንሽ፡በመንገድ፡አንዱን፡ያገኘሽ፡ እንደሆነ፡ከርሱ፡ጋር፡ትጫወቺአለሽ፡ፈጥ ነሽ፡አትመለሽም፡አላት፡ከዚህም፡በኋላ፡ ቁራ፡ቀርቦ፡እኔን፡ላከኝ፡አለው፡ፊልሞናም፡ እንዲህ፡አለው፡አንተም፡ብቀድሞ፡ዘመን፡ በተላክህ፡ጊዜ፡ለአባታችን፡ኖኅ፡የመልእ ክቱን፡መልስ፡አልመለስክም፡አለው።

፲፩፤ ፊልሞና፡ግን፡ርግብን፡ጠርቶ፡እንዲህ፡ አላት፡እግዚአብሔር፡የዋሂት፡ብሎ፡ስም፡ ያወጣልሽ፡ከአዕዋፍ፡ሁሉ፡የተመረጥሽ፡ ወገን፡አንቺ፡ለአባታችን፡ኖኅ፡በመርከብ፡ ውስጥ፡ሳለ፡መልካም፡ዜና፡አድረሰሽለ ታልና፡አባታችን፡ጻድቅ፡ኖኅም፡ባርኮ ሻልና፡አሁንም፡ወደ፡ልዳ፡ከተማ፡ወደ፡ መምህሬ፡እንድርያስ፡ሒደሽ፡ንገሪው፡ ሰቅለው፡እየገረፉኝ፡ነውና፡ወደ፡እኔ፡ወደ፡ ደቀ፡መዝሙሩ፡ፊልሞና፡ይመጣ፡ዘንድ። በዚያን፡ጊዜ፡ርግብ፡ሒዳ፡ለሐዋርያ፡እንድ ርያስ፡ነግራ፡የመልእክቱን፡መልስ፡ይዛ፡ ተመለሰች፡የተባረከች፡ርግብም፡ለፊል ሞና፡መምህርህ፡እንድርያስ፡እኔ፡እመጣ ለሁና፡አይዞህ፡በርታ፡ብሎሃል፡አለችው።

፲፪፤ በዚያንም፡ጊዜ፡ርግብ፡በሰው፡ቋንቋ፡ ለፊልሞና፡ስትነግረው፡ኒቆሮስ፡መኰንን፡ ሰማት፡እጅግም፡አደነቀ፡ፈጥኖ፡ተነሥ ቶም፡ራሱ፡በእጁ፡ፊልሞናን፡ፈትቶ፡ከተሰ

www.ethiopianorthodox.org

በእዴሁ፡ወአምነ፡ በእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክር
ስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት።
፲፫፤ ወሰይጣንሰ ፡ ቀንአ ፡ ወቦአ ፡ ውስተ ፡ ልባ ፡
ለብእሲተ፡መኰንን፡ወአእበዳ፡ወቀተለት፡
ወልዳ፡ወመጽኡ፡አግብርቲሁ፡ለመኰንን፡
ወነገረዎ፡ኵሎ፡ዘኮነ፡ወይቤሎ፡ፊልሞና፡
ኢትፍራህ ፡ ወእምዝ ፡ ጸውዓ ፡ ለርግብ ፡
ወይቤላ፡ሑሪ፡ውስተ፡ቤተ፡መኰንን፡ወን
ግሪዮሙ፡ከመ፡ኢይትሀወኩ፡ወይጽንሑ፡
በኀድዓት፡ወሖረት፡ርግብ፡ወነገረቶሙ፡
ለሕዝብ፡በከመ፡አዘዛ፡ፊልሞና፡ወሶበ፡
ሰምዑ ፡ ሕዝብ ፡ በቃለ ፡ ሰብእ ፡ እንዘ ፡
ትትናገር፡ርግብ፡አስተዓጸቡ፡ጥቀ፡ወተጋ
ብኡ፡ኀበ፡ሀሎ፡ፊልሞና።
፲፬፤ ወውእተ፡ጊዜ፡በጽሐ፡እንድርያስ፡ሐዋርያ፡
ወአዘዞ፡ለረድኡ፡ ፊልሞና፡ከመ፡ያንሥእ፡
ለዘሞተ ፡ ቀዳሚ ፡ ውእቱኒ ፡ ጸለየ ፡ ኀበ ፡
እግዚእነ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወአንሥኦ ፡
እሞት፡ ወካዕበ ፡ ሖሩ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡
መኰንን፡ወአንሥኦ፡እንድርያስ፡ሐዋርያ፡
ለወልደ ፡ መኰንን ፡ ዘቀተለቶ ፡ እሙ ፡
ወአሕየዋ፡ለብእሲተ፡መኰንን፡ወአኀዞ፡
ለውእቱ ፡ ጋኔን ፡ ዘወጽአ ፡ እምብእሲተ ፡
መኰንን፡ወአሥጠሞ፡ውስተ፡ማዕምቅቲሃ፡
ለምድር፡በቅድመ፡ኵሉ፡ሰብእ።
፲፭፤ ወእምዝ ፡ ጸውዓ ፡ ለርግብ ፡ እንድርያስ ፡
ሐዋርያ፡ወይቤላ፡እስፍንቱ፡መዋዕልኪ፡
ወትቤሎ፡ይእቲ፡፰ቱ፡ዓመት፡መዋዕልየ፡
ወይቤላ፡በእንተ፡ዘተአዘዝኪ፡ለረድእየ፡
ሑሪ፡ውስተ፡ገዳም፡ወኩኒ፡አግዓዚተ፡እም
ቅኔሆሙ ፡ ለሰብእ ፡ ዓለም ፡ ወበጊዜሃ ፡
ሖረት፡ውስተ፡ገዳም፡ወርእዮሙ፡ሕዝብ፡
ዘንተ፡መንክረ፡አምኑ፡ወተጠምቁ፡ጥም
ቀተ፡ክርስትና፡ኵሎሙ።
፲፮፤ ወእምድኅረዝ፡ወጽአ፡እምኀቤሆሙ፡ወሖረ፡
ኀበ፡ሀገረ፡አክራድ፡ወአክሲስ፡ወአክሳስያ፡
ወኀበ፡ሀገረ፡ሴኒፎሮስ፡ወተራከበ፡ምስለ፡
ሐዋርያ፡በርተሎሜዎስ፡ወሖሩ፡ኀቡረ፡ኀበ፡
ሀገረ ፡ ጋዝሪኖስ ፡ ወምስለ ፡ ዘኮነ ፡ ሎሙ ፡
ረድአ፡ገጸ፡ከልብ፡ወሰበኩ፡ወንጌለ፡ወገ
ብሩ፡ መንክራተ፡እስከ፡ተመይጡ፡ሰብአ፡
ሀገር፡ውስተ፡አእምሮ፡እግዚአብሔር።

ቀለበት ፡ አወረደው ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡
በጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ስም፡አመነ።
፲፫፤ ሰይጣን ፡ ግን ፡ ቀና ፡ በመኰንኑ ፡ ሚስት ፡
ልቡና ፡ አድሮ ፡ አሳበዳትና ፡ ልጅዋን ፡
ገደለች፡አገልጋዮቹም፡ሒደው፡የሆነውን፡
ሁሉ ፡ ለመኰንኑ፡ ነገሩት ፡ ፊልሞናም ፡
አትፍራ፡አይዞህ፡አለው። ከዚህም፡በኋላ፡
ርግብን፡ጠርቶ፡ወደ፡መኰንኑ፡ቤት፡ሒጂ፡
እንዳይሸበሩ ፡ በጸጥታ ፡ እንዲቆዩ ፡ ንገሪ
ያቸው፡አላት፡ርግቢቱም፡ሒዳ፡ፊልሞና፡
እንዳዘዛት ፡ ለሕዝቡ ፡ ነገረቻቸው ፡ ሕዝ
ቡም፡ ርግቢቱ ፡ በሰው ፡ ቃል ፡ ስትናገር ፡
በሰሙ፡ጊዜ፡እጅግ፡አድንቀው፡ ፊልሞና፡
ወዳለበት፡ተሰበሰቡ።
፲፬፤ በዚያንም፡ጊዜ፡ ሐዋርያ፡እንድርያስ፡ደረሰ፡
አስቀድሞ፡የሞተውን፡ያስነሣው፡ዘንድ፡
ደቀ፡መዝሙሩ፡ ፊልሞናን፡አዘዘው፡እር
ሱም፡ክብር፡ይግባውና፡ወደ፡ጌታችን፡
በመጸለይ፡ከሞት፡አስነሣው፡ሁለተኛም፡
ወደ፡መኰንኑ፡ቤት፡ሔዱ፡ ሐዋርያ፡እንድ
ርያስም፡የመኰንኑን፡ልጅ፡እናቱ፡የገደለ
ችውን፡አስነሣው፡የመኰንኑንም፡ሚስት፡
አዳናት ፡ ከእርሷ ፡ የወጣውንም ፡ ያንን ፡
ጋኔን፡ ይዞ፡በሰው፡ሁሉ፡ፊት፡ምድርን፡
ከፍቶ፡ወደ፡ጥልቅ፡አዘቅት፡አሰጠመው።
፲፭፤ ከዚህም፡በኋላ፡ ሐዋርያ፡እንድርያስ፡ርግ
ብን፡ ጠርቶ፡ዕድሜሽ፡ስንት፡ነው፡አላት፡
እርሷም፡ስምንት፡ዓመት፡ነው፡አለችው።
እርሱም፡ለደቀ፡መዝሙሬ፡ስለታዘዝሽ፡
ወደ፡ዱር፡ሒጂ፡ለዓለም፡ሰዎች፡ከመገዛት፡
ነጻ ፡ ሁኚ ፡ አላት ፡ ወዲያውኑ ፡ ሔደች ፡
ሕዝቡም፡ይህን፡ድንቅ፡ሥራ፡አይተው፡
አምነው፡ሁሉም፡የክርስትና፡ጥምቀትን፡
ተጠመቁ።
፲፮፤ ከዚህም፡በኋላ፡ከእርሳቸው፡ዘንድ፡ወጥቶ፡
አክራድ፡አክሲስ፡አክሳስያ፡ሴኒፎሮስም፡
ወደ፡ተባሉ፡አገሮች፡ሒዶ፡አስተማረ፡
ከሐዋርያ፡በርተሎሜዎስም፡ጋር፡ተገና
ኝቶ፡ ጋዝሪኖስ፡ወደ፡ ሚባል፡አገር፡በአን
ድነት፡ሔዱ፡የሀገር፡ሰዎች፡እግዚአብ
ሔርን፡ወደ፡ማወቅ፡እስከተመለሱ፡ድረስ፡
ረዳት፡ከተደረገላቸው፡ገጸ፡ከልብ፡ጋር፡
ገብተው፡ወንጌልን፡ሰበኩ፡ድንቅ፡ተአም
ራትንም፡አደረጉ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፯፡ ወእምዝ ፡ ሖረ ፡ ሐዋርያ ፡ እንድርያስ ። ኀበ ፡ ካልዓት ፡ አህጉር ፡ ወመሀረ ፡ ወበተፍጻሜቱ ፡ ቦአ ፡ ኀበ ፡ አሐቲ ፡ ሀገር ፡ ወሰበከ ፡ ሎሙ ፡ ወንጌለ ፡ ቅዱሰ፡ ሰብአ ፡ ይእቲሰ ፡ ሀገር ፡ እኩያን፡ፈድፋደ፡ኢተወክፍዎ።

፲፰፡ ወቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ እለ ፡ አምኑ ፡ በእንተ ፡ ዘርእዩ ፡ ተአምራተ ፡ ወመንክራተ ፡ እምነ ፡ ቅዱስ ፡ ሐዋርያ ፡ እንድርያስ ፡፡ ወእለሰ ፡ ኢአምኑ ፡ ተማከሩ ፡ ላዕለ ፡ ቅዱስ ፡ እንድርያስ፡ እኩየ ፡ ምክረ ፡ ወፈነዉ ፡ ኀቤሁ ፡ ለእካነ ፡ በጽልሑት ፡ ከመ ፡ ይምጽእ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ወይቅትልዎ ፡ ወላእካንሰ ፡ ሶበ ፡ በጽሑ ፡ ኀበ ፡ ቅዱስ ፡ እንድርያስ ፡ ሰምዑ ፡ ትምህርቶ ፡ ሠናየ ፡ ወርእዩ ፡ ገጾ ፡ ብሩሀ ፡ ወአምኑ ፡ በእግዚእነ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወኮንዎ ፡ አርድእተ ፡ ወኢተመይጡ፡ኀበ፡ፈነውዎሙ።

፲፱፡ ወተማከሩ፡ካዕበ፡ከመ፡ያውዕይዎ፡በእሳት፡ ተጋቢአሙ ፡ ሖሩ ፡ ኀቤሁ ፡ ውእቱሰ ፡ ይቤ ሎሙ ፡ ኅድጉ ፡ እከየ ፡ ልብክሙ ፡ ወእመኑ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብ ሐት፡ከመ፡ትድኅኑ፡ወእመ፡አኮሰ፡ትበልዕ፡ ኪያክሙ ፡ ይእቲ ፡ እሳት ፡ ዘትቤሉ ፡ ሊተ ፡ ወሶበ ፡ ኢሰምዑ ፡ ቃሎ ፡ ሰአሎ ፡ ለእግዚእነ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ከመ ፡ ትረድ ፡ እሳት ፡ እምሰማይ ፡ ወታውዕዮሙ ፡ ወበጊዜሃ ፡ ወረ ደት ፡ እሳት ፡ ወአውዓየቶሙ ፡ ወተሰምዐ ፡ ዜናሁ፡ውስተ፡በሐውርቲሃ፡ለይእቲ፡ሀገር፡ ፈርሁ ፡ ፈድፋደ ፡ ወአምኑ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት።

፳፡ ወገነውተ፡ጣዖታትሰ፡ርእዮሙ፡ዘንተ፡ኵሎ፡ ተአምራተ ፡ ወመንክራተ ፡ ኢአምኑ ፡ አላ ፡ ኮኑ፡ የኃሥሥዎ ፡ ለቅዱስ ፡ ሐዋርያ ፡ እንድ ርያስ ፡ ይቅትልዎ ፡ ወእምዝ ፡ ተጋቢአሙ ፡ መጽኡ ፡ ወነሥእዎ ፡ ለቅዱስ ፡ ሐዋርያ ፡ ወቀሠፍዎ ፡ ዐቢየ ፡ ቅሥፈተ ፡ ወአያድዎ ፡ ውስተ ፡ ኵላ ፡ ሀገር ፡ እንዘ ፡ ዕራቁ ፡ ውእቱ ፡ ወወደይዎ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ፡ ከመ ፡ በግኒታ፡ይስቅልዎ፡እስመ፡ልማዶሙ፡ሶበ፡ ይፈቅዱ ፡ ይቅትሉ ፡ ሰብአ ፡ ይነሥእዎ ፡ ወይ ሰቅልዎ ፡ ዲበ ፡ ዕፅ ፡ ወይዌግርዎ ፡ በአዕባን፡ እስከ፡ይመውት።

፲፯፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሐዋርያ ፡ እንድርያስ ፡ ወደ ፡ ሌሎች ፡ አገሮች ፡ ሒዶ ፡ አስተማረ ፡ በፍጻ ሜውም፡ ወደ ፡ አንዲት ፡ አገር ፡ ገብቶ ፡ ቅዱስ፡ ወንጌልን ፡ ሰበከ ፡ የዚያች ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ የከፉ ፡ ስለሆኑ ፡ ትምህ ርቱን፡አልተቀበሉትም።

፲፰፡ከቅዱስ፡ሐዋርያ፡እንድርያስም፡ድንቅ፡ተአ ምራትን ፡ ስለአዩ ፡ ያመኑ ፡ አሉ ፡ ያላመኑ ፡ ግን፡ ወደእነርሱ ፡ እንዲመጣና ፡ እንዲገ ድሉት ፡ በቅዱስ ፡ እንድርያስ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ምክርን ፡ መክረው ፡ በተንኰል ፡ ወደርሱ መልእክተኞችን ፡ ላኩ ፡ መልእክተኞችም ፡ ወደ ፡ ቅዱስ፡እንድርያስ፡ ሲደርሱ ፡ ማራኪ ፡ የሆነ፡ትምህርቱን፡ሰሙ፡ፊቱንም፡ብርሃን፡ ሁኖ፡አዩትና፡ክብር፡ይግባውና፡በጌታችን፡ አመኑ፡ደቀ፡መዝሙሮችም፡ሆኑት፡ወደላኳ ቸውም፡አልተመለሱም።

፲፱፡ ሁለተኛም ፡ በእሳት ፡ ሊአቃጥሉት ፡ ተማ ከሩና፡ተሰብስበው፡ወደርሱ፡ሔዱ፡እርሱ፡ ግን፡የልባችሁን፡ክፋት፡ትታችሁ፡ትድኑ፡ ዘንድ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡እመኑ፡ይህ፡ካልሆነ፡ ግን ፡ ለእኔ ፡ ያላችኋት ፡ ይቺ ፡ እሳት ፡ እናንተን፡ ትበላለች ፡ አላቸው ። ቃሉንም ፡ ባልሰሙ፡ጊዜ፡ከሰማይ፡እሳት፡ወርዳ፡እን ድታቃጥላቸው ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ ጌታችንን ፡ ለመነው ፡ ወዲያውኑ ፡ እሳት ፡ ወርዳ፡አቃጠለቻቸው፡በዚያች፡አገር፡አው ራጃዎች ፡ ሁሉ ፡ ዜናው ፡ ተሰማ ፡ እጅግም ፡ ፈርተው ፡ ብዙዎች ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ በጌታችን፡በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡አመኑ።

፳፡ የጣዖታት ፡ አገልጋዮች ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ድንቅ ፡ ተአምራት ፡ አይተው ፡ አላመኑም ፡ ቅዱስ ፡ ሐዋርያ ፡ እንድርያስን ፡ ሊገድሉት ፡ ፈለጉት፡እንጂ።ከዚህም፡በኋላ፡ተሰብስበው፡ መጡና፡ቅዱስ፡ሐዋርያ፡እንድርያስን፡ይዘው፡ ወሰዱት ፡ ታላቅ ፡ ግርፋትንም ፡ ገርፈው ፡ በከተማው፡ሁሉ፡ራቁቱን፡አዞረው፡ከወህኒ፡ ቤት፡ጨመሩት፡በማግሥቱ፡የሚሰቅሉትን፡ ሰው ፡ ልማዳቸው ፡ እንዲሁ ፡ ነውና ፡ ሰው ፡ ሊገድሉ፡በሚሹ፡ጊዜ፡ወስደው፡በእንጨት፡ ላይ ፡ ይሰቅሉታል፡ እስከሚሞትም ፡ ድረስ ፡ በድንጊያዎች፡ይወግሩታል።

፳፩፤ ወበይእቲ፡ሌሊት፡ሰአሎ፡አቡነ፡ብፁዕ፡እን ድርያስ፡ሐዋርያ፡ለእግዚእነ፡ክርስቶስ፡ሎቱ፡ ስብሐት፡ከመ፡ትረድ፡እሳት፡ወታውዕዮሙ፡ በከመ፡ቀዳሚ፡ወአስተርአዮ፡እግዚእነ፡ሎቱ፡ ስብሐት፡ወይቤሎ፡ኢትኀዝን፡እስመ፡ቀርበ፡ ፍልሰትከ፡እምዝንቱ፡ዓለም፡ወወሀቦ፡ሰላመ፡ ወተሠወረ፡ እምኔሁ ፡ ወተፈሥሐት ፡ ወተሐ ሥየት ፡ መንፈሱ ፡ ለብፁዕ ፡ ሐዋርያ ፡ እንድ ርያስ።

፳፪፤ ወሶበ ፡ ኮነ ፡ ጽባሐ ፡ ነሥእዎ ፡ ወሰቀልዎ ፡ ዲበ፡ ዕፅ ፡ ወወገርዎ ፡ በእዕባን ፡ እስከ ፡ ሞተ ፡ ወመጽኡ ፡ ሰብእ ፡ መሐይምናን ፡ ወነሥኡ ፡ ሥጋሁ ፡ ወገነዝዎ ፡ ወአንበርዎ ፡ ውስተ ፡ መቃብር፡ወተከሥታ፡እምኔሁ፡ተአምራት፡ ወመንክራት፡ዐበይት።

፳፫፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፤ ኪያነኒ ፡ ይም ሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለቅዱስ ፡ እንድርያስ ፡ ሐዋርያ፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን

፳፩፤ በዚያችም ፡ ሌሊት ፡ የተመሰገነ ፡ ሐዋርያ ፡ አባታችን ፡ እንድርያስ ፡ እንደ ፡ ፊተኞቹ ፡ እሳት ፡ ወርዳ ፡ እንድትበላቸው ፡ ክብር ፡ ይግባውና፡ጌታትንን፡ክርስቶስን፤ለመነው፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ ጌታችንም ፡ ተገለጠ ለትና፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ የምትለይበት ፡ ጊዜ ፡ ደርሷልና፡ አትዘን ፡ አለው ፡ ሰላምታም ፡ ሰጥቶት ፡ ከእርሱ ፡ ተሠወረ ፡ የተመሰገነ ፡ የሐዋርያ፡እንድርያስም፤ልቡናው፡ፈጽማ፡ ደስ፡አላት።

፳፪፤ ንጋትም፡በሆነ፡ጊዜ፡ወስደው፡በዕንጨት፡ ላይ፡ሰቀሉት፡እስከ፡ሞተ፡ድረስም፡በደንጊ ያዎች ፡ ወገሩት ፡ አማንያን ፡ ሰዎችም ፡ መጥተው ፡ ሥጋውን ፡ ወስደው ፡ ገንዘው ፡ ቀበሩት፡ከእርሱም፡ታላላቅ፡የሆኑ፡አስደና ቂዎች፡ተአምራት፡ተገለጡ።

፳፫፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ ንም፡በቅዱስ፡በሐዋርያ፡እንድርያስ፡ጸሎት፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለከ፡ረድአ፡ኢየሱስ፡ኬንያ።እንተ፡ሰበከ፡ወንጌሎ፡ወመሀርከ፡በኒቆምድያ።እዜምር፡ለከ፡ ወእየብብ፡በሃሌ፡ሉያ።አንቅሐኒ፡እምኀኬትየ፡እንድርያስ፡ሐዋርያ።ከመ፡በእዴከ፡ነቅሐት፡እሙታን፡ ልድያ።

፳፬፤ ወበዛቲ፡ዕለት፡ተዝካሮሙ፡ለቅዱሳን፡አባ፡ ጻዕ ፡ ወያዕቆብ ፡ ወዘካርያስ ፡ ወስምዖን ፡ ወታዖድራ ፡ ወታወፍልያ ፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፳፬፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ የቅዱስን ፡ የአባ ፡ ጻዕ ፡ የአባ ፡ ያዕቆብ፡የዘካርያስ፡የስምዖን፡የታዖድራና፡ የታውፍልያ ፡ መታሰቢያቸው ፡ ነው። በረከ ታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

***

፩፤ በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩ አምላክ፡አመ፡፳ ለታኅሣሥ፡በዛቲ፡ዕለት፡ አዕረፈ ፡ ዐቢይ ፡ ነቢይ ፡ ናሆም ፡ ወልደ ፡ ኬልቅዩ።

፪፤ ወዝንቱ ፡ ጻድቅ ፡ ነቢይ ፡ እምነገደ ፡ ስምዖን ወውእቱ ፡ በትንቢቱ ፡ ፲ ወ፯ ፡ እምነ ፡ ሙሴ ፡ ነቢይ።

፫፤ ወተነበየ ፡ በመዋዕሊሆሙ ፡ ለዮዳሄ ፡ ካህን ፡ ወኢዮአስ፡ወአሜስያስ፡ወኦዝያን፡ወልዱ፡ ወገሠጾሙ ፡ ለደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ በእንተ ፡ ዐሊዎቶሙ፡ወአምልኮቶሙ፡ጣዖታተ።

***

፩፤ አንድ፡አምላክ፡በሚሆን፡በአብ፡በወልድ፡ በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡ታኅሣሥ፡አምስት፡ በዚች፡ቀን፡የኬልቅዩ፡ልጅ፡ታላቅ፡ነቢይ፡ ናሆም፡አረፈ።

፪፤ ከስምዖን፡ነገድ፡የሆነ፡ይህ፡ጻድቅ፡ነቢይ፡ ከነቢይ፡ሙሴ፡በትንቢቱ፡ዐሥራ፡ሰባተኛ ነው።

፫፤ በካህኑ፡ዮዳሄ፡በነገሥታቱ፡በኢዮአስ፡በአሜ ስያስ ፡ በልጁ ፡ በኦዝያን ፡ ዘመን ፡ ትንቢት ፡ ተነገረ፡ስለ፡ክህደታቸውና፡ጣዖታትን፡ስለ ማምለካቸውም፡የእስራኤልን፡ልጆች፡ገሠጻ ቸው።

www.ethiopianorthodox.org

፩፤ ወከሠተ ፡ በትንቢቱ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእመ፡ኮነ፡መሐሬ፡ወመስተሣህለ፡ወብዙኀ፡ ምሕረት ፡ ውእቱሰ ፡ ሀለዎ ፡ ከመ ፡ ይትበቀሎሙ ፡ ለጸላዕቱ ፡ ወለእለ ፡ ይትቃረንዎ ፡ የዐቅቦሙ፡ዕለተ፡ኵነኔ።

፪፤ ወዓዲ ፡ ተነበየ ፡ በእንተ ፡ ስብከተ ፡ ወንጌል ፡ ቅዱስ፡ወበእንተ፡ሐዋርያት፡እንዘ፡ይብል፡ ናሁ፡እገሪሆሙ፡ውስተ፡አድባር፡ለሰብአ፡ ዜና፡ወይዜንዉ፡ሰላመ።

፫፤ ወተነበየ ፡ በእንተ ፡ ነነዌ ፡ ከመ ፡ ማያት ፡ ወእሳት፡ ሀለዎሙ፡ያጥፍእዋ፡ወኮነ፡በከመ፡ ቃሉ፡እስመ፡እግዚአብሔር፡ረሰየ፡ውስቴታ፡ ድልቅልቀ፡ዐቢየ፡ወነደ፡እሳት፡ውስቴታ፡ ወአውዓየ፡መንፈቃ፡ላዕለ፡እለ፡ተመይጡ፡ እምፍኖተ፡ጽድቅ፡ወገብሩ፡አበሳ፡ወለእለሰ፡ ጸንዑ፡ወነስሑ፡ኀበ፡እግዚአብሔር፡ኢበጽሖሙ ፡ ግሙራ ፡ እምእኩይ ፡ ወኢ ፡ ምንትኒ ። ወፈጺሞ ፡ መዋዕለ ፡ ትንቢቱ ፡ ወአሥመሮ፡ለእግዚአብሔር፡ወአዕረፈ፡በሰላም።

፬፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ ነቢይ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፩፤ እግዚአብሔርም ፡ ምንም ፡ መሐሪና ፡ ይቅር ፡ ባይ፡ምሕረቱም፡የበዛ፡ቢሆን፡ካልተመለሱ፡ ጠላቶቹን፡ይበቀላቸው፡ዘንድ፡እንደ፡አለው፡ ለሚቃወሙትም፡የፍርድ፡ቀን፡እንደሚጠብቃቸው፡በትንቢቱ፡ገለጠ።

፪፤ዳግመኛም፡ስለ፡ከበረ፡የወንጌል፡ትምህርትና፡ ስለ ፡ ሐዋርያት ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ፡ የምሥራች ፡ የሚናገሩ ፡ ሰዎች ፡ እግራቸው ፡ እነሆ ፡ በተራራ ፡ ላይ ፡ ቁሟል ፡ ሰላምንም፡ይናገራሉ።

፫፤ ስለነነዌም ፡ ውኃና ፡ እሳት ፡ ያጠፉአት ፡ ዘንድ እንዳላቸው ፡ ትንቢት ፡ ተናግሮ ፡ እንደቃሉ ፡ ሆነ፡ ከዕውነት ፡ መንገድ ፡ ተመልሰው ፡ በበደሉ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ እግዚአብሔር ፡ በውስጧ ፡ ታላቅ ፡ ንውጽውጽታ ፡ አድርጎ ፡ እሳትም ፡ አውርዶ፡እኩሌታዋን፡አቃጥሏልና።በንስሐ፡ ጸንተው፡ወደ፡እግዚአብሔር፡የተመለሱትን፡ ግን፡ከክፉ፡ነገር፡ከቶ፡ምንም፡ምን፡አልደረሰባቸውም።የትንቢቱንም፡ወራት፡ሲፈጽም፡ እግዚአብሔርንም ፡ አገልግሎ ፡ በሰላም ፡ አረፈ።

፬፤ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡ በዚህ ፡ ነቢይ ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለከ ፡ ሰባኬ ፡ ምጽአቱ ፡ እምሲና ። ዘበድልቅልቅ ፡ ፍና ። ለዝ ፡ አምላክ ፡ እንተ ፡ ርኢኮ ፡ በዐይነ ፡ ሕሊና። አስተብቍዖ ፡ ናሆም ፡ ወሰአሎ ፡ እምፀበለ ፡ እግሩ ፡ ደመና ። ዲበ ፡ ሕማምየ ፡ ይነፍንፍ ፡ ጥዒና።

፭፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካሩ ፡ ለቅዱስ ፡ ኤስድሮስ ፡ ሰማዕት ። በረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን

፭፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ የቅዱስ ፡ ኤስድሮስ ፡ ሰማዕት ፡ መታሰቢያው ፡ ነው ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለከ፡ ኤስድሮስ ፡ ብፁዕ ። ሰማዕተ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእ ። በእንተ ፡ ኢየሱስ ፡ ዘተሰቅለ ፡ ለቤዝዎ፡ ሰብእ። አሀሉ ፡ ኀበ ፡ ሀሎከ ፡ በታሕተ ፡ ዐቢይ ፡ ምሥዋዕ ። ያስተዳልወኒ ፡ ጸሎትከ ፡ ለብእሲ ፡ ኃጥእ።

፩፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ካዕበ ፡ ኮነት ፡ ሰማዕተ ፡ ቅድስት፡አውጋንያ፡እምሀገረ፡ሮሜ።

፪፤ ወለዛቲ ፡ ቅድስት ፡ ስመ ፡ አቡሃ ፡ ፊልጶስ ፡ ወውእቱ ፡ መኰንነ ፡ ሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ወያመልክ ፡ ጣዖተ ፡ ወንጉሥኒ ፡ ዘሮም ፡ ዘስሙ፡ መምድያኖስ ፡ ውእቱኒ ፡ ዘይሰግድ ፡ ለጣዖት ፡ ወተወልደት ፡ ዛቲ ፡ ቅድስት ፡ በሀ

፩፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ ደግሞ ፡ ከሮም ፡ አገር ፡ ቅድስት ፡ አውጋንያ ፡ በሰማዕትነት ፡ አረፈች።

፪፤ የዚችም ፡ ቅድስት ፡ የአባቷ ፡ ስም ፡ ፊልጶስ ፡ ነው፡ እርሱም ፡ የእስክንድርያ ፡ አገር ፡ ገዥ ፡ ነበር ፡ ጣዖትንም ፡ ያመልካል ፡ ስሙ ፡ መምድያኖስ ፡ የሚባል ፡ የሮም ፡ ንጉሥም ፡ ለጣዖት ፡ የሚሰግድ ፡ ነው ፡ ይቺም ፡ ቅድስት ፡ አውጋ

ገረ ፡ እስክንድርያ ፡ እስመ ፡ እማ ፡ ክርስቲያ
ናዊት ፡ ይእቲ ፡ መሀረታ ፡ ሃይማኖተ ፡ ክርስ
ቲያን፡በኅቡእ።
፲፭ ወሶበ ፡ ልሕቀት ፡ ፈኀርዋ ፡ መኳንንት ፡
ዐበይት፡ወሶበ፡ነገራ፡አቡሃ፡ዘንተ፡ትቤሎ፡
አ ፡ አቡየ ፡ አብሐኒ ፡ ቅድመ ፡ ከመ ፡ እባእ ፡
ገዳመ ፡ እስክንድርያ ፡ ወእፍታሕ ፡ አዕይ
ንትየ ፡ ወእትፈሣሕ ፡ በርእየ ፡ አድባራት
ወሰሚያ፡አቡሃ፡ደመረ፡ላቲ፡፪ተ፡ሕጽዋነ፡
ወአብሐ፡ከመ፡ትግበር፡ዘፈቀደት።

፲፮ ወወጺአ ፡ ያደት ፡ ኵሎ ፡ አድባራተ ፡ መነኰ
ሳት፡ ወበጽሐት ፡ ኀበ ፡ አሐቲ ፡ ቤተ ፡ ክርስ
ቲያን ፡ ዘባቲ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ጻድቅ ፡ ዘስሙ ፡
ቴዎድሮስ፡ወቀሪባ፡ነገረቶ፡ኵሎ፡ዘውስተ፡
ልባ፡ወተጠምቀት፡ምስለ፡ሕፅዋኒሃ፡ወመን
ኰሰት ፡ በህየ ፡ ወተመሰለት ፡ ከመ ፡ ብእሲ ፡
ወሰመየት ፡ ስማ ፡ አባ ፡ አውጋንዮስ ፡ ወኢያ
እመረ፡መኑሂ፡ከመ፡ብእስቲ፡ይእቲ።

፲፯ ወሶበ ፡ ኢተመይጠት ፡ ኀበ ፡ አቡሃ ፡ ኃሠሣ ፡
ውስተ፡ኵሉ፡መካን፡ወሶበ፡ኢረከባ፡ገብረ፡
ጣዖተ፡በአምሳሊሃ፡ወነበረ፡እንዘ፡ይሰግድ፡
ላቲ፡ሠርከ፡ወነግሀ።
፲፰ ወእምድኅረ ፡ ነበረት ፡ አሐደ ፡ ዓመተ ፡ አዕ
ረፈ ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ ዘውእቱ ፡ መካን ፡ ወኀረ
ይዋ ፡ መነኮሳት ፡ ወሤምዋ ፡ አበ ፡ ምኔት ፡
ወጸገዋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሀብተ ፡ ፈውስ፡
ከመ፡ታውጽእ፡አጋንንተ፡ወትክሥት፡አዕይ
ንተ፡ዕውራን፡ወትፈውስ፡ኵሎ፡ደዌ።

፲፱ ወእምዝ ፡ ወደየ ፡ ሰይጣን ፡ ውስተ ፡ ልበ ፡
አሐቲ ፡ ብእሲት ፡ ፍትወተ ፡ እኪተ ፡ እምድ
ኅረ ፡ ፈወሰታ ፡ እስመ ፡ መሰለታ ፡ ብእሴ ፡
ወትቤላ ፡ ኅድግ ፡ ዘንተ ፡ ደብረ ፡ ወምንኵ
ስናከ ፡ ወኩነኒ ፡ ሊተ ፡ ምትየ ፡ እስመ ፡ ብየ፡
ብዙኀ ፡ ንዋይ ፡ ወትቤላ ፡ ቅድስት ፡ ዘተሰ
ምየት ፡ አባ ፡ አውጋንዮስ ፡ አ ፡ እምየ ፡ ሑሪ ፡
እምኔየ፡እስመ፡ሰይጣን፡አስርሐኪ፡ወሶበ፡
አስተኃፈረታ፡ሖረት፡ኀበ፡መኰንነ፡እስክ
ንድርያ፡ወትቤሎ፡እስመ፡አነ፡ሶበ፡ሖርኩ፡
ውስተ ፡ መካነ ፡ ዕገሌ ፡ መጽአ ፡ ኀቤየ ፡

ንያ፡ በእስክንድርያ ፡ ከተማ ፡ ተወለደች፡ እና
ቷም ፡ ክርስቲያን ፡ ስለሆነች ፡ በሥውር ፡ የክር
ስቲያን፡ሃይማኖትን፡አስተማረቻት።
፲፭ በአደገችም ፡ ጊዜ ፡ ታላላቆች ፡ መኳንንት ፡
አጩት ፡ አባቷም ፡ ይህን ፡ በነገራት ፡ ጊዜ ፡
አባቴ ፡ ሆይ ፡ መጀመሪያ ፡ ወደ ፡ እስክን
ድርያ፡ ገዳም ፡ እንድገባና ፡ እንድጐበኝ ፡
ተራሮችን፡ በማየት ፡ ዐይኖቼ ፡ አይተው ፡
ደስ፡ ይለኝ ፡ ዘንድ ፡ ፍቀድልኝ ፡ አለችው ፡
አባቷም ፡ ሰምቶ፡ ሁለት ፡ ጃንደረቦችን ፡
ጨምሮ፡ የወደደችውን ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡
ፈቀደላት።
፲፮ በወጣችም ፡ ጊዜ ፡ የመነኰሳቱን ፡ ገዳማት ፡
ሁሉ ፡ ዞረች ፡ ስሙ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የሚባል ፡
ጻድቅ፡ደግ፡ኤጲስቆጶስ፡ወደሚኖርባትም፡
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደረሰች ፡ ቀረብ ፡ ብላም ፡
በልቧ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ነገረችው ፡ ከጃንደረ
ቦቿም ፡ ጋር ፡ ተጠምቃ ፡ በዚያ ፡ መነኰሰች ፡
በወንድ፡አምሳልም፡ሁና፡ስሟን፡አባ፡አው
ጋንዮስ ፡ አሰኘች ፡ እርሷ ፡ ሴት ፡ እንደሆነች፡
ማንም፡አላወቀም።
፲፯ ወደ፡አባቷም፡ባልተመለሰች፡ጊዜ፡በቦታው፡
ሁሉ፡ፈለጋት፡ሲአጣትም፡በርሷ፡አምሳል፡
ጣዖት ፡ ሠርቶ ፡ ማታና ፡ ጧት ፡ እየሰገደላት ፡
ኖረ።
፲፰ አንድ፡ዓመትም፡ከኖረች፡በኋላ፡የዚያ፡ቦታ፡
አበ ፡ ምኔት ፡ አረፈ ፡ መነኰሳቱም ፡ መረጧ
ትና፡ አበ ፡ ምኔት ፡ አድርገው ፡ ሾሟት፡ እግዚ
አብሔርም ፡ አጋንንትን ፡ ታስወጣ ፡ ዘንድ ፡
የዕውራንን ፡ ዐይኖች ፡ ትገልጥ ፡ ዘንድ ፡ ደዌ
ውን ፡ ሁሉ ፡ ታድን ፡ ዘንድ ፡ ሀብተ ፡ ፈውስን ፡
ሰጣት።
፲፱ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሰይጣን ፡ በአንዲት ፡ ሴት ፡
ልብ ፡ ክፉ ፡ ሐሳብ ፡ አሳደረባት ፡ ከአዳነቻት ፡
በኋላ ፡ ወንድ ፡ መስላ ታለችና ፡ ገዳምህንና ፡
ምንኵስናህን ፡ ትተህ ፡ ለኔ ፡ ባል ፡ ሁነኝ ፡ ብዙ ፡
ገንዘብ ፡ አለኝና ፡ አለቻት ። አባ ፡ አውጋንዮስ፡
የተባለችው ፡ ቅድስቷም ፡ እናቴ ፡ ሆይ፡ ከእኔ ፡
ዘንድ ፡ ሒጂ ፡ ሰይጣን ፡ በከንቱ ፡ አድክሞሻል፡
አለቻት ፡ በአሳፈረቻትም ፡ ጊዜ ፡ ወደ፡ እስክን
ድርያ ፡ ገዥ ፡ ሒዳ ፡ እንዲህ ፡ አለችው ፡ እኔ ፡
ወደ ፡ ዕገሌ ፡ ቦታ ፡ በሔድኩ ፡ ጊዜ ፡ ሊደፍረኝ ፡
ሽቶ ፡ ወጣት ፡ መነኵሴ ፡ በሌሊት ፡ ወደእኔ ፡

www.ethiopianorthodox.org

በሌሊት ፡ ወሬዛ ፡ መነኰስ ፡ ፈቂዶ ፡ ያኀስ
ረኒ፡ ወሶበ ፡ ከላሕኩ ፡ ኀበ ፡ አግብርትየ ፡
ወጺአ፡ጐየ፡እምኔየ።

፲፮፡ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ መኰንን ፡ ዘውእቱ ፡ አቡሃ ፡
ለቅድስት፡አውጋንያ፡አዘዘ፡ያምጽእዎሙ፡
ለመነኰሳት፡ኵሎሙ፡አሣሮሙ፡ወሶበሂ፡
አብጽሕዎሙ ፡ መጠዎሙ ፡ ለካልዕ ፡ መኰ
ንን ፡ ከመ ፡ ይኰንኖሙ ፡ ወቦ ፡ እለ ፡ ሞቱ፡
እምኔሆሙ፡እምጽንዐ፡ኵነኔ።

፲፯፡ ወሶበ ፡ ርእየት ፡ ኀሣሮሙ ፡ ለመነኰሳት ፡
ትቤሎ ፡ ለመኰንን ፡ አቡሃ ፡ አ ፡ እግዚእየ ፡
መሐል ፡ ሊተ ፡ ከመ ፡ እሙነ ፡ እንግርከ ፡
ምሥጢርየ ፡ ወኢትክልአኒ ፡ መፍቅድየ ፡
ወሶበ፡መሐለ፡ላቲ፡ወሰደቶ፡ኀበ፡መካነ፡
ጽማዌ፡ወከሠተት፡ሎቱ፡ምሥጢራ፡ወአ
ጠየቀቶ፡ከመ፡ይእቲ፡ወለቱ፡አውጋንያ፡
ወርእዮ፡መኰንን፡ይቤላ፡በአማን፡አንቲ፡
ወለትየ፡አውጋንያ፡ወአንሰ፡አመንኩ፡በአ
ምላክኪ።

፲፰፡ ወአዘዘ፡ሶቤሃ፡ከመ፡ይፍትሕዎሙ፡ለመነ
ኰሳት ፡ ወለእለ ፡ ሞቱሂ ፡ በኵነኔ ፡ ይቅብ
ርዎሙ፡ወበጊዜሃ፡ተጠምቀ፡ምስለ፡ኵሉ፡
ሰብአ፡ቤቱ፡ወኮኑ፡ክርስቲያነ።

፲፱፡ ወሶበ፡ርእዩ፡ሰብአ፡እስክንድርያ፡ጽንዐ፡
ሃይማኖቱ፡ሤምዎ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ላዕለ፡
መንበረ፡ማርቆስ፡ወንጌላዊ፡ወነበረ፡ብዙኃ፡
ዓመታተ ፡ እንዘ ፡ ይሰብክ ፡ ሃይማኖተ ፡
እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡
ስብሐት ። ወእምዝ ፡ ተንሥአ ፡ ላዕሌሁ፡
ካልዕ፡ መኰንን ፡ ዐላዊ ፡ ወፈነወ ፡ ሐራሁ ፡
ከመ፡ይቅትልዎ፡በኀቡእ፡ለውእቱ፡ፊልጶስ፡
ሊቀ፡ጳጳሳት፡ወእንዘ፡ይጼሊ፡ቀዊሞ፡ውስተ፡
ቤተ፡ክርስቲያን፡ቀተልዎ፡ወነሥአ፡አክሊለ፡
ሰማዕት።

፳፡ ወሶበ፡ሰምዐ፡ዜናሃ፡ለቅድስት፡አውጋንያ፡
ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘሮሜ፡ተመጠዋ፡መንገሌሁ፡
ወሤማ፡እመ፡ምኔት፡ላዕለ፡ደብረ፡ዚአሁ፡
ዘሐነፀ፡ወየአክሉ፡መነኰሳይያት፡፹ወ፫ተ፡
፫ተ፡ወለ፪ቱ፡ሕጽዋን፡እለ፡ነበሩ፡ምስሌሃ፡
ሤሞሙ፡ኤጲስቆጶሳተ፡ላዕለ፡፪ኤሆን፡አህ
ጉር።

መጣ ፡ ወደ ፡ አገልጋዮቼም ፡ ስጮህ ፡ ከእኔ ፡
ዘንድ፡ወጥቶ፡ሸሸ።

፲፮፡ መኰንኑም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ይኸውም ፡ የቅ
ድስት፡አውጋንያ፡አባቷ፡የሆነ፡መነኰሳቱን፡
ሁሉ፡አሥረው፡ያመጧቸው፡ዘንድ፡አዘዘ፡
በአደረሷቸውም፡ጊዜ፡እንዲአሠቃያቸው፡
ለሌላ ፡ መኰንን ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው፡
ከሥቃይም ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ ከእርሳቸው ፡
የሞቱ፡አሉ።

፲፯፡የመነኰሳቱንም፡መጐሳቈል፡በአየች፡ጊዜ፡
መኰንን፡አባቷን፡እንዲህ፡አለችው፡ጌታዬ፡
ሆይ ፡ ምሥጢሬን ፡ ዕውነቱን ፡ እነግርህ ፡
ዘንድ ፡ የምፈልገውንም ፡ እንዳትከለክለኝ ፡
ማልልኝ፡አለችው። በማለላትም፡ጊዜ ወደ፡
ሥውር፡ቦታ፡ወስዳ፡ምሥጢርዋን፡ሁሉ፡
ገለጠችለትና፡ልጁ፡አውጋንያ፡እርሷ፡እን
ደሆነች፡አስረዳችው። መኰንኑም፡አይቶ፡
በእውነት ፡ አንቺ ፡ ልጄ ፡ አውጋንያ ፡ ነሽ ፡
እኔም፡በአምላክሽ፡አመንኩ፡አላት።

፲፰፡ በዚያንም፡ጊዜ፡መነኰሳቱን፡ይፈቷቸው፡
ዘንድ፡በመሠቃየት፡የሞቱትንም፡ይቀብሩ
አቸው ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ ወዲያውኑ ፡ ከቤተ ፡
ሰቦቹ፡ሁሉ፡ጋር፡ተጠምቆ፡ሁሉም፡ክርስ
ቲያን፡ሆኑ።

፲፱፡ የእስክንድርያ ፡ ሰዎችም ፡ የሃይማኖቱን ፡
ጽናት፡በአዩ፡ጊዜ፡በወንጌላዊው፡ማርቆስ፡
ወንበር ፡ ላይ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አድርገው ፡
ሾሙት ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ የጌታችንን ፡
የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ሃይማኖት ፡ እያስ
ተማረ፡ብዙ፡ዓመታትን፡ኖረ። ከዚህም፡
በኋላ፡በእርሱ፡ላይ፡ሌላ፡ከሀዲ፡መኰንን፡
ተነሥቶ፡ይህን፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ፊልጶስን፡
በሥውር፡ይገድሉት፡ዘንድ፡ጭፍሮቹን፡ላከ፡
በቤተ፡ክርስቲያንም፡ውስጥ፡ቁም፡ሲጸልይ፡
ገደሉት፡የሰማዕታትንም፡አክሊል፡አገኘ።

፳፡ የሮሜ፡ሊቀ፡ጳጳሳትም፡የቅድስት፡አውጋ
ንያን፡ዜና፡በሰማ፡ጊዜ፡ወደርሱ፡ወስዶ፡
እርሱ፡በሠራው፡ገዳም፡ላይ፡እመ፡ምኔት፡
አድርጎ፡ሾማት፡የመነኰሳይያቱም፡ብዛት፡
ሦስት፡ሺህ፡ሦስት፡መቶ፡ነው፡እነዚያንም፡
ከእርሷ ፡ ጋር ፡ የኖሩ ፡ ሁለት ፡ ጃንደረቦች ፡
በሁለት ፡ አገሮች ፡ ላይ ፡ ኤጲስቆጶስትነት ፡
ሾማቸው።

፳፩፡ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ተሠይመ ፡ ካልዕ ፡ መኰንን ፡
ዐላዊ ፡ አኀዛ ፡ ለቅድስት ፡ አውጋንያ ፡ ወኰ
ነና ፡ ዅነኔ ፡ ጽኑዐ ፡ እስከ ፡ መጠወት ፡ ነፍሳ ፡
በእንተ ፡ ስመ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወነሥአት ፡ አክሊለ ፡ ስምዕ ።

፳፪፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐ
ረነ ፡ በጸሎታ ፡ ወበረከታ ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓ
ለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

፳፩፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ ከሀዲ ፡ መኰንን ፡
በተሾመ ፡ ጊዜ ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ በጌታችን ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ነፍሷን ፡ ለሞት ፡
አሳልፋ ፡ እስከ ፡ ሰጠች ፡ ድረስ ፡ ቅድስት ፡ አው
ጋንያን ፡ ይዞ ፡ በጽኑ ፡ ሥቃይ ፡ አሠቃያት ፡ የሰ
ማዕትነት ፡ አክሊልንም ፡ ተቀበለች ።

፳፪፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ
ንም ፡ በጸሎቷ ፡ ይማረን ፡ በረከቷም ፡ ከእኛ ፡
ጋር ፡ ይኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለአውጋንያ ፡ ዘተመሰለት ፡ ሕጽወ ። በእንተ ፡ ክርስቶስ ፡ ታዝኅን ፡ መነኰሳተ ፡ አኃወ ። ወጽድቀ ፡
አቡሃ ፡ ፊልጶስ ፡ እዜኑ ፡ መትልወ ። እመንግሥተ ፡ ምድር ፡ ኃላፊ ፡ ለመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ አድለወ ። እስከ ፡ በት
ረያርከ ፡ ኮነ ፡ ዘይጌሥጽ ፡ አበወ ።

፳፫፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ካዕበ ፡ ኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ ቅዱስ ፡
ፊቅጦር ፡ ዘሀገረ ፡ ሻው ፡ ዘእምአድያመ ፡ አስ
ዩጥ ።

፳፬፡ ወለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ስመ ፡ አቡሁ ፡ መርመር ፡
ወስማ ፡ ለእሙ ፡ ማርታ ፡ ወእሙንቱ ፡
ጻድቃን ፡ ዘያመልክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ዘእንበለ ፡ ፍርሀት ፡ ወባሕቱ ፡ ኢኮነ ፡ ሎሙ ፡
ወልድ ፡ ወነበሩ ፡ እንዘ ፡ ይስእሉ ፡ ኀበ ፡
እግዚእነ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወይሁቡ ፡
ምጽዋተ ፡ ለነዳያን ፡ ወተወክፈ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ስእለቶሙ ፡ ወፀንሰቶ ፡ ቡርክት ፡
ማርታ ፡ ለዝንቱ ፡ ማር ፡ ፊቅጦር ፡ ወወለደቶ ፡
አመ ፡ ፲ ለግንቦት ፡ ወሐፀንዎ ፡ በተግሣጽ ፡
ወበፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር ።

፳፭፡ ወሶበ ፡ ኮኖ ፡ ፳ ዓመተ ፡ ወሰዶ ፡ አቡሁ ፡ ኀበ ፡
ንጉሥ ፡ ወሤሞ ፡ ንጉሥ ፡ መስፍነ ፡ ህየንተ ፡
አቡሁ ፡ እስመ ፡ ረሥአ ፡ አቡሁ ፡ በመዋ
ዕሊሁ ።

፳፮፡ ወእምድኅረ ፡ ኅዳጥ ፡ መዋዕል ፡ በጽሐ ፡ መልእ
ክተ ፡ ንጉሥ ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ኀበ ፡ መኰንነ ፡
እንጽና ፡ ከመ ፡ ይቅትል ፡ ዅሎ ፡ ክርስቲያነ ፡
እለ ፡ ኢያመልኩ ፡ አማልክተ ፡ ውእቱሰ ፡
መኰንን ፡ መጽአ ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ ሻው ፡ እንዘ ፡
የኃሥሦሙ ፡ ለክርስቲያን ፡ አሜሃ ፡ አስተዋ
ደይዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ፊቅጦር ፡ ሰብእ ፡
እኩያን ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ያመልኮ ፡ ለክርስ
ቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ። ወአዘዘ ፡ ሶቤሃ ፡
ያምጽእዎ ፡ ወሶበ ፡ አምጽእዎ ፡ አገበሮ ፡

፳፫፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ ደግሞ ፡ ከአስዩጥ ፡ አውራጃ ፡
ሻው ፡ ከሚባል ፡ ከተማ ፡ ቅዱስ ፡ ፊቅጦር ፡ በሰ
ማዕትነት ፡ አረፈ ።

፳፬፡ የዚህም ፡ ቅዱስ ፡ የአባቱ ፡ ስም ፡ መርመር ፡
የእናቱ ፡ ማርታ ፡ ይባላል ፡ እነርሱም ፡ ያለ ፡
ፍርሀት ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያመልኩት ፡
እውነተኞች ፡ ጻድቃን ፡ ናቸው ፡ ነገር ፡ ግን ፡
ልጅ ፡ አልነበራቸውምና ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡
ጌታችንን ፡ እየለመኑ ፡ ኖሩ ፡ ለድኆችም ፡
ምጽዋትን ፡ ይሰጡ ፡ ነበር ። እግዚአብሔርም ፡
ልመናቸውን ፡ ተቀበለ ፡ ይቺ ፡ የተባረከች ፡
ማርታም ፡ ይህን ፡ ሊቅ ፡ ፊቅጦርን ፡ ፀንሳ ፡
ግንቦት ፡ ዘጠኝ ፡ ቀን ፡ ወለደችው ፡ እግዚአብ
ሔርን ፡ በመፍራትም ፡ ሠርተው ፡ ቀጥተው ፡
አሳደጉት ።

፳፭፡ ሃያ ፡ ዓመትም ፡ ሲሆነው ፡ አባቱ ፡ ወደ ፡
ንጉሥ ፡ አቀረበውና ፡ ንጉሡም ፡ በአባቱ ፡
ፈንታ ፡ ምስፍና ፡ ሾመው ፡ አባቱ ፡ በዕድ
ሜው ፡ ሸምግሎ ፡ ነበርና ።

፳፮፡ ከጥቂት ፡ ወራትም ፡ በኋላ ፡ ጣዖታትን ፡ የማያ
መልኩ ፡ ክርስቲያኖችን ፡ ሁሉ ፡ ይገድል ፡
ዘንድ ፡ የንጉሥ ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ መልእ
ክት ፡ ወደ ፡ እንጽና ፡ አገር ፡ መኰንን ፡ ደረሰ ።
መኰንኑም ፡ ክርስቲያኖችን ፡ እየፈለገ ፡ ወደ ፡
ሻው ፡ ከተማ ፡ ደረሰ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ክብር ፡
ይግባውና ፡ ክርስቶስን ፡ እንደሚአመልከው ፡
ክፉዎች ፡ ሰዎች ፡ ይህን ፡ ቅዱስ ፡ ፊቅጦርን ፡
ወነጀሉት ፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ እንዲአመጡት ፡
አዘዘና ፡ በአመጡት ፡ ጊዜ ፡ ለጣዖታት ፡

www.ethiopianorthodox.org

ከመ፡ ይሡዕ፡ ለአማልክት፡ ወሶበ፡ አበዮ፡ አዘዘ፡ይእሥርዎ፡ውስተ፡ቤተ፡ሞቅሕ።

፳፪፡ ወእንዘ፡ሀሎ፡ህየ፡መሠጠ፡ሊቀ፡መላእክት፡ ሚካኤል፡ ውስተ፡ሰማይ፡ዐቀብትሰ፡ዘቤተ፡ ሞቅሕ፡ ሶበ፡ ኃጥእዎ፡ ተሀውኩ፡ ፈድፋደ፡ ወእምድኅረ፡ ሰቡዕ፡ መዋዕል፡ ረከብዎ፡ ወወሰድዎ፡ኀበ፡መኰንን፡ውእቱሰ፡ተራኀ ርኀ፡ላዕሌሁ፡ወፈነዎ፡ኀበ፡ንጉሥ፡ወንጉ ሥኒ፡ኄጠ፡ብዙኀ፡እንዘ፡ይዬውሆ፡ከመ፡ ይሚጦ፡ እምአምልኮተ፡እግዚአብሔር። ወሶበ፡ስእነ፡መይጦቶ፡ፈነዎ፡ኀበ፡አውጣኪ ያኖስ፡መኰንን፡ወአዘዘ፡እንዘ፡ይብል፡ናሁ፡ ፈነውክዎ፡ለፈቅጦር፡ኀቤከ፡ለእመ፡ሰምዐ፡ እምኔከ፡ይሡዕ፡ለአማልክት፡ወለእመሰ፡ኢሰ ምዐከ፡ኢትምሐኮ፡አላ፡ቅትሎ።

፳፫፡ ወእምዝ፡ አሠርዎ፡ እደዊሁ፡ ወእገሪሁ፡ ወወደዩ፡ ልጓመ፡ ኀፂን፡ ውስተ፡ አፉሁ፡ ወጸዓንዎ፡ በሐመር፡ ከመ፡ ይሰድዎ፡ ኀበ፡ መኰንን፡ ወወረደ፡ መልአከ፡ እግዚአ ብሔር፡ ወፈትሖ፡ እማእሠሩ፡ ወአብጽሖ፡ ኀበ፡ መኰንን። ቅዱስሰ፡ፈቅጦር አኀዘ፡ ይርግሞ፡ ለመኰንን፡ ወለንጉሥ፡ ዐላዊ፡ ወተቈጥዐ፡ መኰንን፡ ወኰነኖ፡ ኵነኔ፡ ጽኑዐ፡ ወእምዝ፡ አሠሮ፡ ውስተ፡ ቤተ፡ ሞቅሕ፡ ወእንዘ፡ ሀሎ፡ በህየ፡ አስተርአዮ፡ መድኃኒነ፡ ሎቱ፡ ስብሐት፡ በሠረገላ፡ ብርሃን፡ ወአወፈዮ፡ ኪዳነ፡ ወኮነ፡ እም ይእቲ፡ ዕለት፡ ዘይገብር፡ ተአምረ፡ ወመን ክረ፡ወፈወሰ፡ብዙኃነ፡ዱያነ።

፳፬፡ ወሰሚዖ፡ መኰንን፡ ዘንተ፡ ተምዐ፡ ወአ ብጽሖ፡ ኀቤሁ፡ ወዓዲ፡ የውሆ፡ ከመ፡ ይሚጦ፡ቅዱስሰ፡ፈቅጦር፡ጸአሎ፡ወረገመ፡ አማልክቲሁ፡ ርኩሳነ፡ ወሶቤሃ፡ አዘዘ፡ መ ኰንን፡ ይእሥርዎ፡ ውስተ፡ ዘነበ፡ ፈረስ፡ ወይስሐብዎ፡ መጠነ፡ ምሕዋረ፡ አሐቲ፡ ዕለት፡ወእምዝ፡ይደይዎ፡ውስተ፡ምንዳደ፡ እሳት፡ ዘቤተ፡ ብለኔ፡ ወከመዝ፡ ፈጸመ፡ ገድሎ፡ሠናየ።

፳፭፡ ወሥጋሁሰ፡ ኢያውጽኡ፡ እምዝንቱ፡ ቤተ፡ ብለኔ፡ዳዕሙ፡ወረዱ፡በሰዋስው፡ወገነዝዎ፡ በአልባስ፡ሠናያን፡ወአምዓዝዎ፡በአፈው፡

እንዲሠዋ፡አስገደደው፡እምቢ፡በአለውም፡ ጊዜ፡በወህኒ፡ቤት፡እንዲአሥሩት፡አዘዘ።

፳፪፡ በዚያም፡እያለ፡የመላእክት፡አለቃ፡ቅዱስ፡ ሚካኤል፡ ወደ፡ ሰማይ፡ አወጣው፡ የወህኒ፡ ቤት፡ጠባቂዎችም፡በአጡት፡ጊዜ፡ተሸበሩ፡ ከሰባት፡ቀኖችም፡በኋላ፡አገኙትውት፡ወደ፡ መኰንኑ፡ ወሰዱት፡ መኰንኑ፡ ግን፡ ራራለ ትና፡ ወደ፡ ንጉሡ፡ ሰደደው፡ ንጉሡም፡እግ ዚአብሔርን፡ ከማምለክ፡ይመልሰው፡ዘንድ፡ በማባበል፡ ብዙ፡ ሸነገለው። መመለስም፡ በተሳነው፡ ጊዜ፡ አውጣኪያኖስ፡ ወደሚ ባል፡ መኰንን፡ ሰደደው።እንዲህም፡ብሎ፡ አዘዘው፡ እነሆ፡ ፊቅጦርን፡ ወደንተ፡ ልኬ ዋለሁ፡ያንተን፡ምክር፡ከሰማ፡ለአማልክት፡ ይሠዋ፡ ካልሰማህ፡ ግን፡ ግደለው፡ እንጂ፡ አትራራለት።

፳፫፡ ከዚህም፡በኋላ፡ወደ፡መኰንኑ፡ሊወስዱት፡ እጆቹንና፡እግሮቹን፡አሠሩ፡በአፉም፡የብ ረት፡ ልጓም፡ አግብተው፡ በመርከብ፡ አሳፈ ሩት፡የእግዚአብሔርም፡መልአክ፡ ወርዶ፡ ከማሠሪያውም፡ ፈትቶ፡ ወደ፡ መኰንኑ፡ አደረሰው፡ቅዱስ፡ፊቅጦርም፡ መኰንኑንና፡ ከሀዲውን፡ ንጉሥ፡ ሊረግም፡ ጀመረ፡ መኰንኑም፡ ተቆጣ፡ ጽኑዕ፡ ሥቃይንም፡ አሠቃይቶ፡ በወህኒ፡ ቤት፡ አሠረው። በዚ ያም፡ ሳለ፡ክብር፡ይግባውና፡መድኃኒታችን፡ በብርሃን፡ ሠረገላ፡ ላይ፡ ሁኖ፡ ተገለጠለትና፡ ቃል፡ ኪዳን፡ ሰጠው፡ ከዚያችም፡ ቀን፡ ጀምሮ፡ ድንቅ፡ ተአምራትን፡ በማድረግ፡ ብዙ፡በሽተኞችን፡የሚፈውስ፡ሆነ።

፳፬፡ መኰንኑም፡ይህን፡ሰምቶ፡ተቆጣ፡ወደርሱ፡ አስመጣውና፡ ይመልሰው፡ ዘንድ፡ ደግሞ ሸነገለው፡ ቅዱስ፡ ፊቅጦር፡ ግን፡ የረከሱ፡ አማልክቶቹን፡ ረገመ፡ በዚያንም፡ ጊዜ፡ በፈረስ፡ ጅራት፡ ላይ፡ አሥረው፡ የአንድ፡ ቀን፡ መንገድ፡ ያህል፡ እንዲጎትቱት፡ ከዚያም፡ ከውሽባ፡ ቤት፡ እሳት፡ ማንደጃ፡ ውስጥ፡ እንዲጨምሩት፡ አዘዘ፡ እንዲህም፡ መልካም፡ተጋድሎውን፡ፈጸመ።

፳፭፡ ሥጋውን፡ ግን፡ ከዚያ፡ ውሽባ፡ ቤት፡ አላወ ጡትም፡ በመሰላል፡ ወርደው፡ በአማሩ፡ ልብሶች፡ገንዘው፡በሽቱዎች፡አጣፈጡት፡

ወሐነፀ፡ዴቤሁ፡ቤተ፡ክርስቲያን።
፴፩፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም
ሐረነ፡በጸሎቱ፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡
ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

እንጂ፡በላዩም፡ቤተ፡ክርስቲያንን፡ሠሩ።
፴፩፡ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡
በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡
ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለከ ፡ መርዓዊ ፡ ሥርግው ። በደመ ፡ ስምዕ ፡ ቀይሕ ፡ ወበልብሰ ፡ አሚን ፡ ጽዕድው ። ፊቅጦር ፡ ሰማዕት ፡ ዘደወለ ፡ ሻው ። አጥዕሞ ፡ ለማኅሌትየ ፡ ውስተ ፡ ዕዝነ ፡ ኵሉ ፡ ዕደው ። ከመ ፡ ምረተ ፡ ማይ ፡ ነቢይ ፡ ቀሰመ፡በዔው።

ሰላም፡ለዝክረ፡ስምከ እምነ፡ኵሉ፡አፈው።ጥዑም፡ዓዲ፡እምነ፡መዓር፡ወዔው፡ፊቅጦር፡በግዕ፡ዘአ ርአያከ፡ቅድው።ይኩነኒ፡ቤዛ፡አመ፡ጠብሖከ፡በሻው።ደመ፡ስምዕከ፡ከመ፡ማይ፡ክዕው።

፴፪፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለፊንጦስ ፡
ወሐናንያ ፡ ወባርክዮስ ፡ ወዮሐንስ ፡ ወፊል
ጳስ ፡ አቡሃ ፡ ለቅድስት ፡ አውጋንያ ፡ ተጋዳ
ሊት ። ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓ
ለመ፡ዓለም፡አሜን።
፴፫፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካሩ ፡ ለቅዱስ ፡ ኤላው
ትሮስ፡ሰማዕት፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡
ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።
፴፬፡ ወበዛቲ፡ዕለት፡አዕረፈ፡አብ፡ቅዱስ፡አባ፡
ገብረ፡ናዝራዊ፡ንጹሕ፡ድንግል፡ወመስተ
ጋድል፡ወቀናኢ፡ለሕገ፡እግዚአብሔር።
፴፭፡ ወለዝንቱ፡ቅዱስ፡አበዊሁ፡ቅዱሳን፡ፈራህ
ያነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወክቡራነ ፡ ዘመድ ፡
እሙንቱ፡ወአቡሁኒ፡ካህን፡ዘየዐቅብ፡ሕገ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወሥርዓታ ፡ እሙኒ ፡
ኄርት፡ወመፍቀሪተ፡አምላክ።
፴፮፡ ወሶበ ፡ ተወልደ ፡ ዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ልሕቀ ፡
በጥበብ፡ወበትምህርት፡ወበፈሪሀ፡እግዚአ
ብሔር፡ ወእምዝ፡ሶበ፡ተሠይመ፡ዲያቆነ፡
ኮነ፡ ዘያነብብ ፡ መጻሕፍተ ፡ ብሉይ ፡ ወሐ
ዲስ።ወረከበ፡በውስተ፡ኦሪት፡ዘሰ፡ሠዓረ፡
ወገብረ፡ባቲ፡ግብረ፡በዕለተ፡ሰንበት፡ሞተ፡
ለይሙት፡ወእምውስተ፡ወንጌልሂ፡ረከበ፡
ዘይቤ ፡ ዘኬ ፡ ፈትሐ ፡ አሐተ ፡ እምእላ ፡
ትእዛዛት ፡ እንተ ፡ ተሐጽጽ ፡ ወይሜህር ፡
ከመዝ ፡ ለሰብእ ፡ ሕጹጸ ፡ ይከውን ፡ በመን
ግሥተ ፡ ሰማያት፡ ወዘሰ ፡ ይገብር ፡ ወይሜ
ህር፡ከመዝ፡ውእቱ፡ዐቢየ፡ይከውን፡በመን
ግሥተ፡ሰማያት፡ወዓዲ፡ለበወ፡ዘይቤ፡መድ
ኃኒነ፡ዘኢኃደገ፡አባሁ፡ወእሞ፡ወዘኢገደፋ፡
ለነፍሱ፡ኢይክል፡ይጸመደኒ፡ወኢይክል፡

፴፪፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ የፊንጦስ ፡ የሐናንያ ፡ የባር
ክዮስ ፡ የዮሐንስ ፡ የተጋዳይዋ ፡ የቅድስት ፡
አውጋንያ ፡ አባት ፡ የፊልጶስ ፡ መታሰቢ
ያቸው፡ ነው ። በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡
ትኑር፡ለላለሙ፡አሜን።
፴፫፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ የሰማዕት ፡ ቅዱስ ፡ ኤላው
ትሮስ ፡ መታሰቢያው ፡ ነው ፡ በረከቱም ፡
ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።
፴፬፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡
የሚቀና፡ገድለኛ፡የሆነ፡ንጹሕ፡ድንግል፡
ቅዱስ፡አባት፡አባ፡ገብረ፡ናዝራዊ፡አረፈ።
፴፭፡ የዚህም፡ቅዱስ፡ወላጆቹ፡በወገን፡የከበሩ፡
እግዚአብሔርን፡የሚፈሩ፡ናቸው፡አባቱም፡
የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሕጓንና፡ ሥርዓቷን ፡
የሚጠብቅ፡ካህን፡ነው፡እናቱም፡ፈጣሪዋን፡
የምትወድ፡ደግ፡ሴት፡ናት።
፴፮፡ ይህም፡ቅዱስ፡በተወለደ፡ጊዜ፡በዕውቀት፡
እግዚአብሔርን ፡ በመፍራት ፡ በመማር ፡
አደገ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ዲቁናን ፡ በተሾመ ፡
ጊዜ፡ የብሉይና ፡ የሐዲስ ፡ መጻሕፍትን ፡
የሚያነብ ፡ ሆነ ፡ በኦሪትም ፡ ውስጥ ፡ የሰን
በትን፡ ቀን ፡ የሻረና ፡ ሥራ ፡ የሠራባት ፡
በሞት፡ይቀጣ፡የሚል፡አገኘ።ከወንጌልም፡
ውስጥ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ አገኘ ፡ ከእነዚህ ፡
ትእዛዛት፡ታንሳለች፡ብሎ፡የሚያስተምር፡
አንዲቱን፡የሻረ፡ለሰውም፡እንዲህ፡ብሎ፡
የሚያስተምር፡ በመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡
የተለየ ፡ ይሆናል ፡ የሚያደርግና ፡ የሚያስ
ተምር ፡ ግን፡ እርሱ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡
ታላቅ፡ይሆናል፡ዳግመኛም፡መድኃኒታችን
አባትና፡ እናቱን ፡ ያልተወ ፡ ሰውነቱንም ፡
ለመከራ ፡ አሳልፎ ፡ ያልጣላት ፡ ሊአገለ

www.ethiopianorthodox.org

ከዊነ፡ረድእየ።

፴፯፤ ወእምዝ ፡ ሖረ ፡ ኀበ ፡ አቡነ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ውእቱኒ ፡ ወልዱ ፡ ለአቡነ ፡ አኖሬዎስ ፡ ዘደብረ፡ ጽጋጃ ፡ ወመንኰሰ ፡ በህየ ፡ ወነበረ ፡ እንዘ ፡ ይተግህ ፡ በጾም ፡ ወበጸሎት ፡ ወበሰጊድ፡ወእምዝ፡ተሠይመ፡ቀሲስ፡ወእምህየ፡ሖረ ፡ ብሔረ ፡ ትግራይ ፡ ወተራከበ፡ ምስለ ፡ አባ ፡ ያዕቆብ ፡ ወተዚያነዉ ፡ እምቃላተ ፡ መጻሕፍት፡ቅዱሳት።

፴፰፤ ወእምዝ፡ከሠተ፡ሎቱ፡ሕሊናሁ፡ወይቤሎ፡አባ፡ያዕቆብ፡እፎ፡ይትከሀል፡ወይቤ፡አባ፡ገብረ፡ናዝራዊ፡እግዚአብሔር፡ይረድአኒ፡ወነሥአ፡እምአባ፡ያዕቆብ፡ጕልተ፡ወተሌለዩ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ በፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ። ወእምዝ ፡ ገብረ፡ ምኔተ ፡ ወተዘራግሐ፡ወተጋብኡ፡ኀቤሁ፡ብዙኃን፡ሰብእ፡ወኮኑ፡መነኰሳተ፡ወገብረ፡ቀኖና፡በእንተ፡ዐቂበ ፡ ሰንበታት ፡ ወበዓላት ፡ ዘመፍትው ፡ ወሥርዓተ ፡ ዘይደሉ ፡ ለመነኰሳት ፡ ጸዊም ፡ እስከ ፡ ሠርክ ፡ እንበለ ፡ አጽርዖ ፡ ለለኵሉ ፡ ሰሙን፡ዘእንበለ፡በሰንበታት፡ወበዓለ፡ልደቱ፡ወጥምቀቱ ፡ ለመድኃኒነ ፡ ወበመዋዕለ፡ ጰንጠቈስቴ፡ወዓዲ፡ኢይንሥኡ፡ንዋየ፡ባዕድ። ወኢይርግሙ ፡ ወኢይምሐሉ፡ በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡ ወዘንተ ፡ ኵሎ ፡ ይሜህሮሙ፡ለደቂቁ።

፴፱፤ ወሎቱሰ፡አልቦ፡ዓቅም፡ለጸሎቱ፡ተዘኪሮ፡ዘይቤ ፡ ዳዊት ፡ ነቢይ ፡ እባርኮ ፡ ለእግዚአብሔር፡በኵሉ፡ጊዜ።ወዘልፈ፡ስብሐቲሁ፡ውስተ፡አፉየ።ወዓዲ፡ዘይቤ፡ወእዛዋዕ፡በትእዛዝከ ፡ ወአኃሥሥ ፡ ፍናዊከ ፡ ወአነብብ ፡ ትእዛዛቲከ፡ወኢይረስዕ፡ቃለከ።

፵፤ ወዓዲ ፡ ይትኄረም ፡ እምነ ፡ ስቡሕ ፡ ዘቦ ፡ ደም ፡ ወእምነ ፡ መባልዕት ፡ ጥዑማት ፡ እስመ ፡ ያዜክራ ፡ ለነፍሱ ፡ ሕማማተ ፡ እግዚኡ ፡ ወይውኅዝ ፡ አንብዑ ፡ እንበለ ፡ አጽርዖ ፡ ወይሰግድ ፡ ወይዜምር ፡ እንበለ ፡ ጽርዓት ፡ ወይትዌከፍ ፡ ነግደ ፡ ወፈላሴ ፡ ወይሔውጾሙ፡ ለነዳያን ፡ ወለምስኪናን ፡ ተዘኪሮ ፡ ዘይቤ ፡ ነቢይ ፡ ብፁዕ፡ዘቦ፡ዘርእ፡በጽዮን፡ወአብያት፡በኢየ

ግለኝ፡ ደቀ ፡ መዝሙሬም ፡ ሊሆነኝ ፡ አይችልም፡ያለውን፡አስተዋለ።

፴፯፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አቡነ ፡ ጎርጎርዮስ፡ሔደ፡ እርሱም ፡ ጽጋጃ ፡ በሚባል ፡ ገዳም ፡ የአቡነ ፡ አኖሬዎስ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ በዚያም ፡ መንኵሶ ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ በስግደት ፡ እየተጋ ፡ ኖረ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ቅስና ፡ ተሾመ፡ ከዚያም፡ ወደ ፡ ትግራይ ፡ አገር ፡ ሔዶ፡ከአባ፡ያዕቆብ፡ጋር፡ተገናኝቶ፡በቅዱሳት፡መጻሕፍት፡ቃሎች፡ተነጋገሩ።

፴፰፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሀሳቡን ፡ ገለጠለት ፡ አባ ፡ ያዕቆብም ፡ እንዴት ፡ ይቻላል ፡ አለው ፡ አባ ፡ ገብረ ፡ ናዝራዊም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይረዳኛል፡ አለ፡ከአባ፡ያዕቆብም፡ጕልት፡ተቀብሎ፡እርስበርሳቸው፡ በእግዚአብሔር፡ፈቃድ፡ተለያዩ። ከዚህም፡በኋላ፡ተስፋፍቶ፡ገዳምን፡ሠራ፡ብዙ፡ሰዎችም፡ወደርሱ፡ተሰብስበው፡መነኰሳትን ፡ ሆኑ ፡ ስለሰንበታትና፡ በዓላትም፡አከባበር ፡ እንደሚገባ ፡ ሥርዓትን፡ ሠራ ። ለመነኰሳትም፡ከመድኃኒታችን፡ከልደቱና፡ከጥምቀቱ ፡ በዓል ፡ ከሰንበታትና ፡ ከበዓለ ፡ ሃምሳ፡በቀር፡በየሰሞኑ፡ሁሉ፡እስከ፡ማታ፡ያለ ፡ ማቋረጥ ፡ መጾም ፡ እንደሚገባቸው፡ሥርዓትን ፡ ሠራ ። ዳግመኛም ፡ የሌላውን ፡ ገንዘብ፡እንዳይነኩ፡እንዳይረግሙ፡በሕያው፡እግዚአብሔርም ፡ ስም ፡ እንዳይምሉም ፡ ለልጆቹ፡ይህን፡ሁሉ፡ያስተምራቸው፡ነበር።

፴፱፤ ለእርሱ ፡ ግን ፡ ለሚጸልየው ፡ ጸሎት ፡ ልክ ፡ የለውም ፡ ነቢይ ፡ ዳዊት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ አመሰግነዋለሁ ። ምስጋናውም ፡ ዘወትር፡በአፌ፡ውስጥ፡አለ፡ያለውን፡አስቦ፡ዳግመኛም ፡ ትእዛዝህን ፡ በማሰብ ፡ እጫወታለሁ፡ሕግህን፡እሻለሁ፡ትእዛዞችህንም፡አስተምራለሁ፡ቃልህንም፡አልረሳም፡ያለውን፡አስቦ።

፵፤ ዳግመኛም፡ከሰባውና፡ደም፡ካለው፡ጣዕም፡ካላቸውም ፡ መብሎች ፡ ሁሉ ፡ ይከለከላል ፡ የጌታውን፡መከራ፡ለነፍሱ፡ያሳስባታልና፡ዕንባው ፡ ያለ፡ ማቋረጥ ፡ ይፈስ ፡ ነበር ፡ ያለ ፡ ማቋረጥም፡ይሰግዳል፡ያመሰግናልም፡እንግዳና፡መጻተኛውን፡ይቀበላል፡በጽዮን፡ዘር፡በኢየሩሳሌም፡ቤቶች፡ያሉት፡ብፁዕ፡ነው፡ያለውን፡የነቢይ፡ቃል፡አስቦ፡ድኆችንና፡

ወመተረ ፡ ኵሎ ፡ ልማደ ፡ በመዋዕለ ፡ ሢመቱ ፡ ወአውገዞሙ ፡ ለኤጲስቆጶሳት ፡ ከመ ፡ ኢይንሥኡ ፡ ህልያነ ፡ በእንተ ፡ ሢመተ ፡ ክህነት ወለእለሂ ፡ በሙ ፡ ዕቁባት ፡ አውገዞሙ ፡ ከመ ፡ ይኅድጉ ፡ ዕቁባቲሆሙ ፡ ወሶበ ፡ ሰምዑ ፡ ግዘቶ ፡ ፈርሁ ፡ ኵሎሙ ፡ ወኅደጉ ፡ እኩየ ፡ ልማዶሙ ፡ ወመጽኡ ፡ ኀቤሁ ፡ ወወድቁ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ፡ ወሰአልዎ ፡ ከመ ፡ ይስረይ ፡ ሎሙ ፡ አባሳሆሙ ።

፮ ወኢደፈረ ፡ መኑሂ ፡ ያስተኃቅር ፡ ቃሎ ፡ ዘእንበለ ፡ ፩ ፡ ብእሲ ፡ ዘኮነ ፡ ጸሐፊሁ ፡ ለንጉሥ ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ኢፈርሆ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ ወኢፈርሀ ፡ እምግዘቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ክቡር ፡ ዝንቱሰ ፡ አብ ፡ ሰአሎ ፡ ብዙኀ ፡ ጊዜ ፡ በእንተ ፡ ድኅነተ ፡ ርእሱ ፡ ወገሠጾ ፡ ወመዓዶ ፡ ከመ ፡ ይትመየጥ ፡ እምእከዩ ፡ ወይድኃን ፡ እመ ቅሠፍት ፡ ውእቱሰ ፡ ኢሰምዖ ።

፯ ወዝንቱኒ ፡ አብ ፡ ኢኀደጎ ፡ ምሒሮቶ ፡ ወገሥጾቶ ፡ ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ዕቅፍተ ፡ ለካልኣን ፡ ወበእንተዝ ፡ ሖረ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ ለውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ወሰሚዖ ፡ ምጽአቶ ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዐጸወ ፡ ኆኅቶ ፡ ወቆመ ፡ ዝንቱ ፡ አብ ፡ እንዘ ፡ ይጐድጕድ ፡ ኆኅቶ ፡ መጠነ ፡ ፪ቱ ፡ ሰዓት ፡ ወእምዝ ፡ ነገፈ ፡ ጸበለ ፡ እገሪሁ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ደሙ ፡ ለዝንቱ ፡ ብእሲ ፡ ላዕለ ፡ ርእሱ ፡ ወአነ ፡ ንጹሕ ፡ እምደሙ ፡ ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ ተመይጠ ፡ እንዘ ፡ የኀዝን ፡ ወበጊዜሃ ፡ ከሠተ ፡ እግዚእነ ፡ ትእምርተ ፡ ላዕለ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ እስመ ፡ ተሠጥቀ ፡ መድረከ ፡ ኆኅቱ ፡ ዘዕብን ፡ ወኮነ ፡ ፪ተ ፡ ክፍለ ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ መንክር ፡ ወመድምም ፡ እምቃለ ፡ ግዘቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ተሠጥቀ ፡ ኰኵሕ ፡ ጽኑዕ ፡ ወልበ ፡ ብእሲ ፡ ልምሉም ፡ ጸንዐ ፡ እምኰኵሕ ።

፰ ወዓዲ ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትእምርተ ፡ ዕፁበ ፡ ላዕለ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ እስመ ፡ ኮነ ፡ ነዳየ ፡ እምኵሎሙ ፡ ነዳያን ፡ ፈድፋደ ፡ ወሠዓርዎ ፡ እምሢመቱ ፡ በኀሳር ፡ ወኢተርፈ ፡ ሎቱ ፡ እምንዋዩ ፡ ፩ ፡ ጸሪቅ ፡ ወአመንደቦ ፡ ዓዲ ፡ ሥጋሁ ፡ በደዌ ፡ ዕፁብ ፡ ወተመትሩ ፡ እደዊሁ ፡ ወእገሪሁ ፡ ወሞተ ፡ በእኩይ ፡ ሞት ፡ ወኮነ ፡ አርአያ ፡ ለኵሉ ፡ ወፈርሁ ፡ ብዙኃን ፡ እምኃ

ሰጥቶ ፡ የሊቀ ፡ ጵጵስናውን ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ጀመረ ። በሹመቱም ፡ ወራት ፡ ክፉ ፡ ልማድን ፡ ሁሉ ፡ አስገወደ ፡ ኤጲስቆጶሳቱንም ፡ ስለ ፡ ክህነት ፡ ሹመት ፡ መማለጃ ፡ እንዳይቀበሉ ፡ አወገዛቸው ፡ ዕቁባቶች ፡ ያሉአቸውንም ፡ ሰዎች ፡ ዕቁባቶቻቸውን ፡ እንዲተዉ ፡ አወገዛቸው ፡ ውግዘቱንም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ ፈርተው ፡ ክፉ ፡ ልማዳቸውን ፡ ተዉ ፡ ወደ ርሱም ፡ መጥተው ፡ ከእግሮቹ ፡ በታች ፡ ወድቀው በደላቸውን ፡ ያስተሰርይላቸው ፡ ዘንድ ፡ ለመኑት ።

፮ የንጉሥ ፡ ጸሐፊ ፡ ከሆነ ፡ ከአንድ ፡ ሰው ፡ በቀር ፡ ቃሉን ፡ ያስተሐቅር ፡ ዘንድ ፡ የደፈረ ፡ ማንም ፡ የለም ፡ ይህም ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ስለ ማይፈራ ፡ የዚህን ፡ የቅዱስ ፡ አባት ፡ ግዝትን ፡ አልፈራም ፡ ይህ ፡ አባት ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ድኅነት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ለመነው ፡ ከክፋቱ ፡ ተመልሶ ፡ ከመቅሠፍት ፡ ይድንም ፡ ዘንድ ፡ ገሠጸው ፡ መከረውም ፡ ሰውዬው ፡ ግን ፡ አልሰ ማውም ።

፯ ይህም ፡ አባት ፡ ማስተማሩንና ፡ መገሠጹን ፡ ስለችቶ ፡ አልተወውም ፡ ለሌሎች ፡ ዕንቅፋት ፡ እንዳይሆን ፡ ስለዚህ ፡ ወደዚያ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ሔደ ፡ የሊቀ ፡ ጳጳሳቱንም ፡ መምጣት ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ደጁን ፡ ዘጋ ፡ ይህ ፡ አባትም ፡ ደጁን ፡ እያንኳኳ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ቆመ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የዚህ ፡ ሰው ፡ ደሙ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ እኔ ፡ ከደሙ ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ የእግሩን ፡ ትቢያ ፡ አራግፎ ፡ ተመለሰ ። ወዲያውኑ ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ምልክትን ፡ ጌታችን ፡ ገለጸ ፡ ከደንጊያ ፡ የተሠራ ፡ የቤቱ ፡ መድረክ ፡ ከሁለት ፡ ተከፈለ ፡ ይህ ፡ ፈጽሞ ፡ ድንቅ ፡ ነውና ፡ ከዚህ ፡ አባት ፡ ግዝት ፡ የተነሣ ፡ ጠንካራው ፡ ዐለት ፡ ተሠነጠቀ ፡ ለምለም ፡ የነበረ ፡ የሰውየው ፡ ልብ ፡ ግን ፡ ከዐለት ፡ ጠነከረ ።

፰ ዳግመኛም ፡ ድንቅ ፡ ምልክትን ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ አደረገ ፡ ከድኆች ፡ ሁሉ ፡ እጅግ ፡ የባሰ ፡ ድኃ ፡ ሁኖአልና ፡ ከሹመቱም ፡ በጕስቍልናው ፡ ሻሩት ፡ ከገን ዘቡም ፡ አንዲት ፡ መሐልቅ ፡ እንኳ ፡ አልቀረ ለትም ፡ ደግሞም ፡ ሥጋውን ፡ ጭንቅ ፡ በሆነ ፡ ደዌ ፡ ቀሠፈው ፡ እጆቹና ፡ እግሮቹም ፡ ተቆራ ርጠው ፡ በክፉ ፡ አሟሟት ፡ ሞተ ፡ ለሁሉም ፡

ንጉሥ ፡ ወይቤሎ ፡ ናሁ ፡ አንትሙ ፡ አእላፋት ፡ ወትእልፊተ ፡ አእላፋት ፡ ብክሙ፡ ሃይማኖትክሙ ፡ ወእፈቅድ ፡ ከመ ፡ ታምጽእ ፡ ሊተ ፡ ፩ደ፡ እምኔክሙ ፡ ዘይከሥት ፡ ሊተ ፡ ዘንተ ፡ ትእምርተ ፡ ወእመአኮ ፡ አንተ ፡ ርእሶሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ወይደልወከ ፡ ከመ ፡ ትክሥት ፡ ዘንተ ። ወሰሚዖ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ደንገፀ ፡ ወፈርሀ ፡ ፈድፋደ፡ ወይቤሎ ፡ ለንጉሥ ፡ ተዓገሠኒ ፡ ሠሉሰ ፡ መዋዕለ ፡ ወይቤ ፡ ንጉሥ ፡ ይኩን ፡ ለከ።

፲፫፡ ወወጽአ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ እምቅድመ ፡ ንጉሥ፡ ወአስተጋብኦሙ ፡ ለኤጲስቆጶሳት፡ ወለኵሎሙ ፡ ካህናት ፡ ወመነኮሳት ፡ እለ ፡ ቅሩባን ፡ ወነበሩ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ በመዓልቃ ፡ ዘምስር ፡ እንዘ ፡ ይጼልዩ ፡ ወይጸውሙ ፡ በእሎን ፡ ሠላስ ፡ መዋዕል ፡ ወያስተበቍዑ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀዊሞሙ ፡ ቅድመ ፡ ሥዕላ፡ ለእግዝእትነ ።

፲፬፡ ወአመ ፡ ሣልስት ፡ ዕለት ፡ አስተርአየቶ ፡ ሌሊተ ፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በብሩህ ፡ ገጽ ፡ ወትቤሎ ፡ ኢትፍራህ ፡ እስመ ፡ አነ ፡ ተወከፍኩ ፡ አንብዓከ ፡ ዘከዐውከ ፡ ቅድሜየ ፡ ወሰአልክዎ ፡ ለወልድየ ፡ በእንቲአከ ፡ ወይእዜኒ፡ ተንሥእ ፡ ወሑር ፡ ውስተ ፡ መርህብ ፡ ዘኀቢጊ ፡ ዘይወስድ ፡ ውስተ ፡ ምሥያጥ ፡ ወትረክብ ፡ ብእሴ ፡ ዘይፀውር ፡ ቀሡተ ፡ ማይ ፡ ወቦቱ ፡ አሐቲ ፡ ዓይን ፡ አኅዝ ፡ ኪያሁ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይከሥት ፡ ለከ ፡ ዘንተ ፡ ትእምርተ ፡ ወስሙ፡ ለውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ስምዖን ፡ ሰፋዬ ፡ አሳዕን፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ መልሐ ፡ ዐይኖ ፡ በእንተ ፡ ትእዛዘ ፡ ወልድየ ፡ ወፍቁርየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ።

፲፭፡ ወሶቤሃ ፡ ተንሥአ ፡ ወሖረ ፡ ፍጡነ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወረከቦ ፡ ለውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ወአኀዞ ፡ ወይቤሎ ፡ መሐሮሙ ፡ ለሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ወነገሮ ፡ ዘከመ ፡ አስተርአየቶ፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ወዘከመ ፡ አመረቶ ፡ ኪያሁ ፡ ውእቱኒ ፡ ሰገደ ፡ ሎቱ ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳሳት ። ወይቤሎ ፡ ስረይ፡ ሊተ ፡ እ ፡ አቡየ፡ እስመ ፡

እንዲህ ፡ አለው ፡ እነሆ ፡ ይህ ፡ ሃይማኖት ፡ ያላችሁ ፡ እናንተ ፡ የብዙ፡ ብዙ፡ ናችሁ ። ከእናንተ ፡ ውስጥ ፡ ይህን ፡ ምልክት ፡ የሚገልጥ ፡ አንድ ፡ ሰው፡ ልታመጣልኝ ፡ እሻለሁ ፡ አለዚያም፡ ለክርስቲያን ፡ ወገኖች፡ ሁሉ ፡ አንተ ፡ አለቃቸው፡ ነህና ፡ ይህን፡ ምልክት፡ ትገልጥ፡ ዘንድ፡ ይገባሃል፡ አለው። ሊቀ ፡ ጳጳሳቱም ፡ ሰምቶ ፡ ደነገጠ ፡ እጅግም፡ ፈራ ፡ ንጉሡንም ፡ እስከ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ታገሠኝ ፡ አለው ፡ ንጉሡም፡ ይሁንልህ ፡ አለው።

፲፫፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱም ፡ ከንጉሡ ፡ ፊት ፡ ወጥቶ ፡ በአቅራቢያው ፡ የሚገኙትን ፡ ኤጲስቆጶሳቱን፡ ካህናቱንና ፡ መነኰሳቱን ፡ ሁሉ ፡ ሰበሰባቸው ፡ በምስር ፡ አገር ፡ በመዓልቃ ፡ በእመቤታችን ፡ በቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ በእሊህ ፡ በሦስቱ ፡ ቀኖች ፡ እየጾሙና ፡ እየጸለዩ ፡ በእመቤታችን ፡ ሥዕል ፡ ፊት ፡ ቁመው ፡ ወደ፡ እግዚአብሔር ፡ ሲማልዱ፡ ቆዩ።

፲፬፡ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ በሌሊት ፡ እመቤታችን ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ለሊቀ፡ ጳጳሳቱ ፡ በብሩህ ፡ ገጽ ፡ ተገልጻ ፡ እንዲህ ፡ አለችው ፡ በፊቴ ፡ ያፈሰስከውን ፡ ዕንባህን ፡ ተቀብዬ ፡ ስለአንተ ፡ ልጄን ፡ ለምኜዋለሁና፡ አትፍራ ፡ አሁንም ፡ የብረት ፡ አፈር፡ በአለበት ፡ ሜዳ ፡ ወደ ፡ ገበያ ፡ በሚወስደው፡ ጐዳና ፡ ተነሥተህ ፡ ሒድ ፡ አንድ ፡ ዓይና ፡ የሆነ ፡ የውኃ ፡ እንስራ፡ የተሸከመ ፡ ሰው ፡ ታገኛለህ ፡ ይህን፡ ምልክት ፡ እርሱ ፡ ያደርግልሃልና ፡ እርሱን ፡ ያዘው ፡ የዚህም ፡ ሰው ፡ ስሙ ፡ ጫማ ፡ ሰፊ ፡ ስምዖን ፡ ይባላል፡ እርሱም ፡ ስለምወደው ፡ ልጄ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ትእዛዝ ፡ ዓይኑን ፡ አውልቆ ፡ ጥሏልና።

፲፭፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ተነሥቶ ፡ ፈጥኖ ፡ ሔደ ፡ ያንንም ፡ ሰው፡ አግኝቶ ፡ ያዘው ፡ የክርስቲያን ፡ ወገኖችን ፡ እዘንላቸው፡ ራራላቸው ፡ አለው ፡ አምላክን ፡ የወለደች ፡ እመቤታችን ፡ ቅድስት፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ እንደተገለጸች ለትና ፡ እርሱንም ፡ እንዳመለከተችው ፡ ነገረው ። እርሱም ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ሰግዶ ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡ እኔ ፡ ኃጥእ ፡ በደለኛ ፡ ነኝና ፡ ይቅርታ፡ አድርግ

www.ethiopianorthodox.org

አነ ፡ ኃጥእ ፡ ወአባሲ ፡ ወኢይክሎ ፡ ለዘት
ቢለኒ ፡ ዳዕሙ ፡ ፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለይ
ኩን ፡ በጸሎታ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡
ድንግል ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ወበ
ጸሎትከ ፡ ቅድስት ፡ ከመ፡ ትርድአሙ ፡ ለሕ
ዝበ ፡ ክርስቲያን።

፲፯፡ ወአንሰ ፡ እስእለከ ፡ ከመ ፡ ኢትክሥተኒ ፡
ለመኑሂ ፡ እስመ ፡ አልብየ ፡ ክሂል ፡ ከመ ፡
እፁር ፡ ክብረ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ አላ ፡ ባሕቱ ፡
ዘእቤለከ ፡ ግበር ፡ ወአንተ ፡ ባእ ፡ ኀበ ፡
አንጻረ ፡ ውእቱ ፡ ደብር ፡ ዘይቤለከ ፡ ንጉሥ፡
ምስለ ፡ ካህናቲከ ፡ ወሕዝብከ ፡ ወንሥኡ ፡
ምስሌክሙ ፡ ወንጌላተ ፡ ወመስቀላተ ፡ ወማ
ዕጠንታተ ፡ ወመኃትወ ፡ ሰምዕ ። ወንጉሥኒ፡
ይቁም ፡ ምስለ ፡ ሠራዊቱ ፡ በአሐቲ ፡ ጽንፍ ፡
ወአነ ፡ እቀውም ፡ ቅድሜከ ፡ ውስተ ፡ ሕዝብ
ከመ፡ ኢያእመረኒ ፡ መኑሂ ፡ ወአስተብቍዕ ፡
ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወጽርሑ ፡ እንዘ ፡
ትብሉ ፡ ኪራላይሶን ፡ ፻ወ፩ ፡ ጊዜ ፡ ዘውእቱ፡
እግዚኦ ፡ መሐረነ ፡ ክርስቶስ።

፲፰፡ ወእምዝ ፡ አዝዞሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ያርምሙ ፡
ወእንዘ ፡ እሰግድ ፡ አነ ፡ አሚሃ ፡ ስግድ ፡
አንተሂ ፡ ወግበር ፡ ከመዝ ፡ ሠለስተ ፡ ጊዜ ፡
እንዘ ፡ ተአትብ ፡ በትእምርተ ፡ መስቀል ፡
ማሕየዊ ፡ አንጻረ ፡ ውእቱ ፡ ደብር።

፲፱፡ ወሰሚዖ ፡ ዘንተ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አስም
ዖሙ ፡ ወአለበዎሙ ፡ ለእሊአሁ ፡ ወለን
ጉሥኒ ፡ ነገሮ ፡ ከመ ፡ ይጸእ ፡ ምስለ ፡ ሠራ
ዊቱ ፡ ወይቁም ፡ በካልዕ ፡ ጽንፍ ፡ በአንጻረ ፡
ውእቱ ፡ ደብር ፡ ወወጽኡ፡ ኵሎሙ፡ ወቆሙ፡
በከመ ፡ ይቤሎሙ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ። ወእ
ምዝ ፡ አኀዙ ፡ ይጸልዩ ፡ ወይብሉ ፡ እግዚኦ ፡
መሐረነ ፡ ክርስቶስ ፡ ፻ወ፩ ጊዜ ፡ ወእምዝ ፡
ሰገዱ ፡ ምስለ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ሠለስተ ፡
ጊዜ ፡ ወእንዘ ፡ ይትነሣእ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡
ያመአትብ ፡ ኀበ ፡ ደብር ፡ ውእተ ፡ ጊዜ ፡
ተነቅለ ፡ ውእቱ ፡ ደብር ፡ ወጸለለ ፡ ውስተ ፡
አየር ፡ወሶበ፡ ይሰግዱ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡
ወኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ይወርድ ፡ ውእቱ ፡ ደብር ፡
ውስተ ፡ መካኑ ፡ ወሶበሂ ፡ ይትነሥኡ ፡ ይሬ

ልኝ ፡ ይህን ፡ የምትለኝን ፡ ላደርገው ፡ የማ
ልችል ፡ ነኝ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡
ፈቃድ ፡ ይሁን ፡ አምላክን፡ በወለደች ፡ በእ
መቤታችን ፡ በቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማር
ያም፡ ጸሎት ፡ በአንተም ፡ በከበረች ፡ ጸሎ
ትህ፡ የክርስቲያንን ፡ ወገኖች ፡ እንድትረ
ዳቸው ፡ ይሁን።

፲፯፡ እኔንም ፡ ለማንም ፡ እንዳትገልጠኝ ፡ እለም
ንሃለሁ ፡ እኔ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ክብር ፡ መሸ
ከም ፡ አልችልምና ፡ ነገር፡ ግን ፡ የምልህን ፡
አድርግ ፡ አንተም ፡ ንጉሡ ፡ ይነግልኝ ፡ በሚ
ልህ ፡ ተራራ ፡ ትይዩ ፡ ከካህናቶችህና ፡ ከሕ
ዝብህ ፡ ጋር ፡ ገብተህ ፡ ቁም ፡ ወንጌሎችን ፡
መስቀሎችን ፡ ማዕጠንቶችን ፡ የሰም ፡ መብ
ራቶችን ፡ ያዙ ። ንጉሡም ፡ ከነሠራዊቱ ፡
በአንዲት ፡ ዳርቻ ፡ ይቁም ፡ እኔም ፡ ማንም ፡
እንዳያውቀኝ ፡ ከሕዝቡ ፡ ተደባልቄ ፡ በፊ
ትህ ፡ እቆማለሁ ፡ አርባ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡
ኪራላይሶን ፡ እያላችሁ ፡ በመጮህ ፡ ወደ ፡
እግዚአብሔር፡ ማልዱ ፡ ይኸውም ፡ አቤቱ ፡
ክርስቶስ ፡ ማረን ፡ ራራልን ፡ ይቅር ፡ በለን ፡
ማለት ፡ ነው።

፲፰፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ዝም ፡ እንዲሉ ፡ ሕዝቡን ፡
እዘዛቸው ፡ እኔም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ስሰግድ ፡
አንተ ፡ ስገድ ፡ እንዲህም ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡
አድርግ ፡ በዚያ ፡ ተራራ ፡ አንጻር ፡ ማሕየዊ፡
በሆነ ፡ በመስቀል ፡ ምልክት ፡ በየስግደትህ፡
አማትብ ፡ አለው።

፲፱፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱም ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ ለወገ
ኖቹ ፡ በማሰማት ፡ አስገነዘባቸው ፡ በዚያም፡
ተራራ ፡ በሌላ ፡ ገጽ ፡ ከሠራዊቱ ፡ ጋር ፡
ወጥቶ ፡ እንዲቆም ፡ ለንጉሡ ፡ ነገረው ፡
ሊቀ ፡ ጳጳሳቱም ፡ እንደነገራቸው ፡ ሁሉም ፡
ወጥተው ፡ ቆሙ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሊጸልዩ፡
ጀመሩ ፡ አርባ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ አቤቱ ፡
ክርስቶስ ፡ ማረን ፡ አሉ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡
ሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ሰገደ ፡ ሲነ
ሣም ፡ ወደዚያ ፡ ተራራ ፡ አማተበ ፡ በዚያ
ንም ፡ ጊዜ ፡ ተራራው ፡ ከቦታው ፡ ተነቅሎ ፡
በአየር ፡ ላይ ፡ ተንሳፈፈ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱና ፡
ሕዝቡም ፡ ሲሰግዱ ፡ ያ ፡ ተራራ ፡ ወደ፡
ቦታው፡ ይወርዳል ፡ ከሰገዱበትም ፡ ሲነሡ ፡
ከቦታው ፡ ተነቅሎ ፡ ወደ ፡ አየር ፡ ወጥቶ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ልስ ፡ ወየዓርግ ፡ ውስተ ፡ አየር ፡ ወከመዝ ፡ ገብረ ፡ ሠለስተ ፡ ጊዜ።

፲፱፡ ወርእዮሙ ፡ ዘንተ ፡ መንክረ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ፡ አንከሩ ፡ ፈድፋደ ፡ ወሰብሕዎ ፡ ለእግዚአ ብሔር ፡ ስቡሕ ፡ ወፈርህዎ ፡ ለሊ.ቀ ፡ ጳጳሳት፡ አባ ፡ አብርሃም ፡ ወንጉሥኒ ፡ አብጽሖ ፡ ለሊ.ቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ኀቤሁ ፡ ወአክበሮ ፡ ዐቢየ፡ ክብረ ፡ ወይቤሎ ፡ ሰአለኒ ፡ ዘትፈቅድ ፡ ወተመነይ ፡ እምኔየ ፡ ወአነ ፡ ኢይከልአከ፡ ምንተኒ ፡ ወሶበ ፡ አገበሮ ፡ ንጉሥ ፡ ለሊ.ቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ይቤሎ ፡ እፈቅድ ፡ ከመ ፡ እሕንፅ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወፈድፋደሰ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ለቅዱስ ፡ መርቆሬዎስ ፡ ሰማ ዕት ፡ በሀገረ ፡ ምስር ፡ ወአዘዘ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይሕንፅ ፡ በከመ ፡ ፈቀደ ፡ ወንዋየሂ ፡ ብዙኀ፡ አቀረበ ፡ ሎቱ ፡ እምቤተ ፡ መንግሥቱ፡ ወይ ቤሎ ፡ አባ ፡ አብርሃም ፡ ሊ.ቀ ፡ ጳጳሳት ፡ እግዚአብሔር ፡ ያኑኅ ፡ መዋዕሊ.ከ ፡ በዲበ ፡ ምድር ፡ ወያጽንዕ ፡ መንግሥተከ ፡ ወአንሰ ፡ ኢይፈቅድ ፡ ንዋየ።

፳፡ ወሶበ ፡ ይቤሎ ፡ ዘንተ ፡ አንከረ ፡ ንጉሥ ፡ ወአፍቀሮ ፡ ፈድፋደ ፡ በእንተ ፡ መንኖቱ ፡ ንዋየ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም።

፳፩፡ ወእምዝ ፡ ወጽአ ፡ ንጉሥ ፡ ወተጽዕነ፡ ፈረሰ፡ ወሖረ ፡ ምስለ ፡ ሠራዊቱ ፡ ወቆመ ፡ ምስሌሁ፡ ለሊ.ቀ ፡ ጳጳሳት ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ፈጸመ ፡ ሐኒፆታ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘቅዱስ ፡ መርቆሬዎስ ፡ ወካልአነሂ ፡ አብያተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ ብዙኃን ፡ በሀገረ ፡ ምስር ፡ እስመ ፡ ነበሩ ፡ ሰብእ ፡ እኩያን ፡ እለ፡ ይትቃወሙ ፡ ወይፈቅዱ ፡ ከመ ፡ ያንህሉ ፡ ዘተሐነፀ ፡ በእንተዝ ፡ አጽንዐ ፡ ንጉሥ ፡ ዐቂቦተ ።

፳፪፡ ወሶበ ፡ ፈጸመ ፡ ገድሎ፡ ወአሥመሮ ፡ ለእግ ዚአብሔር ፡ አዕረፈ ፡ በሰላም ፡ እምድኅረ ፡ ነበረ ፡ ዲበ፡ መንበረ ፡ ማርቆስ ፡ ወንጌላዊ፡ ፮ተ ፡ ዓመተ ፡ ወ፮ተ ፡ አውራኀ።

፳፫፡ ወቦ ፡ ዘይቤ ፡ በውስተ ፡ ገድሉ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ጸሐፊ ፡ ዘአውገዞ ፡ በእንተ ፡ ዕቁባቲሁ ፡ ዘውእቱ ፡ ቀተሎ ፡ በሕ ምዝ።

ይንሳፈፋል ፡ እንዲህም ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ አደረገ።

፲፱፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ይህን ፡ ድንቅ ፡ ሥራ፡ አይተው ፡ እጅግ ፡ አደነቁ ፡ ምስጉን ፡ እግዚ. አብሔርንም ፡ አመሰገኑት ፡ ሊ.ቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ አብርሃምንም ፡ ፈሩት ፡ ንጉሡም ፡ ወደ. ርሱ ፡ አስቀርቦ ፡ ታላቅ ፡ ክብርን ፡ አከበ ረው ፡ እንዲህም ፡ አለው ፡ የምትሻውን ፡ ለምነኝ ፡ ከእኔም ፡ ተመኝ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ አልከለክልህም ፡ ንጉሡም ፡ ሊ.ቀ ፡ ጳጳሳቱን፡ ግድ ፡ ለምነኝ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ ልሠራ ፡ እሻለሁ ፡ ይል ቁንም ፡ የሰማዕት ፡ ቅዱስ ፡ መርቆሬዎስን ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን ፡ በምስር ፡ ሀገር ፡ ልሠራ ፡ እሻለሁ ፡ አለው ፡ እንደወደደም ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘለት ፡ ከቤተ ፡ ምንግሥቱም ፡ ብዙ ፡ ገንዘብን ፡ አቀረበለት፡ ሊ.ቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ አብርሃምም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እግዚ. አብሔር፡ ዕድሜህን ፡ ያርዝም ፡ መንግሥት ህንም ፡ ያጽና ፡ እኔ ፡ ገንዘብ ፡ አልሻም ፡ አለው።

፳፡ ይህንንም ፡ በአለው ፡ ጊዜ ፡ ንጉሥ ፡ አደነቀ ፡ የዚህንም፡ ዓለም ፡ ገንዘብ ፡ በመናቁ ፡ እጅግ፡ ወደደው።

፳፩፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የቅዱስ ፡ መርቆሬዎስ ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን ፡ ሥራዋ ፡ እስቲፈጸም ፡ ሌሎችም ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ የተሠሩ ፡ ብዙ ዎች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ እስቲሠሩ ፡ ንጉሡ ፡ በፈረስ ፡ ተቀምጦ ፡ ከሠራዊቱ ፡ ጋር፡ በመሔድ ፡ ከሊ.ቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ለሥራ ፡ ይሰለፍ ፡ ነበር ፡ የሚቃ ወሙ፡ ክፉዎች ፡ ሰዎች ፡ የተሠራውንም ፡ ያፈርሱ ፡ ዘንድ ፡ የሚሹ ፡ ስለነበሩ ፡ ስለዚህ፡ ንጉሥ ፡ አጽንቶ ፡ አስጠበቀ።

፳፪፡ ተጋድሎውንም ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብ ሔርንም ፡ አገልግሎ ፡ በወንጌላዊ ፡ ማርቆስ፡ ወንበር ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ ከኖረ ፡ በኋላ ፡ በሰላም ፡ አረፈ።

፳፫፡ በዚህም ፡ አባት ፡ በገድሉ ፡ መጽሐፍ ፡ ያ ፡ ስለ፡ ዕቁባቶቹ ፡ ያወገዘው ፡ ጸሐፊ ፡ በመርዝ፡ ገደለው ፡ የሚል ፡ አለ።

www.ethiopianorthodox.org

| | |
|---|---|
| ፳፬፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን። | ፳፬ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በዚህ ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን። |

## አርኬ

ሰላም ፡ ለከ ፡ አብርሃም ፡ ነጋዲ። ወሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዓዲ። ሶበ ፡ ዐጸወ ፡ ቅድሜከ ፡ በግዝፈተ ፡ ልብ ፡ አባዲ። ሰሚዖ ፡ ቃለ ፡ ግዘት ፡ እምልሳንከ ፡ ነዳዲ። መድረከ ፡ ኆኅቱ ፡ ተሠጥቀ ፡ ለብእሲ ፡ ከሀዲ።

ሰላም ፡ ለስምዖን ፡ በአፈ ፡ ማርያም ፡ ዘተአምረ። እንበይነ ፡ ትእዛዙ ፡ ለወልዳ ፡ ከመ ፡ ዓይኖ ፡ አዖረ። ኢይሌብውዎ ፡ ሎቱ ፡ ወኢይጸግውዎ ፡ ክብረ። ሶበ ፡ ጸለየ ፡ ቀዊሞ ፡ ዘሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ድኅረ ። ነቀለ ፡ ደብረ ፡ ወተከለ ፡ ደብረ።

| | |
|---|---|
| ፳፭፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካረ ፡ ቅዳሴ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያና ፡ ለቅድስት ፡ አርሴማ ፡ ድንግል። ወፍልሰተ ፡ ሥጋሃ ፡ ወሥጋሆን ፡ ለቅዱሳት፡ ደናግል ፡ እለ፡ ምስሌሃ ፡ ተቀትላ ፡ ፳ ፡ ወ፯ ፡ ሰማዕታት ። | ፳፭፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ የድንግሊቱ ፡ አርሴማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኗ ፡ የከበረችበትና ፡ የሥጋዋ፡ ፍልሰት ፡ የሆነበት ፡ ከእርሷ ፡ ጋር ፡ የተገደሉ ፡ የሃያ፡ ሰባት ፡ ደናግልም ፡ የሥጋቸው ፡ ፍልሰት ፡ የሆነበት ፡ ነው። |
| ፳፮፤ ለዛቲስ፡ ቅድስት ፡ አርሴማ ፡ ይቤላ ፡ ንጉሥ ፡ ድርጣድስ ፡ አልቦኑ ፡ ልብኪ ፡ ዘመጠነዝ ፡ ሕይወት ፡ ነቢረ ፡ ዘአበይኪ ፡ ምስሌነ ፡ ወትቤሎ ፡ ዘበሰማያት ፡ የዐቢ ፡ ወይኄይስ ፡ ፈድፋደ ፡ ወአዘዘ ፡ ይሰድዋ ፡ ኀበ ፡ ገቦ ፡ ወያዕርቅዋ ፡ ወይምትሩ ፡ ክሣዳ ፡ በሰይፍ ፡ ወለከተሎን ፡ ደናግል ፡ ይምትሩ ፡ ክሣዶን ፡ አዘዘ። | ፳፮፤ ይችንም ፡ ቅድስት ፡ አርሴማን ፡ ንጉሥ ፡ ድርጣድስ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ታላቅ ፡ ክብር ፡ ካለው ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ መኖርን ፡ እምቢ ፡ ያልሽ ፡ ልብ ፡ የለሽምን ፡ አላት ፡ እርሷም ፡ በሰማያት ፡ ያለው ፡ ይበልጣል ፡ እጅግም ፡ ይሻላል ፡ አለችው ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ ወስደው ፡ ልብሷን ፡ ገፈው ፡ አንገቷን ፡ በሰይፍ ፡ እንዲቆርጡ ፡ አዘዘ ፡ የደናግሉንም፡ ሁሉ ፡ አንገት ፡ እንዲቆርጡ ፡ አዘዘና ፡ ተቆረጡ ። |
| ፳፯፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቶን ፡ ለደናግል ፡ አሜን። | ፳፯፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በደናግል ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ አሜን። |

## አርኬ

ሰላም ፡ ለፍልሰተ ፡ ሥጋኪ ፡ በስብሐተ ፡ ብዙኅ ፡ ጉባኤ። አመ ፡ ሰከብኪ ፡ አርሴማ ፡ እስከ ፡ ይከውን ፡ ትንሣኤ ። ወእኤምኅ ፡ ካዕበ ፡ በቃለ ፡ ስብሐት ፡ ወውዋዔ ። ሰማዕታተ ፡ ዘቅድሜኪ ፡ እስራ ፡ ወሱባዔ ። ወእለ ፡ ድኅሬኪ ፡ ተስዓ ፡ ወክልኤ።

| | |
|---|---|
| ፳፰፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ኤልያስ ፡ አረሚ ፡ ወበጥልስ ፡ ወሱርፍት ፡ ወማርያ ፡ ወሚካኤል ፡ ወይልሰውል፡ ወተለሜዎስ። ወበረከቶሙ ፡ ትብጽሐነ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አሜን። | ፳፰፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ የቅዱሳን ፡ አረሚ ፡ የነበረ፡ የኤልያስ ፡ የበጥልስ ፡ የሱርፍት ፡ የማርያ ፡ የሚካኤል፡ የይልሰውል፡ የተለሚዎስ፡ መታሰቢያቸው ፡ ነው ። በረከታቸውም ፡ ትድረሰን ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና፡ ይሁን ፡ አሜን። |
| * * * | * * * |
| ፩፤ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፯ ለታኅሣሥ ፡ በዛቲ ፡ | ፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ታኅሣሥ ፡ ሰባት ፡ |

www.ethiopianorthodox.org

ዕለት ፡ አዕረፈ፡ አባ ፡ ዳንኤል ፡ ዘደብረ ፡
ሲሐት ፡ ዘደብረ ፡ አባ፡ መቃርስ።

፪፤ ወዝንቱ ፡ አባ ፡ ዳንኤል ፡ ዘገነዛ ፡ ለበጥሪቃ ፡
ንግሥት ፡ ዘሰመየት ፡ ስማ ፡ እንጣልዮስሃ ፡
ወይእቲ ፡ ኢተአምረት፡ ከመ ፡ ብእሲት ፡
ይእቲ ፡ ዘእንበለ ፡ እምድኅረ፡ ሞታ።

፫፤ ወአሐተ ፡ ዕለተ ፡ እንዘ ፡ የሐውር ፡ ምስለ ፡
ረድኡ ፡ ሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ረከበ ፡ እቡደ ፡
ዘስሙ ፡ ምህርካ ፡ ወይተልውዎ ፡ ብዙኃን ፡
እቡዳን ፡ ለሰብአ ፡ ሀገርኒ ፡ ይመስሎሙ ፡
እቡደ ፡ በጽድቅ ፡ ወአኀዞ ፡ አባ ፡ ዳንኤል ፡
እዴሁ ፡ ወወሰዶ ፡ ኀበ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወነ
ገሮ ፡ ትሩፋቲሁ ፡ ወሶበ ፡ አምሐልዎ ፡ ነገ
ሮሙ ፡ ከመ ፡ ጐየ ፡ እምጸብአ ፡ ዝሙት ፡
ወረሰየ ፡ ርእሶ ፡ አብደ ፡ ወሰሚያሙ፡ ሰብ
ሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር።

፬፤ ወአሐተ ፡ ዕለተ ፡ በጽሐ ፡ ውስተ ፡ አሐቲ ፡
ሀገር ፡ ወረከበ ፡ ብእሴ ፡ ዘይወቅር ፡ ዕብነ ፡
ዘስሙ ፡ አውሎጊስ ፡ ወውእቱ ፡ ይምሕር ፡ ነዳ
ያነ ፡ ወይትዌከፍ ፡ ነግደ ፡ ለውእቱኒ ፡ አኅ
ደሮ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ በፍሥሐ ፡ ወርእየ ፡
ሠናይቶ ፡ ሰአለ ፡ በእንቲአሁ ፡ እምኀበ፡
እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ የሀቦ ፡ ንዋየ ፡ ለአውሎ
ጊስ ፡ በዘይትዌከፍ ፡ ነዳያነ ፡ ወአስተርአዮ፡
እግዚእነ፡ በአምሳለ ፡ ሕፃን ፡ ወይቤሎ፡ ትትሀ
በዮኑ ፡ አንተ ፡ ከመ ፡ ኢይወልጥ ፡ ግዕዞ ፡
ወይቤ ፡ አባ ፡ ዳንኤል ፡ እወ ፡ እትሀበዮ።

፭፤ ወእምዝ ፡ ረከበ ፡ አውሎጊስ ፡ ወርቀ ፡ ምሉዐ፡
መቅፀት ፡ ወነሢአ ፡ ሖረ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡
ወተሠይመ ፡ መኰንነ ፡ ሊቀ ፡ ሐራ ፡ ወወ
ለጠ ፡ ግዕዞ ፡ ወሰሚያ ፡ አባ፡ ዳንኤል ፡ ከመ
ወለጠ ፡ ግዕዞ ፡ አውሎጊስ ፡ ሖረ ፡ ከመ ፡
ይገሥጾ ፡ ወዘበጥዎ ፡ ሐራሁ ፡ ለአውሎጊስ
እስከ ፡ አብጽሕዎ፡ ለሞት ፡ ወእንዘ ፡ የኀዝን፡
በዝንቱ ፡ አስተርአዮ ፡ ውእቱ ፡ ሕፃን ፡ በሕ
ልም ፡ ወአዘዘ ፡ ከመ ፡ ይስቅልዎ ፡ ለአባ ፡
ዳንኤል ፡ ወይቤሎ ፡ ለምንት ፡ ቦእከ ፡ ውስተ፡
ነገረ ፡ ባዕድ ፡ ወእምዝ ፡ መጽአት ፡ እግዝእ

በዚች ፡ ቀን ፡ በአባ ፡ መቃርስ ፡ ገዳም ፡ በደ
ብረ ፡ ሲሐት ፡ የሚኖር ፡ አባ ፡ ዳንኤል ፡
አረፈ ።

፪፤ ይህም ፡ አባ ፡ ዳንኤል ፡ ስሟን ፡ እንጣልዮስ ፡
አስኝታ ፡ የነበረች ፡ ንግሥት ፡ በጥሪቃን ፡
የገነዛት ፡ ነው ፡ እርሷም ፡ ከሞቷ ፡ በኋላ ፡
እንጂ ፡ ሴት ፡ እንደሆነች ፡ አልታወቀችም
ነበር።

፫፤ በአንዲት ፡ ቀንም ፡ ወደ፡ እስክንድርያ ፡ አገር፡
ከረድኡ ፡ ጋር ፡ ሲጓዝ ፡ ስሙ ፡ ምህርካ ፡
የሚባል ፡ እብድ ፡ አገኘ ፡ ብዙ ፡ እብዶችም ፡
ይከተሉታል ፡ ለአገር ፡ ሰዎችም ፡ በእውነት፡
ያበደ ፡ ይመስላቸው ፡ ነበር ፡ አባ ፡ ዳንኤልም፡
እጁን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ወስዶ ፡
ትሩፋቱን ፡ ተጋድሎውን ፡ ነገረው ፡ እንዲነግ
ራቸውም ፡ በአማሉት ፡ ጊዜ ፡ ከዝሙት ፡ ጦር፡
በመሸሽ ፡ ራሱን ፡ እብድ ፡ እንዳስመሰለ ፡ ነገ
ራቸው ፡ ሰምተውም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመ
ሰገኑት።

፬፤ በአንዲትም ፡ ዕለት ፡ ወደ ፡ አንዲት ፡ አገር ፡
ደረሰ ፡ በዚያም ፡ አውሎጊስ ፡ የሚባል ፡ ለድ
ኆች ፡ የሚራራ ፡ እንግዳም ፡ የሚቀበል ፡ ደን
ጊያ ፡ በመውቀር ፡ የሚኖር ፡ ሰው ፡ አገኘ ፡
እርሱንም ፡ ተቀብሎ ፡ በደስታ ፡ አሳደረው ፡
መልካም ፡ ሥራውንም ፡ በአየ፡ ጊዜ ፡ ድኆ
ችን ፡ የሚረዳበት ፡ ገንዘብን ፡ ለአውሎጊስ ፡
ይሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ስለርሱ ፡ ለመነ ፡ ጌታችንም ፡ በሕፃን ፡ አም
ሳል ፡ ተገለጠለትና ፡ ገንዘብ ፡ ባገኘ ፡ ጊዜ ፡
ጠባዩን ፡ እንዳይለውጥ ፡ አንተ፡ ትዋሰዋለህን፡
አለው ፡ አባ ፡ ዳንኤልም ፡ አዎን ፡ እዋሰዋለሁ፡
አለ።

፭፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አውሎጊስ ፡ በድስት፡ የመላ፡
ወርቅን ፡ አግኝቶ ፡ ያንን ፡ ይዞ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡
ሒዶ ፡ የጭፍራ ፡ አለቃ ፡ ሆኖ ፡ ተሾመ ፡
ጠባዩንም ፡ ለወጠ ። ጠባዩንም ፡ እንደለወጠ ፡
አባ ፡ ዳንኤል ፡ ሰምቶ ፡ ሊመክረውና ፡ ሊገ
ሥጸው ፡ ሔደ ፡ የአውሎጊስ ፡ ወታደሮችም ፡
ለመሞት ፡ እስኪደርስ ፡ ድረስ ፡ ደበደቡት ፡
በዚህም ፡ እያዘነ ፡ ሳለ ፡ ያ ፡ ሕፃን ፡ በሕልም ፡
ታየው ፡ አባ ፡ ዳንኤልንም ፡ ለምን ፡ በሌላ ፡
ሰው፡ነገር፡ገባህ፡ብሎ፡እንዲሰቅሉት፡አዘዘ።
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እመቤታችን ፡ ቅድስት ፡ ድን

www.ethiopianorthodox.org

ትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ወሰገ
ደት ፡ ወሰዓመት ፡ እገሪሁ ፡ ለሕፃን ፡ ወሰአ
ለቶ ፡ በእንተ ፡ አባ፡ ዳንኤል ፡ ወአድኃነቶ።
፮፤ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ነግሠ ፡ ካልዕ ፡ ንጉሥ ፡ ኃሠሠ፡
ለአውሎጊስ ፡ ከመ ፡ ይቅትሎ ፡ አሚሃ ፡ ጐየ ፡
አውሎጊስ ፡ ወበጽሐ ፡ ውስተ ፡ ሀገሩ ፡ ወተ
መይጠ ፡ ኀበ ፡ ዘቀዳሚ ፡ ግብሩ ፡
፯፤ ወአሐተ ፡ ዕለተ ፡ እንዘ ፡ የሐውር ፡ ሌሊተ ፡
በብርሃነ ፡ ወርኅ ፡ በውስተ ፡ ገዳም ፡ ረከበ ፡
ብእሲተ ፡ በመልዕልተ ፡ ደብር ፡ ወሥዕርታ ፡
ይከድን፡ ኵሎ ፡ ሥጋሃ ፡ ወይእቲ ፡ ዘነበረት ፡
እንዘ ፡ ትትጋደል ፡ ፴ወ፰ተ ፡ ዓመተ ፡ ወነ
ገረቶ ፡ ኵሎ ፡ ምሥጢራ ፡ ወእምዝ ፡ አዕረ
ፈት ።
፰፤ ወእምዝ ፡ በአሐቲ ፡ ዕለት፡ አምጽኡ ፡ ሰብእ ፡
ጠማረ፡ ልዮን፡ ወአንበብዋ፡ በቅድመ፡ ሕዝብ፡
ወቀነጸ ፡ አባ፡ ዳንኤል ፡ ወመሠጣ ፡ ለመጽ
ሐፈ ፡ ልዮን ፡ ወሠጠጣ ፡ ወይቤ ፡ ውጉዝ ፡
ሃይማኖተ ፡ ኬልቄዶን ፡ ወርእዮሙ፡ ሐራ ፡
ዘበጥዎ ፡ ወሰደድዎ ፡ እምደብሩ።

፱፤ ወአሐተ ፡ ዕለተ ፡ በጽሐ ፡ ኀበ ፡ ደብረ ፡ ደናግል ፡
አባ ፡ ዳንኤል ፡ ወጐድጐደ ፡ ኆኅተ ፡ ወአእ
ሚሮን ፡ ከመ ፡ አባ ፡ ዳንኤል ፡ ውእቱ ፡ አርኀዋ ፡
ሎቱ ፡ ወተቀበላሁ ፡ በፍሥሐ ፡ ወአሐቲ ፡
እምኔሆን ፡ ዘትሰክብ ፡ ኀበ ፡ ኆኅት ፡ ዘረሰየት ፡
ርእሳ ፡ አብደ ፡ ወተሰአላ ፡ ለእመ ፡ ምኔት ፡ በእን
ቲአሃ ፡ ወትቤሎ ፡ እመ ፡ ምኔት ፡ አብድ ፡ ይእቲ ፡
ወነገራ ፡ አባ ፡ ዳንኤል ፡ ከመ ፡ ኢኮነት ፡ አላ ፡
ተጋዳሊት ፡ ቅድስት ፡ ይእቲ ፡ ወበሌሊት ፡
ጸሐፈት ፡ እንዘ ፡ ትብል ፡ ስረያ ፡ ሊተ ፡ ኦ ፡
አኃትየ ፡ ቅዱሳት ፡ በእንተ ፡ ዘአማዕኩክን ፡
ወዘንተ ፡ ኀዲጋ ፡ ተኀጥአት ፡ ወሰሚያን ፡
ደናግል ፡ ተከዛ ፡ ጥቀ ፡ ወነስሓ።
፲፤ ወሀሎ ፡ ደብር ፡ ዘይነብራ ፡ ውስቴቱ ፡ ደናግል
ብዙኃት ፡ ወአንቀጹኒ ፡ ጽኑዕ ፡ ወአንሥአ ፡
ሰይጣን ፡ ላዕሌሆን ፡ ፈያተ ፡ ከመ ፡ ይበርብሩ ፡
ንዋዮን ፡ ወተኬነወ ፡ ሊቀ ፡ ፈያት ፡ ወረሰየ ፡
ቆብዐ፡ ዲበ ፡ ርእሱ ፡ ወተዓጽፈ ፡ በአምሳለ ፡
አባ፡ ዳንኤል ፡ ወሐረ ፡ ወጐድጐደ ፡ ኆኅቶን ፡
ወይቤ ፡ አነ ፡ አባ ፡ ዳንኤል ፡ ወርእዮን ፡
አርኀዋሁ ፡ መነኮሳይያት ፡ ወተቀበላሁ ፡
በፍሥሐ ፡ ወሐፀባ ፡ እገሪሁ ፡ ወተረቅያ ፡

ግል ፡ ማርያም ፡ መጥታ ፡ ለሕፃኑ ፡ ሰገደች ፡
እግሮቹንም ፡ እየሳመች ፡ ስለ ፡ አባ ፡ ዳንኤል፡
ለምና ፡ ከስቅለት ፡ አዳነችው ።
፮፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ ንጉሥ ፡ በነገሠ ፡
ጊዜ ፡ አውሎጊስን ፡ ሊገድለው ፡ ፈለገው፡
ያን ፡ ጊዜ ፡ አውሎጊስ ፡ ሸሸ ፡ ወደ፡ አገሩም ፡
ደርሶ፡ ወደ ፡ ቀድሞ ፡ ሥራው ፡ ተመለሰ።
፯፤ በአንዲት ፡ ቀንም ፡ በሌሊት ፡ በበረሀ ፡ ውስጥ፡
በጨረቃ ፡ ብርሃን ፡ ሲኳዝ ፡ በተራራ፡ ላይ ፡
ተቀምጣ ፡ ሴት ፡ አገኘ ፡ ጠጉሩዋም ፡ ሥጋ
ዋን ፡ ሁሉ ፡ ሸፍኖአል ፡ እየተጋደለች ፡ ሠላሳ፡
ስምንት ፡ ዓመት ፡ የኖረች ፡ ናት ፡ ምሥጢር
ዋንም ፡ ሁሉ ፡ ነግራው ፡ ከዚህ፡ በኋላ ፡
አረፈች።
፰፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በአንዲት ፡ ዕለት ፡ የልዮ
ንን፡ ደብዳቤ ፡ ሰዎች ፡ አምጥተው ፡ በሕዝብ ፡
ፊት ፡ አነበቧት ፡ አባ ፡ ዳንኤልም ፡ ዘሎ ፡ የል
ዮንን ፡ ደብዳቤ ፡ ነጥቆ ፡ ቀደዳትና ፡ የኬልቄ
ዶን ፡ ሃይማኖት ፡ የተወገዘ ፡ ነው ፡ አለ ፡
ወታደሮችም ፡ አይተው ፡ ደበደቡት ፡ ከገዳ
ሙም ፡ አሳደዱት ።
፱፤ በአንዲት ፡ ዕለትም ፡ አባ ፡ ዳንኤል ፡ ከደናግል ፡
ገዳም ፡ ደርሶ ፡ ደጁን ፡ አንኳኳ ፡ አባ ፡
ዳንኤልም፡እንደሆነ፡አውቀው፡ከፈቱለትና፡
በደስታ ፡ ተቀበሉት ፡ ከእነርሱም ፡ አንዲቷ ፡
ራሷን፡እብድ፡አስመስላ፡በደጅ፡የምትተኛ፡
አለች ፡ ስለርሷ ፡ እመ ፡ ምኔቷን ፡ ጠየቃት ፡
እርሷም ፡ እብድ ፡ ናት ፡ አለችው ። እርሱም ፡
መስተጋድልት ፡ ቅድስት ፡ ሴት ፡ እንጂ ፡
እብድ፡እንዳልሆነች፡ነገራት።እብድ፡የተባለ
ችውም ፡ በሌሊት ፡ ተነሥታ፡ የከበራችሁ ፡
እኅቶቼ ፡ ስለአሳዘንኳችሁ ፡ ይቅር ፡ በሉኝ ፡
ብላ፡ ጽፋ ፡ ያንን ፡ ትታ ፡ ታጣች ፡ ደናግሉም ፡
እጅግ፡አዘኑ፡ተጸጸቱም።
፲፤ በውስጡ ፡ ብዙ ፡ ደናግል ፡ የሚኖሩበት ፡ ገዳም፡
ነበረ ፡ መዝጊያውም ፡ የጸና ፡ ነው። ገንዘባቸ
ውንም ፡ ይበረብሩአቸው ፡ ዘንድ ፡ ሰይጣን ፡
ወንበዴዎችን ፡ በላያቸው አስነሣ ፡ የወንበ
ዴዎች ፡ አለቃም ፡ በመራቀቅ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡
ቆብ ፡ አድርጎ ፡ በአባ ፡ ዳንኤል ፡ አምሳያ ፡
ለብሶ፡ ደጃፉቸውን ፡ ሒዶ ፡ በማንኳኳት ፡ አባ
ዳንኤል ፡ ነኝ ፡ አለ ፡ አይተውም ፡ ከፈቱለት ፡
በደስታም ፡ ተቀብለው ፡ እግሩን ፡ አጠቡትና፡

www.ethiopianorthodox.org

በምሕፃበ፡ እገሪሁ፡ ውስተ፡ ገጾን፡ በእንተ፡ በረከት። ወአሐቲ፡ እምኔሆን፡ ዕውርት፡ ሶበ፡ ለከፋ፡ ማይ፡ ተከሥታ፡ አዕይንቲሃ፡ ወይቤላ፡ ደናግል ፡ ብፁዕ ፡ አንተ ፡ አባ ፡ ዳንኤል ፡ ወርእዮ፡ ሊቀ ፡ ፈያት ፡ ደንገፀ ፡ ወነስሐ ፡ ወመንኰሰ፡ በኀበ፡ አባ፡ ዳንኤል፡ ወኮነ፡ መስ ተጋድለ።

ስለ ፡ በረከት ፡ የእግሮቹን ፡ እጣቢ ፡ በየፊ ታቸው ፡ ረጩት ፡ ከውስጣቸው ፡ አንዲት ፡ ዕውር፡ ነበረች፡ ውኃው፡ ሲነካት፡ ዐይኖቿ፡ በሩላት፡ ደናግሉም፡ አንተ፡ አባ፡ ዳንኤል፡ ንዑድ፡ ክቡር፡ ነህ፡ አሉት፡ የሽፍቶቹም፡ አለቃ፡ አይቶ፡ ደነገጠ፡ ተጸጸተም፡ ከአባ፡ ዳንኤልም፡ዘንድ፡መንኵሶ፡የሚጋደል፡ሆነ።

፲፩፡ ወሶበ፡ ቀርበ፡ ጊዜ፡ ፍልሰቱ፡ ነገሮ፡ መልአከ፡ እግዚአብሔር፡ ወሐመ፡ ንስቲተ፡ ወጸለየ፡ ኀበ፡ እግዚእነ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ሎቱ፡ ስብሐት፡ ወአዕረፈ፡ በሰላም።

፲፪፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ ጻድቅ ፡ ወበረከቱ፡ ተሀሉ፡ ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ ዓለም፡ አሜን።

፲፩፡ ዕረፍቱም፡ በቀረበ፡ ጊዜ፡ የእግዚአብሔር መልአክ፡ ነገረው፡ ጥቂት፡ ጊዜም፡ ታመመ፡ ክብር፡ ይግባውና፡ ወደ፡ ጌታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ጸለየና፡ በሰላም፡ አረፈ።

፲፪፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም፡ በዚህ፡ ጻድቅ፡ ጸሎት፡ ይማረን፡ በረከቱም፡ ከእኛ፡ ጋር፡ ትኑር፡ ለዘላለሙ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ ለከ፡ በቃለ፡ ብፅዓን፡ ዘካህናት። ዘደብረ፡ ሲሐት ።ዳንኤል፡ ዑጹፍ፡ በቈጽለ፡ ፀበርት ። እንዘ፡ ትሴፈዋ፡ ለትርሲተ፡ ሰማይ፡ ጽጊት። ዘኢያድምዕዋ፡ በምድር፡ ብዑላን፡ ነገሥት።

ሶበ፡ ሰአለ፡ ኀቤኪ፡ እንዘ፡ ስመኪ፡ ይሰሚ። በእንተ፡ አውሎጊስ፡ ማሕመሚ። አእጋረ፡ ክርስቶስ፡ ሎቱ፡ እንዘ፡ ትስዕሚ። በከመ፡ አድኃንኪ፡ ነፍሰ፡ ዳንኤል፡ ቀዳሚ። አድኅኖትየ፡ ማርያም፡ ድግሚ።

፲፫፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካራ ፡ ለዲዮጥርስ ፡ ብፅዕት፡ እግዚአብሔር፡ ይምሐረነ፡ በጸሎታ፡ ለዓለመ፡ ዓለም፡ አሜን።

፲፫፡ በዚችም፡ ቀን፡ የብፅዕት፡ ዲዮጥርስ፡ መታሰ ቢያዋ ፡ ነው ፡ እግዚአብሔርም ፡ በጸሎቷ ፡ ይማረን፡ ለዘላለሙ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ ለዲዮጥርስ፡ እምገቢረ፡ ሕሩም፡ አበሳ። ዘአብደረት፡ መጥዎተ፡ ርእሳ። በምክረ፡ ዳንኤል፡ ነቢየ ሱሳ። ሶበ፡ ጸለየ፡ ብእሲ፡ በዊአ፡ መቅደሳ። ሐመረ፡ ሥጋሁ፡ አንጽሐት፡ ለፍትወት፡ እምርኵሳ።

፲፬፡ ወበዛቲ፡ ዕለት፡ ካዕበ፡ አዕረፈ፡ አብ፡ ክቡር፡ ወመስተጋድል፡ አባ፡ ማቴዎስ፡ ሊቀ፡ ምኔት፡ ዘእምርት፡ ዘደብረ፡ እስዋን።

፲፭፡ ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ተሐፅነ ፡ እምንእሱ ፡ በፈሪሀ፡ እግዚአብሔር። ወመንኰሰ፡ ውስተ፡ ፩ደብር፡ እምአድባራት፡ ወኮነ፡ መስተጋድለ፡ በጾም፡ ወበጸሎት፡ ወሐነፀ፡ ሎቱ፡ ማሕደረ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ ወይትጌበር ፡ በእደዊሁ ፡ መርበብተ፡ ወይመጽእዎ፡ ሄጦ፡ ለነዳያን፡ በከመ ፡ ዜነዉ ፡ ገድሎ ፡ ወግብሮ ፡ ወተአ ምሪሁ፡ አርድእቱ፡ አባ፡ ሰራብዮን፡ ወአባ፡ ኀድራ።

፲፬፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ ለታወቀች ፡ እስዋን ፡ ለተባለች፡ ገዳም ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ የሆነ ፡ የሚጋደል፡ ቅዱስ፡ አባት፡ አባ፡ ማቴዎስ፡ አረፈ።

፲፭፡ ይህም፡ ቅዱስ፡ ከታናሽነቱ፡ ጀምሮ፡ በፈሪሀ፡ እግዚአብሔር፡ ጸንቶ፡ ያደገ፡ ነው፡ ከገዳማ ትም፡ በአንዱ፡ መንኵሶ፡ በጾም፡ በጸሎት፡ ተወስኖ፡ የሚጋደል፡ ሆነ፡ በገዳሙም፡ ውስጥ፡ ለራሱ፡ መኖሪያ፡ ሠራ፡ ደቀ፡ መዛሙርቱ፡ አባ፡ ሰራብዮንና፡ አባ፡ ኅድራ፡ ሥራውን፡ ተጋ ድሎውንና ፡ ተአምራቱን ፡ እንደተናገሩ ፡ መረብንም፡ በመሥራት፡ ሽያጩን፡ ለድኆች፡ ይመጸውታል።

www.ethiopianorthodox.org

፲፮፡ ወእሙንቱ ፡ ዜነዉ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ አሐተ ፡ ዕለተ ፡ እንዘ ፡ ንነብር ፡ አፍአ ፡ አንቀጽ ፡ እማኅደሩ ፡ ሰማዕነ ፡ ቃለ ፡ በውሳጤ ፡ ማኅደር ፡ ከመ ፡ ዘይትናገር ፡ አሐዱ ፡ ምስለ ፡ ካልዑ ፡ ወሶበ ፡ ቦእነ ፡ አልቦ ፡ ዘረከብነ ፡ ዘእንበሌሁ ፡ ወንቤሎ፡ኦ፡አቡነ፡እስመ፡ሰማዕነ፡በአፍአ፡ ከመ ፡ ካልዕ ፡ ዘይትናገር ፡ ምስሌከ ፡ ወሶበ ፡ ቦእነ ፡ አልቦ ፡ ዘረከብነ ፡ ዘእንበሌከ ። ወይቤለነ፡ በብዙኅ ፡ ትሕትና ፡ ኦ ፡ ደቂቅየ ፡ አንሰ ፡ ተዘኪርየ ፡ ብዝኅ ፡ ኃጣውእየ ፡ ተዛዋዕኩ ፡ ምስለ ፡ ርእስየ ፡ ወአዘከርክዋ ፡ ለነፍስየ ፡ ኵነኔያተ ፡ ወፃዕረ ፡ ሞትሂ ፡ እንተ ፡ ትረክበኒ ፡ ወይቤ ፡ አሌ ፡ ሎቱ ፡ ለማቴዎስ ፡ ነዳይ ፡ እስመ ፡ የዓርቅዎ ፡ እምላዕሌሁ ፡ አልባሰ፡ ወያቀውምዎ ፡ ቅድመ ፡ መንበሩ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ ማዕከለ ፡ ጉባኤ ፡ መላእክት ፡ ወማኅበረ፡ ጻድቃን ፡ ወሰማዕት ፡ እለ ፡ ይለብሱ፡ ንጽሐ ፡ ወቅድስና ፡ ከመ ፡ ልብስ፡ ወከመዝ ፡ መዓዶሙ ፡ ለደቂቁ ፡ ኵነኔ፡ ዘኃጥአን፡ወዕሴት፡ዘጻድቃን።

፲፯፡ወኮነ፡ቅዱስ፡ማቴዎስ፡ይገብር፡ጸሎተ፡ወተጋድሎተ ፡ ወተቀንዮተ ፡ በውስተ፡ ምኔት ፡ ዘሐነፀ ፡ ወቀደሰ ፡ በስመ ፡ አቡነ ፡ ጳኵሚስ ፡ ወምኔቱሂ ፡ ንእስት ፡ ዘእምርት ፡ ደብረ ፡ በቀልት።

፲፰፡ ወኮኑ ፡ ሠይጣናት ፡ መናፍስት ፡ ርኵሳን ፡ ያፈርህዎ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ እንዘ ፡ ይሬእዮሙ፡ገጸ፡በገጽ፡ወእሙንቱ፡ይረውፁ፡ ቅድሜሁ፡ወይተልውዎ፡በድኅሬሁ፡ውስተ፡ ኵሉ ፡ መካን ፡ በዘዘኢአሁ ፡ አርአያ ፡ ፍሉጥ ፡ ውእቱሰ ፡ ኢይፈርህ ፡ እምኔሆሙ ፡ ሶበ ፡ ይሰፍሕ ፡ እደዊሁ ፡ ወየአትብ ፡ በትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ውእተ ፡ጊዜ ፡ ይዘረዉ ፡ አጋንንት ፡ ከመ፡ጢስ፡ዘቅድመ፡ገጸ፡ነፋስ።

፲፱፡ወአሐተ፡ዕለተ፡አዘዞ፡ለረድኡ፡ሰራብዮን፡ ከመ ፡ ይንሣእ ፡ እምደብር ፡ቀሡተ ፡ ማይ ፡ ወንስቴተ ፡ ኅብስተ ፡ ወይሖር ፡ ኀበ ፡ በዓቱ ዘሀለወት ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ ከመ ፡ ይጽንሖ ፡ በህየ ፡ እስከ ፡ ይመጽእ ፡ ጌሠመ ። ወበጺሖ ፡ ሰራብዮን፡ውስተ፡በዓት፡ሶበ፡አርኃወ፡ርእየ፡ ፪ተ ፡ አራዊተ ፡ ዐበይተ ፡ እንዘ ፡ ስኩባን ፡ ውሳጤ ፡ በዓት፡ ወፈሪሆ ፡ ዐጸወ ፡ ኆኅተ ወዐርገ፡መልዕልተ፡ኰኵሕ።

፲፮፡ እነርሱም ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ፡ በአንዲት ፡ ዕለት ፡ ከማደሪያው ፡ በውጭ ፡ ተቀምጠን፡ሳለ፡በማደሪያው፡ውስጥ፡አንዱ፡ ከሌላው፡ጋር፡እንደሚነጋገር፡ሁኖ፡ቃልን፡ ሰማን ፡ በገባንም ፡ ጊዜ ፡ ከእርሱ ፡ በቀር ፡ ያገኘነው፡የለም ። አባታችን ፡ ሆይ ፡ በውጭ፡ ሳለን ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ ሰው ፡ እንደሚነጋገር ፡ ድምፅ፡ሰምተን፡ነበር፡በገባን፡ጊዜ፡ከአንተ፡ በቀር ፡ ያገኘነው ፡ የለም ፡ አልነው ። በብዙ ፡ ትሕትና፡እንዲህ፡አለን፡ልጆቼ፡ሆይ፡የምት ጠብቀኝን ፡ የሞት ፡ ፃዕርና ፡ ሥቃዮችን ፡ ለነፍሴ ፡ በማሳሰብ ፡ የኃጢአቴን ፡ ብዛት ፡ አስቤ ፡ ከራሴ ፡ ጋር ፡ ተነጋገርኩ ። ለድኃ ፡ ማቴዎስ ፡ ወዮለት ፡ ንጽሕናን ፡ ቅድስናን ፡ በለበሱ ፡ የመላእክት ፡ የጻድቃንና ፡ የሰማዕታት ፡ ጉባኤ ፡ አንድነት ፡ በአለበት ፡ በልዑል፡ እግዚአብሔር፡ መንበር ፡ ፊት ፡ ራቁቱን፡ ያቆሙታልና ፡ እንዲህም ፡ አድርጎ፡ የኃጥአንን ፡ ሥቃይ ፡ የጻድቃንን ፡ መልካም፡ ዋጋ፡ለልጆቹ፡አስተማራቸው።

፲፯፡ቅዱስ፡ማቴዎስም፡በሠራት፡ገዳም፡ውስጥ፡ ጸሎትን ፡ ተጋድሎን ፡ አገልግሎትን ፡ በማድረግ ፡ ጸንቶ ፡ኖረ ፡ ገዳሙንም ፡ በአባ፡ ጳኵሚስ፡ስም፡አከበረ፡እርሷም፡የታወቀች፡ ሰሌን፡ያለባት፡ተራራ፡ናት።

፲፰፡ ርኵሳን ፡ የሆኑ ፡ ረቂቃን ፡ ሰይጣናትም ፡ በቀንና ፡ በሌሊት ፡ የሚያስፈራሩት ፡ ሆኑ ፡ በየዓይነቱ ፡ በተለያየ ፡ መልክ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ እያያቸው ፡ እነርሱ ፡ በፊቱ ፡ ይሮጣሉ ፡ በኋላውም ፡ ይከተሉታል ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ አይፈራቸውም ፡ እጁንም ፡ ዘርግቶ ፡ በመስቀል ፡ ምልክት፡ሲአማትብ፡በዚያን፡ጊዜ፡በነፋስ፡ ፊት፡እንዳለ፡ጢስ፡ይበተናሉ።

፲፱፡በአንዲትም፡ዕለት፡ጥቂት፡እንጀራና፡ውኃ፡ በመንቀል ፡ ከገዳም ፡ ውስጥ ፡ ይዞ ፡ በበረሀ ፡ ውስጥ ፡ ወደአለች ፡ ዋሻው ፡ እንዲሔድና ፡ እርሱ ፡ በማግሥቱ ፡ እስቲመጣ ፡ በዚያ ፡ እንዲ ጠብቀው ፡ ረወድኡን ፡ ሰራብዮንን ፡ አዘዘው ። ሰራብዮንም ፡ ወደ ፡ ዋሻው ፡ ሲደርስ ፡ ሁለት ፡ ታላላቅ ፡ አራዊት ፡ በውስጥ ፡ ተኝተው ፡ አገኘ፡ ፈርቶ ፡ በሩን ፡ ዘግቶ ፡ ከዐለት ፡ ቋጥኝ ፡ ላይ ፡ ወጣ።

፳፡ ወእምዝ ፡ መጽአ ፡ አባ ፡ ማቴዎስ ፡ እንዘ ፡ ያነብብ ፡ መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ ወሶበ ፡ ርእዮ ፡ ለረድኡ፡አክሞሰሰ፡ወይቤሎ፡ኦ፡ሰራብዮን፡ ለምንትኑ ፡ ኢቦእከ ፡ ውሳጤ ፡ በዓት ፡ እስከ ፡ እመጽእ ፡ አነ ፡ ኀቤከ ፡ ወይቤሎ ፡ ረድኡ ፡ ኦ ፡ አቡየ፡ረከብኩ፡፪ተ፡አራዊተ፡ዐቢያነ፡እንዘ፡ ይሰክቡ፡ወፈሪህየ፡ኢያሆሙ፡ኢቦእኩ።

፳፩፡ ወይቤሎ ፡ አረጋዊ ፡ ብፁዕ ፡ ወየዋህ ፡ ወንጹሐ፡ነፍስ፡እመነኒ፡ኦ፡ወልድየ፡እስመ፡ ናሁ ፡ ሊተ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ዓመት ፡ እነብር ፡ ምስሌሆሙ ፡ ወአነ ፡ ዘሐፀንክዎሙ ፡ ወዘንተኒ ፡ ኅብስተ፡ወማየ፡ዘአዘዝኩከ፡ከመ፡ታምጽእ፡ በእንቲአሆሙ፡ውእቱ።

፳፪፡ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ አርኀወ ፡ ኆኅተ ፡ መጽኡ ፡ እሉ፡ አራዊት ፡ ኀቤሁ ፡ ወለሐሱ ፡ እገሪሁ ፡ ለቅዱስ፡አባ፡ማቴዎስ፡ወኮኑ፡ሎቱ፡መስተባይጻነ ፡ በተጋንዮ ፡ ዐቢይ ፡ ወከዓወ ፡ ሎሙ ፡ ውእተ ፡ ማየ ፡ እምነ ፡ ቀሱት ፡ ወሰትዩ ፡ ወኅብስተኒ፡በልዑ፡ወእምዝ፡ወጽኡ፡ገዳመ።

፳፫፡ ወዝንቱ ፡ አባ ፡ ማቴዎስ ፡ ነበረ ፡ እንዘ ፡ ይገብር፡ ተአምረ ፡ እስከ ፡ መልአ ፡ስሙዓተ ፡ ዜናሁ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ መካን ፡ ወያመጽኡ ፡ ኀቤሁ፡ኵሎ፡ድውያነ፡ዘዘዚአሁ፡ደዌሆሙ፡ ወይፌውሶሙ ፡ በኃይለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንተ፡ኀደረት፡ላዕሌሁ።

፳፬፡ ወ፩ ፡ እምተአምሪሁ ፡ ወአሐተ ፡ ዕለተ ፡ አምጽኡ ፡ ኀቤሁ ፡ ብእሴ ፡ በሐመ ፡ ዘቦቱ ፡ ጋኔን፡ ወሶበ ፡ ነጸሮ ፡ ለቅዱስ ፡ ማቴዎስ ፡ ከልሐ፡ በዐቢይ ፡ ቃል ፡ ወነጽሐ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ለብእሲ ፡ ወጸለየ ፡ ቅዱስ ፡ ላዕለ ፡ ዘይት፡ ወአተቦ ፡ በትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ወቀብኦ ፡ ወሶቤሃ ፡ ድኅነ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ወገብአ ፡ ልቡ ፡ ወሰምዐ ፡ ወተናገረ ፡ ወሖረ ፡ ቤቶ፡በፍሥሐ።

፳፭፡ ወሶበ ፡ ይመጽኡ ፡ ሕዝባውያን ፡ ያቀርብ ፡ ሎሙ ፡ ማዕደ ፡ ወይፌንዎሙ ፡ በሰላም ፡ ወእሙንቱ ፡ ይወስዱ ፡ ንስቲተ ፡ ፍተ ፡ ለበረከት፡ውስተ፡አብያቲሆሙ፡ወሶበ፡ያነብርዎ፡ ዲበ ፡ ድውያን ፡ ወሶቤሃ ፡ ይትፌወሱ ፡ ወይሴ

፳፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አባ ፡ ማቴዎስ ፡ የዳዊትን ፡ መዝሙር ፡ እያነበበ ፡ መጣ ፡ ረድኡንም ፡ አይቶ፡ፈገግ፡ብሎ፡ሳቀ፡ሰራብዮን፡ሆይ፡እኔ፡ ወዳንተ፡እስከምመጣ፡ወደ፡ዋሻው፡ውስጥ፡ ለምን፡አልገባህም፡አለው።እርሱም፡ረድኡ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡ ሁለት ፡ ታላላቅ ፡ አውሬዎች ፡ ተኝተው፡ስለ፡አገኘሁ፡እነርሱን፡ፈርቼ፡አልገባሁም፡አለው።

፳፩፡ ንጽሐ ፡ ነፍስ ፡ ያለው ፡ የዋህ ፡ የሆነ ፡ የተመሰገነ ፡ አረጋዊም ፡ ልጄ ፡ እመነኝ ፡ እኔ ፡ ከእነርሱ፡ጋር፡ስኖር፡ዐሥራ፡ሁለት፡ዓመት፡ ሆነኝ፡ያሳደግኋቸውም፡እኔ፡ነኝ፡ይህንንም፡ እንጀራና ፡ ውኃ ፡ እንድታመጣ ፡ ያዘዝኩህ ፡ ለእነርሱ፡ነው፡አለው።

፳፪፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በሩን ፡ በከፈተ ፡ ጊዜ ፡ እነዚያ፡ አውሬዎች ፡ ወደርሱ ፡ መጥተው ፡ ቅዱስ፡አባ፡ማቴዎስን፡እግሮቹን፡ላሱ፡ባልንጀሮችም ፡ ሁነውት ፡ በታላቅ ፡ መለማመጥ ፡ ተገዙለት፡ያንንም፡ውኃ፡ከገንዳ፡ላይ፡አፍስሶለቸው ፡ ጠጡ ፡ እንጀራውንም ፡ በሉ ፡ ከዚያም፡በኋላ፡ወደ፡ዱር፡ሔዱ።

፳፫፡ ይህም ፡ አባ ፡ ማቴዎስ ፡ የዜናው ፡ መሰማት ፡ በቦታው ፡ ሁሉ ፡ እስከመላ ፡ ድረስ ፡ ተአምራትን፡እያደረገ፡ኖረ፡በየዓይነቱ፡በሆነ፡ደዌ፡ የተያዙትን፡ያመጡለታል።እርሱም፡በላዩ፡ በአደረች፡በእግዚአብሔር፡ኃይል፡ይፈውሳቸዋል።

፳፬፡ ከተአምራቶቹም ፡ አንዱ ፡ በአንዲት ፡ ቀን ፡ ጋኔን ፡ ያደረበት ፡ ዲዳ ፡ ሰውን ፡ ወደርሱ ፡ አመጡ፡ቅዱስ፡ማቴዎስንም፡በአየው፡ጊዜ፡ በታላቅ፡ድምፅ፡ጩኾ፡ሰውዬውን፡ከምድር፡ ላይ ፡ ጣለው ፡ ቅዱሱም ፡ በዘይት ፡ ላይ ፡ ጸለየ ፡ በመስቀል ፡ ምልክትም ፡ አማትቦ ፡ ቀባው፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ድኖ ፡ አእምሮው ፡ ተመለሰ፡ የሚሰማና፡የሚናገርም፡ሆነ፡ደስ፡ብሎትም፡ ወደቤቱ፡ሔደ።

፳፭፡ ጨዋዎችም ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ማዕድ ፡ ያቀርብላቸውና ፡ በሰላም ፡ በፍቅር ፡ ያሰናብታቸዋል ፡እነርሱም ፡ ለበረከት ፡ እያሉ ፡ ጥቂት ፡ ቍራሽ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ይወስዳሉ ፡ በበሽተኞች ፡ ላይም ፡ በአደረጉት ፡ ጊዜ ፡ ወዲያውኑ ፡ ድነው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግ

www.ethiopianorthodox.org

ብሕዎ፡ ለእግዚአብሔር።

፳፮፡ ካልዕ ፡ ተአምር ፡ ወአሐተ ፡ ዕለተ ፡ አምጽኡ፡ ኀቤሁ፡ወለተ፡ሠናይተ፡ላሕይ፡ዘባቲ፡ጋኔን፡ ወብዙኀ ፡ ጊዜ ፡ ትሠጥጥ ፡አልባሲሃ፡ ወኢ ይክል ፡ መኑሂ ፡ ይቅረብ ፡ ኀቤሃ ፡ ወኮኑ ፡ አበዊሃ፡ ውስተ ፡ ዐቢይ ፡ ኀዘን ፡ ወቅዱስኒ ፡ አባ፡ ማቴዎስ ፡ ጸለየ፡ ላዕሌሃ ፡ ወአሕየዋ ፡ ቀቢዖ ፡ ዘይተ ፡ በስሙ ፡ ለእግዚ እነ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት።

፳፯፡ ሣልስ ፡ ተአምር ፡ በአሐቲ ፡ ዕለት ፡ አም ጽኡ፡ኀቤሁ፡ብእሲተ፡ኃጥእተ፡ዘወድቀት፡ ውስተ ፡ ኃጢአት ፡ ዐባይ ፡ ወእኪት ፡ ጥቀ ፡ ወይእቲ ፡ ፅንስት ፡ ወበጽሐ ፡ ዕለተ ፡ ወሊ ዶታ፡ ወትትመነደብ ፡ በሕማመ ፡ ወሊድ ፡ መዓልተ፡ወሌሊተ፡ወይቤላ፡አባ፡ማቴዎስ፡ ኦ ፡ ወለትየ ፡ ተአመኒ ፡ ኃጢአተኪ ፡ ወኢተ ሐስዊ፡በቅድመ፡ እግዚአብሔር።ወትቤሎ፡ አንሰ፡ነበርኩ፡እንዘ፡እሰክብ፡ምስለ፡፪ቱ፡ አኃው ፡ እንበለ ፡ ያእምሩ ፡ እሙንቱ ፡ ወሶበ ፡ ፀነስኩ፡አውጻእኩ፡በሥራይ፡ሕፃነ፡ወወሀ ብክዎሙ፡ለከለባት፡ወሰሚዖ፡አባ፡ማቴዎስ፡ ጸለየ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ወሶቤሃ ፡ አብ ቀወት ፡ ምድር ፡ አፉሃ ፡ ወውሕጠታ ፡ ከመ ፡ ትኩን፡አርአያ፡ለካልዓን።

፳፰፡ ወብዙኀ፡ተአምሪሁ፡ለዝንቱ፡አብ፡ባሕቱ፡ ኢየኀልቅ፡በነጊር፡ወአሐተ፡ዕለተ፡እንዘ፡ ያንሶሱ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ ሰሐበቶ ፡ ዝዕብ ፡ ውስተ ፡ ውሳጤ ፡ ገዳም ፡ እጊዛ ፡ አልባ ሲሁ፡በአስናኒሃ፡ወአርአየቶ፡ዕጐሊሃ፡እለ፡ ወድቁ፡ ውስተ ፡ ንቅዓተ ፡ ዕብን ፡ ወሶበ ፡ አውጽአ ፡ ላቲ ፡ ሰገደት ፡ ሎቱ ፡ ወለሐሰት ፡ እገሪሁ።

፳፱፡ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ቀርበ ፡ ጊዜ ፡ ዕረፍቱ ፡ ርእየ፡ራእየ፡አመ፡፫ ለታኅሣሥ፡ከመ፡ዘይ ጼውዖ፡ውስተ፡ከብካብ፡ዘመርዓ፡አበው፡ ቅዱሳን፡ አባ፡ እንጦንስ፡ ወአባ፡ መቃርስ፡

ኑታል።

፳፮፡ ሁለተኛ፡ተአምር፡በአንዲትም፡ዕለት፡ደም፡ ግባቷ ፡ ያማረ ፡ ጋኔን ፡ ያደረባትን ፡ ብላቴና ፡ ወደርሱ ፡ አመጡ ፡ እርሷ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ፡ ልብ ሷን ፡ ትቀዳለች ፡ ወደርሷም ፡ መቅረብ ፡ የሚ ችል ፡ የለም ፡ ወላጆቿም ፡ በታላቅ ፡ ኀዘን ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ ፡ ቅዱስ ፡ አባ፡ ማቴዎስም ፡ በላይዋ ፡ ጸለየና ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ በጌታ ችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ስም ፡ ዘይቱን ፡ ቀብቶ፡አዳናት።

፳፯፡ ሦስተኛ ፡ ተአምር፡በአንዲት፡ዕለት፡እጅግ፡ በከፋችና ፡ ታላቅ ፡ በሆነች ፡ ኃጢአት ፡ ላይ ፡ የወደቀች ፡ ኃጢአተኛ ፡ ሴት ፡ ወደርሱ ፡ አመጡ ፡ እርሷ ፡ ፀንሳ ፡ የመውለጃዋ ፡ ጊዜ ፡ የደረሰ ፡ ነው ፡ በቀንና ፡ በሌሊትም ፡ በምጥ ፡ ሕማም ፡ ትሠቃይ ፡ ነበር ፡ አባ ፡ ማቴዎስም ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ኃጢአትሽን ፡ እመኚ፡ በእግዚአ ብሔር ፡ፊት ፡ አትዋሺ ፡ አላት ። እርሷም ፡ እንዲህ ፡ አለችው ፡ እኔ ፡ ከሁለት ፡ ወንድማ ማቾች ፡ ጋር ፡ እነርሱ ፡ ሳያውቁ ፡ ሳመነዝር ፡ ኖርኩ ፡ በፀነስኩም ፡ ጊዜ ፡ ሕፃኑን ፡ በመርዝ ፡ አውጥቼ ፡ ለውሾች ፡ ሰጠሁት ፡ አባ ፡ ማቴ ዎስም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር፡ ጸለየ፡በዚያንም፡ጊዜ፡ለሌሎች፡መቀጣጫ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ምድር ፡ አፏን፡ ከፍታ ፡ ዋጠቻት።

፳፰፡ የዚህም፡አባት፡ተአምራቶቹ፡ብዙ፡ናቸው፡ ተነግሮ ፡ አያልቅም ፡ በአንዲትም ፡ ቀን ፡ በበረሀ ፡ ውስጥ ፡ ሲጓዝ ፡ ጅብ ፡ ልብሶቹን ፡ በጥርሶቿ፡ይዛ፡ሳበችውና፡በሠንጣቃ፡ገደል፡ ውስጥ፡የወደቁ፡ልጆቿን፡አሳየችው፡ በአወ ጣላትም ፡ ጊዜ ፡ ሰገደችለት ፡ እግሮቹንም ፡ ላሰች።

፳፱፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ዕረፍቱ ፡ ሲቀርብ ፡ በታኅ ሣሥ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ሠርግ ፡ እንደሚ ጠራው፡ራእይን፡አየ፡ይኸውም፡የቅዱሳን፡ አባቶች ፡ የአባ ፡ እንጦንስ ፡ የአባ ፡ መቃርስ ፡ የአባ ፡ ጳኵሚስ ፡ የአባ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የአባ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወአባ፡ ጳኵሚስ፡ ወአባ፡ ቴዎድሮስ፡ ወአባ፡ ሙሴ፡ ጸሊም፡ ወአባ፡ ሲኖዳ፡ ወይቤልዎ፡ ሠናይ፡ ምጽአትከ፡ ኀቤነ፡ ከመ፡ ትኅድር፡ ምስሌነ፡ ውስተ፡ ኢየሩሳሌም፡ ሰማያዊት። ወአብጽሕዎ፡ ኀበ፡ ኆኅተ፡ ጽርሕ፡ ዐቢይ፡ ዘቦቱ፡ ገነታት፡ ወመናብርት፡ ወሰምዐ፡ ቃለ፡ ዘይብል፡ አርኅዉ፡ ኆኃተ፡ ጽርሕ፡ ከመ፡ ይባእ፡ ማቴዎስ፡ ወእምዝ፡ አዕረፈ፡ አመ፡ ፲ወ፬ ለዝ፡ ወርኀ፡ ወተመጠወ፡ ሠለስተ፡ አክሊላተ።

፴፡ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፡ ኪያነኒ፡ ይምሐረነ፡ በጸሎቱ፡ ለዝንቱ፡ ጻድቅ፡ ወበረከቱ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ሙሴ፡ ጸሊም፡ የአባ፡ ሲኖዳ፡ የአንድነት፡ ተድላ፡ ደስታ፡ ወዳለበት፡ ነው። እነርሱም፡ በኢየሩሳሌም፡ ሰማያዊት፡ ከእኛ፡ ጋር፡ ትኖር፡ ዘንድ፡ ወደእኛ፡ መምጣትህ፡ መልካም፡ ነው፡ አሉት፡ ብዙ፡ አትክልቶችና ዙፋኖች፡ ወዳሉት፡ ታላቅ፡ አዳራሽም፡ ደጅ፡ አደረሱት፡ ማቴዎስ፡ ይገባ፡ ዘንድ፡ የአዳራሹን፡ ደጆች፡ ክፈቱ፡ የሚልንም፡ ቃል፡ ሰማ፡ ከዚህም፡ በኋላ፡ በዚሁ፡ ወር፡ በሰባት፡ አረፈ፡ሦስት፡አክሊላትንም፡ተቀበለ።

፴፡ ለእግዚአብሔርም፡ ምስጋና፡ ይሁን፡ እኛንም፡ በዚህ፡ ጻድቅ፡ ጸሎት፡ ይማረን፡ በረከቱም፡ ከእኛ፡ ጋር፡ ትኑር፡ ለዘላለሙ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ ዕብል፡ ለዘሱታፌሁ፡ አሐዱ። ምስለ፡ አብ፡ ወምስለ፡ ወልዱ። ማቴዎስ፡ ነዳይ፡ ለዓለመ፡ ፍትወት፡ወእመፍቅዱ።እምብዝኀ፡ኂሩቱ፡ሶበ፡ኪያሁ፡ለመዱ።አራዊተ፡ገዳም፡ያበልዕ፡እኂዞ፡በእዱ።

፴፩፡ ወበዛቲ፡ ዕለት፡ ኮነ፡ ተዝካረ፡ ስብከቱ፡ ለመድኃኒነ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ሎቱ፡ ስብሐት፡ በአፈ፡ ነቢያት፡ ቅዱሳን፡ ዘከመ፡ ይትወለድ እማርያም፡ እምቅድስት፡ ድንግል፡ እግዝእትነ፡ ማህሉ፡ ወምሕረቱ፡ የሀሉ፡ ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፴፩፡ በዚችም፡ ዕለት፡ ከእመቤታችን፡ ከቅድስት፡ ድንግል፡ ማርያም፡ ክብር፡ ይገባውና፡ ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ከሥጋዋ፡ሥጋ፡ ከነፍሷ፡ ነፍስ፡ ነሥቶ፡ እንደሚወለድ፡ በከበሩ፡ ነቢያት፡ አፍ፡ ለመሰበኩ፡ መታሰቢያ፡ ሆነ፡ ይቅርታውና፡ ቸርነቱ፡ ከእኛ፡ ጋር፡ ለዘላለሙ፡ ይኑር፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ ለስብከትከ፡ መዓዛ፡ ርኄ፡ ጽጌረዳ። በአፈ፡ ነቢያት፡ ቅዱሳን፡ በቤተ፡ ልሔም፡ ዘይሁዳ። ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ከመ፡ ታድኅነነ፡ እሞተ፡ ዕዳ። ዘኀረይከ፡ እግዚኦ፡ በጥበብከ፡ እንግዳ። ለድንግል፡ ማርያም፡ ከመ፡ ትኩን፡ ወልዳ።

ሰላም፡ እብል፡ መቢዛዌ፡ አምላከ። ምሥጢረ፡ ትሥጉቱ፡ ይንብቡ፡ ከናፍረ፡ ነቢያት፡ ዘሆከ። በእንቲአሁ፡ ዳዊት፡ እንዘ፡ ያቀድም፡ ሰቢከ። ቦ፡ ኀበ፡ ይቤ፡ ፈኑ፡ እዴከ። ወቦ፡ ኀበ፡ ይቤ፡ አንሥእ፡ ኃይለከ።

* * *

፩፡ በስመ፡ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ፩ አምላክ፡ አመ፡ ፰ ለታኅሣሥ፡ በዛቲ፡ ዕለት፡ አዕረፈ፡ አብ፡ ቅዱስ፡ አባ፡ ያሮክላ፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ ዘሀገረ፡ እስክንድርያ፡ ወውእቱ፡ እምኍልቆሙ፡ ለአበው፡ ሊቃነ፡ ጳጳሳት፡ ፲ወ፫ቱ።

* * *

፩፡ አንድ፡ አምላክ፡ በሚሆን፡ በአብ፡ በወልድ፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ስም፡ ታኅሣሥ፡ ስምንት፡ በዚች፡ ቀን፡ የእስክንድርያ፡ አገር፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ ቅዱስ፡ አባት፡ አባ፡ ያሮክላ፡ አረፈ፡ እርሱም፡ ለአባቶች፡ ሊቃነ፡ ጳጳሳት፡ ዐሥራ፡ ሦስተኛ፡ ቊጥር፡ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

ወስሙ፡ለውእቱ፡መስፍን፡ዲዮስቆሮስ፡ወው
እቱ ፡ ገብረ ፡ ለወለቱ ፡ በርባራ ፡ ማሕፈደ ፡
ጽኑዐ፡ ከመ ፡ ኢይርአያ ፡ መኑሂ ። ወእምዝ ፡
ዓዲ፡ አዘዘ ፡ ይግበሩ ፡ ማኅፈደ ፡ ቤተ ፡ ብለኔ ፡
ወይግበሩ ፡ ውስቴቱ ፡ ፪ተ ፡ መሳክወ ፡ እለ ፡
ይትረኃዋ ፡ ወሶበ ፡ ርእየት ፡ ቅድስት ፡ በርባራ ፡
፪ተ ፡ መሳክወ ፡ አዘዘቶሙ ፡ ለነደቅት ፡ ከመ ፡
ይግበሩ፡ ሣልሳየ ፡ መስኮተ ፡ ወእምዝ ፡ አግ
በረት ፡ ላዕለ ፡ ምሕፃበ ፡ ማይ ፡ ትእምርተ ፡
መስቀል ፡ ማሕየዊ ፡ ዘእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክር
ስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት።

፲፡ ወሶበ ፡ ቦአ ፡ አቡሃ ፡ ውስተ ፡ ውእቱ ፡ ማኅፈድ ፡
ርእየ ፡ ዘንተ ፡ ዘአግበረት ፡ ወለቱ ፡ ወተሰአለ ፡
በእንተዝ ፡ ወይቤልዎ ፡ ነደቅት ፡ እስመ ፡ ወለ
ትከ ፡ በርባራ ፡ አዘዘተነ ፡ ንግበር ፡ ዘንተ ፡ ወለይ
እቲኒ፡ ጸውዓ ፡ ወይቤላ ፡ ለምንት ፡ ገበርኪ ፡
ከመዝ ፡ ወትቤሎ ፡ አእምር ፡ ወለቡ ፡ አ ፡ አቡየ ፡
እስመ ፡ በሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ይትፌጸም ፡ ኵሉ ፡
ግብር ፡ በእንተዝ ፡ አግበርኩ ፡ ሣልሲተ ፡
መስኮተ። ወዘንተኒ ፡ መስቀለ ፡ በአምሳለ ፡
ስቅለቱ ፡ ለመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ዘቦቱ ፡ ኮነ ፡ መድኃኒተ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፡ ወአን
ተኒ ፡ አ ፡ አቡየ፡ ተመየጥ ፡ እምስሕተትከ ፡ ወአ
ምልኮ ፡ ለአምላክ ፡ ዘፈጠረከ።
፲፩፡ ወሰሚዖ ፡ አቡሃ ፡ ዘንተ ፡ እምኔሃ ፡ ተምዐ ፡ ጥቀ ፡
ወመልሐ ፡ ሰይፎ ፡ ወሮፀ ፡ በድኅሬሃ ፡ ወጐ
የት ፡ ወዘኮነት ፡ በቅድሜሃ ፡ ኰኵሕ ፡ ተሠ
ጥቀት ፡ ወቦአት ፡ ውስቴታ ፡ ወከደነታ።
፲፪፡ ወእምድኅረዝ ፡ ተመይጠት ፡ ኀበ ፡ አቡሃ ፡
ውእቱኒ ፡ መጠዋ ፡ ለካልዕ ፡ መኰንን ፡ ከመ ፡
ይኰንና ፡ ወኰነና ፡ ኵነኔ ፡ ዐቢየ ፡ ወሀለወት ፡
በህየ ፡ ብእሲት ፡ እንተ ፡ ስማ ፡ ዮልያና ፡ ወር
እየታ ፡ ለቅድስት ፡ በርባራ ። ወኮነት ፡ ዘታጸ
ንዓ ፡ ወትናዝዛ ፡ ወእግዚእነሂ ፡ ኢየሱስ ፡ ክር
ስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ አስተርአያ ፡ ለቅድ
ስት ፡ በርባራ ፡ ወናዘዛ።

፲፫፡ ወእምድኅረዝ ፡ አዘዘ ፡ አቡሃ ፡ ይምትሩ ፡ ርእሳ ፡
በሰይፍ ፡ ወለካልዕታ ፡ ዮልያና ፡ ወመተሩ ፡
አርእስቲሆን ፡ በሰይፍ ፡ ወነሥአ፡ አክሊለ ፡
ስምዕ ፡ ወሶቤሃ ፡ ወረደ ፡ እሳት ፡ እምሰማይ ፡
ወአውዓዮሙ ፡ ለአቡሃ ፡ ወለካልኡ ፡ መርት
ያኖስ ፡ መኰንን ። ውእቱኒ ፡ ምሕፃብ ፡
ዘገብረቶ ፡ በትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ውስተ ፡

ልጁ ፡ ናት ፡ ስሙም ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ነው ፡ እር
ሱም፡ ለልጁ ፡ ለበርባራ ፡ ማንም ፡ እንዳያያት ፡
ታላቅ ፡ ጽኑ ፡ የሆነ ፡ ሕንፃ ፡ አሠራ ፡ ከዚህም ፡
ዳግመኛ ፡ መታጠቢያ ፡ የውሽባ ፡ ቤት ፡
በግንብ፡ ሠራ ፡ የሚከፈቱ ፡ ሁለት ፡ መስኮቶ
ችንም ፡ በውስጡ ፡ እንዲሠሩ ፡ አዘዘ ። ቅድስት ፡
በርባራም ፡ ሁለቱን ፡ መስኮቶች ፡ በአየች ፡
ጊዜ፡ ሦስተኛ ፡ መስኮትን ፡ እንዲሠሩ ፡ ሐናፂ
ዎችን ፡ አዘዘቻቸው ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ክብር ፡
ይግባውና ፡ የጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡
አዳኝ፡ የሆነ ፡ የመስቀሉን ፡ ምልክት ፡ በውኃ ፡
መታጠቢያው ፡ ላይ ፡ አሠራች።
፲፡ አባቷም ፡ ወደዚህ ፡ ሕንፃ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡
ልጁ ፡ ያሠራችውን ፡ አይቶ ፡ አናፂዎችን ፡
ጠየቀ ፡ እነርሱም ፡ ይህን ፡ እንድንሠራ ፡
ልጅህ ፡ አዘዘችን ፡ አሉት ፡ እርሷንም ፡ ጠርቶ ፡
ለምን ፡ እንዲህ ፡ አደረግሽ ፡ አላት ። እርሷም ፡
አባቴ ፡ ሆይ ፡ አስተውል፡ ልዩ ፡ ሦስት ፡ በሆነ ፡
በሥላሴ ፡ ስም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ይፈጸማልና ፡ ስለ
ዚህ ፡ ሦስተኛ ፡ መስኮት ፡ አሠራሁ ፡ ይህም ፡
መስቀል ፡ ዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ በእርሱ ፡ በዳነበት ፡
በመድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መስ
ቀል ፡ አምሳል ፡ ነው ፡ አንተም ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡
ከስሕተትህ ፡ ተመልሰህ ፡ የፈጠረህን ፡
አምላክ፡ አምልከው ፡ አለችው።
፲፩፡ አባቷም ፡ ከእርሷ ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ሰይፉን
መዝዞ ፡ በኋላዋ ፡ ሮጠ ፡ እርሷም ፡ ሸሸች ፡ በፊ
ቷም ፡ የነበረች ፡ ዐለት ፡ ተሠንጥቃ ፡ በው
ስጧ ፡ ገብታ ፡ ሠወረቻት።
፲፪፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አባቷ ፡ ተመለሰች ፡
እርሱም ፡ እንዲአሠቃያት ፡ ለሌላ ፡ መኰንን ፡
አሳልፎ ፡ ሰጣት ፡ እርሱም ፡ ታላቅ ፡ ሥቃይን ፡
አሠቃያት ፡ በዚያም ፡ ዮልያና ፡ የምትባል ፡
ሴት ፡ ነበረች ፡ ቅድስት ፡ በርባራንም፡ አየቻ
ትና ፡ የምታጽናናትና ፡ የምታረጋጋት ፡ ሆነች፡
ክብር ፡ ይግባውና ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስ
ቶስም ፡ ለቅድስት ፡ በርባራ ፡ ተገለጸላትና፡
አረጋጋት።
፲፫፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አባቷ ፡ በሰይፍ ፡ ራሷን ፡ እንዲ
ቆርጡ ፡ የባልንጀራዋ ፡ የዮልያናንም ፡ ራስ ፡
እንዲቆርጡ ፡ አዘዘና ፡ ቆረጧቸው፡ የሰማዕ
ትነት ፡ አክሊልንም ፡ ተቀበሉ ። በዚያንም ፡
ጊዜ ፡ ከሰማይ ፡ እሳት ፡ ወርዶ ፡ አባቷንና ፡
ጓደኛው ፡ የሆነ ፡ መኰንን ፡ መርትያኖስን ፡
አቃጠላቸው ፡ ያም ፡ በውሽባ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡
በመስቀል ፡ ምልክት ፡ ያሠራችው ፡

www.ethiopianorthodox.org

ቤተ፡ብለኔ፡ኮነ፡ውስቴቱ፡ዐቢይ፡ፈውስ፡ ለኵሉ፡ዘይደዊ፡ሶበ፡ይትሐፀብ፡እምኔሁ።

፲፬፡ ወእምዝ ፡ ነሥኡ ፡ ሥጋሆን ፡ ለቅዱሳት ፡ ሰማዕት፡ወአንበርዎን፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስ ቲያን፡ዘአፍአ፡ሀገር፡እንተ፡ስማ፡ገላልያ፡ ወሥጋሆሙ ፡ ለቅዱሳት ፡ ሰማዕት ፡ ሀሎ ፡ እስከ፡ይእዜ፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያኖሙ፡ ለቅዱሳን፡አቡቂር፡ወዮሐንስ፡ሰማዕታት፡ በሀገረ፡ምስር።

፲፭፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ፡በጸሎቶን፡ለቅዱሳት፡ሰማዕት፡ ወበረከቶን ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም፡አሜን።

መታጠቢያ ፡ ለታመመ ፡ ሁሉ ፡ ከእርሱ ፡ በታጠበ፡ጊዜ፡የሚያድን፡በውስጡ፡ታላቅ፡ ፈውስ፡ያለበት፡ሆነ።

፲፬፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የቅዱሳት ፡ ሰማዕታትን ፡ ሥጋቸውን ፡ ወስደው ፡ ከከተማ ፡ ውጭ ፡ ባለች፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስሟ ፡ ገላልያ ፡ በሚባል ፡ ቦታ ፡ አኖሩአቸው ፡ ይህ ፡ ሥጋቸውም ፡ በቅዱሳን ፡ ሰማዕታት ፡ በአቡ ቂርና፡በዮሐንስ፡በምስር፡አገር፡በአለ፡ቤተ፡ ክርስቲያናቸው፡እስከ፡ዛሬ፡አለ።

፲፭፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም፡ በቅዱሳት ፡ ሰማዕታት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን፡በረከታቸውም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለበርባራ፡እንተ፡አግሀደት፡ሃይማኖታ።እንዘ፡ታርኢ፡ሥላሴ፡በመስኮተ፡ቤታ።ኢያፍርሃ፡ መጥባሕት፡ወሞሠርተ፡ኀፂን፡ኢያሕመመታ። ወሰላም፡ካዕበ፡ለዮልያና፡ካልዕታ።እንተ፡ሰቀልዋ፡ በክልኤ፡አጥባታ።

፲፮፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካራ ፡ ለብፅዕት ፡ እንባ ምሬና ፡ ወበረከታ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፲፮፡በዚችም፡ዕለት፡የብፅዕት፡እንባምሬና፡መታ ሰቢያዋ፡ነው፡በረከቷም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡እብል፡ለዘአጥብዓት፡ሐሊና።በውስተ፡ገዳም፡ታልሕቅ፡እንተ፡ኢኮነ፡ሕፃና።ወእንዘ፡ ይመስልዋ፡ብእሴ፡እለ፡መነንዋ፡በኢልቡና። አንከርዋ፡ማኅበራኒሃ፡ለብፅዕት እንባምሬና።ከመ፡ ብእሲት፡ይእቲ፡ሶበ፡ርእዩ፡በድና።

፲፯፡ ወበዛቲ፡ዕለት፡አዕረፈ፡አብ፡ቅዱስ፡አባ፡ ሳሙኤል ፡ ዘደብረ ፡ ቀልሞን ፡ ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ እምሀገረ ፡ ደክሉባ ፡ እምብሔረ ፡ መጺል፡እምደቡበ፡ግብጽ።

፲፰፡ አበዊሁኒ፡ቅዱሳን፡ወንጹሐን፡ወኢኮነ፡ ሎሙ ፡ ወልድ ፡ ዘእንበሌሁ ፡ ወአቡሁኒ ፡ ቀሲስ፡ውእቱ፡ወርእየ፡ራእየ፡በሌሊት፡ ከመ፡ብእሲ፡ዘገጹ፡ብሩህ፡ወውእቱ፡እንዘ፡ ይብሎ፡ሀለዎ፡ለዝንቱ፡ወልድከ፡ከመ፡ ይኩን ፡ ምእመነ ፡ ወመምህረ ፡ ኄረ ፡ ለብዙኃን፡ሰብእ፡ወይከውን፡ኅሩየ፡በኀበ፡ እግዚአብሔር፡በኵሉ፡መዋዕሊሁ።

፲፱፡ ወኮነ፡አባ፡ሳሙኤል፡ንጹሐ፡እምንእሱ፡ ከመ፡ሳሙኤል፡ነቢይ፡ወኵሎ፡አሚረ፡

፲፯፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ ቅዱስ ፡ አባት ፡ የደብረ ፡ ቀልሞን ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ፡ አረፈ ፡ ይህም ፡ ቅዱስ ፡ ለግብጽ ፡ ደቡብ ፡ ከሆነ ፡ መጺል ፡ ከሚባል፡አገር፡ደክሉባ፡ከሚባል፡መንደር፡ ነው።

፲፰፡ወላጆቹም፡ቅዱሳንና፡ንጹሐን፡ናቸው፡ያለ፡ እርሱም፡ልጅ፡አልነበራቸውም፡አባቱም፡ ቄስ፡ነበር።በሌሊት፡በራእይ፡ፊቱ፡ብሩህ፡ የሆነ፡ሰው፡አየ።ይህ፡ልጅህ፡ለብዙ፡ሰዎች፡ የታመነ ፡ ቸር ፡ መምህር ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ አለው፡ በዘመኑም ፡ ሁሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተመረጠ፡ይሆናል፡አለው።

፲፱፡ አባ ፡ ሳሙኤልም ፡ ከታናሽነቱ ፡ ጀምሮ ፡ እንደ፡ ነቢዩ፡ሳሙኤል፡ንጹሕ፡ነው፡ሁል፡

www.ethiopianorthodox.org

ይሔሊ፡ከመ፡ይልበስ፡አልባሰ፡ምንኵስና፡ ወበአሐቲ ፡ ዕለት ፡ ረከበ ፡ ምክንያተ ፡ ወወጽአ፡ እምኀበ ፡ አቡሁ ፡ ከመ ፡ ይሑር ፡ ኀበ፡ገዳመ፡አስቄጥስ፡ወባሕቱ፡ኢየአምር፡ ፍኖቶ ፡ ወኮነ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተመሰለ ፡ በአምሳለ ፡ መነኰስ ፡ ወሖረ ፡ ምስሌሁ፡እንዘ፡ይመርሖ፡ወሶበ፡አብጽሖ፡ ወመጠዎ ፡ ለአሐዱ ፡ መነኰስ ፡ አረጋዊ ፡ ዘስሙ ፡ አጋቶን፡ ዘይነብር ፡ ውስተ ፡ በዓት ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ጻድቅ ፡ ፈድፋደ ፡ ወነገሮ ፡ ውእቱ ፡ መልአክ ፡ ለቅዱስ ፡ አባ ፡ አጋቶን ፡ በእንተ ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ተወከፎ፡ለሳሙኤል፡በፍሥሓ፡ወአልብሶ፡ አልባሰ ፡ ምንኵስና፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይከውነከ ፡ ወልደ፡ ዘበአማን ፡ ወያጸንዕ ፡ ርሥአነከ ፡ ወአንተ ፡ መሀሮ ፡ ኵሎ ፡ ሕገ ፡ ምንኵስና፡ወሶበ፡ይቤሎ፡ዘንተ፡መልአክ፡ ተሠወረ፡እምኔሁ።

፳፤ ወሶበ ፡ በጽሐ ፡ ሳሙኤል ፡ ተወክፎ ፡ አባ ፡ አጋቶን፡ በፍሥሓ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ሠናይ ፡ ምጽአትከ ፡ አ ፡ ሳሙኤል ፡ ገብረ ፡ እግዚአ ብሔር ፡እስመ ፡ ፈነወከ ፡ እግዚእ ፡ ኀቤየ ፡ በጊዜ፡ርሥአንየ፡ወበጊዜሃ፡አብኦ፡ውስተ፡ ቤተ፡ክርስቲያን፡ጸለየ፡ወባረከ፡ላዕለ፡ሠቀ፡ ጸጕር ፡ ወቆብዕ ፡ ወቅናት ፡ ወአስኬማ ፡ ወአልበሶ ፡ ኪያሆሙ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ አምላኮሙ ፡ ለአበውየ ፡ ቅዱሳን ፡ አባ ፡ እንጦ ንዮስ ፡ ወአባ ፡ መቃርዮስ ፡ የሀሉ ፡ ምስሌከ ፡ ወልድየ ፡ ሳሙኤል ፡ ወይኩንከ ፡ ረዳኤ ፡ በውስተ፡ኵሉ፡ምንዳቤከ።

፳፩፤ ወቅዱስሰ ፡ አባ ፡ አጋቶን ፡ መሀሮ ፡ ለአባ ፡ ሳሙኤል ፡ ትሕትና ፡ ወአርምሞ ፡ ወኮነ ፡ ይብል ፡ ኵሎ ፡ ጊዜ ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ፡ ሥረይ ፡ ሊተ ፡ አ ፡ አቡየ ፡ ቅዱስ ፡ ወቡሩክ ፡ ወግበር ፡ ምስሌየ ፡ ፍቅረ ፡ ወመሀረኒ ፡ ወተዘከረኒ ፡ በጸሎትከ ፡ ቅድስት ፡ ከመ ፡ ይረስየኒ ፡ እግዚአ ዘእገብር ፡ ፈቃዶ ፡ ወተምህረ ፡ ኵሎ ፡ ፍኖተ ፡ ምንኵስና ፡ መንፈሳዌ ፡ ወኮነ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ፡ ዘይትራድኦ ፡ በኵሉ ፡ ግብር ወነበረ ፡ ምስለ ፡ አረጋዊ ፡ አባ ፡ አጋቶን ፡ ፫ተ ፡ ዓመተ፡እንዘ፡ይገብር፡ሎቱ፡ኵሎ፡ዘይኤዝዞ፡ ወእምዝ፡አዕረፈ፡አባ፡አጋቶን።

ጊዜም፡የምንኵስና፡ልብስን፡ይለብስ፡ዘንድ፡ ያስብ ፡ ነበር ። በአንዲትም ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ አስቄጥስ፡ገዳም፡ይሔድ፡ዘንድ፡ምክንያት፡ አግኝቶ ፡ ከአባቱ ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ፡ ግን ፡ መንገዱን፡ አያውቅም ፡ ነበር ። የእግዚአብ ሔርም፡መልአክ፡በመነኵሴ፡አምሳል፡ሁኖ፡ እየመራው፡አብሮት፡ተጓዘ፡በአደረሰውም፡ ጊዜ ፡ በበዓት ፡ ውስጥ ፡ ለሚኖር ፡ ለአንድ ፡ ስሙ ፡ አባ ፡ አጋቶን ፡ ለሚባል ፡ ሽማግሌ ፡ መነኰስ፡ሰጠው፡እርሱ፡እጅግ፡ጻድቅ፡ሰው፡ ነውና።ይህም፡መልአክ፡ስለ፡አባ፡ሳሙኤል፡ ለአባ ፡ አጋቶን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነገረው ፡ ሳሙኤልን፡ደስ፡ብሎህ፡ተቀበለው፡የምንኵ ስናንም፡ልብስ፡አልብሰው፡እርሱ፡የሽምግ ልናህን ፡ ድካም ፡ የሚያጽናና ፡ ዕውነተኛ ፡ ልጅ፡ ይሆንሃልና፡አንተም፡የምንኵስናን፡ ሕግ፡ሁሉ፡አስተምረው፡ይህንንም፡ከተና ገረው፡በኋላ፡መልአኩ፡ከእርሱ፡ተሠወረ።

፳፤ ሳሙኤልም፡በደረሰ፡ጊዜ፡አባ፡አጋቶን ፡ በደስታ፡ተቀበለው፡እንዲህም፡አለው፡ ግዚአብሔር፡አገልጋይ፡ሳሙኤል፡ሆይ፡ መምጣትህ፡መልካም፡ነው፡በሽምግልናዬ፡ ጊዜ ፡ ጌታ ፡ ወደእኔ ፡ ልኮሃልና ፡ አለው ፡ ወዲያውኑ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስገ ባውና ፡ ከፀጉር ፡ በተሠራው ፡ ቀሚስና ፡ በቆቡ ፡ ላይ ፡ በቅናትና ፡ በአስኬማ ፡ ላይ ፡ ጸለየና ፡ ባረከው ፡ የአባቶቼ ፡ የአባ ፡ እንጦን ዮስና ፡ የአባ ፡ መቃርዮስ ፡ ፈጣሪ ፡ ከአንተ ፡ ጋር፡ይኑር፡ልጄ፡ሳሙኤል፡ሆይ፡በችግርህ፡ ሁሉ፡ረዳት፡ይሁንህ፡ብሎ፡እኒያን፡የምን ኵስና፡ልብሶችን፡አለበሰው።

፳፩፤ ቅዱስ ፡ አጋቶንም ፡ ለአባ ፡ ሳሙኤል ፡ ትሕትናን ፡ አርምሞን ፡ አስተማረው ፡ አባ ፡ ሳሙኤልም፡ቅዱስና፡ቡሩክ፡የሆንክ፡አባቴ፡ ሆይ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ ከእኔ ፡ ጋርም ፡ ፍቅርን ፡ አድርግ ፡ አስተምረኝም ፡ እግዚአብሔርም ፡ የሚወደውን ፡ የምሠራ ፡ ያደርገኝ ፡ ዘንድ ፡ በከበረች ፡ ጸሎትህ ፡ አስበኝ ፡ ይለው ፡ ነበር ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ መንፈሳዊ ፡ የሆነ ፡ የምንኵስናን ፡ ሥርዓትም ፡ ሁሉ ፡ ተማረ ። ቅዱስ ፡ አባ ፡ ሳሙኤልም ፡ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ ይራዳው ፡ ነበረ፡የሚያዝዘውንም፡ሁሉ፡እየሠራ፡ከአባ፡ አጋቶን፡ጋር፡ሦስት፡ዓመት፡ኖረ፡ከዚህም፡ በኋላ፡አባ፡አጋቶን፡አረፈ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፱፡ ወነበረ ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ፡ እንዘ ፡ ይጸውም ፡
በበሱባዔ ፡ ወይትጋደል ፡ ገድለ ፡ ዐቢየ ፡
ወእምዝ፡ተሠይመ፡ቀሲሰ፡ውስተ፡ቤተ፡ክር
ስቲያን፡ዘቅዱስ፡አባ፡መቃርስ፡ዘአስቄጥስ።

፴፡ ወእምድኅረ ፡ ኅዳጥ ፡ መዋዕል ፡ አምጽኡ ፡
ጦማረ ፡ ልዮን፡ ኀበ ፡ ገዳመ ፡ አስቄጥስ ፡ ወአን
በብዋ፡ወሰሚዖሙ፡አረጋውያን፡መነኰሳት፡
ኀዘኑ ፡ ፈድፋደ ፡ ወቀንአ ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ፡
ቅንአተ፡መንፈሳዊተ፡ወተንሥአ፡እማዕከለ፡
ሰብእ፡ወመሠጣ፡ለይእቲ፡ጦማር፡ወሠጠጣ፡
ወይቤ ፡ ውጉዝ ፡ ውእቱ ፡ ኵሉ ፡ ዘይዌልጥ ፡
ሃይማኖተ፡ርትዕተ፡ዘአበዊነ።

፴፩፡ ወሶበ ፡ ርእየ ፡ ላእኩ ፡ ለንጉሥ ፡ ዐላዊ ፡
ተመልአ፡መዓተ፡ወአዘዘ፡ከመ፡ይዝብጥዎ፡
ለቅዱስ ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ፡ በድንቡሳት ፡
ዘኀጺን፡ ወይስቅልዎ ፡ በመዝራዕቱ ፡ ወይጽ
ፍዕዎ ፡ ገጾ ፡ ወሶበ ፡ ጸፍዕዎ ፡ ተመልሐት ፡
አሐቲ ፡ ዐይኑ ፡ ወእምዝ ፡ ካዕበ ፡ አዘዘ ፡
ይስድድዎ፡እምደብረ፡አስቄጥስ።

፴፪፡ ወአስተርአዮ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡
ለአባ ሳሙኤል ፡ ወአዘዞ ፡ ከመ ፡ ይሑር
ወይኅድር ፡ ኀበ ፡ ደብረ ፡ ቀልሞን ፡ ወሖረ ፡
ቢጊዜሃ ፡ ወኀደረ ፡ ህየ ፡ ወነበረ ፡ እንዘ ፡
ይሜህሮሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ሰብእ ፡ ሃይማኖተ ፡
ርትዕተ ፡ ወሰምዐ ፡ ዜናሁ ፡ መቶዝዝ ፡
መኰንን፡ ዘእስክንድርያ ፡ መለካዊ ፡ ወዘኮነ ፡
ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወመጽአ ፡ ኀበ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡
ሳሙኤል ፡ ወቀሠፎ ፡ ዐቢየ ፡ መቅሠፍተ ፡
ወሰደዶ፡እምደብሩ።

፴፫፡ ወሖረ ፡ ወኀደረ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
ዘደብረ ፡ ቀልሞን ፡ ወበውእቱ ፡ መዋዕል ፡
መጽኡ ፡ በርበር ፡ አረማውያን ፡ ህየ ፡
ወነሥእዎ፡ለአባ፡ሳሙኤል፡ኀበ፡ብሔሮሙ፡
ከመ፡ይሰድዎ፡ወሰአሎ፡ለእግዚእ፡ክርስቶስ፡
ሎቱ፡ ስብሐት ፡ ከመ ፡ ያድኅኖ ፡ እምኔሆሙ ፡
ወሶበ፡ጸዓንዎ፡ዲበ፡፩ገመል፡ኢክህለ፡አንሰ
ሐስሖ፡ውእቱ፡ገመል፡ወዘበጥዎ፡ዝብጠተ፡
ወሶበ፡ስእንዎ፡ኀደግዎ፡ወሖሩ፡ብሔሮሙ፡
ውእቱሂ ፡ ተመይጠ ፡ ኀበ ፡ ደብሩ ፡ ቀልሞን ፡
ወነበረ፡እንዘ፡ይጸመድ፡በፍኖተ፡ምንኵስና፡
በኵሉ፡ተጋድሎ።

፳፱፡ አባ ፡ ሳሙኤልም ፡ ሰባት ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡
እየጾመና ፡ ታላቅ ፡ ተጋድሎን ፡ እየተጋደለ ፡
ኖረ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በአስቄጥስ ፡ በአለች ፡
በከበረች፡በአባ፡መቃርስ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡
ቅስና፡ተሾመ።

፴፡ከጥቂት፡፡ቀኖች፡በኋላም፡የልዮንን፡ደብዳቤ
ወደ ፡ አስቄጥስ ፡ ገዳም ፡ አምጥተው ፡
አነበቧት፡ አረጋውያን ፡ መነኰሳትም ፡
በሰሙ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ አዘኑ ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ፡
መንፈሳዊ ፡ ቅናትን ፡ ቀና ፡ ከሰዎችም ፡
መካከል ፡ ተነሥቶ ፡ ያቺን ፡ ደብዳቤ ፡ ነጥቆ ፡
ቀደዳት ፡ እንዲህም ፡ አለ ፡ የቀናች ፡ የአባቶቻ
ችንን ፡ ሃይማኖት ፡ የሚለውጥ ፡ ሁሉ ፡
የተወገዘ፡ነው።

፴፩፡የንጉሥ፡መልክተኛም፡በአየ፡ጊዜ፡ቍጣን፡
ተመላ፡አባ፡ሳሙኤልንም፡በብረት፡ዘንጎች፡
እንዲደበድቡት፡በክንዱም፡ሰቅለው፡ፊቱን፡
እንዲጸፉት፡አዘዘ፡በጸፉትም፡ጊዜ፡አንዲት፡
ዐይኑ፡ወለቀች፡ከዚህም፡በኋላ፡ከአስቄጥስ፡
ገዳም፡እንዲአሳድዱት፡ሁለተኛ፡አዘዘ።

፴፪፡ ከእግዚአብሔርም ፡ የታዘዘ ፡ መልአክ ፡
ለአባ፡ ሳሙኤል ፡ ተገለጸለትና ፡ ወደ ፡
ቀልሞን፡ተራራ፡ሒዶ፡በዚያ፡ይኖር፡ዘንድ፡
አዘዘው ፡ ወዲያውኑ ፡ ሒዶ ፡ በዚያ ፡ ኖረ ፡
የቀናች፡ሃይማኖትንም፡ለሰዎች፡ሁሉ፡እያስ
ተማረ ፡ ተቀመጠ ። ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ የሆነው ፡
መለካዊ ፡ የእስክንድርያ ፡ መኰንን ፡
ምቆዝዝም ፡ ዜናውን ፡ ሰምቶ ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡
አባ፡ሳሙኤል፡መጥቶ፡ታላቅ፡ግርፋትንም፡
ገርፎ፡ከገዳሙ፡አሳደደው።

፴፫፡ ወደ ፡ ቀልሞን ፡ ገዳም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡
ሒዶ ፡ በዚያ ፡ ተቀመጠ ፡ በዚያም ፡ ወራት ፡
የበርባር፡አረማውያን፡ወደዚያ፡መጡ፡ወደ፡
አገራቸውም ፡ ሊወስዱት ፡ አባ ፡ ሳሙኤልን ፡
ያዙት፡ከእርሳቸውም፡እጅ፡ያድነው፡ዘንድ፡
ክብር፡ይግባውና፡ጌታችንን፡ኢየሱስ፡ክርስ
ቶስን ፡ ለመነው፡ በአንድ ፡ ግመል ፡ ላይም ፡
በጫኑት ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ ግመል ፡ መንቀሳቀስ ፡
አልቻለም ፡ ታላቅ ፡ ድብደባም ፡ ደበደቡት ፡
በተሳናቸውም፡ ጊዜ ፡ ትተውት ፡ ሔዱ ፡
እርሱም ፡ ወደ፡ ቀልሞን ፡ ገዳሙ ፡ ተመልሶ ፡
በምንኵስና፡ ሥርዓት ፡ በመጠመድ ፡ በሁሉ ፡
ተጋድሎ፡እየተጋደለ፡ኖረ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፯፤ ወእምድኅረዝ ፡ መጽኡ ፡ በርበር ፡ ዳግመ ፡
ወፈርሀ፡እምኔሆሙ፡ወሰምዐ፡ቃለ፡ዘይብል፡
ኢትፍራህ፡ አ፡ ሳሙኤል፡ አላ፡ ባእ፡ ውስተ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወኢትትናገር ፡
ምስሌሆሙ፡ ወአነ፡ እሬስዮሙ፡ ከመ፡ ኢይር
አዩከ፡ወሶቤሃ፡መጽኡ፡ወቦኡ፡ውስተ፡ቤተ፡
ክርስቲያን፡እንዘ፡አስይፍት፡ምሉሐን፡በእደ
ዊሆሙ፡ ወእሙንቱ፡ ይኬልሑ፡ በቃሎሙ፡
ዘመፍርህ ፡ ፈድፋደ ፡ ወቅዱስ ፡ ሳሙኤል ፡
ነጸሮሙ፡ እንዘ፡ ይገብሩ፡ ኃጢአተ፡ ውስተ፡
ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ወኢተክህሎ ፡ ያርምም ፡
በእንተ ፡ ድፍረቶሙ ፡ ዳዕሙ ፡ ተናገሮሙ ፡
ወይቤሎሙ ፡ ምንትኑ ፡ ዘትገብሩ ፡ አ ፡
ዐላውያን፡ እለ፡ አልብክሙ፡ ፈሪሀ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ወእግዚአብሔር ፡ ይፍዲክሙ ፡
በከመ፡እከየ፡ምግባሪክሙ።

፳፰፤ ወይቤልዎ ፡ እሙንቱ ፡ አረማውያን ፡
አንተኑ፡ ትነብር፡ ዝየ፡ ንሕነሰ፡ ኢርኢናከ፡
ወአኀዝዎ፡ ወአሠርዎ ፡ በጽኑዕ ፡ ውስተ ፡
ዓምደ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ወቀሠፍዎ፡ እስከ፡
ቀርበ ፡ ለመዊት ፡ ወፈትሕዎ ፡ እማእሠሩ ፡
ወወድቀ፡ በገጹ፡ ወሰሐብዎ፡ እስከ፡ መካነ፡
አግማል ፡ እንዘ ፡ ይዘብጥዎ ፡ ዲበ ፡ ርእሱ ፡
በአሣዕን ፡ ወእምብዝኀ ፡ ዝብጠት ፡
ኢተክህሎ፡ አንስሐስሖ ፡ ወጸዓንዎ ፡ ዲበ ፡
ገመል ፡ ወኮነ ፡ ዘይበኪ ፡ በእንተ ፡ ጽንዐ ፡
ሕማሙ፡ ብካየ፡ መሪረ። ወተመይጠ፡ ኀቤሁ፡
ውእቱ፡ ገመል፡ ወተናገሮ፡ በልሳነ፡ ሰብእ፡
ወይቤሎ ፡ ሠናይ ፡ ዘዘበጡከ ፡ እስመ ፡
ይደልወከ ፡ መዊት ፡ በእንተ ፡ ዘተዓደውከ ፡
ትእዛዘ፡እግዚአብሔር፡አምላክከ፡ዘይቤለከ፡
አርምም፡ወኢትትናገር፡ወሶበ፡ሰምዐ፡አባ፡
ሳሙኤል፡ በከየ፡ ወይቤ፡ በአማን፡ አበስኩ፡
ባሕቱ ፡ እስመ ፡ ከሀሊ ፡ እግዚአብሔር ፡
ይኅድግ፡ሊተ፡ተዓድዎትየ።

፳፱፤ ወእምዝ፡ወሰድዎ፡ኀበ፡ብሔሮሙ፡ወበህየ፡
ረከቦ፡ ለአባ፡ዮሐንስ፡ አበ፡ ምኔት፡ ዘገዳመ፡
አስቄጥስ፡ ዘኮነ፡ ዘእምቅድሜሁ፡ ፄወውዎ፡
ወተናዘዙ፡በበይናቲሆሙ፡በህየ።

፴፤ ወእግዚኡሰ፡ ለአባ፡ ሳሙኤል፡ ያጌብሮ፡ ከመ
ያምልክ ፡ ፀሐየ ፡ ውእቱሰ ፡ ኢይሰምዖ ፡

፳፯፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የበርበር ፡ አረማውያን ፡
ዳግመኛ ፡ መጡ ፡ ከእርሳቸውም ፡ የተነሣ ፡
ፈራ፡ ሳሙኤል ፡ ሆይ ፡ አትፍራ ፡ ግን ፡ ወደ ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገብተህ ፡ ዝም ፡ በል ፡ ከእር
ሳቸው፡ ጋር፡ አትናገር፡ እኔም፡ እንዳያዩህ፡ አደ
ርጋቸዋለሁ፡ የሚልን፡ ቃል፡ ሰማ፡ በዚያንም፡
ጊዜ ፡ የተመዘዙ ፡ ሰይፎቻቸውን ፡ ይዘው ፡
ወደ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ገቡ ፡
እነርሱም፡ እጅግ፡ በሚያስፈራ፡ ድምፃቸው፡
ይጮኹ፡ ነበር፡ ቅዱስ፡ ሳሙኤልም፡ በቤተ፡
መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ ኃጢአትን ፡ ሲሠሩ ፡
ተመለከተ ፡ ስለ ፡ ድፍረታቸውም ፡ ዝም ፡
ማለት፡ አልተቻለውም፡ ተናገራቸው፡ እንዲ፡
እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ የሌላችሁ ፡
እናንተ፡ ከሀድያን፡ እግዚአብሔር፡ እንደ፡ ክፉ
ሥራችሁ፡ ይክፈላችሁ፡ አላቸው።

፳፰፤ እነዚያ ፡ አረማውያንም ፡ አንተ ፡ ከዚህ ፡
ነበርክን ፡ እኛ ፡ ግን ፡ አላየንህም ፡ አሉት ፡
ከዚህም፡ በኋላ፡ ይዘው፡ ከቤተ፡ ክርስቲያኑ፡
ምሰሶ ፡ ጋር ፡ አሠሩት ፡ ለመሞት ፡ እስቲቀ
ርብም፡ ገረፉት፡ ከማሠሪያውም፡ ሲፈቱት፡
በግምባሩ፡ ተደፋ፡ ግመሎች፡ እስካሉበትም፡
ቦታ፡ ጐተቱት፡ ራሱንም፡ በጫማ፡ መቱት፡
ከድብደባ፡ ብዛት፡ የተነሣ፡ መንቀሳቀስ፡ አል
ተቻለውም ፡ በግመልም ፡ ጫኑት ፡
ከሕመሙም ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ መሪር ፡
ልቅሶን፡ የሚያለቅስ ፡ ሆነ ፡ ያም ፡ ግመል ፡
ወደርሱ፡ ተመልሶ፡ በሰው፡ ቋንቋ፡ እንዲህ፡
ብሎ፡ ተናገረው፡ መደብደብህን፡ መልካም፡
አደረጉ፡ ምዝ፡ በል፡ አትናገር፡ ያለህን፡ የፈጣ
ሪህን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡
ተላለፍክ ፡ ሞት ፡ ይገባሃልና ፡ አለው ፡ አባ ፡
ሳሙኤልም፡ ሲሰማ፡ በእውነት፡ በድያለሁ፡
ነገር፡ ግን፡ እግዚአብሔር፡ ቻይ፡ ነውና፡ መተ
ላለፌን፡ ይቅር፡ ይበለኝ፡ አለ።

፳፱፤ ከዚህም፡ በኋላ፡ ወደ፡ አገራቸው፡ ወሰዱት፡
በዚያም ፡ የአስቄጥስ ፡ ገዳም ፡ አበ ፡ ምኔት ፡
የሆነውን፡ ከእርሱ፡ አስቀድሞ፡ የማረኩትን፡
አባ፡ ዮሐንስን፡ አገኘውና፡ እርስበርሳቸው፡
ተጽናኑ።

፴፤ የአባ፡ ሳሙኤልም፡ ጌታው፡ ፀሐይን፡ እንዲአ
መልክ ፡ ያስገድደው ፡ ነበር ፡ እርሱ ፡ ግን ፡

www.ethiopianorthodox.org

ግሙራ ፡ ወእምዝ ፡ አሥሮ ፡ እግሮ ፡ ምስለ ፡ አሐቲ ፡ ወለት ፡ በምክረ ፡ ሰይጣን ፡ ወፈነዎሙ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ ከመ ፡ ይርዐዩ ፡ አግማለ ፡ እስመ ፡ ሐለየ ፡ ከመ ፡ ቅዱስ ፡ ሳሙኤል ፡ ይወድቅ ፡ በኃጢአት ፡ ምስሌሃ ፡ ወይትኤዘዝ ፡ ሎቱ ፡ በኵሉ ፡ ዘይቤሎ ፡ ወአምከሮ ፡ ዲያብሎስ።

፴፩፤ ወበዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ ኮነ ፡ ቅዱስ ፡ ሳሙኤል ፡ ይትዌሰክ ፡ ሎቱ ፡ ኃይል ፡ ወጽንዕ ፡ ወነበረ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ደወየ ፡ እግዚኡ ፡ ወቀርበ ፡ ለመዊት ፡ ወጸለየ ፡ ላዕሌሁ ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ፡ ወፈወሶ ፡ እምደዌሁ ፡ ወተሰምዐ ፡ ዜናሁ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ብሔር ፡ ወኮኑ ፡ ኵሎሙ ፡ ዘቦ ፡ ደዌ፡ ይመጽኡ ፡ ኀቤሁ ፡ ውእቱኒ ፡ ይጼሊ ፡ ላዕለ ፡ ዘይት ፡ ወይቀብዖሙ ፡ ወይትፌወሱ ፡ በጊዜሃ ፡ ወርእዮ ፡ እግዚኡ ፡ ዘንተ ፡ አንከረ ፡ ፈድፋደ ፡ ወሰገደ ፡ ሎቱ ፡ ወይቤሎ ፡ ስረይ ፡ ሊተ ፡ አበሳየ ፡ ዘገበርኩ ፡ ላዕሌከ ፡ ወአፍቀሮ ፡ ወአክበሮ ፡ ፈድፋደ ፡ ወይቤሎ ፡ሰአለኒ ፡ ዘትፈቅድ ፡ ወአነ ፡ እገብር ፡ ለከ ፡ ወይቤሎ ፡ አባ፡ ሳሙኤል ፡ እፈቅድ ፡ እግባእ ፡ ውስተ ፡ ብሔርየ ፡ እግዚኡኒ ፡ አስተዳለወ ፡ ሎቱ ፡ ብዙኀ ፡ ንዋየ ፡ አምኃሁ ፡ ወአግማለ ፡ ወአስተ ፋነዎ ፡ በሰላም።

፴፪፤ ወተጋብኡ ፡ ደቂቁ ፡ ወበዝኁ ፡ ፈድፋደ ፡ እስከ፡ ኮኑ ፡ አእላፈ ፡ ወአስተርአየቶ ፡ እግዝ እትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ወትቤሎ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ መካን ፡ ማኅደርየ ፡ ይከውን ፡ እስከ ፡ ለዓለም።

፴፫፤ ወእምይእቲ ፡ ዕለት ፡ ኢተመይጡ ፡ አረማ ውያን ፡ ኀበ ፡ ውእቱ ፡ ደብር ። ወዝንቱ ፡ አብ ፡ ሳሙኤል ፡ ደረሰ ፡ ድርሳናተ ፡ ብዙኃተ ፡ ወተነበየ ፡ በእንተ ፡ ምጽአቶሙ ፡ ለተንባላት ፡ እሉ ፡ ውሉደ ፡ አጋር ፡ ወበእንተ ፡ መንግ ሥቶሙ ፡ ወእሙንቱ ፡ ከመ ፡ ያመነድብዎሙ ፡ ለሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ በኵሉ ፡ መካን።

፴፬፤ ወሶበ ፡ ቀርበ ፡ ጊዜ ፡ ፍልሰቱ ፡ አስተጋብአሙ ፡ ለደቂቁ ፡ መነኮሳት ፡ ወአዘዞሙ ፡ ከመ ፡ ይጽንኡ ፡ ወይሑሩ ፡ ውስተ ፡ ፍኖተ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ወይትጋደሉ ፡ በእንተ ፡ ሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ እስከ ፡ ነፍስ ፡ ደኃሪት ፡ ወእምዝ ፡

ከቶ፡ አልሰማውም ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከአንዲት ፡ ብላቴና ፡ ጋር ፡ በሰይጣን ፡ ምክር ፡ እግሩን ፡ አቆራኝቶ ፡ ግመሎችን ፡ እንዲጠብቁ ፡ ወደጫካ ፡ ሰደዳቸው ፡ ቅዱስ ፡ ሳሙኤል ፡ ከእርሷ ፡ ጋር ፡ በኃጢአት ፡ እንደ ሚወድቅና ፡ ዲያብሎስ ፡ በአስተማረውና ፡ በመከረው ፡ ሁሉ ፡ እንደሚታዘዝለት ፡ አስቧልና።

፴፩፤ በዚህም ፡ ሁሉ ፡ ቅዱስ ፡ ሳሙኤል ፡ ኃይልና ፡ ብርታት ፡ የሚጨመርለት ፡ ሁኖ ፡ ጌታው ፡ ታሞ ፡ ለሞት ፡ እስከ ፡ ቀረበ ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ ኖረ። አባ ፡ ሳሙኤልም ፡ በላዩ ፡ ጸለየና ፡ ከደዌው፡ ፈወሰው ፡ ዜናውም ፡ በሀገሩ ፡ ሁሉ ፡ ተሰምቶ ፡ ደዌ ፡ ያለባቸው ፡ ሁሉ ፡ ወደርሱ ፡ የሚመጡ ፡ ሆኑ ፡ እርሱም ፡ በዘይቱ ፡ ላይ ፡ ጸልዮ፡ ሲቀባቸው ፡ ወዲያውኑ ፡ ይድናሉ ፡ ጌታውም ፡ ይህን ፡ አይቶ ፡ እጅግ ፡ አደነቀ ፡ በአንተ ፡ ላይ ፡ ያደረግሁትን ፡ በደሌን ፡ ሁሉ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ ብሎ ፡ ሰገደለት ፡ እጅግም ፡ ወደደው ፡ አከበረውም ፡ የምትሻውንም ፡ ጠይቀኝ ፡ አደርግልሃለሁ ፡ አለው ። አባ ፡ ሳሙኤልም ፡ ወደ ፡ ሀገሬ ፡ እመለስ ፡ ዘንድ ፡ እሻለሁ ፡ አለው ፡ ጌታውም ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ብዙ፡ ገንዘብንና ፡ ግመሎችን ፡ አዘጋጅቶ ፡ በፍቅር ፡ በሰላም ፡ ሸኘው።

፴፪፤ ልጆቹ ፡ መነኮሳትም ፡ ወደርሱ ፡ ተሰበሰቡ ፡ አእላፋትም ፡ እስከሆኑ ፡ ድረስ ፡ እጅግ ፡ በዙ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ እመቤታችን ፡ ማርያምም ፡ ተገልጻለት ፡ ይህ ፡ ቦታ ፡ ለዘላለም ፡ ማደሪያዬ ፡ ይሆናል ፡ አለችው።

፴፫፤ ከዚያቺም ፡ ዕለት ፡ ወዲህ ፡ ወደዚህ ፡ ገዳም ፡ አረማውያን ፡ ተመልሰው ፡ አልመጡም። ይህ ፡ አባት ፡ ሳሙኤልም ፡ ብዙ ፡ ድርሳናትን ፡ ደረሰ ፡ ስለ ፡ እስላሞችም ፡ መምጣት ፡ መንግሥ ትንም፡ ስለመያዛቸው ፡ የክርስቲያን ፡ ወገኖ ችንም ፡ በቦታው ፡ ሁሉ ፡ እንደሚአሠቃዩ አቸው ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ፡ እነርሱም ፡ የአጋር ልጆች ፡ ናቸው።

፴፬፤ ዕረፍቱም ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ መነኮሳት ፡ ልጆቹን ፡ ሰበሰባቸውና ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ ጸንተው ፡ እንዲኖሩ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ዩቱም ፡ ሕቅታ ፡ ድረስ ፡ ስለ ፡ ቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ እንዲጋደሉ ፡ አዘዛቸው። ከዚህም፡

www.ethiopianorthodox.org

ሐመ፡ንስቲተ፡ወአዕረፈ፡በሰላም።

፴፭፡ ወተብህለ ፡ በእንቲአሁ ፡ አሐተ ፡ ዕለተ ፡ አዕረፈ ፡ አሐዱ ፡ እምውሉዱ ፡ ሶበ ፡ ኀቤሁ ፡ መጽአ ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ፡ ገብአት ፡ ነፍሱ ፡ ወተንሥአ ፡ በቅድመ ፡ ኵሎሙ ፡ አኃው ፡ ወነገሮሙ ፡ ዘከመ ፡ ርእየ ፡ ኵነኔሆሙ ፡ ለኃጥአን ፡ ወተድላሆሙ ፡ ለጻድቃን ፡ ወእምዝ፡ተመይጠ፡ወአዕረፈ።

፴፮፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ፡በጸሎቱ፡ለዝንቱ፡አብ፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

በኋላ፡ጥቂት፡ታሞ፡በሰላም፡አረፈ።

፴፭፡ ስለርሱም ፡ እንዲህ ፡ ተባለ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከልጆቹ ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ አረፈ ፡ አባ ፡ ሳሙኤልም ፡ ወደርሱ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ነፍሱ ፡ ተመልሳለት ፡ በመነኰሳቱ ፡ ፊት ፡ ተነሣ ፡ የኃጥአንን ፡ ሥቃይ ፡ የጻድቃንንም ፡ ተድላ ፡ ደስታቸውን፡እንዳየ፡ተናግሮ፡ተመልሶ፡አረፈ።

፴፮፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም፡ በዚህ ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለከ፡መጋቤ፡ሥርዓታ፡ወሕጋ።ለደብረ፡ቀልሞን፡ምልእተ፡ጸጋ።እስከ፡አዕረጎ፡ሳሙኤል፡ኀበ፡ላዕላዊት፡እንግልጋ።እምካልአኒሁ፡አመ፡ኮነ፡ንትጋ።ለመልአከ፡ሰማይ፡ጸለይከ፡እንዘ፡አንተ፡ዘሥጋ።

፴፯፡ ወበዛቲ፡ዕለት፡ኮኑ፡ሰማዕተ፡ቅዱሳን፡አባ፡ኤሲ፡ ወእኅቱ፡ ቴክላ፡ ዘእምሀገረ፡ ብጺር፡ ዘምዕራብ፡ደወለ፡እስሙናይን።

፴፰፡ ወለዝንቱ፡ቅዱስ፡ኤሲ፡ቦ፡ብዙኅ፡ንዋይ፡ ፈድፋደ፡ወአዕፃዳት፡ወአባግዕ፡ወይሁብ፡ ሜጠ፡ጸጕረ፡አባግዒሁ፡ለነዳያን፡ወለምስኪናን፡ምጽዋተ፡እስመ፡ውእቱ፡ፈራሄ፡እግዚአብሔር ፡ ፈድፋደ ፡ ወእኅቱኒ ፡ ቴክላ ፡ ከማሁ፡ፈራሂተ፡እግዚአብሔር፡ይእቲ።

፴፱፡ ወስመ ፡ አቡሆሙ ፡ ኤልያስ ፡ ወስመ ፡ እሞሙ፡ ማርያም ፡ ወእሙንቱ ፡ ሰአልዎ ፡ ለኤሲ፡ወልዶሙ፡ወይቤልዎ፡ኦ፡ወልድነ፡ፍቁር፡ንፈቱ፡ናስተዋስብከ፡በሕይወትነ፡ከመ፡ንትፌሣሕ፡ብከ፡ውእቱሰ፡ኢፈቀደ፡ዘንተ፡ግብረ፡ዳዕሙ፡ይቤሎሙ፡ኦ፡አቡየ፡ወእምየ፡ቡሩካን፡ጸልዩ፡ላዕሌየ፡ወኵሎ፡ዘትኤዝዙኒ ፡ አነ ፡ እትዌከፍ ፡ በፍሥሓ ፡ ለዝንቱሰ ፡ ኢትትናገሩኒ ፡ በእንቲአሁ ፡ እስመ ፡ ኢይገብሮ ። ወእምአሜሃ ፡ ኢተናገርዎ ፡ ግሙራ ፡ በእንተ ፡ ሰብሳብ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ፡ያፈቅርዎ፡ፈድፋደ።

፵፡ ወእምዝ፡ሞተ፡አቡሁ፡እንዘ፡መዋዕሊሁ፡፳፡ ዓመት ፡ ወእምድኅረ ፡ ኅዳጥ ፡ መዋዕል ፡ አዕረፈት ፡ እሙ ፡ ወበውእቱ ፡ መዋዕል ፡ አዘዘ ፡ ዲዮቅልጥያኖስ፡ንጉሥ፡ዐላዊ፡ከመ፡ኵሉ፡ሰብእ ፡ ይስግድ ፡ ለጣዖት ፡ ወሐረ ፡ ቅዱስ ፡

፴፯፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ ለእስሙናይን ፡ በስተምዕራብ፡ ካለ ፡ አውራጃ ፡ ብጺር ፡ ከሚባል ፡ መንደር፡ቅዱሳን፡አባ፡ኤሲና፡እኅቱ፡ቴክላ፡በሰማዕትነት፡አረፉ።

፴፰፡ ይህም ፡ አባ ፡ ኤሲ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ቦታዎችና ፡ በጎችም ፡ አሉት ፡ የበጎቹንም ፡ ጠጕር ፡ ሸያጭ ፡ ለድኆችና ፡ ለችግረኞች ፡ ምጽዋት፡አድርጎ፡ይሰጥ፡ነበር፡እርሱ፡እግዚአብሔርን ፡ እጅግ ፡ ይፈራ ፡ ነበርና ፡ እ ቱ ፡ ቴክላም፡እንደርሱ፡እግዚአብሔርን፡የምትፈራ፡ናት።

፴፱፡ የአባታቸውም ፡ ስም ፡ ኤልያስ ፡ የእናታቸውም ፡ ማርያም ። ይባላል ፡ እነርሱም ፡ ልጃቸውን ፡ ኤሲን ፡ የተወደድክ ፡ ልጃችን ፡ ሆይ፡ በሕይወታችን ፡ ሳለን ፡ልናጋባህና ፡ በአንተ፡ደስ፡እንዲለን፡እንወዳለን፡ብለው፡ለመኑት፡እርሱ፡ግን፡ይህን፡አልወደደም፡እንዲህም፡አለቸው፡የተባረካችሁ፡አባቴና፡እናቴ፡ሆይ፡ጸልዩልኝ፡የምታዝዙኝም፡ሁሉ፡በደስታ፡እቀበላለሁ፡ስለጋብቻ፡ግን፡አትናገሩኝ ፡ አላደርገውምና ፡ ከዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ፡ስለ፡ጋብቻ፡ከቶ፡አልተናገሩትም፡እጅግ፡ይወዱት፡ነበርና።

፵፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ዕድሜው ፡ ሃያ ፡ ዓመት ፡ ሲሆነው፡አባቱ፡ሞተ፡ከጥቂት፡ቀኖችም፡በኋላ፡እናቱ፡ሞተች፡ከሀዲ፡ንጉሥ፡ዲዮቅል

www.ethiopianorthodox.org

ኤሲ፡ኀበ፡ሀገረ፡እስክንድርያ፡ከመ፡ይሚጥ፡ ንዋዮ።

፶፩፡ ወሀለዎ ፡ ለአባ ፡ ኤሲ. ፡ ዐርክ ፡ በሀገረ ፡ እስክንድያ ፡ ዘስሙ ፡ ጳውሎስ ፡ ወውእቱ ፡ ደወየ ፡ ደዌ ፡ ጽኑዐ ፡ ወነበረ ፡ ኤሲ. ፡ ኀቤሁ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ሐይወ ፡ እምደዌሁ ፡ ወኮነ ፡ ምንዳቤ ፡ ዐቢይ ፡ ላዕለ ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ በውእቱ ፡ መዋዕል ፡ ወእሉ ፡ ቅዱሳን ፡ አባ ፡ ኤሲ. ፡ ወዐርኩ ፡ ጳውሎስ ፡ ይሣየጡ ፡ መብልዐ ፡ ሠናየ፡ ወጥዑመ ፡ በንዋዮሙ ፡ ወይወስዱ ፡ ለቅዱሳን፡እለ፡ሀለዉ፡ውስተ፡ሀገረ፡እስክንድርያ ፡ ወከማሁ ፡ ይሔውጽዎሙ ፡ ለእለ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ፡ በእንተ ፡ ስሙ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወኮኑ ፡ ዘይናዝዝዎሙ ፡ ወይትለአክዎሙ፡ከመ፡አግብርት፡ወእሉኒ፡ቅዱሳን፡ ይትኔበዩ፡ላዕሌሆሙ፡ወይቤልዎሙ፡ሀለወክሙ፡ከመ፡አንትሙ፡ትንሥኡ፡አክሊለ፡ ስምዕ።

፶፪፡ ወበውእቱ፡መዋዕል፡አብጽሕዎ፡ለቅዱስ፡ ፊቅጦር፡ወልደ፡ህርማኖስ፡ኀበ፡ሀገረ፡እስክንድርያ ፡ ወሶበ ፡ ርእይዎ ፡ አባ ፡ ኤሲ. ፡ ወዐርኩ፡ ጳውሎስ ፡ አንከሩ ፡ ወቀንኡ ፡ ላዕሌሁ ፡ መንፈሳዌ ፡ ቅንአተ ፡ እስመ ፡ ውእቱ፡ መነነ ፡ መንግሥተ ፡ ዝንቱ ፡ዓለም ፡ ኀላፊ ፡ ወእምዝ ፡ ቀርበ ፡ አባ ፡ ኤሲ. ፡ ኀበ ፡ መኰንን ፡ ወተአመነ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ መኰንንኒ ፡ አዘዘ ፡ ከመ ፡ ይኰንንዎ፡ወቀሥፍዎ፡መቅሠፍተ፡ብዙኀ፡ በአስዋጥ ፡ ወሰተሩ ፡ አባላቲሁ ፡ በመጥባሕት፡ ወረሰዩ ፡ መኃትወ ፡ እሳት ፡ ውስተ ፡ ሥጋሁ ፡ ወአሠርዎ ፡ በሰናስለ ፡ ኀፂን ። ወአንደዱ ፡ ካዕበ፡ እሳተ ፡ ውስተ ፡ እቶን ፡ እስከ ፡ ተለዓለ ፡ ፈድፋደ ፡ ነበልባሉ ፡ ወወገርዎ ፡ ለአባ ፡ ኤሲ. ፡ ውስቴቱ ፡ ውእቱኒ ፡ ጸለየ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ አ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ዘለከ ፡ ስብሐት ፡ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ዘአድኃንኮሙ ፡ ለ፫ቱ ፡ ደቂቅ ፡ እምእቶነ ፡ እሳት ፡ ወለዳንኤል ፡ እምአፈ ፡ አናብስት ፡ ወለሰማዕትከ ፡ ፊቅጦር፡ እምእሳት ፡ ዘቤተ ፡ ብለኔ ፡ ከማሆሙ ፡ አድኅነኒ ፡ ወፌኑ ፡ ሊተ ፡

ጥያኖስም ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ለጣዖት፡እንዲሰግድ፡አዘዘ፡ቅዱስ፡ኤሲም፡ የንግድ፡ዕቃውን፡ይሸጥ፡ዘንድ፡ወደ፡እስንድርያ፡ሔደ።

፶፩፡ ለአባ ፡ ኤሲም ፡ በእስክንድርያ ፡ አገር ጳውሎስ፡የሚባል፡ወዳጅ፡አለው፡እርሱም፡ ጽኑ፡በሆነ፡ደዌ፡ታሞ፡ነበር፡ከደዌውም፡ እስከሚድን ፡ አባ ፡ ኤሲ. ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ተቀመጠ፡በዚያም፡ወራት፡በክርስቲያን፡ ወገኖች ፡ላይ ፡ ታላቅ ፡ መከራ ፡ ሁኖ ፡ ነበር ። እኒህ ፡ የከበሩ ፡ ኤሲ.ና ፡ ወዳጁ ፡ ጳውሎስ ፡ ጣፋጭና፡መልካም፡የሆነውን፡መብል፡በገንዘባቸው ፡ እየገዙ ፡ በእስክንድርያ ፡ አገር ፡ ለሚኖሩ ፡ ቅዱሳን ፡ ይወስዳሉ ፡ እንዲሁም ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ በጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ስም ፡ የታሠሩትን ፡ ይጐበኙዋቸዋል፡ያረጋጓቸዋልም፡እንደ፡ባሮችም፡ያገለግሏቸው ፡ ነበር፡ እኒህ ፡ ቅዱሳንም ፡ የሰማዕትነት፡አክሊልን፡እናንተ፡ትቀበሉ፡ዘንድ፡ አላችሁ፡ብለው፡በእነርሱ፡ላይ፡ትንቢት፡ ተናገሩ።

፶፪፡ በዚህም፡ወራት፡የህርማኖስ፡ልጅ፡ቅዱስ፡ ፊቅጦርን ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ አገር ፡ አመጡት፡አባ፡ኤሲ.ና፡ወዳጁ፡ጳውሎስም፡ በአዩት ፡ ጊዜ ፡ አደነቁ ፡ መንፈሳዊ ፡ ቅንአትንም ፡ ቀኑበት ፡ እርሱ ፡ የዚህን ፡ የኃላፊውን፡ ዓለም ፡ መንግሥት ፡ ንቋልና ። ከዚህም፡በኋላ፡አባ፡ኤሲ.፡ወደ፡መኰንኑ፡ ቀርቦ ፡ በክብር ፡ ባለቤት ፡ በጌታችን ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ ፡ ታመነ ፣ መኰንኑም ፡ ያሠቃዩት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ በአለንጋዎችም ፡ ብዙ ፡ ግርፋትን ፡ ገረፉት ፡ ሕዋሳቱንም ፡ በሾተሎች፡ሠንጣጠቁ፡በሥጋውም፡የችቦ፡ መብራቶችን ፡ አደረጉ ፡ በሰንሰለትም ፡ አሠሩት ፡ ሁለተኛም ፡ ነበልባሉ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ከፍ፡እስከሚል፡በማንደጃ፡ውስጥ፡እሳትን፡ አነደዱ።አባ፡ኤሲ.ንም፡ከውስጡ፡ጣሉት፡ እርሱም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ጸለየ ፡ ጌትነት ፡ ገንዘብህ፡የሆነ፡ጌታዬ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ሆይ፡ሠለስቱ፡ደቂቅን፡ከነደደ፡እሳት፡ዳንኤልን፡ከአንበሶች፡አፍ፡ምስክርህ፡ፊቅጦርንም፡ከውሽባ፡ቤት፡እሳት፡ያዳንካቸው፡ አንተ፡ነህና፡እንደ፡እነርሱ፡አድነኝ፡የሚረ

www.ethiopianorthodox.org

መልአከከ ፡ ኄረ ፡ ዘይረድአኒ ፡ ወለከ ፡ ስብ
ሐት፡አሜን፡

፴፫፡ ወሶበ ፡ ጸለየ ፡ ዘንተ ፡ጸሎተ ፡ ናሁ ፡ ወረደ ፡
ሱርያል ፡መልአክ ፡ እምሰማይ ፡ ወቆመ ፡ በየ
ማኑ ፡ ለአባ ፡ ኤሲ. ፡ ድንግል ፡ ወይቤሎ ፡
ሰላም ፡ ለከ ፡ አ ፡ ብእሲ. ፡ ጻድቅ ፡ ኢ.ትፍራህ ፡
እስመ ፡እግዚአብሔር ፡ ምስሌከ ፡ ወውእቱ ፡
ያድኅነከ፡እምኵሉ፡ምንዳቤከ፡ወሶቤሃ፡ኮነ፡
እቶነ፡እሳት ፡ ከመ ፡ ጠል ፡ ቈሪር ፡ ወሠጠቀ ፡
መልአክ ፡ አረፍተ ፡ እቶን ፡ ወአኀዘ፡ እዴሁ ፡
ለቅዱስ ፡ አባ ፡ ኤሲ. ፡ ወአውጽአ ፡ ጥዑየ፡
ዘእንበለ ፡ ሙስና ፡ ወሶቤሃ ፡ ሖረ ፡ አባ ፡ ኤሲ. ፡
ኀበ ፡ መኰንን ፡ ወጸርሐ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡
ኀፈር ፡ አ ፡ መኰንን ፡ አንተ ፡ ወንጉሥከ ፡
ከሀዲ. ፡ ወጣዖታቲከ ፡ ርኵሳን ፡ ወሶበ ፡ ርእ
ይዎ ፡ ሕዝብ ፡ለአባ ፡ ኤሲ.፡ ከመ ፡ ሕያው ፡
ውእቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ሙስና ፡ አንከሩ ፡ ፈድፋደ ፡
ወጸርሑ ፡በ፩ዱቃል ፡ ወይቤሉ ፡ ንሕነ፡ ክርስ
ቲያን ፡ ገሀደ ፡ ወነአም ን ፡ በአምላኩ ፡ ለቅ
ዱስ ፡ ኤሲ. ፡ ወአዘዘ ፡ መኰንን ፡ ይምትሩ ፡
አርእስቲሆሙ፡ በሰይፍ ፡ ወነሥኡ ፡ አክሊለ ፡
ስምዕ፡በመንግሥተ፡ሰማያት።

፴፬፡ ወእምዝ ፡ አዘዘ ፡ መኰንን ፡ ይሰድዎ ፡ ለአባ ፡
ኤሲ.፡ውስተ፡ቤተ፡ሞቅሕ፡ወገብሩ፡በከመ፡
አዘዞሙ።

፴፭፡ ወአስተርአያ ፡ ለእኅቱ ፡ ቴክላ ፡ መልአከ፡እግ
ዚአብሔር ፡ ወአዘዛ ፡ ከመ ፡ ትሑር ፡ ኀበ ፡
ሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ከመ ፡ ተሐውጾ ፡
ለእኁሃ፡ አባ ፡ ኤሲ. ፡ ወተንሥአት ፡ ሶቤሃ ፡
እምሀገረ ፡ እንዴናው ፡ ወበጽሐት ፡ ኀበ ፡
ጽንፈ፡ባሕር፡ወአስተርአየት፡ላቲ፡ሐመር፡
መንፈሳዊት ፡ ወውስቴታ ፡ሀለወት ፡ እግዝ
እትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡ማርያም፡ምስለ፡
ኤልሳቤጥ፡እሙ፡ለዮሐንስ፡መጥምቅ፡ወነ
ጸረቶን፡ኀዘናተ፡ወትቤሎን፡ቴክላ፡አ፡አጋ
እዝትየ ፡ ምንትኑ ፡ ዘበጽሐ ፡ ላዕሌክን ፡
እስመ፡ እሬእየክን ፡ ኅዙናተ ፡ ወትቤላ ፡
ቅድስት፡ኤልሳቤጥ፡ሊ.ተ፡፩ወልድ፡ዘወለ
ድክዎ፡በርሥአንየ፡ወነሥእዎ፡ወሐረድዎ፡
ወእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡ማርያም፡
ትቤላ፡ሊ.ተኒ፡ወልድ፡ዋህድ፡ለውእቱኒ፡
ነሥእዎ፡ወሰቀልዎ ዲ.በ፡ዕፅ፡ወቀተልዎ፡

ዳኘንም፡ቸር፡መልአክ፡ላክልኝ፡ለአንተም፡
ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

፴፫፡ ይህንንም ፡ጸሎት ፡ በጸለየ ፡ ጊዜ ፡ እነሆ ፡
ሱርያል ፡ መልአክ ፡ ከሰማይ ፡ ወርዶ ፡ በአባ ፡
ኤሲ. ፡ ቀኝ ፡ ቆመና ፡ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ሆይ ፡
ሰላም፡ ላንተ ፡ ይሁን ፡ እግዚአብሔር ፡ ከአ
ንተ ፡ ጋር ፡ ነውና ፡ ከመከራህም ፡ ሁሉ ፡
እርሱ ፡ ያድንሃልና ፡ አትፍራ ፡ አለው ።
በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ የእሳቱ ፡ ማንደጃ ፡ እንደ ፡
ቀዝቃዛ ፡ ጠል ፡ ሆነ ፡ መልአኩም ፡ የእቶኑን ፡
ግድግዳ ፡ ሠንጠቆ ፡ የከበረ ፡ አባ ፡ ኤሲ.ን ፡
እጁን ፡ ይዞ ፡ ያለ፡ ጥፋት ፡ በጤና ፡ አወጣው ፡
በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ አባ ፡ ኤሲ. ፡ ወደ ፡ መኰንኑ ፡
ሒዶ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ፡ አንተ ፡ ከከሀዲ. ፡
ንጉሥህና ፡ ከረከሱ ፡ ጣዖቶችህ ፡ ጋር ፡ እፈር።
ሕዝቡም ፡ ሕያው ፡ ሁኖ ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ አባ ፡
ኤሲ.ን ፡ በአዩት ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ አደነቁ ፡
በአንድ ፡ ቃልም ፡ እኛ ፡ በግልጥ ፡ ክርስቲያን ፡
ነን ፡ በቅዱስ ፡ አባ ፡ ኤሲ. ፡ አምላክ ፡ እናም
ናለን ፡ ብለው ፡ ጮኹ ፡ መኰንኑም ፡ ራሶቻ
ቸውን ፡ በሰይፍ ፡ እንዲቆርጡ ፡ አዘዘ ፡ በመን
ግሥተ ፡ ሰማያትም ፡ የሰማዕትነት ፡ አክል
ሊ.ን፡ተቀበሉ።

፴፬፡ ከዚ.ህም ፡ በኋላ ፡ አባ ፡ ኤሲ.ን ፡ ወደ ፡ እሥር ፡
ቤት ፡ እንዲወስዱት ፡ መኰንኑ ፡ አዘዘ ፡ እንደ
ዘዛቸውም፡አደረጉ።

፴፭፡ ለእኅቱም ፡ ለቴክላ ፡ የእግዚአብሔር ፡
መልአክ ፡ ተገልጾላት ፡ ወንድሟን ፡ አባ ፡
ኤሲ.ን ፡ ትጐበኘው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እስክን
ድርያ ፡ አገር ፡ እንድትሔድ ፡ አዘዛት ፡ ያን ፡
ጊዜ ፡ ከእንዴናው ፡ ከተማ ፡ ተነሥታ ፡ ከባ
ሕር ፡ ዳርቻ ፡ ደረሰች ፡ መንፈሳዊት ፡ መር
ከብም ፡ ተገለጸችላት ። እመቤታችን ፡
ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያምም ፡ ከመጥምቁ፡
ዮሐንስ ፡ እናት ፡ ከኤልሳቤጥ ፡ ጋር ፡ በው
ስጧ ፡ አለች ፡ አዝነውም ፡ ተመለከተቻ
ቸውና ፡ እመቤቶቼ ፡ ሆይ ፡ የደረሰባችሁ ፡
ምንድን ፡ ነው ፡ አዝናችሁ ፡ አያለሁና ፡ አለ
ቻቸው ፡ ቅድስት ፡ ኤልሳቤጥም ፡ በእር
ጅናዬ፡ ወራት ፡ የወለድኩት ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡
ነበረኝ ፡ ወስደው ፡ አረዱብኝ ፡ አለቻት ፡ እመ
ቤታችንም ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያምም ፡
ለእኔም ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ነበረኝ ፡ እርሱንም ፡

ወትቤሎን፡ቴክላ፡አ፡አኃእዝትየ፡በአማን፡
ረከባክን ፡ ጽኑዕ ፡ ኀዘን ፡ ወእንዘ ፡ ዘንተ ፡
ይትናገራ፡አብጽሐሃ፡ኀበ፡ሀሎ፡እኁሃ፡አባ፡
ኤሲ፡ወኢያእመረት፡ከመ፡መኑ፡እማንቱ፡
ዘአስተርአያሃ።

፵፮፡ ወሶበ ፡ ርእያ ፡ አባ ፡ ኤሲ ፡ ለእኅቱ ፡ ቴክላ ፡
ተፈሥሐ ፡ ዐቢየ ፡ ፍሥሐ ፡ ወተሰነዓወት ፡
ምስሌሁ ፡ ይእቲኒ ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ ሰማዕተ ፡
ኅቡረ።

፵፯፡ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ኮነ ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ አስተ
ርአዮ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሱርያል ፡
ለቅዱስ፡አባ፡ኤሲ፡ወፆሮ፡በክነፊሁ፡ብርሃ
ናውያን ፡ ወአዕረጎ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ ወአ
ርአዮ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሰማያዊተ ፡ ወወ
ጽኡ ፡ ኵሎሙ ፡ ቅዱሳን ፡ ወተአምኅዎ ፡
ወአርአዮ ፡ ዕበያ ፡ ወክብራ ፡ ዐባየ ፡ ዘኢ
ይክል፡ልሳነ፡ሰብእ፡ይትናገር፡በእንቲአሃ፡
ወመራህብቲሃኒ፡ዘሥርግዋት፡በወርቅ፡ወበ
ዕንቍ፡ወብርሃነ፡ዘውስቴታ፡ዘይፈደፍድ፡
ምስብዒተ ፡ እደ ፡ እምብርሃነ ፡ ፀሐይ ፡ ወአ
ርአዮ ፡ ካዕበ ፡ ማኅደሮሙ ፡ ለጻድቃን ፡ ወሰ
ማዕት ፡ እለ ፡ ፃመዉ ፡ በእንተ ፡ ስሙ ፡ ለእግ
ዚእነ፡ክርስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት።

፵፰፡ ወእምዝ ፡ ወሰዶ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡
ኀበ፡ካልዕ፡መካን፡ወአርአዮ፡ጽርሐ፡ዐቢየ፡
ዘውስቴቱ ፡ ፫፻ አዕማድ ፡ ዘሥርግዋት ፡ በወ
ርቅ፡ወበዕንቍ፡ወመናብርት፡ዘሥርግዋን፡
በአዕናቍ ፡ ወውስተ ፡ ውእቱ ፡ ጽርሕ ፡ ይነ
ብሩ ፡ ፪፻ ሐራ ፡ወእሙንቱ ፡ ቅኑታን ፡ በቅ
ናተ ፡ ወርቅ ፡ ወሥርግዋን ፡ ወለለ፩፩
እምኔሆሙ ፡ ኑኁ ፡ ፲ ወ ፫ በእመት ፡ ዘኢኮነ ፡
አምሳሎሙ ፡ በውስተ ፡ ዓለም ፡ ወእቤሎ ፡
አነ፡ኤሲ፡ለመልአክ፡ለመኑ፡ዝንቱ፡ጽርሕ፡
ዐቢይ፡እስመ፡ኢይክል፡መኑሂ፡እምሰብእ፡
ዓለም ፡ ከመ ፡ ይሕንፅ ፡ አምሳለ ፡ ዝንቱ ፡
ጽርሕ።

፵፱፡ ወይቤለኒ ፡ መልአክ ፡ አ ፡ እኁየ ፡ አባ ፡ ኤሲ ፡
ለእመ፡ኵሎሙ፡ነገሥተ፡ምድር፡ተጋብኡ፡
ምስለ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፡ ኢይክሉ ፡ ሜጠ ፡
አሐዱ፡ ዓምድ ፡ እምእሉ ፡ ሠለስቱ ፡ ምእት ፡
አዕማድ፡ዘይፀውርዎ፡ለዝንቱ፡ጽርሕ፡ወአ

ወስደው ፡ ሰቅለው ፡ ገደሉብኝ ፡ አለቻት ።
ቴክላም ፡ እመቤቶቼ ፡ ሆይ ፡ በእውነት ፡
ጽኑዕ ፡ ኀዘን ፡ አግኝቷችኋል ፡ አለቻቸው ፡
ይህንንም ፡ እየተነጋገሩ ፡ ወንደሟ ፡ አባ ፡
ኤሲ ፡ ወዳለበት ፡ አደረሷት ፡ የተገለጹላት ፡
እነማን፡እንደሆኑ፡አላወቀችም፡ነበር።

፵፮፡ አባ ፡ ኤሲም ፡ እኅቱ ፡ ቴክላን ፡ በአያት ፡ ጊዜ ፡
ፈጽሞ፡ደስ፡አለው፡እርሷም፡ከእርሱ፡ጋር፡
በሰማዕትነት፡ትሞት፡ዘንድ፡ተስማማች።

፵፯፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የሌሊቱ ፡ እኩሌታ ፡ በሆነ ፡
ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡መልአክ ፡ ሱርያል ፡
ለአባ ፡ ኤሲ ፡ ተገለጸለት ፡ በብርሃናውያን ፡
ክንፎቹም ፡ ተሸክሞ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አወ
ጣው ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሰማያዊትንም ፡ አሳየው።
ቅዱሳንም ፡ ሁሉ ፡ ወጥተው ፡ ሰላምታ ፡ ሰጡት ፡
የሰው ፡ አንደበት ፡ ስለርሷ ፡ ሊናገር ፡ የማይ
ቻለው ፡ ልዕልናዋንና ፡ ክብርዋን ፡ አሳየው ፡
በወርቅ ፡ በዕንቍ ፡ ያጌጡ ፡ አደባባዮቿንም ፡
ከፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ ሰባት ፡ እጅ ፡ የሚበልጥ ፡
በውስጧ ፡ ያለውንም ፡ ብርሃን ፡ አሳየው ፡ ስለ ፡
ክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡
መከራ ፡ የተቀበሉ ፡ የጻድቃንንና ፡ የሰማዕ
ታትን፡መኖሪያንም፡ዳግመኛ፡አሳየው።

፵፰፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡
ወደ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ ወሰደውና ፡ ታላቅ ፡
አዳራሽንም ፡አሳየው ፡በውስጡም፡ በወርቅ ፡
በዕንቍ ፡ የተሸለሙ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ምሰሶ
ዎች፡አሉ፡ዙፋኖችም፡በዕንቍ፡የተሸለሙ፡
አሉ፡ በዚያም ፡ አዳራሽ ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡
መቶ ፡ ጭፍሮች ፡ ቆመው ፡ ነበር ። እነር
ሱም ፡ በወርቅ ፡ ዝናር ፡ የታጠቁና ፡ ያጌጡ ፡
ናቸው ፡ ከእርሳቸውም ፡ እያንዳንዱ ፡ ርዝ
መቱ፡ ዐሥራ፡ አምስት ፡ ዐሥራ ፡ አምስት፡
ክንድ ፡ ይሆናል ፡ እኔም ፡ ኤሲ ፡ ያንን፡ መል
አክ፡ከዓለም፡ሰዎች፡ውስጥ፡በዚህ፡አዳራሽ፡
አምሳል፡ማንም፡ሊሠራ፡የማይቻለው፡ይህ፡
አዳራሽ፡ለማን፡ነው፡አልሁት።

፵፱፡ መልአኩም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፡ ወንደሜ ፡ አባ ፡
ኤሲ ፡ ሆይ ፡ የምድር ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉም ፡
ከዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ቢሰበሰቡ ፡ ይህን ፡
አዳራሽ ፡ ከተሸከሙት ፡ ከእሊህ ፡ ከሦስት ፡
መቶ ፡ ምሰሶዎች ፡ የአንዱን ፡ ምሰሶ ፡ ሽያጭ ፡

www.ethiopianorthodox.org

፱፫፡ ወለእመ ፡ ኮነት ፡ ይእቲ ፡ ነፍስ ፡ ኃጥእተ ፡
ፈድፋደ ፡ ይወጽእ ፡ ቃል ፡ እምኀበ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ በአፉሁ ፡ ለሊቀ ፡ መላእክት ፡
ሚካኤል፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ እግዚአብሔር ፡
አኃዜ፡ ኵሉ፡ አዘዘ፡ ከመ፡ ይውርውዋ፡ ለዛቲ፡
ነፍስ፡ውስተ፡ ኵነኔ፡ ምዕረ፡ አሐተ፡ ቅጽበተ፡
ወእምዝ ፡ የሀብዎ ፡ለውእቱ ፡ ሰማዕት ፡ አው፡
ጻድቅ ፡ ዘበእንቲአሃ ፡ ተንበለ ፡ ወከመዝ ፡
ትትወሀቦ፡ ለውእቱ፡ ሰማዕት፡ አው፡ ጻድቅ፡
ውእቱኒ ፡ ይትሜጠዋ ፡ ወይወስዳ ፡ ወያጠ
ምቅዋ ፡ ውስተ ፡ ምጥማቃት ፡ ወያለብስዋ ፡
አልባስተ ፡ ሠናያነ ፡ ወያነብርዋ ፡ ዲበ ፡ ፩
መንበር ፡ እምእሉ ፡ መናብርት ፡ እለ ፡ ኮንከ ፡
ትሬእዮሙ ፡ ወይኬልልዋ ፡በአክሊል ፡ ዘኢይ
ማስን ፡ ወትትፌሣሕ ፡ ምስለ ፡ ኵሎሙ ፡
ቅዱሳን፡ወተሐዩ፡ለዓለመ፡ዓለም።
፱፬፡ወእምድኅረዝ፡ፆረኒ፡ወሜጠኒ፡ውስተ፡ቤተ፡
ሞቅሕ ፡ወተአምኀኒ ፡ ወዐርገ ፡ ሰማየ ፡ ወአነ፡
አንከርኩ፡ ፈድፋደ፡ በእንተ፡ ጸጋ፡ ዐቢይ፡ ዘይ
ትወሀብ ፡ ለእለ ፡ ይትጋደሉ ፡ በእንተ፡ ስሙ ፡
ቅዱስ።
፱፭፡ ወጸቢሖ ፡ አዘዘ ፡ መኰንን ፡ ያምጽእዎ ፡
ለቅዱስ ፡ አባ ፡ ኤሲ ፡ ምስለ ፡ እኅቱ ፡ ቴክላ ፡
ወአምጽእዎሙ፡ ወኰነንዎሙ፡ ኵነኔ፡ ዐቢየ፡
በመንኰራኵር ፡ ወበዋዕየ ፡ እሳት ፡ ወበቅ
ንዋተ፡ ኀፂን፡ ወዘሐቁ፡ አነዳ፡ አርእስቲሆሙ፡
ወእግዚአብሔር ፡ አንሥኦሙ ፡ ጥዑየ ፡ ዘእን
በለ፡ ሙስና፡ ወሶበ፡ ደክመ፡ እምኰንኖቶሙ፡
መጠዎሙ ፡ ለመኰንነ ፡ ሀገረ፡ እንዴናው ፡
ከመ ፡ ይሰዶሙ ፡ ኀበ ፡ ላዕላይ ፡ ግብጽ ፡ ወሶበ፡
ሖሩ ፡ መጠነ ፡ ፳ መዓልት ፡ ቆመት ፡ ሐመር ፡
ኀበ ፡ ጽንፈ ፡ ባሕር ፡ ወአዘዘ ፡ መኰንን ፡
ይምትሩ ፡ አርእስቲሆሙ ፡ በሰይፍ ፡
ወተፈሥሑ ፡ ቅዱሳን ፡ አባ ፡ ኤሲ ፡ ወቴክላ ፡
እኅቱ ፡ ተፈሥሑ ፡ ፈድፋደ ፡ ወጸለዩ ፡
ወፈጺሞሙ፡ ጸሎቶሙ፡ መተርዎሙ፡ አርእስ
ቲሆሙ፡ በሰይፍ።

፱፮፡ ወአዘዞ ፡እግዚአብሔር ፡ ለአሐዱ ፡ ቀሲስ ፡
ዘስሙ ፡ አሪ ፡ ዘእምሀገረ ፡ ስንጡፍ ፡ ከመ ፡
ይንሣእ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ውእቱኒ ፡
ነሥአሙ ፡ ወገነዞሙ ፡ በአልበስ ፡ ሠናያን ፡
ወበዕጣን ፡ወአንበሮሙ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡

፱፫፡ ያቺ፡ ነፍስ፡ እጅግ፡ ኃጢአተኛ፡ ከሆነች፡ ግን፡
ከእግዚአብሔር፡ዘንድ፡ ቃል፡ ይወጣል፡ በመ
ላእክት፡ አለቃ፡ በሚካኤልም፡ አፍ፡ እንዲህ፡
ተብሎ ፡ ይነገራል ፡ ሁሉን ፡ የያዘ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ይቺን ፡ ነፍስ ፡ ለአንዲት ፡ ቅጽበት ፡
አንድ ፡ ጊዜ ፡ እንዲወረውሩዋት ፡ አዘዘ ።
ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ስለርሷ ፡ ለማለደ ፡ ለዚያ ፡
ሰማዕት ፡ ወይም ፡ ለጻድቁ ፡ ይስጡት ፡ ይላል ፡
እንደዚህም ፡ ለዚያ ፡ ሰማዕት ፡ ወይም፡ ለጻ
ድቁ፡ ትሰጠዋለች፡ እርሱም፡ ተቀብሎ፡ ይወስ
ዳታል ፡ በመጠመቂያም ፡ ውስጥ ፡ ያጠም
ቋታል ፡ ያማሩ ፡ ልብሶችንም ፡ አልብሰው ፡
ከእነዚህ ፡ ከምታያቸው ፡ ዙፋኖች ፡ በአንዱ ፡
ዙፋን ፡ ላይ ፡ ያስቀምጧታል ፡ በማይጠፋ ፡
አክሊልም ፡ ይጋርዷታል ፡ ከቅዱሳን ፡ ሁሉ ፡
ጋር፡ ደስ፡ እያላት፡ ለዘላለሙ፡ ትኖራለች።
፱፬፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ያ ፡ መልአክ ፡ ተሸክሞ ፡ ወደ ፡
እሥር ፡ ቤት ፡ መለሰኝ ፡ ሰላምታም ፡ ሰጥቶኝ ፡
ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዐረገ ፡ እኔም ፡ ስለ ፡ ከበረ ፡
ስሙ፡ ለሚጋደሉ፡ ስለሚሰጥ፡ ታላቅ፡ ሀብት፡
እጅግ፡ አደነቅሁ።
፱፭፡ በነጋም ፡ ጊዜ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ ኤሲን ፡ ከእኅቱ ፡
ቴክላ ፡ ጋር ፡ ያመጡት ፡ ዘንድ ፡ መኰንኑ ፡
አዘዘ፡ አምጥተውም፡ በጽኑ፡ ሥቃይ፡ በተሽከ
ርካሪዎች ፡ መሣሪያ ፡ በእሳት ፡ ቃጠሎ ፡ በብ
ረት ፡ ችንካሮች ፡ የራሳቸውንም፡ ቆዳ ፡ በመ
ግፈፍ ፡ አሠቃዩአቸው ። እግዚአብሔርም፡
ያለ፡ ጉዳት ፡ በጤና ፡ አስነሣቸው ፡ ከሥቃያ
ቸውም ፡ የተነሣ ፡ በሰለቸ ፡ ጊዜ ፡ ወደ፡ ላይ
ኛው ፡ ግብጽ ፡ ይወስዳቸው ፡ ዘንድ ፡ ለእን
ዴናው፡ አገር፡ መኰንን፡ አሳልፎ፡ ሰጣቸው፡
ስምንት ፡ ቀንም ፡ ያህል ፡ እንደ ፡ ተጓዙ ፡
መርከቢቱ ፡ ከባሕሩ ፡ ዳር ፡ ቆመች ፡ መኰ
ንኑም ፡ ራሶቻቸውን ፡ በሰይፍ ፡ እንዲቆረጡ ፡
አዘዘ፡ ቅዱሳን፡ አባ፡ ኤሲና፡ እኅቱ፡ ቴክላም፡
እጅግ ፡ ደስ ፡ አላቸው ፡ ጸሎታቸውንም ፡ ጸል
የው ፡ በፈጸሙ ፡ ጊዜ ፡ በሰይፍ ፡ ራሶቻቸውን ፡
ቆረጧቸው።
፱፮፡ እግዚአብሔርም ፡ ስንጡፍ ፡ ከሚባል ፡ አገር ፡
ስሙ ፡ አሪ ፡ የሚባለውን ፡ ቄስ ፡ የቅዱሳንን ፡
ሥጋቸውን ፡ እንዲአነሣ ፡ አዘዘው ፡ እርሱም ፡
አንሥቶ ፡ ወስዶ ፡ አጥኖ ፡ በአማሩ ፡ ልብሶች ፡
ገነዛቸው ፡ የመከራውም ፡ ወራት ፡ እስቲፈ

ንጹሕ ፡እስከ ፡ ተፍጻሜተ ፡ መዋዕለ ፡ ስደት ፡ ወኮነ፡እምኔሆሙ፡ተአምራት፡ወመንክራት፡ ዐበይት ፡ ወኍልቆሙ ፡ ለእለ ፡ ኮኑ ፡ ሰማዕተ ፡ ምስሌሆሙ፡፬፻፸ወ፯ነፍስ።

፶፯፡ ወስብሐት ፡ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱሙ ፡ ለሰማዕት ፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ጾም፡ በንጹሕ ፡ ቦታ ፡ አኖራቸው ፡ ከእርሳቸውም፡ታላላቅ፡ተአምራት፡ተገለጡ፡ከእነርሱም ፡ ጋር ፡ በሰማዕትነት ፡ የሞቱ ፡ ቍጥራቸው ፡ አራት ፡ መቶ፡ ሰባ ፡ ሰባት ፡ ነፍስ፡ ናቸው።

፶፯፡ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡ በሰማዕታት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከታቸውም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

<u>አርኬ</u>

ሰላም ፡ እብል ፡ ለዘዚአከ ፡ ናላ ። በተሰትሮ ፡ መጥባሕት ፡ ዘሐመ ፡ ወለነድ ፡ በነበልባላ ። ኤሲ ፡ ክሉል ፡ በትርሲተ ፡ ብርሃን ፡ ቀጸላ ። ወሰላም ፡ ካዕበ ፡ ለእኅትከ ፡ ቴክላ ። በቆዐ፡ማርያም ፡ ዕፍረት ፡ ዘተቀብዐ ፡ አባላ። ሰላም ፡ ለክሙ ። ማኅበራነ ፡ ቴክላ ፡ ወኤሲ ። አንስት ፡ ዘምስለ ፡ ብእሲ ። አምሳለ ፡ አበውየ ፡ አነ ፡ እስመ ፡ ነግድ ፡ ወፈላሲ ። ከመ ፡ ታንግፉኒ ፡ እምዘ ፡ ይጸንሐኒ ፡ ከይሲ ። ውስተ ፡ ኃይልክሙ ፡ ልብየ ፡ እሬሲ ።

፶፰፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ። አብ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ዘደማስቆ ።

፶፱፡ ወውእቱ ፡ ቅዱስ ፡ ወልደ ፡ መንሱር ፡ እምክቡራኒሃ ፡ ወዐበይታ ፡ ለደማስቆ ፡ ወተሐፅነ ፡ በጥቡብ ፡ ወበፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወተምህረ ፡ ትምህርተ ፡ ፈላስፋ ፡ እምነ ፡ መምህሩ ፡ ቍልህፋ ፡ ቍልዝማዊ ፡ መነኰስ ፡ ፍልሱፍ ፡ ዘቀርሊ ፡ ወፈጺሞ ፡ ትምህርቶ ፡ ተሰነአሎ ፡ ለመምህሩ ፡ ቍልዝማዊ ፡ ወሖረ ፡ ኀበ ፡ ምኔተ ፡ ቅዱስ ፡ ማሪ ፡ ሳበ ፡ ሰማዕት ። ወሶበ ፡ አዕረፈ ፡ አቡሁ ፡ ኮነ ፡ ጸሐፌ ፡ ለመኰንነ ፡ ሀገር ፡ ወኢየኀብእ ፡ ምሥጢሮ።

፷፡ ወበውእቱ ፡ መዋዕል ፡ ተንሥአ ፡ ቄስጠንጢኖስ ፡ ወልደ ፡ ልዮን ፡ ዐላዊ ፡ ወተጻብአ ፡ በእንተ ፡ ሥዕላት ፡ አምላካውያት ፡ ወሆከ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ወዘንቱ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ እንዘ ፡ አልቦ ፡ ሢመት ፡ ዘቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኮነ ፡ ዘይጽሕፍ ፡ ወይፌኑ ፡ መልእክተ ፡ ኀበ ፡ ኵሎሙ ፡ መሐይምናን ፡ እንዘ ፡ ያጸንዖሙ፡ በሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ወከመ ፡ ይደሉ ፡ ሰጊድ ፡ ለሥዕላት ፡ አምላካውያት ፡ እንዘ ፡ ያመጽእ ፡ ስምዐ ፡ እምጸሕፍት ፡ ቅዱሳት።

፷፩፡ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ቄስጠንጢኖስ ፡ ዐላዊ ፡ ዘንተ ፡ ሐቀየ ፡ ስነኒሁ ፡ ወኃሠሠ ፡ ጸሐፌ ፡ ዘይጽሕፍ፡ በአምሳለ ፡ ብርዓ ፡ ዮሐንስ ፡ ወአጽሐፎ ፡ በአምሳለ ፡ ብርዐ ፡ ዮሐንስ ፡ እንዘ፡ ይብል ፡ እስመ ፡ ዮሐንስ ፡ ዘሀሎ ፡

፶፰፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ በደማስቆ ፡ የተከበረ ፡ አባት ፡ አባ፡ዮሐንስ፡አረፈ፤

፶፱፡ ይህም ፡ ቅዱስ ፡ ከደማስቆ ፡ ከከበርቴዎቿና ፡ ከታላላቆቿ ፡ ወገን ፡ መንሱር ፡ ለሚባል ፡ ሰው፡ ልጅ፡ ነው፡ በጥበብና፡ በፈሪሀ፡እግዚአብሔርም ፡ አደገ ፡ የቀርሊ ፡ ፈላስፋ ፡ ከሆነ ፡ ቍልህፋ ፡ ከሚባል ፡ ቁልዝማዊ ፡ መነኰስ ፡ መምህሩ ፡ ዘንድ ፡ የፍልስፍና ፡ ትምህርትን ፡ ተማረ፡ ትምርቱንም፡ ሲጨርስ፡ ቁልዝማዊ፡ መምህሩን ፡ ተሰናብቶ ፡ ወደ ፡ ከበረ ፡ ሊቀ ፡ ሳበ ፡ ሰማዕት ፡ ገዳም ፡ ሔደ ። አባቱም ፡ በሞተ፡ ጊዜ ፡ ለአገረ ፡ ገገርው ፡ ጸሐፊ ፡ ሆነ ፡ ግን፡ምሥጢሩን፡አይሠውርም።

፷፡ በዚያንም ፡ ወራት ፡ የከሀዲው ፡ ልዮን ፡ ልጅ ፡ ቄስጠንጢኖስ፡ ተነሥቶ፡ በአምላክ ፡ ፈቃድ፡ ስለተሣሉ ፡ ሥዕሎች ፡ ጸብ፡ በማንሣት ፡ አብያተ፡ክርስቲያናትን፡አወከ፡ ይህም፡ አባ፡ ዮሐንስ ፡ የቤተክርስቲያን ፡ ሹመት ፡ ሳይኖረው፡ በቀናች፡ ሃይማኖት፡ እያጸናቸው፡ በአምላክ ፡ ፈቃድ ፡ ለተሣሉ ፡ ሥዕሎችም ፡ ስግደት ፡ እንደሚገባ ፡ መስክር ፡ ከቅዱሳት ፡ መጽሕፍት ፡ እያመጣ ፡ የሚጽፍና ፡ ወደ ፡ ምእመናን፡ሁሉ፡የሚልክ፡ሆነ።

፷፩፡ ከሀዲው ፡ ቄስጠንጢኖስም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ጥርሱን ፡ አፋጨ ፡ በዮሐንስ ፡ ብርዕ ፡ አምሳል፡ የሚጽፍ ፡ ጸሐፊንም ፡ ፈልጎ ፡ በዮሐንስ ፡ ብርዕ ፡ አምሳያ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አጻፈ ፡ ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ ያለ ፡ ዮሐንስ ፡ ከአንተ፡ ጋር ፡ ተዋግቼ ፡ አገርህን ፡ እማርክ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ኀቢከ፡ ፈነወ ፡ ሊተ ፡ ዘንተ ፡ ክታበ ፡ ከመ ፡
እጸባእ ፡ ምስሌከ ፡ ወእማህርከ ፡ ሀገረከ ፡
ውእቱ፤ ፡ ሰሚዖ ፡ አምነ ፡ እስመ ፡ መሰሎ ፡
እሙነ ፡ ወመተረ ፡ እዴሁ ፡ ዘየማን ፡ ለአባ ፡
ዮሐንስ፡ዘኮነ፡ይጽሕፍ፡ባቲ።

፳፪፤ ወነሚኦ ፡ ምትርተ ፡ እዴሁ ፡ ሖረ ፡ አባ ፡
ዮሐንስ ፡ ኀበ ፡ ሥዕላ ፡ ለእግዝእትነ ፡
ቅድስት፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ወሰአላ ፡
በአንብዕ ፡ ጽፉቅ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ኦ ፡ እግዝ
እትየ ፡ አኮኑ ፡ ሶበ ፡ ተጸባእኩ ፡ በእንተ ፡
ሰጊድ፡ ለሥዕልኪ ፡ ዘበጽሐኒ ፡ ዝንቱ ፡
ወይእዜኒ ፡ ፈውስኒ ፡ በኂሩትኪ ፡ እስመ ፡
ከሀሊት ፡ አንቲ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ግብር ፡
ወዘንተ፡ ብሂሎ፡ ኖመ ፡ ወአስተርአየቶ ፡ እግ
ዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡
ወሜጠት ፡ሎቱ ፡ እዴሁ ፡ ከመ ፡ ቀዳሚ ፡
ወነቂሖ፡ ረከባ፡ ድኅንተ ፡ ወሰብሐ፡ ለእግዚ
አብሔር ፡ ወአእኰታ ፡ ለእግዝእትነ ፡
ቅድስት፡ ድንግል፡ማርያም።

፳፫፤ ወእምዝ ፡ ሖረ ፡ ኀበ ፡ ምኔት ፡ ወመንኰሰ ፡
ወአበ ፡ ምኔት ፡ መጠዎ ፡ ለ፩አረጋዊ ፡
መንፈሳዊ ፡ ከመ ፡ ይምሀሮ ፡ ሥርዓተ ፡
ምንኵስና፡ወአረጋዊ፡ይቤሎ፡ኦ፡ወልድየ፡
ዮሐንስ ፡ ኢትግበር ፡ ምንተኒ ፡ እምትምህ
ርትከ ፡ አፍአዊት ፡ ዳዕሙ ፡ ተመሀር ፡
አርምሞ ፡ ወእምብዝኀ፡ ትሕትናሁ ፡ ሞዖ ፡
ለሰይጣን።

፳፬፤ ወበአሐቲ ፡ እመዋዕል ፡ አዕረፈ ፡ አሐዱ ፡
አረጋዊ ፡ እምነ ፡ መነኮሳት ፡ ወሰአልዎ ፡
አኃው ፡ ለአባ ፡ ዮሐንስ ፡ ከመ ፡ ያውጽእ ፡
ሎቱ፡ ሰቆቃወ ፡ በእንተ ፡ እኁሆሙ ፡
ወይቤሎሙ፡አባ፡ዮሐንስ፡አንሰ፡እፈርሀ፡
እምትእዛዘ ፡ መምህርየ ፡ አረጋዊ ፡
ወይቤልዎ፡ ኢይትከሠት፡ ለመኑሂ ፡ ወሶበ፡
አብዝኁ ፡ አስተብቍዖተ ፡ ደረሰ ፡ ሎቱ ፡
ሰቆቃወ ፡ ማኅዘኒተ ፡ ለዘይሰምዓ ፡
ወአእሚሮ፡ መምህሩ ፡ ተምዐ ፡ ላዕሌሁ ፡
ወሰደዶ፡እማኅደሩ፡ወውእቱ፡አባ፡ዮሐንስ፡
ተማሕፀነ ፡ ኀበ ፡ ኵሎሙ ፡ አረጋውያን ፡
ወሶበ ፡ አገበርዎ ፡ ለአረጋዊ ፡ ይቤሎሙ ፡
ለእመ ፡ ኰስተረ ፡ ቤተ ፡ ማይ ፡ እምሕሮ ፡
ወሰሚዖ፡አባ፡ዮሐንስ፡ገብረ፡በከመ፡አዘዞ፡
መንፈሳዊ ፡ መምህሩ ፡ ውእቱ፤፡ ርእዮ ፡

ዘንድ ፡ ይህን ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፎ ፡ ላከልኝ ፡ ብሎ ፡
በወንጀል ፡ ለደማስቆ ፡ ገዥ ፡ ላከለት ፡ በሰማ ፡
ጊዜም ፡ እውነት ፡ ስለ ፡ መሰለው ፡ የሚጽ
ፍባት ፡ ቀኝ ፡ እጁን ፡ ቆረጠው።

፳፪፤ አባ ፡ ዮሐንስም ፡ የተቆረጠች ፡ እጁን ፡ ይዞ ፡
ወደ ፡ እመቤታችን ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡
ማርያም ፡ ሥዕል ፡ ሒዶ ፡ በብዙ ፡ ዕንባ ፡
እንዲህ ፡ ብሎ ለመናት ፡ እመቤቴ ፡ ሆይ ፡
ለሥዕልሽ ፡ መስገድ ፡ ስለሚገባ ፡ በተጣለሁ ፡
ጊዜ ፡ አይደለምን ፡ ይህ ፡ መቆረጥ ፡ የደረ
ሰብኝ ፡ አሁንም ፡ በቸርነትሽ ፡ ፈውሺኝ ፡
አንቺ ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ችሎታ ፡
አለሽና ፡ ይህንንም ፡ ብሎ ፡ ጥቂት ፡ አንቀላፋ።
በእንቅልፉም ፡ ሳለ ፡ እመቤታችን ፡ ቅድስት ፡
ድንግል ፡ ማርያም ፡ ተገለጸችለትና ፡ እጁን ፡
እንደ ፡ ቀድሞው ፡ መለሰችለት ፡ በነቃም ፡
ጊዜ ፡ ድና ፡ አገኛት ፡ እግዚአብሔርንም ፡
አመሰገነው ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ እመቤ
ታችን ፡ ማርያምንም ፡ አመሰገናት።

፳፫፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ገዳም ፡ ሒዶ ፡ መነኰሰ ፡
አበ ፡ ምኔቱም ፡ የምንኵስናን ፡ ሥርዓት ፡ ያስ
ተምረው ፡ ዘንድ ፡ ለአንድ ፡ ሽማግሌ ፡
መንፈሳዊ ፡ አባት ፡ ሰጠው ፡ ሽማግሌውም ፡
ልጄ ፡ ዮሐንስ ፡ ሆይ ፡ አፍአዊት ፡ ከሆነች ፡
ትምርትህ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ አታድርግ ፡ ግን ፡
ዝምታን ፡ ተማር ፡ አለው ፡ ከትሕትናውም ፡
ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ሰይጣንን ፡ ድል ፡ ነሣው።

፳፬፤ ከዕለታትም ፡ በአንዲቷ ፡ ከመነኰሳቱ ፡
አንዱ፡ ሽማግሌ ፡ ሞተ ፡ መነኰሳቱም ፡ ስለ ፡
ወንድማቸው ፡ ሙሾ ፡ እንዲአወጣለት ፡ አባ ፡
ዮሐንስን ፡ ለመኑት ፡ አባ ፡ ዮሐንስም ፡ ከሽማ
ግሌው ፡ መምህሬ ፡ ትእዛዝ ፡ የተነሣ ፡ እኔ ፡
እፈራለሁ ፡ አላቸው ፡ ለማንም ፡ አይገለጥም ፡
አሉት ፡ ምልጃንም ፡ በአበዙበት ፡ ጊዜ ፡
ለሚሰማት ፡ ሁሉ ፡ የምታሳዝን ፡ ሙሾ ፡
ደረሰ፡ መምህሩም ፡ አውቆ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡
ተቆጣ ፡ ከበዓቱም ፡ አባረረው ፡ እርሱም ፡
አባ፡ ዮሐንስ ፡ ወደ ፡ አረጋውያን ፡ ሁሉ ፡
ተማጠነ ፡ ሽማግሌውንም ፡ ይቅር ፡ እንዲያ
ደርግ ፡ ግድ ፡ በአሉት ፡ ጊዜ ፡ የመነኰሳቱን ፡
የመፀዳጃ ፡ ቤት ፡ የጠረገ ፡ እንደሆነ ፡ እምረ
ዋለሁ ፡ አለ ፡ አባ ፡ ዮሐንስም ፡ ሰምቶ ፡
መንፈሳዊ ፡ መምህሩ ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረገ ፡

www.ethiopianorthodox.org

የውሃቶ፡ወትሩፋቲሁ፡ተቀበሎ፡በፍሥሐ፡ ወአብአ፡ውስተ፡ማኅደሩ።

፳፩፡ ወእግዝእትነ ቅድስት፡ድንግል፡ማርያም፡ አዘዘቶ ፡ ለአረጋዊ ፡ መምህሩ ፡ ከመ ፡ ኢይክልአ ፡ ደሪሰ ፡ ድርሳናት ፡ ወእምዝ ፡ ደረሰ፡ድርሳናተ፡ብዙኃተ፡ወሊቀ፡ጳጳሳት፡ ዘኢየሩሳሌም፡ሜሞ፡ቀሲስ፡ወነበረ፡እንዘ፡ ይትጋደል፡በእንተ፡ክብረ፡ሥዕላት፡አምላ ካውያት፡ወበእንተ፡ሃይማኖት፡ርትዕት፡ እንዘ ፡ ይዛለፎሙ ፡ ለነገሥት ፡ ወለመኳ ንንት፡ወበጺሖ፡ኀበ፡ርሥእና፡ፈለሰ፡ኀበ፡ ክርስቶስ፡ዘአፍቀሮ።

፳፪፡ ወስብሐት ፡ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ፡በጸሎቱ፡ለጻድቅ፡ወበረከቱ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

እርሱም ፡ ቅንነቱንና ፡ ትሩፋቱን ፡ አይቶ ፡ በደስታ ፡ ተቀብሎ ፡ ወደ ፡ ማደሪያው ፡ አስገባው።

፳፩፡ እመቤታችን ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያምም፡ አረጋዊ ፡ መምህሩን ፡ ድርሳ ናትን ፡ መድረስን ፡ እንዳይከለክለው ፡ አዘዘችው፡ከዚህም፡በኋላ፡ብዙ፡ድርሳናት፡ ደረሰ ፡ የኢየሩሳሌሙም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ቅስና ፡ ሾመው ፡ በአምላክ ፡ ፈቃድ ፡ ስለ ፡ ተሣሉ፡ሥዕሎች፡ክብር፡ስለ፡ቀናች፡ሃይማ ኖትም፡ነገሥታቱንና፡መኳንንቱን፡ሲዘል ፋቸው፡ኖረ፡ወደ፡ሽምግልናም፡በደረሰ፡ ጊዜ፡ወደ፡ወደደው፡ክርስቶስ፡ ሔደ

፳፪፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም፡ በጻድቁ ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ እብል፡ እንዘ፡እነግር፡ጽድቀ፡ለዮሐንስ፡ ዘደማስቆ። ሶበ፡መምህሩ፡አረጋዊ፡እምደሪሰ፡ ድርሳን፡አስተርኀቆ።አኀደገቶማርያም፡ በዘይፌጽም፡ጸሕቆ።እስከ፡በርሥአን፡ጥሉል፡አዕረፈ፡አልጺቆ።

፳፫፡ ወበዛቲ፡ዕለት፡አዕረፈ፡አበ፡ቅዱስ፡ተክለ፡ አልፋ፡ አበ፡ምኔት፡ዘደብረ፡ድማሕ፡ወዓዲ፡ ዕረፍቱ ለገብረ፡ማርያም፡ ጻድቅ፡ተአማኒ፡ በክርስቶስ ፡ ወውእቱ ፡ ዘይገብር ፡ ተዝካሮሙ፡ ለሰማዕታት፡ወጻድቃን፡ለለ፩ በዕለተ፡ዕረፍቶሙ፡በአጽግቦ፡ርኁባን፡ወበ አልብሶ፡ዕሩቃን።

፳፬፡ ወእንዘ፡ሀሎ፡በዘከመዝ፡ግብር፡አሚሃ፡ መጽኡ፡ተንባላት፡ውስተ፡ሀገረ፡ሸዋ፡ ውእቱኒ፡ለብሰ፡አልባሰ፡ሠናያነ፡ወሖረ፡ ወቦአ ስተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ወጸለየ፡ ጸሎተ፡ወእንዘ፡ይጼሊ፡መጽኡ፡ኀቤሁ፡ ተንባላት ፡ ወመተሩ ፡ ርእሶ ፡ በሰይፍ ፡ ወነሥአ፡አክሊለ፡ስምዕ፡በመንግሥተ፡ ሰማያት።

፳፭፡ ወስብሐት ፡ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ፡በጸሎተ፡ኵሎሙ፡ቅዱሳን፡ወበ ረከቶሙ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡ አሜን።

፳፫፡ በዚችም፡ቀን፡የደብረ፡ድማሕ፡ገዳም፡አበ፡ ምኔት፡ቅዱስ፡አባት፡ተክለ፡አልፋ፡አረፈ። ዳግመኛም ፡በክርስቶስ ፡ የሚታመን ፡ የገብረ፡ማርያም፡ ዕረፍቱ፡ነው፡እርሱም፡ የሰማዕታትንና ፡ የጻድቃንን ፡ በየዕረፍ ታቸው ፡ ቀን ፡ ለየአንዳዱ ፡ ርኁባንን ፡ በማጥገብ፡የተራቆቱትን፡በማልበስ፡መታ ሰቢያቸውን፡የሚያደርግ፡ነው።

፳፬፡እንዲህም፡ባለ፡ሥራ፡ላይ፡እያለ፡ይን፡ጊዜ፡ እስላሞች፡ወደ፡ሸዋ፡አገር፡መጡ፡እርሱም፡ ያማሩ ፡ ልብሶችን ፡ ለብሶ ፡ ወደቤተክርስ ቲያን ፡ ሔዶ ፡ ገብቶ ፡ ጸሎትን ፡ ጸለየ ፡ ሲጸልይም፡እስላሞች፡ወደርሱ፡መጥተው፡ ራሱን፡በሰይፍ፡ቆረጡት፡የሰማዕትነት፡ አክሊልንም ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ተቀበለ።

፳፭፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም፡በቅዱሳን፡ሁሉ፡ጸሎት፡ይማረን፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ፡አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩አምላክ ፡ አመ ፡ ፲ወ፩ለታኅሣሥ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ በአሚን ፡ ተአማኒ ፡ ዘኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ ዘእንበለ ፡ ክዕወተ ፡ ደም።

፪፡ ወውእቱ ፡ ዘእምደቂቀ ፡ ሐዊብ ፡ ዘእምደቡብ ፡ ግብጽ ፡ እምደወለ ፡ እስሙናይን ፡ ቅሩበ ፡ ሀገረ ፡ ቴርሳ ፡ ወኮነ ፡ መጋቢሁ ፡ ለ፩ባዕል ፡ ወኮነ ፡ ፍቁረ ፡ በኀበ ፡ ኵሉ ፡ በእንተ ፡ ንጽሕናሁ ፡ ወቅድስናሁ ፡ ወብእሲቱኒ ፡ ለባዕል ፡ ኮነት ፡ ዘታፈቅሮ ፡ ፈድፋደ ፡ ለአባ ፡ በአሚን ፡ ወትትአመኖ።

፫፡ ወእቱሰ ፡ አባ ፡ በአሚን ፡ ሐለየ ፡ ማኅለቅተ ፡ ገዘንቱ ፡ ዓለም ፡ ወኀደገ ፡ መልእክቶ ፡ ለባዕል ፡ ወሖረ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ ወመንኰሰ ፡ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ውእቱ ፡ ባዕል ፡ ከመ ፡ ኀደጎ ፡ አባ ፡ በአሚን ፡ ኀዘነ ፡ ጥቀ ፡ ወነሥአ ፡ ለብእሲቱ ፡ ወሖሩ ፡ ኀበረ ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፡ አባ ፡ በአሚን ፡ ወሰአልዎ ፡ ከመ ፡ ይትመየጥ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ወይቤልዎ ፡ ንሕነ ፡ ኢይትከሀለነ ፡ ግሙራ ፡ ንትፈለጥ ፡ እምኔከ ፡ ወኢነኀድገከ ፡ በእንተዝ።

፬፡ ወይቤሎሙ ፡ አባ ፡ በአሚን ፡ እስመ ፡ እንሰ ፡ አብፃዕኩ ፡ ርእስየ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወሰሚዖሙ ፡ ዘንተ ፡ ኀደግዎ ፡ ወገብኡ ፡ አንዘ ፡ የኀዝኑ ፡ በእንተ ፡ ተፈልጠቶሙ ፡ እምኔሁ።

፭፡ ወእምዝ ፡ አኀዘ ፡ ይትጋደል ፡ ተጋድሎ ፡ ዐቢየ ፡ በኵሉ ፡ ገድል ፡ ሠናይ ፡ ወተጸምዶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብዙኀ ፡ አዝማነ ፡ ወእምዝ ፡ ሠምረ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ሰማዕተ ፡ ወይክዕው ፡ ደሞ ፡ በእንተ ፡ ስሙ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ሖረ ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ እንዴናው ፡ ወረከቦሙ ፡ ለብዙኃን ፡ ምእመናን ፡ እንዘ ፡ ይኴንንዎሙ ፡ ወተአመነ ፡ ውእቱኒ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወኰነንዎ ፡ ኵነኔ ፡ ጽኑዐ ፡ ወአውዓዩ ፡ ሥጋሁ ፡ በእሳት ፡ ወሠተርዎ ፡ መለያልያቲሁ ፡ ወወደይዎ ፡ ውስተ ፡ መንኰራኵር ፡ ወዓዲ ፡ አውዓይዎ ፡ በአብትረ ፡ ኀፂን ፡ ዘአርሰንዎ ፡ በእሳት ፡ በዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ ኮነ ፡ ጽኑዐ ፡ ወእግዚእነ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ያንሥእ ፡ ጥዑየ ፡ ዘእንበለ ሙስና።

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ታኅሣሥ ፡ ፲፩ ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ያለ ፡ ደም ፡ መፍሰስ ፡ ታማኝ ፡ የሆነ ፡ ቅዱስ ፡ አባት ፡ አባ ፡ በአሚን ፡ በሰማዕትነት ፡ አረፈ።

፪፡ እርሱም ፡ በደቡብ ፡ ግብጽ ፡ በእስሙናይን ፡ አውራጃ ፡ ለሀገረ ፡ ቴርሳ ፡ አቅራቢያ ፡ ከሆኑ ፡ ከሐዊብ ፡ ተወላጆች ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ለአንድ ፡ ባለጸጋም ፡ በጅሮንድ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ስለ ፡ ንጽሕናውና ፡ ስለ ፡ ቅድስናው ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ተወዳጅ ፡ ሆነ ፡ የባለ ፡ ጸጋውም ፡ ሚስት ፡ አባ ፡ በአሚንን ፡ እጅግ ፡ የምትወደውና ፡ የምትተማመንበት ፡ ሆነች።

፫፡ እርሱ ፡ ግን ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ አሰበ ፡ የባለ ጸጋውንም ፡ አገልግሎት ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ገዳም ፡ ሒዶ ፡ መነኰሰ ፡ ባለጸጋውም ፡ መሔዱን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ አዘነ ፡ ሚስቱንም ፡ ይዞ ፡ አባ ፡ በአሚን ፡ ወዳለበት ፡ በአንድነት ፡ ሔዱ ፡ ወደ ፡ እርሳቸው ፡ እንዲመለስም ፡ ለመኑት ፡ እንዲህም ፡ አሉት ፡ ከአንተ ፡ እንለይ ፡ ዘንድ ፡ ከቶ ፡ አንችልም ፡ ስለዚህ ፡ አንተውህም ፡ አሉት።

፬፡ አባ ፡ በአሚንም ፡ እኔ ፡ ራሴን ፡ ብፅዓት ፡ አድርጌ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰጥቻለሁ ፡ እኮን ፡ አላቸው ፡ ይህንንም ፡ ሲሰሙ ፡ ከእርሱ ፡ በመለያታቸው ፡ እያዘኑ ፡ ትተውት ፡ ተመለሱ።

፭፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በአማረ ፡ ተጋድሎ ፡ ሁሉ ፡ ታላቅ ፡ ተጋድሎን ፡ በመጋደል ፡ ብዙ ፡ ዘመናት ፡ እግዚአብሔርን ፡ አገለገለው። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ ስለ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ምስክር ፡ ሁኖ ፡ ደሙን ፡ ሊአፈስ ፡ ወዶ ፡ ወደ ፡ እንዴናው ፡ ከተማ ፡ ሒደ ፡ ብዙዎች ፡ ምእመናንንም ፡ ሲአሠቃዩአቸው ፡ አገኛቸው ፡ እርሱም ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ታመነ ፡ ጽኑ ፡ ሥቃይንም ፡ አሠቃዩት ፡ ሥጋውን ፡ በእሳት ፡ ለበለቡ ፡ ሕዋሳቱንም ፡ ሠነጣጥቀው ፡ ከመንኰራኵር ፡ ውስጥ ፡ ጨመሩት ፡ ዳግመኛም ፡ በአጋሏቸው ፡ የብረት ፡ ዘንጎች ፡ አቃጠሉት ፡ በዚህም ፡ ሁሉ ፡ ጸና ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ ጌታችን ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ በጤና ፡ ያስነሣው ፡ ነበር።

www.ethiopianorthodox.org

፮፡ ወእንዘ፡ ከመዝ፡ ይትኴነን፡ ኀለፈ፡ መዋዕለ፡ አምልኮ፡ ጣዖት፡ ወነግሠ፡ ቈስጠንጢኖስ፡ ጻድቅ ፡ ወአዘዘ ፡ ከመ ፡ ያውጽእዎሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ሙቁሐነ ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ በእንተ ፡ ስሙ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ ሎቱ፡ ስብሐት፡ ወእግዚእነሂ፡ አስተርአዮ፡ ለአባ፡ በአሚን፡ ወአጠየቆ፡ ከመ፡ ውእቱ፡ ኍለቆ፡ ምስለ፡ ሰማዕታት።

፯፡ ወንጉሥሰ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ አዘዘ ፡ ከመ ፡ ያምጽኡ ፡ ኀቤሁ ፡ እምኔሆሙ ፡ ፸ወ፪ተ ፡ ሙቁሐነ ፡ አረጋውያነ ፡ ከመ ፡ ይትባረክ ፡ እምኔሆሙ፡ ወሀሎ፡ ህየ፡ ምስሌሆሙ፡ አባ፡ ኖብ ፡ ወዝንቱኒ ፡ አባ ፡ በአሚን ፡ አሐዱ ፡ እምኔሆሙ።

፰፡ ወእምዝ ፡ ኮነ ፡ ዘየኀድር ፡ ውስተ ፡ ደብር ፡ ዘአፍአ ፡ ሀገረ ፡ እስሙናይን ፡ ወወሀቦ ፡ እግዚእነ፡ ጸጋ፡ ዐባየ፡ ወኮነ፡ ዘይፌውሶሙ፡ ለድውያን፡ ወተሰምዐ፡ ዜናሁ፡ ውስተኵሉ፡ መካን።

፱፡ ወበውእቱ ፡ መዋዕል ፡ ሀለወት ፡ አሐቲ ፡ ንግሥት፡ ብእሲቱ፡ ለንጉሠ፡ ሮም፡ ወይእቲ፡ ደወየት፡ ፈድፋደ፡ በእንተ፡ ፩ዲያቆን፡ ፈራሄ፡ እግዚአብሔር፡ ዘይሄሉ፡ ምስሌሃ፡ ወያነብር፡ ላቲ ፡ ኵለሂ ፡ መጽሐፈ ፡ ራእዩ ፡ ለዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ፡ ወቀንአ፡ ላዕሌሁ፡ እምነ፡ መገብቱ፡ ለንጉሥ ፡ ወሖረ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ወይቤሎ ፡ አእምር ፡ አ ፡ እግዚእየ ፡ ንጉሥ ፡ እስመ ፡ ዮሐንስ፡ ዲያቆን ፡ ይሰክብ ፡ ምስለ ፡ እግዝእትየ፡ ንግሥት ፡ ብእሲትከ፡ እንዘ፡ ያመከኒ፡ በአንብቦ፡ መጸሐፈ፡ ራእየ፡ ዮሐንስ፡ ኵሎ፡ አሚረ።

፲፡ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ንጉሥ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡ ኀዘነ ፡ ፈድፋደ፡ ወተንሥአ፡ ሶቤሃ፡ ወቦአ፡ ውስተ፡ ጽርሐ፡ መንግሥቱ፡ ኀበ፡ ሀለወት፡ ንግሥት፡ ወረከቦ፡ ለውእቱ፡ ዲያቆን፡ እንዘ፡ ይቀውም፡ ቅድሜሃ ፡ ወያነብብ ፡ መጽሐፈ ፡ ራእየ ፡ ዮሐንስ፡ወአዘዘ፡ከመ፡ይንሥእዎ፡ለውእቱ፡ ዲያቆን ፡ ወያሥጥምዎ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ ወነሥእዎ ፡ ፪ቱ ፡ ዕደው ፡ ወጾዓንዎ ፡ ዲበ ፡ ንኡስ፡ ሐመር፡ ወወረውዎ፡ ማዕከለ፡ ባሕር፡ ወበጊዜሃ፡ ወረደ፡ ብእሲ ብርሃናዊ፡ ወመሠጦ፡ ለውእቱ ፡ ዲያቆን ፡ ምስለ ፡ መጽሐፉ ፡

፮፡ እንዲህም፡ እየተሠቃየ፡ ሳለ፡ ጣዖት፡ የሚመለክበት ፡ ወራት ፡ አለፈና ፡ ጻድቅ ፡ ቈስጠንጢኖስ፡ ነገሠ፡ ክብር፡ ይግባውና፡ በጌታችን፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ያሠራቸውን ፡ እሥረኞች ፡ ሁሉ ፡ እንዲፈቷቸው ፡ አዘዘ ፡ ጌታችንም ፡ ለአባ ፡ በአሚን ፡ ተገለጠና፡ ከሰማዕታት፡ ጋር፡ እንደቈጠረው፡ አስረዳው።

፯፡ ንጉሥ፡ ቈስጠንጢኖስም፡ ከእሳቸው፡ ቡራኬ፡ ሊቀበል ፡ ሽቶ ፡ ከውስጣቸው ፡ ሰባ ፡ ሁለት ፡ እሥረኞችን፡ ወደርሱ፡ ያመጡ፡ ዘንድ፡ አዘዘ፡ አባ፡ ኖብ፡ ከእርሳቸው፡ ጋር፡ በዚያ፡ ነበረ፡ ከእርሳቸውም፡ አንዱ፡ ይህ፡ አባ፡ በአሚን፡ ነው።

፰፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከእሥሙናይን ፡ ውጭ ፡ በሆነች ፡ ገዳም ፡ የሚኖር ፡ ሆነ ፡ ጌታችንም ፡ ታላቅ ፡ ጸጋን ፡ ሰጥቶት ፡ በሽተኞችን ፡ ሁሉ ፡ የሚፈውሳቸው ፡ ሆነ ፡ ዜናውም ፡ በቦታው ፡ ሁሉ ፡ ተሰማ።

፱፡ በዚያም ፡ ወራት ፡ የሮም ፡ ንጉሥ ፡ ሚስት ፡ የሆነች፡ አንዲት፡ ንግሥት፡ ነበረች፡ እርሷም፡ ከእርሷ ፡ ጋር ፡ ስለሚኖር ፡ የወንጌላዊውን ፡ ዮሐንስ፡ የራእዩን፡ መጽሐፍ፡ ሁል፡ ጊዜ፡ የሚያነብላት ፡ የሆነ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ስለሚፈራ ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ ዲያቆን ፡ እጅግ ፡ የታመመች ፡ ናት ፡ ከንጉሥ ፡ ሹሞች ፡ አንዱ ፡ በቀናበት ፡ ጊዜ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ሒዶ ፡ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ፡ ዕወቅ ፡ ይህ ፡ ዲያቆን ፡ ዮሐንስ ፡ ሁል ፡ ጊዜ፡ የዮሐንስ ፡ የራእዩን ፡ መጽሐፍ ፡ በማንበብ ፡ እያመካኘ ፡ ከእመቤቴ ፡ ንግሥት ፡ ጋር፡ ይተኛል፡ አለው።

፲፡ ንጉሡም ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ አዘነ ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ተነሥቶ ፡ ንግሥቲቱ ፡ ወዳለችበት ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ገባ ፡ ያንንም ፡ ዲያቆን ፡ በፊቷ ፡ ቁሞ ፡ የዮሐንስን ፡ የራእይ ፡ መጽሐፍ ፡ ሲያነብ ፡ አገኘውና ፡ ከነመጽሐፉ ፡ ወስደው ፡ ዲያቆኑን ፡ ከባሕር ፡ እንዲአሠጥሙት ፡ አዘዘ ፡ ሁለት ፡ ሰዎችም ፡ በታናሽ ፡ ጀልባ ፡ ጭነው ፡ ወስደው ፡ ከባሕር ፡ መካከል ፡ ወረወሩት ፡ ወዲያውኑ ፡ ብርሃንን ፡ የለበሰ ፡ ሰው ፡ ከሰማይ ፡ ወርዶ ፡ ያንን ፡ ዲያቆን ፡ ከመጽሐፉ ፡ ጋር ፡ ነጥቆ ፡ ወስዶ ፡ ከአንዲት ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወወሰዶ፡ ወአንበሮ ፡ ውስተ ፡ አሐቲ ፡ ደሴት ፡
እንዘ ፡ ይሬእዩ ፡ እሉ ፡ ፪ቱ ፡ ዕደው ፡
ወተመይጡ፡ እንዘ ፡ ያነክሩ ፡ ፈድፋደ ፡ ወኢነ
ገርዎ፡ለንጉሥ፡ዘርእዩ።
፲፩፡ ወንግሥትሰ ፡ ሶበ ፡ ርእየት ፡ በውእቱ ፡
ዲያቆን፡ ዘተገብረ ፡ ኀዘነት ፡ ፈድፋደ ፡
ወጸንዐ ፡ ላዕሌሃ ፡ ደዌ ፡ ወቈስለ ፡ ከርሣ ፡
ወነበረት ፡ ፲ወ፰ተ ፡ ዓመተ ፡ ወመጽኡ ፡
ኀቤሃ፡ ብዙኃን ፡ ጠቢባን ፡ ወኢክህሉ ፡
ፈውሶታ ፡ ወአምከሩ ፡ አሐዱ ፡ ማእምር ፡
ወይቤላ፡ለእመ፡ሖርኪ፡ኀበ፡ቅዱሳን፡እለ፡
ብሔረ፡ግብጽ፡እምተፈወስኪ፡እምደዌኪ፡
ወተንሥአት ፡ ሶቤሃ ፡ ወምስሌሃ ፡ ብዙኅ ፡
ሠራዊት ፡ ወበጽሐት ፡ ውስተ ፡ ብሔረ ፡
ግብጽ ፡ ወዖደት ፡ ኩሎ ፡ አድባራተ ፡
ብዙኃተ፡ ወኀበ፡ አብያተ፡ክርስቲያን፡ወኢ
ተፈወስት።
፲፪፡ ወሶበ፡በጽሐት፡ኀበ፡ሀገረ፡እንዴናው፡እለ፡
ርእይዋ፡መኳንንተ፡ሀገረ፡አንከሩ፡በእንተ፡
ምጽአታ ፡ ወይእቲ ፡ ነገረቶሙ ፡ ኵሎ ፡
ምንዳቤሃ ፡ ወእሙንቱ ፡ አምከርዋ ፡ ከመ ፡
ትሑር፡ኀበ፡ቅዱስ፡አባ፡በአሚን፡ወተጽ
ዕነት ፡ ሶቤሃ ፡ ሐመረ ፡ ወበጽሐት ፡ ኀበ ፡
ደብሩ፡ለቅዱስ፡አባ፡በአሚን፡ወነገርዎ፡
ወይቤልዎ ፡ ናሁ ፡ ንግሥት ፡ መጽአት ፡
ኀቤከ፡ወትፈቅድ፡ከመ፡ትትባረክ፡እምኔከ፡
ወይቤሎሙ፡ምንት፡ብየ፡ምስለ፡ንግሥተ፡
ምድር፡ወአበየ፡ወጺአ፡ወሰአልዎ፡አኃው፡
ዐቢየ፡ስእለተ፡ከመ፡ይጸእ፡ኀቤሃ፡ወሶበ፡
ርእየቶ፡ሰገደት፡ሎቱ፡ታሕተ፡እገሪሁ፡
ውእቱኒ፡ጸለየ፡ላዕለ፡ዘይት፡ወቀብዓ፡
ወሐይወት፡ሶቤሃ፡ወይቤላ፡ቅዱስ፡አባ፡
በአሚን ፡ አእምሪ ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ኵሉ ፡
ዘበጽሐኪ ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡ ዲያቆን ፡
ዘአሥጠሞ ፡ ንጉሥ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡
ወውእቱሰ፡ሕያው፡እስከ፡ይእዜ፡እስመ፡
ሀሎ፡ውስተ፡አሐቲ፡ደሴት፡ወምስሌሁ፡
መጽሐፈ፡ራእዩ፡ለዮሐንስ፡አቡቀለምሲስ፡
ወሰሚዓ፡ንግሥት፡አንከረት፡ፈድፋደ፡
ወተፈሥሐት፡በእንተ፡ሕይወቱ፡ለውእቱ፡
ዲያቆን፡ወበእንተ፡ረኪቦታ፡ፈውሰ፡ወአቅ
ረበት፡ሎቱ፡ለቅዱስ፡አባ፡በአሚን፡ንዋየ፡
ብዙኀ ፡ አምኃሁ ፡ ውእቱኒ ፡ ኢነሥአ ፡

ደሴት፡ላይ፡አኖረው፡እንዚያ፡ሁለት፡ሰዎች፡
ሲያዩ፡ነበር፡እጅግም፡እያደነቁ፡ተመለሱ፡
ያዩትንም፡ለንጉሡ፡አልነገሩትም።

፲፩፡ንግሥቲቱም፡በዲያቆኑ፡ላይ፡የተደረገውን፡
በአየች፡ጊዜ፡እጅግ፡አዘነች፡በእርሷም፡
ደዌ፡ጸናባት፡ሆድዋም፡ቈሰሎ፡ዐሥራ፡
አምስት፡ዓመት፡ኖረች፡ወደርሷም፡ብዙ፡
ጥበበኞች ፡ ባለመድኃኒቶች ፡ መጥተው ፡
ነበር፡ግን፡ሊፈውሷት፡አልቻሉም፡አንድ፡
አዋቂ፡ሰውም፡እንዲህ፡ብሎ፡መከራት፡
በግብጽ ፡ አገር ፡ ወደሚኖሩ ፡ ቅዱሳን ፡
ብትሔጂ ፡ ከደዌሽ ፡ በተፈወስሽ ፡ ነበር ።
በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተነሣች ፡ ከእርሷም ፡ ጋር ፡
ብዙ፡ ሠራዊት፡ አለ፡ ወደግብጽ፡ አገርም፡
ደርሳ ፡ ገዳማቱንና ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያ
ናንም፡ ሁሉ ፡ ዞረች ፡ ግን ፡ አልዳነችም ።
፲፪፡ ፡ ወደ ፡ እንዴናው ፡ ከተማም ፡ በደረሰች ፡
ጊዜ ፡ ስለ ፡ መምጣቷ ፡ የአገሩ ፡ መኳንንት ፡
አደነቁ ፡ እርሷም ፡ ችግርዋን ፡ ሁሉ ፡ ነገረ
ቻቸው ፡ እንሱም ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ በአ
ሚን ፡ እንድትሔድ ፡ መከሩዋት ፡ በመር
ከብም ፡ ተሳፍራ ፡ ወዲያውኑ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡
በአሚን ፡ ወዳለበት፡ ገዳም ፡ ደረሰች ፡ እነሆ ፡
ንግሥት ፡ ወዳንተ ፡ መጥታለች ፡ ከአንተም ፡
ልትባረክ ፡ ትሻለች ፡ ብለው ፡ ነገሩት ፡
እርሱም ፡ ከምድር፡ ንግሥት ፡ ጋር ፡ ምን ፡
አለኝ፡ብሎ፡መውጣትን፡እምቢ፡አለ፡መነ
ኰሳትም፡ወደርሷ፡እንዲወጣ፡አጽንተው፡
ለመኑትና፡ ወጣ ፡ በአየችውም ፡ ጊዜ ፡ ከእ
ግሩ፡በታች፡ወድቃ፡ሰገደችለት፡እርሱም፡
በዘይት ፡ ላይ ፡ ጸልዮ ፡ ቀባት ፡ በዚያንም ፡
ጊዜ፡ዳነች።ቅዱስ፡አባ፡በአሚንም፡ንጉሥ፡
ከባሕር ፡ በአሠጠመው ፡ በዚያ ፡ ዲያቆን ፡
ምክንያት፡ይህ፡ሁሉ፡እንደደረሰብሽ፡ዕወቂ፡
እርሱ ፡ ግን ፡ በአንዲት ፡ ደሴት ፡ ውስጥ ፡
በሕይወት ፡ ይኖራል ፡ የአቡቀለምሲስ ፡
ዮሐንስ ፡ የራእይ ፡ መጽሐፍም ፡ ከእርሱ ፡
ጋር ፡ አለ ፡ አላት። ንግሥቲቱም ፡ ሰምታ ፡
እጅግ፡አደነቀች፡ደስ፡አላትም፡ ስለ ዚያ፡
ዲያቆን ፡ በሕይወት ፡ መኖርና ፡ እርሷም ፡
ፈውስ ፡ ስለማግኘቷ ፡ ለቅዱስ ፡ አባ ፡
በአሚንም፡እጅ፡መንሻ፡ብዙ፡ገንዘብ፡አቀ

ምንተኒ፡ዘእንበለ፡ንዋየ፡ቅድሳት።

፲፫፡ ወእምዝ ፡ ተመይጠት ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ ሮሜ ፡ እንዘ፡ትሴብሖ፡ለእግዚአብሔር፡ወነገረቶ፡ ለንጉሥ ፡ ኵሎ ፡ ዘኮነ ፡ ላዕሌሃ ፡ ወዘከመ ፡ ነገራ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ በአሚን ፡ በእንተ ፡ ውእቱ፡ ዲያቆን ፡ ዘአሥጠምዎ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ ወውእቱ ፡ ሕያው ፡ እስከ ፡ ይእዜ ፡ ወሰሚዖ ፡ ንጉሥ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡ አንከረ ፡ ፈድፋደ ፡ ወፈነወ ፡ ላእካነ ፡ ይኅሥሥዎ ፡ ውስተ ፡ ደሴት ፡ ወረከብዎ ፡ ሕያወ ፡ ወመጽ ሐፍኒ ፡ ምስሌሁ ፡ ወገቢኦሙ ፡ ዜነውዎ ፡ ለንጉሥ ፡ ወካዕበ ፡ ፈነወ ፡ ኀቤሁ ፡ እንዘ ፡ ያሰ ተበቍዖ ፡ ከመ ፡ ይምጻእ ፡ ኀቤሁ ፡ ወመጽአ ፡ ምስለ ፡ ላእካን ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ወሶበ ፡ ርእዮ ፡ ንጉሥ ፡ ተፈሥሐ ፡ ዐቢየ ፡ ፍሥሓ ፡ ወሰገደ ፡ ሎቱ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ፡ ወይቤሎ ፡ ስረይ ፡ ሊተ ፡ አበሳየ ፡ ዘገበርኩ ፡ ላዕሌከ ፡ ውእቱኒ ፡ ይቤ ፡ ይኅድግ ፡ ለነ ፡እግዚአብሔር ፡ አበሳነ ፡ ኅቡረ።

፲፬፡ ወእምድኅረዝ ፡ ተሠይመ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ላዕለ ፡ ሀገረ ፡ ሮሜ ፡ ውእቱ ፡ ዲያቆን ፡ ወተርጐመ ፡ ውእቱ ፡ ራእየ ፡ዮሐንስ ፡ አቡቀ ለምሲስ።

፲፭፡ ወቅዱስሰ ፡ አባ ፡ በአሚን ፡ ኮነ ፡ ዘይትጋደል ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ ዘእንበለ ፡ ጽርዐት።

፲፮፡ ወሀሎ ፡ ቅሩበ ፡ እምኔሁ ፡ ኤጴስቆጶስ ፡ ኄር ፡ ወእንዘ ፡ ይገብር ፡ በዓለ ፡ ምስለ ፡ መሐይ ምናን ፡ ውስተ ፡ አሐቲ ፡ ደብር ፡ ዘሰማዕታት ፡ ወአርዮሳውያን ፡ ነሥኡ ፡ ሎሙ ፡ ኤጲስ ቆጶሰ ፡ ሐሳዌ ፡ ወኮኑ ፡ ዘያስሕቱ ፡ ሕዝበ ፡ ወመጽአ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሀገር ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ በአሚን ፡ ወነገሮ ፡ ኵሎ ፡ ኀዘኖ ፡ በእንተ ፡ እሉ ፡ ዐላውያን ፡ ዘበጽሐ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወአመ ፡ ኮነ ፡ በዓለ ፡ ሰማዕታት ፡ ጸለየ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ በአሚን ፡ በስኢል ፡ ወበሰጊድ ፡ ምስለ ፡ ሕዝቡ ፡ ከመ ፡ ይዘርዝር ፡እግዚአብሔር ፡ ምክሮሙ ፡ ለእሉ ፡ ዓላውያን ፡ ወእምዝ ፡ ነሥአ ፡ በትረ ፡ በቀልት ፡ ወኵሎሙ ፡ ሕዝብ ፡ ለለ፩ ፡ ነሥኡ ፡ አብትረ ፡ በእደዊሆሙ ፡ ወሖሩ ፡ ኀበ ፡ እሉ ፡ ዓላውያን ፡ ወርእዮሙ ፡ ዓላውያን ፡ ተዘርው ፡ ወኢደገሙ ፡ መጺአ ፡ ህየ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘረወ ፡ ምክሮሙ።

ረበችለት ፡ ከንዋየ ፡ ቅድሳት ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ምን ፡ ገንዘብ ፡ አልተቀበለም።

፲፫፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያመሰ ገነች ፡ ወደ ፡ ሮሜ ፡ አገር ፡ ተመለሰች ፡ በእርሷ ፡ ላይ ፡ የሆነነውን ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ስለ ፡ አሠጠሙት ፡ ስለዚያ ፡ ዲያቆንም ፡ እርሱም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በአንዲት ፡ ደሴት ፡ ውስጥ ፡ በሕይወት ፡ እንዳለ ፡ ለንጉሡ ፡ ነገረችው ። ንጉሡም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ሰምቶ ፡ እጅግ ፡ አደነቀ ፡ ይፈልጉትም ፡ ዘንድ ፡ መልክ ተኞችን ፡ ላከ ፡ በደሴትም ፡ ውስጥ ፡ በሕይወት ፡ አገኙት ፡ መጽሐፉም ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ አለ፦ተመልሰውም ፡ ለንጉሡ ፡ ነገሩት ፡ ሁለተኛም ፡ ወደርሱ ፡ እንዲመጣ ፡ እየማለደ ፡ ላከ ፡ ከመልክተኞችም ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ መጣ ፡ ንጉሡም ፡ በአየው ፡ ጊዜ ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ አደረገ ፡ ከእግሩ ፡ በታችም ፡ ወድቆ ፡ በአንተ ፡ ላይ ፡ ስለአደረግሁት ፡ በደል ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ አለው ፡ እርሱም ፡ በአንድነት ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ ይበለን ፡ አለ።

፲፬፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ያ ፡ ዲያቆን ፡ በሮሜ ፡ ሀገር ፡ ላይ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ተሾመ ፡ ያንንም ፡ የዮሐንስ ፡ አቡቀለምሲስ ፡ ራእይ ፡ ተረጐመው።

፲፭፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ በአሚንም ፡ በቀንና ፡ በሌሊት ፡ ያለማቋረጥ ፡ የሚጋደል ፡ ሆነ።

፲፮፡ በአቅራቢያውም ፡ አንድ ፡ ደግ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አለ ፡ በአንዲት ፡ የሰማዕታት ፡ ገዳም ፡ ከምእ መናን ፡ ጋር ፡ በዓልን ፡ ሲያደርግ ፡ አርዮሳው ያንም ፡ ለራሳቸው ፡ ሐሰተኛ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ይዘው ፡ ሕዝቡን ፡ የሚያስቱ ፡ ሆኑ ፡ የሀገሩም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወደ ፡ አባ ፡ በአሚን ፡ መጥቶ ፡ ስለ ፡ እሊህ ፡ ከሀድያን ፡ የደረሰበትን ፡ ኃዘኑን ፡ ሁሉ ፡ ነገረው ። የሰማዕታትም ፡ በዓል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የእሊህን ፡ ከሀድያን ፡ ምክር ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ይበትን ፡ ዘንድ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ በአሚን ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋር ፡ በመለመንና ፡ በመስገድ ፡ ጸለየ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የሽመል ፡ በትር ፡ ያዘ ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ እየአንዳዱ ፡ በትሮችን ፡ ይዘው ፡ ወደእነዚያ ፡ ከሀድያን ፡ ሔዱ ፡ ከሀድያንም ፡ በአዩ ፡ ጊዜ ፡ ተበተኑ ፡ ወደዚያ ፡ ዳግመኛ ፡ አልተመለሱም ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ምክራቸውን ፡ በትኖባቸዋልና።

www.ethiopianorthodox.org

፲፯፡ ወቅዱስ ፡ አባ ፡ በአሚን ፡ ሶበ ፡ ልሕቀ ፡ ወረሥአ፡ ደወየ ፡ ደዌ ፡ ሞት ፡ ወአስተጋብአሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ አኃው ፡ ወነገሮሙ ፡ ከመ፡ መዋዕሊሁ ፡ ቀርበ ፡ ወናዘዞሙ ፡ ውኂዘኑ፡ በእንተ ፡ ተፈልጦቶሙ ፡ እምኔሁ ፡ ወእምዝ፡መጠወ፡ነፍሶ፡ውስተ፡እደ፡እግዚአብሔር ፡ ፈጣሪሁ ፡ ወአኃው ፡ ገነዝዎ ፡ ሠናየ፡ግንዘተ፡እንዘ፡ይሴብሑ፡ወይዜምሩ፡በከመ፡ይደሉ፡ወኮነ፡ሥጋሁ፡ፀወነ፡ለኵሉ፡ዘይመጽእ፡ኀቤሁ፡በተአምኖ፡አው፡ኀበ፡ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በርትዕት ፡ ሃይማኖት ፡ ይከውን፡ሎቱ፡ዘሰአለ፡በኀቤሁ።

፲፯፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ በአሚንም ፡ ፈጽሞ ፡ በአረጀ ፡ ጊዜ ፡ የሞት ፡ ደዌን ፡ ታመመ ፡ መነኮሳቱንም ፡ ሁሉ ፡ ሰብስቦ ፡ ዕድሜው ፡ እንደ ቀረበ፡ነገራቸውና፡አጽናናቸው፡እነርሱም፡ከእርሱ ፡ ስለመለየታቸው ፡ አዘኑ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በፈጣሪው ፡ እግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ነፍሱን ፡ ሰጠ ። መነኮሳቱም ፡ እንደሚገባ ፡ እያመሰገኑና ፡ እየዘመሩ ፡ መልካም ፡ አገናነዝን፡ገነዙት፡ሥጋው፡በእምነት፡ወደርሱ፡ለሚመጣ ፡ ሁሉ ፡ መጠጊያ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በቀናች ፡ሃይማኖት፡ጸንቶ፡ወደ፡ቤተ፡ክርስቲያን ፡ ሒዶ ፡ በስሙ ፡ ለሚለምን ፡ ሁሉ ፡ የለመነው፡ይሆንለታል።

፲፰፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ ጻድቅ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

፲፰፡ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡ በዚህ ፡ ጻድቅ ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለከ ፡ በአሚን ፡ስኩብ። በዐራተ ፡ ኀጺን ፡ልሁብ። ለዕጓለ ፡ ማውታ ፡ ቀዋሚ ፡ ወለመዓስብ ። ወሰላም፡ለእለ፡ምስሌሁ፡በቤተ፡መከራ፡ወጻሕብ።በእንተ፡ክርስቶስ፡ሙቁሐን፡ሕዝብ።

፲፱፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካረ ፡ ዕረፍቶሙ ፡ ለበድላም ፡ ወአርምያ ፡ ወዘካርያስ ፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለም ፡ ዓለም ፡ አሜን።

፲፱፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ የበድላም ፡ የአርምያና ፡ የዘካርያስ ፡ የዕረፍታቸው ፡ መታሰቢያ ፡ ነው ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

* * *

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፲ ለታኅሣሥ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ አምጽኡ ፡ ሥጋሁ ፡ ለቅዱስ ፡ አባ ፡ ሳዊሮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሀገረ ፡ አንጾኪያ ፡ ኀበ ፡ ደብረ ፡ ዝጋግ ፡ ዘአፍአ ፡ ሀገረ ፡ እስክንድርያ።

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ታኅሣሥ ፡ ዐሥር ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ የአንጾኪያ ፡ አገር ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ የነበረ፡የቅዱስ፡አባ፡ሳዊሮስን፡ሥጋ፡ከእስክንድርያ፡ውጪ፡ወደሆነች፡ደብረ፡ዝጋግ፡ገዳም፡ አመጡ።

፪፡ ወኮነ ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ አብ ፡ ሶበ ፡ አዕረፈ ፡ በውስተ ፡ ሀገረ ፡ ስሐ ፡ ኀበ ፡ ብእሲ ፡ ባዕል ፡ ክርስቲያናዊ ፡ መፍቀሬ ፡ አምላክ ፡ ዘስሙ ፡ ዱራታዎስ ፡ ወውእቱ ፡ አስተፋነዎ ፡ ምስለ ፡ ሰብእ ፡ መሐይምናን ፡ ኀበ ፡ ደብረ ፡ ዝጋግ፡በሐመር፡ወአዘዞሙ፡ከመ፡ኢይሑሩ፡ ኀበ ፡ ፈለግ ፡ ንኡስ ፡ አላ ፡ ይሑሩ ፡ ውስተ ፡ ባሕር፡ ዐቢይ ፡ ወእምዝ ፡ ይዕርጉ ፡ ውስተ ፡ መርሶ።

፪፡ እንዲህም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ቅዱስ ፡ አባት ፡ በሀገረ ፡ ስሐ ፡ አምላክን ፡ በሚወድ ፡ ክርስቲያን ፡ ባለጸጋ ፡ ስሙ ፡ ዱራታዎስ ፡ በሚባል ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ በአረፈ ፡ ጊዜ ፡ እርሱም ፡ ከምእመናን ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ በመርከብ ፡ አሳፍሮ ፡ ላከው ፡ በጥልቅ ፡ ባሕር ፡ ላይ ፡ እንጂ ፡ በአነስተኛ ፡ ሸለቆ ፡ እንዳይሔዱ ፡ ከዚያም ፡ በወደቡ ፡ እንዲወጡ ፡ አዘዛቸው።

www.ethiopianorthodox.org

፫፤ ወሶበ፡በጽሐ፡ኀበ፡ባሕረ፡ቅርጣስ፡መንገለ፡
ደቡብ ፡ ወምስሌሆሙ ፡ ሥጋሁ ፡ ለቅዱስ ፡
ወሖሩ ፡ መንገለ ፡ ምዕራብ ፡ ንስቲተ ፡ ወኢ
ረከቡ፡ማየ፡ዘይፀውር፡ሐመሮሙ፡ወፃመዉ፡
ፃማ፡ዐቢየ፡እንዘ፡ይስሕቡ፡ሐመረ፡ወሐለዩ፡
ከመ ፡ ይሚጡ ፡ ሐመሮሙ ፡ መንገለ ፡ ከዋላ ፡
ወኢተክህሎሙ፡ኀዘኑ፡ወተከዙ፡ወደንገፁ፡
ወተኀብኦ፡ጥበቦሙ፡እስመ፡እግዚአብሔር፡
መፍቀሬ ፡ ሰብእ ፡ ዘሠወሮሙ ፡ ለደቂቀ ፡
እስራኤል፡ እምቅድመ ፡ ፀሮሙ ፡ ወከሠተ ፡
ሎሙ፡ ፍኖተ፡ውስተ፡ባሕረ፡ኤርትራ፡ወአኀ
ለፎሙ ፡ ውእቱ፡ ሠወረ ፡ ሥጋሁ ፡ ለቅዱስ ፡
ሳዊሮስ ፡ እምነ ፡ ዐላውያን ፡ ሰብእ ፡ መለካ
ውያን፡ እስመ ፡ ውእቶሙ ፡ ኮኑ ፡ ዘይጸልእዎ ፡
በሕይወቱ ፡ ወከማሁ ፡ እምድኅረ ፡ ሞቱኒ ፡
እስመ፡ቃሉ፡ኮነ፡ዘይመትር፡አልባቢሆሙ፡
ከመ፡ሰይፍ።

፬፤ ወእምዝ፡ከሠተ፡እግዚአብሔር፡እምተአም
ራቲሁ ፡ ወረሰያ ፡ ለይእቲ ፡ ሐመር ፡ ከመ ፡
ትሑር ፡ ላዕለ ፡ ማይ ፡ ንስቲት ፡ መጠነ ፡ ፯ቱ ፡
ምዕራፍ ፡ እስከ ፡ በጽሐት ፡ ኀበ ፡ መርሶ ፡ ዘየዐ
ርጉ ፡ቦቱ ፡ ወእምህየ ፡ ፆርዎ ፡ ወአብጽሕዎ ፡
ኀበ ፡ ደብረ ፡ ዝጋግ ፡ ወአንበርዎ ፡ በዘሐነፀ ፡
ሎቱ ፡ ውእቱ ፡ ባዕል ፡ ዱራታዎስ ፡ ወኮነ ፡
ፍሥሐ፡ዐቢይ፡ውስተ፡ኵሉ፡ብሔረ፡ግብጽ፡
ወፈድፋደሰ፡ውስተ፡ሀገረ፡እስክንድርያ።

፭፤ ወገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተአምራተ ፡ ወመን
ክራተ፡ዐበይተ፡እምነ፡ሥጋሁ፡ኮነት፡እምአስ
ናኒሁ ፡ አሐቲ ፡ ዘወድቀት ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡
በሕይወቱ ፡ ወነሥአ ፡ ፩ መነኮስ ፡ ዘደብረ ፡
ዝጋግ ፡ ወጠብለላ ፡ በጸርቀ ፡ ሐሪር ፡ ወይእቲ ፡
ኮነት ፡ ፈውሰ ፡ ለዱያን ፡ ሕዝብ ፡ እስመ ፡ እሙ
ንቱ፡ኮኑ፡ያመጽእዋ፡ኀበ፡ሀገረ፡እስክንድርያ፡
ወያነብርዋ ፡ ዲበ ፡ ድውያን ፡ ወየሐይዉ ።
እስመ ፡ አዕበዮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለቅዱስ ፡ ሳዊ
ሮስ ፡ እምድኅረ ፡ ሞቱ ፡ ፈድፋደ ፡ እምሕይ
ወቱ።

፮፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም
ሐነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ወበረከቱ ፡
ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፫፡ ወደ፡ደቡባዊ፡ባሕረ፡ቅርጣስ፡በደረሱ፡ጊዜ፡
የቅዱሱም፡ሥጋ፡ከእሳቸው፡ጋር፡ሳለ፡ወደ፡
ምዕራብ፡አቅጣጫ፡ጥቂት፡እንደተጓዙ፡መር
ከቡን ፡ የሚሸከም ፡ ውኃ ፡ አላገኙም ፡ መርከ
ቡንም፡እየጐተቱ፡ታላቅ፡ድካምን፡ደከሙ፡
መርከባቸውንም፡ወደ፡ኋላ፡ይመልሱ፡ዘንድ፡
አሰቡ፡ግን፡አልተቻላቸውም፡ፈጽሞ፡አዘኑ፡
ደነገጡም ፡ ዕውቀታቸውም፡ ተሠወረባቸው ፡
ሰውን ፡ የሚወድ ፡ እግዚአብሔር ፡ የእስራኤ
ልን ፡ ልጆች ፡ ከጠላቶቻቸው ፡ ፊት ፡ ሠውሮ ፡
በኤርትራ፡ባሕር፡ውስጥ፡መንገድ፡ገልጦ፡ያሳ
ለፋቸው ፡ እርሱ ፡ የቅዱስ ፡ ሳዊሮስን ፡ ሥጋ ፡
መለካውያን ፡ ከሆኑ ፡ ከከሀድያን ፡ ሰዎች ፡
ሠወረ ፡ እነርሱ ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ ይጠሉት ፡
ነበርና ፡ እንዲሁ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ቃሉ ፡ እንደ ፡
ሰይፍ፡የሚቆራርጣቸው፡ሆነ።

፬፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከተአምራቱ ፡
ገለጠ ፡ ያቺን ፡ መርከብ ፡ ወደሚወጡበት ፡
ወደብ፡እስከምትደርስ፡በጥቂት፡ውኃ፡ላይ፡
ሰባት ፡ ምዕራፍ ፡ ያህል ፡ እንድትጓዝ ፡ አደረ
ጋት ፡ ገዳም ፡ ከዚያም ፡ ተሸክመው ፡ ወደ ፡
ደብረ፡ዝጋግ፡ገዳም፡አድርሰው፡ያ፡ባለጸጋ፡
ዱራታዎስ፡በሠራለት፡ቦታ፡ውስጥ፡አኖሩት፡
በግብጽ፡አገርም፡ታላቅ፡ደስታ፡ሆነ፡ይልቁ
ንም፡በእስክንድር፡ከተማ።

፭፡ እግዚአብሔርም፡ታላላቅ፡የሆኑ፡ድንቆች፡ተአ
ምራቶችን፡ገለጠ፡በሕይወቱ፡ሳለ፡ከጥርሶቹ፡
የወደቀች፡አንዲት፡ነበረች፡የደብረ፡ዝጋግ፡
ገዳም ፡ አንድ ፡ መነኰሴ ፡ አንሥቶ ፡ በሐር ፡
ጨርቅ ፡ ጠቅልሎ ፡ አኖራት ፡ እርሷም ፡ ለታ
መሙ ፡ ሕዝቦች ፡ የምትፈውስ ፡ ሆነች ፡ እነር
ሱም፡ወደእስክንድርያ፡ሀገር፡ያመጧትና፡በበ
ሽተኞች ፡ ላይ ፡ ያኖሩዋታል፡ እነርሱም ፡ ይድ
ናሉ ። እግዚአሔርም ፡ ቅዱስ ፡ ሳዊሮስን ፡ በሕ
ይወቱ ፡ ካለበት ፡ ጊዜ ፡ ይልቅ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡
እጅግ፡ከፍ፡ከፍ፡አደረገው።

፮፡ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡
በዚህ ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡
ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለብጽሐተ፡ሥጋከ፡በዕለት፡ዛቲ።ውስተ፡ደብረ፡ዝጋግ፡ተሀሉ፡እስመ፡አምጽኡከ፡ላቲ።
ዕልዋነ፡ሳዊሮስ፡በሰይፈ፡ሃይማኖት፡ነሳቲ። ወእንተ፡ወድቀት፡በሕይወትከ፡እምአስናኒከ፡አሐቲ።
ፈውሰ፡ሕሙማን፡ኮነት፡እስከ፡ዮም፡ይእቲ።

www.ethiopianorthodox.org

፯፡ ወበዛቲ፡ ዕለት፡ አዕረፈ፡ አብ፡ ቅዱስ፡ ታውፋ ኒዎስ፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ ዘእስክንድርያ፡ ወው እቱ፡ እምኍልቆሙ፡ ለአበው፡ ሊቃነ፡ ጳጳ ሳት፡ ፴፮።

፰፡ ወእምድኅረ፡ ነበረ፡ ዲበ፡ መንበረ፡ ማርቆስ፡ ወንጌላዊ፡ ፱ተ፡ ዓመተ፡ ወ፯አውራኀ፡ ሞተ፡ በቅትለት፡ እምዐላውያን። ወስብሐት፡ ለእግ ዚአብሔር፡ ወለነኒ፡ ይምሐረነ፡ በጸሎቱ፡ ለዓለመ፡ ዓለም፡ አሜን።

፯፡ በዚችም፡ ቀን፡ ቅዱስ፡ አባት፡ የእስክንድርያ፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ ታውፋኒዎስ፡ አረፈ፡ እርሱም፡ ለአባቶች፡ ሊቃነ፡ ጳጳሳት፡ ስልሣኛ፡ ነው።

፰፡ በማርቆስ፡ ወንጌላዊ፡ መንበር፡ ዘጠኝ፡ ዓመት፡ ከሰባት፡ ወር፡ ከኖረ፡ በኋላ፡ በከሀድያን፡ እጅ፡ ሞተ። ለእግዚአብሔርም፡ ምስጋና፡ ይሁን፡ እኛንም፡ በጸሎቱ፡ ይማረን፡ ለዘላለሙ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ እብል፡ ለታውፋኒዎስ፡ በሕቁ። እምኍልቈ፡ ጳጳሳት፡ ኍልቍ። ዘምስለ፡ ሳዊሮስ፡ አብ፡ ወኒቆ ላዎስ፡ ልጹቁ። ያንቅሕኒ፡ እምንዋምየ፡ ወያንሥአኒ፡ በጽድቁ። እስመ፡ መዋዕልየ፡ ኮሎሙ፡ በሐኬት፡ ሐልቁ።

፱፡ ወበዛቲ፡ ዕለት፡ አዕረፈ፡ አብ፡ ክቡር፡ አባ፡ ኒቆላዎስ፡ ጻድቅ፡ ኤጲስቆጶስ፡ ዘበትር ጓሜሁ፡ መዋዔ፡ ሕዝብ።

፲፡ ወዝንቱ፡ ጻድቅ፡ እምሀገረ፡ ሜራ፡ ወስሙ፡ ለአቡሁ፡ ኤጲፋንዮስ፡ ወስማ፡ ለእሙ፡ ዮና፡ ወእሉ፡ ብዑላን፡ ፈድፋደ፡ በሀገረ፡ ሜራ፡ ወፈ ራህያነ፡ እግዚአብሔር፡ ወባሕቱ፡ አልቦሙ፡ ውሉድ፡ ወነበሩ፡ እንዘ፡ የኀዝኑ፡ ወይጼልዩ፡ ወያስተበቍዑ፡ ኀበ፡ እግዚአብሔር፡ ከመ፡ የሀቦሙ፡ ወልደ፡ ሠናየ፡ ወዘይወርስ፡ ብዕ ሎሙ፡ ወይትፌሣሕ፡ ቦቱ፡ ወነበሩ፡ እስከ፡ ኃለፈ፡ እምኔሆሙ፡ ጊዜ፡ ወሊድ፡ ወሶበ፡ አእ መሩ፡ ከመ፡ ኃለፈ፡ መዋዕሊሆሙ፡ ኀደጉ፡ ሰኢለ፡ በእንተ፡ ወልድ።

፲፩፡ እግዚአብሔርሰ፡ ዘመንክር፡ ግብሩ፡ ተሣሃለ፡ ላዕሌሆሙ፡ ወወሀቦሙ፡ ዘንተ፡ ወልደ፡ ቅዱሰ፡ ኒቆላዎስሃ፡ ዘረሰዮ፡ ቅዱሰ፡ ወቡሩከ፡ ወፍ ጹመ፡ ወከሡተ፡ በኀቤሁ፡ ገቢረ፡ ጽድቅ፡ ወውእቱ፡ ሶበ፡ ተወልደ፡ ተንሥአ፡ ወቆመ፡ ማዕከለ፡ ሰብእ፡ መጠነ፡ ፪ቱ፡ ሰዓት፡ ወይኤ ምር፡ በዝንቱ፡ በእንተ፡ ተንሥኦቱ፡ ለገቢረ፡ ጽድቅ፡ ወበጊዜ፡ ይጠቡ፡ አጥባተ፡ እሙ፡ ኮነ፡ ዘኢይጠቡ፡ ዘእንበለ፡ የማናይ፡ ጥባ፡ ለእሙ፡ ወይከሥት፡ በዝንቱኒ፡ ከመ፡ በኮሉ፡ መዋዕለ፡ ሕይወቱ፡ ኢይሰቲ፡ ዘእንበለ፡ ነቅዐ፡ ማይ፡ መንፈሳዊ፡ ዘውእቱ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር።

፲፪፡ ወፈጸመ፡ ቀኖና፡ ሐዋርያት፡ እምንእሱ፡ እስመ፡ ኢይጠቡ፡ ጥበ፡ እሙ፡ ዘእንበለ፡

፱፡ በዚችም፡ ዕለት፡ የከበረ፡ አባት፡ ጻድቅ፡ ኤጲስ ቆጶስ፡ የስሙ፡ ትርጓሜ፡ የሕዝብ፡ አሸናፊ፡ የሆነ፡ አባ፡ ኒቆላዎስ፡ አረፈ።

፲፡ ይህም፡ ጻድቅ፡ ሰው፡ ሜራ፡ ከሚባል፡ አገር፡ ነው፡ የአባቱ፡ ስም፡ ኤጲፋንዮስ፡ የናቱ፡ ዮና፡ ነው፡ እሊህም፡ በሀገረ፡ ሜራ፡ እጅግ፡ ባለጸጎች፡ ናቸው፡ እግዚአብሔርንም፡ የሚፈሩትና፡ የሚ ያመልኩት፡ ናቸው፡ ግን፡ ልጅ፡ አልነበራ ቸውም፡ ሀብታቸውን፡ የሚወርስ፡ የተባረከ፡ ልጅን፡ ሰጥቷቸው፡ በርሱ፡ ደስ፡ ይላቸው፡ ዘንድ፡ እያዘኑ፡ ወደ፡ እግዚአብሔር፡ ሲጸልዩና፡ ሲማልዱ፡ ኖሩ፡ የመውለጃቸውም፡ ጊዜ፡ እስቲ አልፍ፡ ኑረው፡ የመወለጃቸው፡ ጊዜ፡ እንዳለፈ፡ በአወቁ፡ ጊዜ፡ ስለ፡ ልጅ፡ መለመንን፡ ተዉ።

፲፩፡ ሥራው፡ ልዩ፡ ድንቅ፡ የሆነ፡ እግዚአብሔር፡ በበረከትና፡ በቅድስና፡ ፍጹም፡ ያደረገውን፡ ይህን፡ ቅዱስ፡ ልጅ፡ ኒቆላዎስን፡ ሰጣቸው፡ በእርሱም፡ ዘንድ፡ የጽድቅን፡ ሥራ፡ ገለጠ፡ እርሱም፡ በተወለደ፡ ጊዜ፡ ተነሥቶ፡ በሰዎች መካከል፡ ሁለት፡ ሰዓት ያህል፡ ቆመ፡ በዚህም፡ ለጽድቅ፡ ሥራ፡ የሚነሣ፡ መሆኑን፡ ያመለ ክታል፡ የእናቱንም፡ ጡት፡ በሚጠባ፡ ጊዜ፡ ከቀኝ፡ ጡቷ፡ በቀር፡ አይጠባም፡ በዚህም፡ በሕይወቱ፡ ዘመን፡ ሁሉ፡ ከመንፈሳዊ፡ የውኃ፡ ምንጭ፡ በቀር፡ እንደማይጠጣ፡ ይገልጣል፡ ይኸውም፡ የእግዚአብሔር፡ ቃል፡ መንፈሳዊ፡ ትምህርት፡ ነው።

፲፪፡ በሕፃንነቱም፡ የሐዋርያትን፡ ሥርዓት፡ ፈጸመ፡ በረቡዕና፡ በዓርብ፡ ቀን፡ ያለ፡ ዘጠኝ፡ ሰዓት፡

www.ethiopianorthodox.org

ተሰዓቱ ፡ ሰዓተ ፡ መዓልት፡ በዕለተ ፡ ረቡዕ ፡
ወዓርብ።

፲፫፡ወሶበ፡ኮነ፡ወሬዛ፡ንኡሰ፡መጠውዎ፡አበዊሁ፡
ለመምህር ፡ ወበኀዳጥ ፡ መዋዕል ፡ ተምህረ ፡
ትምህርተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወተሠይመ ፡
ዲያቆነ፡ወኮነ፡ዘይዌስክ፡ምግባረ፡መንፈሳዌ፡
ለለዕለቱ ፡ ወመንኰሰ ፡ ውስተ ፡ ፩ ደብር ፡ በዘ
ኮነ ፡ ወልደ ፡ እኁወ ፡ አቡሁ ፡ አበ ፡ ምኔት ፡
ወበውእቱ ፡ ደብር ፡ ተጋደለ ፡ ገድለ ፡ ጽኑዐ ፡
ዘኢይክል ፡ መኑሂ ፡ ይግበር ፡ ዘከማሁ ፡ እም
ስብእ ፡ ወእምዝ ፡ ተሰይመ ፡ ቀሲስ ፡ እንዘ ፡
መዋዕሊሁ ፲ወ፱ቱ ፡ ዓመት ፡ ወወሀቦ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ጸጋ፡ ሀቢየ፡ ገቢረ፡ ተአምራት፡ ወመን
ክራት፡ ወፈውሶ፡ ለዱያን።

፲፬፡ ወመንክራቲሁሰ ፡ ዘኮነ ፡ ይትዌሰክ ፡ ኵሎ ፡
አሚረ ፡ በውስተ ፡ ኵሉ ፡ መካን ፡ በሕይወቱ ፡
ወእምድኅረ ፡ ፍልሰቱ ፡ አልቦ ፡ ኍልቍ። ወን
ዜከር ፡ ንስቲተ ፡ እምትሩፋቲሁ ፡ ዘገብረ ፡
በሕይወቱ ፡ ውእቱኬ ፡ እስመ ፡ ሀሎ ፡ ፩ብእሲ ፡
ባዕል ፡ በሀገሩ ፡ ወእምድኅረ ፡ መዋዕል ፡ ኅዳጥ ፡
ነድየ ፡ ፈድፋደ ፡ እስከ ፡ ኢረከበ ፡ሲሳየ ፡ ዕለት ፡
ወሀለዋሁ፡ አርባዕ፡ አዋልድ፡ ወኢረከበ፡ ዘያወ
ስቦን ፡ በእንተ ፡ ንዴቱ ፡ ወአሕለዮ ፡ ሰይጣን ፡
ሕሊና፡ ርኩሰ፡ ከመ፡ ይግበር፡ ቤተ፡ ዘማ፡ ለአዋ
ልዲሁ፡ ወያንብሮን፡ ውስቴቱ፡ ከመ፡ ያዘምዋ፡
ወይንሥአ፡ አስበ፡ ዝሙቶን።

፲፭፡ ወከሠተ ፡ሎቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ለቅዱስ፡ አባ፡
ኒቆላዎስ፡ ዘሐለየ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ወሶቤሃ ፡
ተንሥአ፡ አባ፡ ኒቆላዎስ፡ በሌሊት ፡ ወነሥአ፡
እምንዋየ፡ አቡሁ ፡ ፻ተ፡ ዲናረ፡ ወርቅ ፡ ወእም
ቅድመ ፡ ይጽባሕ ፡ ሌሊት ፡ ሖረ ፡ኀበ ፡ ቤቱ ፡
ለውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ወአንበሮ ፡ ለወርቅ ፡ በኖ
ኀተ ፡ ቤቱ ፡ ውስጠ ፡ ወነቂሖ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡
ረከበ ፡ ውእተ ፡ ወርቀ ፡ ወተፈሥሐ ፡ ዐቢየ ፡
ፍሥሓ ፡ ወአስተውሰባ ፡ ለእንተ ፡ ትልሕቅ ፡
ወለቱ ። ወከማሁ ፡ ካልአየ ፡ ወሣልሳየ ፡ ጊዜ ፡
በበምእት ፡ ዲናረ ፡ ወርቅ ፡ ወገረ ፡ ሎቱ ፡ ወአስ
ተዋሰቦን ፡ ለኵሎን ፡ አዋልዲሁ ፡ ወበተፍ
ጻሚቱ ፡ ኮነ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ዘይጸንሖ ፡
ነቂሖ ፡ ያእምር ፡ ከመ ፡ መኑ ፡ ውእቱ ፡
ዘይዌግር፡ ሎቱ ፡ ወእምዝ ፡ ረከቦ ፡ ለቅዱስ ፡
አባ፡ ኒቆላዎስ፡ እንዘ፡ ያነብር፡ ሎቱ፡ ወሰገደ፡

የእናቱን፡ ጡት፡ አይጠባምና።

፲፫፡ ታናሽ ፡ ብላቴናም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ወላጆቹ ፡
ለመምህር ፡ ሰጡት ፡ በጥቂት ፡ ቀኖች ፡ የቤተ ፡
ክርስቲያንን፡ ትምርት፡ ተምሮ፡ ዲቁና፡ ተሾመ፡
መንፈሳዊ ፡ ሥራንም ፡ በየቀኑ ፡ የሚጨምር ፡
ሆነ ፡ የአባቱ ፡ የወንድም ፡ ልጅ ፡ አበ ፡ ምኔት ፡
በሆነበት ፡ በአንድ ፡ ገዳም ፡ መነኰሰ ፡ ከሰው ፡
ማንም፡ እንደርሱ፡ ሊሠራው፡ የማይቻለውን፡
ጽኑዕ፡ ገድል ፡ ተጋደለ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡
ዕድሜው ፡ ዐሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ሲሆነው ፡
ቅስናን ፡ ተሾመ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ታላቅ ፡
ጸጋን፡ ድንቆች፡ ተአምራትን፡ ማድረግና፡ በሽ
ተኞችን፡ የመፈወስ፡ ሀብትን፡ ሰጠው።

፲፬፡ በሕይወቱም ፡ ሳለ ፡ ከሞተም ፡ በኋላ ፡
በየጊዜው ፡ በመጨመር ፡ የሠራቸው ፡
ተአምራቱ ፡ ግን ፡ ቍጥር ፡ የላቸውም ። በሕ
ይወቱ፡ ሳለ፡ ከሠራው፡ ትሩፋቱ፡ ጥቂት፡ እንና
ገራለን፡ ይህም፡ እንዲህ፡ ነው፡ አንድ፡ ባለጸጋ፡
በሀገሩ ፡ ነበር ፡ ከጥቂቱ ፡ ጊዜም ፡ በኋላ ፡ የዕ
ለት ፡ ራት ፡ እስከሚያጣ ፡ እጅግ ፡ ድኃ ፡ ሆነ ፡
አራት፡ ሴቶች ፡ ልጆችም ፡ ነበሩት ፡ ስለ ፡
ድኅነቱም ፡ የሚያገባለት ፡ አላገኘም ፡ የአመ
ንዝራ ፡ ቤትም ፡ ሠርቶ ፡ ልጆቹን ፡ በዚያ ፡
አኑሮ ፡ እያመነዘሩ ፡ የዝሙት ፡ ዋጋ ፡ በማግ
ኘት ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ የረከሰ ፡ ሐሳብ፡
ሰይጣን፡ አሳሰበው።

፲፭፡ እግዚአብሔርም ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ያሰበውን ፡
ለቅዱስ ፡ አባ ፡ ኒቆላዎስ ፡ ገለጠለት ፡ በዚያ
ንም ፡ ጊዜ ፡ ተነሥቶ ፡ ከአባቱ ፡ ገንዘብ ፡ መቶ ፡
የወርቅ ፡ ዲናር ፡ ይዞ ፡ ሌሊቱ ፡ ሳይነጋ ፡ ወደ
ዚያ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ሔዶ ፡ በበሩ ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡
አስገብቶ ፡ አኖረለት ፡ ሰውዬውም ፡ በነቃ ፡
ጊዜ ፡ ያን ፡ ወርቅ ፡ አገኘ ፡ እጅግም ፡ ደስ ፡
አለው ፡ ታላቂቱንም ፡ ልጁን ፡ አጋባት። እን
ዲሁም ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ሦስተኛ ፡ ጊዜ ፡
መቶ ፡ መቶ ፡ የወርቅ ፡ ዲናር ፡ እንዲሁ ፡ አኖረ
ለትና ፡ ሁሉንም ፡ ልጆቹን ፡ አጋባቸው ፡ በፍጻ
ሜውም ፡ ይህን ፡ ገንዘብ ፡ የሚጥልለት ፡ ማን ፡
እንደሆነ ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ ነቅቶ ፡ የሚጠ
ብቀው ፡ ሆነ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሲያኖርለት ፡
ቅዱስ ፡ አባ ፡ ኒቆላዎስን ፡ አገኘው ፡ ሰገደለ
ትም ፡ ከገንዘብ ፡ ችግርና ፡ በኃጢአትም ፡ ከመ

www.ethiopianorthodox.org

ሎቱ : ወይቤሎ : ዕሴትከ : ዐቢይ : በመን
ግሥተ : ሰማያት : እስመ : አድኃንከኒ :
እምንዴተ : ንዋይ : ወእምወዲቅ : ውስተ :
ኃጢአት።

፲፮፤ ወእምዝ፡ሰደዶሙ፡ቅዱስ፡አባ፡ኒቆላዎስ፡ለሰ
ይጣናት፡እምላዕለ፡ሰብእ፡ወእምነ፡ዕፀው፡
ዘኮኑ፡የኀድሩ፡ውስቴቶን፡ወያስሕትዎሙ፡
ለሰብእ፡ወለዱያንኒ፡ፈውሶሙ።

፲፯፤ ወዓዲ : ባረከ : ላዕለ : ንስቲት : ኅብስት :
ወአጽገበ : ብዙኃነ : ሕዝበ : እምኔሁ : ወነ
ሥኡ፡ዘተርፈ፡ብዙኀ፡ፈድፋደ።

፲፰፤ ወእምቅድመ : ይሠየም : ኤጲስቆጶስ : ርእየ :
ራእየ : ዘከመ : መንበር : ዐቢይ : ንቡር :
ወልብሰ፡ክህነት፡ክቡር፡በኀቤሁ፡ወዘከመ፡
ይቤሎ : ብእሲ : ብርሃናዊ : ልበስ : ዘንተ :
ልብሰ : ክህነት : ወንበር : ዲበ : ዝንቱ :
መንበር። ወካዕበ : ርእየ : በካልዕ : ዕለት :
ዘከመ : እግዝእትነ : ቅድስት : ድንግል : ማር
ያም : እሙ : ለንጉሠ : ስብሐት : ወሀበቶ :
ልብሰ : ክህነት : ወእግዚእነ : ኢየሱስ : ክርስ
ቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት፡ወሀቦ፡ወንጌለ።

፲፱፤ ወሶበ፡አዕረፈ፡ኤጲስቆጶስ፡ዘሀገረ፡ሜራ፡አስ
ተርአዮ : መልአክ : ለሊቀ : ጳጳሳት : ዘሀገረ :
ሮሜ፡ወነገሮ፡በእንተ፡ኒቆላዎስ፡ወአጠየቆ፡
ስሞ : ወአምሳሎ : ወነቂሖ : ሊቀ : ጳጳሳት :
ነገሮሙ : ለኤጲስቆጶሳት : ዘርእየ : ወሰሚ
ዖሙ፡ኵሎሙ፡አምኑ፡ከመ፡እሙንቱ፡ውእቱ፡
ራእይ፡ወነሥእዎ፡ለቅዱስ፡ኒቆላዎስ፡ ወሤ
ምዎ፡ኤጲስቆጶሰ፡ላዕለ፡ሀገረ፡ሜራ።

፳፤ ወሶበ : ነገሠ : ዲዮቅልጥያኖስ : ዕልው : ወከ
ሀደ፡ ወአምለከ : ጣዖታተ : ወአዘዞሙ : ለኵ
ሎሙ : ሰብእ : ከመ : ያምልኩ : ጣዖታተ :
ወዝንቱ : አባ : ኒቆላዎስ : ኮነ : ዘይሜህሮሙ :
ለሕዝብ : ወያጸንዖሙ : ውስተ : ሃይማኖት :
ርትዕት።

፳፩፤ ወሶበ : ሰምዐ : ዜናሁ : ለቅዱስ : አባ : ኒቆላ
ዎስ፡አኀዞ፡ዲዮቅልጥያኖስ፡ወኰነኖ፡ኵነኔ፡
ዐቢየ : ብዙኀ : ዓመታተ : ወእግዚእነ : ኢየ
ሱስ፡ክርስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት፡ያጸንዖ፡ወያስ
ተዔግሦ፡ወያነሥእ፡ጥዑየ፡ዘእንበለ፡ሙስና፡
ወሶበ፡ደክመ፡እምኰንኖቱ፡ዲዮቅልጥያኖስ፡
ወደዮ፡ውስተ፡ቤተ፡ሞቅሕ፡ወነበረ፡በህየ፡

ውደቅ፡አድነኸኛልና፡ዋጋህ፡በመንግሥተ፡
ሰማያት፡ፍጹም፡ነው፡አለው።

፲፮፤ ከዚህም : በኋላ : ከሰዎች : ላይና : ሰዎችን :
ለማሳት : ከሚያድሩባቸው : ዛፎች : ውስጥ :
ሰይጣናትን፡አበረራቸው፡በሽተኞችንም፡አዳ
ናቸው።

፲፯፤ ዳግመኛም : በጥቂት : እንጀራ : ላይ : ባርኮ :
ብዙ : ሕዝቦችን : ከዚያ : እንጀራ : አጠገበ :
እጅግ፡ብዙ፡የሆነ፡ትራፊንም፡አነሡ።

፲፰፤ ኤጲስቆጶስነትንም፡ከመሾሙ፡ፊት፡ታላቅ፡
ዙፋንና : የከበረ : የክህነት : ልብስ : በእርሱ :
ዘንድ : ተቀምጦ : ብርሃንን : የለበሰ : ሰውም :
ይህን፡የክህነት፡ልብስ፡ልበስ፡በዙፋኑም፡ላይ፡
ተቀመጥ : የሚለውን : ራእይ : አየ። ሁለ
ተኛም፡በሌላ፡ቀን፡ለክብር፡ባለቤት፡እናቱ፡
የሆነች : እመቤታችን : ቅድስት : ድንግል :
ማርያም : የክህነት : ልብስን : ስትሰጠው :
ክብር : ይግባውና : ጌታችን ኢየሱስ : ክርስ
ቶስም፡ወንጌልን፡ሲሰጠው፡አየ።

፲፱፤ የሀገረ : ሜራ : ኤጲስቆጶስም : በአረፈ : ጊዜ :
ለሮሜ : ሊቀ : ጳጳሳት : መልአክ : በራእይ :
ተገልጾ : ስለ : አባ : ኒቆላዎስ : ነገረው : ስሙ
ንና : የመልኩን : አምሳያም : አስረዳው ። በነ
ቃም : ጊዜ : ያየውን : ለኤጲስቆጶሳቱ : ነገራ
ቸው : እነርሱም : በሰሙ : ጊዜ : ራእዩ : እው
ነት፡እንደሆነ፡ሁሉም፡አመኑ፡ቅዱስ፡ኒቆላዎ
ስንም፡ወስደው፡በሀገረ፡ሜራ፡ላይ፡ኤጲስቆ
ጶስነት፡ሾሙት።

፳፤ ዲዮቅልጥያኖስም : ሲነግሥ : ክዶ : ጣዖታትን :
በአመለከ፡ጊዜ፡ሰዎችን፡ሁሉ፡ጣዖታትን፡እን
ዲአመልኩ : አዘዛቸው : ይህ : አባ : ኒቆላዎስ :
ግን :ሕዝቡን : የሚያስተምራቸውና : በቀናች :
ሃይማኖት፡የሚያጸናቸው፡ሆነ።

፳፩፤ የቅዱስ : አባ : ኒቆላዎስንም : ዜና : በሰማ :
ጊዜ፡ዲዮቅልጥያኖስ፡ይዞ፡ለብዙ፡ዓመታት፡
ታላቅ : ሥቃይን : አሠቃየው : ክብር : ይግ
ባውና፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስም፡በትዕ
ግሥት : አጸናው : ያለ : ጉዳትም : በጤና :
አስነሣው፡ዲዮቅልጥያኖስም፡ከማሠቃየቱ፡
የተነሣ : በሰለቸ : ጊዜ : ከወህኒ : ቤት :

www.ethiopianorthodox.org

እስከ ፡ አጥፍአ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዲዮቅልጥ
ያኖስ፡ወአንገሦ፡ለቈስጠንጢኖስ፡ጻድቅ።

፳፱ ወእምዝ ፡ አውጽአሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ሙቁሐን፡ተአማንያን፡በክርስቶስ፡ወምስሌሆሙ፡ ብፁዕ ፡ ኒቆላዎስ ፡ ወገብአ ፡ ውስተ ፡ መካነ ፡ ሢመቱ ፡ ወነበረ ፡ እንዘ ፡ ይሜህሮሙ ፡ ለኵሎሙ፡ሕዝብ፡ሃይማኖተ፡ርትዕተ።

፴ ወሶበ ፡ ኮነ ፡ ማኅበረ ፡ ጉባኤ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ፫፻፲ወ፰ቱ ፡ ርቱዓነ ፡ ሃይማኖት ፡ ወዝንቱ ፡ አብ ፡ አሐዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወምስሌሆሙ ፡ ሰደዶ ፡ ለአርዮስ ፡ ወሠርዐ ፡ ኵሎ ፡ ቀኖና ፡ ዘቤተ፡ክርስቲያን።

፴፩ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ፈጸመ ፡ ገድሎ ፡ ሠናየ ፡ ወአሥመሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወእምድኅረ ፡ ነበረ ፡ በመንበረ ፡ ጽጽስናሁ ፡ እም ፵ ዓመት ፡ ዘይፈድፍድ፡አዕረፈ፡በሰላም።

፴፪ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ጨመረው ፡ እግዚአብሔርም ፡ ዲዮቅልጥያኖስን፡ አጥፍቶ ፡ ጻድቅ ፡ ቈስጠንጢኖስን ፡ እስከ አነገሠው፡ድረስ፡በዚያ፡ኖረ።

፳፱ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ክርስቶስን ፡ በማመን ፡ የታሠሩትን ፡ ሁሉንም ፡ አወጡአቸው ፡ ከእርሳቸውም ፡ ጋር ፡ ቅዱስ ፡ ኒቆላዎስ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ፡ መንበረ ፡ ጵጵስናው ፡ ተመለሰ ፡ ሕዝቡንም ፡ ሁሉ፡የቀናች፡ሃይማኖትን፡እያስተማራቸው፡ ኖረ።

፴ ሃይማኖታቸው፡የቀና፡የሦስት፡መቶ፡ዐሥራ፡ ስምንት፡ኤጲስቆጶሳት፡የአንድነት፡ስብሰባ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ አባት ፡ ከእሳቸው ፡ አንዱ ፡ ነው፡ ከእርሳቸውም ፡ ጋር፡ ሁኖ ፡ አርዮስን ፡ አሳደደው፡የቤተ፡ክርስቲያንንም፡ሥርዓት፡ ሠራ።

፴፩ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ያማረ ፡ ተጋድሎውን ፡ በፈጸመ፡ጊዜ፡እግዚአሔርንም፡አገልግሎ፡በመንበረ ፡ ጵጵስናው ፡ ከአርባ ፡ ዓመት ፡ የሚበዛ ፡ ከኖረ፡በኋላ፡በሰላም፡አረፈ።

፴፪ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡ በዚህ ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ትደርብን፡ለዘላለሙ፡አሜን።

<u>አርኬ</u>

ሰላም ፡ ለኒቆላዎስ ፡ ዘውዱስ ፡ ዝክሩ። በውስተ ፡ ሜራ ፡ ሀገሩ ። ተደሙ ፡ ሕዝቡ ፡ ወአዝማዲሁ ፡ አንከሩ።
በዕለተ፡ተወልደ፡ሶበ፡ኪያሁ፡ነጸሩ።መጠነ፡ክልኤቱ፡ሰዓት፡ቀዊሞ፡በእግሩ።

፩ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮኑ ፡ ሰማዕተ ፡ ቅዱሳን ፡ ተላስስ ፡ ወአልዓዛር ፡ ወዝንቱ ፡ ተላስስ ፡ እምሰብአ ፡ ባቢሎን ፡ እምደወለ ፡ ነነዌ ፡ ወአኀዞ ፡ ሳቦር ፡ ንጉሠ ፡ ፋርስ ፡ ወይቤሎ ፡ ስግድ ፡ ለእሳት ፡ ወሡዕ ፡ ለአማልክት ፡ ወይቤሎ፡ ቅዱስ፡ ተላስስ፡ አንሰ፡ እሰግድ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላኪየ፡ ወሎቱ ፡ እሠውዕ ። ወሶቤሃ ፡ አዘዘ ፡ ያምጽኡ ፡ መቃኒተ ፡ ሥቃይ ፡ ከመ ፡ ያፍርሆ ፡ ውእቱሰ ፡ ኢፈርሀ ፡ ወአዘዘ ፡ ይቅሥፍዎ ፡ ምእተ ፡ ቅሥፈታተ ፡ ነዋኀ ፡ ሰዓተ ። ወእምዝ ፡ ይቤሎ ፡ አ ፡ ተላስስ ፡ ከመ ፡ ታዕርፍ ፡ እምዝንቱ ፡ ኵነኔ ፡ ሡዕ ፡ ለአማልክት፡ወይቤሎ፡ተላስስ፡ሊተሰ፡ኢተዐውቀኒ፡ ኵነኔከ፡እስመ፡አምላኪየ፡የዓቅበኒ።

፪ ወሶቤሃ፡ቀሠፍዎ፡፪ተ፡፫ተ፡ጊዜያተ፡ወተከሉ፡

፩ በዚችም ፡ ቀን ፡ ቅዱሳን ፡ ተላስስና ፡ አልዓዛር ፡ በሰማዕትነት ፡ አረፉ። ይህም ፡ ተላስስ ፡ ከነነዌ ፡ አውራጃ ፡ ከባቢሎን ፡ ሰዎች ፡ ወገን ፡ ነው፡ የፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ ሳቦርም ፡ ይዞት ፡ ለእሳት ፡ ስገድ ፡ ለአማልክትም ፡ ሠዋ ፡ አለው፡ ቅዱስ ፡ ተላስስም ፡ እኔስ ፡ ለፈጣሪዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ እሰግዳለሁ ፡ ለእርሱም ፡ እሠዋለሁ ፡ እንጂ ፡ ለጣዖት ፡ አልሠዋም ፡ አለው ። ያስፈራውም ፡ ዘንድ፡ የቅጣት ፡ መሣሪያዎችን ፡ አስመጣ ፡ እርሱ ፡ ግን፡ አልፈራም ፡ መቶ፡ ግርፋትንም ፡ ለረዥም፡ጊዜ፡እንዲገርፉት፡አዘዘ፡ከዚህም፡ በኋላ ፡ ተላስስ ፡ ሆይ ፡ ከዚህ ፡ ሥቃይ ፡ እንድታርፍ ፡ ለአማላክት ፡ ሠዋ ፡ አለው፡ እርሱም ፡ ፈጣሪዬ ፡ ስለሚጠብቀኝ ፡ ለእኔ ፡ ሥቃይህ ፡ አልታወቀኝም፡አለው።

፪ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ጊዜ ፡ ገረፉት ፡

www.ethiopianorthodox.org

ውስተ ፡ አዕይንቲሁ ፡ ቅንዋተ ፡ ወዘበጥዎ ፡ በመክድነ ፡ ብርት ፡ እስከ ፡ ስእነ ፡ አውሥኦተ ፡ ወመተሩ ፡ ርእሶ ፡ በሰይፍ ።

፳፰፡ ወእምዝ ፡ አቅረብዎ ፡ ለአልዓዛር ፡ ወይቤልዎ ፡ ሳቦር ፡ ንጉሥ ፡ ሡዕ ፡ ለአማልክት ፡ ወሶበ ፡ አበየ ፡ ሠዊዐ ፡ ለአማልክቲሁ ፡ ርእሳን ፡ ሶቤሃ ፡ ወረዎ ፡ ውስተ ፡ እሳት ፡ ወፈጸመ ፡ ስምዖ ፡ ሠናየ ።

፳፱፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቶሙ ፡ ለሰማዕት ፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

በዐይኖቹም ፡ ውስጥ ፡ የብረት ፡ ችንካሮችን ፡ ተከሉ ፡ መናገርም ፡ እስከሚሳነው ፡ በነሐስ ፡ መክደኛ ፡ ሸፍነው ፡ ደበደቡት ፡ ራሱንም ፡ በሰይፍ ፡ ቆረጡ ።

፳፰፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አልዓዛርን ፡ አቀረቡት ፡ ንጉሥ ፡ ሳቦርም ፡ ለአማልክት ፡ ሠዋ ፡ አለው ፡ ለረከሱ ፡ አማልክቶቹም ፡ መሠዋትን ፡ እምቢ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ወዲያውኑ ፡ ወደ ፡ እሳት ፡ ወረወረው ፡ ያማረ ፡ ምስክርነቱንም ፡ ፈጸመ ።

፳፱፡ ለእግዚአሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በሰማዕታት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለከሙ ፡ ተላስስ ፡ ቅሡፍ ። ወአልዓዛር ፡ ዓዲ ፡ በውሳጤ ፡ ነድ ፡ ግዱፍ ። አድኅኑኒ ፡ ሊተ ፡ እመ ፡ ይደኅን ፡ እምጽንፍርት ፡ ዖፍ ። ወከመ ፡ ያመሥጥ ፡ ወይጠል ፡ እመሥገርት ፡ ገሪፍ ። ሥገርተ ፡ ልሳን ፡ ወአፍ ። ከመ ፡ ያመሥጥ ፡ ወይጠል ፡ እመሥገርት ፡ ገሪፍ ።

፴፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈት ፡ ቅድስት ፡ ሱርስት ፡ እምሀገረ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ ወለተ ፡ ክቡራን ፡ ሰብእ ።

፴፩፡ ወዛቲ ፡ ቅድስት ፡ ተሐፅየት ፡ ለአሐዱ ፡ ወልደ ፡ ብእሲ ፡ ክቡር ፡ ወሰሚዓ ፡ ዘንተ ፡ ትቤሎ ፡ ለአቡሃ ፡ አብሐኒ ፡ ቅድመ ፡ ከመ ፡ እሑር ፡ ወእስግድ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ወበተመይጦትየ ፡ ይከውን ፡ በከመ ፡ ፈቀደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይቤላ ፡ አቡሃ ፡ ባኢ ፡ ቅድመ ፡ ኀበ ፡ መጻምርትኪ ፡ ወእምድኅረ ፡ ተፈጸመ ፡ ከብካብኪ ፡ ተሐውሪ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ኀበ ፡ ዘፈቀድኪ ፡ ወትፌጽሚ ፡ ብፅዓተኪ ፡ ወይእቲ ፡ ትቤሎ ፡ ተካየድክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ውስተ ፡ እንትኩ ፡ መካን ፡ ቅድስት ፡ ከመ ፡ እጸሊ ፡ እንዘ ፡ አነ ፡ ድንግል ፡ ወእመሰ ፡ ሐሰውኩ ፡ ቃልየ ፡ ይትመዓዕ ፡ ላዕሌየ ፡ እግዚአብሔር ።

፴፪፡ ወእምዝ ፡ ፈነዋ ፡ አቡሃ ፡ ምስለ ፡ ወዓልት ፡ ወአእማት ፡ ዘይትለአክዋ ፡ ወወሀባ ፡ ወርቀ ፡ መጠነ ፡ ፫ቱ ፡ ፻ት ፡ ዲናር ፡ ከመ ፡ ተሀብ ፡ ምጽዋተ ፡ ወበጺሓ ፡ ህየ ፡ ዖደት ፡ ውስተ ፡ ኵሎን ፡ መካናት ፡ ቅዱሳት ፡ ወበጺሓ ፡ ውስተ ፡ ምኔተ ፡ ግብጸውያን ፡ ረከበት ፡ አረጋዌ ፡ መነኮሰ ፡ ለቢሶ ፡ ሠቀ ፡ ወነገረቶ ፡ ኵሎ ፡ ዘውስተ ፡ ልባ ፡ ወእቲኒ ፡ ይቤላ ፡ ፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለይኩን ።

፴፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ ከቍስጥንጥንያ ፡ አገር ፡ ለከበሩ ፡ ሰዎች ፡ ልጅ ፡ የሆነች ፡ ቅድስት ፡ ሱርስት ፡ አረፈች ።

፴፩፡ ይችም ፡ ቅድስት ፡ ለአንድ ፡ ለከበረ ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ ታጨች ፡ ይህንንም ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ አባቷን ፡ እንዲህ ፡ አለችው ፡ አስቀድሜ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሔጄ ፡ እሰግድ ፡ ዘንድ ፡ ፍቀድልኝ ፡ በምመለስበት ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ፈቀደ ፡ ይሁን ፡ አባቷም ፡ አስቀድመሽ ፡ ወደባልሽ ፡ ግቢ ፡ ሠርግሽ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ወደድሽው ፡ ሒደሽ ፡ ስዕለትሽን ፡ ትፈጽሚያለሽ ፡ አላት ፡ እርሷም ፡ በድንግልናዬ ፡ ሳለሁ ፡ ወደዚያች ፡ የከበረች ፡ ቦታ ፡ ሒጄ ፡ ልጸልይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ገብቻለሁ ፡ ቃሌን ፡ ብዋሽ ፡ በእኔ ፡ ላይ ። እግዚአብሔር ፡ ይቆጣል ፡ አለችው ።

፴፪፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አባቷ ፡ ከሚያገለግሏት ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ አሽከሮች ፡ ጋር ፡ አሰናበታት ፡ ለምጽዋትም ፡ የምትሰጠው ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ያህል ፡ የወርቅ ፡ ዲናር ፡ ሰጣት ፡ ወደዚያም ፡ በደረሰች ፡ ጊዜ ፡ በከበሩ ፡ ቦታዎች ፡ ሁሉ ፡ ዞረች ፡ ወደ ፡ ግብጸውያን ፡ ገዳምም ፡ በደረሰች ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ አረጋዊ ፡ መነኵስ ፡ ማቅ ፡ ለብሶ ፡ አገኘች ፡ የልቧንም ፡ ሁሉ ፡ ሐሳብ ፡ ነገረችው ፡ እርሱም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ይሁን ፡ አላት ።

www.ethiopianorthodox.org

፴፫፤ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ተደለዉ ፡ ለሐዊር ፡ ወገቢእ ፡ ውስተ ፡ ሀገሮሙ ፡ ቦአት ፡ ኀበ ፡ መካነ ፡ ጽማዌ ፡ ወጸሐፈት ፡ ኀበ ፡ ወላድያኒሃ ፡ እንዘ ፡ ትብል ፡ አንሰ ፡ አቅረብኩ ፡ ነፍስየ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢትኅሥሡኒ ፡ እስመ ፡ ኢትረክቡኒ ፡ ወአሠረት ፡ መጽሐፈ ፡ በልብሳ ፡ ወሤመቶ ፡ ውስተ ፡ ንዋያ ፡ ወአምሰለቶሙ ፡ ከመ ፡ ተሐውር ፡ ምስሌሆሙ ፡ ወሶበ ፡ ቀደምዋ ፡ እሊአሃ ፡ ጽዒኖሙ ፡ ንዋየ ፡ ወትቤሎ ፡ ለገብር ፡ ዘምስሌሃ ፡ ሀሎ ፡ አንሰ ፡ እፈቅድ ፡ እጸሊ ፡ ውስተ ፡ መካነ ፡ ጎልጎታ ፡ እምቅድመ ፡ ሑረትነ ፡ ወይቤላ ፡ ነዋ ፡ ቀደሙነ ፡ እሊአነ ፡ እፎ ፡ ተሐውሪ ፡ ባሕቲተኪ ፡ ወትቤሎ ፡ ሚ ፡ ላዕሌከ ፡ አሐውር ፡ ባሕቲትየ ፡ ወእትመየጥ ።

፴፬፤ ወእምዝ ፡ ነሥአታ ፡ ለአመታ ፡ ወቦአት ፡ ጎልጎታ ፡ ወትቤላ ፡ ለአመታ ፡ ተገኃሢ ፡ እምኔየ ፡ ወሶቢሃ ፡ ተሠወረታ ፡ ወበጽሐት ፡ ኀበ ፡ ውእቱ ፡ አረጋዊ ፡ መነኮስ ፡ ወሰገደት ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ፡ ወወሀበቶ ፡ ውእተ ፡ ፫፻ተ ፡ ዲናረ ፡ ወርቅ ፡ ከመ ፡ ይዝርዎ ፡ ለነዳያን ፡ ወዓዲ ፡ ሰአለቶ ፡ ከመ ፡ ያመንኵሳ ፡ ውእቱኒ ፡ ላጸየ ፡ ርእሳ ፡ ወአልበሳ ፡ አልባሰ ፡ ምንኵስና ፡ ዘውእቱ ፡ ሠቅ ፡ ወጸለየ ፡ ላዕሌሃ ፡ ወአብሐ ፡ ከመ ፡ ትሑር ፡ ኀበ ፡ መርሐ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይእቲ ፡ ሖረት ፡ ወቦአት ፡ ውስተ ፡ በዓት ፡ እንዘ ፡ ወለተ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ዓመት ፡ ይእቲ ፡ ወነበረት ፡ ውስተ ፡ ይእቲ ፡ በዓት ፡ ዘእንበለ ፡ ትርአይ ፡ ገጸ ፡ ሰብእ ፡ ፳ወ፲ተ ፡ ዓመታተ ።

፴፭፤ ወሀሎ ፡ መነኮስ ፡ መስተጋድል ፡ ዘስሙ ፡ ሲላስ ፡ እምሀገረ ፡ ቃህራ ፡ ወሎቱ ፡ ቦ ፡ ፍቁር ፡ ፈላሲ ፡ ገዳማዊ ፡ ዘየኀድር ፡ ውስተ ፡ በዓታተ ፡ ቀልሞን ፡ ወለለዕለታት ፡ ይሔውጾ ፡ ምስለ ፡ ንስቲት ፡ መብልዕ ፡ ወይትባረክ ፡ እምኔሁ ፡ ወሶበ ፡ በጽሐ ፡ ፋሲካ ፡ ነሥአ ፡ ኀዳጠ ፡ ኅብስተ ፡ ወሖረ ፡ በከመ ፡ ልማዱ ፡ ወኃሠሦ ፡ ወኢረከቦ ፡ ወፃመወ ፡ በኃሢሦቱ ፡ ወዔለ ፡ አድባረ ፡ ወአውግረ ፡ ወእምዝ ፡ ረከበ ፡ አሠረ ፡ ምክያደ ፡ ብእሲ ፡ ወተለዎ ፡ ወረከበ ፡ ሙባአ ፡ ንስቲተ ፡ ወይቤ ፡ ባርክ ፡ ላዕሌየ ፡ አ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወሶበ ፡ ኃጥአ ፡ ዘይሠጥዎ ፡ ቦአ ፡ ውስጠ ፡ ወረከበ ፡ መነኮሰ ፡ ንቡረ ፡ ጽምወ ፡ ወሰገደ ፡ ካልኡኒ ፡ ሰገደ ፡ ወሰአለ ፡

፴፫፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሀገራቸው ፡ ተመልሰው ፡ ሊሔዱ ፡ በተዘጋጁ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሥውር ፡ ቦታ ፡ ገብታ ፡ ለወላጆቿ ፡ እኔ ፡ ሰውነቴን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አቅርቢያለሁ ፡ አታገኙኝምና ፡ አትፈልጉኝ ፡ ብላ ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፈች ፡ ደብዳቤውንም ፡ በልብሷ ፡ አሥራ ፡ ከዕቃዋ ፡ ውስጥ ፡ አኖረችው ፡ ከእሳቸውም ፡ ጋር ፡ የምትሔድ ፡ መሰላቸው ፡ ሰዎቿም ፡ ዕቃ ፡ ጭነው ፡ በቀደሟት ፡ ጊዜ ፡ ከእርሷ ፡ ጋር ፡ ያለውን ፡ አገልጋይ ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ ጎልጎታ ፡ ገብቼ ፡ ልጸልይ ፡ እሻለሁ ፡ አለችው ። እርሱም ፡ እነሆ ፡ ሰዎቻችን ፡ ቀድመውናል ፡ ብቻሽን ፡ እንዴት ፡ ትሔጃለሽ ፡ አላት ፡ እርሷም ፡ አንተ ፡ ምን ፡ አግዶህ ፡ ብቻዬን ፡ ሔጄ ፡ እመለሳለሁ ፡ አለችው ።

፴፬፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሴት ፡ አገልጋይዋን ፡ ይዛ ፡ ወደ ፡ ጎልጎታ ፡ ገባችና ፡ አገልጋይዋን ፡ ከእኔ ፡ ራቅ ፡ በዩ ፡ አለቻት ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ተሠወረቻት ፡ ወደዚያ ፡ ሽማግሌ ፡ መነኰስም ፡ ደርሳ ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ ሰገደችለት ፡ ለድሆችም ፡ እንዲአከፋፍለው ፡ ያንን ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ የወርቅ ፡ ዲናር ፡ ሰጠችው ፡ ዳግመኛም ፡ ያመነኵሳት ፡ ዘንድ ፡ ለመነችው ፡ እርሱም ፡ ራሷን ፡ ላጭቶ ፡ የምንኵስና ፡ ልብስን ፡ አለበሳት ፡ ይኸውም ፡ የማቅ ፡ ነው ፡ በላይዋም ፡ ጸለየላት ፡ እግዚአብሔርም ፡ ወደ ፡ መራት ፡ ትሔድ ፡ ዘንድ ፡ ፈቀደላት ፡ እርሷም ፡ ሒዳ ፡ ወደ ፡ አንዲት ፡ ዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ገባች ፡ እርሷ ፡ የዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ብላቴና ፡ ስትሆን ፡ የሰው ፡ ፊት ፡ ሳታይ ፡ በዚያች ፡ ዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ሃያ ፡ ሰባት ፡ ዓመታት ፡ ኖረች ።

፴፭፤ ቃህራ ፡ ከሚባል ፡ አገር ፡ በገድል ፡ ሥራ ፡ የሚኖር ፡ ሲላስ ፡ የሚባል ፡ መነኰስ ፡ ነበረ ፡ ለርሱም ፡ መጸተኛ ፡ ገዳማዊ ፡ በቀልሞን ፡ ዋሻ ፡ ውስጥ ፡ የሚኖር ፡ ወዳጅ ፡ አለው ፡ በየጊዜውም ፡ ጥቂት ፡ ምግብ ፡ በመያዝ ፡ በመጎብኘት ፡ ከእርሱ ፡ በረከትን ፡ ይቀበላል ፡ ፋሲካም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ጥቂት ፡ እንጀራ ፡ ይዞ ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ሔዶ ፡ ፈለገው ፡ ግን ፡ አላገኘውም ፡ በመፈለግም ፡ ደከመ ፡ ተራራዎችንና ፡ ኮረብታዎችንም ፡ ዞረ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሰው ፡ ርግጫ ፡ ዱካ ፡ አግኝቶ ፡ ተከተለው ፡ ታናሽ ፡ መግቢያም ፡ አገኘና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ሆይ ፡ ባርከኝ ፡ አለ ፡ የሚመልስለትም ፡ በአጣ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡

www.ethiopianorthodox.org

፴፡ ወነቂሖ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ አዘዘ ፡ ያምጽእዎ ፡ ለውእቱ ፡ መነኮስ ፡ ወአኀዘ ፡ ይቅላዕ ፡ ልብሶ ፡ ከመ ፡ ይርአይ ፡ ዘባኖ ፡ ዘቈስለ ፡ ወሶቤሃ ፡ ወድቀ ፡ ልብሱ ፡ እምላዕሌሁ ፡ ወረከብዎ ፡ ከመ ፡ ሕፅው ፡ ውእቱ ፡ ወበከየ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ወሠዐሮሙ ፡ ለእለ ፡ አምጽእዎ ፡ ወዘበጥዎ ፡ እመዐርጊሆሙ ፡ ወከልአሙ ፡ ተመጥዎተ ፡ ቍርባን ፡ መጠነ ፡ ፫ቱ ፡ ዓመት ፡ ወፈቀደ ፡ ከመ ፡ የሀቦ ፡ ፻ተ ፡ ዲናረ ፡ ውእቱሰ ፡ ኢፈቀደ ፡ ነሢአ ፡ ወሖረ ፡ ውስተ ፡ በዓቱ ፡ ወነበረ ፡ እንዘ ፡ ይትጋደል ፡ ወእምዝ ፡ አዕረፈ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ።

፴፩፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

፴፪፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ካዕበ ፡ ተዘካረ ፡ ዕረፍቶሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ሜልዮስ ፡ ወታውፍያ ። ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ አሜን ።

* * *

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፲ወ፩ ለታኅሣሥ ። በዛቲ ፡ ዕለት ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ በኪሞስ ። አዕረፈ ፡ ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ እምሰብአ ፡ ሀገረ ፡ ሬስ ፡ እምደወለ ፡ መጺል ፡ እምደቡበ ፡ ግብጽ ።

፪፡ ወኮነ ፡ ውእቱ ፡ ዘየዐቅብ ፡ አባግዐ ፡ አቡሁ ፡ ወእንዘ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ፲ ወ ፪ ዓመት ፡ አስተርአዮ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ። በአምሳለ ፡ ወሬዛ ፡ ወይቤሎ ፡ ትመጽእኑ ፡ ከመ ፡ ንሑር ፡ ኅቡረ ፡ ወንኩን ፡ መነኮሳተ ፡ ውእቱኒ ፡ ይቤ ፡ እወ ፡ ወተሰነዓዉ ፡ ፪ሆሙ ፡ ወሖሩ ፡ ኅቡረ ፡ ኅበ ፡ ገዳመ ፡ አስቄጥስ ፡ ወረከቡ ፡ ሠለስተ ፡ መነኮሳተ ፡ አረጋውያነ ፡ ወነበረ ፡ አባ ፡ በኪሞስ ፡ በኀቤሆሙ ፡ ፳ወ፬ተ ፡ ዓመታተ ።

፫፡ ወእምዝ ፡ ሖረ ፡ አባ ፡ በኪሞስ ፡ እምህየ ፡ መጠነ ፡ ምሕዋረ ፡ ሠለስቱ ፡ ዕለት ፡ ወቦአ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ ርኁቅ ፡ ወአስተርአዩ ፡ ሎቱ ፡ ሰይጣናት ፡ በአምሳለ ፡ አኅርው ፡ ወአክይስት ፡ ወአብቀዉ ፡ አፉሆሙ ፡ ከመ ፡ ይንስክዎ ፡ ወዐገ

፴፡ አባ ፡ ዮሐንስም ፡ በነቃ ፡ ጊዜ ፡ ያንን ፡ መነኰሴ ፡ ያመጡት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ የቈሰለ ፡ ጀርባውንም ፡ ሊአይ ፡ ልብሱን ፡ ሲይዝ ፡ ከላዩ ፡ ልብሱ ፡ ወደቀ ፡ ጃንደረባም ፡ ሁኖ ፡ አገኙት ፡ አባ ፡ ዮሐንስም ፡ አለቀሰ ፡ ያመጡትንና ፡ የደበደቡትን ፡ ከመዐርጋቸው ፡ ሽሮ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ቅዱስ ፡ ቍርባንን ፡ ከመቀበል ፡ ከለከላቸው ፡ መቶ ፡ ዲናርንም ፡ ሊሰጠው ፡ ወደደ ፡ እርሱም ፡ ግን ፡ መውሰድ ፡ አልፈለገም ፡ ወደ ፡ በዓቱ ፡ ሒዶ ፡ እየተጋደለ ፡ ኖረ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በዚች ፡ ዕለት ፡ አረፈ ።

፴፩፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

፴፪፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ ደግሞ ፡ የቅዱሳን ፡ ሜልዮስና ፡ የታውፍያ ፡ የዕረፍታቸው ፡ መታሰቢያ ፡ ነው ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ አሜን ።

* * *

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ታኅሣሥ ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ የግብጽ ፡ ደቡብ ፡ ከሆነ ፡ ከመጺል ፡ አውራጃ ፡ ከሬስ ፡ ከተማ ፡ ሰዎች ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ ቅዱስ ፡ አባት ፡ አባ ፡ በኪሞስ ፡ አረፈ ።

፪፡ እርሱም ፡ የአባቱን ፡ በጎች ፡ የሚጠብቅ ፡ ነበር ፡ ዕድሜውም ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ሲሆነው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የታዘዘ ፡ መልአክ ፡ በጐልማሳ ፡ አምሳል ፡ ተገለጠለትና ፡ በአንድነት ፡ ሒደን ፡ እንመነኵስ ፡ ዘንድ ፡ ትሻለህ ፡ አለው ፡ እርሱም ፡ አዎን ፡ አለ ፡ ሁለቱም ፡ ተስማምተው ፡ ወደ ፡ አስቄጥስ ፡ ገዳም ፡ በአንድነት ፡ ተጓዙ ፡ ሦስት ፡ አረጋውያን ፡ መነኰሳትንም ፡ አገኙ ፡ አባ ፡ በኪሞስም ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ሃያ ፡ አራት ፡ ዓመታትን ፡ ኖረ ።

፫፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አባ ፡ በኪሞስ ፡ ከዚያ ፡ ተነሥቶ ፡ የሦስት ፡ ቀን ፡ ጐዳና ፡ ያህል ፡ ተጓዘና ፡ ሩቅ ፡ ወደ ፡ ሆነ ፡ በረሀ ፡ ውስጥ ፡ ገባ ፡ ሰይጣናትም ፡ በእሪያዎችና ፡ በዘንዶዎች ፡ አምሳል ፡ ሁነው ፡ መጡበት ፡ ሊነክሱትም ፡ አፋቸውን ፡

www.ethiopianorthodox.org

ትዎ፡ውእቱሰ፡አእመረ፡ሕሊናሆሙ፡ለአጋንንት፡ወነፍሐ፡ላዕሌሆሙ፡በኃይለ፡እግዚአብሔር፡ወሶቤሃ፡ተዘርዉ።

፬፡ ወውእቱ ፡ ረከበ ፡ ፈለገ ፡ ወነበረ ፡ በህየ ፡ ፫ተ ፡ ዓመተ ፡ እንዘ ፡ ይጸውም ፡ በበሱባዔ ፡ ወበተፍጻሜተ ፡ ሱባዔ ፡ ይመልዕ ፡ በእራኁ ፡ ተምረ ፡ ወይበልዕ ፡ ወማየኒ ፡ ንስቲተ ፡ ይሰቲ ፡ ወይጼሊ ፡ በሌሊት ፡ ፳ወ፬፻ተ ፡ ጸሎታተ ፡ ወበመዓልት፡ከማሁ፡ይጼሊ፡አቡነ፡ዘበሰማያት።

፭፡ ወእምዝ ፡ ነበረ ፡ መጠነ ፡ ፳ወ፬ ፡ ዓመት ፡ እንዘ ፡ ይጸውም ፡ በበ፵ ዕለት ፡ ወበተፍጻሜተ ፡ ፵ዓ ፡ ዕለት ፡ ይበልዕ ፡ አሐተ ፡ ጊዜ፡ወእምዝ፡ጾመ፡አሐተ፡ጊዜ፡፹ ዕለተ፡እስከ፡ተላጸቃ፡አዕፅምቲሁ፡ምስለ፡ማዕሱ፡ወሶቤሃ፡አምጽአ፡ሎቱ፡መልአከ፡እግዚአብሔር፡ኅብስተ፡ከመ፡ይብላዕ፡ወማየ፡ከመ፡ይስተይ፡ወነበረ፡ውእቱ፡ማይ፡ወኅብስት፡ብዙኀ፡ዓመታተ፡ወኢኀልቀ፡እስከ፡አመ፡አዕረፈ።

፮፡ወአስተርአዮ፡እግዚአብሔር፡አምላክ፡በራእየ፡ሌሊት፡ወአዘዞ፡ከመ፡ይትመየጥ፡ኀበ፡ሀገሩ፡ወተንሥአ ፡ ሶቤሃ ፡ ወሖረ ፡ ወበጽሐ ፡ ኀበ ፡ ሀገሩ ፡ ወሐነፀ ፡ በህየ ፡ ማኅደረ ፡ ንስቲተ ፡ ወኀደረ ፡ ውስቴቱ ፡ ባሕቲቶ ፡ ወኮነ ፡ ፀወነ ፡ ወመርሶ ፡ ወተስፋ ፡ ሠናየ ፡ ለኵሉ ፡ ዘይመጽእ ፡ ኀቤሁ ፡ ወኵሎሙ ፡ ሰብእ ፡ ነበሩ ፡ እንዘ ፡ ይትናዘዙ ፡ ቦቱ ፡ በትምህርታቲሁ ፡ ወይቀንኡ ፡ ቅንአተ፡ መንፈሳዌ ፡ በአምልኮቱ፡ንጹሕ፡ወጽድቁ፡ወተጋድሎቱ።

፯፡ወበአሐቲ፡ዕለት፡ፆሮ፡መልአከ፡እግዚአብሔር ወአብጽሖ፡ኀበ፡ምድረ፡ኤፍራጥስ፡እስመ፡ሰብአ ፡ ውእቱ ፡ ብሔር ፡ ኮኑ ፡ ዘተዐደዉ ፡ ወወጽኡ ፡ እምፍኖተ ፡ ጽድቅ ፡ ወሜጠሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ውስተ ፡ ሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ወምግባር ፡ ሠናይ ፡ ወእምዝ ፡ ተመይጠ፡ኀበ፡መካኑ።

፰፡ወአሐተ፡ጊዜ፡እንዘ፡የሐውር፡ውስተ፡ሀገር፡ፀዊሮ፡መሣይምተ፡ከመ፡ይሢጥ፡ወይርከብ፡ሲሳዮ፡ወደክመ፡በፍኖት፡ወአንበሮን፡ለመሣይምት፡ወነበረ፡ከመ፡ያዕርፍ፡ንስቲተ፡

ከፍተው፡ከበቡት፡እርሱ፡ግን፡የአጋንንትን፡ሐሳብ፡አወቀ፡በእግዚአብሔርም፡ኃይል፡እፍ፡አለባቸው፡በዚያንም፡ጊዜ፡ተበተኑ።

፬፡ እርሱም ፡ ወንዝ ፡ አገኘ ፡ ሰባት ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ እየጾመ፡ በዚያ፡ሦስት፡ዓመት፡ኖረ፡በሱባዔውም፡መጨረሻ፡በመሀል፡እጁ፡ተምር፡መልቶ፡ያንን፡ይመገባል፡ውኃም፡በጥቂቱ፡ይጠጣል ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ጊዜ ፡ በሌሊት ፡ እንዲሁም ፡ በቀን ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ጊዜ ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያትን፡ይጸልያል።

፭፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አርባ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ እየጾመ ፡ ሃያ፡አራት፡ዓመታት፡ያህል፡ኖረ፡አርባውም፡ቀን ፡ ሲፈጸም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይበላል ፡ ከዚህም፡በኋላ፡አንድ፡ጊዜ፡ቆዳው፡ከዐጥንቶቹ፡ጋር ፡ እስቲጣበቅ ፡ ሰማንያ ፡ ቀን ፡ ጾመ ፡ በዚያንም፡ጊዜ፡የእግዚአብሔር፡መልአክ፡ይበላና፡ይጠጣ፡ዘንድ፡እንጀራና፡ውኃን፡አመጣለት፡ያም፡ውኃና፡እንጀራ፡ሳያልቅ፡እስከ፡አረፈ፡ድረስ፡ብዙ፡ዓመታትን፡ኖረ።

፮፡ ፈጣሪ፡ እግዚአብሔርም ፡ በሌሊት ፡ ራእይ ፡ ተገልጦ፡ወደ፡አገሩ፡እንዲመለስ፡አዘዘው፡በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ተነሥቶ ፡ ሔደ ፡ ወደ ፡ አገሩም፡ደርሶ፡በዚያ፡ታናሽ፡ማደሪያ፡ጎጆ፡ሠርቶ፡በውስጡ፡ብቻውን፡የሚኖር፡ሆነ፡ወደርሱም ፡ ለሚመጣ ፡ ሁሉ ፡ መጠጊያና ፡ ወደብ፡በጎ፡አለኝታም፡ሆነ፡ሰዎችም፡ሁሉ፡በትምህርቱ፡እየተጽናኑ፡ኖሩ፡ንጹሕ፡በሆነ፡አምልኮቱ ፡ በትሩፋቱና ፡ በተጋድሎው ፡ መንፈሳዊ፡ቅናትን፡ይቀኑበት፡ነበር።

፯፡በአንዲት፡ዕለትም፡ከእግዚአብሔር፡የታዘዘ፡መልአክ፡ተሸክሞ፡ወደ፡ኤፍራጥስ፡ምድር፡አደረሰው፡የዚያ፡አገር፡ሰዎች፡በመተላለፍ፡ከእውነተኛ፡ሃይማኖት፡ወጥተው፡ነበርና፡ሁሉንም፡ወደ፡ቀናች፡ሃይማኖትና፡ወደ፡በጎ፡ምግባር፡መለሳቸው፡ከዚያም፡ወደ፡ቦታው፡ተመለሰ።

፰፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ሸጦ ፡ ምግቡን፡ያገኝ፡ዘንድ፡አገልግሎችን፡ተሸክሞ፡ወደ፡ከተማ፡ሲሔድ ፡በጐዳና፡ላይ፡ደክሞት፡አገልግሎቹን ፡ አስቀምጦ ፡ ጥቂት ፡ ያርፍ ፡ ዘንድ ፡

ወፆሮ ፡ ሶቤሃ ፡ ኃይለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአብጽሖ ፡ ኀበ ፡ መካን ፡ ዘይፈቅድ ፡ መሣይ ምትኒ ፡ ምስሌሁ ።

፱፡ ወውእተ ፡ አሚረ ፡ ርእየ ፡ አባ ፡ ሲኖዳ ፡ ዓምደ ፡ ዕንቈ ፡ ባሕርይ ፡ ልዑለ ፡ ወደንገፀ ፡ ወይቤ ፡ ምንት ፡ ውእቱ ፡ ዝንቱ ፡ ዐምድ ፡ ዐቢይ ፡ ወአስተርአዮ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአባ ፡ ሲኖዳ ፡ ወይቤሎ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ አባ ፡ በኪሞስ ፡ ወበጊዜሃ ፡ ተንሥአ ፡ አባ ፡ ሲኖዳ ፡ ወአንሶሰወ ፡ በእግሩ ፡ እስከ ፡ በጽሐ ፡ ኀበ ፡ ሀገሩ ፡ ለአባ ፡ በኪሞስ ፡ ወእምቅድመ ፡ ይእቲ ፡ ዕለት ፡ ኢርእየ ፡ ገጾ ፡ ግሙራ ፡ ወሶበ ፡ ተራከቡ ፡ ፪ሆሙ ፡ ተአምኁ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ወፈቀደ ፡ አባ ፡ በኪሞስ ፡ ከመ ፡ ያብስል ፡ ንስቲተ ፡ ጸብሐ ፡ ወይቤሎ ፡ ለአባ ፡ ሲኖዳ ፡ ንሥአ ፡ ለዛቲ ፡ ቀሱት ፡ ሑር ፡ ወቅዳሕ ፡ ማየ ፡ ወምላዕ ፡ ወአምጽእ ፡ ሊተ ፡ ወሶቤሃ ፡ ተንሥአ ፡ አባ ፡ ሲኖዳ ፡ ወፆራ ፡ ለይእቲ ፡ ቀሱት ፡ ወቀድሐ ፡ ማየ ፡ ወመልአ ፡ ወአምጽአ ፡ ሎቱ ፡ ወረከቦ ፡ ለውእቱ ፡ ጸብሕ ፡ ፍሉሐ ፡ ወብሱለ ፡ ወውእተ ፡ ጊዜ ፡ አእመረ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ አባ ፡ በኪሞስ ፡ ወደገመ ፡ ምስሌሁ ፡ ሰላመ ፡ ወተአምኖተ ።

፲፡ ወእምዝ ፡ ነገሮ ፡ አባ ፡ ሲኖዳ ፡ ዘከመ ፡ ርእየ ፡ ራእየ ፡ በእንቲአሁ ፡ ወነበረ ፡ በኀቤሁ ፡ ኅዳጠ ፡ መዋዕለ ።

፲፩፡ ወካዕበ ፡ በአሐቲ ፡ ዕለት ፡ እንዘ ፡ ያንሶስዉ ፡ እሙንቱ ፡ ኅቡረ ፡ ረከቡ ፡ ርእሰ ፡ ምውት ፡ ወነክነኮ ፡ አባ ፡ ሲኖዳ ፡ በበትሩ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ተንሥእ ፡ አ ፡ ምውት ፡ ከመ ፡ ትንግረነ ፡ ወታጠይቀነ ፡ ዘርኢከ ፡ ወሶቤሃ ፡ ገብአት ፡ ነፍሱ ፡ ውስተ ፡ ይእቲ ፡ ዐፅም ፡ ወኮነ ፡ ሥጋ ፡ ወተንሥአ ፡ ወሰገደ ፡ ሎሙ ፡ ወነግሮሙ ፡ ኵሎ ፡ ግብረ ፡ ሲኦል ፡ ወእለ ፡ ይትኴነኑ ፡ ውስቴታ ፡ ብበፆታሆሙ ፡ ወበእንተ ፡ ርእሱ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ አረማዊ ። ወይቤ ፡ ቦ ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ እምታሕቴነ ፡ ሰብእ ፡ ክርስቲያን ፡ እለ ፡ አምኑ ፡ በስሙ ፡ ለእግዚእ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ዘኢዐቀቡ ፡ ትእዛዞ ፡ ወእለ ፡ ሖሩ ፡ በሑረተ ፡ አሕዛብ ፡ ወበርኵስና ፡ አረሚ ፡ ዘነበሩ ። ወይቤልዎ ፡ ቅዱሳን ፡ ስክብ ፡ ወኑም ፡ ወበጊዜሃ ፡ ሰከበ ፡ ወኮነ ፡ ከመ ፡ ቀዳሚ ።

ተቀመጠ ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ከአገልግሎቹ ፡ ጋር የእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ተሸክሞ ፡ ወደሚሻው ፡ ቦታ ፡ አደረሰው ።

፱፡ በዚያንም ፡ ወቅት ፡ አባ ፡ ሲኖዳ ፡ ከፍተኛ ፡ የዕንቈ ፡ ባሕርይ ፡ ምሰሶ ፡ በራእይ ፡ አየና ፡ ይህ ፡ ታላቅ ፡ ምሰሶ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ደነገጠ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ተገልጦ ፡ ይህ ፡ አባ ፡ በኪሞስ ፡ ነው ፡ አለው ። አባ ፡ ሲኖዳም ፡ ወዲያውኑ ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ አባ ፡ በኪሞስ ፡ አገር ፡ እስቲደርስ ፡ በእግሩ ፡ ተጓዘ ፡ ከዚያችም ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ከቶ ፡ አላየውም ፡ ነበር ፡ በተገናኙም ፡ ጊዜ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሰላምታ ፡ ተሰጣጡ ።
አባ ፡ በኪሞስም ፡ ወጥ ፡ ሊአበስል ፡ ወደደ ፡ አባ ፡ ሲኖዳንም ፡ ይቺን ፡ እንስራ ፡ ያዛትና ፡ ሔደህ ፡ ውኃ ፡ ቀድተህ ፡ መልተህ ፡ አምጣልኝ ፡ አለው ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ አባ ፡ ሲኖዳ ፡ ተነሣና ፡ ያቺን ፡ እንስራ ፡ ተሸከማት ፡ ውኃውንም ፡ ቀድቶ ፡ መልቶ ፡ አመጣለት ፡ ወጡንም ፡ ፈልቶና ፡ በስሎ ፡ አገኘው ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ አባ ፡ በኪሞስ ፡ መሆኑን ፡ አወቀ ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ሰላምታን ፡ ደገመ ፡ እጅ ፡ በመነሣሣትም ፡ ሰላምታ ፡ ተለዋወጡ ።

፲፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አባ ፡ ሲኖዳ ፡ ስለርሱ ፡ ያየውን ፡ ራእይ ፡ ነገረው ፡ በእርሱም ፡ ዘንድ ፡ ጥቂት ፡ ቀኖች ፡ ኖረ ።

፲፩፡ ዳግመኛም ፡ በአንዲት ፡ ቀን ፡ በአንድነት ፡ ሲጓዙ ፡ የሞተ ፡ ሰው ፡ ራስ ፡ አገኙ ፡ አባ ፡ ሲኖዳም ፡ በበትሩ ፡ ነቅንቅ ፡ አደረገውና ፡ ምውት ፡ ሆይ ፡ ያየኸውን ፡ ትነግረንና ፡ ታስረዳን ፡ ዘንድ ፡ ተነሣ ፡ አለው ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ነፍሱ ፡ ወደ ፡ ዐፅሙ ፡ ተመልሳ ፡ ሥጋ ፡ ለብሶ ፡ ተነሣና ፡ ሰገደላቸው ፡ በሲኦል ፡ የሚሠራውንም ፡ ሁሉ ፡ በየወገናቸውም ፡ በውስጧ ፡ የሚሠቃዩትን ፡ እርሱም ፡ አረማዊ ፡ እንደሆነ ፡ ነገራቸው ። እንዲህም ፡ አለ ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ በጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ያመኑ ፡ ትእዛዙን ፡ ግን ፡ ያልጠበቁ ፡ በአሕዛብ ፡ ሥራና ፡ በአረማውያን ፡ ርኵስት ፡ የኖሩ ፡ ከእኛ ፡ በታች ፡ የሚኖሩ ፡ ክርስቲያኖች ፡ አሉ ፡ አለ ፡ ቅዱሳንም ፡ ተመልሰህ ፡ ተኛ ፡ አሉት ፡ ወዲያውኑ ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ሆነ ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፪፤ ወእምዝ ፡ ተአምኖ ፡ አባ ፡ ሲኖዳ ፡ ለብፁዕ ፡ አባ፡በኪሞስ፡ወተመይጠ፡ኀበ፡መካኑ።

፲፫፤ ወሶበ፡ቀርበ፡ጊዜ፡ፍልሰቱ፡ለአባ፡በኪሞስ፡ ክቡር ፡ ጸውዖ ፡ ለላእኩ ፡ ወአዘዞ ፡ ከመ ፡ ይቅብር ፡ ሥጋሁ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ዘሀሎ ፡ ውስቴቱ ፡ ወእምዝ ፡ ሐመ ፡ ንስቲተ ፡ በሕማመ ፡ ፈጸንት ፡ ወርእዮሙ ፡ ለማኅበረ ፡ ቅዱሳን ፡ እንዘ ፡ ይመጽኡ ፡ ኀቤሁ ፡ ወሶቤሃ ፡ መጠወ፡ነፍሶ፡ውስተ፡እደ፡እግዚአብሔር፡ ወአዕረግዋ፡መላእክት፡እንዘ፡ይሴብሑ፡ወይወይዜምሩ፡እስከ፡አብጽሕዋ፡ውስተ፡ኢየሩሳሌም፡ሰማያዊት።

፲፬፤ ወኮነ ፡ ኵሉ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ፸ዓ ፡ ወነበረ ፡ ፲ወ፪ተ ፡ ዓመተ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ወውስተ ፡ ግብረ፡ምንኵስና፡፶ወ፰ተ፡ዓመተ።

፲፭፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፲፪፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አባ ፡ ሲኖዳ ፡ ቅዱስ ፡ በኪሞስን ፡ ተሰናብቶ ፡ ወደ ፡ ቦታው ፡ ተመለሰ።

፲፫፤ ዕረፍቱም ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ በኪሞስ ፡ አገልጋዩን ፡ ጠርቶ ፡ በኖረበት ፡ ቦታ ፡ ሥጋውን፡ እንዲቀብር ፡ አዘዘው ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በሆድ ፡ ዝማ ፡ ሕመም ፡ ጥቂት ፡ ታመመ ። ቅዱሳንን ፡ በአንድነት ወደርሱ ፡ ሲመጡ ፡ አያቸው ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ፡ ነፍሱን፡በእግዚአብሔር፡እጅ፡ሰጠ። መላእክትም፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡ሰማያዊት፡ እስከአደረሷት ፡ እያመሰገኑና ፡ እየዘመሩ ፡ አሳረጓት።

፲፬፤ መላ፡ዕድሜውም፡ሰባ፡ዓመት፡ሆነ፡ዐሥራ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ በዓለም ፡ ውስጥ ፡ ሃምሳ ፡ ስምንት፡ዓመት፡በምንኵስና፡ሥራ፡ኖረ።

፲፭፤ ለእግዚአብሔር፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡ በዚህ፡አባት፡ጸሎት፡ይማረን፡በረከቱም፡ ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለከ ፡ ፀዋሬ ፡ ክቡድ ፡ አስፈሬዳ ። ወመንሥኤ ፡ ምውት ፡ በምድረ ፡ በዳ ። ዐስበ ፡ ፃማከ ፡ በኪሞስ፡ ወዘተቀንዮትከ፡ፍዳ። መንበረ፡ብርሃናዌ፡ወአክሊለ፡ክብር፡ፀዓዳ።እግዚአብሔር እርአዮ፡ ለአባ፡ሲኖዳ።

፲፮፤ ወበዛቲ፡ዕለት፡ተዝካሮሙ፡ለበርተሎሜዎስ፡ ኤጲስቆጶስ፡ወበጥላን፡ሰማዕት፡በረከቶሙ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፲፮፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ የኤጲስቆጶሱ ፡ በርተሎሜዎስና፡ የሰማዕቱ፡በጥላን፡መታሰቢያቸው፡ ነው ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለከ፡በርተሎሜዎስ፡ አቡነ።ዘደለወከ፡በርትዕ፡ኤጲስቆጶስ፡ከዊነ።እምጽድቅ፡ኵሉ፡ዘይጸንሐነ።ኃይለ፡ጸሎትከ፡ይዕቀብ፡ኪያነ።በአምሳለ፡ብንት፡ዘየዓቅብ፡ዐይነ።

ሰላም፡ለልደትከ፡ቴዎድሮስ፡ ፍሡሐ፡ገጽ። አምሳለ፡ፍሬ፡ሥርናይ፡ወፍሬ፡ሠናይ፡ዕፅ። ውስተ፡ፍኖትከ፡ሚጠኒ፡እምነ፡ፍኖትየ፡ዘዳኀጽ።በእንተ፡ሥጋከ፡በዝብጠተ፡በትር፡ቅሩጽ።ወበእንተ፡ዐፅምከ፡ካዕበ፡በማኅረፅ፡ኀሩፅ።

* * *

፩፤ በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩፡ አምላክ፡አመ፡፲ወ፪ለታኅሣሥ፡በዛቲ፡ዕለት፡ ተዝካረ ፡ በዓሉ ፡ ለቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት፡እስመ፡በዛቲ፡ዕለት፡ወበዝ፡ወርኀ፡

* * *

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ታኅሣሥ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ የቅዱስ፡ሚካኤል፡የበዓሉ፡መታሰቢያ፡ነው።

www.ethiopianorthodox.org

ፈነዎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ ባቢሎን ፡ ወኮነ ፡ ራብዓየ ፡ ገጸ ፡ ምስለ ፡ ፫ቱ ፡ ደቂቅ ፡ አናንያ ፡ ወአዛርያ ፡ ወሚሳኤል ፡ ሶበ ፡ ገደፎሙ ፡ ውስተ ፡ እቶነ ፡ እሳት ፡ ናቡከደነፆር ፡ ንጉሠ ፡ ባቢሎን ።

፪፤ ወተለዓለ ፡ ነበልባለ ፡ እሳት ፡ መጠነ ፡ ፵፱ ፡ ወ፱ቱ ፡ በእመት ፡ ወአውዓዮሙ ፡ ለእለ ፡ ወደ ይዎሙ ፡ ሰብእ ፡ ወለእለ ፡ ያነድዱ ፡ እሳተ ፡ ወዝንቱ ፡ መልአክ ፡ ሚካኤል ፡ ክቡር ፡ ዘበጦ ፡ ለነበልባለ ፡ እሳት ፡ በበትረ ፡ እዴሁ ፡ ወአ ጥፍአ ፡ እምላዕለ ፡ ፫ቱ ፡ ደቂቅ ፡ ወአድኃኖሙ ፡ ወኢ.ለከፎሙ ፡ ወረሰዮ ፡ ለእሳት ፡ ከመ ፡ ጠል ፡ ቈሪር ፡ ዘጊዜ ፡ ጽባሕ ።

፫፤ ወበውእቱ ፡ ጊዜ ፡ ሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር አምላከ ፡ አበዊነ ፡ ስቡሕኒ ፡ ውእቱ ፡ ወል ዑልኒ ፡ ውእቱ ፡ ለዓለም ፡ ዘንተ ፡ ፮ተ ፡ ቃላተ ፡ ተነበዩ ፡ ከመ ፡ እምድኅረ ፡ ፮ቱ ፡ ፻ት ፡ ዓመት ፡ ይትወለድ ፡ ክርስቶስ ።

፬፤ ወእምዝ ፡ ባረክዎ ፡ ፴ወ፫ተ ፡ ጊዜያተ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ይባርክዎ ፡ ኵሉ ፡ ግብረ ፡ እግዚእ ፡ ለእ ግዚአብሔር ፡ ስቡሕኒ ፡ ውእቱ ፡ ወልዑልኒ ፡ ውእቱ ፡ ለዓለም ። በዝንቱኒ ፡ አመሩ ፡ ከመ ፡ ክርስቶስ ፡ ይነብር ፡ዲበ ፡ ምድር ፡ ሠላሳ ፡ ወሠለስተ ፡ ዓመተ ።

፭፤ ወበእንተዝ ፡ ሠርዑ ፡ አበዊነ ፡ መምህራነ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመ ፡ ንግበር ፡ ተዝካረ ፡ በዓሉ ፡ ለሊቀ ፡ መላእክት ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ።

፮፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም ሐረነ ፡ በትንብልናሁ ፡ ለቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

በዚች ፡ ቀን ፡ በዚህ ፡ ወር ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደባ ቢሎን ፡ አገር ፡ ላከው ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከ ደነፆር ፡ ሦስቱን ፡ ልጆች ፡ አናንያን ፡ አዛርያንና ፡ ሚሳኤልን ፡ ከእሳት ፡ ማንደጃ ፡ ውስጥ ፡ በጣላ ቸው ፡ ጊዜ ፡ አራተኛ ፡ ገጽ ፡ ሁኖ ፡ ታየ ።

፪፤ የእሳቱም ፡ ነበልባል ፡ አርባ ፡ ዘጠኝ ፡ ክንድ ፡ ያህል ፡ ወደላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ፡ የጨመሩአ ቸውን ፡ ሰዎችና ፡ እሳት ፡ የሚያንዱትን ፡ አቃ ጠላቸው ፡ ይህም ፡ የከበረ ፡ መልአክ ፡ ሚካኤል ፡ የእሳቱን ፡ ነበልባል ፡ በበትሩ ፡ መትቶ ፡ ከሦስ ስቱ ፡ ደቂቅ ፡ ላይ ፡ አጥፍቶ ፡ አዳናቸው ፡ ምንም ፡ አልነካቸውም ፡ እንደ ፡ ቀዘቀዘ ፡ እንደ ፡ ጧት ፡ ጤዛ ፡ አድርጎታልና ።

፫፤ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ የአባቶቻችን ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ፡ እያሉ ፡ ስድስት ፡ ቃላትን ፡ ተናገሩ ፡ በዚህም ፡ ከስድስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደሚወለድ ፡ ትንቢት ፡ ተናገሩ ።

፬፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሥራዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ያመሰግኑታል ፡ እርሱ ፡ ለዘላለሙ ፡ ምስጉን ፡ ልዑልም ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ሠላሳ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ አመሰገኑት ፡ በዚህም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሠላሳ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ክርስቶስ ፡ እንደሚኖር ፡ አመለከቱ ።

፭፤ ስለዚህም ፡ አባቶቻችን የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መምህራን ፡ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ የሆነ ፡ የቅ ዱስ ፡ ሚካኤልን ፡ የበዓሉን ፡ መታሰቢያ ፡ እን ድናደርግ ፡ ሠሩ ።

፮፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ አማላጅነት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለከ ፡ ዐቃቤ ፡ ቅዱሳን ፡ እምተሀውኮ ። ወለፀረ ፡ ነፍሶሙ ፡ ዘሞቃኮ ። አመ ፡ መጽአ ፡ ወልድ በአፈ ፡ ነቢያት ፡ ተሰቢኮ ። ከመ ፡ ያስተፋኑ ፡ ሐራ ፡ መልአኮ ። እስከ ፡ ምጽንዓት ፡ ኃምስ ፡ ሚካኤል ፡ ተለውኮ ።

፯፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ካዕበ ፡ ተዝካረ ፡ ዕረፍቱ ፡ ለአብ ፡ ክቡር ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ፡ ዘዋልድባ ።

፰፤ ወለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ስመ ፡ አቡሁ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ወስመ ፡ እሙ ፡ አመተ ፡ ማርያም ፡ ወእሙንቱ ፡

፯፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡ ዳግመኛ ፡ የከበረ ፡ አባት ፡ የዋ ልድባው ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ፡ የዕረፍቱ ፡ መታሰ ቢያ ፡ ነው ።

፰፤ ለዚህም ፡ ቅዱስ ፡ የአባቱ ፡ ስም ፡ እስጢፋኖስ ፡ የእናቱ ፡ ስም ፡ አመተ ፡ ማርያም ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ኄራን ፡ ወክቡራን ፡ ዘመድ ፡ ወወለድዎ ፡ በምድረ ፡ አክሱም ፡ ወሶበ ፡ ልሕቀ ፡ መሀርዎ ፡ መጻሕፍተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ። ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ሞቱ ፡ አቡሁ ፡ ወእሙ ፡ ሖረ ፡ ኀበ ፡ ደብረ ፡ መንኰል ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ አድኃኒ ፡ ወለብሰ ፡ አልባሰ ፡ ምንኵስና ፡ ወነበረ ፡ እንዘ ፡ ይትጋደል ፡ በጾም ፡ ወበጸሎት ፡ ወኢይበልዕ ፡ ዘእንበለ ፡ ሐምል ፡ ዘጼአ ፡ ወአጸየ ፡ ወስቴሁኒ ፡ ማይ ፡ ወይትለአኮሙ ፡ ለመነኰሳት ፡ በግብረ ፡ ማኅረፅ ፡ ወበቀዲሐ ፡ ማይ ።

፱፡ ወሶበ ፡ አጽሐብዎ ፡ አዝማዲሁ ፡ እንዘ ፡ ይመጽኡ ፡ ኀቤሁ ፡ ሖረ ፡ ኀበ ፡ ካልዕ ፡ መካን ፡ ወተጸምደ ፡ በጾም ፡ ወበቀዊም ፡ ወበሰጊድ ፡ እስከ ፡ ሐብጣ ፡ እገሪሁ ፡ ወእምህየኒ ፡ ሖረ ፡ ገዳመ ፡ ወነበረ ፡ ፵ዓ ፡ መዓልተ ፡ ወ፵ዓ ፡ ሌሊተ ፡ እንዘ ፡ ኢይጥዕም ፡ ምንተኒ ፡ ወይመጽኡ ፡ ኀቤሁ ፡ አናብስት ፡ ወአናምርት ፡ ወኵሎሙ ፡ አራዊት ፡ ግሩማን ፡ ወይሰግዱ ፡ ወይልሕሱ ፡ ፀበለ ፡ እገሪሁ ።

፲፡ ወአሐተ ፡ ዕለተ ፡ እንዘ ፡ የሐውር ፡ ውስተ ፡ ፍኖት ፡ በጽሐ ፡ ኀበ ፡ ፈለግ ፡ ዘምሉዕ ፡ ማየ ፡ ወሀሎ ፡ ምስሌሁ ፡ መጽሐፍ ፡ ወእሳት ፡ ወገቢሮ ፡ ጸሎተ ፡ ቦአ ፡ ውስተ ፡ ማይ ፡ ወውኅጦ ፡ ማይ ፡ ወአውረዶ ፡ ታሕተ ፡ ወበኃይለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሶበ ፡ ገደፎ ፡ ማዕዶተ ፡ ረከቦ ፡ ለመጽሐፍ ፡ እንዘ ፡ ኢይደመሰስ ፡ ወለእሳት ፡ እንዘ ፡ ኢይጠፍእ ።

፲፩፡ ወሰይጣንሰ ፡ ያሜክሮ ፡ ተመሲሎ ፡ አራዊተ ፡ ግሩማነ ፡ ወእቱሰ ፡ ኢፈርሀ ፡ እስመ ፡ እሡር ፡ ሕሊናሁ ፡ በትውክልተ ፡ አምላኩ ። ወእንዘ ፡ ይጼሊ ፡ ለሊሁ ፡ መጽአ ፡ ኀቤሁ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወኀተመ ፡ በምራቁ ፡ ኵሎ ፡ መለያልያቲሁ ፡ ወመልአ ፡ ኃይለ ፡ ወኮነ ፡ እምይእቲ ፡ ዕለት ፡ ሞቅሐ ፡ እገሪሁ ፡ ወለብሰ ፡ ሠቀ ፡ ወለለኵሉ ፡ ለያልይ ፡ ይበውእ ፡ ውስተ ፡ ማይ ፡ ወያበጽሕ ፡ መዝሙረ ፡ ፭ተ ፡ ጊዜያተ ፡ ወይቀሥፍ ፡ ዘባኖ ፡ ዘአልቦ ፡ ኍልቍ ።

፲፪፡ ወአናብስት ፡ ይትረአዩ ፡ ውስተ ፡ በዓቱ ፡ ከመ ፡ አባግዕ ፡ ወእቱኒ ፡ ይሰፍር ፡ አካሎሙ ፡ ወይ

እነርሱም ፡ በዘመድ ፡ የከበሩ ፡ ደጎች ፡ ናቸው ፡ በአክሱም ፡ ምድርም ፡ ወለዱት ፡ በአደገ ፡ ጊዜም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ መጻሕፍት ፡ አስተማሩት ፡ አባቱና ፡ እናቱም ፡ በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ በንኰል ፡ ገዳም ፡ ወደ ፡ አባ ፡ አድኃኒ ፡ ሒዶ ፡ የምንኵስና ፡ ልብስን ፡ ለብሶ ፡ በጾምና ፡ በጸሎት ፡ እየተጋደለ ፡ ኖረ ። ፈጽሞ ፡ ከሻገተ ፡ ጎመን ፡ በቀር ፡ አይበላም ፡ የሚጠጣውም ፡ ውኃ ፡ ነው ፡ እህል ፡ በመፍጨትና ፡ ውኃ ፡ በመቅዳት ፡ ሥራ ፡ መነኰሳቱን ፡ ይረዳቸው ፡ ነበር ።

፱፡ ዘመዶቹም ፡ ወደርሱ ፡ እየመጡ ፡ በአስቸገሩት ፡ ጊዜ ፡ ወደሌላ ፡ ቦታ ፡ ሔደ ፡ እግሮቹም ፡ እስቲያብጡ ፡ ድረስ ፡ በጾም ፡ በስግደት ፡ በመቆም ፡ ተጋደለ ፡ ከዚያም ፡ ወደሌላ ፡ በረሀ ፡ ሒዶ ፡ አርባ ፡ መዓልት ፡ አርባ ፡ ሌሊት ፡ ምንም ፡ ምን ፡ ሳይቀምስ ፡ ኖረ ፡ አንበሶችና ፡ ነብሮች ፡ የሚያስፈሩም ፡ አራዊት ፡ ሁሉ ፡ ወደርሱ ፡ በመምጣት ፡ ይሰግዱለታል ፡ የእግሮቹን ፡ ትቢያ ፡ ይልሱ ፡ ነበር ።

፲፡ በአንዲት ፡ ዕለትም ፡ በጐዳና ፡ ሲጓዝ ፡ ታላቅ ፡ ወንዝን ፡ ውኃው ፡ መልቶ ፡ አገኘ ፡ መጽሐፍና ፡ እሳትም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ነበረ ፡ ጸሎትንም ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ውኃው ፡ ገባ ፡ ውኃውም ፡ ዋጠውና ፡ ወደታች ፡ አወረደው ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ኃይል ፡ ወደማዶ ፡ በጣለው ፡ ጊዜ ፡ መጽሐፉ ፡ ሳይደመሰስ ፡ እሳቱም ፡ ሳይጠፋ ፡ አገኘው ።

፲፩፡ ሰይጣንም ፡ በሚያስፈሩ ፡ አራዊት ፡ እየተመሰለ ፡ ይፈታተነው ፡ ነበር ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ፈጣሪውን ፡ በመታመን ፡ ልቡ ፡ የታሠረና ፡ የጸና ፡ ስለሆነ ፡ አይፈራም ። እርሱም ፡ ሲጸልይ ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወደርሱ ፡ መጣ ፡ በምራቁም ፡ መላ ፡ ሕዋሳቱን ፡ ቀብቶ ፡ ኃይልን ፡ አሳደረበት ፡ ከዚያችም ፡ ዕለት ፡ ጀምሮ ፡ እግሮቹን ፡ የሚያሥር ፡ ሆነ ። ማቅንም ፡ ለብሶ ፡ በየሌሊቱ ፡ ሁሉ ፡ ከውኃ ፡ ውስጥ ፡ በመግባት ፡ የዳዊትን ፡ መዝሙር ፡ አምስት ፡ ጊዜ ፡ ያደርሳል ፡ ቍጥር ፡ በሌለውም ፡ ግርፋት ፡ ጀርባውን ፡ ይገርፍ ፡ ነበር ።

፲፪፡ አንበሶችም ፡ በበዓቱ ፡ አጠገብ ፡ ይሰማራሉ ፡ እርሱም ፡ አካላቸውን ፡ ይሰፍራል ፡ ይለካል ፡

www.ethiopianorthodox.org

በጥሕ፡ቊስሎሙ፡ወያወጽእ፡እምኔሆሙ፡
ሦከ፡ወአሜከላ።

፲፫፤ ወእምዝ፡ተጋብኡ፡ኀቤሁ፡ብዙኃን፡አር
ድእት፡ወተጸምዱ፡ወእምኔሆሙ፡ቀዳማይ፡
አባ፡ዘሩፋኤል።

፲፬፤ ወአሐተ፡ዕለተ፡ተራከበ፡ምስለ፡አባ፡ገብረ፡
መስቀል፡ዘደብረ፡ሊጋስ፡ወእምቅድመ፡
ዝኒ፡ኢተናጸሩ፡ወወዐሉ፡እንዘ፡ይዜያነዉ፡
ዕበያቲሁ፡ለእግዚአብሔር፡ወበጊዜ፡ድራር፡
ሶበ፡ገብሩ፡ጸሎተ፡ወረደ፡ሎሙ፡ማዕድ፡
ሥሩዕ፡ወበልዑ፡ወአእኰትዎ፡ለእግዚአ
ብሔር።

፲፭፤ ወእምዝ፡በአሐቲ፡ዕለት፡ተራከበ፡ምስለ፡፩
ገዳማዊ፡ወሶበ፡ወጠኑ፡ይትናገሩ፡ምሥጢ
ራተ፡ዘገብረ፡ሎሙ፡እግዚአብሔር፡ይቤ፡
አቡነ፡ሳሙኤል፡ናሁ፡፲ተ፡ወ፪ተ፡ዓመተ፡
ኮነኒ፡ሊተ፡እንዘ፡እቀውም፡ውስተ፡አርያም፡
ወአዐጥን፡መንበረ፡አምላክ፡ምስለ፡፳ወ፬ቱ፡
ካህናተ፡ሰማይ። ወሶበ፡ይበውእ፡ይቀድስ፡
ቊርባነ፡ይወርድ፡ሎቱ፡ኅብስት፡ወጽዋዐ፡
ወይን፡ወሶበሂ፡ያነብብ፡ውዳሴሃ፡ለእግዝ
እትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡ማርያም፡ይት
ሌዓል፡እምድር፡መጠነ፡እመት፡ወመ
ጽአት፡ኀቤሁ፡እግዝእትነ፡ማርያም፡ወሀ
በቶ፡ዕንቌ፡ዘያበርህ፡ወዕጣነ፡ንጹሐ።

፲፮፤ ወእምዝ፡ሶበ፡ቀርበ፡ፍልሰቱ፡መጽአ፡
ቅዱስ፡ ሚካኤል፡ሊቀ፡መላእክት፡ወመ
ሠጦ፡በክነፊሁ፡ወአርአዮ፡ኵሎ፡ተድላሃ፡
ለኢየሩሳሌም፡ሰማያዊት፡ወአብጽሖ፡
ቅድመ፡መንበሩ ለእግዚአብሔር፡ልዑል፡
ወነሥአ፡ኪዳነ፡ለዘይጼውዕ፡ስሞ፡ወይ
ገብር፡ተዝካሮ፡ወተመይጠ፡ውስተ፡በዓቱ፡
ነገሮሙ፡ለአርዳኢሁ፡ኵሎ፡ዘርእየ፡ወእ
ምዝ፡አዕረፈ፡በሰላም።

፲፯፤ ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ኪያነኒ፡ይም
ሐረነ፡በጸሎቱ፡ለዝንቱ፡አብ፡ቅዱስ፡ወበረ
ከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ቊስላቸውንም፡በጥቶ፡እሾህና፡አሜከላ፡ያወ
ጣለቸዋል።

፲፫፤ ከዚህም፡በኋላ፡ብዙ፡ደቀ፡መዛሙርት፡
ወደርሱ፡ተሰበሰቡ፡በተጋድሎም፡ተጠ
መዱ፡ከእርሳቸውም፡የመጀመሪያው፡አባ፡
ዘሩፋኤል፡ነው።

፲፬፤ በአንዲትም፡ዕለት፡በገዳመ፡ሊጋስ፡
ከሚኖር፡ ከአባ፡ገብረ፡መስቀል፡ጋር፡
ተገናኙ፡ከዚህም፡በፊት፡አልተያዩም፡ነበር፡
የእግዚአብሔርንም፡ገናናነት፡ሲጫዋወቱ፡
ዋሉ፡በራት፡ጊዜም፡ጸሎትን፡ሲያደርጉ፡
የተዘጋጀ፡ማዕድ፡ወርዶላቸው፡ተመግበው፡
እግዚአብሔርን፡አመሰገኑ።

፲፭፤ ከዚህም፡በኋላ፡በአንዲት፡ዕለት፡ከአንድ፡
ገዳማዊ፡ጋር፡ተገናኘ፡እግዚአብሔርም፡ያደ
ረገላቸውን፡ምሥጢር፡በሚነጋገሩ፡ጊዜ፡
አባታችን፡ሳሙኤል፡እንዲህ፡አለ፡እነሆ፡
እኔ፡በአርያም፡ቁሜ፡ከሃያ፡አራቱ፡ካህናተ፡
ሰማይ፡ጋር፡የአምላክን፡መንበር፡ሳጥን፡
ዐሥራ፡ሁለት፡ዓመት፡ሆነኝ። ለመቀደስም፡
በሚገባ፡ጊዜ፡ኅብስትና፡ወይንን፡የተመላ፡
ጽዋ፡ይውርድለታል። የእመቤታችን፡የቅድ
ስት፡ድንግል፡ማርያምን፡ውዳሴዋን፡ሲያ
ነብ፡ክንድ፡ያህል፡ከምድር፡ወደ፡ላይ፡ከፍ፡
ከፍ፡ይላል፡እመቤታችን፡ማርያምም፡ወደ
ርሱ፡መጥታ፡የሚያበራ፡ዕንቍንና፡ንጹሕ፡
ዕጣንን፡ሰጠችው።

፲፮፤ ፍልሰቱም፡ሲቀርብ፡የመላእክት፡አለቃ፡
ቅዱስ፡ሚካኤል፡በክንፎቹ፡ተሸክሞ፡
አወጣው፡የሰማያዊት፡ኢየሩሳሌምን፡ተድ
ላዋን፡ሁሉ፡አሳየው፡ወደ ልዑል፡እግዚአብ
ሔርም፡ዙፋን፡ፊት፡አቅርቦት፡ስሙን፡
ለሚጠራ፡መታሰቢያውንም፡ለሚያደርግ፡
ቃል፡ኪዳን፡ተቀበለ፡ወደ፡በዓቱም፡
ሲመለስ፤ ለደቀ፡መዛሙርቱ፡ነገራቸው፡
ከዚህም፡በኋላ፡በሰላም፡በፍቅር፡አረፈ።

፲፯፤ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛ
ንም፡በዚህ፡ቅዱስ፡አባት፡ጸሎት፡ይማረን፡
በረከቱም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡
አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለከ፡ዘፈረይከ፡ሕገ። ሳሙኤል፡ዘኮንከ፡ለአስካለ፡ወይን፡ሐረገ። በረድኤትከ፡ክፍለኒ፡ወእደ፡
ሀሎከ፡ዐሪገ። ረድኤትከሰ፡ወለተ፡ከለባት፡መዘገ። ምስለ፡ክቡራን፡ከመ፡ተሀሉ፡ደርገ።

www.ethiopianorthodox.org

| | |
|---|---|
| ፲፰፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ካዕበ ፡ ተዝካሩ ፡ ለአባ ፡ ኅድራ፡ ዘእምደብረ ፡ እስዋን ፡ ወተዝካሩ ፡ ለቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ ተአማኒ ፡ ወበረከቶሙ ፡ ትብጽሐነ ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አሜን። | ፲፰፡ በዚችም ፡ ዕለት ፡ ደግሞ ፡ የአባ ፡ ኅድራ ፡ ከደብረ ፡ እስዋን ፡ የታማኙም ፡ የቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ መታሰቢያ ፡ ነው ፡ በረከታቸውም ፡ ትድረሰን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ አሜን። |

## አርኬ

ሰላም፡ለከ፡ኅድራ፡ምእመን። ዘእምደብረ፡እስዋን። ሶበ፡እጼውዓከ፡ዘልፈ፡በውስተ፡ዛቲ፡መካን። ይሰደድ፡በጸሎትከ፡ወይጕየይ፡ሰይጣን። ከመ፡አስሐትያ፡ይሰደድ፡በነፋስ፡ቀጢን።

| | |
|---|---|
| ፲፱፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ማኅበረ ፡ ጉባኤ ፡ ቅዱሳን፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ወቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት፡በሀገረ፡ሮሜ። | ፲፱፡ በዚችም፡ቀን፡የቅዱሳን፡ኤጲስቆጶሳት፡የቀሳውስትና ፡ የዲያቆናት ፡ የአንድነት ፡ ስብሰባ፡በሮሜ፡ከተማ፡ሆነ። |
| ፳፡ ወዝንቱ፡ዘኮነ፡በቀዳሚ፡ዓመተ፡መንግሥቱ፡ ለዳኬዎስ ፡ ከሀዲ ፡ ወበሢመቱ ፡ ለቆርኔሌዎስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘሮሜ፡ወዲዮናስዮስ፡ ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘእስክንድርያ፡ወበላንድዮስ፡ ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘአንጾኪያ፡ወግርማኖስ፡ዘኢየሩሳሌም፡ ወምክንያቱሰ፡ ለዝንቱ፡ ማኅበረ፡ ጉባኤ፡በእንተ፡ብናጥስ፡ቀሲስ፡ዘስሕተ፡ በብሂሎቱ፡እስመ፡ኵሉ፡ዘክህደ፡በጊዜ፡ ስደት፡አው፡ዘወድቀ፡በዝሙት፡ወሚመ፡ በዘዘዚአሁ ፡ ኃጢአት ፡ ኢይደሉ ፡ ይትወከፍዎ፡ጊዜ፡ይኔስሕ። | ፳፡ ይህም ፡ የሆነው ፡ ከሀዲው ፡ ዳኬዎስ ፡ በነገሠ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ በሮሜው፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት፡በቆርኔሌዎስ፡የሹመት፡ዘመን፡በእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በዲዮናስዮስ ፡ ዘመን ፡ በላንድዮስም ፡ በአንጾኪያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ሁኖ ፡ ሳለ ፡ ግርማኖስም ፡ የኢየሩሳሌም፡ኤጲስቆጶስ፡ሁኖ፡ሳለ፡ነው፡ይህም፡ የሆነበት፡ምክንያት፡በስደት፡ጊዜ፡የካደ፡ ቢኖር፡ወይም፡በዝሙት፡የወደቀ፡ወይም፡ በየአይነቱ ፡ በሆነ ፡ ኃጢአት ፡ ቢሰናከል ፡ በንስሓ ፡ ሊቀበሉት ፡ አይገባም ፡ በማለቱ ፡ ስለ፡ቀሲስ፡ብናጥስ፡ነው። |
| ፳፩፡ ወገሠጾ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ አብ፡ በእንተዝ፡ ምእረ፡ ዳግመ፡ ወሥልሰ፡ ወኢሰምዖ፡ ወአስተጋብአ፡ ላዕሌሁ፡፴ ኤጲስቆጶሳተ፡ ፲ወ፰ተ፡ ቀሳውስተ፡ ወ፵፡ ዲያቆናተ፡ ማእምራነ፡ መጻሕፍት። ወተዋሥኡ፡ምስለ፡ብናጥስ፡ ቀሲስ፡በእንተ፡ዝንቱ፡ነገር፡ወአመክንዮ፡ ብናጥስ፡በቃለ፡ጳውሎስ፡ሐዋርያ፡ዘይቤ፡ በመልእክቱ፡ለሰብአ፡ዕብራውያን፡በ፮ቱ፡ አንቀጽ፡ዘይብል፡ኢይትከሃል፡እምድኅረ፡ ነሥኡ፡ጥምቀተ፡ወጥዕሙ፡ጸጋሁ፡ዘእምሰማያት፡ ወተሳተፉ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ። ወጥዕሙ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሠናየ ፡ ወኃይለ፡ዓለም፡ዘይመጽእ፡ኢይደሉ፡ከመ፡ ይደቁ፡የሐድስዋ፡ካዕበ፡ለንስሓሆሙ፡ወይ | ፳፩፡ አባት ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ዳግመኛም ፡ ሦስተኛም ፡ ጊዜ ፡ ገሠጸው ፡ መከረውም፡ግን፡አልሰማውም፡ስለዚህም፡ ሰልሳ ፡ ኤጲስቆጶሳትን ፡ መጻሕፍትን ፡ የተማሩ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ቀሳውስትና ፡ አርባ ፡ ዲያቆናትን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ሰበሰበ። እነርሱም፡ስለዚህ፡ነገር፡ብናጥስ፡ቀሲስን፡ ተከራከሩት፡ቀሲስ፡ብናጥስም፡ምክንያት፡ አድርጎ፡የተነሣው፡ ሐዋርያ፡ጳውሎስ፡ለዕብራውያን፡ሰዎች፡በስድስተኛው፡ምዕራፍ ጥምቀትን ፡ ከተቀበሉ ፡ በኋላ ፡ ከሰማይ ፡ የሚሰጥ ፡ ጸጋውን ፡ ከቀመሱ ፡ በኋላ ፡ በመንፈስ፡ቅዱስም፡አንድ፡ከሆኑ፡በኋላ፡ አይቻልም ። መልካሙንም ፡ የእግዚአብ |

www.ethiopianorthodox.org

ሴነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለጉባኤክሙ፡ውስተ፡አሐተኒ፡ከኒሳ።ኤጲስቆጶሳት፡ስሳ።ባህለ፡ብናጥስ፡ታጽርኡ፡ዘተመሰለ፡ከመ፡እንስሳ።ኢይተወከፉ፡ንስሓ፡ዘይቤ፡እምድኅረ፡ገብረት፡አበሳ።እስመ፡ኢትነጽሕ፡ነፍስ፡ዳግመ፡እምርኵሳ።

፳፮፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮኑ ፡ ሰማዕተ ፡ ቅዱሳን ፡ አንቂጦስ፡ወፎጢኖስ፡በመዋዕለ፡ዲዮቅል ጥያኖስ፡ከሀዲ።

፳፯፤ ወዝንቱ ፡ አንቂጦስ ፡ ሰማዕት ፡ ሶበ ፡ ርእየ ፡ መብዓልተ ፡ ኵነኔ ፡ ዘአግበሮሙ ፡ ንጉሥ ፡ ወአንበሮሙ፡ቅድሜሁ፡ከመ፡ያፍርሆሙ፡ለምእመናን ፡ ተንሥአ ፡ እማዕከለ ፡ ሕዝብ ፡ በጥቡዕ ፡ ልብ ፡ ወተዛለፎ ፡ ለንጉሥ ፡ ንጉ ሥኒ፡አዘዘ፡ይእሥርዎ፡ወያዕርግዎ፡ውስተ፡

ትያጥሮን ፡ ወይስድዱ ፡ ላዕሌሁ ፡ አንበሳ ፡ ጸዋገ ፡ ወበጺሐ ፡ አንበሳ ፡ ኀቤሁ ፡ ሰፍሐ ፡ የማኖ ፡ ወመዝመዘ ፡ ገጾ ፡ ወመላትሒሁ ። ወርእዮ ፡ ንጉሥ ፡ አዘዘ ፡ ይምትሩ ፡ ርእሶ ፡ በሰይፍ፡ወሶበ፡መልሐ፡ሰገራታዊ፡ሰይፎ፡ርዕደ፡ወስእነ፡ተሐውሶ፡ወካዕበ፡ወደይዎ፡ውስተ፡መንኰራኵር፡ዘርቡብ፡ታሕቴሁ፡አፍሐመ ፡ እሳት ፡ ወመናቅዕት ፡ ከመ ፡ ትትበተክ፡ነፍስቱ፡ፍጡነ፡ወአድኃኖ፡እግ ዚአብሔር ፡ እምዝኒ ፡ ወአንሥኦ ፡ ጥዑየ ፡ ዘእንበለ፡ሙስና።

፳፰፤ ወካዕበ፡አዘዘ፡ይደይዎ፡ውስተ፡ጽሕርት፡ ዘአፍልሁ ፡ ውስቴታ ፡ አረረ ፡ ወእንዘ ፡ ይኔጽሩ፡ ሕዝብ፡መጽአ፡መልአከ፡እግዚአ ብሔር፡ወመሠጠ፡እምውስተ፡ጽሕርት፡ ወአቀሞ፡ቅድመ፡ዲዮቅልጥያኖስ፡ወርእዮ፡ ፎጢኖስ ፡ ዘንተ ፡ ተአምረ ፡ መንክረ፡ ተንሥአ ፡ ዕራቆ ፡ ወተአምኖ ፡ ለእኁሁ ፡ አንቂጦስ ፡ ወረገሞ ፡ ለመምዓሊ ፡ እንዘ ፡ ይብል፡አ፡ኅሱር፡እፎ፡ትመውዖ፡ለእኁየ። ወሰሚዖ ፡ ዲዮቅልጥየኖስ፡ አዘዘ ፡ ይደዩ ፡ ውስተ ፡ ክሣውዲሆሙ ፡ ጋጋ ፡ ወውስተ፡ እገሪሆሙ፡ገንዶራ፡ወይደይዎሙ፡ውስተ፡

፳፮፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡ በከሀዲው ፡ ዲዮቅልጥ ያኖስ፡ ዘመን ፡ ቅዱሳን ፡ አንቂጦስና ፡ ፎጢ ኖስ፡በሰማዕትነት፡አረፉ።

፳፯፤ ይህም፡ሰማዕት፡አንቂጦስ፡ንጉሡ፡ምእመ ናንን፡ያሥራቸው፡ዘንድ፡አሠርቶ፡በፊቱ፡ ያኖራቸውን፡የሥቃይ፡መሣሪያዎች፡በአየ፡ ጊዜ ፡ በቆራጥነት ፡ ከሕዝብ ፡ መካከል ፡ ተነሥቶ፡ንጉሡን፡ተከራከረው፡ንጉሡም፡ አሥረው ፡ ወደ ፡ ጨዋታ ፡ ማያ ፡ ቦታ ፡ አውጥተው ፡ ክፉውን ፡ አንበሳ ፡ እንዲለ ቁበት ፡ አዘዘ ። አንበሳውም ፡ ወደርሱ ፡ በደ ረሰ ፡ ጊዜ ፡ ቀኝ ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ ፊቱንና ፡ ጕንጩን ፡ አሻሽቶ ፡ ተወው ፡ ንጉሡም ፡ አይቶ ፡ ራሱን ፡ በሰይፍ ፡ ይቆርጡ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ። ወታደሩም ፡ ሰይፉን ፡ በመዘዘ ፡ ጊዜ ፡ ተንቀጠቀጠ ፡ መንቀሳቀስም ፡ ተሳነው ፡ ሁለተኛም ፡ ሰውነቱ ፡ ፈጥና ፡ እንደትቆ ራረጥ ፡ ከበታቹ ፡ የእሳት ፡ ፍም ፡ ወደተነሠነ ሠበትና ፡ ቆራርጦ ፡ የሚለያይ ፡ መሣሪያ ፡ ወዳለው ፡ መንኰራኵር ፡ ውስጥ ፡ እንዲጨ ምሩት ፡ አዘዘ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከዚህ አድኖት፡ያለ፡ጉዳት፡በጤና፡አስነሣው።

፳፰፤ ዳግመኛም ፡ በውስጧ ፡ እርሳስ ፡ ወደአፈ ሉባት፡ጋን፡ውስጥ፡እንዲጨምሩት፡አዘዘ፡ ሕዝቡም፡እያዩ፡የእግዚአብሔር፡መልአክ፡ መጥቶ፡ከጋኑ፡ውስጥ፡ነጥቆ፡በዲዮቅልጥ ያኖስ፡ፊት፡አቆመው፡ፎጢኖስም፡ይህን፡ ድንቅ፡ተአምር፡በአየ፡ጊዜ፡ልብሱን፡ጥሎ፡ ተነሥቶ፡ወንድሙን፡አንቂጦስን፡ሳመው። ከዳተኛውንም ፡ ንጉሥ ፡ አንተ ፡ ጐስቋላ ፡ ወንድሜን፡እንዴት፡ታሸንፈዋለሁ፡ብሎ፡ ረገመው፡ዲዮቅልጥያኖስም፡ሰምቶ፡በአንገ ታቸው ፡ ዛንጅር ፡ በእግሮቻቸው ፡ እግር ብረት፡አግብተው፡ወደ፡ወህኒ፡ቤት፡እንዲ

www.ethiopianorthodox.org

፴፪፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ አውሲስ ፡ ሰማዕት ፡ ወእንጦንዮስ ፡ ወአባ ፡ መሐር ፡ ዘሮሜ ፡ ወበረከቶሙ ፡ ይብጽሐነ ፡ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፡አሜን።

* * *

፩፤ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፲ወ፫ ለታኅሣሥ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት፡ ኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ አባ ፡ በጽንፍርዮስ ፡ በመዋዕሊሆሙ፡ለተንባላት።

፪፤ ወዝንቱ፡ብፁዕ፡መንኰሰ፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያኑ፡ለቅዱስ፡ገብርኤል፡ሊቀ፡መላእክት፡ ዘሀለወት ፡ በሀገረ ፡ ምስር ፡ በጽንፈ፡ ፈለግ ፡ ወነበረ ፡ እንዘ ፡ ይትጋደል ፡ ገድለ ፡ ዐቢየ ፡ ወተዋሥአ ፡ ምስለ ፡ መሳፍንቲሆሙ ፡ ለተንባላት፡በእንተ፡ሃይማኖት፡ርትዕት፡ወከሠተ፡ሎሙ፡መለኮቶ፡ለእግዚእነ፡ክርስቶስ፡ወአጠየቆሙ፡ከመ፡ውእቱ፡አምላክ፡ወበእንተዝ፡ ተምዑ፡ተንባላት ፡ ተኀፊሮሙ ፡ ወኰነንዎ ፡ ኵነኔ ፡ ዐቢየ ፡ ወመተሩ ፡ ርእሶ ፡ በሰይፍ ፡ ወነሥአ ፡ አክሊለ ፡ ስምዕ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት።

፫፤ ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ኪያነኒ፡ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፴፪፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የቅዱሳን ፡ የሰማዕት ፡ አውሲስና፡የእንጦንዮስ፡የሮሜው፡የአባ፡ መሐር ፡ መታሰቢያቸው ፡ ነው ፡ በረከታቸውም ፡ ትድረሰን ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

* * *

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ታኅሣሥ ፡ ዐሥራ ፡ ሦስት ፡በዚች፡ቀን፡በእስላሞች፡ዘመን፡አባ፡ በጽንፍርዮስ፡በሰማዕትነት፡አረፈ።

፪፤ ይህም ፡ የከበረ ፡ መነኰስ ፡ በምስር ፡ አገር ፡ በወንዝ ፡ ዳር ፡ በአለች ፡ በሊቀ ፡ መላእክት ፡ ቅዱስ፡ገብርኤል፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ውስጥ፡ መንኵሶ፡ታላቅ፡ተጋድሎን፡ሲጋደል፡ኖረ፡ ስለቀናች፡ሃይማኖትም፡ከእስላሞች፡መሳፍንት ፡ ጋር ፡ ተከራከረ ፡ የጌታችን ፡ ክርስቶስንም ፡ መለኮቱን ፡ ገለጠላቸው ፡ አምላክነቱንም፡አስረዳቸው፡ስለዚህም፡እስላሞች፡ በአፈሩ፡ጊዜ፡ተቆጡ፡ጽኑዕ፡ሥቃይንም፡ አሠቃዩት፡ራሱንም፡በሰይፍ፡ቆረጡ፡የሰማዕትነት፡አክሊልን፡በመንግሥተ፡ሰማያት፡ ተቀበለ።

፫፤ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለበጽንፍርዮስ፡እንተ፡ለብሰ፡ምንኵስና። በቤተ፡ ገብርኤል፡ፀዋሬ፡ዜና። በእንተ፡ሃይማኖት፡ ርትዕት ፡ ለብሔረ ፡ ተንባላት ፡ መስፍና ። በብዙኅ ፡ ኵነኔ ፡ ድኅረ ፡ ለሥጋሁ ፡ ኰነና። በተመትሮ ፡ ርእሱ ፡ አድምዐ፡በሰማይ፡ልዕልና።

፬፤ ወበዛቲ፡ዕለት፡አዕረፈ፡አብ፡ቅዱስ፡አብራኮስ፡ ዘእምላዕላይ ፡ ግብጽ ። ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ መንኰሰ ፡ እንዘ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ፳ ዓመት ፡ ወተጋደለ፡ተጋድሎ፡ዐቢየ፡ወሠናየ።

፭፤ ወሶበ ፡ ደክመ ፡ ሰይጣን ፡ እምተቃርኖቱ ፡ ወተመውዐ፡ወኢተክህሎ፡ላዕሌሁ፡በምንትኒ፡ መጽአ ፡ ኀቤሁ ፡ ገጸ ፡ በገጽ ፡ ወይቤሎ ፡ ናሁ ፡ ተርፈ፡እመዋዕሊከ፡፶ዓመት፡ካልዕ፡ወፈቀደ፡ በዝንቱ ፡ ከመ ፡ ያውድቆ ፡ ውስተ ፡ ሀኬት ፡ አውሥአ ፡ አረጋዊ ፡ ወይቤሎ ፡ አኀዘንከኒ ፡ እስመ፡አንሰ፡ኮንኩ፡አሐሊ፡ከመ፡እሕየው፡ ፻ተ፡ዓመተ፡በእንተዝ፡ተሐየይኩ፡ወለእመ፡

፬፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ ከላይኛው ፡ ግብጽ ፡ ቅዱስ ፡ አባት ፡ አብራኮስ ፡ አረፈ። ይህም ፡ ቅዱስ ፡ ዕድሜው ፡ ሃያ ፡ ዓመት ፡ ሲሆን ፡ መንኵሶ ፡ መልካም፡የሆነ፡ታላቅ፡ተጋድሎን፡ተጋደለ።

፭፤ ሰይጣንም ፡ ከእርሱ፡ ጋር ፡ በመጣላት ፡ በተሸነፈና፡በደከመ፡ጊዜ፡በእርሱም፡ላይ፡ምንም፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ባልተቻለው ፡ ጊዜ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተገልጦ ፡ መጥቶ ፡ እነሆ ፡ ከዚህ ፡ ዕድሜህ፡ሌላ፡ኀምሳ፡ዓመት፡ቀረህ፡አለው። በዚህም፡ወደ፡ስንፍና፡ሊጥለው፡ወዶ፡ነው፡ ሽማግሌውም፡እንዲህ፡ብሎ፡መለሰለት፡አሳዘንከኝ፡እኔ፡ሌላ፡መቶ፡ዓመት፡እኖር፡ዘንድ፡

www.ethiopianorthodox.org

ቢጽን ፡ ዘበሐሜት ፡ ወየአምር ፡ አምላኪየ ፡ ከመ ፡ አልብየ ፡ ካልዕ ፡ ሲሳይ ፡ ወእምይእቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ያሠግሮን ፡ ለቈቀ፝ሐት ፡ ወይሠገራ ፡ ሎቱ ፡ በበዕለቱ ፡ አሐተ ፡ አሐተ ፡ ወነበረ ፡ እንዘ ፡ ይሴሰይ ፡ ኪያሆን ፡ ወይሰቲ ፡ እምውእቱ ፡ ማይ ፡ ወየአኵት ። ወይተግህ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ በጸሎት ፡ ወበሰጊድ ፡ ወይስእል ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብዙኀ ፡ ዓመታተ ፡ ወኢይሰምዕ ፡ ቃለ ፡ ሰብእ ፡ ወኢይሬኢ ፡ ገጸ ፡ ሰብእ ፡ ወኢይትናገር ፡ ምስሌሁ ፡ ኢ ፡ ሐሜተ ፡ ወኢ ፡ ጸሪፈ ፡ ላዕለ ፡ መኑሂ ፡ እስመ ፡ ይትበሀል ፡ ኢይመጽእ ፡ ሰይጣን ፡ ዘእንበለ ፡ ምስለ ፡ ሰብእ ።

፲፪ ፡ ወእምዝ ፡ መጽአ ፡ ፩መነኮስ ፡ እምሀገረ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ እንዘ ፡ የኃሥሥ ፡ ጸላዕተ ፡ ወበጽሐ ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፡ አባ ፡ መቃሬ ፡ ወርእየ ፡ እንዘ ፡ ያሠግር ፡ ቈቀ፝ሐ ፡ ወኢተዓገሠ ፡ ሶቤሃ ፡ ባሕቱ ፡ ገጒዓ ፡ እስከ ፡ ይቀትሎ ፡ ለእኁሁ ፡ በሐሜት ። ወተመይጠ ፡ ሀገረ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ ኀበ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወዜነዎ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ አንሰ ፡ ሖርኩ ፡ ገዳመ ፡ እንዘ ፡ አኀሥሥ ፡ በዓታተ ፡ ወበህየ ፡ ርኢኩ ፡ መነኮሰ ፡ እንዘ ፡ ያሠግር ፡ ቈቀ፝ሐ ፡ ከመ ፡ ይብላዕ ፡ ሥጋ ፡ ከመ ፡ ያረስሐነ ፡ በኀበ ፡ አሕዛብ ፡ ሶበ ፡ ይሬእዩ ፡ ዘይገብር ።

፲፫ ፡ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡ ፈነወ ፡ ምስለ ፡ ውእቱ ፡ መነኮስ ፡ ካልአ ፡ መነኮሰ ፡ ከመ ፡ ያእምር ፡ ወይጠይቅ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ እሙነ ፡ ዘነገሮ ፡ ወእንዘ ፡ ሀለዉ ፡ እሙንቱ ፡ በፍኖት ፡ ዓዲ ፡ እምቅድመ ፡ ይብጽሑ ፡ ሖረ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ ኀበ ፡ መሥገርቱ ፡ በከመ ፡ ልማዱ ፡ ወረከበ ፡ ሠላሰ ፡ ቈቀ፝ሐተ ፡ እለ ፡ ተሠግራ ፡ በአሐቲ ፡ መሥገርት ። ወሐለየ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ኪያየኑ ፡ እንዘ ፡ ያሜክር ፡ ወሀበኒ ፡ እግዚእየ ፡ ወሚመ ፡ ኢጸገበትኑ ፡ ከርሥየ ፡ እምቅድመ ፡ ዝኒ ፡ ዕለት ፡ ወለእመኒ ፡ ለካልአን ፡ ኮነ ፡ አልቦ ፡ ዘርኢኩ ፡ እምሰብእ ፡ በውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ገዳም ።

፲፬ ፡ ወሶበ ፡ ከመዝ ፡ ይሔሊ ፡ በጽሑ ፡ እሉ ፡ መነኮሳት ፡ ዘተፈነዉ ፡ እምኀበ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ሶበ ፡ ርእዮሙ ፡ ተፈሥሐ ፡ ወሰገደ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ አአኵተከ ፡ እግዚኦ ፡ ዘወሀ

ያለውስ ፡ የባልንጀራችንን ፡ ሥጋ ፡ በሐሜት ፡ የምንበላውን ፡ አይደለምን ፡ ሌላ ፡ ምግብም ፡ እንደሌለኝ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ያውቃል ፡ ብሎ ፡ ከዚያችም ፡ ዕለት ፡ ወዲህ ፡ ቆቆችን ፡ የሚያጠምድ ፡ ሁኖ ፡ በየቀኑ ፡ አንዳንድ ፡ የሚያዙለት ፡ ሆኑ ። እርሳቸውንም ፡ እየተመገበ ፡ ከዚያ ፡ ውኃም ፡ እየጠጣ ፡ በማመስገን ፡ ኖረ ፡ በቀንና ፡ በሌሊትም ፡ ለጸሎትና ፡ ለስግደት ፡ በመትጋት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ እየለመነ ፡ ብዙ ፡ ዘመናት ፡ ኖረ ፡ የሰውንም ፡ ድምፅ ፡ አይሰማም ፡ የሰውንም ፡ ፊት ፡ አያይም ፡ ሐሜትንም ፡ ሆነ ፡ ስድብን ፡ በማንም ፡ ላይ ፡ አብሮ ፡ አይነጋገርም ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሰይጣን ፡ አይመጣም ፡ ይባላልና ።

፲፪ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከቍስጥንጥንያ ፡ ከተማ ፡ አንድ ፡ መነኰሴ ፡ ዋሻ ፡ እየፈለገ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ ከአለበት ፡ ደርሶ ፡ ቆቅን ፡ ሲያጠምድ ፡ አየው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ አልታገሠም ፡ ግን ፡ ወንድሙን ፡ በሐሜት ፡ እስከሚገድለው ፡ ቸኰለ ፡ ወደ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ተመልሶ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነገረው ፡ እኔ ፡ ዋሻ ፡ እየፈለግሁ ፡ ወደ ፡ በረሀ ፡ ሔድሁ ፡ በዚያም ፡ ሥጋ ፡ ሊበላ ፡ ቆቅን ፡ ሲያጠምድ ፡ መነኰሴውን ፡ አየሁት ፡ የሚሠራውን ፡ ሲያዩ ፡ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ ሊያስነቅፈን ፡ ነው ፡ አለው ።

፲፫ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ነገሩ ፡ እውነት ፡ እንደሆነ ፡ ያውቅ ፡ ይረዳ ፡ ዘንድ ፡ ከዚያ ፡ ከነገረው ፡ መነኰሴ ፡ ጋር ፡ ሌላ ፡ መነኰሴ ፡ ላከ ። እነርሱም ፡ በጕዞ ፡ ላይ ፡ በጐዳና ፡ ሳሉ ፡ ገና ፡ ሳይደርሱ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ እንደልማዱ ፡ ወደ ፡ ወጥመዱ ፡ ሔደ ፡ በአንዲት ፡ ወጥመድ ፡ የተያዙ ፡ ሦስት ፡ ቆቆችን ፡ አገኘ ፡ እንዲህም ፡ ብሎ ፡ አሰበ ፡ ጌታዬ ፡ እሊህን ፡ የሰጠኝ ፡ እኔን ፡ ሊፈትነኝ ፡ ነውን ። ወይስ ፡ ከዚች ፡ ዕለት ፡ በፊት ፡ ሆዴ ፡ ያልጠገበች ፡ ኑራለችን ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ነው ፡ እንዳልል ፡ በዚህ ፡ በረሀ ፡ ውስጥ ፡ ከሰው ፡ ወገን ፡ ያየሁት ፡ የለም ።

፲፬ ፡ እንዲህም ፡ እያሰበ ፡ ሳለ ፡ ከሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ የተላኩት ፡ እሊያ ፡ መነኰሳት ፡ ደረሱ ፡ በአያቸው ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ አለው ፡ ችግረኛነቴን ፡ አውቀህ ፡ ለአገልጋዮችህ ፡ ቅዱሳን ፡ ምግባ

www.ethiopianorthodox.org

ብከኒ ፡ ሲሳዮሙ ፡ ለአግብርቲከ ፡ ቅዱሳን ፡
አእሚረከ ፡ ንዴትየ ፡ እሙንቱሰ ፡ ይትቃ
ጸብዎ፡እስከ፡አስተዳለወ፡ወአቅረበ፡ሎሙ፡
ማዕደ ፡ ወእምዝ ፡ አቀረበ ፡ ሎሙ ፡ ወይቤ
ሎሙ ፡ አ ፡ አበውየ ፡ ንሥኡ ፡ ወባርኩ ፡
ወተሴስዩ ፡ ውእቱኒ ፡ ነሥአ ፡ ዘሎቱ ፡
ወተሴሰየ፡በጽሙና፡ዘእንበለ፡ነገር፡እስከ፡
ይፌጽም ። ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ አንሥአ ፡ አዕይ
ንቲሁ፡ርእየ፡ከመ፡ኢበልዑ፡ወይቤሎሙ፡
አ ፡ አበውየ ፡ እፎኑ ፡ ኢበላዕክሙ ። ወይ
ቤልዎ፡ እስመ ፡ ንሕነ ፡ መነኮሳት ፡ ኢን
በልዕ፡ ሥጋ ፡ ወብነ ፡ ትኅርምት ፡ እስመ ፡
መነኮሳት፡ንሕነ፡ውእቱሰ፡ኀደጎሙ፡ወኢ
ያገበሮሙ፡ወነሥኦን፡ለእማንቱ፡ቈቀሐት፡
ዘአብሰሎን ፡ ወነፍሐ ፡ ላዕሌሆን ፡ ሥልሰ ፡
ወሠረራ ፡ ሶቤሃ ፡ ወሖራ ፡ ውስተ ፡ መካና
ቲሆን ፡ ወርእዮሙ ፡ እሙንቱ ፡ መነኮሳት ፡
ተአምረ ፡ ዘንተ ፡ ደንገፁ ፡ ወሰገዱ ፡ ሎቱ ፡
ወይቤልዎ ፡ ስረይ ፡ ለነ ፡ አባሳነ ፡ አ ፡ ቅዱሱ ፡
ለእግዚአብሔር፡ወይቤሎሙ፡ይስረይ፡ለነ፡
እግዚአብሔር፡አበሳነ፡ለኵልነ።
፲፭፡ወእምዝ፡ገብኡ፡ኀበ፡ብሔሮሙ፡ወነገርዎ፡
ለሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘንተ ፡ መንክረ ፡ ዘርእዩ ፡
ውእቱኒ ፡ ሰሚዖ ፡ አንከረ፡ ወለአከ ፡ ኀበ ፡
ንጉሥ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ እስመ ፡ ተረክበ ፡ በመ
ዋዕሊነ ፡ ብእሲ ፡ ጻድቅ ፡ መነኮስ ፡ ወአንተኒ ፡
ነዓ፡ከመ፡ንሑር፡ወንንሣእ፡በረከቶ።

፲፮፡ ወበጊዜሃ ፡ ተንሥአ ፡ ንጉሥ ፡ ምስለ ፡ ሠራ
ዊቱ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳትኒ ፡ ምስለ ፡ ካህናቲሁ፡
ወሖሩ፡ኀበ፡ሀሎ፡አባ፡መቃርስ፡እንዘ፡ይመ
ርሕዎሙ፡እሉ፡መነኮሳት፡ወሶበ፡ቀርቡ፡
ኀቤሁ፡ነሥአ፡መልአክ፡ወፆሮ፡በክነፊሁ፡
ከመ ፡ ያብጽሖ ፡ ብሔረ ፡ ሕያዋን ፡ ወሶበ ፡
ርእይዎ ፡ እንዘ ፡ የዐርግ ፡ ከልሑ ፡ እንዘ ፡
ይብሉ፡አ፡ቅዱሱ፡ለእግዚአብሔር፡ባርከነ፡
ወንግረነ ፡ አሐተ ፡ ቃለ ፡ በዘንድኅን ። ወይ
ቤሎሙ ፡ ይጹም ፡ ልሳንክሙ ፡ እምነገረ ፡
ውዴት ፡ ወሐሜት። ካህን ፡ እምኢተምህረ ፡
ብዙኀ፡ትምህርተ፡እምኢመጽአ፡ትዕቢት፡
ወትዝኅርት ፡ ወመነኮስ ፡ እምኢያብዝኃ ፡
ትኅምርተ፡እመኢመጽአ፡ትምክህት፡ወተ
ፋቀሩ ፡ በበይናቲክሙ ፡ ወእግዚአብሔር ፡

ቸውን፡የሰጠኸኝ፡አቤቱ፡አመሰግንሃለሁ፡
ብሎ፡ሰገደ።እነርሱ፡ግን፡ማዕድ፡ሠርቶ፡
አዘጋጅቶ፡እስከአቀረበላቸው፡ድረስ፡ይጠ
ቃቀሱበት፡ነበር፡ከዚህም፡በኋላ፡አቅርቦ
ላቸው፡ንሱ፡አባቶቼ፡ባርኩና፡ተመገቡ፡
አላቸው፡እርሱም፡የራሱን፡ድርሻ፡ይዞ፡እስ
ከሚጨርስ ፡ ያለ ፡ መነጋገር ፡ በጸጥታ ፡
ተመገበ። ከዚህም፡በኋላ፡ዓይኖቹን፡ቀና፡
ቢያደርግ ፡ እንዳልበሉ ፡ አየ ፡ አባቶቼ ፡
እንዴት ፡ አልበላችሁም ፡ አላቸው ፡ እኛ ፡
መንኰሳት፡ስለሆን፡ሥጋ፡አንበላም፡ትኅር
ምትም፡አለን፡አሉት፡እርሱም፡ተዋቸው፡
አላስገደዳቸውም፡እነዚያን፡ያበሰላቸውን፡
ቆቆች ፡ አንሥቶ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ እፍ ፡
አለባቸው፡ያን፡ጊዜም፡ድነው፡በረሩ፡ወደ፡
ቦታቸውም፡ሔዱ፡እነዚያ፡መነኰሳትም፡
ይህን፡ተአምር፡አይተው፡ደነገጡ፡የእግዚ
አብሔር፡ቅዱስ፡ሆይ፡በደላችንን፡ይቅር፡
በለን፡ብለው፡ሰገዱለት፡እርሱም፡የሁላች
ንንም ፡ በደል ፡ እግአዚአብሔር ፡ ይቅር ፡
ይበለን፡አላቸው።
፲፭፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሀገራቸው ፡ ተመል
ሰው፡ያዩትን፡ይህን፡ድንቅ፡ተአምር፡ለሊቀ፡
ጳጳሳቱ፡ነገሩት፡እርሱም፡ሰምቶ፡አደነቀ፡
ወደ፡ንጉሥም፡እንዲህ፡ብሎ፡ላከ፡በዘመ
ናችን፡ጻድቅ፡ሰው፡መነኰስ፡ተገኝቷልና፡
አንተም ፡ ና ፡ ሒደን ፡ በረከቱን ፡ እንድን
ቀበል፡አለው።
፲፮፡ወዲያውኑ፡ንጉሡ፡ከሠራዊቱ፡ጋር፡ተነሣ፡
ሊቀ ፡ ጳጳሳቱም ፡ ከካህናቱ ፡ ጋር ፡ አባ ፡
መቃርስ፡ወዳለበት፡እነዚያ፡መነኰሳት፡
እየመሩአቸው፡ሔዱ፡ወደርሱም፡ሲቀርቡ፡
ወደ፡ብሔረ፡ሕያዋን፡ያደርሰው፡ዘንድ፡
መልአክ፡አንሥቶ፡በክንፎቹ፡ተሸከመው፡
ሲያርግም፡በአዩት፡ጊዜ፡የእግዚአብሔር፡
ቅዱስ ፡ ሆይ ፡ ባርከን ፡ የምንድንበትን ፡
አንዲት፡ቃል፡ንገረን፡ብለው፡ጮኹ።እር
ሱም ፡ ከሐሜትና ፡ ከነገር ፡ ሥራ ፡ አንደበ
ታችሁ፡ይከልከል። ካህን፡ብዙ፡ባይማር፡
ትዕቢትና፡መታጀር፡ባልመጣበት፡ነበር፡
መነኵሴም ፡ ትኅርምት ፡ ባያበዛ ፡ ባልተ
መካም፡ነበር፡ርስበርሳችሁ፡ተፋቀሩ፡እግ
ዚአብሔርም ፡ አድሮባችሁ ፡ ይኑር ፡

www.ethiopianorthodox.org

የሀሉ ፡ ምስሌክሙ ፡ ወዘንተ ፡ ብሂሎ፡ ዐርገ ፡ ወተሠወረ፡እምአዕይንቲሆሙ።
፲፯፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ ጻድቅ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

አላቸው፡ ይህንንም ፡ ብሎ ፡ ዐረገ ፡ ከዐይናቸ ውም፡ ተሠወረ።
፲፯፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም፡ በዚህ ፡ ጽድቅ ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለመቃርዮስ፡ዘተመሥጠ፡መልዕልተ።በቅድመ፡ጉቡአን፡ይንብብ፡ዘይብል፡ቃላተ።እም ኢያእመሩ፡ትዕቢተ፡ወዘይመስሎ፡ትምክህተ።እመ፡ኢያፈድፈደ፡ካህን፡ትምህርተ።ወእመ፡ኢያብዝኁ፡ካዕበ፡መነኮስ፡ትኅርምተ።

፲፰፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ካዕበ ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለቅዱሳን፡ አብራቂስ ፡ ሰማዕት ፡ ወሐርስፎስ ፡ ወቆርኔሌዎስ፡ መኰንን፡ ወወርቅጥጵስ፡ ወአፍሬ። ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ፡ ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡አሜን።

፲፰፡ በዚችም፡ቀን፡ደግሞ፡የሰማዕት፡አብራቂስ፡ የሐርስፎስ፡የመኰንኑ፡ቆርኔሌዎስ፡የወርቅጥጵስና፡የአፍሬ፡መታሰቢያቸው፡ነው።በረከታቸውም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

* * *

* * *

፩፡ በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፲ወ፬፡ ለታኅሣሥ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት፡ ኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ ቅዱስ ፡ ስምዖን ፡ ዘእምሀገረ፡መኑፍ፡ልዕልት።
፪፡ ውእቱኬ ፡ በመዋዕሊሆሙ ፡ ለተንባላት ፡ ተዋሥአ፡ምስለ፡፩፡እመሳፍንተ፡ተንባላት፡ ወሞዖ ፡ ቅዱስ ፡ ስምዖን ፡ ወአስተኀፈሮ ፡ ወሐረ ፡ ውእቱ ፡ ተንባላታዊ ፡ ወአስተዋደዮ ፡ ኀበ ፡ ርእሰ ፡ መሳፍንት ፡ ወይቤሎ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ስምዖን ፡ አስተሐቀረ ፡ ሃይማኖተ ፡ ተንባላት ፡ ወበእንተዝ ፡ አኀዝዎ ፡ ወኰነንዎ፡ ዘነኔ ፡ ጽኑዐ ፡ ወእምዝ ፡ መተሩ ፡ ርእሶ ፡ በሰይፍ፡ወነሥአ፡አክሊለ፡ስምዕ፡በመንግሥተ፡ ሰማያት።
፫፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም፡አሜን።
፬፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮኑ ፡ ሰማዕተ ፡ ቅዱሳን ፡ አባ፡ ብሖር፡ወአባ፡ሚናስ፡አረጋዊ፡ወበረከቶሙ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ታኅሣሥ ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ካለች ፡ ከመኑፍ፡ ከተማ ፡ ቅዱስ ፡ ስምዖን ፡ በሰማዕትነት፡አረፈ።
፪፡ እርሱም ፡ በእስላሞች ፡ ዘመን ፡ ከመሳፍንቶቻቸው ፡ ከአንዱ ፡ ጋር ፡ ተከራከረና ፡ ቅዱስ ፡ ስምዖን ፡ ረትቶ ፡ አሳፈረው ፡ ያም ፡ እስላም ፡ ወደ ፡ መሳፍንቱ ፡ አለቃ ፡ ሒዶ ፡ ይህ ፡ ስምዖን ፡ የእስላሞችን ፡ ሃይማኖት ፡ ያቃልላል ፡ ብሎ ፡ ወነጀለው ፡ ስለዚህም ፡ ይዘው ፡ በጽኑዕ ፡ ሥቃይ ፡ አሠቃዩት ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ራሱን ፡ በሰይፍ ፡ ቆረጡት ፡ የሰማዕትነት ፡ አክሊልን ፡ በመንግሥተ፡ሰማያት፡ተቀበለ።
፫፡ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።
፬፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ ቅዱሳን ፡ አባ ፡ ብሖርና ፡ አረጋዊ፡ ሚናስ ፡ በሰማዕትነት ፡ አረፉ ። በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

## አርኬ

ሰላም፡ለስምዖን፡ ምቱረ፡ክሣድ፡በሰይፍ። ዘሀገረ፡መኑፍ። ለብሑር፡ወሚናስ፡ዘወንጌል፡አዕዋፍ። ፀሩኒ፡በመዝራዕት፡ወሕዝሉኒ፡በክንፍ። ከመ፡ታዕድዉኒ፡እምቀልቀል፡ወጸድፍ።

፫፤ ወበዛቲ፡ዕለት፡ ኮኑ፡ሰማዕተ፡ቅዱሳን፡መርምህናም፡ወእኅቱ፡ሣራ፡ወአግብርቲሁ፡፵ዓ።

፬፤ ወለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ አቡሁ ፡ ንጉሠ ፡ አቶር ፡ ዘያመልክ ፡ ግልፍዋተ ፡ ዘስሞሙ ፡ ቤል ፡ ወአጽሎን፡ወእሙሰ፡ክርስቲያናዊት፡ይእቲ።

፭፤ ወዝንቱ፡ቅዱስ፡መርምህናም፡ሰአሎ፡ለአቡሁ ከመ ፡ ያብሖ ፡ ወይጻእ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ ወይንዓው፡አራዊተ፡ወሶበ፡አብሖ፡ሖረ፡ኀበ፡ እሙ ፡ ወይቤላ፡ አሐውር ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ እንዓው፡አራዊተ፡ወትቤሎ፡እሙ፡አምላከ፡ ሰማያት፡ወምድር ፡እግዚአብሔር፡ ይባርክ፡ ላዕሌከ።

፮፤ ወእምዝ፡ወጽአ፡ምስለ፡፵ዓ፡አግብርቲሁ፡ መስተጽዕናን፡አፍራስ፡ወሖረ፡ወበጽሐ፡ኀበ፡ ደብረ፡መቅሉብ፡ወኀደረ፡በህየ፡ወበሌሊት፡ ጸውዖ ፡መልአከ፡እግዚአብሔር ፡ወይቤሎ፡አ፡ መርምህናም ፡ ተንሥእ ፡ ወዕርግ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ፡ ደብር ፡ ወትረክብ ፡ ብእሴ ፡ ቅዱሰ ፡ ዘስሙ፡ማቴዎስ፡ወውእቱ፡ይነግረከ፡ነገረ፡ ሕይወት ፡ ወጸቢሖ ፡ ዐርገ ፡ ውስተ ፡ ውእቱ፡ ደብር፡ወረከቦ፡ለአባ፡ማቴዎስ፡ለቢሶ፡ልብሰ፡ ፀጉር ፡ ከመ ፡ በግዕ ፡ ወርእዮ ፡ መርምህናም ፡ ፈርሀ ፡ እምኔሁ ፡ ወይቤሎ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ ማቴዎስ፡አ፡ወልድየ፡ቅረብ፡ኀቤየ፡እስመ፡ አነሂ ፡ ሰብእ ፡ ዘከማከ ፡ ፍጥረቱ ፡ለእግዚአብሔር።

፯፤ ወይቤሎ ፡ መርምህናም ፡ ቦኑ ፡ አምላክ ፡ ዘእንበለ ፡ አማልክተ ፡ አቡየ ፡ ወመሀሮ ፡ አባ ፡ ማቴዎስ፡ ሃይማኖተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወህላዌሁ ፡ ለክርስቶስ፡ምስለ፡አቡሁ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ ወሥጋዌሁ፡ወሕማሞ፡ወሞቶ፡ወትንሣኤሁ፡ ወዕርገቶ ፡ ወዕለተ ፡ ኵነኔ ፡ ከመ ፡ ቦ ፡ ዕሴት ፡ ለጻድቃን፡ወሥቃይ፡ለኃጥአን።

፰፤ ወይቤሎ ፡ መርምህናም ፡ ሀለውትኒ ፡ እኅትየ ፡ ዘአኀዛ ፡ ሕማመ ፡ ለምጽ ፡ እምርእሳ ፡ እስከ ፡ እግራ፡ ወለእመ፡ፈወስካ፡በጸሎትከ፡በስሙ፡

፫፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ የቅዱሳን ፡ መርምህናምና ፡ እኅቱ ፡ ሣራ ፡ አርባ ፡ አገልጋዮቹም ፡ በሰማዕትነት፡አረፉ።

፬፤ የዚህም ፡ ቅዱስ ፡ አባቱ ፡ የአቶር ፡ ንጉሥ ፡ የተቀረጹ ፡ ስማቸው ፡ ቤል ፡ አጽሎን ፡ የሚባሉ፡ ጣዖቶችን ፡ የሚያመልክ ፡ ነው ፡ እናቱ፡ግን፡ክርስቲያን፡ናት።

፭፤ ይህም፡ቅዱስ፡መርምህናም፡ወደ፡ዱር፡ሒዶ፡ አራዊትን፡ያድን፡ዘንድ፡እንዲፈቅድለት፡ አባቱን፡ለመነው፡በፈቀደለትም፡ጊዜ፡ወደ፡ እናቱ፡ሒዶ፡አራዊትን፡ለማደን፡ወደበረሀ፡ እሔዳለሁ ፡ አላት ፡ እናቱም ፡ የሰማይና ፡ የምድር ፡ አምላክ ፡እግዚአርሔር፡ በላይህ ፡ በረከትን፡ያሳድር፡አለችው።

፮፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከአርባ ፡ ፈረሰኞች ፡ አገልጋዮቹ ፡ ጋር ፡ ወጥቶ ፡ ሔደ ፡ መቅሉብ ፡ ወደሚባል፡ተራራም፡ደርሶ፡በዚያ፡አደረ። በሌሊትም ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ጠራው ፡ እንዲህም ፡ አለው ፡መርምህናም ፡ ሆይ፡ተነሥተህ፡ወደዚህ፡ተራራ፡ላይ፡ውጣ፡ ስሙ ፡ ማቴዎስ ፡ የሚባል ፡ ቅዱስ ፡ ሰው ፡ ታገኛለህ፡እርሱም፡የሕይወትን፡ነገር፡ይነግርሃል፡ሲነጋም፡ወደ፡ተራራው፡ወጣ፡እንደ፡ በግ፡ጠጉር፡ለብሶ፡አባ፡ማቴዎስን፡አገኘው፡ መርምህናም ፡ በአየው ፡ ጊዜ ፡ ፈራ ፡ ቅዱስ ፡ አባ፡ማቴዎስም፡ልጄ፡ሆይ፡ወደ፡እኔ፡ቅረብ፡ እኔም ፡የእግዚአብሔር፡ ፍጥረቱ ፡ የሆንኩ ፡ እንዳንተ፡ሰው፡ነኝ፡አለው።

፯፤ መርምህናምም፡ከአባቴ፡አማልክቶች፡በቀር፡ አምላክ፡አለን፡አለው፡አባ፡ማቴዎስም፡የክርስትና፡ሃይማኖትን ፡ከአባቱና፡ከመንፈስ፡ ቅዱስ፡ጋር፡የክርስቶስን፡ ህልውና፡በተለየ፡ አካሉ፡ሰው፡መሆኑንና፡መከራ፡ተቀብሎ፡ መሞቱን ፡ መነሣቱን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ማረጉንም፡የፍርድ፡ቀንም፡እንዳለ፡ለጻድቃን፡ በጎ፡ዋጋ፡ለኃጢአተኞች፡ቅጣት፡እንዳለ፡ አስተማረው።

፰፤ መርምህናምም ፡ ከራስዋ ፡ እስከ ፡ እግርዋ ፡ ለምጽ፡የያዛት፡እኅት፡አለችኝ፡የአምላክህን፡ ስም፡ ጠርተህ፡ በጸሎትህ፡ ብታድናት፡ እኔ፡

www.ethiopianorthodox.org

ለአምላክከ፡አነ፡አአምን፡ቦቱ፡ወይቤሎ፡አባ፡
ማቴዎስ፡ነዓ፡ንረድ፡ኅቡረ፡ወአነ፡እፌውሳ፡
ወወሪዶሙ ፡ እምደብር ፡ ኀደጎ ፡ ለአባ ፡
ማቴዎስ፡ በፍኖት ፡ ወሖረ ፡ ቅዱስ ፡ መርም
ህናም ፡ ኀበ ፡ እሙ፡ ወነገራ ፡ ኵሎ ፡ ወነሥአ ፡
ለእኅቱ፡በኀቡእ፡ወወሰዳ፡ኀበ፡አባ፡ማቴዎስ፡
ወአባ፡ማቴዎስኒ፡ጸለየ፡ኀበ፡እግዚአብሔር፡
ወጐድዓ፡ለምድር፡በማእተቡ፡ወነቅዐ፡ማይ፡
ሶቤሃ ፡ ወኮነ ፡ ከመ ፡ ባሕር፡ ወአውረዶሙ ፡
ውስተ፡ባሕር፡ወአንበረ፡እዴሁ፡ላዕሌሆሙ፡
ወአጥመቆሙ ፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡
ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ወለፃዕደው፡አግብርቲሁ፡
ወወሀቦሙ፡ምሥጢራተ፡ቅድሳት፡ወበጊዜሃ፡
ነጽሐት፡ሣራ፡እምለምጻ።

፲፩፡ ወእምዝ ፡ መዐዶሙ ፡ አባ ፡ ማቴዎስ ፡ ከመ ፡
ይጽንኡ ፡ በሃይማኖተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ አመ ፡ ይትቄከፉ ፡
ሕማመ ፡ ወምንዳቤ ፡ ዘይመጽእ ፡ ላዕሌሆሙ፡
በእንተ ፡ ስሙ ፡ ቅዱስ ፡ ወእምዝ፡ ጸለየ ፡ ላዕሌ
ሆሙ፡ወፈነዎሙ፡በሰላም።

፲፪፡ ወመጺአ ፡ ቅዱስ ፡ መርምህናም ፡ ቦአ ፡ ኀበ ፡
እሙ፡ወኢሖረ፡ኀበ፡አቡሁ፡ወኢ፡ቤተ፡አማ
ልክቲሁ ፡ ወሰሚያ ፡ ንጉሥ ፡ አቡሁ ፡ ተምዐ ፡
ወአዘዘ፡ከመ ፡ ይጸውዕዎ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ አማ
ልክቲሁ ፡ ወቅዱስሰ ፡ መርምህናም፡ ምስለ ፡
እኅቱ ፡ ወሠራዊቱ ፡ ወጽአ ፡ ወዐርገ ፡
መልዕልተ ፡ ደብር ፡ ዘስማ ፡ ቅሳር ፡ ወነበረ ፡
ህየ።
፲፫፡ ወሰሚያ ፡ አቡሁ ፡ ፈነወ ፡ መኳንንተ ፡ ምስለ ፡
አልባሰ ፡ ክብር ፡ ወአክሊለ ፡ መንግሥት ፡
ወከመ ፡ ይበልዎ ፡ ንሣእ ፡ መንግሥትየ ፡
ውእቱሰ ፡ ነጸሮሙ ፡ በቍጥዓ ፡ ወይቤሎሙ ፡
አንስ ፡ አኃሥሥ ፡ መንግሥተ ፡ እግዚእየ ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ዘኢ
ይበሊ ፡ ወኢይማስን ፡ ወሶቤሃ ፡ ተምዐ ፡
አቡሁ ፡ ንጉሠ ፡ አቶር ፡ ወአዘዘ ፡ ከመ ፡
ይቅትሉ ፡ አግብርቲሁ ፡ በቅድሜሁ ፡ ከመ ፡
ይፍራህ ፡ ልቡ ፡ ወይትመየጥ ፡ ወእመሰ ፡
ኢተመይጠ ፡ ይቅትሉ ፡ ኪያሁኒ ፡ ምስለ ፡
እኅቱ።
፲፬፡ ወሰሚያ ፡ ቅዱስ ፡ መርምህናም ፡ ጸለየ ፡ ኀበ ፡
እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ የሀቦ ፡ ኵሎ ፡ ተምኔቶ ፡

አምንበታለሁ፡አለው፡አባ፡ማቴዎስም፡እኔ፡
አድናታለሁ ፡ ና ፡ በአንድነት ፡ እንውረድ ፡
አለው ፡ ከተራራው ፡በወረዱ ፡ ጊዜ ፡ አባ ፡
ማቴዎስን ፡ በመንገድ ፡ ትቶ ፡ ቅዱስ ፡ መርም
ህናም ፡ ወደ ፡ እናቱ ፡ ሒዶ ፡ ሁሉን ፡ ነገራት ፡
እኅቱንም ፡ በሥውር ፡ ወደ ፡ አባ ፡ ማቴዎስ፡
ወሰዳት ፡ አባ ፡ ማቴዎስም ፡ ወደ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ጸለየና ፡ ምድሪቱን ፡ አመሳቅሎ ፡
መታት ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ውኃ ፡ መንጭቶ ፡
እንደ፡ ባሕር ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ ባሕሩም ፡ አውርዶ ፡
እጁን ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ አድርጎ ፡ በአብ ፡
በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ አጠመ
ቃቸው ፡ አሽከሮቹን ፡ አርባ ፡ ሰዎችንም ፡
ሥጋውንና ፡ ደሙንም ፡ አቀበላቸው ፡ ወዲ
ያውኑ፡ሣራ፡ከለምጽዋ፡ነጻች።
፲፩፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አባ ፡ ማቴዎስ ፡ ስለ ፡ ከበረ ፡
ስሙ ፡ በላያቸው ፡ የሚመጣውን ፡ መከራ ፡
በሚቀበሉ ፡ ጊዜ ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ ጌታ
ችንን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ በማመን ፡
እንዲጸኑ መከራቸው ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡
በላያቸው፡ጸለየና፡በፍቅር፡አንድነት፡አሰና
በታቸው።
፲፪፡ ቅዱስ ፡ መርምህናምም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡
እናቱ ፡ ቤት ፡ ገባ ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡
አማልክቶቹ ፡ አልሔደም ፡ አባቱም፡ ሰምቶ ፡
ተቆጣ ፡ ወደ ፡ አማልክቶቹ ፡ ቤትም ፡ እንዲ
ጠሩት ፡ አዘዘ ፡ ቅዱስ ፡ መርምህናም ፡ ግን ፡
ከእኅቱና ፡ ከሠራዊቱ ፡ ጋር ፡ ስሟ ፡ ቅሳር ፡
ወደ፡ምትባል፡ተራራ፡ሒዶ፡ከላይ፡ወጥቶ፡
በዚያ፡ተቀመጠ።
፲፫፡ አባቱም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ከልብሰ ፡ መንግ
ሥትና፡ከዘውድ፡ጋር፡መኳንንቱን፡የመንግ
ሥቱን፡ሥልጣን፡ተረከብ፡ብሎሃል፡እንዲ
ሉት፡ላካቸው፡እርሱ፡ግን፡በቍጣ፡ተመለከ
ታቸውና ፡ እኔ ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ የጌታዬ ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ፈጽሞ ፡ የማይጠፋ ፡
መንግሥት ፡ እሻለሁ ፡ አላቸው ። የአቶር ፡
ንጉሥ፡አባቱም፡በዚያን፡ጊዜ፡ተቆጣ፡ልቡ፡
ፈርቶ፡ይመለስ፡ዘንድ፡አገልጋዮቹን፡በፊቱ፡
እንዲገድሏቸው ፡ ካልተመለሰ ፡ ግን ፡ እርሱ
ንም፡እኅቱንም፡እንዲገድሉ፡አዘዘ።

፲፬፡ ቅዱስ ፡ መርምህናምም ፡ ሰምቶ ፡ የተመ
ኘውን፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እግዚአ

www.ethiopianorthodox.org

ወመጽአ ፡ ቃል ፡ እምሰማይ ፡ ዘይብል ፡ ሰማዕኩ ፡ ጸሎተከ ፡ ወወሀብኩከ ፡ ፈቃደ ፡ ልብከ ፡ ወእምዝ ፡ መተሩ ፡ አርእስቲሆሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ በሰይፍ ፡ ወወገርዎሙ ፡ ውስተ ፡ ግብ ፡ ወአምጽኡ ፡ ዕፀወ ፡ ብዙኀ ፡ ከመ ፡ ያውዕዩ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ወኢረከብዎሙ ፡ እስመ፡ሠወሮሙ፡እግዚአብሔር።

፲፩፡ ወበጊዜሃ፡ኮነ፡ድልቅልቅ፡ወፀልመ፡ፀሐይ፡ ወፈርሁ ፡ ወጐዩ ፡ ሐራ ፡ ወቦአ ፡ ሰይጣን ፡ ላዕለ ፡ ሰናክሬም ፡ ንጉሠ ፡ አቶር ፡ ወከለሐ ፡ ከመ ፡ ሐራውያ ፡ ወሰሚዓ ፡ እሙ ፡ ለቅዱስ ፡ መርምህናም ፡ ፈነወት ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ ማቴዎስ፡ ወአብጽሐቶ ፡ ወነገረቶ ፡ ግብሮ ፡ ለንጉሥ ፡ ውእቱኒ ፡ ጸለየ ፡ ላዕለ ፡ ዘይት ፡ ወቀብዖ ፡ ወወጽአ ፡ እምኔሁ ፡ ሰይጣን ፡ በአምሳለ ፡ ሐራውያ ፡ ወሶቤሃ ፡ አምነ ፡ ንጉሥ ፡ በእግዚእነ ፡ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወተጠምቀ፡ምስለ፡ኵሉ፡ሰብአ፡ቤቱ፡ወምስለ፡ኵሎሙ፡ሰብአ፡ሀገረ፡መንግሥቱ።

፲፪፡ ወእምዝ ፡ አዘዘ ፡ ይሕንፁ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በስመ ፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ድንግል ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ወይዝርዉ ፡ ንዋዮ ፡ ለነዳያን ፡ ወለምስኪናን ፡ ወገብሩ ፡ ኵሎ ፡ በከመ ፡ አዘዞሙ።

፲፫፡ ወእሙ ፡ ለቅዱስ ፡ መርምህናም ፡ ገብረት ፡ ፵ዓ፡ ሣፀናተ ፡ እምአዕባን ፡ ክቡራን ፡ ወአስተጋብአት ፡ አዕፅምቲሆሙ ፡ ለእሙንቱ ፡ ፵ዓ፡ ሰማዕታት ፡ ሐራሁ ፡ ለወልዳ ፡ ወወደየቶሙ ፡ ለለ፩ዱ ፡ ውስተ ፡ ፩ ሣፀናት ፡ ወለደቂቃ ፡ ገብረት ፡ ፪ተ ፡ ሣፀናተ ፡ ዘማሕው ፡ ወወደየቶሙ ፡ ውስቴቶን ፡ ወአንበረቶሙ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘሐነፀት ፡ ወተከሥታ ፡ እምሥጋሆሙ ፡ ተአምራት ፡ ወመንክራት ፡ ዐበይት ፡ ዘአልቦ ፡ ኍልቍ።

፲፬፡ ወስብሐት ፡ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቶሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ሰማዕት ፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም፡ አሜን።

ብሔር፡ ጸለየ ፡ ጸሎትህን ፡ ሰማሁ ፡ ልብህ ፡ የወደደውንም ፡ ሰጠሁህ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ከሰማይ፡ መጣ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የቅዱሳኑን ፡ ራሳቸውን ፡ በሰይፍ ፡ ቆረጡና ፡ ከጕድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ጣሏቸው ፡ ሥጋቸውንም ፡ ያቃጥሉ ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ ዕንጨቶችን ፡ ሰበሰቡ ፡ ግን ፡ አላገኙአቸውም ፡እግዚአብሔር ፡ሠውሮዋቸዋልና።

፲፩፡ ወዲያውኑ ፡ ንውጽውጽታ ፡ ሆነ ፡ ፀሐይም ፡ ጨለመ ፡ ወታደሮችም ፡ ፈርተው ፡ ሸሹ ፡ ሰይጣንም ፡ በአቶር ፡ ንጉሥ ፡ በሰናክሬም ፡ ላይ፡ አድሮ፡አሳበደው፡እንደእሪያም፡ጮኸ፡ የቅዱስ ፡ መርምህናምም ፡ እናት ፡ አይታ ፡ ወደ፡ አባ ፡ ማቴዎስ ፡ ልካ ፡ አስመጣችውና ፡ የንጉሡን ፡ ነገር ፡ ነገረችው ፡ እርሱም ፡ በዘይት፡ላይ፡ጸልዮ፡ቀባው፡ሰይጣንም፡በእሪያ፡ አምሳል ፡ ከርሱ ፡ ወጣ ። በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ በጌታችን ፡ኢየሱስ ክርስቶስ ፡ አመነ ፡ ከቤተ ፡ ሰቦቹና ፡ በሚገዛው ፡ አገር ፡ ካሉ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ተጠመቀ።

፲፪፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አምላክን ፡ በወለደች ፡ በእመቤታችን ፡ በቅድስት ፡ድንግል ፡ማርያም ፡ ስም፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲሠሩ ፡ ገንዘቡንም ፡ ለድኆችና ፡ ለችግረኞች ፡ እንዲበትኑ፡ አዘዘ፡ ሁሉንም፡እንዳዘዛቸው፡አደረጉ።

፲፫፡ የቅዱስ፡መርምህናምም፡እናት፡ከከበሩ፡ደንጊያዎች ፡ አርባ ፡ ሣጥኖችን ፡ አሠራች ፡ የልጅዋ ፡ ጭፍራ ፡ የነበሩ ፡ የእነዚያን ፡ አርባ ፡ ሰማዕታት ፡ አጥንቶቻቸውን ፡ አሰብስባ ፡ በየአንዳንዱ ፡ ሣጥን ፡ ጨመረቻቸው ፡ ለልጆቿም ፡ ብርሌ ፡ ከሚመስል ፡ ዕንቍ ፡ ሁለት ፡ ሣጥን ፡ አሠርታ ፡ በውስጣቸው ፡ አድረጋ ፡ በሠራችው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ አኖረቻቸው ፡ ከሥጋቸውም ፡ ታላላቅ ፡ የሆኑ ፡ ቍጥር፡ የሌላቸው፡ተአምራት፡ተገለጡ።

፲፬፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም፡ በቅዱሳን፡ ሰማዕታት ፡ጸሎት፡ ይማረን፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

## አርኬ

ሰላም፡ለመርምህናም፡እንተ፡ዔለ፡በድወ።ሃይማኖተ፡ክርስቶስ፡ ይኅሥሥ፡ ድኅረ፡ ሐልዮቱ፡ንዒወ። ነጺ.ሮ፡ደሞ፡በእንተ፡ሃይማኖት፡ክዕወ።ከመ፡ሐራውያ፡ንጉሥ፡ነቀወ።ወፀሐየ፡ራማ፡ብርሃኖ፡ሐሰወ።

ሰላም፡ሰላም፡ ዕደ.ወ፡ኃይል፡ሐራ።ዘኍላቌሆሙ፡ካዕበተ፡እስራ።በእንተ፡ክርስቶስ፡ ዘፆሩ፡ለክበደ፡ ዕለት፡ፃዕራ።ዘመርምህናም፡እግዚ.አሙ፡ሶበ፡ነጸሩ፡መከራ።ወዘምስሌሁ፡እንተ፡ሐመት፡ሣራ።

፲፱፡ወበዛቲ፡ ዕለት፡ ኮነ፡ ተዝካሮሙ፡ ለ ፲ወ፯ ፼ ሰማዕታት፡እምነ፡ሠራዊቱ፡ለንጉሠ፡አቶር፡ ሰናክሬም፡አቡሁ፡ለቅዱስ፡መርምህናም።

፳፡ውእቱኬ፡እምድኅረ፡ሞተ፡ሰናክሬም፡ንጉሠ፡ አቶር፡ ወነግሠ፡ ህየንቴሁ፡ ወልዱ፡ ንዑስ፡ ሕፃን ፡ ዘኢ.ይክል ፡ ዐቂበ ፡ መንግሥት ፡ ወትእዛዘ፡ወባሕቱ፡ኮነት፡እሙ፡ህየንቴሁ፡ ዘትኤዝዞሙ፡ለመገብት፡ወእሙንቱ፡ይትቀነዩ፡ላቲ።

፳፩፡ወሰሚያ፡ንጉሥ፡ከለዳዊ፡ዘንተ፡በእንተዝ፡ አስተጋብአ ፡ ሠራዊቶ ፡ ከመ ፡ ይንሣእ ፡ መንግሥተ፡አቶር፡ወመጽአ፡ለተቃትሎ፡ ወወጽኡ፡አግብርቲሁ፡ለሰናክሬም፡ወአግብርተ፡ መርምህናም፡ እለ፡ ኮኑ፡ የዐቅቡ፡ መቃብሮ ፡ ከመ ፡ ይትቃተሉ ፡ ወሞዖሙ ፡ ንጉሠ ፡ ከለዳውያን ፡ ወአርኀዋ ፡ ለሀገር ፡ ወአኀዞ፡ለሕፃን፡ንጉሥ፡ወቀተሎ፡ምስለ፡ እሙ፡ ወእምዝ፡ገረሩ፡ሎቱ፡ሰብአ፡ሀገረ፡ አቶር፡ወነግሠ፡ላዕሌሆሙ።

፳፪፡ወእምድኅረ፡ኅዳጥ፡መዋዕል፡አስተጋብአሙ፡ ለሰብአ ፡ ሀገረ ፡ አቶር ፡ ወተሰአሎሙ ፡ በእንተ፡ሃይማኖት፡ወይቤልዎ፡እሙንቱ፡ ንሕነ፡ክርስቲያን፡ወአዘዞሙ፡ከመ፡ይስግዱ ፡ ለጣዖት ፡ ወቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ እለ ፡ ዐለዉ፡ሃይማኖቶሙ፡ወሰገዱ፡ለጣዖት።

፳፫፡ወመጽኡ፡አግብርተ፡ቅዱስ፡መርምህናም፡ ወአግብርተ፡አቡሁ፡ወይቤልዎ፡ንሕነ፡ክርስቲያን፡ ገሀደ፡ አግብርቲሁ፡ ለክርስቶስ፡ ወኢ.ንክህድ፡ ሃይማኖተነ፡ ዘመሀረነ፡ እግእነ፡ ወግበር፡ ላዕሌነ፡ ዘፈቀድከ። ወሶቤሃ፡ ተምዐ ፡ ወአዘዘ ፡ ይቅትልዎሙ ፡ ወኮነ ፡ ኍልቆሙ፡፲ተ፡ወ፯ተ፡፼ፈ።ወእሙንቱ፡ተሰምዩ፡ማኅበራኒሁ፡ለቅዱስ፡መርምህናም።

፲፱፡ በዚ.ችም፡ ዕለት፡ ዳግመኛ፡ ከቅዱስ፡ መርምህናም፡ አባት፡ ከአቶር፡ ንጉሥ፡ ከሰናክሬም፡ ሠራዊት፡የአሥራ፡ሰባት፡እልፍ፡ሰማዕታት፡ መታሰቢ.ያቸው፡ሆነ።

፳፡ ይህም ፡ እንዲ.ህ ፡ ነው ፡ የአቶር ፡ ንጉሥ ፡ ሰናክሬም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ መንግሥቱን ፡ መጠበቅና ፡ ማዘዝ ፡ የማይችል ፡ ታናሽ ፡ ብላቴና፡ልጁ.፡በእርሱ፡ፈንታ፡ነገሠ፡ግን፡ እናቱ ፡ ስለርሱ ፡ ሹሞችን ፡ ታዝዛቸዋለች ፡ እነርሱም፡ይታዘዙላት፡ነበር።

፳፩፡ ከለዳዊ ንጉሥም፡ይህን፡በሰማ፡ጊዜ፡የአቶርን መንግሥት ለመውሰድ ፡ ስለዚ.ህ ሠራዊቱን ፡ ሰብስቦ ፡ ለመዋጋት ፡ መጣ ፡ የሰናክሬምም፡አሽከሮችና፡መቃብሩን፡ጠባቂዎች፡ የሆኑ፡የቅዱስ፡መርምህናም፡አሽከሮችም፡ ሊ.ከላከሉ፡ ወጡ፡ የከለዳውያን፡ ንጉሥም፡ አሸንፎ፡ ከተማዪቱን፡ ከፍቶ፡ ገባ፡ ብላቴናውንም፡ንጉሥ፡ይዞ፡ከእናቱ፡ጋር፡ገደለው፡ ከዚ.ህም ፡ በኋላ ፡ የአቶር ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ተገዙለት፡በላያቸውም፡ነገሠ፡መንግሥትን፡ ያዘ።

፳፪፡ ከጥቂት፡ ቀኖችም፡ በኋላ፡ የአቶርን፡ አገር፡ ሰዎች ፡ ሰብስቦ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ጠየቃቸው፡እነርሱም፡ክርስቲያን፡ነን፡አሉት። እርሱም፡ለጣዖት፡እንዲሰግዱ፡አዘዛቸው፡ ከእነርሱም፡ ውስጥ ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ ለውጠው፡ለጣዖት፡የሰገዱ፡አሉ።

፳፫፡የቅዱስ፡መርምህናምና፡የአባቱ፡አገልጋዮች፡ መጥተው፡እንዲህ፡አሉት፡እኛ፡የክርስቶስ፡ አገልጋዮች፡የሆን፡በግልጥ፡ክርስቲያኖች፡ ነን ፡ ጌታችን ፡ ያስተማረንን ፡ ሃይማኖታችንን ፡ አንክድም ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ የፈለግኸውን፡ አድርግ፡ አሉት፡ በዚ.ያንም፡ ጊዜ፡ ተቆጣ፡ይገድሏቸውም፡ዘንድ፡አዘዘ፡ቍጥራቸውም፡አንድ፡መቶ፡ሰባ፡ሺ.ህ፡ሆነ፡እነርሱም ፡ የቅዱስ ፡ መርምህናም ፡ ማኅበር ፡ ተብለው፡ተጠሩ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፬፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፳፭፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእስክንድርያ ፡ ወውእቱ ፡ እምኍልቆሙ ፡ ለአበው ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ፺ወ፮ቱ።

፳፮፤ ወኮኑ ፡ በመዋዕሊሁ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ተአምራት ፡ ወመንክራት ፡ ብዙኃት ፡ ወናሁ ፡ ውእቱ ፡ ሰምዐ ፡ በእንተ ፡ አሐቲ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘተሐንፀት ፡ በስመ ፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ በብሔረ ፡ እንዱልስ ፡ ወከመ ፡ ዕፀ ፡ ዘይት ፡ ይብስት ፡ ሀለወት ፡ በአንቀጸ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወበ ዕለተ ፡ በዓላ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ትሠርፅ ፡ ወትጸጊ ፡ ወታፈሪ ፡ ብዙኀ ፡ ወድኅረ ፡ ተፈጸመ ፡ በዓል ፡ ትትመየጥ ፡ ወትየብስ ፡ ወትከውን ፡ ከመ ፡ ቀዳሚ። ወበእንተዝ ፡ ጸለየ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ይክሥት ፡ ሎቱ ፡ ተአምረ ፡ ዝንተ ፡ ወበይእቲ ፡ ዕለተ ፡ በዓላ ፡ ለእግዝእትነ ፡ መሥጠ ፡ መልእከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአብጽሖ ፡ ኀበ ፡ ይእቲ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወርእያ ፡ ለይእቲ ፡ ዕፅ ፡ እንዘ ፡ ይብስት ፡ ይእቲ ፡ አሜሃኒ ፡ ሠረፀት ፡ ወጸገየት ፡ ወፈረየት ፡ ብዙኀ ፡ ወድኅረ ፡ ፍጻሜ ፡ በዓል ፡ ተመይጠት ፡ ኀበ ፡ ይብሰታ ፡ ወነገሮሙ ፡ ዘንተ ፡ ለሕዝቡ ፡ ወእሙንቱ ፡ ናፈቁ።

፳፯፤ ወእምድኅረ ፡ ኅዳጥ ፡ መዋዕል ፡ በጽሐ ፡ መኰንን ፡ እምይእቲ ፡ ሀገረ ፡ እንዱልስ ፡ ዘስሙ ፡ ዮሐንስ ፡ ወተስአሎ ፡ ውእቱ ፡ አብ ፡ አባ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በቅድመ ፡ ኵሎሙ ፡ ካህናት ፡ ወሕዝብ ፡ ወይቤሎ ፡ አማንኑ ፡ ዘሰማዕነ ፡ ከመ ፡ ሀለወት ፡ ዕፀ ፡ ዘይት ፡ ይብስት ፡ ኀበ ፡ አንቀጸ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያና ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ በሀገረ ፡ እንዱልስ ፡ በዕለተ ፡ በዓላ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ዘትሠርፅ ፡ ወታፈሪ።

፳፰፤ ወተሠጥዎ ፡ ውእቱ ፡ መኰንን ፡ ወይቤሎ ፡ እሙን ፡ ውእቱ ፡ አቡየ ፡ እስመ ፡ አነ ፡ ነበርኩ ፡ ህየ ፡ ወበዕለተ ፡ በዓላ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ርኢክዋ ፡ ቅድመ ፡ ከመ ፡ ይብስት ፡ ይእቲ ፡ ወሶበ ፡ ሠረቀ ፡ ፀሐይ ፡ በዕለተ ፡ በዓላ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ሠረፀት ፡

፳፬፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

፳፭፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ ቅዱስ ፡ አባት ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ አረፈ ፡ እርሱም ፡ ለአባቶች ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ስሳ ፡ ስድስተኛ ፡ ነው።

፳፮፤ በዚህም ፡ አባት ፡ ዘመን ፡ ብዙዎች ፡ አስደናቂዎች ፡ ተአምራት ፡ ተደረጉ ። እነሆ ፡ እንዱልስ ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ በእመቤታችን ፡ በቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ስም ፡ የተሠራች ፡ አንዲት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዳለች ፡ በደጃፍዋም ፡ የደረቀች ፡ የወይራ ፡ ዕንጨት ፡ እንዳለች ፡ በእመቤታችንም ፡ በበዓልዋ ፡ ቀን ፡ እንደምትለመልም ፡ እንደምታብብና ፡ ብዙ ፡ እንደምታፈራ ፡ በዓሉም ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ተመልሳ ፡ እንደምትደርቅና ፡ እንደ ፡ ቀድሞዋ ፡ እንደምትሆን ፡ ሰማ። ስለዚህም ፡ ይህን ፡ ተአምር ፡ ይገልጽለት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለመነ ፡ በዚያችም ፡ በእመቤታችን ፡ በዓል ፡ ዕለት ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ የታዘዘ ፡ መልአክ ፡ ነጥቆ ፡ ወደዚያች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አደረሰው ፡ ያቺንም ፡ ዕንጨት ፡ ደረቅ ፡ ሁና ፡ አያት ፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ ለመለመች ፡ አበበችና ፡ ብዙ ፡ ፍሬንም ፡ አፈራች ፡ ከበዓሉ ፡ ፍጻሜ ፡ በኋላም ፡ ወደ ፡ ደረቅነቷ ፡ ተመለሰች ፡ ይህንንም ፡ ለሕዝቡ ፡ ቢነግራቸው ፡ እነርሱ ፡ ተጠራጠሩ።

፳፯፤ ከጥቂት ፡ ቀኖችም ፡ በኋላ ፡ ከዚያች ፡ እንዱልስ ፡ ከምትባል ፡ አገር ፡ ስሙ ፡ ዮሐንስ ፡ የሚባል ፡ መኰንን ፡ መጣ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ አባ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስም ፡ በካህናቱና ፡ በሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ፡ እንዱልስ ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ በእመቤታችን ፡ በቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደጃፍ ፡ የደረቀች ፡ የዘይት ፡ ዕንጨት ፡ እንዳለች ፡ በእመቤታችንም ፡ የበዓል ፡ ቀን ፡ እንደምትለመልምና ፡ እንደምታፈራ ፡ የሰማነው ፡ እውነት ፡ ነውን ፡ አለው።

፳፰፤ ያም ፡ መኰንን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ እኔ ፡ በዚያ ፡ ነበርኩ ፡ በእመቤታችንም ፡ በቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ደረቅ ፡ እንደሆነች ፡ አየኋት ፡ በእመቤታችንም ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ ፀሐይ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ያቺ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ይእቲ፡ ዕፅ ፡ ወጸገየት ፡ ወፈረየት ፡ ብዙኀ ፡ ዘአልቦ ፡ መጠን ፡ ወኵሎሙ ፡ ሕዝብ፡ ይሬእየዋ ፡ ክሡተ።

፳፱፡ ወእምድኅረ፡ፈጸሙ፡ገቢረ፡በዓል፡ይወጽእ፡ መጋቢ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወኵሎሙ ፡ ካህናት ፡ ወያስተጋብኡ ፡ እሎንተ ፡ ፍሬያተ ፡ ወይሬስይዎን ፡ ቅብዐ ፡ ለማኅቶተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወለሲሳዮሙ ፡ ዘየአክሎሙ ፡ እስከ ፡ ዓመት ፡ ወሕዝብኒ ፡ በበንስቲት ፡ ይነሥኡ ፡ ለበረከት ፡ ወእምዝ ፡ ትየብስ ። ወሰሚዖሙ ፡ ሕዝብ ፡ አንከሩ ፡ ፈድፋደ ፡ ወሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወአእኰትዋ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም።

፴፡ ወበመዋዕሊሁ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ሖረ ፡ ፩ ብእሲ ፡ ዘስሙ ፡ ቆሪል ፡ ብሔረ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወረሰዮ ፡ ርእሶ ፡ ጳጳሰ ፡ በሐሰት ፡ ወፈነወ ፡ ንዋየ ፡ ብዙኀ ፡ ኀበ ፡ ንጉሠ ፡ ግብጽ ፡ እንዘ ፡ ይብሎ ፡ አዝዞ ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመ ፡ ይፈኑ ፡ ሊተ ፡ መጽሐፈ ፡ መልእክት ፡ ወይሢመኒ ፡ ጳጳሰ ፡ በኀበ ፡ ሀሎኩ ፡ ብሔረ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወአነሂ ፡ ለለዓመት ፡ እፌኑ ፡ ለከ ፡ ብዙኀ ፡ ወርቀ ፡ አምኃከ።

፴፩፡ ወጸውዖ ፡ ንጉሥ ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወይቤሎ ፡ ፈኑ ፡ መጽሐፈ ፡ መልእክት ፡ ኀበ ፡ ብሔረ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወሢሞ ፡ ጵጵስና ፡ በኀበ ፡ ሀሎ ፡ ቆሪል ፡ አውሥአ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወይቤሎ ፡ ለንጉሥ ፡ ኢኮነ ፡ ዝንቱ ፡ መፍትው ፡ ዘእንበለ ፡ ይብጻሕ ፡ ዝየ ፡ ብእሲሁ ፡ ወይቤሎ ፡ ንጉሥ ፡ ግበር ፡ በከመ ፡ አዘዝኩከ ፡ ይእነ ፡ ውእቱኒ ፡ ይቤሎ ፡ ፈቃድከ ፡ ይኩን ፡ ወወጽአ።

፴፪፡ ወተመይጠ ፡ እንዘ ፡ ይቴክዝ ፡ ፈድፋደ ፡ ወአስተጋብአሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ወነገሮሙ ፡ ዘከመ ፡ አዘዞ ፡ ንጉሥ ፡ ወሶበ ፡ ሰምዑ ፡ እሙንቱ ፡ ኀዘኑ ፡ ፈድፋደ ፡ ጸለዩ ፡ ወአስተብቍዑ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀቡረ ፡ ከመ ፡ ያድኅኖሙ ፡ እምተንኰልዎቱ ፡ ለቆሪል ሐሳዊ።

፴፫፡ ወበውእቱ ፡ መዋዕል ፡ ተንሥአ ፡ ቆሪል ፡ ሐሳዊ ፡ ወነሥአ ፡ ወርቀ ፡ ብዙኀ ፡ ወጐየ ፡ እምብሔረ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወበጽሐ ፡ ኀበ ፡ ብሔረ ፡ ዳኅሉክ ፡ ወአኀዞ ፡ ንጉሠ ፡ ዳኅሉክ ፡ ወነሥአ ፡ ኵሎ ፡ ንዋየ ፡ ዘሰረቀ ፡ እምብሔረ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወአሠሮ ፡ ወፈነዎ ፡ ኀበ ፡ ንጉሠ ፡

ዕንጨት ፡ ለመለመች ፡ አብባም ፡ መጠን ፡ የሌለው ፡ ብዙ ፡ ፍሬን ፡ አፈራች ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ በግልጽ ፡ ያይዋታል።

፳፱፡ የበዓሉንም ፡ አከባበር ፡ ሥራ ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሹም ፡ ይወጣል ፡ ካህናቱም ፡ ሁሉ ፡ ወጥተው ፡ እነዚያን ፡ ፍሬዎች ፡ ሰብስበው ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መብራትና ፡ ለምግባቸው ፡ እስከ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ የሚበቃቸውን ፡ ያዘጋጃሉ ፡ ሕዝቡም ፡ ለበረከት ፡ እያሉ ፡ በየጥቂቱ ፡ ይወስዳሉ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ትደርቃለች ። ሕዝቡም ፡ ሰምተው ፡ እጅግ ፡ አደነቁ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ አመሰገኑ ፡ እመቤታችን ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያምንም ፡ አመሰገኑዋት።

፴፡ በዚህም ፡ አባት ፡ ዘመን ፡ ስሙ ፡ ቆሪል ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አገር ፡ ሒዶ ፡ በሐሰት ፡ ራሱን ፡ ጳጳስ ፡ አደረገ ፡ ለግብጽ ፡ ንጉሥም ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ላከለትና ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ በአለሁበት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሀገር ፡ የጵጵስና ፡ ሹመት ፡ እንዲሾመኝና ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤ ፡ እንዲልክልኝ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስን ፡ እዘዘው ፡ እኔም ፡ እጅ ፡ መንሻህን ፡ በየዓመቱ ፡ ብዙ ፡ ወርቅ ፡ እልክልሃለሁ ፡ አለው።

፴፩፡ ንጉሡም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱን ፡ ጠርቶ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ ቆሪልን ፡ በአለበት ፡ በኢትዮጵያ ፡ አገር ፡ ጵጵስና ፡ ሹመውና ፡ የሹመቱን ፡ ደብዳቤ ፡ ላክለት ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱም ፡ ወደዚህ ፡ ሰውዬው ፡ ሳይቀርብ ፡ ይህ ፡ ሊሆን ፡ አይገባም ፡ ብሎ ፡ ለንጉሡ ፡ መለሰለት ፡ ንጉሡም ፡ እኔ ፡ እንዳዘዝኩህ ፡ አድርግ ፡ አለው ። እርሱም ፡ ፈቃድህ ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ ወጣ።

፴፪፡ እጅግም ፡ እያዘነ ፡ ተመለሰ ፡ ኤጲስቆጶሳቱን ፡ ሁሉንም ፡ ሰበሰባቸውና ፡ ንጉሥ ፡ ያዘዘውን ፡ ነገራቸው ፡ እነርሱም ፡ ሲሰሙ ፡ እጅግ ፡ አዘኑ ፡ ከሐሰተኛውም ፡ ከቆሪል ፡ ተንኰል ፡ ያድናቸው ፡ ዘንድ ፡ በአንድነት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በመጸለይ ፡ ማለዱ።

፴፫፡ በዚያም ፡ ወራት ፡ ሐሰተኛው ፡ ቆሪል ፡ ተነሣ ፡ ብዙ ፡ ወርቅንም ፡ ይዞ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ አገር ፡ ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ ዳኅላክ ፡ ደረሰ ፡ የዳኅላክም ፡ ንጉሥ ፡ ይዞ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ አገር ፡ የሰረቀውን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ወረሰው ። እርሱንም ፡ አሥሮ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ አስተላለፈው ፡

www.ethiopianorthodox.org

ግብጽ ፡ ውእቱኒ ፡ ንጉሠ ፡ ግብጽ ፡ ሞቅሖ ፡ ፮ተ ፡ አውራኀ ፡ ወእምዝ ፡ አምተረ ፡ ርእሶ ፡ በሰይፍ ፡ ወሞተ ፡ በእኩይ ፡ ሞት ፡ እስመ ፡ ተወከፈ ፡ እግዚእነ ፡ ጸሎቶ ፡ ለዝንቱ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ።

፴፬ ፡ ወነበረ ፡ ዝንቱ ፡ አብ ፡ ዲበ ፡ መንበረ ፡ ማርቆስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ፴ዓመተ ፡ ወአሥመሮ ፡ ለእግዚእነ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወአዕረፈ ፡ በሰላም ።

፴፭ ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

እርሱም ፡ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ አሥሮ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ራሱን ፡ በሰይፍ ፡ አስቆረጠው ፡ በክፉ ፡ አሟሟትም ፡ ሞተ ፡ የሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስን ፡ ጸሎት ፡ እግዚአብሔር ፡ ተቀብሏልና ።

፴፬ ፡ ይህም ፡ አባት ፡ በወንጌላዊ ማርቆስ ፡ ወንበር ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፡ ክብሩ ፡ ይግባውና ፡ ጌታችንንም ፡ አገልግሎ ፡ በሰላም ፡ አረፈ ።

፴፭ ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በዚህ ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ በቅብዐ ፡ ክህነት ፡ ዘተኀትመ ። አበ ፡ ድኩማን ፡ ይኩን ፡ ወዘመዓስባን ፡ ቃውመ ። ከመ ፡ ርእየ ፡ ይቤ ፡ በቤተ ፡ ማርያም ፡ መድምመ ። ይቡስ ፡ ዕፀ ፡ ዘይት ፡ እስከ ፡ ይፈሪ ፡ ጥዑመ ። ለለበዓላ ፡ ሠሪፆ ፡ ይየይብስ ፡ ዳግመ ።

፴፮ ፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ስምዐ ፡ አባ ፡ አሞንዮስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘሀገረ ፡ እስና ።

፴፯ ፡ ወሶበ ፡ በጽሐ ፡ አርያኖስ ፡ ሀገረ ፡ እስና ፡ ረከበሙ ፡ ለብዙኃን ፡ ሰብእ ፡ ተጋቢኦሙ ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ አሞንዮስ ፡ እንዘ ፡ ይትሜሀሩ ፡ ነገረ ፡ ሃይማኖት ፡ ወአኀዞሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ወቀተሎሙ ፡ ወለአባ ፡ አሞንዮስሰ ፡ አሠሮ ፡ ወወሰዶ ፡ ወአገበሮ ፡ ብዙኀ ፡ ከመ ፡ ይስግድ ፡ ለጣዖት ። ወይቤሎ ፡ አባ ፡ አሞንዮስ ፡ እስመ ፡ ጽሑፍ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡ ትስግድ ፡ ወኪያሁ ፡ ባሕቲቶ ፡ ታምልክ ፡ ወአንሰ ፡ ኢይሠምር ፡ በተዛውዖትክሙ ፡ ከንቱ ፡ ወኢይሰምዕ ፡ ነገረክሙ ፡ በከ ፡ ወኢይፈቅድ ፡ እርአይ ፡ አማልክቲክሙ ፡ ርኩሳነ ፡ ወኢያንሶሱ ፡ ቤተ ፡ ጣዖትክሙ ፡ ምዝበር ፡ ወኢይእኀዝ ፡ ማዕጠንተክሙ ፡ ወምሥዋዒክሙ ፡ ፍጉገ ።

፴፮ ፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ የሀገረ ፡ እስና ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አባ ፡ አሞንዮስ ፡ በምስክርነት ፡ አረፈ ።

፴፯ ፡ አርያኖስም ፡ ወደ ፡ እስና ፡ ከተማ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ከአባ ፡ አሞንዮስ ፡ ዘንድ ፡ ተሰብስበው ፡ የሃይማኖትን ፡ ትምህርት ፡ ሲማሩ ፡ አገኛቸውና ፡ ሁሉንም ፡ ይዞ ፡ ገደላቸው ፡ አባ ፡ አሞንዮስን ፡ ግን ፡ አሥሮ ፡ ወሰደው ፡ ለጣዖትም ፡ እንዲሰግድ ፡ ብዙ ፡ አግባባው ። አባ ፡ አሞንዮስም ፡ ለፈጣሪህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትሰግድ ፡ ዘንድ ፡ እርሱንም ፡ ብቻውን ፡ ታመልክ ፡ ዘንድ ፡ ተጽፎአልና ፡ ከንቱ ፡ የሆነ ፡ የእንቶቅልሽ ፡ ጨዋታችሁን ፡ ብላሽ ፡ የሆነ ፡ ነገራችሁንም ፡ መስማት ፡ አልወድም ፡ የረከሱ ፡ አማልክቶቻችሁንም ፡ ማየት ፡ አልሻም ፡ ፈራሽ ፡ በሆነ ፡ የጣዖት ፡ ቤታችሁም ፡ መመላለስን ፡ የከረፋ ፡ የሸተተ ፡ ማዕጠንታችሁንና ፡ መሥዋዕታችሁን ፡ አልይዝም ፡ አለው ።

፴፰ ፡ ወሶበ ፡ ርእየ ፡ አርያኖስ ፡ መኰንን ፡ ከመ ፡ ሕሊናሁ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ኢይፈልስ ፡ ወኢይትዌለጥ ፡ አዘዘ ፡ ያውዕይዎ ፡ በእሳት ፡ እንዘ ፡ ሕያው ፡ ውእቱ ፡ ወሰአሎሙ ፡ ለሐራ ፡ አባ ፡ አሞንዮስ ፡ ከመ ፡ ይጽንሕዎ ፡ ንስቲተ ፡ እስከ ፡ ይጼሊ ፡ ወቆመ ፡ እንዘ ፡ እሡር ፡ እደዊሁ ፡ ወእገሪሁ ፡ ወጸለየ ፡ ጸሎተ ፡ ወንጌል ፡ ወባረከ ፡ ሀገሮ ፡ ወሕዝቦ ፡ ወኵሎ ፡ ምእመናነ ፡ በክርስቶስ ። ወጸለየ ፡ ዓዲ ፡ በእንተ ፡ አርያኖስ ፡ መኰንን ፡ ወተነበየ ፡ በእንቲአሁ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ይከውን ፡ ሰማዕተ ፡ ወዓዲ ፡ ፈተሐ ፡ ነፍሶ ፡

፴፰ ፡ መኰንኑ ፡ አርያኖስም ፡ የዚህ ፡ አባት ፡ ልብ ፡ ፈጽሞ ፡ እንደማይበገር ፡ በአየ ፡ ጊዜ ፡ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ በእሳት ፡ እንዲአቃጥሉት ፡ አዘዘ ፡ አባ ፡ አሞንዮስም ፡ እስከሚጸልይ ፡ ጥቂት ፡ ይጠብቁት ፡ ዘንድ ፡ ወታደሮቹን ፡ ለመናቸውና ፡ እጆቹና ፡ እግሮቹም ፡ እንደታሠሩ ፡ ቆመ ፡ የወንጌልንም ፡ ጸሎት ፡ ጸለየና ፡ ሀገሩን ፡ ሕዝቡን ፡ በክርስቶስም ፡ የሚታመኑትን ፡ ሁሉ ፡ ባረከ ፡ ዳግመኛም ፡ ስለ ፡ መኰንኑ ፡ አርያኖስ ፡ ጸለየ ፡ በሰማዕትነትም ፡ እንደሚሞት ፡ ስለርሱ ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ፡ ደግሞ ፡ ነፍሱን ፡ አሰናበተ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወፈጺሞ ፡ ጸሎቶ ፡ ወገርዎ ፡ ውስተ ፡ እሳት ፡
ወፈጸመ፡ገድሎ፡ሠናየ፡ወእምገ፡ሶበ፡ጠፍአ፡
እሳት ፡ ረከቡ ፡ ሥጋሁ ፡ ንጹሐ ፡ እንዘ ፡ አልቦ ፡
ዘለከፎ ፡ እምእሳት ፡ ወገነዝዎ ፡ በአልባስ ፡
ሠናያን ፡ ወቀበርዎ ፡ ውስተ ፡ ምዕራቢሃ ፡
ለሀገረ ፡ እንጽና ፡ ውስተ ፡ ማኅፈድ ፡ ዘሐነፀቶ ፡
አክላወባጥራ ፡ ንግሥት ፡ ወለተ ፡ በጥሊሞስ ፡
ንጉሥ ፡ ወኮነ ፡ እምነ ፡ ሥጋሁ ፡ ተአምራት ፡
ወመንክራት ፡ ዐበይት ።

፴፱ ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም
ሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓ
ለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

ጸሎቱንም ፡ ሲፈጽም ፡ ወደ ፡ እሳት ፡ ወረወ
ሩትና ፡ ያማረ ፡ ተጋድሎውን ፡ ፈጸመ ፡ ከዚ
ህም ፡ በኋላ ፡ እሳቱ ፡ በጠፋ ፡ ጊዜ ፡ ከእሳት ፡
ቃጠሎ ፡ የነካው ፡ ሳይኖር ፡ ንጹሕ ፡ ሁኖ ፡
ሥጋውን ፡ አገኙት ፡ በአማሩ ፡ ልብሶችም ፡
ገንዘው ፡ በእንጽና ፡ ከተማ ፡ በስተምዕራብ ፡
የንጉሥ ፡ በጥሊሞስ ፡ ልጅ ፡ ንግሥት ፡ አክላ
ወባጥራ ፡ በአሠራችው ፡ ግምብ ፡ ውስጥ ፡ ቀበ
ሩት ፡ ከሥጋውም ፡ ታላልቅ ፡ አስደናቂዎች ፡
ተአምራት ፡ ተገለጡ ።

፴፱ ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ
ንም ፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡
ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

## አርኬ

፡ ሰላም ፡ ለአሞንዮስ ፡ ለአድያመ ፡ እንጽና ፡ ዘዖዳ ። ምስለ ፡ ቃለ ፡ ምክር ፡ ሠናይ ፡ ማዕከለ ፡ ብዙኃን ፡
ውሉዳ ። በጊዜ ፡ ፈጸመ ፡ ስምዖ ፡ ለእቶነ ፡ እሳት ፡ በነዳ ። ድኅረ ፡ አርመመ ፡ ማዕበላ ፡ ወድኅረ ፡ ኀድዐ ፡ ሞገዳ ።
በአምሳለ ፡ በረድ ፡ ተረክበ ፡ ሥጋሁ ፡ ፀዓዳ ።
፡ ሰላም ፡ እብል ፡ አርያኖስሃ ፡ ቀሲሰ ። ወለአርክሊስ ፡ እኁሁ ፡ ፈሪሀ ፡ እግዚአብሐር ፡ ዘለብሰ ። ደቂቀ ፡ ኅር
ኅርዮስ ፡ እለ ፡ ዘኢየአምሩ ፡ ደነሰ ። አሐዱ ፡ በኒሩቱ ፡ ተሠይመ ፡ ጳጳሰ ። ወካልኡኒ ፡ መኒኖ ፡ ገዳመ ፡ ፈለሰ ።

፴ ፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈት ፡ ወለተ ፡ ንጉሠ ፡
ሮም ፡ ዘስማ ፡ ነሳሒት ፡ በከመ ፡ ነገረ ፡ በእን
ቲአሃ ፡ አባ ፡ ያዕቆብ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘው
ሲም ።

፴፩ ፡ ወይቤ ፡ በአሐቲ ፡ ዕለት ፡ እንዘ ፡ ሀሎኩ ፡
ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያና ፡ ለእግዝእትነ ፡
ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አም
ላክ ፡ ሰማዕኩ ፡ እንዘ ፡ ይጐድጕድ ፡ ሰብእ ፡
አንቀጸ ፡ ምኔት ፡ ወተንሣእኩ ፡ ወሖርኩ ፡
ወርኢኩ ፡ ሰብአ ፡ ዘዲቤሁ ፡ ዓጽፍ ፡ ብሉይ ፡
ወገጹ ፡ ግልቡብ ። ወእቤሎ ፡ እምአይቴ ፡ መጻ
እከ ፡ ወነበ ፡ አይቴ ፡ ተሐውር ፡ ወይቤለኒ ፡ መጻ
እኩ ፡ እምደብረ ፡ አባ ፡ መቃርዮስ ፡ ወእፈቅድ ፡
እቢት ፡ በዛቲ ፡ ሌሊት ፡ ውስተ ፡ ዛቲ ፡ ምኔት ፡
ከመ ፡ እትመጦ ፡ ቍርባነ ፡ አሜሃ ፡ ዕለተ ፡
ቀዳሚት ፡ ሰንበት ፡ ወእቤሎ ፡ ኢያርኁ ፡ ለከ ፡
ለእመ ፡ ኢያርአይከኒ ፡ ገጸከ ፡ ውእቱኒ ፡ ይቤለኒ ፡
ኢትኅሥሥ ፡ ኀበ ፡ ርእየተ ፡ ገጽየ ፡ እስመ ፡
ገጽየ ፡ መጽልም ፡ በእንተ ፡ ኃጢአትየ ፡ ወለዘ
ይሬኢ ፡ ገጽየ ፡ ታስተርኢ ፡ ሎቱ ፡ ምግባርየ ፡
እኪት ።

፴፪ ፡ ወሶበ ፡ አበይክዎ ፡ ፈቀደ ፡ ይትመየጥ ፡ ውስተ ፡
ገዳም ፡ ወሐለይኩ ፡ በልብየ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡
ርኁብ ፡ አው ፡ ጽሙዕ ፡ ወበእንተዝ ፡ አርኀ
ውኩ ፡ ሎቱ ፡ ወአባእክዎ ፡ ውስተ ፡ ማኅደርየ ፡
ወአምጻእኩ ፡ ሎቱ ፡ መብልዐ ፡ ወአበየኒ ፡ ወይ

፴ ፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ የውሲም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አባ ፡
ያዕቆብ ፡ ስለርሷ ፡ እንደተናገረ ፡ የሮም ፡
ንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ስሟ ፡ ነሳሒት ፡ የተባለ ፡
አረፈች ።

፴፩ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፡ በአንዲት ፡ ዕለት ፡ አምላክን ፡
በወለደች ፡ በእመቤታችን ፡ በቅድስት ፡ ድን
ግል ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡
እያለሁ ፡ የገዳሙን ፡ ደጅ ፡ ሰው ፡ ሲያንኳኳ ፡
ሰማሁ ፡ ተነሥቼም ፡ ወደ ፡ በሩ ፡ ሔድኩ ፡
ያረጀ ፡ ዓጽፍ ፡ የለበሰ ፡ ፊቱንም ፡ የተሸፋፈነ ፡
ሰው ፡ አየሁ ፡ ከወዴት ፡ መጣህ ፡ ወዴትስ ፡
ትሔዳለህ ፡ አልሁት ። ከአባ ፡ መቃርዮስ ፡
ገዳም ፡ መጣሁ ፡ በዚች ፡ ሌሊት ፡ ከዚህ ፡ ገዳም ፡
አድሬ ፡ ቍርባንን ፡ መቀበል ፡ እሻለሁ ፡ አለኝ ፡
ያን ፡ ጊዜ ፡ ቀዳሚት ፡ ሰንበት ፡ ነበረች ፡ እኔም ፡
ፊትህን ፡ ካላሳየኸኝ ፡ አልከፍትልህም ፡ አል
ሁት ፡ እርሱም ፡ ፊቴን ፡ ማየት ፡ አትሻ ፡ ፊቴ ፡
በኃጢአቴ ፡ የጨለመ ፡ ነውና ፡ ፊቴንም ፡ ለሚ
ያይ ፡ የከፋች ፡ ሥራዬ ፡ ትታየዋለች ፡ አለኝ ።

፴፪ ፡ በከለከልኩትም ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ዱር ፡ ሊመለስ ፡
ወደደ ፡ እኔም ፡ ተርቦ ፡ ወይም ፡ ተጠምቶ ፡
እንደሆነ ፡ ብዬ ፡ በልቤ ፡ አሰብኩ ፡ ስለዚህም ፡
ከፈትኩለትና ፡ ወደ ፡ ማደሪያዬ ፡ አስገባሁት ፡
መብልንም ፡ አመጣሁለት ፡ እርሱም ፡ ከነገ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ቤለኒ ፡ አንሰ ፡ ኢይበልዕ ፡ ዘእንበለ ፡ ጌሠም ፡ እምድኅረ፡ቀኊርባን።

፵፫፡ ወእምዝ ፡ ቦአ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወቆመ ፡ ውስተ ፡ መካነ ፡ ጽልመት ፡ ወሰማዕኩ፡ድምፆ፡ከመ፡ድምፀ፡መላእክት፡እንዘ፡ያነብብ፡መዝሙረ፡ዳዊት፡እስከ፡አንከሩ፡አኃው፡እለ፡ሀለዉ፡ህየ፡ወበጽባሕ፡ነበረ፡በእገሪሁ ፡ ወኢፈቀደ ፡ ያንብብ ፡ ወኢ ፡ ምንተኒ፡ንሕነሰ፡ቀረብነ፡ከመ፡ንስአሎ፡ይጸሊ፡ላዕሌነ፡ወይቤለነ፡እፎ፡እጼሊ፡በእንቲአክሙ፡አ፡አበውየ፡እንዘ፡መጽልመ፡ገጽ፡አነ፡በብዝኀ፡አበሳየ።

፵፬፡ ወሶበ ፡ አዕረግነ ፡ ቀኊርባነ ፡ ቆመ ፡ በእገሪሁ ፡ ወአኀዘ፡ያንብብ፡መጽሐፈ፡ጳውሎስ፡ወመልእክታተ፡ሐዋርያት፡ወግብረ፡ሐዋርያት፡ወበራብዕት፡ጊዜ፡ቆመ፡ቅድመ፡ምሥዋዕ፡ወወጠነ ፡ ያንብብ ፡ ወንጌለ ፡ ዮሐንስ ፡ ወከልአ ፡ ልብሰ ፡ እምዲበ ፡ ገጹ ፡ ወኢተክህሎሙ ፡ ይርአይዎ ፡ እምዕበየ ፡ ብርሃን ፡ ዘላዕለ ፡ ገጹ ፡ ወእምድኅረ ፡ ተመጠውነ ፡ ቀኊርባነ፡ውእቱኒ፡ተመጠወ፡እምድኅሬነ፡ወተሐዘብነ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ እምደቂቀ ፡ ነገሥት ፡ ወአቅረብነ ፡ ሎቱ ፡ መብልዐ ፡ ወኢነሥአ፡እምኔነ፡ወባሕቱ፡መዐደነ፡ከመ፡ንትገኃሥ፡እምርእየተ፡አንስት፡ዘያስሕት፡ቦቶን፡ሰይጣን።

፵፭፡ ወሀሎ፡፩አረጋዊ፡መነኰስ፡እምዘመደ፡ሮም፡ኄር፡ወጻድቅ፡ብእሲ፡ወውእቱ፡ይቤለኒ፡አ፡አቡየ፡ያዕቆብ፡እስመ፡ዛቲ፡ብእሲት፡ይእቲ፡እምአዋልደ፡ነገሥት፡ወበእንተዝ፡ትሜውር፡ገጻ፡እምሰብእ፡ከመ፡ኢያእምርዋ።

፵፮፡ ወእምዝ ፡ ሖርኩ ፡ ኀቤሃ ፡ ከመ ፡ አምሕላ ፡ በስመ፡ክርስቶስ፡ከመ፡ኢትኅባእ፡እምኔየ፡ግብራ ፡ ወትንግረኒ ፡ ባሕቱ ፡ ኢረከብክዋ ፡ ወእምድኅረ ፡ ኃምስቱ ፡ አውራኅ ፡ መጽኡ ፡ ብዙኃን ፡ ሰብእ ፡ እለ ፡ ተፈነዉ ፡ እምኀበ ፡ አቡሃ ፡ ንጉሥ ፡ እንዘ ፡ የኃሥሡ ፡ ኪያሃ ፡ ወእሙንቱ ፡ ዜነዉነ ፡ ግብራ ፡ ከመ ፡ ይእቲ ፡ ወጽአት፡በሌሊት፡እምድኅረ፡ኖሙ፡ሰብአ፡ቤታ፡ሎሙኒ፡ከመ፡ኮኖሙ፡፲ወ፪ተዓመተ፡እንዘ፡የኃሥሥዋ ፡ ወእምድኅረዝ ፡ ዜነዉነ ፡ ፈላስያን፡ከመ፡አዕረፈት፡በዛቲ፡ዕለት።

ከቍርባን ፡ በኋላ ፡ በቀር፡ እኔ ፡ አልበላም ፡ በማለት፡እምቢ፡አለኝ።

፵፫፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገባና፡በጨለማ፡ቦታ፡ቆመ፡ከዚያ፡ያሉ፡መነኰሳትም ፡ እስከ ፡ አደነቁ ፡ ድረስ ፡ የዳዊትን ፡ መዝሙር ፡ ሲያነብ ፡ ድምፁን ፡ እንደ ፡ መላእክት ፡ ድምፅ ፡ ሁኖ ፡ ሰማሁት ፡ በነጋም ፡ ጊዜ ፡ በእግሮቹ ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ ማንበብ ፡ አልሻም። እኛ ፡ ግን ፡ ይጸልይልን ፡ ዘንድ ፡ ልንለምነው ፡ ቀረብን ፡ እርሱም ፡ አባቶቼ ፡ ሆይ፡ በበደሌ ፡ ብዛት ፡ ፊቴን ፡ ያጨለምኩ ፡ ስሆን ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ እንዴት ፡ እጸልያለሁ ፡ አለን።

፵፬፡ ቍርባንንም ፡ በምናሳርግ ፡ ጊዜ ፡ በእግሩ ፡ ቁሞ፡ የጳውሎስን ፡ መልእክት ፡ የሐዋርያትንም ፡ መልእክትና ፡ የሐዋርያትን ፡ ሥራ ፡ ማንበብ ፡ ጀመረ ፡ በአራተኛም ፡ ጊዜ ፡ በመሠዊያው ፡ ፊት ፡ ቁሞ ፡ የዮሐንስን ፡ ወንጌል ፡ ማንበብ ፡ ጀመረ ፡ በፊቱም ፡ ላይ ፡ የተከናነበውን ፡ ልብስ፡ አስወገደ ፡ ከፊቱም ፡ ብርሃን ፡ ገናናነት ፡ የተነሣ ፡ ሊያዩት ፡ አልተቻላቸውም። እኛ ፡ ቍርባንን ፡ ከተቀበልን ፡ በኋላ ፡ ቆረበ፡ከነገሥታት፡ልጆች፡ወገንም፡እንደሆነ፡ተጠራጠርን ፡ መብልንም ፡ በአቀረብንለት ፡ ጊዜ ፡ ከእኛ ፡ አልተቀበለም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሰይጣን ፡ በእነርሱ ፡ ከሚያስትባቸው ፡ ሴቶችን፡ ከማየት፡እንርቅ፡ዘንድ፡መከረን።

፵፭፡ ሮማዊ፡የሆነ፡አንድ፡ደግ፡ጻድቅ፡አረጋዊ፡መነኵሴ ፡ ነበር ፡ እርሱም ፡ አባቴ ፡ ያዕቆብ ፡ ሆይ ፡ ይቺ ፡ ከነገሥታት ፡ ልጆች ፡ ውስጥ ፡ የሆነች ፡ ሴት ፡ ናት ፡ ስለዚህም ፡ እንዳትታወቅ፡ፊቷን፡ከሰው፡ትሠውራለች፡አለኝ።

፵፮፡ ከዚህም፡በኋላ፡ሥራዋን፡ከእኔ፡ሳትሠውር፡እንድትነግረኝ፡በክርስቶስ፡ስም፡አምላት፡ዘንድ ፡ ወደርሷ ፡ ሔድሁ ። ግን ፡ አላገኘኋትም ፡ ከአምስት ፡ ወርም ፡ በኋላ ፡ ከንጉሥ ፡ አባቷ ፡ ዘንድ ፡ የተላኩ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ እርሷን ፡ እየፈለጉ ፡ መጡ ። እነርሱም ፡ ቤተ ፡ ሰቦቿ፡ከተኙ፡በኋላ፡በሌሊት፡እንደወጣች፡እነርሱም፡እርሷን፡ሲፈልጉ፡ዐሥራ፡ሁለት፡ዓመት ፡ እንደሆናቸው ፡ ሥራዋን ፡ ነገሩን ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ መጻተኞች ፡ ሰዎች ፡ በዚች፡ቀን፡እንዳረፈች፡ነገሩን።

www.ethiopianorthodox.org

በእንተ ፡ ቅድስት ፡ አርሴማ ፡ እንዘ ፡ ይዜክር ፡
ስነ፡ላሕያ።
፬፡ ወእምዝ ፡ ሰአልዎ ፡ እሊአሁ ፡ ወይቤልዎ ፡
ተጸዓን ፡ ፈረሰ ፡ ወንጻእ ፡ ገዳመ ፡ ከመ ፡ ትን
ዓው ፡ አራዊተ ፡ ወይትአተት ፡ ኀዘን ፡ ዘው
ስተ ፡ ልብከ ፡ ወሶቤሃ ፡ ተጽዕነ ፡ ፈረሰ ፡ ወወ
ጽአ ፡ ገዳመ ፡ ከመ ፡ ይንዓው ፡ አራዊተ ፡
ወበጊዜሁ፡ተጽዕነ፡ላዕሌሁ፡ሰይጣን፡ወኮነ፡
ዘይነስክ ፡ ሥጋሁ ፡ ወይነስኮሙ ፡ ለእሊአሁ ።
ወወለጠ፡እግዚአብሔር፡አርአያሁ፡ወረሰዮ፡
ከመ ፡ ሐራውያ ፡ ወይነስክ ፡ ኵሎ ፡ ዘረከበ ፡
ወከማሁ ፡ ብዙኀን ፡ እምሰብአ ፡ ቤተ ፡
መንግሥት ፡ ተጽዕነ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ሰይጣን ፡
ወኮነ ፡ ዐቢይ ፡ ድንጋፄ ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ኵሉ ፡
ዘኮነ ፡ በእንተ ፡ ቅዱሳት ፡ ደናግል ፡ ወበእንተ፡
ቅድስት፡አርሴማ።
፭፡ ወእኅቱሰ ፡ ለንጉሥ ፡ ርእየት ፡ ራእየ ፡ ዘከመ ፡
ብእሲ ፡ ይቤላ ፡ ለእመ ፡ ኢያዕረግምዎ ፡ ለጎርጎ
ርዮስ፡እምውስተ፡ግብ፡አልብክሙ፡ድኂን፡
ወነገረት፡ዘንተ፡ለእሊአሃ፡ወደንገፁ፡እስመ፡
መሰሎሙ፡ከመ፡ውእቱ፡ሞተ፡እምቀዳሚ፡
በውስተ ፡ ግብ ። ወሶቤሃ ፡ ሖሩ ፡ ኀበ ፡ ግብ ፡
ወአውረዱ ፡ አሕባለ ፡ ውስተ ፡ ግብ ፡ ከመ ፡
ያእምሩ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ውእቱ ፡ ሕያወ ፡ ወጸ
ርሑ ፡ ኀቤሁ ፡ ከመ ፡ የአኀዝ ፡ አኅባለ ፡ ውእ
ቱኒ ፡ አኀዘ ፡ አኅባለ ፡ ወሰሐብዎ ፡ ወአውጽ
እዎ ፡ ወኀፀብዎ ፡ ወአልበስዎ ፡ ንጹሐ ፡ ልብሰ ፡
ወአጽዓንዎ ፡ ዲበ ፡ በቅል ፡ ወአብጽሕዎ ፡
ውስተ፡ቤተ፡መንግሥት።
፮፡ ወሶቤሃ፡ተሰአለ፡በእንተ፡ሥጋሆን፡ለደናግል፡
እለ ፡ ኮና ፡ ሰማዕተ ፡ ወእሙንቱ ፡ መርሕዎ ፡
ወአብጽሕዎ፡ኀበ፡ሀሎ፡ሥጋሆን፡ለደናግል፡
ወረከቦን፡ድኁናነ፡እምአራዊተ፡ገዳም፡ወእ
ምአዕዋፍ፡ወአዘዘ፡ከመ፡ያስተዳልዉ፡ሎቶን፡
መካናተ ፡ ሠናያነ ፡ ወያንብርዎን ፡ ውስቴቶን ፡
በክብር፡ወገብሩ፡በከመ፡አዘዞሙ።
፯፡ ወእምዝ ፡ ሰአልዎ ፡ ሕዝብ ፡ ከመ ፡ ይፊውሶ፡
ለንጉሥ ፡ ወአብጽሕዎ ፡ በድወ ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፡
ንጉሥ ፡ ወይቤሎ ፡ ቦኑ ፡ ትትመየጥኑ ፡ እምግ
ባሪከ ፡ እኩይ ፡ ወተአምንሁ ፡ በእግዚእነ ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወአመረ
በርእሱ ፡ ንጉሥ ፡ ዘኮነ ፡ ሐራውያ ፡ ከመ ፡
እወ ፡ ዘይብል ፡ ወሶቤሃ ፡ ጸለየ ፡ ቅዱስ ፡ ጎርጎ

ቅድስት ፡ አርሴማ ፡ አብዝቶ ፡ የሚያዝንና ፡
የሚጸጸት፡ሆነ።
፬፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወገኖቹ ፡ ለመኑት ፡ እንዲህም ፡
አሉት ፡ አውሬ ፡ ታድን ፡ ዘንድ ፡ በፈረስ ፡
ተቀመጥና ፡ ወደ ፡ዱር ፡ እንውጣ ፡ የልብህም ፡
ኀዘን፡ይወገድልሃል።በዚያንም፡ጊዜ፡አውሬ፡
ለማደን፡በፈረሱ፡ተቀምጦ፡ወደ፡ዱር፡ወጣ።
ወዲያውኑ ፡ ሰይጣን ፡ አደረበትና ፡ ሥጋውን ፡
የሚነክስ፡ሆነ፡ወገኖቹንም፡ነከሳቸው፡እግዚ
አብሔርም፡መልኩን፡ለውጦ፡እንደ፡እሪያ፡
አደረገው ፡ ያገኘውን ፡ ሁሉ ፡ የሚነክስ ፡ ሆነ ።
እንዲሁም፡ከቤተ፡መንግሥት፡ሰዎች፡በብዙ
ዎቹ ፡ ላይ ፡ ሰይጣን ፡ አደረባቸው ፡ ታላቅ ፡
ድንጋጤም ፡ ሆነ ፡ ይህም ፡ ሁሉ ፡ የሆነ ፡ ስለ ፡
ቅዱሳት ፡ ደናግልና ፡ ስለቅድስት ፡ አርሴማ ፡
ነው።
፭፡ የንጉሡ ፡ እኅት ፡ ግን ፡ ጎርጎርዮስን ፡ ከጕድጓድ ፡
ካላወጣችሁት ፡ ድኅነት ፡ የላችሁም ፡ የሚላ
ትን፡ ሰው ፡ በራእይ ፡ አየች ፡ ይህንንም ፡ ለወ
ገኖቿ፡ ነገረች ፡ እርሱ ፡ አስቀድሞ ፡ በጕድጓድ ፡
ውስጥ ፡ የሞተ ፡ ስለ ፡ መሰላቸው ፡ ደነገጡ ።
በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ጕድጓዱ ፡ ሔዱ ፡
በሕይወት ፡ እንዳለም ፡ ያውቁ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡
ጕድጓዱ ፡ ውስጥ ፡ ገመዶችን ፡ አወረዱና ፡
ገመዶቹን ፡ እንዲይዝ ፡ ወደርሱ ፡ ጮኹ ፡
እርሱም ፡ ገመዶችን ፡ ያዘ ፡ ስበው ፡ አወጡት ፡
አጥበውም ፡ ንጹሕ ፡ ልብስን ፡ አለበሱት ፡
በበቅሎም ፡ አስቀምጠው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡
መንግሥት፡አደረሱት።
፮፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ በሰማዕትነት ፡ ስለሞቱ ፡
ደናግል ፡ ሥጋ ፡ ጠየቀ ፡ እነርሱም ፡ የደናግሉ ፡
ሥጋቸው ፡ ወዳለበት ፡ መርተው ፡ አደረሱት ፡
የዱር ፡ አራዊትና ፡ አዕዋፍ ፡ ሳይበሏቸው ፡
በደኅና ፡ አገኛቸው ፡ ያማሩ ፡ ቦታዎችን ፡ አዘጋ
ጅተው ፡ በውስጣቸው ፡ ያኖሩዋቸው ፡ ዘንድ ፡
አዘዘ፡እንዳዘዛቸውም፡አደረጉ።
፯፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ንጉሡን ፡ ያድነው ፡ ዘንድ ፡
ሕዝቡ ፡ ለመኑት ፡ ንጉሡም ፡ ወዳለበት ፡ ዱር ፡
አደረሱት ፡ እርሱም ፡ ከክፉ ፡ ሥራህ ፡ ትመለሳ
ለህን ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ በጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ ታምናለህን ፡ አለው ። እሪያ ፡ የሆነ
ውም ፡ ንጉሥ ፡ አዎን ፡ እንደሚል ፡ ራሱን ፡
ዘንበል ፡ አድርጎ ፡ አመለከተ ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ርዮስ ፡ ወአውጽአ ፡ ለሰይጣን ፡ እምላዕለ ፡ ንጉሥ ፡ በአምሳለ ፡ ሐራውያ ፡ ወገብአ ፡ ልቡ ፡ ለንጉሥ ። ወአርአያሁኒ ፡ ከመ ፡ ቀዳሚ ፡ ወባሕቱ ፡ አትረፈ ፡ ውስተ ፡ እገሪሁ ፡ እምጽፍረ ፡ ሐራውያ ፡ ከመ ፡ ኢይትዓበይ ፡ ዳግመ ፡ ወይኩን ፡ ግሩረ ፡ ለፈጣሪሁ ፡ ወካዕበ ፡ ፈወሶሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ሰብአ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ወአውጽአ ፡ እምላዕሌሆሙ ፡ አጋንንተ ፡ ወሰደዶሙ ።

፰፡ ወእምዝ ፡ አስተጋብአሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ሰብአ ፡ አርማንያ ፡ ወሠርዐ ፡ ሎሙ ፡ ቀኖና ፡ ወአዘዘሙ ፡ ከመ ፡ ይጹሙ ፡ ፰ተ ፡ ዕለተ ፡ ወገበሩ ፡ በከመ ፡ አዘዞሙ ፡ ወነበሩ ፡ እንዘ ፡ ይሜህሮሙ ፡ ፍኖተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዓዲ ፡ መሀሮሙ ፡ ተሠግዎቶ ፡ ለመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወተወክፉ ፡ ትምህርቶ ፡ ዐቢዮሙ ፡ ወንኡሶሙ ፡ ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ምክንያተ ፡ ሃይማኖቶሙ ፡ ለሰብአ ፡ አርማንያ ።

፱፡ ወእምዝ ፡ ሰአልዎ ፡ ለቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ከመ ፡ ያጥምቆሙ ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ ወይቤሎሙ ፡ እስመ ፡ ኢኮንኩ ፡ አነ ፡ ካህነ ፡ ወኢይደልወኒ ፡ ባሕቱ ፡ ፈንዉ ፡ ለእካነ ፡ ኀበ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሮሜ ፡ ይፈኑ ፡ ለክሙ ፡ ካህነ ፡ ዘያጠምቀክሙ ። ወሶቤሃ ፡ ፈነዉ ፡ ላእካነ ፡ ምስሌሁ ፡ ኀበ ፡ አኖሬዎስ ፡ ንጉሥ ፡ ዘምስለ ፡ አምኃ ፡ ውኀበ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወአጠየቅዎሙ ፡ ከመ ፡ ሰብአ ፡ አርማንያ ፡ ተመይጡ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወተፈሥሐ ፡ ሰሚያሙ ፡ ንጉሥኒ ፡ ወሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሮሜ ፡ ወእምዝ ፡ ሤሞ ፡ ለቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ላዕለ ፡ ሀገረ ፡ አርማንያ ፡ ወፈነዎ ፡ በክብር ፡ ኀበ ፡ ድርጣድስ ፡ ንጉሥ ፡ ዘአርማንያ ።

፲፡ ወሶበ ፡ በጽሐ ፡ ቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ሀገረ ፡ አርማንያ ፡ ነሢአ፡ ሢመተ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ተፈሥሐ ፡ ቦቱ ፡ በእንተ ፡ ምጽአቱ ፡ ኀቤሆሙ፡ ውእቱኒ ፡ አጥመቆሙ ፡ለኵሎሙ ፡ ሰብአ ፡ አርማንያ ፡ ወሐነፀ ፡ ሎሙ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሠናይተ ፡ በስመ ፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ወእምድኅረ ፡ አጽንዖሙ ፡ በሃይማኖት ፡ ወፈጸሞ ፡ ሑረቶ ፡ ሠናየ ፡ አዕረፈ ፡ በሰላም ።

ቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ጸለየ ፡ ከንጉሡም ፡ ላይ ፡ በእሪያ ፡ አምሳል ፡ ሰያጣንን ፡ አስወጣው ። የንጉሡም ፡ አእምሮውና ፡ መልኩ ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ተመለሰለት ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ዳግመኛ ፡ እንዳይታይበይ፡ ከእግሩ ፡ ላይ ፡ የእሪያ ፡ ጥፍር ፡ አስቀረ ፡ ለፈጣሪውም ፡ ተገዢ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ዳግመኛም ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሰዎችን ፡ ሁሉንም ፡ አዳናቸው ፡ ከላያቸውም ፡ አጋንንትን፡አስወጥቶ፡ሰደዳቸው።

፰፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የአርማንያን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉንም ፡ ሰበሰባቸውና ፡ ሥርዓትን ፡ ሠራላቸው ፡ ስምንት ፡ ቀንም ፡ እንዲጾሙ ፡ አዘዛቸው ፡ እንዳዘዛቸውም ፡ አደረጉ ፡ የእግዚአርሔርንም ፡ሕግ ፡ እያስተማራቸው ፡ ኖሩ ። ዳግመኛም ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ መሆኑን ፡ አስተማራቸው ፡ ታላቆችም ፡ ታናሾችም ፡ ትምህርቱን ፡ ተቀበሉት ፡ ለአርማንያም ፡ ሰዎች ፡ ሃይማኖትን ፡ የመቀበላቸው ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ነው ።

፱፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የክርስትና ፡ ጥምቀትን ፡ ያጠምቃቸው ፡ ዘንድ ፡ ቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስን ፡ ለመኑት ፡ እርሱም ፡ እኔ ፡ ካህን ፡ ስለአልሆንኩ ፡ አይገባኝም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የሚያጠምቃችሁን ፡ ካህን ፡ ይልክላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ወደሮሜ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ መልእክተኞችን ፡ ላኩ ፡ አላቸው ። በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ አኖሬዎስና ፡ ወደ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ መልክተኞችን ፡ ልከው ፡ የአርማንያ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርጵንያ ተመለሱ ፡ አስረዱአቸው፡ ንጉሡም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱም ፡ ሰምተው ፡ ደስ ፡ አላቸው ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ የአርማንያ ፡ አገር ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስን ፡ ሾመው ፡ ወደ ፡ አርማንያን ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ድርጣድስም ፡ በክብር ፡ ላከው ።

፲፡ ቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስም ፡ ተሹሞ ፡ ወደ ፡ አርማንያ ፡ አገር ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ በመምጣቱ ፡ ደስ ፡ ተሰኙበት ፡ እርሱም ፡ የአርማንያን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉንም ፡ አጠመቃቸው ፡ በእመቤታችን ፡ በቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያምም ፡ ስም ፡ ያማረች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሠራላቸው ፡ በሃይማኖትም ፡ ከአጸናቸውና ፡ መልካም ፡ ጉዞውንም ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ በሰላም ፡ በፍቅር ፡ አረፈ ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፩፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፲፩፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምሥጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በዚህ ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ለዘላለሙ ፡ ትኑር ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለጎርጎርዮስ ፡ ዘተዓገሠ ፡ ሥቃየ ። በሌሊት ፡ ቊረ ፡ ወበመዓልት ፡ ዋዕየ ። ዓመታተ ፡ ዐሥርተ ፡ ወኃምስተ ፡ አመ ፡ ውስተ ፡ ግብ ፡ ተወድየ ። ወሰላም ፡ ለአረጊት ፡ ዘተልእከቶ ፡ ሠናየ ። እንዘ ፡ ትዌግር ፡ ሎቱ ፡ በኅቡእ ፡ ሲሳየ ።

፲፪፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለሉቃስ ፡ ዘዓምድ ፡ ወለአባ ፡ ይምላህ ፡ ወአባ ፡ ኤዎስጣቴዎስ ፡ ዘዓደወ ፡ ባሕረ ። በረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን

፲፪፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የሉቃስ ፡ ዘዓምድ ፡ የአባ ፡ ይምላህ ፡ ባሕርን ፡ በዓጽፉ ፡ የተሻገረ ፡ የአባ ፡ ኤዎስጣቴዎስ ፡ መታሰቢያቸው ፡ ነው ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለሉቃስ ፡ ዘፃመወ ፡ ፃማ ። በልብሰ ፡ ኀፂን ፡ ይትጋደል ፡ ወይትቃተል ፡ ምስለ ፡ መስቴማ ። መዋዕለ ፡ ጾሙ ፡ ስዱስ ፡ እስከ ፡ ይትፌጸማ ። ለዕርቅት ፡ ከርሡ ፡ እንዘ ፡ ይሠርዕ ፡ ዓቅማ ። በዕለተ ፡ ሰንበት ፡ ይሴሰይ ፡ አሐደ ፡ ጳኵሲማ ።

ሰላም ፡ ለከ ፡ ይምላህ ። መዝገበ ፡ ረድኤት ፡ ወንጽሕ ። ውስተ ፡ ቤተ ፡ ትፍሥሕት ፡ አብአኒ ፡ በስነ ፡ ጽድቅከ ፡ ብሩህ ። እምነ ፡ ኃጥአን ፡ እለ ፡ ከማየ ፡ በጊዜ ፡ ሐተታ ፡ ወፍትሕ ። አምሳለ ፡ ፈለግ ፡ ብዙኅ ፡ አመ ፡ ይደምፅ ፡ ላህ ።

* * *

፩፤ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፲ ወ ፯ ለታኅሣሥ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ ጌዴዎን ፡ አሐዱ ፡ እመሳፍንተ ፡ እስራኤል ፡ ወዝንቱ ፡ እምነገደ ፡ ምናሴ ፡ ወስመ ፡ አቡሁ ፡ ዮአስ ፡ ወአስተርአዮ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወሜሞ ፡ መስፍነ ፡ ላዕለ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ወአዘዞ ፡ ከመ ፡ ያንህል ፡ ምሥዋዓ ፡ ጣዖታት ፡ ወይግዝም ፡ ዕፀወ ፡ ወይሕንፅ ፡ ምሥዋዓ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወይሡዕ ፡ በውእቱ ፡ ዕፅ ፡ ዘሰበረ ፡ ወገብረ ፡ ኵሎ ፡ በከመ ፡ አዘዞ ።

፪፤ ወነጸሮ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይቤሎ ፡ ሑር ፡ በኃይልከ ፡ ወታድኅኖሙ ፡ ለእስራኤል ፡ እምእደ ፡ ምድያም ፡ ወናሁ ፡ ፈነውኩከ ።

፫፤ ወይቤ ፡ ጌዴዎን ፡ እመ ፡ ታድኅኖሙ ፡ ለእስራኤል ፡ በእዴየ ፡ በከመ ፡ ትቤ ፡ ናሁ ፡ አነ ፡ እሰፍሕ ፡ ፀምረ ፡ ብዝተ ፡ ውስተ ፡ ዐውድ ። ወእምከመ ፡ ወረደ ፡ ጠል ፡ ውስተ ፡ ፀምር ፡

* * *

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ታኅሣሥ ፡ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ከእስራኤል ፡ መሳፍንት ፡ አንዱ ፡ ጌዴዎን ፡ አረፈ ፡ ይህም ፡ ከነገደ ፡ ምናሴ ፡ የሆነ ፡ የአባቱ ፡ ስም ፡ ዮአስ ፡ ይባላል ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ የታዘዘ ፡ መልአክ ፡ ተገለጠለትና ፡ ለእስራኤል ፡ ምስፍና ፡ ሾመው። የጣዖታቱንም ፡ መሠዊያ ፡ እንዲያፈርስ ፡ ዛፎችንም ፡ እንዲቆርጥ ፡ አዘዘው ፡ መሠዊያም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሠርቶ ፡ በዚያ ፡ በሰበረው ፡ ዕንጨት ፡ እንዲሠዋ ፡ አዘዘው ፡ ሁሉንም ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረገ።

፪፤ እግዚአብሔር ፡ የላከው ፡ መልአክም ፡ ተመለከተው ፡ እስራኤልን ፡ ከምድያም ፡ እጅ ፡ ታድናቸዋለህና ፡ ከሠራዊትህ ፡ ጋር ፡ ሒድ ፡ እነሆ ፡ ላክሁህ ፡ አለው።

፫፤ ጌዴዎንም ፡ አድናቸዋለሁ ፡ እንዳልክ ፡ እስራኤልን ፡ በእጄ ፡ ታድናቸው ፡ እንደሆነ ፡ እነሆ ፡ እኔ ፡ በአደባባይ ፡ የተባዘተ ፡ ፀምርን ፡ እዘረጋለሁ። ጠል ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሳይወርድ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ባሕቲቱ ፡ ወኵሉ ፡ ምድር ፡ ይቡስ ፡ አአምር ፡
እንከ ፡ ከመ ፡ ታድኅኖሙ ፡ ለእስራኤል ፡
በእዴየ፡በከመ፡ትቤ፡ወኮነ፡ከማሁ።

፬፡ ወጌሠ ፡ ጌዴዎን ፡ በሣኒታ ፡ ወዐጸሮ ፡ ለውእቱ ፡
ፀምር ፡ ወወጽአ ፡ ማይ ፡ እምውእቱ ፡ ፀምር ፡
ምልአ፡ዐይገን።
፭፡ ወይቤሎ ፡ ጌዴዎን ፡ ለእግዚአብሐር ፡ ኢትት
መዓዕ ፡ በመዓትከ ፡ ላዕሌየ ፡ ወእንግርከ ፡ ካዕበ ፡
አሐተ ፡ ነገረ ፡ ፀምር ፡ ይኩን ፡ ይቡሰ ፡ እንተ ፡
ባሕቲቱ ፡ ወውስተ ፡ ኵሉ ፡ ምድር ፡ ይረድ ፡
ጠል። ወገብረ ፡ ከማሁ ፡ እግዚአብሐር ፡ በይ
እቲ፡ ሌሊት ፡ ወኮነ ፡ ይቡሰ ፡ ፀምር ፡ ባሕቲቱ ፡
ወውስተ፡ኵሉ፡ምድር፡ወረደ፡ጠል።
፮፡ወአጽንዖ፡ መንፈሰ፡እግዚአብሐር፡ለጌዴዎን፡
ወነፍሐ ፡ ቀርነ ፡ ወወውዐ ፡ አብያዜር ፡ በድ
ኅሬሁ ። ወፈነወ ፡ መልእክተ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡
ምናሴ ፡ ወአውየወ ፡ ውእቱኒ ፡ እምድኅሬሁ ፡
ወፈነወ፡መላእክተ፡ውስተ፡አሴር፡ወውስተ፡
ዛብሎን ፡ ወንፍታሌም ፡ ወዐርጉ ፡ ወተቀበ
ልዎሙ።

፯፡ ወጌሠ ፡ ጌዴዎን ፡ ወኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ዘምስሌሁ ፡
ወኀደሩ ፡ ውስተ ፡ ምድረ ፡ አሮኤድ ፡ ወትዕይ
ንቶሙ ፡ ለምድያም ፡ ወለአማሌቅ ፡ እመንገለ ፡
መስዕ፡እምሥዋዕ፡ዘእንበሬም፡ውስተ፡ቈላ።
፰፡ ወይቤሎ ፡ እግዚአብሐር ፡ ለጌዴዎን ፡ ብዙኀ ፡
ሕዝብ ፡ ዘምስሌከ ፡ ከመ ፡ ኢይክል ፡ አግብ
ኦቶሙ ፡ ለምድያም ፡ ውስተ ፡ እዴሆሙ ፡ ከመ ፡
ኢይትመክሁ ፡ እስራኤል ፡ ላዕሌየ ፡ ወኢይ
በሉ፡እዴነ፡አድኃነተነ።
፱፡ወይቤሎ፡እግዚአብሐር፡ለጌዴዎን፡ንግሮሙ፡
ለሕዝብ ፡ ወበሎሙ ፡ ዘይፈርህ ፡ እምኔከሙ ፡
ለይግባእ ፡ እምኀበ ፡ ሕዝብ ። ወተመይጡ ፡
እምድረ ፡ ገለዓድ ፡ ወገብኡ ፡ እምሕዝብ ፡ ፳ቱ ፡
እልፍ፡ወእስራ፡ምእት፡ወተርፉ፡እልፍ።

፲፡ ወይቤሎ ፡ እግዚአብሐር ፡ ለጌዴዎን ፡ ዓዲ ፡
ብዙኀ፡ሕዝብ፡አውርዶሙ፡ኀበ፡ማይ፡ወአመ
ክሮሙ ፡ ለከ ፡ በህየ ፡ ወእለ ፡ አነ ፡ እቤለከ ፡
እሙንቱ ፡ ይሑሩ ፡ ምስሌከ ፡ ወአውረዶሙ ፡
ኀበ፡ማይ፡ለሕዝብ።
፲፩፡ ወይቤሎ ፡ እግዚአብሐር ፡ ለጌዴዎን ፡ ኵሉ ፡
ዘሰትየ፡በልሳኑ፡እማይ፡ከመ፡ይሰቲ፡ከልብ፡

በፀምሩ፡ላይ፡ብቻ፡ቢወርድ፡አድናቸዋለሁ፡
እንዳልክ ፡ እስራኤልን ፡ በእጄ ፡ እንድታድ
ናቸው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ አውቃለሁ ፡ አለ ፡ እንዳ
ለውም፡ሆነ።
፬፡ ጌዴዎንም ፡ በማግሥቱ ፡ ማልዶ ፡ ሒዶ ፡ ያንን ፡
ጠመቀው ፡ ከዚያ ፡ ፀምር ፡ አንድ ፡ መንቀል
ሙሉ፡ውኃ፡ወጣ።
፭፡ ጌዴዎን ፡ እግዚአብሔርን ፡ በቍጣህ ፡ አትቆ
ጣኝ፡ዳግመኛ፡አንድ፡ጊዜ፡ልናገር፡በፀምር፡
ላይ ፡ ብቻ ፡ ሳይወርድ ፡ ጠል ፡ በምድር ፡ ሁሉ ፡
ላይ ፡ ይውረድ ፡ አለው ። እግዚአብሔርም ፡በዚ
ያች ፡ ሌሊት ፡ እንዳለው ፡ አደረገ ። ፀምሩ ፡
ብቻ ፡ ደረቅ ፡ ሁኖ ፡ ጠል ፡ በምድር ፡ ሁሉ ፡ ላይ
ወረደ።
፮፡ ጌዴዎንንም ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡
ረድኤት ፡ አጸናው ፡ ነጋሪትንም ፡ መታ ፡ አብያ
ዜርም ፡ በኋላው ፡ ሁኖ ፡ ደነፋ ። ወደ ፡ ነገደ ፡
ምናሴም ፡ ሁሉ ፡ መልክተኞችን ፡ ላከ ፡ እር
ሱም ፡ ከኋላው ፡ ሁኖ ፡ ደነፋ ፡ ወደ ፡ ነገደ ፡
አሴር ፡ ወደ ፡ ነገደ ፡ ዛብሎን ፡ ወደ ፡ ነገደ ፡
ንፍታሌምም ፡ መልእክተኞችን ፡ ላከ ፡ ወጥተ
ውም፡ተቀበሏቸው።
፯፡ጌዴዎንም፡ከርሱ፡ጋር፡ያሉ፡ወገኖቹም፡ሁሉ፡
ሔዱ፡አሮኤድ፡በሚባል፡አገርም፡ሰፈሩ፡የም
ድያምና፡የአማሌቅ፡ሠራዊትም፡በእንበሬም፡
ቆላ፡መሠዊያ፡ቀኝ፡ሰፈሩ።
፰፡ እግዚአብሔርም ፡ ጌዴዎንን ፡ እኛችን ፡ አዳነ
ችን ፡ ብለው ፡ እንዳይመኩብኝ ፡ የምድያምን ፡
ሰዎች ፡ በእጃቸው ፡ መጣል ፡ እንደማልችል ፡
ካንተ፡ጋር፡ያሉ፡ሕዝብ፡ብዙ፡ናቸው፡አለው።

፱፡ እግዚአብሔር ፡ ጌዴዎንን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡
ከእናንተ ፡ የሚፈራ ፡ የሚደነግጥ ፡ ሰው ፡ ከሕ
ዝቡ ፡ ተለይቶ ፡ ይመለስ ፡ ብለህ ፡ ለሕዝቡ ፡
ንገራቸው ። ሕዝቡም ፡ ከገለዓድ ፡ ተመለሱ ፡
ከሕዝቡም ፡ ሁለት ፡ እልፍ ፡ ከሁለት ፡ ሽህ ፡
ተመልሰው፡እልፍ፡ሰዎች፡ቀሩ።
፲፡ እግዚአብሔር ፡ ጌዴዎንን ፡ ገና ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡
አሉ ፡ ወደ ፡ ውኃ ፡ አውርደህ ፡ በዚያ ፡ ፈት
ናቸው ፡ እኔ ፡ ይሒዱ ፡ የምልህ ፡ ሰዎች ፡
እነሳቸው ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ ይሒዱ ፡ አለው ፡
ሕዝቡንም፡ወደ፡ውኃ፡አወረዳቸው።
፲፩፡ እግዚአብሔር ፡ ጌዴዎንን ፡ ውሻ ፡ በምላሱ ፡
ጠለፍ፡ጠለፍ፡አድርጎ፡እንዲጠጣ፡ከውኃው፡

www.ethiopianorthodox.org

ሚም ፡ ወጋውር ፡ ወተዝካሩ ፡ ለማርያም ፡ እኅተ፡ሙሴ።

፲፰፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም ሐረነ ፡ በጸሎተ ፡ ኵሎሙ ፡ ቅዱሳን ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም፡አሜን።

የሙሴ፡እኅት፡ማርያምም፡መታሰቢያቸው፡ ነው።

፲፰፤ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡ በቅዱሳን፡ሁሉ፡ጸሎት፡ይማረን፡ለዘላለሙ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለክሙ፡ዘማየ፡አእምሮ፡አፍላግ። ሐናንያ፡ወኵዚ፡ወሐርዋግ።ብፁዓን፡ኄራን፡መምህራነ፡ ሕግ።ሐውጹ፡ማኅበረነ፡ወባርኩነ፡በደርግ።እስመ፡በረከተ፡ለደቂቅ፡ይሁቡ፡አእሩግ።

* * *

፩፤ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፲ወ፯ ለታኅሣሥ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት፡ኮነ፡ፍልሰተ፡ሥጋሁ፡ለቅዱስ፡ሉቃስ፡ ዘዓምድ።

፪፤ ወውእቱ ፡ እምብሔረ ፡ ፋርስ ፡ ወኮነ ፡ ቀዳሚ ፡ መኰንነ ፡ ላዕለ ፡ ፪ት ፡ ሐራ ፡ ወእምዝ ፡ ኀደገ ፡ ሢመቶ ፡ ወለብሰ ፡ አልባሰ ፡ ምንኵስና ፡ ወኀደረ፡ ውስተ ፡ ደብር ፡ እምነ ፡ አድባራት ፡ ዘሀገረ ፡ ምሥራቅ ፡ ብዙኀ ፡ መዋዕለ ፡ እንዘ ፡ ይትጋደል ፡ ወሶበ ፡ ፈጸመ ፡ ግብረ ፡ ምንኵስና ፡ ወተጋድሎተ ፡ ወትሩፋተ ፡ ተሠይመ ፡ ቀሲስ ፡ በውስተ ፡ ውእቱ ፡ ደብር።

፫፤ ወበጊዜ ፡ ሢመቱ ፡ ለብሰ ፡ ልብሰ ፡ ኀፂን ፡ መጠነ፡ ንብረቱ ፡ በህየ ፡ ወእምይእቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ዘይጸውም ፡ ፯ መዋዕለ ፡ ወበዕለተ ፡ ሰንበተ፡ ክርስቲያን ፡ ይቄድስ ፡ ቍርባነ ፡ ወይትሜጦ፡ምሥጢራተ፡ቅድሳት፡ወእምድ ኅረዝ፡ይሲሰይ፡፩፡ጳኵሲማ፡ኀብስት፡ምስለ፡ ሐምል።

፬፤ ወእምድኅረዝ ፡ ዐርገ ፡ ላዕለ ፡ ዓምድ ፡ ወቆመ ፡ ዲቤሁ ፡ ፫ተ፡ ዓመተ ፡ ወሰምዐ ፡ ቃሎ ፡ ለመል አክ ፡ እንዘ ፡ ይጼውዖ ፡ በስሙ ፡ ወይኤዝዞ ፡ ከመ፡ ይረድ ፡ እመልዕልተ ፡ ውእቱ፡ ዓምድ ፡ ወአርአዮ ፡ መስቀለ ፡ ዘብርሃን፡ ወወረደ ፡ ወተ ለዎ ፡ ለውእቱ ፡ መስቀል ፡ ወመርሖ ፡ እስከ፡ አብጽሖ ፡ ውስተ ፡ ፩ደብር ፡ እምነ ፡ አድባራት ፡ ወነበረ፡ በህየ ፡ ወይመጽኡ፡ ኀቤሁ ፡ ኵሎሙ ፡ ሰብእ ፡ ወይትናዘዙ ፡ በትምህርቱ።

፭፤ ወእምዝ ፡ ኮነ ፡ አርማሜ ፡ ወወደየ ፡ ዕብነ ፡ ውስተ፡ አፉሁ ፡ ከመ ፡ ኢይትናገር ፡ ግሙራ ፡ ምስለ ፡ ሰብእ ፡ ወአዘዞ ፡ ካዕበ ፡ መልአክ ፡ ከመ ፡ ይሑር ፡ ኀበ ፡ ጽንፈ ፡ ሀገረ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡

* * *

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ታኅሣሥ ፡ ዐሥራ ፡ ሰባት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ የቅዱስ ፡ ሉቃስ ፡ ዘዓምድ ፡ የሥጋው ፡ ፍልሰት ፡ ሆነ።

፪፤ እርሱም ፡ ከፋርስ ፡ አገር ፡ ነው ፡ በመጀመሪያ ፡ በመቶ ፡ ጭፍራ ፡ ላይ ፡ መኰንን ፡ ሁኖ ፡ ተሹሞ ፡ ነበር ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሹመቱን ፡ ትቶ ፡ የምን ኵስና ፡ ልብስን ፡ ለበሰ ። በምሥራቅ ፡ አገር ፡ ካሉ ፡ ገዳማትም ፡ በአንዱ ፡ ገዳም ፡ እየተጋ ደለ ፡ ብዙ ፡ ወራት ፡ ኖረ ፡ የምንኵስናንም ፡ ሥራ ፡ ተጋድሎንና ፡ ትሩፋትንም ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ ገዳም ፡ ውስጥ ፡ ቅስና ፡ ተሾመ።

፫፤ በተሾመም ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ በኖረበት ፡ መጠን ፡ የብረት ፡ ልብስን ፡ ለበሰ ፡ ከዚያቺም ፡ ወዲህ ፡ ስድስት ፡ ቀን ፡ የሚጾም ፡ ሆነ ፡ በክርስቲያን ፡ ሰንበት ፡ ቀንም ፡ ቀድሶ ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ይቀበላል ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከጎመን ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ የዳቦ ፡ ለከት ፡ ይመገባል።

፬፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከዓምድ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ በላዩ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ቆመ ፡ በስሙም ፡ ሲጠራውና ፡ ከዚያም ፡ ዓምድ ፡ ላይ ፡ እንዲወርድ ፡ ሲያዝ ዘው ፡ የመልአክን ፡ ቃል ፡ ሰማ ፡ የብርሃን ፡ መስ ቀልንም ፡ አሳየው ፡ ወርዶም ፡ ያን ፡ መስቀል ፡ ተከተለው ፡ ከገዳማት ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ገዳም ፡ እስከ ፡ አደረሰውም ፡ ድረስ ፡ መራው ፡ በዚያም ፡ የሚኖር ፡ ሆነ ፡ ሰዎችም ፡ ሁሉ ፡ ወደርሱ ፡ እየመጡ ፡ በትምህርቱ ፡ ይረጋጉ ፡ ነበር።

፭፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የማይናገር ፡ ሆነ ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ ከቶ ፡ እንዳይናገር ፡ ከአፉ ፡ ውስጥ ፡ ደንጊያ ፡ ጐረሰ ፡ ዳግመኛም ፡ ወደ ቍስጥንጥንያ ፡ አገር ፡ ዳርቻ ፡ ይሔድ ፡ ዘንድ ፡ መልአክ ፡ አዘዘው ፡

www.ethiopianorthodox.org

፩፤ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፲ወ፱ ፡ ለታኅሣሥ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካረ ፡ በዓሉ ፡ ለመልአክ ፡ ክቡር ፡ ገብርኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ ወውእቱ ፡ ዘባልሖሙ ፡ ለአናንያ ፡ ወአዛርያ ፡ ወሚሳኤል ፡ አመ ፡ ወደይዎሙ ፡ ውስተ ፡ እቶነ ፡ እሳት ፡ ውስተ፡ሀገረ፡ባቢሎን።

፪፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ፡በትንብልናሁ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ታኅሣሥ ፡ ዐሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ የመልአኩ ፡ የቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ የበዓሉ ፡ መታሰቢያ፡ነው፡እርሱም፡በባቢሎን፡አገር፡ ከነደደ ፡ እሳት ፡ ውስጥ ፡ በጨመሩአቸው ፡ ጊዜ፡ አናንያን ፡ አዛርያን ፡ ሚሳኤልን፡ ያዳናቸው፡ነው።

፪፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በአማላጅነቱ፡ያምረን፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡እብል፡ ኪያከ፡ክቡረ። ለስመ፡ዚአከ፡ገብርኤል፡እንዘ፡አነሥእ፡መዝሙረ።እግዚአብሔር፡ መንበሮ፡ሰማየ፡ሰማያት፡ዘገብረ። ይትመሰል፡በአርአያከ፡አመ፡ጊዜ፡ሐወጸ፡ምድረ።እምነ፡መላእክት፡ ኵሉ፡ስነከ፡አፍቀረ።

፫፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ ክቡር ፡ አባ ፡ ዮሐንስ፡ ኤጲስቆጶስ፡ዘሀገረ፡ቡርልስ፡ዘኮነ፡ እምዘመዶሙ፡ለካህናት።

፬፤ ወለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ አበዊሁኒ ፡ ክቡራን ፡ ወእሙንቱ፡ይሁቡ፡እምንዋዮሙ፡ለነዳያን፡ ወለምስኪናን ፡ ወሶበ ፡ አዕረፉ ፡ አበዊሁ ፡ ነሥአ ፡ ንዋየ ፡ ዘኀደጉ ፡ ሎቱ ፡ ሐነፀ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወሐነፀ ፡ ካዕበ ፡ ቤተ ፡ ነግድ ፡ ወአስተጋብአ ፡ ውስቴቱ ፡ ፈላስያነ ፡ ወድውያነ፡ወኮነ፡ዘይትለአኮሙ፡ወያቄርብ፡ሎሙ፡ ኵሎ፡ዘይፈቅዱ።

፭፤ ወበውእቱ ፡ መዋዕል ፡ መጽአ ፡ ኀቤሁ ፡ ፩ መነኮስ ፡ ወደሰ ፡ ሎቱ ፡ ግብረ ፡ ምንኵስና ፡ ወከሠተ ፡ ሎቱ ፡ ክብሮ ፡ ወእምድኅረ ፡ ሖረ ፡ ውእቱ ፡ መነኮስ ፡ ወሀበ ፡ ኵሎ ፡ ንዋዮ ፡ ለነዳያን።ወሖረ፡ኀበ፡ገዳመ፡አስቄጥስ፡በመዋዕሊሁ ፡ ለአባ ፡ ዳንኤል ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ ዘገዳመ ፡ አስቄጥስ ፡ ወመንኰሰ ፡ በኀቤሁ ፡ ወተጋደለ፡ገድለ፡ዐቢየ፡እንዘ፡ይነብር፡ውስተ፡ ጸማዕት ፡ ባሕቲቶ ። ወቀንአ ፡ ላዕሌሁ ፡ ሰይጣናት ፡ በእንተ ፡ ሠናይ ፡ ገድሉ ፡ ወቀሠፍዎ ፡ መቅሠፍተ ፡ ዐቢየ ፡ እስከ ፡ ነበረ ፡ ብዙኀ ፡ መዋዕለ፡እንዘ፡ይደዊ።

፮፤ ወእምዝ፡ፈወሶ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወረሰዮ ፡ ጽኑአ ፡ ወኃያለ ፡ ወሞዖሙ፡ለሰይጣናት፡ወበሥምረቱ፡ለእግዚአብሔር ፡ ተሠይመ ፡ ኤጲስቆጶሰ ፡ ላዕለ ፡

፫፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ ከካህናት ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ የሀገረ ፡ ቡርልስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ቅዱስ ፡ አባት ፡ አባ ፡ ዮሐንስ፡ዐረፈ።

፬፤ የዚህም ፡ ቅዱስ ፡ ወላጆቹ ፡ የከበሩ ፡ ናቸው ፡ እነርሱም ፡ ከገንዘባቸው ፡ ለድኆችና ፡ ለችግረኞች ፡ ይሰጡ ፡ ነበር ፡ ወላጆቹም ፡ በአረፉ ፡ ጊዜ፡የተዉለትን፡ገንዘብ፡ወስዶ፡ቤተ፡ክርስቲያን ሠራ፡ዳግመኛም፡የእንግዳ፡ቤት፡ሠራ በውስጡም ፡ መጻተኞችንና ፡ በሽተኞችን ፡ ሰብስቦ ፡ የሚያገለግላቸው ፡ ሆነ ፡ የሚሹትንም፡ሁሉ፡ያቀርብላቸዋል።

፭፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ ወደርሱ ፡ አንድ ፡ መነኵሴ ፡ መጣ ፡ የምንኵስናንም ፡ ሥራ ፡ አመሰገነለት ፡ ክብሩንም፡ገለጠለት፡ያ፡መነኵሴም፡ከሔደ፡ በኋላ፡ገንዘቡን፡ሁሉ፡ለድኆች፡ሰጥቶ፡አባ፡ ዳንኤል ፡ ለአስቄጥስ ፡ ገዳም ፡ አበ፡ ምኔት ፡ ሁኖ ፡ በነበረበት ፡ ወራት ፡ ወደ ፡ አስቄጥስ ፡ ሒዶ ፡ በአባ ፡ ዳንኤል ፡ ዘንድ ፡ መነኰሰ ፡ በዋሻ ፡ ውስጥም ፡ ብቻውን ፡ ሁኖ ፡ ታላቅ ፡ ተጋድሎን፡ተጋደለ። ስለ፡መልካም፡ተጋድሎውም፡ሰይጣናት፡ቀኑበት፡ብዙ፡ዘመንም፡ ታሞ ፡ ከኖረ ፡ በኋላ ፡ በደዌ ፡ መቅሠፍት ፡ ቀሠፉት።

፮፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ፈወሰውና ፡ ኃይለኛ ፡ ጽኑዕ ፡ አደረገው ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ፈቃድ፡ቡርልስ፡በሚባል፡አገር፡ላይ፡ኤጲ

www.ethiopianorthodox.org

ሀገረ፡ቡርልስ። ወኮነ፡በመዋዕሊሁ፡ኑፋቄ፡
ብዙኅ ፡ ውስተ ፡ አህጉር ፡ ወፃመወ ፡ ፃማ ፡
ብዙኀ፡ከመ፡ይምላሕ፡ክርዳደ፡እማዕከለ፡
ሥርናይ፡እስመ፡ሀሎ፡፮ ብእሲ፡ዘእምላዕ
ላይ ፡ ግብጽ ፡ ዘይትናገር ፡ ነገረ ፡ ብዙኀ ፡
ወይብል ሚካኤል፡ሊቀ፡መላእክት፡ይከ
ሥት ፡ ሊተ ፡ ምሥጢረ ፡ ወውእቱ ፡ አስሐ
ቶሙ ፡ ለብዙኃን ፡ ሰብእ ፡ ወሶበ ፡ አእመረ ፡
ዘንተ፡አዘዘ፡የአኀዝዎ፡ወይቅሥፍዎ፡ወአ
ምኑ፡ስሕተቶ፡ወሰደድዎ፡እምሀገር።

፯፤ ወሀሎ፡ካልዕኒ፡ዘይብል፡እስመ፡ዕንባቆም፡
ነቢይ፡ያስተርኢ፡ሊተ፡ወይከሥት፡ምሥ
ጢራተ፡ብዙኃተ፡ወተለውዎ፡ብዙኃን፡ለው
እቱኒ፡ሰደዶ፡ወሠዓረ፡ትምህርቶ፡ወመጻ
ሕፍቲሁ፡ሠጠጠ፡ወሜጠሙ፡ለኑፋቃን፡
ውስተ፡ሃይማኖት፡ርትዕት።
፰፤ ወውእቱ፡አባ፡ዮሐንስ፡ሶበ፡ይቄድስ፡ቅዳሴ፡
ከመ፡ያዕርግ፡ቍርባነ፡ይከውን፡ገጹ፡እሳተ፤
ወሥጋሁኒ፡ከመ፡ዘወጽአ፡እማዕከለ፡እቶን፡
ወይውኅዝ፡አንብዑ፡ከመ፡ዝናም፤እስመ፡
ይኔጽር፡ገሀደ፡ሠራዊተ፡መላእክት፡በዐ
ውደ፡ምሥዋዕ።
፱፤ ወሶበ፡ይቄድስ፡፫ተ፡ቅዳሴያተ፡በጊዜ፡ፈትቶ፡
ወሶበሂ፡ያመዓትብ፡ዲበ፡ጽዋዕ፡እዴሁ፡
ይረክቦ፡ለጽዋዕ፡ንዱደ፡ከመ፡አፍሐመ፡
እሳት።
፲፤ ወእምዝ፡በመዋዕሊሁ፡ተንሥኡ፡ሰብእ፡
እኩያን፡እምድኅረ፡በልኡ፡እለ፡ይቄርቡ፡
ክልኤተ፡ጊዜያተ፡በዋሕድ፡ዕለት፡ለእሉኒ፡
መሀሮሙ፡ወገሠጾሙ፡ወኢሰምዕዎ፡ወአው
ገዞሙ፡ካዕበ፡ወረገሞሙ፡ወኢተመይጡ።
ወሶበ፡ኢተመይጡ፡ሰአሎ፡ለእግዚእነ፡በእን
ቲአሆሙ፡ወወረደ፡እሳት፡ወአውዓዮ፡
ለሊቆሙ፡ወእለ፡ተርፉ፡ርእዮሙ፡ዘንተ፡
ፈርሁ፡ፈድፋደ፡ወነስሑ፡ወተመይጡ፡
ውስተ፡ሃይማኖት፡ርትዕት።
፲፩፤ ወእምዝ፡ሶበ፡ፈቀደ እግዚአብሔር፡ከመ፡
ያዕርፎ፡እምፃማ፡ዝንቱ፡ዓለም፡ኃላፊ፡
ለአኮሙ፡ኀቤሁ፡ለቅዱሳን፡አባ፡እንጦንስ፡
ወአባ፡መቃርስ፡ወእሉ፡አጠየቅዎ፡ከመ፡
በጽሐ፡ዕረፍቱ፡ወአስተጋብኦሙ፡ለሕዝቡ፡
ወአዘዞሙ፡ከመ፡ይዕቀቡ፡ሕገ፡ወሥርዓተ፡

ስቆጶስነት፡ተሾመ፡በዘመኑም፡በሀገሮች፡
ውስጥ፡ብዙ፡ኑፋቄ፡ነበረ፡እርሱም፡እንክር
ዳዱን፡ከሥንዴ፡መካከል፡ይነቅል፡ዘንድ፡
ብዙ፡ድካምን፡ደከመ፡ከላይኛው፡ግብጽ፡
የሆነ፡አንድ፡ሰው፡ነበረ፡ብዙ፡ነገርንም፡
ይቀባጥር፡ነበር፡የመላእክት፡አለቃ፡ሚካ
ኤል፡ምሥጢር፡ይገልጥልኛል፡በማለት፡
እርሱ፡ብዙ፡ሰዎችን፡አሳታቸው፡ይህንንም፡
በአወቀ፡ጊዜ፡ይዘው፡ይገርፉት፡ዘንድ፡
አዘዘ፡ስሕተቱንም፡አመነ፡ከሀገርም፡አሳደ
ዱት።
፯፤ ነቢይ፡ዕንባቆም፡ይታየኛል፡ብዙ፡ምሥጢራ
ትንም፡ይገልጥልኛል፡የሚል፡ሌላ፡ሰው፡
ነበረ፡ብዙዎችም፡ተከተሉት፡እርሱንም፡
አሳደደው፡ትምህርቱንም፡አጠፋ፡መጻሕፍ
ቱንም፡ቀደደ፡የሳቱትንም፡ወደ፡ቀናች፡
ሃይማኖት፡መለሳቸው።
፰፤ ይህ፡አባ፡ዮሐንስም፡መሥዋዕትን፡ለማሳረግ፡
በሚቀድስ፡ጊዜ፡ፊቱ፡እሳት፡ይሆናል፡
ሥጋውም፡ከእሳት፡ማንደጃ፡ውስጥ፡እንደ
ወጣ፡ይሆናል፡ዕንባውም፡እንደ፡ዝናብ፡
ይዘንባል፡የመላእክትን፡ሠራዊት፡በመሠ
ዊያው፡ዙሪያ፡በግልጥ፡ያያቸዋልና።
፱፤ ኅብስቱ፡በሚፈተት፡ጊዜ፡ሦስቱን፡የመፈ
ተቻ፡ምስጋናዎች፡አንብቦ፡ጽዋውን፡
ሲባርከው፡እንደ፡ፍም፡የጋለ፡ሁኖ፡ጽዋ
ውን፡ያገኘዋል።
፲፤ ከዚህም፡በኋላ፡በዘመኑ፡በቀን፡ከበሉ፡
በኋላ፡በአንድ፡ቀን፡ሁለተኛ፡የሚቆርቡ፡
ክፉዎች፡ሰዎች፡ተነሡ፡አስተማራቸው፡
ገሠጻቸውም፡ግን፡አልተመለሱም፡ዳግመ
ኛም፡አወገዛቸው፡ባልተመለሱም፡ጊዜ፡ስለ
እሳቸው፡ጌታን፡ለመነው፡እሳትም፡ከሰማይ፡
ወርዶ፡አለቃቸውን፡አቃጠለው፡የቀሩትም፡
ይህን፡አይተው፡እጅግ፡ፈሩ፡ተጸጽተውም፡
ወደ፡ቀናች፡ሃይማኖት፡ተመለሱ።

፲፩፤ ከዚህም፡በኋላ፡ከዚህ፡ከኃላፊው፡ዓለም፡እግ
ዚአብሔር፡ሊአሳርፈው፡በወደደ፡ጊዜ፡
ቅዱሳን፡አባ፡እንጦንስንና፡አባ፡መቃርስን፡
ወደርሱ፡ላካቸው፡እነርሱም፡ዕረፍቱ፡እንደ፡
ደረሰ፡አስረዱት፡ሕዝቡንም፡ሰብስቦ፡ሕግና፡
ሥርዓትን፡እንዲጠብቁ፡እርስ፡በርሳቸውም፡

www.ethiopianorthodox.org

ወከመ ፡ ይትፋቀሩ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ወይጽንዑ ፡ ውስተ ፡ ሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ወእምዝ ፡ ሰከበ፡ዲበ፡ምስካቡ፡ወመጠወ፡ነፍሶ፡ውስተ፡እደ፡እግዚአብሔር።

፲፪፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ወበረከቱ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ይፋቀሩ ፡ ዘንድ ፡ በቀናች ፡ ሃይማኖትም ፡ እንዲጸኑ፡አዘዛቸው፡ከዚህም፡በኋላ፡በመኝታው፡ላይ ፡ ጋደም ፡ ብሎ ፡ ነፍሱን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ፡ሰጠ።

፲፪፡ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡በዚህ ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለዮሐንስ፡እንተ፡ፃመወ፡ፈድፋደ።ከመ፡ይምላሕ፡ነግሀ፡እማዕከለ፡ሥርናይ፡ክርዳደ።ዝንቱ፡
ካህን፡ተመሊዖ፡ረዓደ።በጊዜ፡ቅዳሴ፡እንዘ፡ያመዓትብ፡እደ።በአምሳለ፡እሳት፡ይረክቦ፡ለጽዋዕ፡ንዱደ።

* * *

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ፡አመ፡፳ሁ፡ለታኅሣሥ፡በዛቲ፡ዕለት፡አዕረፈ፡ሐጌ፡ነቢይ፡እምውሉደ፡አሮን፡ዘእምነገደ፡ሌዊ።

፪፡ ወውእቱ ፡ እም ፲ወ፪ቱ ፡ ደቂቀ ፡ ነቢያት ፡ ወሶበ ፡ ፄወዋ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ተፄወዉ ፡ አበዊሁ ፡ ለዝንቱ ፡ ጻድቅ ፡ ነቢይ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ለደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ ባቢሎን ፡ ወሶበ ፡ ነገሠ ፡ ኮርዝ ፡ ዘይሰመይ ፡ ዳርዮስ ፡ ተነበየ ፡ ዝንቱ ፡ ነቢይ ፡ በዳግም ፡ ዓመተ፡መንግሥቱ፡ለኮርዝ።

፫፡ ወሶበ ፡ ፈነዎሙ ፡ ኮርዝ ፡ ለደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ይእትዉ ፡ ብሔሮሙ ፡ ወእሙንቱ ፡ አቲዎሙ፡ ሶበ ፡ ተሀየዩ ፡ ሐኒፀ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ገሠጾሙ ፡ ለሕዝቡ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ የኀድሩ ፡ ውስተ ፡ አብያት ፡ ሠናያት ፡ ወሥርግዋት ፡ ወይቤሎሙ ፡ ከመዝ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ ፡ እስመ ፡ ቤትየሰ ፡ ምዝቡር ፡ ወአንትሙሰ ፡ ታጸንዑ ፡ አብያቲክሙ ፡ ኵልክሙ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ታቀውም ፡ ሰማይ ፡ ዝናመ ፡ እምላዕሉ፡ ወምድርኒ፡ ኢትሁብ፡ፍሬሃ።

፬፡ ወሰምዑ ፡ ጸድቃኒሆሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ወፈርሁ ፡ ፈድፋደ፡ወአኀዙ፡ይሕንፁ፡ቤተ፡መቅደሱ፡ለእግዚአብሔር ፡ በከመ ፡ ይደሉ ፡ ወሐይወ ፡ ዝንቱ ፡ ነቢይ ፡ ጻድቅ ፡ መጠነ ፡ ፸፡ ዓመት ፡ ወመዋዕለ፡ትንቢቱኒ፡እምቅድመ፡ምጽአቱ፡ለክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ በ፬፻ ወ፴ ዓመት፡ወእምዝ፡አዕረፈ፡በሰላም።

* * *

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ታኅሣሥ ፡ ሃያ ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ከሌዊ ፡ ነገድ ፡ ከአሮን ፡ ትውልድ፡የሆነ፡ነቢይ፡ሐጌ፡አረፈ።

፪፡ እርሱም ፡ ከዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ደቂቀ ፡ ነቢያት ፡ አንዱ፡ነው፡ናቡከደነጾርም፡የኢየሩሳሌምን፡ሕዝብ፡በማረከ፡ጊዜ፡የዚህ፡ጻድቅ፡ነቢይ፡ወላጆች ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ አገር ፡ ተማርከው ፡ ሔዱ ፡ ዳርዮስ ፡ የተባለውም ፡ ኮርዝ ፡ በነገሠ ፡ ጊዜ ፡ በሁለተኛው ፡ ዘመነ ፡ መንግሥቱ ፡ ይህ ፡ ነቢይ ፡ ትንቢት፡ተናገረ።

፫፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ ኮርዝ ፡ ዳርዮስ ፡ በአሰናበታቸው፡ጊዜ፡እነርሱም፡ከገቡ፡በኋላ፡ቤተ፡መቅደስን፡ከመሥራት፡ቸለል፡በአሉ፡ጊዜ፡እነርሱ፡ግን፡በአማሩና፡በተሸለሙ፡ቤቶች፡ውስጥ ፡ ይኖሩ ፡ ነበርና ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ። ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ የኔ ፡ ቤት ፡ ፈርሷል ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ ሁላችሁም ፡ ቤታችሁን ፡ ታጸናላችሁ ፡ አላቸው ። ስለዚህ ፡ ከምድር ፡ በላይ ፡ ያለች ፡ ሰማይ ፡ ዝናም ፡ ለዘር፡ ትነሣለች ፡ ምድርም ፡ ፍሬዋን፡አትሰጥም፡አላቸው።

፬፡ ከሕዝቡም ፡ ደጋጎቻቸው ፡ ሰምተው ፡ እጅግ ፡ ፈሩ፡የእግዚአብሔርንም፡መመስገኛ፡ቤት፡እንደሚገባ ፡ መሥራት ፡ ጀመሩ ። ይህም ፡ ጻድቅ፡ነቢይ፡ሰባ፡ዓመት፡ያህል፡ኖረ፡የትንቢቱም፡ወራት፡ክብር፡ይግባውና፡ክርስቶስ፡ከመምጣቱ ፡ በፊት ፡ በአራት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በኋላም ፡ በሰላም ፡ በፍቅር፡አረፈ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፩፤ ወእምዝ፡ተፈልጠ፡ቅዱስ፡ በርናባስ፡እምነ፡ ጳውሎስ ፡ እምድኅረ ፡ መሀሩ ፡ ብዙኀ ፡ አህጉረ፡ ወነሥአ ፡ ለማርቆስ ፡ ምስሌሁ ፡ ወሖረ ፡ ውስተ ፡ ቆጵሮስ ፡ ወሰበከ ፡ በህየ ፡ ወሜጠሙ ፡ ለብዙኃን ፡ ውስተ ፡ አሚነ፡እግ ዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሎቱ፡ ስብሐት፡ ወአጥመቆሙ፡ጥምቀተ፡ክርስትና።

፲፪፤ ወቀንዐ ፡ ላዕሌሁ ፡ አይሁድ ፡ እለ ፡ ሀገረ ፡ ቆጵሮስ፡ወአስተዋደይዎ፡ኀበ፡መኳንንት፡ ወአኀዝዎ፡ወቀሠፍዎ፡መቅሠፍተ፡ጽኑዐ፡ ወማሕመሜ፡ ወእምዝ፡ ወገርዎ፡ በአዕባን፡ ወነሥእዎ፡ካዕበ፡ወወደይዎ፡ውስተ፡እሳት ወፈጸመ፡ስምዖ፡ወማርቆስ፡ ሐዋርያ፡ ሀሎ፡ ምስሌሁ፡ ባሕቱ፡ አትረፎ፡ እግዚአብሔር፡ ወዐቀቦ ፡ ወውእቱ፡ አውጽአ፡ ለበርናባስ፡ ብፁዕ፡እምውስተ፡እሳት፡ወኢለከፎ፡እሳት፡ ግሙራ፡ለሥጋሁ፡ወገነዞ፡በአልባስ፡ሠና ያን፡ወፆሮ፡ ወአንበሮ፡ ውስተ፡ በዓት፡ ዘአፍአ፡ሀገረ፡ቆጵሮስ።

፲፫፤ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፥ኪያነኒ፡ይምሐ ረነ፡በጸሎቱ፡ለዝንቱ፡ሐዋርያ፡ወበረከቱ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፲፩፤ ከዚያም፡ብዙ፡ሀገሮችን፡ከአስተማሩ፡በኋላ ቅዱስ ፡ በርናባስ ፡ ከቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ተለይቶ ፡ ማርቆስን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ቆጵሮስ ፡ ሔደ ፡ በዚያም ፡ አስተማረ ፡ ብዙዎችን ፡ ክብር፡ይግባውና፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስ ቶስን ፡ ወደ ፡ ማመን ፡ መለሳቸውና ፡ የክር ስትና፡ጥምቀትን፡አጠመቃቸው።

፲፪፤ በቆጵሮስ ፡ አገር ፡ የሚኖሩ ፡ አይሁድም ፡ ቀኑበት፡በመኳንንትም፡ዘነድ፡ወነጀሉት፡ በእግር፡ብረትም፡አሥረው፡ጽኑ፡ግርፋትን ገረፉት፡ከዚህም፡በኋላ፡በደንጊያ፡ወገሩት ዳግመኛም፡ወስደው፡ከእሳት፡ጨመሩት፡ ምስክርነቱንም፡ፈጸመ፡ማርቆስም፡ከርሱ፡ ጋር ፡ አለ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠብቆ ፡ አተረፈው ። እርሱም ፡ ቅዱስ ፡ በርናባስን ፡ ከእሳት ፡ ውስጥ ፡ አወጣው ፡ ሥጋውንም ፡ እሳት ፡ ከቶ ፡ አልነካውም ፡ በአማሩ ፡ ልብሶችም ፡ ገነዘውና ፡ ተሸክሞ ፡ ወስዶ ፡ ከቆጵሮስ ፡ ከተማ ፡ ውጭ ፡ በዋሻ ፡ ውስጥ ፡ አኖረው።

፲፫፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ ንም፡ በዚህ ፡ ሐዋርያ ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለበርናባስ ፡ በማእሠረ ፡ ጌጋይ ፡ ዘኢተእኅዘ ። ከመ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አዘዘ ። ሥርዓተ ፡ ፈጺሞ ፡ ወመልእክተ ፡ ቃሉ ፡ አዚዘ ። በዋዕየ ፡ እሳት ፡ ሶበ ፡ እምዓለም ፡ ግዕዘ ። ለወንጌላዊ ፡ ማርቆስ ፡ በእዴ፡ተገንዘ።

፲፬፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ አስተርእዮተ ፡ መድኃ ኒነ፡ በአምሳለ ፡ ኖላዊ ፡ ወሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፲፬፤ በዚችም፡ቀን፡በበግ፡እረኛ፡አምሳል፡መድኃ ኒታችን ፡ የተገለጸበት ፡ ነው ፡ ለእርሱም ፡ ምስጋና፡ይሁን፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለርደትከ ፡ ዘእምቅድመ ፡ ዓለም ፡ ሀላዊ ። ነበልባለ ፡ እሳት ፡ ውዑይ ፡ ለተዓጽፎ ፡ አባል ፡ ምድራዊ ። ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወልደ ፡ አብ ፡ መለኮታዊ ። ይሴፈውከ ፡ መርዔትከ ፡ ለዘተዓቅብ ፡ ኖላዊ ። ትቤዝዎሙ፡እምአርዌ፡ነዓዊ።

ሰላም ፡ ለኖላዊ ፡ አልቦ ፡ ዘይመስሎ ። ዘመጽአ ፡ ይእዜ ፡ ወእምቅድመ ፡ ዓለም ፡ ዘሀሎ ። መራዕየ ፡ ይዕቀብ፡እሙስና፡ወእምተሀጕሎ።መንገለ፡ወፈረ፡ያወፍር፡መትሎ።አባግዕኒ፡ይሰምዓ፡ቃሎ።

* * *

፩፤ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፳ወ ፪ ለታኅሣሥ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት፡ ተዝካረ ፡ በዓሉ ፡ ለመልአክ ፡ ክቡር ፡

* * *

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ታኅሣሥ ፡ ሃያ ፡ ሁለት፡ በዚች ፡ ቀን ፡ የከበረ ፡ መልአክ ፡ የመላ

www.ethiopianorthodox.org

ገብርኤል፡ሊቀ፡መላእክት፡ወሕንፀተ፡ቤተ፡
ክርስቲያኑ፡በሀገረ፡ዳናህ፡ወአርአየ፡ባቲ፡
ተአምራተ፡ወቅዳሴሃ፡በዛቲ፡ዕለት፡በከመ፡
ስምዐ፡ኮነ፡አርኬላዎስ፡ኤጲስቆጶስ፡ዘይ
እቲ፡ሀገር።

፪፡ ወዝንቱ፡መልአክ፡ዘተአምነ፡በእንተ፡
ምሥጢረ፡ሥጋዌሁ፡ለወልደ፡እግዚአብ
ሔር፡ወተፈነወ፡ኀበ፡እግዝእትነ፡ቅድስት፡
ድንግል፡ማርያም፡ወይቤላ፡ተፈሥሒ፡
ፍሥሕት፡ኦ፡ምልእተ፡ጸጋ፡እግዚአብሔር፡
ምስሌኪ፡ቡርክት፡አንቲ፡እምአንስት።

፫፡ ወውእቱ፡ዘአብሠሮ፡ለዘካርያስ፡ካህን፡
በእንተ፡ልደቱ፡ለዮሐንስ፡መጥምቅ፡እስመ፡
ዝንቱ፡መልአክ፡ጥቀ፡ዐቢይ፡ወክቡር፡
ወኅሩይ፡ወይደልወነ፡ከመ፡ንግበር፡ተዝካሮ፡
አንጺሐነ፡ልበነ፡ወእንዘ፡ንስእል፡ኀበ፡
ዝንቱ፡መልአክ፡ክቡር፡ከመ፡ይተንብል፡በእ
ንቲአነ፡ኀበ፡እግዚአብሔር።

፬፡ ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ኪያነኒ፡ይምሐ
ረነ፡በትንብልናሁ፡ለዝንቱ፡መልአክ፡
ክቡር፡በረከቱ፡ወረድኤቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡
ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

እክት፡አለቃ፡የገብርኤል፡የበዓሉ፡መታ
ሰቢያ፡ዳናህ፡በሚባል፡አገርም፡ቤተ፡ክርስ
ቲያኑ፡የተሠራችበት፡ተአምራትም፡ያሳየ
በትና፡በዚች፡ቀን፡ቤተ፡ክርስቲያኒቱ፡የከበ
ረችበት፡ነው፡የዚያች፡ሀገር፡ኤጲስቆጶስ፡
አርኬላዎስም፡ምስክር፡የሆነበት፡ነው።

፪፡ ይህም፡መልአክ፡ስለ፡ወልደ፡እግዚአ
ብሔር፡ሰው፡መሆን፡ምሥጢር፡የታመነ፡
ሆኖ፡ወደ፡እመቤታችን፡ቅድስት፡ድንግል፡
ማርያም፡የተላከ፡የደስታ፡መገኛ፡ደስ፡
ይበልሽ፡ጸጋን፡የተመላሽ፡ሆይ፡እግዚአ
ብሔር፡ካንቺ፡ጋር፡ነው፡አንቺም፡ከሴቶች፡
ተለይተሽ፡የተባረክሽ፡ነሽ፡አላት።

፫፡ ስለ፡መጥምቁ፡ዮሐንስ፡መወለድም፡ካህኑን፡
ዘካርያስን፡ያበሠረው፡እርሱ፡ነው፡ይህ፡
መልአክ፡እጅግ፡የከበረ፡የተመረጠ፡ገናና፡
የሆነ፡ነውና፡ስለ፡እኛ፡ወደ፡እግዚአብሔር፡
ይማልድ፡ዘንድ፡ልባችንን፡አንጽተን፡
ወደዚህ፡የከበረ፡መልአክ፡እየለመንን፡መታ
ሰቢያውን፡ልናደርግ፡ይገባናል።

፬፡ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡
በዚህ፡በከበረ፡መልአክ፡አማላጅነት፡
ይማረን፡በረከቱ፡ረድኤቱም፡ከእኛ፡ጋር፡
ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለቤትከ፡በሀገረ፡ዳናህ፡ዘቀደሳ። አርኬላዎስ፡ኤጲስቆጶሳ። ገብርኤል፡ዜናዊ፡ምጽአተ፡
ክርስቶስ፡አንበሳ። ለዛቲ፡በዓልከ፡በዘይትሌዓል፡ሞገሳ። በዓለ፡ማርያም፡አንበረ፡ደቅስዮስ፡በርእሳ።

፭፡ ወበዛቲ፡ዕለት፡ካዕበ፡ገብረ፡በዓለ፡ደቅስዮስ፡
በዘአብሠራ፡ገብርኤል፡ለእግዝእትነ፡ቅድ
ስት፡ድንግል፡ማርያም።

፮፡ ወከመዝ፡ኮነ፡ምክንያተ፡አብዕሎቱ፡እስመ፡
ውእቱ፡ደቅስዮስ፡ኤጲስቆጶስ፡እምንደተ፡
ፍቅሩ፡አስተሐመመ፡ላቲ፡ወአስተጋብአ፡
መጽሐፈ፡ተአምሪሃ።

፯፡ ወአስተርአየቶ፡እግዝእትነ፡ቅድስት፡
ድንግል፡በ፪ ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡
አክሊሎሙ፡ለመሐይምናን፡ወነሥአት፡
በእዴሃ፡መጽሐፈ፡ወትቤሎ፡ኦ፡ፍቁርየ፡
ደቅስዮስ፡አንሰ፡ሠመርኩ፡ብከ፡ወንዕ
ድኩከ፡በእንተ፡ዘገበርከ፡ሊተ፡ዘንተ፡

፭፡ በዚችም፡ዕለት፡ዳግመኛ፡እመቤታችንን፡
ቅድስት፡ድንግል፡ማርያምን፡የከበረ፡
ገብርኤል፡በአበሠራት፡መሠረት፡ደቅስዮስ፡
በዓልን፡አደረገ።

፮፡ በዓልን፡የማክበሩ፡ምክንያትም፡እንዲህ፡ሆነ፡
ይህ፡ኤጲስቆጶስ፡ደቅስዮስ፡ከፍቅሩ፡ጽናት፡
የተነሣ፡አስቦ፡በመትጋት፡የተአምራቷን፡
መጽሐፍ፡ሰብስቦ፡አዘጋጀላት።

፯፡ የምእመናን፡ክብር፡የሆነች፡አምላክን፡
የወለደች፡በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡
ነፍስ፡የጸናች፡ክብርት፡እመቤታችን፡
ማርያምም፡ተገለጸችለትና፡መጽሐፉን፡
በእጅዋ፡አንሥታ፡ይዛ፡ወዳጄ፡ደቅስዮስ፡
ሆይ፡ይህን፡መጽሐፍ፡ስለ፡ጻፍክልኝ፡ባንተ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወእምዝ፡ተሠወረት፡እምኔሁ።

፰፤ ወሶበ ፡ ርእየ ፡ ደቅስዮስ ፡ ዘንተ፡ ግብረ ፡ እም
ራእይ ፡ ወእምፍቅረ ፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡
ድንግል ፡ ማርያም ፡ ተፈሥሐ ፡ ዐቢየ ፡ ፍሥሐ ፡
ወነደ ፡ ከመ ፡ እሳት ፡ በእንተ ፡ ፍቅራ ። ወኮነ ፡
ዘይሔሊ ፡ ዘከመ ፡ ይገብር ፡ ምንተ ፡ ከመ ፡
ይወስክ፡ወያፈድፍድ፡ክብረ፡ዚአሃ።

፱፤ ወእምዝ ፡ ገብረ ፡ በዓለ ፡ በዘዜነዋ፡ ገብርኤል፡
ሊቀ ፡ መላእክት ፡ ዘኢተክህሎሙ ፡ ሰብእ ፡
ይግበርዎ ፡ ቀዳሚ ፡ በውእቱ፡ ጊዜ፡ በእንተ፡
ጾም ። ወረሰየ ፡ ውእቱ ፡ እምቅድመ ፡ በዓለ ፡
ልደት ፡ ስቡሕ ፡ በ፰ መዋዕል ፡ ዘውእቱ ፡ አመ ፡
፳ወ፪ ለታኅሣሥ ፡ ወተሠርዐ ፡ በመዋዕለ ፡
ጽጽስናሁ፡እስከ፡ዛቲ፡ዕለት።

፲፤ ወሶበ ፡ አብዓልዎ ፡ ሰብእ፡ ተፈሥሑ፡ ዐቢየ፡
ፍሥሐ።

፲፩፤ ወአስተርአየቶ ፡ ካዕበ ፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡
ድንግል፡ በ፪ ማርያም፡ ወላዲተ፡ አምላክ ፡
መፍቀሪተ ፡ ምሕረት ፡ ወኂሩት ፡ ወሠናይት ፡
ወውስተ ፡ እዴሃ ፡ ልብስ ፡ ክቡር ። ወትቤሎ ፡
ኦ ፡ ፍቁርየ ፡ ደቅስዮስ ፡ ወላእክየ ፡ ዘበአማን ፡
አንሰ ፡ ንዕድኩከ ፡ ወተፈሣሕኩ ፡ ብከ ፡ ወሠ
መርኩ ፡ በግብርከ ። ወበከመ ፡ ተፈሣሕከ ፡
ብየ ፡ ወገበርከ፡ ሊተ ፡ በዓለ ፡ በብሥራተ ፡
ገብርኤል ፡ መልአክ ፡ ክቡር ፡ ዘአብሠረኒ ፡
ወአስተፍሣሕከ፡ ኵሎ ፡ ሰብአ ፡ በእንቲአየ፡
አንሰ ፡ እፈቅድ፡ እዕሲከ፡ ወአክብርከ፡ በዝ ፡
ዓለም ፡ በቅድመ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ በከመ ፡ አክበ
ርከኒ፡አንተ።

፲፪፤ ወናሁ ፡ አምጻእኩ ፡ ለከ ፡ ዘንተ ፡ ልብሰ ፡ ከመ ፡
ትልበስ ፡ ኪያሃ ፡ ወዘንተኒ ፡ መንበረ ፡ ከመ ፡
ትንበር ፡ ዲቤሁ ፡ ወአልቦ ፡ አሐዱሂ ፡ እም
ሰብእ ፡ ዘይክል ፡ ይልበሳ ፡ ለይእቲ ፡ ልብስ ፡
ወይንበር ፡ ዲበ ፡ ዛቲ ፡ መንበር ። ወለእመቦ ፡
ዘተዓደወ ፡ ዘንተ ፡ ቃልየ ፡ አንሰ ፡ እትቤቀል ፡
ኪያሁ ፡ ወዘንተ ፡ ብሂላ ፡ ተሠወረት ፡ እም
ኔሁ።

ደስ ፡ አለኝ ፡ አመሰግንኩህም ፡ አለችው ፡
ከዚህምበኋላ፡ከእርሱ፡ተሠወረች።

፰፤ ደቅስዮስም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በራዕይ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡
ክብርት ፡ ድንግል ፡ እመቤታችን ፡ ማርያ
ምን ፡ ከመውደዱ ፡ የተነሣ ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡
አለው ፡ እርሷንም ፡ ስለ ፡ ወደደ ፡ ፍቅርዋ ፡ እንደ
እሳት ፡ አቃጠለው ፡ የሷን ፡ ክብር ፡ አብዝቶ ፡
ይጨምር፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ እንደሚያደርግ ፡ የሚ
ሠራውን፡ያስብ፡ጀመር።

፱፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጾም ፡ ስለነበረ ፡
ሰዎች ፡ አስቀድመው ፡ ሊአከብሩት ፡ ያልተ
ቻላቸውን ፡ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ የከበረ ፡
ገብርኤል ፡ ባበሠራት ፡ ቀን ፡ በዓሏን ፡
አከበረ። እርሱም ፡ የከበረ ፡ የሚሆን ፡
የልደትን ፡ በዓል ፡ ከማክበር ፡ አስቀድሞ ፡
በስምንት ፡ ቀን ፡ አደረገ ፡ ይኸውም ፡
ታኅሣሥ ፡ በባተ ፡ በሃያ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ነው ፡
በጽጽስናውም፡ዘመን፡ተሠርታ፡እስከዚች፡
ቀን፡ጸንታ፡ትኖራለች።

፲፤ ሰዎችም ፡ በዓሉን ፡ በአከበሩት ፡ ጊዜ ፡ ፈጽሞ ፡
ደስ፡አላቸው።

፲፩፤ ደግነትን፡ምሕረትን፡ቸርነትን፡የምትወድ፡
አምላክን ፡ የወለደች ፡ በድንግሌ ፡ ሥጋ ፡
በድንጋሌ ፡ ነፍስ ፡ የጸናች ፡ ክብርት ፡ እመቤ
ታችን ፡ ማርያም ፡ በእጅዋ ፡ የከበረ ፡ ልብስ ፡
ይዛ ፡ ዳግመኛ ፡ ተገለጸችለትና ፡ አገልጋዬ ፡
የሆንክ ፡ ወዳጄ ፡ ደቅስዮስ ፡ ሆይ ፡ በእውነት ፡
አመሰገንኩህ ፡ በአንተም ፡ ደስ ፡ አለኝ ፡
ሥራህንም ፡ ወደድሁ ። በእኔም ፡ ደስ ፡ እንዳ
ለህና ፡ የከበረ ፡ መልአክ ፡ ገብርኤል ፡ እኔን ፡
በአበሠረበት ፡ ቀን ፡ በዓሌን ፡ ስለአከበርክ ፡
ሰውንም ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ደስ ፡ ስለአሰኘህ ፡
እኔም ፡ ዋጋህን ፡ ልሰጥህ ፡ አንተ ፡ በዚህ ፡
ዓለም ፡ እንዳከበርከኝም ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡
አከብርህ፡ዘንድ፡እወዳለሁ፡አለችው።

፲፪፤ እሷን ፡ ትለብስ ፡ ዘንድ ፡ ይችን ፡ ልብስ ፡ እነሆ ፡
አመጣሁልህ ፡ በላዩም ፡ ትቀመጥ ፡ ዘንድ ፡
ይህን ፡ ወንበር ፡ አመጣሁልህ ፡ ከሰው ፡ ወገን ፡
አንድ ፡ስንኳ ፡ ይህችን ፡ ልብስ ፡ ሊለብሳት ፡
በዚህም ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ሊቀመጥ ፡ የሚ
ቻለው ፡ የለም ። ይህን ፡ ነገሬን ፡ የሚተላለፍ ፡
ቢኖር ፡ እኔ ፡ እበቀለዋለሁ ፡ አለችው ፡
ይህንንም፡ተናግራ፡ከእርሱ፡ተሠወረች።

www.ethiopianorthodox.org

፲፫፤ወእምዝ፡ሶበ፡አዕረፈ፡ተሠይመ፡ካልዕ፡ኤጲ
ስቆጶስ፡ወለብሳ፡ለይእቲ፡ልብስ፡ወነበረ፡
ዲበ፡መንበሩ፡ወበጊዜሃ፡ወድቀ፡እምላዕለ፡
መንበር ፡ ወሞተ ፡ ወእለ ፡ ርእዩ ፡ ዘንተ ፡
አንከሩ፡እምተአምሪሃ፡ ለእግዝእትነ፡ ማር
ያም ፡ወፈርሁ ፡ ጥቀ ፡ ወአክበርዋ። ወሰ
ብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ስቡሕ ፡ ወሎቱ፡
ስብሐት፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፲፫፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በአረፈ ፡ ጊዜ ፡ ሌላ ፡ ኤጲስ
ቆጶስ፡ተሾመ፡ያቺንም፡ልብስ፡ለበሳት፡በወ
ንበሩም ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ፡ ወዲያውኑ ፡ ከወ
ንበሩ ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ ሞተ ፡ ይህንንም ፡ ያዩ፡
ከእመቤታችን፡ ማርያም፡ተአምር፡የተነሣ፡
አደነቁ ፡ እጅግም ፡ ፈርተው ፡ እመቤታ
ችንን፡ አከበሩዋት ፡ ምስጉን ፡ እግዚአብሔ
ርንም ፡ አመሰገኑት ፡ ለእርሱም ፡ ምስጋና ፡
ይሁን፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ እብል ፡ ለደቅስዮስ ፡ባሕርያ ። ኤጲስቆጶስ ፡ ዘሀገረ ፡ ጥልጥልያ ። በእንተ ፡ ዘጸሐፈ ፡ ላቲ ፡
ትእምርተ ፡ ዜናሃ ፡ ወጸጋ ፡ ዕበያ ። እንተ ፡ ወሀበቶ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ማርያ ።ልብሰ ፡ ሰማያዊት ፡ እስከ፡
ዮም፡ነያ።

፲፬፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡
አንስጣስዮስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘሀገረ፡እስክንድ
ርያ፡እምኍልቈሙ ፡ለአበው፡ሊቃነ፡ጳጳሳት፡
፴ወ፮ቱ።

፲፭፤ ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ እምውሉደ ፡ ልሒቃነ ፡
ሀገረ፡ እስክንድርያ ፡ ወውእቱ ፡ ኮነ ፡ ቀዳሚ ፡
መስፍነ፡ውስተ፡ቤተ፡መንግሥት፡ወእምዝ፡
ተሠይመ ፡ ቀሲሰ ፡ ላዕለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
ወዓዲ፡ተሠይመ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ላዕለ፡ሀገረ፡
እስክንድርያ ፡ ወኮነ ፡ ዘይሔሊ ፡ በእንተ ፡ አብ
ያተ፡ክርስቲያን፡ወሐነፀ፡ብዙኃተ፡አብያተ፡
ክርስቲያን ፡ ወሤመ ፡ ኤጲስቆጶሳተ ፡
ወካህናተ፡ውስተ፡ኵሎን፡መካናት።ወነሥአ፡
እምነ፡መለካውያን፡አብያተ፡ክርስቲያኖሙ፡
ወረሰዮን ፡ ለያዕቆባውያን ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡
ክቡር ፡ በኀቤሆሙ ፡ በእንተ ፡ አእምሮቱ ፡
ወሜጠሙ ፡ ለብዙኃን ፡ ውስተ ፡ ሃይማኖት ፡
ርትዕት።

፲፮፤ ወሶበ ፡ ሞተ ፡ ንጉሥ ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡
በውእቱ፡መዋዕል፡ተሠይመ፡ካልዕ፡ንጉሥ፡
ዘሃይማኖቱ ፡ እኪት ፡ ፈነወ ፡ አሐደ ፡ እምእ
ኩያን፡መላእክቲሁ፡ወአስተዋደዮ፡በሐሰት፡
ለዝንቱ፡አብ፡አንስጣስዮስ፡ወይቤ፡እስመ፡
አንስጣስዮስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘያዕቆባውያን፡
ሶበ ፡ ሠርዐ ፡ ሥርዓተ ፡ ጸሎት ፡ ወቅዳሴ ፡
ውስተ፡ ቤተ ፡ክርስቲያን፡አውገዞ፡ለንጉሥ፡
ወለሃይማኖቱ፡አርኰሳ፡ውእቱሰ፡ኢገብረ፡
ዘንተ ፡ ወሶበ ፡ አንበበ ፡ ንጉሥ ፡ ዘንተ ፡

፲፬፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ ለአባቶች ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳ
ሳት፡ሠላሳ፡ስድስተኛ፡የሆነ፡የእስክንድርያ፡
አገር፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡የከበረ፡አባት፡ አባ፡አንስ
ጣስዮስ፡ዐረፈ።

፲፭፤ ይህም ፡ ቅዱስ ፡ ከእስክንድርያ ፡ አገር ፡
ተወላጆች ፡ ከታላላቆች ፡ ወገን ፡ ነው ፡ እር
ሱም ፡ አስቀድሞ ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡
ውስጥ ፡ ሹም ፡ ነበር ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ለቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ ቅስና ፡ ተሾመ ፡ ደግሞ ፡ በእስክን
ድርያ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ተሾመ ፡
ስለ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትም ፡ አሳቢ ፡ ሁኖ ፡
ብዙዎች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ አሳነፀ ፡
በቦታውም ፡ ሁሉ ፡ ኤጲስቆጶሳትን ፡ ካህና
ትን፡ሾመ፡የመለካውያንንም፡አብያተ፡ክርስ
ቲያናቸውን ፡ ወስዶ ፡ ለያዕቆባውያን ፡ አደረ
ጋቸው ፡ እርሱ ፡ ስለ ፡ ዕውቀቱ ፡ በእነርሱ ፡
ዘንድ ፡ የከበረ ፡ ነውና ፡ ብዙዎችንም ፡ ወደ ፡
ቀናች፡ሃይማኖት፡መለሳቸው።

፲፮፤ ንጉሥ ፡ ቈስጠንጢኖስም ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡
በዚያን ፡ ወራት ፡ ሃይማኖቱ ፡ የከፋች ፡ ሌላ ፡
ንጉሥ ፡ ተሾመ ፡ እርሱም ፡ ክፉዎች ፡ ከሆኑ ፡
አለቆቹ ፡ ውስጥ ፡ አንዱን ፡ ላከ ፡ ያም ፡ ይህን ፡
አባት ፡ አንስጣስዮስን ፡ በሐሰት ፡ ወነጀለው ፡
እንዲህም ፡ አለ ፡ የያዕቆባውያን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳ
ሳት ፡ አንስጣስዮስ ፡ የጸሎትንና ፡ የቅዳሴን ፡
ሥርዓት ፡ በሚሠራ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡን ፡ አወገ
ዘው ፡ ሃይማኖቱንም ፡ አራከሰ ፡ እርሱ ፡ ግን ፡
ይህን ፡ አላደረገም ፡ ነበር ፡ ንጉሡም ፡ የዚህን ፡

www.ethiopianorthodox.org

መልእክቶ፡ለውእቱ፡መስተዋድይ፡እኩይ፡
ተምዐ፡ጥቀ።
፲፯፤ ወፈነወ፡መልእክተ፡ኀበ፡መኰንነ፡እስክን
ድርያ፡ወአዘዞ፡ከመ፡ይንሣእ፡ቤተ፡ክርስቲ
ያኖሙ፡ለቅዱሳን፡ቆዝሞስ፡ወድምያኖስ፡
ወኵሎ፡ንዋየ፡እምዝንቱ፡አብ፡አንስጣ
ስዮስ፡ወይመጥዎ፡ለአውግንዮስ፡ሊቀ፡ጳጳ
ሳት፡ዘሮም፡ወበእንተዝ፡ኀዘነ፡ዝንቱ፡አብ፡
አላ፡ባሕቱ፡እስመ፡እግዚአብሔር፡ዘየሐ
ትት፡ሕሊናተ፡አልባብ፡ናዘዞ።
፲፰፤ እስመ፡አጥፍአ፡እግዚአብሔር፡ለጴጥሮስ፡
ዓላዊ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘአንጾኪያ። ወተሠ
ይመ፡ህየንቴሁ፡ብእሲ፡ጻድቅ፡ወማእምር፡
ዘስሙ፡አትናስዮስ፡ውእቱኒ፡ፈነወ፡ሎቱ፡
ለዝንቱ፡አብ፡መልእክተ፡ዲበ፡ሃይማኖት
ርትዕት፡ወተፈሥሐ፡ውእቱኒ፡በብጽሐታ፡
ለይእቲ፡መልእክት፡ኀቤሁ፡ወአስተጋ
ብአሙ፡ለኤጲስቆጶሳት፡ወካህናት፡ወአን
በባ፡በቅድሜሆሙ፡ወተፈሥሑ፡ባቲ፡ወአ
ንከሩ፡እምነ፡ቃል፡ዘጽሑፍ፡ውስቴታ፡ወእ
ምአእምሮቱ።

፲፱፤ ወእምዝ፡ተንሥአ፡አባ፡አትናስዮስ፡ሊቀ፡
ጳጳሳት፡ዘአንጾኪያ፡ወምስሌሁ፡ኤጲስቆ
ጶሳት፡ወካህናት፡ወዲያቆናት፡ወረበናት፡
ወመጽአ፡ኀበ፡ሀገረ፡እስክንድርያ፡ወዝን
ቱኒ፡አብ፡አንስጣስዮስ፡ወጽአ፡ወተቀበ
ሎሙ፡በፍሥሐ።

፳፤ ወይቤ፡አባ፡አትናስዮስ፡አ፡ፍቁራንየ፡
ይደልወነ፡ከመ፡ንንሣእ፡መሰንቆሁ፡ለዳ
ዊት፡ወንዘምር፡እንዘ፡ንብል፡ሣህል፡
ወርትዕ፡ተራከባ፡ጽድቅ፡ወሰላም፡ተሰ
ዓማ፡እስመ፡አትናስዮስ፡ወአንስጣስዮስ፡
ተራከቡ፡ወተአምኁ፡በበይናቲሆሙ። ጽድቅ፡
አስተርአየት፡በምድረ፡ግብጽ፡ወርትዕ፡
ሠረቀት፡እምሥራቅ፡ወኮና፡ግብጽ፡ወሶርያ፡
አሐተ፡ሃይማኖተ፡ወሀገረ፡እስክንድርያ፡
ወሀገረ፡አንጾኪያ፡አሐተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡
ወአሐተ፡ድንግልተ፡መርዓተ፡ለ፩፡መርዓዊ፡
ንጹሕ፡ድንግል፡ዘውእቱ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ቃለ፡አብ፡ሕያው።

ክፉ፡ነገረ፡ሠሪ፡መልእክቱን፡በአነበበ፡ጊዜ፡
እጅግ፡ተቆጣ።
፲፯፤ ወደ፡እስክንድርያውም፡ገዥ፡ልኮ፡የቅዱ
ሳን፡ቆዝሞስንና፡የድምያኖስን፡ቤተ፡ክርስ
ቲያናቸውን፡ንዋየ፡ቅድሳቱንም፡ሁሉ፡
ከዚህ፡አባት፡ወስዶ፡ለሮም፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡
ለአውግንዮስ፡እንዲሰጠው፡አዘዘው፡ስለ
ዚህም፡ይህ፡አባት፡አዘነ፡ነገር፡ግን፡የልብን፡
ሐሳብ፡የሚመረምር፡እግዚአብሔር፡አጽ
ናናው።
፲፰፤ የአንጾኪያ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡የነበረ፡መናፍቅ፡
ጴጥሮስን፡እግዚአብሔር፡አጥፍቶታልና፡
በእርሱ፡ፈንታ፡ስሙ፡አትናስዮስ፡የሚባል፡
አዋቂ፡ጻድቅ፡ሰው፡ተሾመ፡እርሱም፡ለዚህ፡
አባት፡አንስጣስዮስ፡በቀናች፡ሃይማኖት፡
ላይ፡የተመሠረተች፡መልእክትን፡ላከለት፡
እርሱም፡ይቺ፡መልእክት፡ወደ፡ርሱ፡
በመድረሷ፡ደስ፡አለው፡ኤጲስቆጶሳቱንና፡
ካህናቱንም፡ሰብስቦ፡በፊታቸው፡አስነበ
ባት፡በእርሷም፡ደስ፡አላቸው፡በውስጧ፡
ከተጻፈው፡ቃል፡የተነሣ፡ከአዋቂነቱም፡
አደነቁ።
፲፱፤ ከዚህም፡በኋላ፡የአንጾኪያ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡
አባ፡አትናስዮስ፡ተነሣ፡ከርሱም፡ጋር፡ኤጲስ
ቆጶሳትን፡ካህናትንና፡ዲያቆናትን፡መምህራ
ንንም፡ይዞ፡ወደ፡እስክንድርያ፡ከተማ፡መጣ፡
ይህ፡አባት፡አንስጣስዮስም፡ወጥቶ፡በደስታ፡
ተቀበላቸው።
፳፤ ይህ፡አባት፡አትናስዮስም፡እንዲህ፡አለ፡
ወንድሞቼ፡የዳዊትን፡በገና፡ይዘን፡ይቅር
ታና፡ቅን፡ሕግ፡ተገናኙ፡ዕውነትና፡
ፍቅርም፡አንድ፡ሆኑ፡እያልን፡ልንዘምር፡
ይገባናል፡አለ፡አትናስዮስና፡አንስጣስዮስ፡
ተገናኝተው፡በመንፈሳዊ፡ሰላምታ፡እርስ፡
በርሳቸው፡አንድ፡ሁነዋልና። ዕውነት፡በም
ድረ፡ግብጽ፡ተገለጠች፡የቀናች፡ሃይማ
ኖትም፡ከአንጾኪያ፡ተገኘች፡ግብጽና፡
ሶርያም፡አንዲት፡ሃይማኖት፡ሁነዋልና፡
እስክንድርያና፡አንጾኪያም፡አንዲት፡ቤተ፡
ክርስቲያን፡ሁነዋልና፡ለአንድ፡ንጹሕ፡
ድንግል፡ሙሽራ፡አንዲት፡ድንግል፡
ሙሽሪት፡ሁነዋልና፡እርሱም፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡የሕያው፡አብ፡አካላዊ፡ቃል፡
ነው።

www.ethiopianorthodox.org

ወኀደረ ፡ ውስተ፡ ፩ ደብር፡ ወመንኰሰ፡
ውስቴታ።

፫፡ ወእምዝ ፡ ሐለየ ፡ ከመ ፡ ይንበር ፡ ባሕቲቶ ፡
ቅሩበ፡እምደብር፡ከመ፡ይትወከፎሙ፡ለፈላ
ስያን፡ወለነዳያን፡ወለርኁባን፡ያብልዖሙ፡
ወወጽአ፡እምደብር፡ወሐነፀ፡ሎቱ፡ማኅደረ፡
ወነበረ ፡ ውስቴቱ ፡ መጠነ ፡ ፳ቱ ፡ ዓመት ፡
እንዘ፡ይትጋደል፡ወይገብር፡ግብረ፡እደዊሁ፡
ወተመክነየ ፡ ላዕሌሁ ፡ ጸላዔ ፡ ሠናያት ።
ወአምጽአ፡ኀቤሁ፡ብእሲተ፡መበለተ፡ከመ፡
ትሣየጥ፡እምኔሁ፡ግብረ፡እደዊሁ፡ወበእንተ፡
ብጽሐታ ፡ ኀቤሁ ፡ ብዙኀ ፡ ጊዜ ፡ ኀደረ ፡
ላዕሌሆሙ ፡ ፍቅረ ፡ ኃጢአት ፡ ወኀብሩ ፡ ፪
ሆሙ ፡ በጊዜ ፡ መብልዕ ፡ ወእምዝ ፡ ወድቀ ፡
ምስሌሃ፡በኃጢአት፡ወነበረ፡ውስተ፡ግብረ፡
ኃጢአት፡፮ተ፡አውራኀ።

፬፡ አሜሃኒ ፡ ኢኀደጎሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢገ
ደፎሙ፡ለዛቲኒ፡ወለዝንቱኒ፡አላ፡አዘከሮሙ፡
ጊዜ ፡ ሞት ፡ ወቀዊመ ፡ ቅድመ ፡ ንጉሠ ፡
ነገሥት፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡በይእቲ፡ዕለት፡
መፍርህት፡ወመደንግፅት።

፭፡ ወተንሥአ ፡ እምውእቱ ፡ መካን ፡ ወቦአ ፡
ውስተ፡ገዳም፡ጽፉቅ፡እስመ፡መርሖ፡እግዚ
አብሔር፡ልዑል፡ወሀሎ፡በህየ፡ነቅዐ፡ማይ፡
ጥዑም ፡ ወተምር ፡ ወነበረ ፡ በህየ ፡ እንዘ ፡
ይትጋደል፡ብዙኀ፡መዋዕለ።

፮፡ወእምዝ፡ቀንአ፡ላዕሌሁ፡ሰይጣን፡ወአምጽአ፡
ቦቱ ፡ ደዌ ፡ ዕፁበ ፡ ውስተ ፡ ከርሡ ፡ ወእም
ብዝኀ፡ሕማሙ፡ኮነ፡ውዱቀ፡በገጹ፡ውስተ፡
ምድር፡ወውእቱ፡ይጼሊ፡ወይብላ፡ለነፍሱ፡
ኦ፡ነፍስ፡ተዓገሢ፡ላዕለ፡ዝንቱ፡ደዌ፡እስመ፡
ዝንቱ ፡ ፍሬ ፡ ኃጢአት ፡ ዘገበርኪ ፡ ወነበረ ፡
በዝንቱ ፡ ሕማም ፡ ፬ተ ፡ ዓመተ ፡ ወእምዝ ፡
ተሣሃሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ መሐሪ ፡ ወመስተ
ሣህል ፡ ወፈነወ፡ ሎቱ፡ መልአከ ፡ ወውእቱ ፡
መዝመዘ፡ከረሦ፡በእዴሁ፡ወሠጠቀ፡ገቦሁ፡
በአጽባዕቱ፡ወአንጽሐ፡ከብዶ፡ወአማዑቲሁ፡
ወእምዝ ፡ ሜጠ ፡ ውስተ ፡ መካኑ ፡ ወአስተ
ላጸቆ፡ ከመ ፡ ቀዳሚ ፡ ወአሕየዎ ፡ ወይቤሎ ፡
ናሁኬ፡እንከ፡ኮንከ፡ጥዑየ፡ተዓቀብ፡ወኢተ

ከአባቱ፡ዘንድ፡ወጥቶ፡ወደ፡አንድ፡ገዳም፡
ሒዶ ፡ በዚያ ፡ የሚኖር፡ ሆነ ፡ በውስጧም ፡
መነኰሰ።

፫፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የተራቡ ፡ ድኆችን ፡ መጻተ
ኞችን ፡ ተቀብሎ ፡ ይመግባቸው ፡ ዘንድ ፡
በገዳሙ ፡ አቅራቢያ ፡ ለብቻው ፡ መኖርን ፡
አሰበ ፡ ከገዳሙም ፡ ወጥቶ ፡ ማደሪያውን ፡
ሠራ። እየተጋደለና ፡ እጁ ፡ ሥራውንም ፡
እየሠራ፡በውስጡ፡አምስት፡ዓመት፡ያህል፡
ኖረ፡የበጎ፡ሥራ፡ጠላት፡ሰይጣንም፡ከእርሱ፡
እጅ፡ ሥራውን ፡ ትገዛ፡ ዘንድ ፡በምክንያት ፡
ጋለሞታ ፡ ሴትን ፡ ወደርሱ ፡ አመጣ ፡ ብዙ ፡
ጊዜ፡ ወደርሱ ፡ ከመመላለሷ ፡ የተነሣ ፡ የኃ
ጢአት፡ፍቅር፡አድሮባቸው፡በመብል፡ጊዜ፡
በአንድነት፡የሚበሉ፡ሆኑ፡ከዚህም፡በኋላ፡
ከእርሷ ፡ ጋር ፡ በኃጢአት ፡ ወደቀና ፡
በኃጢአት፡ሥራ፡ወሰጥ፡ሰባት፡ወር፡ያህል፡
ኖረ።

፬፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡እርሷንም ፡
እርሱንም፡ፈጽሞ፡አልጣላቸውም፡የሞትን፡
ጊዜ ፡ በምታስፈራና ፡ በምታስደነግጥ ፡ ቀን ፡
በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ፊት ፡
መቆምን፡አሳሰባቸው፡እንጂ።

፭፡ ከዚያም፡ቦታ፡ተነሥቶ፡ጥቅጥቅ፡ካለ፡ዱር፡
ውስጥ፡ገባ፡ልዑል፡እግዚአብሔር፡መርቶ
ታልና፡በዚያም፡ጣፋጭ፡የውኃ፡ምንጭና፡
ተምር፡አለ፡በዚያም፡ቦታ፡እየተጋደለ፡ብዙ፡
ዘመን፡ኖረ።

፮፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሰይጣን ፡ በእርሱ ፡ ቀንቶ ፡
አስጨናቂ፡የሆነ፡የሆድ፡በሽታ፡አመጣበት፡
ከሕማሙም ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ በግንባሩ ፡
በምድር፡ላይ፡የወደቀ፡ሁኖ፡ኖረ፡እርሱም፡
ሲጸልይ ፡ ነፍሱን ፡ እንዲህ ፡ ይላት ፡ ነበር ።
ነፍስ፡ ሆይ ፡ ይህ ፡ የሠራሽው ፡ የኃጢአት ፡
ፍሬ፡ ነውና፡ በዚህ፡ ደዌ፡ ላይ፡ ታገሺ፡ በዚህ፡
ሕማምም ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ኖረ። ከዚህም ፡
በኋላ፡መሐሪና፡ይቅር፡ባይ፡እግዚአብሔር፡
ራራለት ፡ መልአኩንም ፡ ላከለት ፡ እርሱም ፡
በእጁ ፡ ሆዱን ፡ አሸው ፡ ጐኑንም ፡ በጣቱ ፡
ሠነጠቀ፡ጨጓራውንና፡አንጀቱንም፡አፀዳ፡
ከዚህም፡በኋላ፡ወደቦታው፡መልሶ፡እንደቀ
ድሞው፡አያይዞ፡አዳነው።እነሆ፡እንግዲህ፡

www.ethiopianorthodox.org

አብስ ፡ ዳግመ ፡ ከመ ፡ ኢይብጻሕከ ፡ እምዝ ፡
ዘየአኪ።
፯፡ ወነበረ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ ፵፡ ዓመተ ፡ እንዘ ፡
ይትጋደል፡ወኮነ፡እምቅድመ፡ዝንቱ፡ዘነበረ፡
ውስተ፡ደብር፡፲ወ፯ተ፡ወውስተ፡በዓትሂ፡፲
ዓመተ ፡ ወበኑኀ ፡ ዝንቱ ፡ ዘመን ፡ ዕሩቅ ፡
ውእቱ፡እምልብስ፡ወእግዚአብሔር፡ልዑል፡
አንጎ፡ ሥዕርተ ፡ርእሱ፡ ወቦቱ፡ ተከድነ፡ በቅ
ድሜሁ፡ወበድኅሬሁ።
፰፡ ወተውህቦ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ዐቢይ ፡ ጸጋ ፡ በእ
ንተ፡ ተጸምዶቱ ፡ ወተጋድሎቱ ፡ ወሠናይ ፡
አምልኮቱ፡እስከ፡አራዊት፡ይሔውጽዎ፡ወይ
ልሕሱ ፡ ፀበለ፡ እገሪሁ ፡ ወእምድኅረ ፡ አሥ
መሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አዕረፈ ፡ በሰላም ፡
እንዘ፡ ይፀውር፡አክሊለ።
፱፡ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፡ ኪያነኒ፡ይም
ሐረነ፡በጸሎቱ፡ለዝ፡አብ፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ጤነኛ ፡ ሆንክ ፡ ዳግመኛ ፡ አትበድል ፡ ከዚህ ፡
የከፋ፡እንዳይደርስብህ፡አለው።
፯፡ በበረሀም ፡ ውስጥ ፡ እየተጋደለ ፡ አርባ ፡
ዓመት ፡ ኖረ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በገዳም ፡ ዐሥራ ፡
ሰባት ፡ ዓመት ፡ በዋሻም ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡
ኖሮዋል ፡ በዚህም ፡ ረጂም ፡ ዘመን ፡ ከልብስ ፡
የተራቈተ ፡ ነው ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔርም ፡
የራሱን ፡ ጠጕር ፡ አስረዘመለት ፡ በርሱም ፡
በፊቱም፡በኋላውም፡ተሸፈነበት።
፰፡ ለዚህም ፡ አባት ፡ ስለ ፡ አገልግሎቱ ፡ ስለ ፡
ተጋድሎው ፡ ስለ ፡ በጎ፡ አምልኮቱ ፡ አራዊት ፡
እስከሚገሙበኙትና ፡የእግሩን ፡ ትቢያ ፡ እስከ
ሚልሱ ፡ ድረስ ፡ ታላቅ ፡ ጸጋ ፡ ተሰጠው ፡እግዚ
አብሔርንም ፡ ከአገለገለ ፡ በኋላ ፡ አክሊሉን ፡
እንደተሸከመ፡በሰላም፡አረፈ።
፱፡ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡
በዚህ ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡
ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

<u>አርኬ</u>

ሰላም ፡ ለጢሞቴዎስ ፡ ህየንተ ፡ ብሊት ፡ ልብሱ ። ዘተከድነ ፡ ሥዕርተ ፡ ርእሱ ። አፍአሁ ፡ አንጺሐ ፡
ወንዋየ፡ዘከርሡ።እግዚአብሔር፡አዕበያ፡ለነፍሱ።እስከ፡አራዊት፡ሐወጽዎ፡ወእግሮ፡ለሐሱ።

፲፡ወበዛቲ፡ዕለት፡አዕረፈ፡ዳዊት፡ንጉሥ፡ወልደ፡
እሴይ፡ ወዝንቱ፡ኮነ፡ንጉሠ፡ላዕለ፡እስራኤል፡
እምድኅረ፡ሳኦል፡ንጉሥ፡ወልደ፡ቂስ፡ዘእም
ነገደ፡ብንያም።
፲፩፡ ወዝንቱ ፡ ዳዊት ፡ ንጉሥ ፡ እስመ ፡ እምቅ
ድሜሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘሖረ ፡ ሑረተ ፡
ሠናየ ፡ ወገብረ ፡ ፍትሐ ፡ ወጽድቀ ፡ እም
ኵሎሙ ፡ ነገሥተ ፡ እስራኤል ፡ ወውእቱ፡
እምነገደ ፡ ይሁዳ ፡ ዘእምቤተ ፡ ልሔም ፡
ወኀረዮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡
ንጉሠ ፡ ለእስራኤል ፡ሶበ ፡ ተዐደወ ፡ ትእዛዞ ፡
ለእግዚአብሔር ፡ ሳኦል ። ወፈነዎ ፡
ለሳሙኤል ፡ ነቢይ ፡ ከመ ፡ ይቅብዖ ፡ ቅብዐ ፡
መንግሥት ፡ ወኀረዮ ፡ ሳሙኤል ፡ ለወልደ ፡
እሴይ ፡ ወርእየ፡ ዘይልሕቅ ፡ እስመ ፡ ሠናይ ፡
አርአያሁ፡ ወጽንዕ፡ ሥጋሁ፡ ወኢኀረዮ፡እግ
ዚአብሔር፡ አላ ፡ ይቤሎ ፡ ኢትርአይ ፡ ገጾ ፡
ወኢትነጽር ፡ ግርማ ፡ ርእየቱ ፡ ለኤልያብ ፡
እስመ፡አኮ፡ዘከመ፡ይሬኢ፡ሰብእ፡ዘይሬኢ፡
እግዚአብሔር፡ እስመ ፡ ሰብእ ፡ ገጸ ፡ ይሬኢ ፡
ወእግዚአብሔር፡ ልበ፡ይሬኢ።

፲፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ የእሴይ ፡ ልጅ ፡ ዳዊት ፡ ንጉሥ ፡
አረፈ ፡ ይህም ፡ ከብንያም ፡ ነገድ ፡ የቂስ ፡ ልጅ ፡
ሳኦል ፡ ከነገሠ ፡ በኋላ ፡ በእስራል ፡ ላይ ፡ የነገሠ ፡
ነው።
፲፩፡ ይህም ፡ ንጉሥ ፡ ዳዊት ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፊት፡ መልካም ፡ ጐዞን ፡ የተጓዘ ፡ ከእስራ
ኤልም ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ እውነተኛ ፡
ፍርድን፡ያደረገ፡ነው፡እርሱም፡ሀገሩ፡ቤተ፡
ልሔም ፡ የሆነች ፡ ከይሁዳ ፡ ነገድ ፡ ነው ፡ ሳኦ
ልም፡የእግዚአብሔርን፡ ትእዛዝ፡በተላለፈ፡
ጊዜ ፡ ለእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡
መረጠው ፡ ነቢይ ፡ ሳሙኤልምንም ፡ ቅብዐ ፡
መንግሥትን፡የእሴይን፡ልጅ፡ይቀባ፡ዘንድ፡
ላከው ። ሳሙኤልም ፡ ታላቁን ፡ ኤልያብን ፡
ተመለከተ፡መልኩ፡ያማረ፡አካሉም፡የጸና፡
ነበርና ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ አልመረ
ጠውም።የኤልያብን፡ፊቱን፡አትይ፡የመል
ኩንም ፡ ማማር ፡ አትመልከት ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ሰው ፡ እንደሚያይ ፡ የሚያይ፡ አይደ
ለምና ፡ አለው ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ መልክ ፡ ያያል ፡
እግዚአብሔር፡ ግን፡ልብን፡ያያል።

www.ethiopianorthodox.org

፲፪፡ ወእምድኅረ፡ሰብዓቲሆሙ፡ደቂቁ፡ለእሴይ፡
ቀብዖ፡ለዳዊት፡ሳሙኤል፡ነቢይ፡ይንግሥ፡
ላዕለ፡ደቂቀ፡እስራኤል፡ወኮነ፡እግዚአ
ብሔር፡ምስሌሁ፡በኵሉ፡ግብሩ።
፲፫፡ ወእምብዝኀ፡ንጽሐ፡ልቡናሁ፡ወየውሃቱ፡
ሶበ፡ረከቦ፡ለጸላኢሁ፡ሳኦል፡ብዙኀ፡ጊዜ፡
ኢገብረ፡ላዕሌሁ፡ምንተኒ፡እምእኩይ።

፲፬፡ ወአሐተ፡ዕለተ፡ነሥአ፡ሳኦል፡ምስሌሁ፡
ሠላሳ፡ምእተ፡ብእሴ፡ኅሩያነ፡እምነ፡ኵሉ፡
እስራኤል፡ወሖረ፡ይኅሥሦ፡ለዳዊት፡
ወለሰብኡ፡ኀበ፡ምንዓወ፡ኀየላት፡ወበጽሐ፡
ኀበ፡ምርዓየ፡ኖሎት፡እለ፡ውስተ፡ፍኖት፡
ወበህየ፡በዓት፡ወቦአ፡ሳኦል፡ውስተ፡
ይእቲ፡በዓት፡ይትዋፈር፡ወሀለዉ፡ህየ፡
ዳዊት፡ወሰብኡ፡ውስጣ፡ለይእቲ፡በዓት፡
ይነብሩ።
፲፭፡ ወተንሥአ፡ዳዊት፡ወመተረ፡እምጽንፈ፡
ልብሱ፡ጽሚተ፡ወበካልዕ፡ጊዜ፡ቦአ፡ኀበ፡
ሀሎ፡ስኩበ፡ዲበ፡ልንጸኔ፡በሌሊት፡ምስለ፡
አቢሳ፡ወዓሊሁ፡ወነሥአ፡እምነ፡ትርአ
ሲሁ፡ኲናቶ፡ወጸፈነ፡ማይ፡ተመይጠ፡
ወሖረ፡ወኢገብረ፡ቦቱ፡እኩየ፡ወሶበ፡
ይቤልዎ፡ሰብኡ፡ቅትሎ፡ለጸላኢከ፡ሳኦል፡
ወአውሥአ፡ዳዊት፡ወይቤሎሙ፡ሐሰ፡
ሊተ፡ከመ፡እስፉሕ፡እዴየ፡ላዕለ፡መሲሐ፡
እግዚአብሔር።
፲፮፡ ወሶበ፡ዜነዎ፡በእንተ፡ቅትለቱ፡ለሳኦል፡፩
ብእሲ፡ወይቤሎ፡ዳዊት፡ለውእቱ፡ብእሲ፡
መኑ፡ቀተሎ፡ወይቤ፡አነ፡ቀተልክዎ፡
ወኀዘነ፡ ዳዊት፡ ፈድፋደ፡ ወሰጠጠ፡አል
ባሲሁ፡ወቀተሎ፡ለውእቱ፡ብእሲ፡ዘይቤ፡
አነ፡ቀተልክዎ፡ለሳኦል።
፲፯፡ ወአስተጋብአ፡እግዚአብሔር፡ውስተ፡ልበ፡
ዝንቱ፡ጻድቅ፡ብዙኀ፡ትሩፋተ፡ትሕትና፡
ወየውሃተ፡ወትዕግሥተ፡ወፍቅረ፡ወእንዘ፡
ንጉሥ፡ክቡር፡ውእቱ፡ይሰሚ፡ርእሶ፡
ከልበ፡ ወዕጼ ፡ወእንስሳ ፡ወበእንተዝ፡አል
ዓሎ፡እግዚአብሔር፡እምኵሎሙ፡ነገሥተ፡
ምድር፡ወወደሶ፡እንዘ፡ይብል፡ረከብክዎ፡
ለዳዊት፡ወልደ፡እሴይ፡ብእሴ፡ምእመነ፡
ዘከመ፡ልብየ፡ወዘይገብር፡ኵሎ፡ፈቃድየ።

፲፪፡ ከእሴይ፡ከሰባቱ፡ልጆቹ፡በኋላ፡ነቢይ፡
ሳሙኤል፡ዳዊትን፡በእስራኤል፡ልጆች፡
ላይ፡ይነግሥ፡ዘንድ፡ቀባው፡እግዚአብ
ሔርም፡በሥራው፡ሁሉ፡ከእርሱ፡ጋር፡ሆነ።
፲፫፡ ከልቡናው፡ንጽሕና፡ከየዋህነቱም፡ብዛት፡
የተነሣ፡ጠላቱን፡ሳኦልን፡ብዙ፡ጊዜ፡
ሲያገኘው፡በላዩ፡ምንም፡ምን፡ክፉ፡ነገር፡
አላደረገበትም።
፲፬፡ በአንዲትም፡ዕለት፡ሳኦል፡ከእስራኤል፡
ሁሉ፡ የተመረጡ፡ሦስት፡ሺህ፡ሰዎችን፡
ይዞ፡ ዳዊትን፡ከሰዎቹ፡ጋር፡ይፈልገው፡
ዘንድ፡ዋሊያዎች፡ወደሚታደኑበት፡ሔዶ፡
በጐዳና፡አጠገብ፡ያሉ፡ዘላኖችም፡ወደሚ
ሠማሩበት፡ደረሰ፡በዚያም፡ዋሻ፡ነበር፡
ሳኦልም፡ይናፈስ፡ዘንድ፡ወደዚያች፡ዋሻ፡
ገባ፡አሽከሮቹና፡ዳዊትም፡በዚያች፡ዋሻ፡
ውስጥ፡ተቀምጠው፡ነበር።
፲፭፡ ዳዊትም፡ተነሥቶ፡ቀስ፡ብሎ፡ከልብሱ፡
ጫፍ፡ቆረጠ። በሁለተኛም፡ጊዜ፡በድንክ፡
አልጋ፡ላይ፡ተኝቶ፡ወዳለበት፡ከአቢሳ፡
ጋር፡ ገብቶ፡ከራስጌው፡ ጦሩንና፡ውኃ፡
ያለበትን፡ረዋቱን፡ይዞ፡ተመልሶ፡ሔደ፡
ክፉ፡ነገርንም፡አላደረገበትም፡ሰዎቹም፡
ጠላትህ፡ሳኦልን፡ግደለው፡በአሉት፡ጊዜ፡
እግዚአብሔር፡በቀባው፡ላይ፡እጄን፡
ልዘረጋ፡አይገባኝም፡ብሎ፡መለሰላቸው።

፲፮፡ ስለ፡ሳኦልም፡መገደል፡አንድ፡ሰው፡
በነገረው፡ጊዜ፡ዳዊትም፡ያንን፡ሰው፡ማን፡
ገደለው፡አለው፡ሰውዬውም፡እኔ፡ገደ
ልሁት፡አለው፡ዳዊትም፡እጅግ፡አዘነ፡
ልብሱንም፡ቀደደ፡ያንንም፡ሳኦልን፡እኔ፡
ገደልሁት፡ያለውን፡ሰው፡ገደለው።
፲፯፡ እግዚአብሔርም፡በዚህ፡በጻድቅ፡ዳዊት፡
ልብ፡ብዙ፡ትሩፋትን፡ትሕትናን፡የዋህ
ነትን፡ቅንነትን፡ትዕግሥትን፡ፍቅርን፡
አከማቸ፡ክብር፡ያለው፡ንጉሥ፡ሲሆን፡
ራሱን፡ውሻ፡ትል፡እንስሳም፡አድርጎ፡
ይጠራል፡ስለዚህም፡ከምድር፡ነገሥታት፡
ሁሉ፡ከፍ፡ከፍ፡አደረገው፡እንዲህም፡ብሎ፡
አመሰገነው፡የእሴይን፡ልጅ፡ዳዊትን፡
እንደ፡ ልቤ፡ሆኖ፡አገኘሁት፡ፈቃዴን፡
ሁሉ፡የሚያደርግ፡ታማኝ፡ሰውም፡ነው።

www.ethiopianorthodox.org

፲፰፡ ወዓቀቦሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለደቂቀ ፡ እስ
ራኤል ፡ ወለኢየሩሳሌም ፡ ብዙኀ ፡ ጊዜ ፡
በእንተ፡የዋሃቱ፡ለዳዊት፡ወእምድኅሬሁኒ፡
አክበሮ ፡ በአፈ ፡ ነቢያቲሁ ፡ ወረሰየ ፡ ነገ
ሥተ፡እምዘርዐ።
፲፱፡ ወተነበየ ፡ ውእቱ ፡ መጽሐፈ ፡ መዝሙር ፡
ዘዕውቅ ፡ በኵሉ ፡ ዘውእቱ ፡ ወልታ ፡ ወኀፅ ፡
ላዕለ፡ሰይጣናት፡ጠምሉዕ፡እምኵሉ፡ቃል፡
ሠናይ ፡ በዘቦቱ ፡ ይሴብሕዎ ፡ ለእግዚአ
ብሔር፡እለ፡ውስተ፡ሰማይ፡ወምድር።
፳፡ ወኮነ ፡ ገጹ ፡ ቀይሐ ፡ ከመ ፡ ሮማን ፡ ወቆሙ ፡
ማዕከላይ ፡ ወውእቱ ፡ ጽኑዕ ፡ ወኃያል ፡
በአካሉ፡ወአመ፡ንኡስ፡ወሬዛ፡ውእቱ፡አመ፡
የዓቅብ ፡ አባግዐ ፡ አቡሁ ፡ ሶበ ፡ ይመጽእ ፡
አንበሳ ፡ አው ፡ ተኵላ ፡ ወይነሥእ ፡ በግዐ ፡
እመራዕይ፡ ወይዴግኖ፡ ወይቀትሎ፡ወያ
ነግፎ፡ እምአፉሁ ፡ ወእመኒ፡ ተንሥአ ፡
ላዕሌሁ፡ይእኀዞ፡ጕርዔሁ፡ወይሠጥቆ።
፳፩፡ ወሶበ ፡ ኮነ ፡ ቀትል ፡ ምስለ ፡ ፍልስጥዔማ
ውያን ፡ ወጽአ ፡ ብእሲ ፡ ጽኑዕ ፡ እምትዕ
ይንተ፡ ኢሎፍሊ ፡ ወስሙ ፡ ጎልያድ ፡
ዘእምጌት ፡ ወኑኅ ፡ ስድስቱ ፡ በእመት ፡
ወስዝር ፡ ወጌራ ፡ ዘብርት ፡ ላዕለ ፡ ርእሱ ፡
ወይለብስ፡ልብሰ፡ኀፂን፡ወድልወተ፡ኵሉ፡
ብርት ፡ ወኀፂን ፡ ዘላዕሌሁ ፡ ኃምሳ ፡ ምእት ፡
ሰቅሎን ፡ ወውስተ፡ አዕማደ ፡ እገሪሁ ፡
ልቡሰ፡ብርተ፡ወአራዊተ፡ብርት፡ማዕከለ፡
መታክፍቲሁ።
፳፪፡ ወዕፀ ፡ ኲናቱ ፡ ከመ ፡ መስቌ ፡ አምነት ፡
ስቅሱቅ፡ ላዕሌሁ ፡ ወድልወተ ፡ ኲናቱ ፡
ስድስቱ ፡ ምእት፡ ሰቅሎን ፡ ኀፂኑ ፡ ወዘይ
ፀውር፡ንዋየ፡ሐቅሉ፡የሐውር፡ቅድሜሁ።
፳፫፡ ወቆመ ፡ ወጸርሐ ፡ ኀበ ፡ ተዐይነ ፡ እስራኤል ፡
ወይቤሎሙ ፡ ለምንት ፡ ወጻዕክሙ ፡ ትጸ
ብኡ፡ወትትቃተሉ፡ምስሌነ፡አኮኑ፡አነ፡ኢሎ
ፍላዊ ፡ ወአንትሙ ፡ አግብርቲሁ ፡ ለሳኦል ፡
ኅረዩ፡እምኔክሙ፡አሐደ፡ብእሴ፡ወይረድ፡
ኀቤየ። ለእመ ፡ ክህለ ፡ ተቃትሎትየ፡ ወቀተ
ለኒ ፡ ንሕነ ፡ ንከውነክሙ ፡ አግብርተ፡ ወእ
መሰ ፡ አነ ፡ ክህልክዎ ፡ ወቀተልክዎ፡ ትከ
ውኑነ ፡ አንትሙ ፡ አግብርተ ፡ ወትትቀነዩ ፡

፲፰ እግዚአብሔርም፣የእስራኤልን፡ልጆች፡ኢየ
ሩሳሌምንም ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡ ደግነት ፡ ብዙ ፡
ጊዜ፡ጠበቃቸው፡እርሱ፡ካለፈ፡በኋላም፡በነ
ቢያቶቹ ፡ አንደበት ፡ አከበረው ፡ ነገሥታ
ትንም፡ከእርሱ፡ዘር፡አደረገ።
፲፱፡ እርሱም ፡ በሁሉ ፡ ዓለም ፡ የታወቀ ፡ የመዝ
ሙሩን ፡ መጽሐፍ ፡ ደረሰ ፡ ይኸውም ፡ በሰይ
ጣናት ፡ ላይ ፡ ጋሻና ፡ ጦር ፡ የሆነ ፡ መልካም ፡
ቃልንም ፡ የተመላ ፡ በሰማይና ፡ በምድርም ፡
ያሉ፡በእርሱ፡እግዚአብሔርን፡የሚያመስግ
ኑበት፡ነው።
፳፡ የዳዊትም ፡ ፊቱ ፡ እንደ ፡ ሮማን ፡ ቀይ ፡ ነው ፡
ቁመቱም ፡ መካከለኛ ፡ የሆነ ፡ አካሉም ፡ የጸና፡
ብርቱ ፡ ነበር ፡ ታናሽ ፡ ብላቴናም ፡ ሁኖ፡ ሳለ ፡
እርሱ ፡ የአባቱን ፡ በጎች ፡ ሲጠብቅ ፡ አንበሳ ፡
ወይም፡ ተኵላ ፡ መጥቶ ፡ ከመንጋው ፡ ውስጥ ፡
በግ ፡ ነጥቆ ፡ በሚወስድ ፡ ጊዜ ፡ ተከትሎ ፡
ገድሎ፡ከአፉ፡ያስጥለው፡ነበር፡ሊጣላውም፡
ቢነሣበት፡ጕረሮውን፡ይዞ፡ይሠነጥቀዋል።
፳፩፡ከፍልስጥዔማውያንም፡ጋራ፡ሰልፍ፡በሆነ፡
ጊዜ፡ብርቱ፡ሰው፡ስሙ፡ጎልያድ፡የሚባል፡
ከጌት፡ሰዎች፡የተወለደ፡ቁመቱ፡ስድስት፡
ክንድ፡ ከስንዝር ፡ የሆነ ፡ ከኢሎፍላውያን ፡
ሰፈር፡ወጣ።በራሱ፡ላይ፡የነሐስ፡በርቦርቴ፡
ደፍቷል፡የነሐስ፡ጽሩርም፡ለብሷል፡በርሱ፡
ላይ፡ያለ፡የብረቱና፡የነሐሱ፡ሁሉ፡ሚዛኑ፡
አምስት ፡ ሺህ ፡ ወቄት ፡ ነበር። በእግሮቹ ፡
ባቶችም ፡ ላይ ፡ የነሐስ ፡ ሰናፊል ፡ ታጥቆ ፡
ነበር ፡ በጫንቃውም ፡ መካከል ፡ የነሐስ ፡
እባቦች፡ነበሩ።
፳፪፡የጦሩም፡ዛቢያ፡እንደ፡ሸማኔ፡መጠቅለያ፡
ሁኖ፡በላዩ፡ሸቦ፡ነበረበት፡የጦሩም፡ብረት፡
መጠን፡ስድስት፡መቶ፡ወቄት፡ነበር፡ጋሻ፡
ጃግሬውም፡በፊቱ፡ይሔድ፡ነበር።
፳፫፡ ቁሞም ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡ ሰፈር ፡ ይጮህ ፡
ነበር ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ትዋጉ ፡ ዘንድ ፡ ለምን ፡
ወጣችሁ፡እኔ፡የኤሎፍላውያን፡ወገን፡ነኝ፡
እናንተም፡የሳኦል፡ባሮች፡አይደላችሁምን፡
ከእናንተ፡አንድ፡ሰው፡መርጣችሁ፡ወደኔ፡
ይውረድ፡ከእኔ፡ጋር፡መዋጋት፡ችሎ፡ቢገ
ድለኝ፡ባሮች፡እንሆናችኋለን፡እኔ፡ከርሱ፡
ጋራ፡ችዬ፡ብገድለው፡እናንተ፡ባሮች፡ሁና
ችሁ፡ትገዙልናላችሁ፡አላቸው።ያም፡ኢሎ

www.ethiopianorthodox.org

ለነ። ወይቤሎሙ ፡ ውእቱ ፡ ኢሎፍላዊ፡ ለሰብኡ ፡ ናሁ ፡ አነ ፡ ተዓየርክዎሙ ፡ ለፀባዒተ ፡ እስራኤል ፡ ወእቤሎሙ ፡ ዮም ፡ በዛቲ፡ ዕለት ፡ ሀቡኒ ፡ ብእሴ ፡ ወንትቃተል ፡ ክልኤነ፡ለባሕቲትነ።

፳፬፡ወሶበ፡ሰምዐ፡ሳኦል፡ወኵሎሙ፡እስራኤል፡ ዘንተ፡ቃሎ፡ለውእቱ፡ኢሎፍላዊ፡ደንገፁ፡ ወፈርሁ፡ጥቀ። ወነበረ፡ከመዝ፡እንዘ፡ይትዔየሮሙ ፡ ለሕዝበ ፡ እስራኤል ፡ ወይትሜካህ፡ ላዕሌሆሙ ፡ መጠነ ፡ ፵ መዋዕል ፡ ወአልቦ፡ዘተሃበለ፡እምሕዝበ፡እስራኤል፡ከመ፡ ይጻእ፡ኀቤሁ።

፳፭፡ ወበውእቱ፡መዋዕል፡ወጽአ ፡ዳዊት፡ ከመ፡ የሐውጽ፡አኃዊሁ፡ወሶበ፡ርእዮ፡ለውእቱ፡ ኢሎፍላዊ፡እንዘ፡ይትዔየሮሙ፡ለሕዝበ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀንአ ፡ ቅንአተ ፡ አምላካዊተ፡ ወይቤሎ ፡ ለሳኦል ፡ አነ ፡ አሐውር ፡ ወእቀትሎ ፡ ለውእቱ ፡ ቈላፍ ፡ ወአሰስል ፡ ዮም ፡ ትዕይርተ ፡ እምእስራኤል ፡ ምንት ፡ ውእቱ ፡ ዝንቱ ፡ ቈላፍ ፡ ከመ ፡ ይትዓየር ፡ ጸባዒተ ፡እግዚአብሔር ፡ ዘሕያው ። ወውእቱ፡እግዚአብሔር፡ ዘአድኃነኒ፡እምአፈ፡ አንበሳ፡ ወእምድብ፡ውእቱ፡ያድኅነኒ፡እምእዴሁ፡ለዝንቱ፡ቈላፍ።

፳፮፡ ወይቤሎ ፡ ሳኦል ፡ ሑር ፡ወእግዚአብሔር ፡ የሀሉ፡ምስሌከ፡ወነሥአ፡ዳዊት፡ሞጸፈ፡ በእዴሁ፡ወኀረየ፡፫ተ፡አዕባነ፡እምውስተ፡ ፈለግ ፡ ወሖረ ፡ ኀበ ፡ ዝንቱ ፡ ኢሎፍላዊ። ወሶበ ፡ ርእዮ ፡ ለዳዊት ፡ አስተኀቀሮ ፡ ጎልያድ፡ወይቤሎ፡ከልብኑ፡አነ፡ከመ፡ትምጻእ፡ ኀቤየ፡በበትር፡ወበዕብን፡ወይቤሎ፡ዳዊት፡ አልቦ፡ዘትኄይስ፡እምከልብ፡አላ፡ተአኪ፡ እምከልብ፡ወረገሞ፡ዝክቱ፡ቈላፍ፡ለዳዊት፡ በአማልክቲሁ።

፳፯፡ ወይቤሎ፡ዝንቱ፡ኢሎፍላዊ ፡ለዳዊት፡ ነዓ፡ ኀቤየ፡ወእሁብ፡ሥጋከ፡ለአዕዋፈ፡ሰማይ፡ ወለአራዊተ፡ገዳም። ወይቤሎ፡ዳዊት፡አንተሰ፡ትመጽእ፡ኀቤየ፡በኲናት፡ወበሰይፍ፡ ወበወልታ፡ወአንሰ፡እመጽእ፡ኀቤከ፡በስሙ፡ ለእግዚአብሔር፡ ጸባዖት ፡ ዘተዓየርከ ፡ ጸባዒተ ፡ እስራኤል ፡ ዮም ፡ የዐጽወከ ፡እግዚአብሔር፡ ዮም ፡ በእዴየ ፡ ወእቀትለከ ፡ ወእ

ፍላዊ ፡ ለወገኖቹ ፡ ዛሬ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ስጡኝና ፡ ሁለታችን ፡ ለብቻችን ፡ እንዋጋ ፡ ብዬ ፡ የእስራኤልን ፡ አርበኞች ፡ እነሆ ፡ ተገዳደርኋቸው ፡ አላቸው።

፳፬፡ እስራኤል ፡ ሁሉና፡ሳኦልም ፡ ይህን ፡ የኢሎፍላዊውን ፡ ቃል ፡ በሰሙ፡ ጊዜ ፡ ደነገጡ ፡ እጅግም ፡ ፈሩ ፡ የእራኤልንም ፡ ወገኖች ፡ እንዲህ ፡ እየተገዳደራቸውና ፡ እየተመካባቸው ፡ አርባ ፡ ቀኖች ፡ ያህል ፡ ኖረ ፡ ከእስራኤልም ፡ ወገን ፡ ወደርሱ ፡ ይወጣ ፡ ዘንድ ፡ የደፈረ፡የለም።

፳፭፡ በዚያም ፡ ወራት ፡ዳዊት ፡ ወንድሞቹን ፡ ሊጐበኝ፡ወጣ፡ያንንም፡የኢሎፍሊ፡ወገን፡ የሆነ፡ሰው፡የእግዚአብሔር፡ ወገኖችን፡ሲገዳደራቸው ፡ በአየው ፡ ጊዜ ፡ አምላካዊ ፡ ቅናትን ፡ ቀና ፡ ሳኦልንም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ እኔ ፡ ሔጄ፡ይህን፡ያልተገረዘ፡ቈላፍ፡ገድዬ፡ዛሬ፡ ከእስራኤል፡ሽሙጥን፡አርቃለሁ። ሕያው፡ የሚሆን የእግዚአብሔርን፡ አርበኞች፡ ይገዳደር፡ዘንድ፡ይህ፡ቈላፍ፡ምን፡ቁም፡ነገር፡ ነው፡ከድብ፡አፍና፡ከአንበሳ፡አፍ፡ያዳነኝ፡ እርሱ ፡እግዚአብሔር፡ ከዚህ፡ካልተገረዘ፡ ኢሎፍላዊ፡እጅ፡ያድነኛል።

፳፮፡ ሳኦል ፡ ሒድ ፡እግዚአብሔርም ፡ ከአንተ ፡ ጋር፡ ይሁን ፡ አለው ፡ ዳዊትም ፡ ወንጭፉን ፡ በእጁ፡ያዘ፡ከወንዝ፡መካከልም፡ሦስት፡ደንጊያዎችን ፡ መረጠና ፡ ወደዚያ ፡ ኢሎፍላዊ ፡ ሔደ። ጎልያድም ፡ ዳዊትን ፡ በአየው ፡ ጊዜ ፡ ናቀው፡እንዲህም፡አለው፡ደንጊያና፡በትር፡ ይዘህ ፡ ወደኔ ፡ ትመጣ ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ ውሻ ፡ ነኝን ፡ ዳዊትም ፡ ከውሻ ፡ የምትሻል ፡ አይደለህም ፡ ከውሻ ፡ ትብሳለህ ፡ እንጂ ፡ ቈላፍ ፡ ጎልያድም ፡ ዳዊትን ፡ በጣዖቶቹ ፡ ስም ፡ ረገመው።

፳፯፡ ያም ፡ ኢሎፍላዊ ፡ዳዊትን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ና ፡ ሥጋህን ፡ ለሰማይ ፡ ወፎችና ፡ ለዱር ፡ አራዊት፡ እሰጣሁ ፡ አለው ፡ ዳዊትም ፡ ያንኑ ፡ ኢሎፍላዊ ፡ አንተ ፡ ጦር ፡ ሰይፍና ፡ ጋሻ ፡ ይዘህ፡ወደኔ፡ትመጣለህ፡እኔ፡ግን፡አሸናፊ፡ በሚሆን ፡በእግዚአብሔር፡ ስም ፡ ወዳንተ ፡ እመጣለሁ። ዛሬ ፡ የእስራኤልን ፡ አርበኞች ፡ የተገዳደርከ ፡ አንተን ፡ ዛሬ እግዚአብሔር፡

www.ethiopianorthodox.org

መትር ፡ ርእሰከ ፡ እምኔከ ፡ ወእሁብ ፡ በድ
ነከ ፡ ወበድነ ፡ ትዕይንቶሙ ፡ ለኢሎፍላው
ያን ፡ ለአዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡ ወአራዊተ ፡ ገዳም ።
ወየአምሩ ፡ ዘውስተ ፡ ኵሉ ፡ ምድር ፡ ከመ ፡
ሀሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስለ ፡ እስራኤል ፡
ወየአምሩ ፡ ኵሉ ፡ ተዓይን ፡ ከመ ፡ አኮ ፡
በሰይፍ ፡ ወበኲናት ፡ ዘያድኅን ፡ እግዚአ
ብሔር፡ እስመ ፡ለእግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡
ቀትል።

፳፰፤ ወወደየ ፡ ዳዊት ፡ እዴሁ ፡ ውስተ ፡ መም
ጠቂሁ ፡ ወነሥአ ፡ አሐተ ፡ ዕብነ ፡ ወወጸፋ ፡
ወሔጾ፡ለዝክቱ፡ኢሎፍላዊ፡ውስተ፡ፍጹሙ፡
ወቦአት፡ይእቲ፡እንተ፡ፍጽሙ፡ውስተ፡ናላሁ፡
ወወድቀ ፡ በገጹ ፡ ውስተ ፡ ምድር። ወሮጸ ፡
ዳዊት ፡ ወነሥአ ፡ ሰይፎ ፡ ወመተረ ፡ ርእሶ ፡
ወአሰሰለ፡ ጽዕለተ፡እምደቂቀ፡እስራኤል።

፳፱፤ ወኵሉ ፡ መዋዕለ ፡ሕይወቱ ፡ለዳዊት ፡ ፸
ወነበረ ፡ ፴ ዓመተ ፡ እንበለ ፡ ይንግሥ ፡ መን
ግሥተ ፡ ወእምድኅረ ፡ ነሥአ ፡ ነበረ ፡ ፵
ዓመተ። ወተነበየ ፡ እምቅድመ ፡ ምጽአቱ ፡
ለክርስቶስ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ በሥጋ ፡ በ፲ወ፩
፻ወ፳ዓመት፡ወአዕረፈ፡በሰላም።

፴፤ ወስብሐት ፡ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነ ፡ ይም
ሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡
ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

በእጄ ፡ ይጥልሃል ፡ እገድልህምአለሁ ፡
ራስህንም ፡ እቆርጣለሁ ፡ የኢሎፍላውያን ፡
ሠራዊት ፡ ሬሳና ፡ ያንተን ፡ ሬሳ ፡ ዛሬ ፡ ለዱር ፡
አራዊትና ፡ ለሰማይ ፡ ወፎች ፡ እሰጣለሁ ፡ ሰዎ
ችም ፡ ሁሉ ፡እግዚአብሔር ፡ ከእስራኤል
ጋር፡ እንዳለ ፡ ያውቃሉ ፡ ሠራዊትም ፡ ሁሉ ፡
እግዚአብሔር ፡ በጦርና ፡ በሰይፍ ፡ የሚያ
ድን፡ እንዳይደለ ፡ ያውቃሉ ፡ ድል ፡ የእግዚአ
ብሔር፡ገንዘብ፡ነውና።

፳፰፤ዳዊትም፡ እጁን ፡ ወደ ፡ ድጉ ፡ ሰዶ ፡ አንዲት ፡
ደንጊያ ፡ አውጥቶ ፡ ወነጨፋት ፡ ያንንም ፡
ኢሎፍላዊ ፡ ግንባሩን ፡ ገመሰው ፡ ያቺም ፡
ደንጊያ ፡ ከግንባሩ ፡ ገብታ ፡ ናላውን ፡ በጠበ
ጠችው ፡ በምድር ፡ ላይም ፡ በግንባሩ ፡ ተደፋ።
ዳዊትም ፡ ሩጦ፡ የገዛ ፡ ሰይፉን ፡ አንሥቶ ፡
ራሱን ፡ ቆረጠው ፡ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡
ስድብን፡አራቀ።

፳፱፤የዳዊትም ፡ መላው ፡ዕድሜው ፡ ሰባ ፡ ነው ፡
መንግሥትን ፡ ሳይይዝ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፡
ከያዘ ፡ በኋላ ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ኖረ። የክብር ፡
ባለቤት ክርስቶስ፡ በሥጋ፡ከመምጣቱ፡በፊት፡
በሺህ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሃያ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡
ትንቢት ፡ የተናገረበት ፡ ዘመን ፡ ነው ፡
በሰላምም፡አረፈ።

፴፤ለእግዚአብሔርም፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም፡
በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡
ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለዳዊት ፡ ትሕትናሁ ፡ ሶበ ፡ ርእየ። ወየውሀቶ ፡ ፍጹመ ፡ ዘአልቦ ፡ እከየ።እግዚአብሔር፡ ይቤ ፡
እንዘ፡ይነብብ፡ሰደየ።እምነ፡ሕዝብየ፡አልዓልኩ፡ኅሩይየ።ወረከብክዎ፡ለዳዊት፡ ገብርየ።

፴፩፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካረ ፡ ዕረፍቶሙ ፡
ለቅዱሳን ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ፡ ወአባ ፡ ስምዖን ፡
ወአባ፡ገብርኤል፡

፴፪፤ ወዝንቱ ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ፡ ኮነ ፡ መነኰሰ ፡
ወባሕታዌ ፡ ወየኀድር ፡ በገቦ ፡ ሀገር ፡ ዘስማ ፡
ቀርጣሚን ፡ ወበህየ ፡ ሀሎ ፡ አስከሬነ ፡ ዐፅሙ ፡
ለአሐዱ ፡ ሰማዕት ፡ ዘስሙ ፡ አቅራፎስ ፡ ወይ
ትባረክ ፡ እምኔሁ ፡ በጥንተ ፡ ጸሎቱ ፡ ወበተፍ
ጻሜቱ።

፴፫፤ወሀሎ ፡ ፩መኰንን ፡ ዘስሙ ፡ ሰሊባ ፡ ወሀለዎ ፡
ወልድ ፡ ዘስሙ ፡ ስምዖን ፡ ወውእቱ ፡ ወልድ ፡
ደወየ ፡ ደዌ ፡ ሞት ፡ ወለአከ፡ አቡሁ ፡ ኀበ ፡ አባ ፡

፴፩፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ የቅዱሳን ፡ የአባ፡ ሳሙኤል ፡
የአባ ፡ ስምዖን ፡ የአባ ፡ ገብርኤል ፡ የዕረፍ
ታቸው፡መታሰቢያ፡ነው።

፴፪፤ ይህም ፡ መነኵሴ ፡ አባ፡ ሳሙኤል ፡ ባሕታዊ ፡
ሁኖ ፡ ቀርጣሚን ፡ በምትባል ፡ አገር ፡ ጐን ፡
የሚኖር ፡ ነው ፡ በዚያም ፡ አቅራፎስ ፡ የሚ
ባል፡ ሰማዕት ፡ ዐፅም ፡ አለ ፡ እርሱም ፡
ጸሎቱን፡ሲጀምርም ፡ ሲፈጽምም ፡ ከዐፅሙ ፡
ይባረካል፡ወይም፡ይሳለማል።

፴፫፤ ሰሊባ ፡ የሚባል ፡ አንድ፡ መኰንን ፡ ነበረ ፡
ስምዖን ፡ የሚባልም ፡ ልጅ ፡ አለው፡ ልጁም ፡
ለሞት ፡ የሚያበቃ ፡ ደዌ ፡ ታመመ ፡ አባቱም፡

www.ethiopianorthodox.org

ሳሙኤል ፡ ከመ ፡ ይጸሊ ፡ ላዕለ ፡ ወልዱ ፡ ውእቱኒ፡ጸለየ፡ወአንሥአ፡እምድኅረ፡ሞተ፡ ወተለዎ፡ውእቱ፡ወልድ፡ለአባ፡ሳሙኤል፡ ወኮኖ ፡ ረድአ ፡ ወመንኰሰ ፡ ወተጸምደ ፡ በገድል።

፴፬፤ ወአሐተ፡ዕለተ፡ሖረ፡ነዊአ፡ቀሱተ፡ከመ፡ ይቅዳሕ ፡ ማየ ፡ ወሰበረ፡ ቦቱ ፡ ሰይጣን ፡ ቀሱቶ፡ ወሶበ ፡ ነገሮ ፡ ለአባ ፡ ሳሙኤል ፡ ወሀቦ፡ ከበሮ ፡ ወይቤ፡ ከመ ፡ ይምላዕ ፡ ቦቱ ፡ ማየ ፡ ወነበረ ፡ ፲ ዓመተ ፡ እንዘ ፡ ኢይቀድሕ ፡ ማየ፡ ወእምዝ ፡ ሰበሮ ፡ ሰይጣን ፡ ወተክዕወ ፡ ማዩ ፡ ወሶበ ፡ ነገሮ፡ ለአባ ፡ ሳሙኤል ፡ ሖሩ ፡ ኀበ፡ ካልዕ ፡ መካን ፡ ወሐነፁ፡ ንስቲተ ፡ ቤተ ፡ ጸሎት፡ ወነበሩ፡ በህየ።

፴፭፤ ወእምዝ ፡ አስተርአዮሙ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሕልም ፡ ወአዘዞሙ ፡ ከመ ፡ ይሕንፁ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን ፡ ወመጽአ ፡ አንስጣስዮስ ፡ ንጉሥ ፡ ወሐነፀ ፡ ሎሙ ፡ ዐባየ ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን ፡ ወ፭፻ተ ፡ አብያተ ፡ መነኰሳት ፡ ወሶበ ፡ ረሥአ ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ፡ ወፃመወ ፡ እምብዝኀ፡ ተጋድሎ ፡ ፈለሰ ፡ ኀበ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘአፍቀሮ ፡ ኀዲጎ ፡ ደቂቆ ፡ ውስተ ፡ እደ፡ወልዱ፡ስምዖን።

፴፮፤ ወበዝኁ ፡ ጥቀ ፡ መነኰሳት ፡ እስከ ፡ ኮኑ ፡ መጠነ፡እልፍ፡ወእስራ፡ምእት።

፴፯፤ ወበመዋዕሊሁ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ስምዖን ፡ ተንሥአ ፡ ፩ ብእሲ ፡ ዓላዊ ፡ ዘኢየአምን ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ ወጸለየ ፡ አባ ፡ ስምዖን ፡ ላዕለ ፡ ምውት ፡ ወአንሥአ ፡ በቅድሜሁ ፡ ወሶበ፡ኢተመይጠ፡ልቡ፡እምኑፋቄ፡ካዕበ፡ ጸለየ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአውረደ ፡ እሳተ፡ እምሰማይ ፡ ወዓውዓዮ ፡ ለዓላዊ ። ወእምዝ ፡ ረሢአ ፡ አዕረፈ ፡ በሰላም ፡ ወበክብር ፡ ተቀብረ ፡ ውስተ ፡ መቃብረ ፡ መምህሩ።

፴፰፤ ወእምዝ ፡ ተሠይመ ፡ አባ ፡ ገብርኤል ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ ወውእቱ ፡ ትሑት ፡ ወየዋህ ፡ ወይለብስ፡ሠቀ፡ወኀቢነ፡እምታሕተ፡መልበሱ፡ ወኢይወዲ፡አሣዕነ፡ውስተ፡እገሪሁ፡ወኢይበውዕ፡ውስተ፡ቤት፡በክረምት፡ወበኀጋይ፡ ወይጸውም ፡ እምሰንበት ፡ እስከ፡ ሰንበት ፡ ወይበልዕ፡እንበለ፡ ፄው፡ወጸብሐ፡ኅብስተ፡ ወኮነ፡ዘይገብር፡ተአምረ፡ወመንክረ።

በልጁ ፡ ላይ ፡ ይጸልይ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አባ ፡ ሳሙኤል ፡ ላከ፡ እርሱም ፡ ጸልዮ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ አስነሣው ፡ ያም ፡ ልጅ ፡ አባ ፡ ሳሙኤልን ፡ የሚከተል ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ሆነ፡መንኵሶም፡በገድል፡ተጠመደ።

፴፬፤ በአንዲትም ፡ ቀን ፡ ውኃ ፡ ሊቀዳ ፡ እንስራ ፡ ይዞ፡ ሔደ ፡ ሰይጣንም ፡ እንስራውን ፡ ሰበረበት፡ ለአባ፡ ሳሙኤልም ፡ በነገረው፡ ጊዜ ፡ ውኃን ፡ ይመላበት ፡ ዘንድ ፡ የወይን ፡ ማስቀመጫ ፡ መሶብን ፡ ሰጠው ፡ ውኃም ፡ ሳይቀዳ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት፡ ኖረ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ፡ ሰይጣን ፡ ሰበረውና ፡ ውኃው ፡ ፈሰሰ ፡ ለአባ ፡ ሳሙኤልም፡ በነገረው ፡ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ ሒደው ፡ ታናሽ ፡ የጸሎት ፡ ቤት ፡ ሠርተው፡በዚያ፡ተቀመጡ።

፴፭፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ፡ በሕልም፡ ተገለጸላቸው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም፡ይሠሩ፡ዘንድ፡አዘዛቸው፡ንጉሥ፡አንስጣስዮስም፡ መጥቶ ፡ ታላቅ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡ ሠራላቸው ፡ ለመነኰሳትም ፡ አምስት፡ መቶ፡ ቤቶችን ፡ ሠራ ። አባ ፡ ሳሙኤልም፡ በአረጀና፡ ከተጋድሎ ፡ ብዛትም፡ በደከመ፡ጊዜ፡ልጆቹን፡በልጁ፡በስምዖን፡ እጅ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ወደደው ፡ እግዚአብሔር ፡ ሔደ።

፴፮፤ መነኰሳቱም ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ እስከሆኑ፡ድረስ፡እጅግ፡በዙ።

፴፯፤ በዚህም ፡ አባት ፡ ስምዖን፡ ዘመን ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታንን ፡ የማያምን ፡ አንድ ፡ ከሀዲ ፡ ሰው ፡ ተነሣ፡አባ፡ስምዖንም፡በሙት፡ላይ፡ጸልዮ፡ በፊቱ ፡ አስነሣው ፡ ልቡም ፡ ከመጠራጠር ፡ ባልተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ ሁለተኛ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር፡ጸለየ፡እሳትንም፡ከሰማይ፡አውርዶ፡ ያንን ፡ ከሀዲ፡ አቃጠለው ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሽምግሎ ፡ በሰላም ፡ አረፈ ፡ በመምህሩም ፡ መቃብር፡በክብር፡ተቀበረ።

፴፰፤ ከዚህም፡በኋላ፡አባ፡ገብርኤል፡አበ፡ምኔት፡ ሁኖ ፡ ተሾመ ፡ እርሱም ፡ ትሑትና ፡ የዋህ ፡ ነበር፡በልብሱም፡ውስጥ፡ማቅና፡መንቆር፡ ይለብሳል፡በእግሮቹም፡ውስጥ፡ጫማ፡አያስገባም፡በክረምትም፡በበጋም፡ወደ፡ቤት፡ አይገባም ፡ ከሰንበትም ፡ እስከ ፡ ሰንበት ፡ ይጾማል ፡ እንጀራውንም ፡ ያለ ፡ ጨው ፡ ያለወጥ ፡ ይበላል ፡ ድንቅ ፡ ተአምራትንም ፡ የሚያደርግ፡ሆነ።

www.ethiopianorthodox.org

፴፱፤ ወአሐተ ፡ ዕለተ ፡ ሶበ ፡ ፈቀዱ ፡ አርድእቲሁ ፡ ያብኡ ፡ ዕብነ ፡ ዐቢየ ፡ ውስተ ፡ ደብር ፡ በዘቦቱ፡ ይገብሩ ፡ ብሑአ ፡ ኅብስት ፡ ኀጥኡ ፡ ፀዊረ ፡ ዘይረድኦሙ ፡ ወሰሚዖ ፡ አባ ፡ ገብ ርኤል ፡ አውገዘ ፡ ከመ ፡ ኢይትርፍ ፡ ውስተ ፡ ደብር ፡ አሐዱሂ ፡ እምሰብእ ፡ ወይጻኡ፡ ለፀዊረ ፡ ዕብን ፡ ወተንሥኡ ፡ ሙታን ፡ መጠነ፡ እልፍ ፡ ወሠላሳ ፡ ነፍስ ፡ ሰሚዖሙ ፡ ቃሎ ፡ ወርእዮ ፡ አባ ፡ ገብርኤል ፡ ይቤሎሙ ፡ አኮ ፡ ኪያክሙ ፡ ዘእቤ ፡ አላ ፡ ሕያዋነ ፡ ወሶቤሃ፡ ተመይጡ ፡ ውስተ ፡ መቃብ ራሆሙ።

፵፤ ወበ ፩ እመዋዕል ፡ አንበረ ፡ አሐዱ ፡ ብእሲ ፡ ወርቀ ፡ ኀበ ፡ ፩ መነኮስ ፡ ወነገደ ፡ ርኁቀ ፡ ብሔረ ፡ ወበተመይጦቱ ፡ ረከቦ ፡ መዊቶ ፡ ዘእንበለ ፡ ይንግር ፡ ለረድኡ ፡ ወሶበ ፡ ሐተትዎ፡ ለረድእ ፡ በእንተ ፡ ወርቅ ፡ አጠየቆሙ ፡ ከመ ፡ ኢየአምር ፡ ኀበ ፡ አንበረ ፡ መምህሩ።

፵፩፤ ወሐዊሮ ፡ አባ ፡ ገብርኤል ፡ ኀበ ፡ መቃብረ ፡ ምውት ፡ ወተሰአሎ ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡ ወርቅ፡ ወነገሮ ፡ ምውት ፡ ኀበ ፡ አንበረ ፡ ወነሢአ፡በዓለ፡ንዋይ፡ሖረ፡እንዘ፡ያነክር።

፵፪፤ ወሀለዎ ፡ ፍቁር ፡ ዘስሙ ፡ ሰሊብ ፡ ወዘእንበለ ፡ ይትራከቡ ፡ ሞተ ፡ ወሰሚዖ ፡ አባ ፡ ገብርኤል ፡ ሖረ ፡ ኀበ ፡ መቃብሩ ፡ በከየ ፡ ወጸለየ ፡ ወይቤ ፡ በስመ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ተንሥእ ፡ ወተንሥአ ፡ ሕያዎ ፡ ወነበረ ፡ ፲ወ፪ተ ፡ ዓመተ።

፵፫፤ ወበመዋዕሊሁ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ኮነ ፡ ስደት ፡ ዐቢይ ፡ ላዕለ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያን ፡ እምነ ገሥተ ፡ ሮም ፡ ወተቀትሉ ፡ ብዙኃን ፡ መሐይ ምናን ፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡ ኍልቍ ፡ ወእምድኅረ ኅዳጥ ፡ መዋዕል ፡ ነግሡ ፡ ተንባላት ፡ ወድኅኑ ፡ ክርስቲያን ፡ እምስደት።

፵፬፤ ወሶበ ፡ ኮኖ ፡ ፹ ዓመተ ፡ እምድኅረ ፡ ነበረ ፡ በተጋድሎ ፡ ብዙኅ ፡ አዕረፈ ፡ በሰላም።

፵፭፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቶሙ ፡ ለእሉ ፡ ቅዱሳን ፡ ወበ ረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

፴፱፤ በአንዲትም ፡ ዕለት ፡ ደቀ ፡ መዘዛሙርቱ ፡ ለእንጀራ ፡ የሚሆን ፡ ቡሖ ፡ የሚያቦኩበት ፡ ታላቅ ፡ የደንጊያ ፡ ገንዳ ፡ ወደ ፡ ገዳሙ ፡ ሊአስገቡ ፡ ሽተው፡ ሸክም ፡ የሚረዳቸው ፡ በአጡ ፡ ጊዜ ፡ አባ ፡ ገብርኤል ፡ ሰምቶ ፡ ከሰው ፡ አንድ ፡ እንኳ ፡ በገዳም ፡ ውስጥ ፡ እንዳይቀር ፡ ለመሸከም፡ እንዲወጣ ፡ አወገዘ ። ዐሥር ፡ ሺህ፡ ሠላሳ ፡ ያህል ፡ ሰዎች ፡ ከሙታን ፡ ተነሡ ፡ አባ ፡ ገብርኤልም ፡ አይቶ ፡ እናንተን ፡ ያልኩ ፡ አይደለም ፡ ሕያዋኑን እንጂ ፡ አላቸው፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ወደ፡ መቃብ ራቸው ፡ ተመለሱ።

፵፤ ከዕለታትም ፡ በአንዱ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከአንድ ፡ መነኰሴ፡ ዘንድ ፡ ወርቁን ፡ አደራ ፡ አኑሮ ፡ ወደ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ ሔደ ፡ በተመለሰም ፡ ጊዜ ፡ መነኰሴው ፡ ለረድኡ ፡ ሳይናገር ፡ ሙቶ ፡ አገኘው ፡ ረድኡንም ፡ ስለ፡ ወርቅ ፡ በመረ መሩት ፡ ጊዜ ፡ መምህሩ ፡ ያኖረበትን ፡ እንደማ ያውቅ ፡ አስረዳቸው።

፵፩፤ አባ ፡ ገብርኤልም ፡ ወደ ፡ ሟቹ ፡ መቃብር ፡ ሒዶ ፡ ስለዚያ ፡ ወርቅ ፡ ጠየቀው ፡ ሟቹም ፡ የአኖረበትን ፡ ሥፍራ ፡ ነገረው ፡ ባለ ፡ ገንዘቡም ፡ እያደነቀ ፡ ገንዘቡን ፡ ይዞ ፡ ሔደ።

፵፪፤ ሰሊብ ፡ የሚባል ፡ ወዳጅ ፡ ነበረው ፡ ሳይገናኙ ፡ ሞተ ፡ አባ ፡ ገብርኤልም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ መቃብሩ፡ ሒዶ ፡ አለቀሰ ፡ ጸሎትንም ፡ አድርጎ ፡ በክብር ፡ ባለቤት ፡ በጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ተነሥ ፡ አለ ፡ ድኖ ፡ ተነሥቶ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ኖረ።

፵፫፤ በዚህም ፡ አባት ፡ ዘመን ፡ ከሮም ፡ ነገሥታት ፡ በክርስቲያን ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ስደት ፡ ሆነ ፡ ቊጥር ፡ የሌላቸውም ፡ ምእመናን ፡ ተገደሉ ፡ ከጥቂት ፡ ወራትም ፡ በኋላ ፡ እስላሞች ፡ ነገሡ ፡ ክርስቲያኖችም ፡ ከስደት ፡ ዳኑ።

፵፬፤ ሰማንያ ፡ ዓመትም ፡ በሆነው ፡ ጊዜ ፡ በብዙ ፡ ተጋድሎ ፡ ከኖረ ፡ በኋላ ፡ በፍቅር ፡ አንድነት ፡ አረፈ።

፵፭፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በእሊህ ፡ ቅዱሳን ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

## አርኬ

ሰላም ፡ ለሳሙኤል ፡ ወለስምዖን ፡ ወልዱ። ወለሣልሳይ ፡ገብርኤል ፡ ዘውስተ፡ ፍቅዶሙ ፡ ፍቅዱ። እንዘ ፡ ይታለዉ ፡ አሐዱ ፡ ድኅረ ፡ አሐዱ። በበዘመኖሙ፡ አንሥአ ፡ ሙታን ፡ አግሃዱ ። እሳተኒ ፡ እምሰማይ፡ አውረዱ።

፴፮፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ይስሐቅ ፡ ወአባ፡ አሞኒ ፡ ወአባ ፡ አቦሊ ፡ ወመቃርስ ፡ ወአይተለአትካ፡ ወፊልጦስ ፡ ወመርቆሬዎስ ፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፴፮፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ የቅዱሳን ፡ የይስሐቅ ፡ የአባ ፡ አሞን ፡ የአባ ፡ አቦሊ ፡ የመቃርስ ፡ የአይተለ አትካ ፡ የፊልጦስ ፡ የመርቆሬዎስ ፡ መታሰቢ ያቸው ፡ ነው። በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ትኑር ፡ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን፡ ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለይስሐቅ ፡ ዘአጥረየ፡ ግብረ ፡ ተገብሮ። እንበለ ፡ መኑ ፡ ያእምሮ። ኑኀ ፡ ዓመታት ፡ ሰብዑ ፡ በሰጊድ፡ወአስተምህሮ።ከመ፡ተመነየ፡ገጸ፡ማርያም፡ ነጺሮ።እምድኅረ፡መዋዕል፡ሠሉስ፡ፈለሰ፡ሀገሮ።

***

፩፤ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፳ ወ፬ ለታኅሣሥ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት፡ ተዝካረ ፡ ዕረፍታ ፡ ለአስቴር፡ ጻድቅት፡ ወለተ፡አሚናዳብ።

፪፤ ወሀሎ ፡ ፩ ብእሲ ፡ አይሁዳዊ ፡ በውስተ ፡ ሱሳ ፡ ሀገር፡ወስሙ፡መርዶክዮስ፡ወልደ፡ኢያኤሩ፡ ዘቈስዩ፡ዘእምነገደ፡ብንያም፡ወተፄወወ፡እም ኢየሩሳሌም ፡ በእደ ፡ ናቡከደነፆር ፡ ንጉሠ ፡ ባቢሎን ። ወቦቱ ፡ ወለት ፡ እንተ ፡ ሐፀና ፡ ወለተ፡ አሚናዳብ ፡እኁሁ ፡ ለአቡሁ ፡ ወስማ፡ አስቴር፡ ወእምድኅረ ፡ ወጽአት ፡ እምእዝ ማዲሃ ፡ ሐፀና ፡ ላቲ ፡ ትኩኖ ፡ ወለቶ ፡ ወይእቲ፡ ወለት፡ሠናይት፡ራእያ።

፫፤ ወአሐተ፡ ዕለተ ፡ ሶበ ፡ ገብረ ፡ አርጤክስስ ፡ ንጉሥ ፡ ተድላ፡ ብዙኀ ፡ ወጸውዐ ፡ መኳን ንቲሁ፡ ወለሐማ ፡ አማሌቃዊ ፡ ርእሰ ፡ መኳን ንቲሁ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ክቡር ፡ እምኵሎሙ፡ መኳንንት ፡ ወእምዝ ፡ አዘዞሙ ፡ ለሰብዓቱ ፡ ሕፅዋኒሁ ፡ እለ ፡ ይትለአክዎ ፡ ከመ ፡ ያምጽእዋ፡ ለአስጢን ፡ ወያንግሥዋ፡ ወያሠር ግውዋ ፡ አክሊለ ፡ ወያርእይዋ ፡ ለኵሎሙ ፡ መላእክተ ፡ አሕዛብ ፡ ስና፡ እስመ ፡ ሠናይት ፡ ይእቲ።

፬፤ ወአበየት ፡ ሰሚያቶ ፡ አስጢን ፡ ንግሥት ፡ ወኢ ፈቀደት ፡ ትምጻእ ፡ ምስለ ፡ ሕፅዋኒሁ ፡ ወተከዘ

***

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ታኅሣሥ ፡ ሃያ ፡ አራት፡ በዚች፡ ቀን ፡ የአሚናዳብ ፡ ልጅ ፡ የጻድቂቱ ፡ የአስቴር ፡ የዕረፍቷ ፡ መታሰቢያ ፡ ነው።

፪፤ የአይሁድ ፡ ወገን ፡ የሚሆን ፡ ስሙ ፡ መርዶ ክዮስ፡ የሚባል ፡ የኢያኤሩ ፡ ልጅ ፡ ከብንያም፡ ወገን ፡ የተወለደ ፡ የቈስዩ ፡ ልጅ ፡ አንድ ፡ ሰው፡ በሱሳ ፡ አገር ፡ ነበረ ። ከኢየሩሳሌምም ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በናቡከደነፆር ፡ እጅ ፡ የተማረከ ፡ ነው ፡ ያሳደጋት ፡ ልጅ ፡ ነበረችው፡ እርሷም ፡ ያባቱ ፡ ወንድም ፡ የአሚናዳብ ፡ ልጅ፡ ናት ፡ ስሟም ፡ አስቴር ፡ ይባላል ፡ ከዘመዶቿም፡ ተለይታ ፡ በወጣች ፡ ጊዜ ፡ ልጅ ፡ ትሆነው ፡ ዘንድ ፡ አሳድጓት ፡ ነበር ፡ ይችም ፡ ልጅ ፡ መልከ፡መልካም፡ነበረች።

፫፤ በአንዲትም ፡ ዕለት ፡ ንጉሥ ፡ አርጤክስስ ፡ ብዙ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ አድርጎ ፡ መኳንንቶቹን፡ የመኳንንቶቹን፡አለቃ፡አማሌቃዊ፡ሐማንም፡ በጠራ ፡ ጊዜ ፡ ከመኳንንቱ ፡ ሁሉ ፡ እርሱ ፡ ሐማ፡ የከበረ ፡ ነበርና ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሰባቱን ፡ ባለሟሎቹን ፡ ንግሥቲቱን ፡ አስጢንን ፡ አምጥተው ፡ የእቴጌነትን ፡ ዘውድ ፡ ያቀዳ ጅዋት ፡ ዘንድ ፡ እሷ ፡ መልከ ፡ መል ካም፡ ናትና ፡ ለአሕዛብ ፡ አለቆች ፡ ሁሉ ፡ ውበቷን ፡ያሳዩ ፡ ዘንድ ፡ አዘዛቸው።

፬፤ ንግሥቲቱ ፡ አስጢንም ፡ ትእዛዙን ፡ መስማት ፡ እምቢ ፡ አለች ፡ ከባለሟሎቹም ፡ ጋር ፡ ትመጣ፡

www.ethiopianorthodox.org

ንጉሥ፡ ወተምዐ ፡ ወሠዓረ ፡ እምንግሣ።

፭፤ ወእምዝ ፡ አዘዘ ፡ ይኅረዩ ፡ ሎቱ ፡ ፲ተ ፡ ፻ተ
አዋልደ ፡ እምኵሉ ፡ አህጉረ ፡ መንግሥቱ ፡
ዘቀኊልቆሙ ፡ ፻ ወ ፳ ወ ፯ቱ ፡ ወኀረዩ ፡ ሎቱ ፡
፲፻ተ ፡ ወእምኔሆን፡ ኀረዩ ፡ ምእተ ፡ ወእምነ፡
ምእት ፡ ዐሠርተ፡ ወእምዐሠርቱ ፡ ሠለስተ ፡
ወእምኵሎን ፡ ተኅርየት፡ አስቴር ፡ በስን ፡
ወበላሕይ።

፮፤ ወኪያሃ ፡ አንገሠ፡ ወአፍቀራ ፡ ንጉሥ ፡
ለአስቴር፡ ፊድፋደ ፡ ወቦአት ፡ አስቴር ፡ ኀበ ፡
አርጤክስስ ፡ ንጉሥ ፡ በዐሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡
አውራኀ ፡ በወርኀ ፡ አዳር ፡ በሰብዐቱ ፡ ዓመተ ፡
መንግሥቱ ፡ ወአደመቶ ፡ አስቴር ፡ ለንጉሥ፡
ወረከበት ፡ ሞገሰ ፡ ፊድፋደ ፡ እምነ ፡ ኵሎን ፡
ደናግል ፡ ወአሠርገዋ ፡ አክሊለ ፡ አንስት።

፯፤ ወእምቅድመ ፡ ዝኒ ፡ ነበረ ፡ መርዶክዮስ ፡
ውስተ፡ ዐፀድ ፡ ምስለ፡ ገቦታ ፡ ወታራ ፡
ክልኤቱ፡ ሕፅዋኒሁ ፡ ለንጉሥ ፡ እለ ፡ የዐቅቡ ፡
ዐፀደ ፡ ወሀገረ።

፰፤ ወሰምዐ ፡ ምክሮሙ ፡ ዘይሔልዩ ፡ ወአእመረ ፡
ወጠየቀ ፡ ከመ ፡ አስተዳለዉ ፡ ማዕሌተ ፡
ይቅትልዎ ፡ ለአርጤክስስ፡ ንጉሥ፡ ወነገሮ ፡
ለንጉሥ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ ወሐተቶሙ ፡
ንጉሥ ፡ ለክልኤሆሙ ፡ ሕፅዋኒሁ ፡ ወአምኑ ፡
ወተኰነኑ።

፱፤ ወጸሐፎ ፡ ንጉሥ ፡ ለዝንቱ ፡ ነገር ፡ ውስተ ፡
ተዝካረ ፡ ኖብያት ፡ ወመርዶክዮስኒ ፡ ጸሐፎ።

፲፤ ወሐማስ፡ ጥቀ ፡ ይጸልእ ፡ ለመርዶክዮስ ፡
ወለኵሎሙ ፡ ሕዝበ፡ እስራኤል ፡ እስመ ፡
አማሌቃዊ ፡ ውእቱ ፡ ወፈቀደ ፡ ከመ ፡
ያጥፍአሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ አይሁድ ፡ ወተሀ
ውከት ፡ ኵላ ፡ ሀገር ፡ ወሶበ ፡ አእመረ ፡ መርዶ
ክዮስ ፡ ዘከመ ፡ ኮነ ፡ ሠጠጠ ፡ አላባሲሁ ፡
ወለብሰ ፡ ሠቀ።

፲፩፤ ወጸውዓቶ ፡ አስቴር ፡ ለአክራትዮስ ፡ ሕፅው ፡
ዘይቀውም፡ ቅድሜሃ ፡ ወለአከቶ ፡ ይስማዕ ፡
ጥዩቀ ፡ ነገረ ፡ በኀበ ፡ መርዶክዮስ ፡ ወነገሮ ፡
መርዶክዮስ ፡ ዘከመ ፡ ኮነ ፡ ወዘከመ ፡ ይቤሎ ፡
ሐማ ፡ ለንጉሥ ፡ እልፈ ፡ መካልየ ፡ አበውእ ፡
ውስተ ፡ መዝገቡ ፡ ለንጉሥ ፡ ከመ ፡
ይቅትሎሙ፡ ለአይሁድ ። ወቃለ ፡ ነገራ ፡

ዘንድ ፡ አልወደደችም ፡ ንጉሡም ፡ አዘነ፡
ተቆጣ ፡ ከንግሥትነቷም ፡ ሻራት።

፭፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ መቶ ፡ ሃያ ፡ ሰባት ፡ ከሆኑ ፡ ከሚ
ገዛቸው ፡ አገሮች ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ ቆነጃጅቶችን፡
ይመርጡለት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ ከሽህ ፡ መቶ ፡
ከመቶ ፡ ዐሥር ፡ ከዐሥር ፡ ሦስት ፡ መረጡ ፡
ከሁሉም ፡ በመልክ ፡ በውበት ፡ በደም ፡ ግባት ፡
አስቴር ፡ አንደኛ ፡ ሁና ፡ ተመረጠች።

፮፤ እርሷንም ፡ አነገሠ ፡ ንጉሡም ፡ አስቴርን ፡
እጅግ፡ ወደዳት ፡ አስቴርም ፡ በነገሠ ፡
በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ በፀሥራ ፡ ሁለተኛው ፡
በመጋቢት ፡ ወር ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ አርጤ
ክስስ ፡ ገባች ፡ አስቴርም፡ ንጉሡን ፡ ደስ ፡
አሰኘችው ፡ ከሴቶችም ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ፊጽማ ፡
ባለሟልነትን ፡ አገኘች ፡ የሴቶች ፡ ዘውድንም ፡
አቀዳጃት።

፯፤ ከዚህም ፡ አስቀድሞ ፡ መርዶክዮስ ፡ አገሩንና ፡
አደባባዩን ፡ ከሚጠብቁ ፡ ከንጉሡ ፡ ባለ
ሟሎች ፡ ከሁለቱ ፡ ከታራና ፡ ከገቦታ ፡ ጋራ ፡
በአደባባይ ፡ ኖረ።

፰፤ ያሰቡት ፡ ምክራቸውንም ፡ ሰማ ፡ ንጉሡ ፡ አርጤ
ክስስን ፡ ይገድሉት ፡ ዘንድ ፡ ወንጀልን ፡ እንዳ
ዘጋጁ ፡ አወቀ ፡ ተረዳ ፡ ለንጉሡም ፡ የነሳ
ቸውን፡ ነገር ፡ ነገረው ። ንጉሡም ፡ ሁለቱን ፡
ባለሟሎቹን ፡ መረመራቸው ፡ ኃጢአታቸ
ውንም ፡ አምነው ፡ ተቀጡ።

፱፤ ንጉሡም ፡ ይህንን ፡ ነገር ፡ ወግ ፡ ታሪክ፡ በተጻ
ፈበት ፡ መጽሐፍ ፡ ጻፈው ፡ መርዶክዮስም ፡
ጻፈው።

፲፤ ሐማ ፡ ግን ፡ አማሌቃዊ ፡ ነበረና ፡ መርዶክዮ
ስንና ፡ የእስራኤልን ፡ ወገኖች፡ እጅግ ፡
ይጠላቸው ፡ ነበር ። የአይሁድንም ፡ ወገን ፡
ሁሉንም ፡ ሊአጠፋቸው ፡ ወደደ ፡ ሀገሪቱም ፡
ሁሉ ፡ ታወከች ፡ መርዶክዮስም ፡ እንዲህ ፡
መሆኑን ፡ በአወቀ ፡ ጊዜ ፡ ልብሱን ፡ ቀዶ ፡ ማቅ ፡
ለበሰ።

፲፩፤ አስቴርም ፡ በፊቷ ፡ የሚቆም ፡ ባለሟሏ ፡ አክራ
ትዮስን ፡ ጠርታ ፡ የተረዳ ፡ ነገርን ፡ ይሰማ ፡
ዘንድ ፡ ወደ ፡ መርዶክዮስ ፡ ላከችው ፡ መርዶክ
ዮስም ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ ሐማ ፡ እስራኤልን ፡
ያጠፋቸው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ግጥን ፡
እልፍ ፡ መክሊት ፡ ወርቅን ፡ አገባለሁ ፡ ብሎ ፡
ለንጉሥ ፡ እንደ ፡ ነገረው ፡ ያጠፋቸውም ፡

www.ethiopianorthodox.org

ለይእቲ፡መጽሐፍ፡ዘአንበሩ፡ውስተ፡ሱሳ፡
ከመ፡ይቅትልዎሙ።
፲፪፡ ወሰሚዓ ፡ አስቴር ፡ አግብአቶ ፡ ለዝንቱ ፡
ዘመጽአ ፡ ኅቤሃ ፡ እምኀበ፡ መርዶክዮስ፡
እንዘ፡ ትብል ፡ ሑር ፡ አስተጋብኦሙ ፡
ለአይሁድ ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ሱሳ ፡ ወጹሙ ፡
ሊተ፡ ወኢትብልዑ ፡ ወኢትስተዩ ፡ እስከ ፡
ሠሉስ ፡ ዕለት ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ አነኒ ፡
ወአዋልድየ ፡ ንጸውም ፡ ወእምዝ ፡ እበውእ ፡
ኀበ፡ንጉሥ፡ወእመ፡አኮ፡እመውት፡ሞተ።
፲፫፡ ወእምዝ ፡ አመ ፡ ሣልስት ፡ ዕለት ፡ ሶበ ፡
አኅለቀት ፡ ጸልዮ ፡ አሰሰለት ፡ አልባሲሃ ፡
ወሉብሰት ፡ አልባሰ ፡ ክብራ ፡ ወኮነት ፡
ግርምተ፡ ወጸውዓቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
መድኅነ ፡ ዘውእቱ ፡ ኵሎ ፡ ይሬኢ።
ወነሥአት ፡ ክልኤ ፡ አዋልዲሃ ፡ ለአሐቲሰ ፡
ትምሕካ ፡ እስመ ፡ ታፈቃራ ፡ ወካልዕታ ፡
ትፀውር ፡ አልባሲሃ ፡ ወትተልዋ፡ ይእቲሰ ፡
ተሠነየት ፡ በኵሉ ፡ ወተሠርገወት ፡ ወተረ
ሰየት፡ወኮነ፡ገጸ፡ፍሡሐ፡ከመ፡ዘተሐውር፡
ኀበ፡ አእርክቲሃ ፡ ወልባሰ ፡ ኅዙን ፡ እምፍ
ርሀተ ፡ ሞት ፡ ወቦአት ፡ ኵሎ ፡ ኆኅተ ፡
ወበጽሐት፡ኀበ፡ንጉሥ፡ውእቱሰ፡ይነብር፡
ዲበ፡መንበረ፡መንግሥቱ።

፲፬፡ ወልቡስ፡ውእቱ፡አልባሰ፡ግርማሁ፡ወኵለ
ንታሁ፡በወርቅ፡ወበዕንቍ፡ዘብዙኅ፡ሤጡ፡
ወግሩም፡ውእቱ፡ጥቀ፡ወተመይጠ፡ገጹ፡
ምስለ፡ውእቱ፡ክብሩ፡ወነጸራ፡በመዓት፡
ወፈርሀት፡ወመጽለወት፡ወተንተነት፡ወአ
ስመከት ፡ ላዕለ ፡ ርእሰ ፡ ወለታ፡ እንተ ፡
ተሐውር ፡ ቅድሜሃ። ወሜጠ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ መንፈሶ ፡ ለንጉሥ፡ መንገለ ፡
የውሃት፡ወተዓገሣ፡ወተንሥአ፡እመንበሩ፡
ወሰሐባ፡ወአንበራ፡ውስተ፡ሕፅኑ፡ወአኀዘ፡
ይዬውሃ፡በቃል፡ሠናይ፡ወይቤላ፡ምንተ፡
ኮንኪ ፡ አስቴር ፡ አነ፡ እኁኪ ፡ ከመ ፡
ኢትሙቲ፡እስመ፡እኩይ፡ሕገ፡ብሔርነ።
ወአንሥአ፡በትሮ፡እንተ፡ወርቅ፡ወአንበረ፡
ውስተ፡ክሣዳ፡ወሐቀፉ፡ወይቤላ፡ንግርኒ፡
ወትቤሎ፡ሶበ፡ርኢኩከ፡እግዚእየ፡ከመ፡
መልአከ፡እግዚአብሔር፡ደንገፀኒ፡ልብየ፡
እምፍርሀተ፡ ክብርከ ፡ እስመ ፡ መድምም ፡

ዘንድ ፡ በሱሳ፡ አገር፡ ያኖራትን ፡ የደብዳቤ
ዪቱን፡ቃል፡ነገረው።
፲፪፡ አስቴርም፡በሰማች፡ጊዜ፡በሱሳ፡ያሉ፡እስራ
ኤልን ፡ ሒደህ ፡ ሰብስብልኝ ፡ ጹሙልኝ ፡
እስከ፡ሦስት፡ቀን፡ድረስ፡ቀንም፡ሌሊትም፡
አትብሉ፡አትጠጡ፡እኔና፡ደንገጡሮቼም፡
እንጾማለን፡ከዚህም፡በኋላ፡ወደ፡ንጉሥ፡
እገባለሁ፡እሞትም፡እንደሆነ፡አልቀርም፡
ብላ፡ከመርዶክዮስ፡ወደርሷ፡የመጣውን፡
ያንን፡መልእክተኛ፡መለሰችው።
፲፫፡ ከዚህም፡በኋላ፡በሦስተኛው፡ቀን፡ጸሎቷን፡
በጨረሰች ፡ ጊዜ ፡ የኀዘን ፡ ልብሷን ፡
አስወግዳ፡ የተድላ ፡ ደስታዋን ፡ ልብስ ፡
ለበሰች፡የምታስፈራም፡ሆነች፡ሁሉን፡የሚ
መለከትና ፡ የሚያድን ፡ እግዚአብሔርን ፡
ጠራችው ፡ ሁለቱን ፡ ደንገጡሮቿን ፡
አስከትላ ፡ ሔደች ፡ አንዲቱን ፡ ትወዳ
ትና፡ ትራራላት ፡ ነበር ፡ ሁለተናዩቱ ፡ ግን ፡
ልብሷን፡ ተሸክማ ፡ ትከተላት ፡ነበር፡
እርሷ ፡ ግን ፡ በጌጡ ፡ ሁሉ ፡ ፈጽማ ፡ አጊጣ ፡
አምሮባት ፡ ነበር ፡ ወደ፡ ወዳጆቿ፡ እንደም
ትሔድ፡ፊቷም፡የሚያበራ፡ሆነ፡ልቧ፡ግን፡
ሞትን፡ከመፍራት፡የተነሣ፡አዝኖ፡ነበር፡
በሩን፡ሁሉ፡ገብታ፡ወደ፡ንጉሡ፡ደረሰች፡
እርሱም፡በጌትነቱ፡ዙፋን፡ላይ፡ነበር።
፲፬፡ ዋጋው፡ብዙ፡የሆነ፡ሁለንተናው፡ወርቅና፡
ዕንቍ፡ያለበት፡የሚያስፈራ፡ልብስ፡ለብሶ፡
ነበር፡ ፈጽሞም፡ ያስፈራ፡ ነበር፡ ፊቱም፡
ተለውጦ ፡ በዓይነ ፡ መዓት ፡ አያት ፡ንግ
ሥቲቱም ፡ ከፍርሃት ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡
ቅጠል፡ ጠወለገች ፡ ለመውደቅም ፡ ተፍገ
ምግማ፡በፊቷ፡የምትሔድ፡የብላቴናዋን፡
ራስ ፡ ተደገፈች ። እግዚአብሔርም ፡
የንጉሡን፡ልቡና፡ወደ፡የዋህነት፡መልሶት፡
ታገሣት ፡ ከዙፋኑም ፡ ተነሥቶ ፡ ስቦ፡
በአጠገቡ ፡ አስቀመጣት ፡ በበጎ ፡ ቃልም ፡
ያባብላት፡ጀመር፡ያገራችን፡ሥርዓት፡ልዩ
ነውና፡እንዳትሞቺ፡እኔ፡ወንድምሽ፡ነኝ፡
አላት ። የወርቁንም ፡ በትር ፡ አንሥቶ ፡
በአንገቷ፡ላይ፡አኖረው፡እቅፍ፡አድርጎ፡
ይዞም፡ንገሪኝ፡አላት፡አንተ፡ድንቅ፡ነህና፡
ፊትህም፡መፈራትን፡የተመላ፡ነውና፡ከጌት
ነትህ፡ግርማ፡የተነሣ፡እንደ፡መልአከ፡እግ

አንተ፡ወገጽከኒ፡ምሉዐ፡ሞገስ።

፲፭፡ ወይቤላ፡ንጉሥ፡ምንተ፡ትፈቅዲ፡አስቴር፡ ወበእንተ፡ምንት፡ዘታስተበቍዕኒ፡እስከ፡ መንፈቀ ፡ መንግሥትየ ፡ ንሥኢ ፡ ለኪ ፡ ይኩንኪ፡ወትቤሎ፡አስቴር፡እስመ፡ዕለተ፡ በዓል ፡ ብየ ፡ እመሰ ፡ ፈቀድከ ፡ ንጉሥ ፡ ትምጻእ፡ ውስተ፡ በዓልየ ፡ ዘእገብር ፡ዮም ፡ አንተ ፡ ወሐማ። ወይቤ ፡ ንጉሥ ፡ጸውዕዎ ፡ ለሐማ፡ ፍጡነ ፡ ከመ ፡ እግበር ፡ ዘትቤለኒ ፡ አስቴር ፡ ወሖሩ ፡ ክልኤሆሙ ፡ ውስተ ፡ በዓል፡ዘገብረት፡አስቴር።

፲፮፡ ወበውስተ ፡ በዓልኒ ፡ ይቤላ ፡ ንጉሥ ፡ ለአስቴር፡ ምንተ ፡ ትፈቅዲ ፡ አስቴር ፡ ንግሥት ፡ ዘታስተበቍዕኒ ፡ እግበር ፡ ለኪ ፡ ወትቤሎ ፡ ስእለትየሰ ፡ ዘአስተበቍዐከ ፡ እመ፡ረከብኩ፡ሞገሰ፡በቅድመ፡አዕይንቲከ፡ ኦ፡ንጉሥ፡ከመ፡ትምጻእ፡አንተ፡ወሐማ፡ ጌሠመ፡ውስተ፡በዓል፡ዘእገብር፡ለክሙ፡ ወጌሠመ፡እገብሮ።

፲፯፡ ወአንፈጸ፡እግዚአብሔር፡ንዋመ፡እምኔሁ፡ ለንጉሥ ፡ በይእቲ ፡ ሌሊት ፡ ወይቤሎ ፡ ለጸሐፊሁ ፡ ያምጽእ ፡ ሎቱ ፡ መጻሕፍተ ፡ ተዝካር ፡ ዘኖብያት ፡ ዘመዋዕለ ፡ ትካት ፡ ወያንብብ ፡ ሎቱ ፡ ዘውስተ ፡ መጻሕፍት። ወእምዝ፡ረከቡ፡ዘጸሐፉ፡ውስተ፡መጽሐፍ፡ በእንተ ፡ መርዶክዮስ ፡ ዘከመ ፡ ዜነዎ ፡ ለንጉሥ፡በእንተ፡ክልኤቱ፡ሕፅዋኒሁ፡እለ፡ የዓቅብዎ፡ለንጉሥ፡ወፈቀዱ፡ይቅትልዎ፡ ለአርጤክስስ፡ንጉሥ፡።

፲፰፡ ወይቤ፡ንጉሥ፡አይ፡ክብር፡ወጸጋ፡ዘገበርነ፡ ሎቱ ፡ ለመርዶክዮስ ፡ ወይቤልዎ ፡ ደቁ ፡ ለንጉሥ፡አልቦ፡ዘተገብረ፡ሎቱ፡እግዚኦ፡ ወእንዘ ፡ ይትናገር ፡ ንጉሥ ፡ በእንተ ፡ አኰቴቱ ፡ ለመርዶክዮስ ፡ በጽሐ ፡ ሐማ ፡ ውስተ ፡ ዐፀድ ፡ ወይቤ ፡ ንጉሥ ፡ መኑ ፡ ዘውስተ፡ዐፀድ፡ወይቤልዎ፡ሐማ፡ውእቱ፡ ወእምዝ ፡ ቦአ ፡ ሐማ ፡ ይንግሮ ፡ ለንጉሥ ፡ ከመ፡ይስቅሎ፡ለመርዶክዮስ፡ውስተ፡ዕፅ፡ ዘአስተዳለወ፡ወይቤልዎ፡ደቁ፡ለንጉሥ፡ ናሁ ፡ ሐማ ፡ ይቀውም ፡ ውስተ ፡ ዐፀድ ።

ዚአብሔር፡ሁነህ፡በአየሁህ፡ጊዜ፡ልቤ፡ደነ ገጠበኝ፡አለችው።

፲፭፡ ንጉሡም፡አስቴር፡ምን፡ትፈልጊ ያለሽ፡የም ትማልጅኝስ ፡ ምንድን ፡ ነው፡ ላንቺ ፡ ይሆንሽ፡ ዘንድ ፡ እስከ ፡ መንግሥቴ ፡ እኩሌታ፡ውሰጂ፡አላት፡አስቴርም፡በዓል፡ የማድርግበት፡ቀን፡አለኝና፡ንጉሥ፡ዛሬ፡ ወደማደርገው፡ በዓል ፡ ትመጣ ፡ ዘንድ ፡ ከፈቀድክ ፡ ሐማና ፡ አንተ ፡ ኑ፡ አለችው ። ንጉሡም ፡ አስቴር ፡ ያለችኝን ፡ አደርግ፡ ዘንድ፡ ፈጥናችሁ ፡ ሐማን ፡ ጥሩት ፡ አለ ፡ ሁለቱም፡ሁሉ፡አስቴር፡ወደ፡አደረገችው፡ በዓል፡ሔዱ።

፲፮፡ በዓልም ፡ በተደረገበት ፡ ቀን ፡ ንጉሡ ፡ አስቴርን፡ንግሥት፡አስቴር፡ሆይ፡የለመን ሽኝን፡አደርግልሽ፡ዘንድ፡ምን፡ትፈልጊ ያለሽ፡አላት።ንጉሥ፡ሆይ፡በፊትህ፡ባለሟ ልነትን፡ካገኘሁ፡የምለምንህ፡ልመናዬ፡ አንተ፡ከሐማ፡ጋር፡ወደ፡ማደርገው፡በዓል፡ ነገ፡ትመጣልኝ፡ዘንድ፡ነው፡ይህንንም፡ነገ፡ አደርገዋለሁ፡አለችው።

፲፯፡ እግዚአብሔርም፡በዚያች፡ሌሊት፡ከንጉሡ፡ እንቅልፍን፡አጠፋ፡የቀድሞ፡ዘመን፡ወግ፡ ታሪክ ፡ የሚያሳስቡ፡ መጻሕፍትን ፡ ያመጣለት ፡ ዘንድ ፡ በመጽሐፉም ፡ የተጻ ፈውን ፡ ያነብለት ፡ ዘንድ ፡ ጸሐፊውን ፡ አዘዘው ።ከዚህም፡በኋላ፡በመጽሐፉ፡ስለ፡ መርዶክዮስ ፡ የጻፉትን ፡ ነገር ፡ አገኙ ፡ ንጉሡን ፡ የሚጠብቁ ፡ ንጉሥ፡ አርጤክ ስስን፡ ይገድሉት ፡ ዘንድ ፡ የወደዱ ፡ የሁለቱን፡ የንጉሡን ፡ ባለሟሎች ፡ ነገር ፡ ለንጉሡ፡እንደ፡ነገረው፡አገኙ።

፲፰፡ ንጉሡም ፡ ለመርዶክዮስ ፡ ያደረግንለት ፡ ስጦታና፡ ክብር ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ አለ ፡ የንጉሥ፡ አሽከሮችም ፡ አቤቱ ፡ ለመርዶ ክዮስ ፡ የተደረገለት ፡ ነገር ፡ የለም፡ አሉ ፡ ንጉሡም ፡ የመርዶክዮስን ፡ ምስጋና ፡ ሲናገር፡ ሐማ ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ግቢ ፡ ደረሰ ፡ ንጉሡም፡በአደባባይ፡ያለ፡ይህ፡ማን፡ነው፡ አለ፡ ሐማ፡ ነው ፡ አሉት። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሐማ፡ በአዘጋጀው ፡ ተራዳ ፡ መርዶክዮስን ፡ ሊሰቅለው፡ለንጉሡ፡ይነግረው፡ዘንድ፡ገባ፡ አሽከሮቹም ፡ ንጉሡን ፡ እነሆ ፡ ሐማ፡ በአደ

www.ethiopianorthodox.org

ወይቤሎሙ፡ ንጉሥ ፡ ጸውዕዎ ፡ ወይቤሎ ፡ ንጉሥ ፡ ለሐማ ፡ ምንተ ፡ እግበር ፡ ሎቱ ፡ ለብእሲ ፡ ዘአነ፡ እፈቅድ ፡ አክብሮ ፡ ወይቤ ፡ ሐማ ፡ በልቡ ፡ መኑ ፡ ይፈቅድ ፡ ንጉሥ ፡ ያክብር ፡ ዘእንበለ ፡ ኪያየ ፡ ወይቤሎ ፡ ለንጉሥ፡ ለብእሲ ፡ ዘይፈቅድ ፡ ንጉሥ ፡ ያክብሮ ፡ ያምጽኡ ፡ ሎቱ ፡ ደቂቀ፡ ንጉሥ፡ ሜላተ ፡ ዘይለብስ ፡ ንጉሥ ፡ ወፈረሰ ፡ ዘይጼዓን፡ንጉሥ፡ወየሀብዎ፡ለአሐዱ፡እም አዕርክቲሁ፡ለንጉሥ፡እለ፡ክቡራን፡ወያልብስዎ፡ለውእቱ፡ብእሲ፡ዘአክበሮ፡ንጉሥ፡ ወያጽዕንዎ፡ዲበ፡ፈረሱ፡ወይስብክ፡ሎቱ፡ ዓዋዲ ፡ ውስተ፡ መርህበ ፡ ሀገር ፡ እንዘ ፡ ይብል፡ ከመዝ ፡ ይከውን ፡ ሎቱ ፡ ለብእሲ ፡ ዘንጉሥ፡አክበሮ።

፲፱፡ ወይቤሎ፡ንጉሥ፡ለሐማ፡ሠናየ፡ትቤ፡ግበር፡ ከማሁ፡ ለመርዶክዮስ ፡ አይሁዳዊ ፡ ዘይጸመድ ፡ ውስተ ፡ ዐፀድ ፡ ወኢትኅድግ ፡ አሐተ ፡ ቃለ ፡ እምዘነበብከ። ወነሥአ ፡ ሐማ፡ አልባሰ፡ወፈረሰ፡ወአልበሶ፡ለመርዶክዮስ፡ ወአጽዓኖ ፡ ዲበ ፡ ፈረስ ፡ ወአየዶ ፡ ውስተ ፡ መርህበ ፡ ሀገር ፡ ወሰበከ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ከመዝ ፡ ይሬሲ ፡ ለኵሉ ፡ ብእሲ ፡ ዘፈቀደ ፡ ንጉሥ፡ያክብሮ።

፳፡ ወእምዝ ፡ ቦኡ ፡ ንጉሥ ፡ ወሐማ ፡ ይምስሑ ፡ ምስለ፡ንግሥት፡አስቴር፡ ወይቤላ፡ንጉሥ፡ ለአስቴር ፡ አመ፡ ሳኒታ ፡ በዓል ፡ ምንተ ፡ ኮንኪ፡አስቴር፡ወምንት፡ውእቱ፡ዘታስተበቊዕኒ ፡ ሶበሰ፡ ፈቀድኪ ፡ መንፈቀ፡ መንግሥትየ ፡ እምወሀብኩኪ ፡ ወአውሥአቶ ፡ ወትቤሎ ፡ እመሰ ፡ ረከብኩ፡ ሞገሰ ፡ በቅድሜከ፡ኦ፡ንጉሥ፡ይትወሀባ፡ለነፍስየ፡ ስእለታ። እስመ፡ተሠየጥነ፡አነ፡ወሕዝብየ፡ ወኮነ ፡ ለሞት ፡ ወለተበርብሮ ፡ እመሰ ፡ ለተቀንዮ፡እምአርመምኩ።

፳፩፡ ወይቤ ፡ ንጉሥ ፡ መኑ ፡ ውእቱ ፡ ዝንቱ፡ ዘተሀበለ፡ይግበር፡ዘንተ፡ግብረ። ወትቤ፡ አስቴር ፡ ብእሲ ፡ ጸላኢነ፡ ሐማ፡ ወሰሚያ ፡ ሐማ ፡ ፈርሀ ፡ እምነ ፡ ንጉሥ ፡ ወእምነ ፡ ንግሥት ፡ ወተንሥአ ፡ ንጉሥ ፡ እምኀበ ፡ ይሰቲ ፡ ወቦአ ፡ ውስተ ፡ ገነት፡ ወሐማሰ ፡

ባባይ ፡ ቁሚል ፡ አሉት ፡ ንጉሡም ፡ ጥሩት ፡ አላቸው ፡ ንጉሡም ፡ ሐማን ፡ አክብረው ፡ ዘንድ፡እኔ፡ለወደድሁት፡ሰው፡ምን፡ላደርግለት ፡ አለው። ሐማም ፡ በልቡ ፡ ንጉሡ ፡ እኔን፡ነው፡እንጂ፡ያለእኔ፡ማንን፡ያከብር፡ ዘንድ ፡ ይወዳል ፡ ብሎ፡ ያከብረው፡ ዘንድ ፡ ንጉሥ፡ለወደደው፡ሰው፡ንጉሡ፡የሚለብሰውን ፡ ነጭ ፡ ሐር ፡ ንጉሥ ፡ የሚቀመጥበትንም ፡ ፈረስ ፡ የንጉሥ ፡ አሽከሮች ፡ ያምጡለት ፡ አለው። ክብር ፡ ካላቸው ፡ ከንጉሥ ፡ ባለሟሎች ፡ ለአንዱ ፡ ይስጡት ፡ ንጉሥ ፡ ላከበረው ፡ ለዚያ ፡ ሰውም ፡ ያልብሱት ፡ በፈረሱም ፡ ያስቀምጡት ፡ ንጉሥ ፡ ላከበረው፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ ይደረግለታል ፡ ብሎ፡ አዋጅ ፡ ነጋሪ ፡ ይንገርለት አለው።

፲፱፡ ንጉሡም፡ሐማን፡በጎ፡ነገርን፡ተናገርህ፡በአደባባይ፡ለሚያገለግል፡ለአይሁዳዊ፡መርዶክዮስ ፡ እንዲሁ ፡ አድርግለት ፡ ከተናገርከውም ፡ ነገር ፡ አንዲት ፡ ቃልን ፡ ስንኳ ፡ አታስቀር ፡ አለው ፡ ሐማም ፡ ልብስን ፡ አምጥቶ ፡ ለመርዶክዮስ ፡ አለበሰው ፡ ፈረስንም ፡ አምጥቶ ፡ አስቀመጠው ፡ ለወደደው፡ሰው፡ሁሉ፡ንጉሥ፡እንዲህ፡ያደርግለታል ፡ ብሎ ፡ በከተማው ፡ አደባባይ ፡ አዋጅ፡ነገረለት።

፳፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ንጉሡና ፡ ሐማ ፡ ከንግሥት ፡ አስቴር፡ ጋር፡ምሳ፡ሊበሉ፡ገቡ። ንጉሡም፡ በሁለተኛው፡በዓል፡አስቴር፡ምን፡ሆንሽ፡ የምትማልጂኝስ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ከወደድሽስ ፡ የመንግሥቴን ፡ እኩሌታ ፡ በሰጠሁሽ፡ ነበር ፡ አላት ፡ እንዲህም፡ ብላ ፡ መለሰችለት፡ንጉሥ፡ሆይ፡በፊትህስ፡ባለሟልነትን ፡ ካገኘሁ ፡ ለሰውነቴ ፡ ልመናዋ ፡ ይሰጣት፡ወገኖቼና፡እኔ፡ተሸጠናልና፡ለመበርበርና ፡ ለሞትም፡ ሁነናልና ፡ ለመገዛት ፡ ቢሆን፡ዝም፡ባልኩ፡ነበር።

፳፩፡ ንጉሡም፡ይህን፡ሥራ፡ይሠራ፡ዘንድ፡የተደፋፈረ፡ማን፡ነው፡አለ፡አስቴርም፡ጥንተ፡ ጠላታችን ፡ ሐማ ፡ ነው ፡ አለች ፡ ሐማም ፡ ይህን ፣ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ከንግሥቲቱና ፡ ከንጉሡ፡ የተነሣ፡ ፈራ። ንጉሡም ፡ ከሚጠጣበት፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ተክል ፡ ቦታ ፡ ገባ ፡

ወድቀ፡ውስተ፡ዓራታ፡ወይትጋነይ፡ላቲ፡ ለንግሥት፡ ወገቢአ ፡ ንጉሥ ፡ እምገነቱ፡ ይቤሎ፡ለሐማ፡ትትዔገለኒኑ፡ብእሲትየ፡ በቤትየ፡ወሶበ፡ሰምዐ፡ሐማ፡ጸልመ፡ገጹ።

፳፱፡ ወይቤሎ፡ቡግታን፡አሐዱ፡እምሕፅዋኒሁ፡ ለንጉሥ፡ሀለወ፡ዕፅ፡ዘአስተደለዎ፡ለመርዶ ክዮስ፡ዘአይድዐ፡በእንተ፡ንጉሥ፡ዕፅሰ፡ ትኩል፡ውስተ፡ቤቱ፡ለሐማ፡ዘኃምሳ፡ በእመት፡ኑኁ፡ወይቤ፡ንጉሥ፡ይስቅልዎ፡ ቦቱ።

፴፡ እስመ፡በእንቲአሃ፡ኮነ፡ድኅነቶሙ፡ለኵ ሎሙ፡ሕዝበ፡እስራኤል፡ወስብሐት፡ለእግ ዚአብሔር፡ለዓለም፡ዓለም፡አሜን።

ሐማ፡ ግን ፡ መከራ ፡ እንደደረሰችበት ፡ አውቋልና ፡ በንግሥቲቱ ፡ ዙፋን ፡ ሥር ፡ ወድቆ ፡ ይለማመጥ ፡ ነበር ፡ ንጉሡም፡ ከተክል፡ቦታ፡ሲመለስ፡ሐማን፡ሚስቴን፡ በቤቴ፡ትጋፋኛለህን፡አለው፡ሐማም ፡ በሰማ፡ጊዜ፡ፊቱ፡ጠቆረ።

፳፱፡ ከንጉሥ ፡ ባለሟሎች ፡ አንዱ ፡ ቡግታን ፡ የንጉሡን፡ነገር፡የተናገረ፡መርዶክዮስን፡ ሊሰቅልበት ፡ ያዘጋጀው ፡ ተራዳ ፡ አለ ፡ ቁመቱ፡ኃምሳ፡ክንድ፡የሆነ፡ዕንጨት፡ በሐማ፡ቤት፡ተተክሏል፡አለው፡ንጉሡም፡ በሱ፡ይስቀሉት፡አለ።

፴፡ የእስራኤል፡ወገኖች፡ሁሉ፡ድኅነታቸው፡ በእርሷ፡ተደርጓልና፡ለእግዚአብሔርም፡ ምስጋና፡ይሁን፡ለዘላለሙ፡አሜን።

<u>አርኬ፡</u>

ሰላም፡ለአስቴር፡እንተ፡ሞአቶ፡በጥበባ።ለመልአከ፡ውዱት፡ዘያጽሕባ።እግዚአብሔር፡ሥመር፡ ዘሠመርከ፡ነገደ፡ሕዝባ።በወርኀ፡አፀባ፡ከመ፡ትትሐፀን፡በጥባ።ደክታም፡ነፍስየ፡እምእማ፡ወአባ።

፴፩፡ ወበዛቲ፡ዕለት፡አዕረፈ፡አባ፡ጳውሊ፡ዘተ ዋሥአ፡ለሰይጣን፡በሀገረ፡ምስር፡እንተ፡ ትሰመይ፡ሰሎንቅያ።

፴፪፡ ወለይእቲ፡ሀገር፡ሰብአ፡ዚአሃ፡እምዘመደ፡ ሔሮድስ፡እኩያን፡እሙንቱ፡ወቦሙ፡ሕግ፡ ወይበውኡ፡ውስተ፡ቤተ፡ብለኔ፡ዕድ፡ ወአንስት፡ኅቡረ። ወይበይቱ፡ወበጽሐ፡ ውስተ፡ይእቲ፡ሀገር፡አባ፡ጳውሊ፡ወም ስሌሁ፡ዲያቆን፡ወሬዛ፡ወረከቦሙ፡በዕለተ፡ ረቡዕ፡እንዘ፡ይበውኡ፡እድ፡ወአንስት፡ ውስተ፡ቤተ፡ብለኔ፡ኅቡረ፡ወርእዮ፡አባ፡ ጳውሊ፡አንከረ፡ወይቤሎ፡ለአሐዱ፡እም ኔሆሙ፡ለምንት፡ትገብሩ፡ዘንተ፡ግብረ፡ ሕሱመ፡ወይቤሎ፡ውእቱ፡ብእሲ፡እስመ፡ አበዊነ፡ነበሩ፡እንዘ፡ይገብሩ፡ዘንተ፡ ወንሕነኒ፡ንገብር፡ከማሆሙ።

፴፫፡ ወከዊኖ፡ሌሊተ፡አኀዘ፡አባ፡ጳውሊ፡ይጸሊ፡ ኀበ፡እግዚአብሔር፡በሕማመ፡ልብ፡ከመ፡ ይቅሥፎሙ፡በመቅሠፍት፡ዐቢይ፡ወሶበ፡ ፈጸመ፡ጸሎቶ፡ርእየ፡ብእሴ፡ጸሊመ፡ ወመጽአ፡ዕራቆ፡እምቤተ፡ብለኔ፡እንዘ፡ ይፀውር፡ሰይፈ፡እሳት፡ወይቤሎ፡አባ፡ ጳውሊ፡መኑ፡አንተ፡ወምንተ፡ተኃሥሥ።

፴፩፡ በዚችም፡ዕለት፡ሰሎንቅያ፡በምትባል፡ በምስር፡አገር፡ሰይጣንን፡ያነጋገረው፡አባ፡ ጳውሊ፡አረፈ።

፴፪፡ የዚያችም፡አገር፡ሰዎች፡የሔሮድስ፡ወገን፡ የሆኑ፡ክፉዎች፡ናቸው፡ለእነርሱም፡ሕግ፡ አላቸው፡ሴቶችና፡ወንዶች፡በአንድነት፡ ከውሽባ፡ቤት፡ገብተው፡ያድራሉ፡አባ፡ ጳውሊም፡ወደዚያች፡አገር፡ደረሰ፡ከር ሱም፡ ጋር፡ጐልማሳ፡ዲያቆን፡ነበረ፡ በረቡዕ፡ ቀንም፡ሴቶችና፡ወንዶች፡በአን ድነት፡ወደ፡ ውሽባ፡ቤት፡ሲገቡ፡አይቶ፡ አደነቀ፡ከእርሳቸውም፡አንዱን፡ለምን፡ ይህን፡የከፋ፡ ሥራ፡ ትሠራላችሁ፡አለው፡ ያም፡ሰው፡አባቶቻችን፡እንዲህ፡ሲሠሩ፡ ኖሩ፡እኛም፡እንደነርሱ፡እንሠራለን፡ አለው።

፴፫፡ ሌሊትም፡በሆነ፡ጊዜ፡በታላቅ፡መቅሠፍት፡ ይቀሥፋቸው፡ዘንድ፡በአዘነ፡ልቡና፡ወደ፡ እግዚአብሔር፡ይጸልይ፡ጀመር። ጸሎ ቱንም፡ ሲፈጽም፡ጥቁር፡ሰው፡ከውሽባ፡ ቤት፡ዕራቁቱን፡የእሳት፡ሰይፍ፡ተሸክሞ፡ መጣ። አባ፡ጳውሊም፡አንተ፡ማን፡ነህ፡ ማንንስ፡ ትሻለህ፡አለው፡እኔ፡ሰይጣን፡ነኝ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወይቤ፡አነ፡ሰይጣን፡ፈነወኒ፡እግዚእ፡ሶበ፡ ሰአልከ : ኀቤሁ : ወይቤሎ : አባ : ጳውሊ : እሴአለከ : ከመ : ትንግረኒ : ኵሎ፡ አስሕ ቶተከ : ወይቤሎ : ሰይጣን : ተሰአል : ዘት ፈቅድ : ወይቤሎ : አባ : ጳውሊ : እፎ : ትረክብ : ምክንያተ : ከመ : ትባእ : ውስተ : ሰብእ፡ዘእንበለ፡ፈቃደ፡እግዚአብሔር።

፳፯፡ወይቤሎ፡ሰይጣን፡አልብነ፡ሥልጣን፡ከመ፡ ንባእ : ውስተ : ሰብእ : እንዘ : ሀሎ : በፍኖተ : እግዚአብሔር : ወላዕለ : ዘይጼውዕ፡ ስመ : አብ : ወወልድ : ወመንፈስ፡ ቅዱስ : ወላዕለ : ዘይትጤጦ : ሥጋሁ : ወደሞ፡ ለክርስቶስ : በንጽሕ።

፳፰፡ ወእምዝ : ነገሮ : ኵሎ : አስሕቶቶ : ወሶቤሃ : ነጸረ : አባ : ጳውሊ : ከመ : ተወለጠ : ኀብሩ : ለሰይጣን : ወኮነ : ከመ : ነበልባለ : እሳት : ወደንገፀ : አባ : ጳውሊ : ወበጊዜሃ : ወረደ : መልአከ : እግዚአብሔር : ወአስተርአዮ : ወአጽንዖ።

፳፱፡ ወበይእቲ : ሌሊት : ወረደ : መቅሠፍት : እም እግዚአብሔር፡ ወአጥፍአሙ : ለእለ : ሀለው : ውስተ : ቤተ : ብለኔ : ወኢ.ተርፉ : ዘእንበለ : ኃምስቱ፡ዕደው፡ወኃምስ፡አንስት።

፴፡ ወይቤሎሙ : አባ : ጳውሊ : ለምንት : ትገብሩ : ከመዝ : ወይቤልዎ : እስመ : አበዊነ : አዘዙነ : ከመ : ንባእ : ውስተ : ቤተ : ብለኔ : ለለወርኁ : አሐተ : ዕለተ : ወንግበር : ፍሥሓ : ምስለ : አንስቲያነ : ወነዐጹ : ኖኅተ : ወናጠፍእ : ማኅቶተ : ወንሰክብ : ምስለ : ብእሲት : ዘቦአት : ውስተ : እዴነ : ወይቤሎሙ : እፎ : የአምር : እምኔክሙ : ወለቶ : አው : እኅቶ : ወይቤልዎ : አልቦ : አላ : ኮነ : ከመ : እንስሳ።

፴፩፡ ወእምዝ : መሀሮሙ : አባ : ጳውሊ : ሃይማኖተ : ክርስቶስ : ሎቱ : ስብሐት : ወአጥ መቆሙ : ጥምቀተ : ክርስትና : ወመጠዎሙ : ምሥጢረ : ቅድሳት : ወእምዝ : ሖረ : ኀበ : በዓቱ : ወፈጸሞ : ተጋድሎቶ : ፈለሰ : ኀበ : እግዚአብሔር : በርሥእ : ጥሉል።

፴፪፡ ወስብሐት : ለእግዚአብሔር : ኪያነኒ : ይም ሐረነ : በጸሎቱ : ወበረከቱ : ተሀሉ : ምስሌነ : ለዓለመ : ዓለም : አሜን።

አንተ : ወደርሱ : በለመንክ : ጊዜ : ጌታ : ላከኝ፡ አለ። አባ : ጳውሊም : የምታስትበትን : ሁሉ : ትነግረኝ : ዘንድ : እጠይቅሃለሁ : አለው ። ሰይጣንም : የምትሻውን : ጠይቅ : አለው : አባ : ጳውሊም : ያለ : እግዚአብሔር : ፈቃድ : በሰው : ላይ : ታድር : ዘንድ : ምክ ንያት : እንዴት : ታገኛለህ : አለው።

፳፯፡ ሰይጣንም : ሰው : በእግዚአብሔር : ሕግ : ጸንቶ : ሳለ : የአብ : የወልድ : የመንፈስ : ቅዱስን : ስም : በሚጠራ : በንጽሕና : ሁኖ : የክርስቶስን : ሥጋና : ደምን፡ በሚቀበል : ላይ : ለማደር : ሥልጣን : የለንም : አለው።

፳፰፡ ከዚህም : በኋላ : የሚያስትበትን : ሁሉ : ነገረው : በዚያንም : ጊዜ : የሰይጣን : መልኩ : ተለውጦ : እንደ : እሳት : ነበልባል : ሲሆን : አባ : ጳውሊ : ተመልክቶ : ደነገጠ : ወዲያውኑ : ከእግዚአብሔር : የታዘዘ : መል አክ : ተገለጸለትና : አጽናናው።

፳፱፡ በዚያችም : ሌሊት : ከእግዚአብሔር : የታ ዘዘ፡ መቅሠፍት : ወርዶ : በውሽባ : ቤት : ያሉትን : አጠፋቸው : ከአምስት : ወንዶ ችና፡ ከአምስት : ሴቶች : በቀር : አልተ ረፉም።

፴፡ አባ : ጳውሊም : ለምን : እንዲህ : ታደርጋ ላችሁ፡ አላቸው ። በየወሩ : አንዲት : ቀን : ወደ : ውሽባ : ቤት : እየገባን : ከሚስቶቻችን : ጋር : ተድላ : ደስታ : እንድናደርግ : አባቶ ቻችን : አዘዙን : በሩንም : ዘግተን : መብራ ትንም : አጥፍተን : ከእጃችን : የገባችዋን : ሴት : ይዘን : እንተኛለን : አሉት። ከእናንተ : ውስጥ ልጁን : ወይም : እህቱን : እንዴት : ያውቃል : አላቸው ። እንደ : እንስሳ : በመሆን : እንጃ : ማወቅ : የለም : አሉት።

፴፩፡ ከዚህም : በኋላ : አባ : ጳውሊ : የክብር : ባለቤት : የሆነ : የክርስቶስን : ሃይማኖት : አስ ተምሮ : የክርስትና : ጥምቀትን : አጠመ ቃቸው : ሥጋውንና : ደሙንም : አቀበ ላቸው፡ ከዚህም : በኋላ : ወደ : በዓቱ፡ ተመ ልሶ : ገድሉን : በፈጸመ : ጊዜ : በመልካም : ሽምግልና : ወደ : እግዚአብሔር : ሔደ።

፴፪፡ ለእግዚአብሔርም : ምስጋና : ይሁን : እኛንም : በጸሎቱ : ይማረን : በረከቱም : ከእኛ : ጋር : ትኑር : ለዘላለሙ : አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

## አርኬ

ሰላም ፡ ለጳውሊ ፡ ለሰይጣን ፡ ዘቀነዮ ። ለዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ዘይጌግዮ ። ወለአቦሊ ፡ ሰላም ፡ ዘነበረ ፡ በጸልዮ ። እንዘ ፡ ኢይሔሊ ፡ ዘዕለት ፡ ሲሳዮ ። እለ ፡ ኢይዘርዑ ፡ አዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡ ርእዮ ።

፴፫ ፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ ቅዱስ ፡ ወክቡር ፡ አግናጥዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘአንጾኪያ

፴፬፤ ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ረድኡ ፡ ለዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ወተልእኮ ፡ በስብከተ ፡ ወንጌል ፡ ወሖረ ፡ ምስሌሁ ፡ አህጉረ ፡ ብዙኃተ ፡ ወእምዝ ፡ ሤሞ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ላዕለ ፡ ሀገረ ፡ አንጾኪያ ፡ ወሰበከ ፡ ውስቴታ ፡ በስብከተ ፡ ወንጌል ፡ ማሕየዊ ፡ ወሜጠሙ ፡ ለብዙኃን ፡ ውስተ ፡ አእምሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአጥመቆሙ ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ ወአብርሀ ፡ አልባቢሆሙ ።

፴፭፤ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ከሠተ ፡ ሎሙ ፡ ስሕተቶሙ ፡ ለእለ ፡ ያመልኩ ፡ ጣዖታተ ፡ ተምዑ ፡ ወአስተዋደይዎ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ጠራብዮስ ፡ አላዊ ፡ ወይቤልዎ ፡ እስመ ፡ አግናጥዮስ ፡ ይሠዕር ፡ አምልኮ ፡ አማልክቲከ ፡ ወይሜህሮሙ ፡ ለሰብእ ፡ ወያበውኦሙ ፡ ውስተ ፡ አሚነ ፡ ክርስቶስ ። ወሶቤሃ ፡ ፈነወ ፡ ሐራ ፡ ወአብጽሑ ፡ ኀቤሁ ፡ ወይቤሎ ፡ ኦ ፡ አግናጥዮስ ፡ ለምንት ፡ ገበርከ ፡ ዘንተ ፡ ወለምንት ፡ ሠዐርከ ፡ አምልኮ ፡ አማልክትየ ፡ ወአባእኮሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ሰብእ ፡ ውስተ ፡ አምልኮቱ ፡ ለእግዚአብሔር ። ወይቤሎ ፡ አግናጥዮጦስ ፡ እመሰ ፡ ተክህለኒ ፡ እምአባእኩከ ፡ ኦ ፡ ንጉሥ ፡ ውስተ ፡ አምልኮቱ ፡ ለክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወይቤሎ ፡ ንጉሥ ፡ ኅድግ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡ ወሡዕ ፡ ለአማልክትየ ፡ ወእመ ፡ አኮ ፡ እኴንነከ ፡ ዐቢየ ፡ ኵነኔ ።

፴፮፤ ወይቤሎ ፡ አግናጥዮስ ፡ ግበር ፡ ዘትፈቅድ ፡ ላዕሌየ ፡ እስመ ፡ አንሰ ፡ ኢይሠውዕ ፡ ለአማልክቲከ ፡ ርኵሳን ፡ ወኢይፈርሀ ፡ ኵነኔከ ፡ እሳተኒ ፡ አንበሳኒ ፡ ወኢትክል ፡ ትፍልጠኒ ፡ እምነ ፡ ፍቅሩ ፡ ለክርስቶስ ፡ ንጉሥ ፡ ሕያው ።

፴፯፤ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ዘንተ ፡ ተምዐ ፡ ንጉሥ ፡ ወአዘዘ ፡ ይኰንንዎ ፡ ወኰነንዎ ፡ በብዙኅ ፡ መክፈልተ ፡ ኵነኔ ፡ ወወደዩ ፡ አፍሐመ ፡ እሳት ፡ ውስተ ፡ እደዊሁ ፡ ወአኀዝዎ ፡ በጕጠት ፡ ምስለ ፡ እደ

፴፫፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ የአንጾኪያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ የከበረና ፡ የተመሰገነ ፡ አግናጥዮስ ፡ ምስክር ፡ ሆኖ ፡ ሞተ ።

፴፬፤ ይህም ፡ ቅዱስ ፡ የወንጌላዊው ፡ ዮሐንስ ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ነው ፡ በስብከተ ፡ ወንጌልም ፡ በማገልገል ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ብዙ ፡ አገሮችን ፡ ዞሮ ፡ አስተምሮአል ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በአንጾኪያ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ሾመው ፡ በውስጥዋም ፡ ሕይወት ፡ የሆነ ፡ የወንጌልን ፡ ትምህርት ፡ አስተማረ ፡ ብዙዎችንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ወደ ፡ ማውቅ ፡ መለሳቸው ፡ የክርስትና ፡ ጥምቀትንም ፡ አጠመቃቸው ፡ በትምህርቱም ፡ ልቡናቸውን ፡ አበራላቸው ።

፴፭፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ጣዖታትን ፡ ለሚያመልኩ ፡ ስሕተታቸውን ፡ በገለጠላቸው ፡ ጊዜ ፡ ተቆጡ ፡ ወደ ፡ ከሀዲው ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ጠራብዮስ ፡ ሔደው ፡ ከሰሱት ፡ እንዲህም ፡ አሉት ፡ አግናጥዮስ ፡ የአማልክቶችህን ፡ አምልኮ ፡ ይሽራል ፡ እኮን ፡ ሰዎችንም ፡ እያስተማረ ፡ ክርስቶስን ፡ ወደ ፡ ማመን ፡ ያስገባቸዋል ። በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ወታደሮች ፡ ልኮ ፡ ወደርሱ ፡ አስመጣውና ፡ አግናጥዮስ ፡ ሆይ ፡ ለምን ፡ ይህን ፡ አደረግህ ፡ የአማልክቶቼን ፡ አምልኮስ ፡ ለምን ፡ ሻርክ ፡ ሰዎችን ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ወደ ፡ ማምለክ ፡ አስገብተሃቸዋልና ፡ አለው ። አግናጥዮስም ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ቢቻለኝስ ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ወደሆነ ፡ ወደ ፡ ክርስቶስ ፡ አምልኮት ፡ ባስገባሁህ ፡ ነበር ፡ አለው ፡ ንጉሡም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ትተህ ፡ ለአማልክቶቼ ፡ ሠዋ ፡ አለዚያ ፡ በታላቅ ፡ ሥቃይ ፡ አሠቃይሃለሁ ፡ አለው ።

፴፮፤ በእኔ ፡ ላይ ፡ የምትሻውን ፡ አድርግ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ለረከሱ ፡ አማልክቶችህ ፡ አልሠዋም ፡ ሥቃይህንም ፡ እሳትም ፡ ቢሆን ፡ አንበሳንም ፡ ቢሆን ፡ አልፈራም ፡ ከሕያው ፡ ንጉሥ ፡ ከክርስቶስ ፡ ፍቅር ፡ ልትለየኝ ፡ አትችልም ፡ አለው ።

፴፯፤ ይህንንም ፡ ሲሰማ ፡ ንጉሡ ፡ ተቆጣ ፡ ያሠቃዩትም ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ በተለያዩ ፡ በብዙ ፡ ሥቃዮችም ፡ አሠቃዩት ፡ በእጆቹም ፡ ውስጥ ፡ እሳት ፡ አድርገው ፡ ከእጆቹ ፡ ጋር ፡ በጉጠት ፡

ዊሁ ፡ ወእምዝ ፡ አውዓዩ ፡ ገበዋቲሁ ፡ በተይ ፡
ወቅብዕ ፡ እንዘ ፡ ያነድዱ ፡ ወሠጠቁ ፡ ሥጋሁ ፡
በመጣብሕ ። ወሶበ ፡ ደክሙ ፡ እምኰንኖቱ ፡
ወደይዎ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ፡ እስከ ፡
ይመክሩ ፡ ዘይገብሩ ፡ ቦቱ ፡ ከመዝ ፡ ወነበረ ፡
ውስተ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ፡ ብዙኀ ፡ መዋዕለ ።

፴፰ ወእምዝ ፡ ተዘከርዎ ፡ ወአውጽእዎ ፡ እምቤተ ፡
ሞቅሕ ፡ ወአቀምዎ ፡ ቅድመ ፡ ንጉሥ ፡
ወይቤሎ ፡ ንጉሥ ፡ ኦ ፡ አግናጥዮስ ፡ ለእመ ፡
ርኢኮሙ ፡ ለአማልክትየ ፡ እምአደመከ ፡
ስኖሙ ፡ አውሥአ ፡ ቅዱስ ፡ ወይቤሎ ፡ ኦ ፡
ንጉሥ ፡ ለእመ ፡ አንተ ፡ አመንከ ፡ በክርስቶስ ፡
ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ እምረሰየከ ፡ ከመ ፡ ታንሥ
አሙ ፡ ለምውታን ፡ ወትፌውሶሙ ፡ ለድው
ያን ። ወይቤ ፡ ንጉሥ ፡ አልቦ ፡ ዘይኄይስ ፡
እምሰጊድ ፡ ለፀሐይ ፡ አውሥአ ፡ ወይቤ ፡
ቅዱስ ፡ አግናጥዮስ ፡ ትሰግድኑ ፡ ለዘተፈጥረ ፡
ወተኃድግ ፡ ፈጣሬ ፡ ዘኢየኀልቅ ፡ መንግሥቱ ፡
ወይቤሎ ፡ ንጉሥ ፡ ለከ ፡ ሠናየ ፡ ትቤ ፡ አላ ፡
ባሕቱ ፡ በተዓድዎትከ ፡ ሰሐብከ ፡ ኵሎ ፡ ሰብአ ፡
ሶርያ ፡ ወአንጾኪያ ፡ ውስተ ፡ አምልኮቱ ፡ ለክር
ስቶስ ፡ ወተምዐ ፡ ቅዱስ ፡ አግናጥዮስ ። ወይ
ቤሎ ፡ ኦ ፡ ንጉሥ ፡ በእንተ ፡ ዘሰሐብክዎሙ ፡
ለሰብእ ፡ እምአምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ከንቱ ፡ ወአባእ
ክዎሙ ፡ ውስተ ፡ አምልኮቱ ፡ ለክርስቶስ ፡
ፈጣሬ ፡ ሰማያት ፡ ወምድር ፡ ትትመዓዕኑ ፡
ላዕሌየ ፡ ወትኤዝዘኒ ፡ እሡዕ ፡ ለአማልክቲከ ፡
ርኵሳን ፡ ወአንሰ ፡ ኢይትዌከፍ ፡ ቃለከ ፡ ወኢ
ይሠውዕ ፡ ለሰይጣናት ፡ አላ ፡ እሠውዕ ፡ ለአም
ላክ ፡ ዘበአማን ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡
ቅዱስ ።

፴፱ ወሶቤሃ ፡ ተምዐ ፡ ንጉሥ ፡ ወአዘዘ ፡ ከመ ፡
ይስድዱ ፡ ላዕሌሁ ፡ ፪ተ ፡ አናብስተ ፡ ርኁባነ ፡
ይብልዕዎ ፡ ወኢያትርፉ ፡ እምሥጋሁ ፡ ምን
ተኒ ።

፵ ወሶበ ፡ ርእዮሙ ፡ ቅዱስ ፡ አግናጥዮስ ፡ ለአና
ብስት ፡ እንዘ ፡ ይቀርቡ ፡ ኀቤሁ ፡ ጸርሐ ፡ በቃል ፡
ልዑል ፡ ወይቤሎሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ስምዑኒ ፡
ቃልየ ፡ ኦ ፡ ሰብአ ፡ ሮሜ ፡ እለ ፡ ተጋባእክሙ ፡
ዝየ ፡ ወአእምሩ ፡ እስመ ፡ አኮ ፡ አነ ፡ በትዕቢት ፡
ወበትምክህት ፡ ዘተዓገሥክዎ ፡ ለዝ ፡ ኵነኔ ፡
ትዕግሥትየሰ ፡ በእንተ ፡ ፍቅሩ ፡ ለእግዚእየ ፡
ወአምላኪየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ንጉሠ ፡

ይዘው ፡ አቃጠሉት ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በዲንና ፡
በቅባት ፡ እያነደዱ ፡ ጐኖቹን ፡ አቃጠሉ ፡ በሾ
ተሎችም ፡ ሥጋውን ፡ ሠነጣጠቁ ። ከማሠቃ
የትም ፡ በደከሙ ፡ ጊዜ ፡ የሚያደርጉበትን ፡ እስ
ኪመክሩ ፡ ድረስ ፡ ከወህኒ ፡ ቤት ፡ ጨመሩት ፡
ብዙ ፡ ቀኖችም ፡ በዚያ ፡ ኖረ ።

፴፰ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አስታወሱት ፡ ከወህኒ ፡
ቤትም ፡ አውጥተው ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ አቆ
ሙት ፡ ንጉሡም ፡ አግናጥዮስ ፡ ሆይ ፡ አማልክ
ቶቼን ፡ ብታያቸው ፡ ውበታቸው ፡ ባማረህ ፡
ነበር ፡ አለው ። ቅዱሱም ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ አንተ ፡
በክብር ፡ ባለቤት ፡ ክርስቶስ ፡ ብታምን ፡
ሙታኖችን ፡ የምታሥነሣቸው ፡ በሽተኞ
ችንም ፡ የምትፈውሳቸው ፡ ባደረገህ ፡ ነበር ።
ንጉሡም ፡ ለፀሐይ ፡ ከመሰገድ ፡ የተሻለ ፡
የለም ፡ አለ ፡ የከበረ ፡ አግናጥዮስም ፡ መን
ግሥቱ ፡ የማያልቀውን ፡ ፈጣሪ ፡ ትተህ ፡ ለተ
ፈጠረ ፡ ፀሐይ ፡ ትሰግዳለህን ፡ ብሎ ፡ መለሰ ፡
ንጉሡም ፡ ለራስህ ፡ መልካም ፡ አልክ ፡ ግን ፡
በመተላለፍ ፡ የአንጾኪያንና ፡ የሶርያን ፡ ሰዎች ፡
ስበሕ ፡ ወደ ፡ ክርስቶስ ፡ አምልኮት ፡ አስገባ
ሃቸው ፡ እንጂ ፡ አለው ፡ የከበረ ፡ አግናጥዮስም ፡
ተቆጥቶ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ከንቱ ፡ የሆነ ፡ ጣዖትን ፡
ከማምለክ ፡ ሰዎችን ፡ ስለሳብኳቸውና ፡ ሰማ
ይና ፡ ምድርን ፡ ወደ ፡ ፈጠረ ፡ ወደ ፡ ክርስቶስ ፡
አምልኮት ፡ ስለአስገባኋቸው ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ትቆ
ጣለህን ፡ ለረከሱ ፡ ጣዖቶችህስ ፡ እንድሠዋ ፡
ታዘኛለህን ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ቃልህን ፡ ተቀብዬ ፡ ለሰ
ይጣናት ፡ አልሠዋም ፡ ለእውነተኛ ፡ አምላክ ፡
ለአብ ፡ ለወልድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እሠ
ዋለሁ ፡ እንጂ ፡ አለው ።

፴፱ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ንጉሥ ፡ ተቆጣ ፡ ከሥጋው ፡
ምንም ፡ ምን ፡ ሳያስቀሩ ፡ ይበሉት ፡ ዘንድ ፡
ሁለት ፡ የተራቡ ፡ አንበሶችን ፡ በላዩ ፡ እንዲሰዱ ፡
አዘዘ ።

፵ የከበረ ፡ አግናጥዮስም ፡ አንበሶች ፡ ወደርሱ ፡
ሲቀርቡ ፡ በአያቸው ፡ ጊዜ ፡ ድምፁን ፡ ከፍ ፡
አድርጎ ፡ ሕዝቡን ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ ከዚህ ፡
የተሰበሰባችሁ ፡ እናንተ ፡ የሮሜ ፡ ሰዎች ፡
ቃሌን ፡ ስሙ ፡ እወቁም ፡ እኔ ፡ ይህን ፡ ሥቃይ ፡
የታገሥኩት ፡ በትዕቢትና ፡ በትምክህት ፡
አይደለም ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ በሆነ ፡
በጌታዬና ፡ በፈጣሪዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ስብሐት፡ ወናሁ ፡ ፈተወት ፡ ነፍስየ ፡ ከመ ፡ ይሕርፀኒ ፡ እሉ ፡ አናብስት ፡ ከመ ፡ ሥርናይ ፡ እስመ ፡ ፈተወት ፡ ነፍስየ ፡ ከመ ፡ ትሑር ፡ ኀበ ፡ እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ንጉሠ፡ስብሐት።

፴፩፤ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ቃሎ ፡ አንከረ ፡ ንጉሥ ፡ ወደንገፀ ፡ ወይቤ ፡ ምንት ፡ ይፈደፍድ ፡ ትዕግሥቶሙ ፡ ለክርስቲያን ፡ ላዕለ ፡ ሁነኔ ፡ መኑ ፡ ውእቱ ፡ እምነ ፡ አረማውያን ፡ ዘይክል ፡ ተዓግሦ ፡ ላዕለ ፡ ዘከመዝ ፡ ሁነኔ ፡ በእንተ ፡ አምልኮት ፡ ወእምዝ ፡ ቀርቡ ፡ እሉ ፡ አናብስት ፡ ኀበ ፡ ቅዱስ ፡ ወቆሙ ፡ ድንጉፃኒሆሙ ። ወእምዝ ፡ ሰፍሐ ፡ ፩ዱ ፡ እምአናብስት ፡ እዴሁ፡ ኀበ ፡ ክሣዱ ፡ ወአኀዞ ፡ ወሶቤሃ ፡ መጠወ ፡ ነፍሶ፡ውስተ፡እዴሁ፡ለክርስቶስ፡አምላኩ፡ በፍሥሓ፡ወፈጸመ፡ሎቱ፡ስእለቶ።

፴፪፤ ወኢ.ተክህሎሙ ፡ ለእሉ ፡ አናብስት ፡ ይግሥሡ ፡ ሥጋሁ ፡ አላ ፡ ኮኑ ፡ ዕቁበ ፡ እስከ ፡ ዳግም፡ ምጽአቱ ፡ ለክርስቶስ ፡ ንጉሠ ፡ ስብሐት፡ ወእምዝ፡ቀበሩ፡ሥጋሁ፡በአፍአ፡ ሀገር ፡ በክብር ፡ ወበስብሐት ፡ ወከመዝ ፡ ፈጸመ፡ ስምዖ ፡ በሠናይ ፡ ገድል ፡ በእንተ ፡ ስሙ፡ ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሎቱ፡ ስብሐት ፡ ወጸሐፉ ፡ ገድሎ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ በቀኑዔተ ፡ ለመሐይምናን ፡ ወገብሩ ፡ ሎቱ ፡ ተዝካረ፡በዓሉ።

፴፫፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ ሐዋርያ ፡ ወበረከቱ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡ አሜን።

ፍቅር፡ነው፡እንጂ።አሁንም፡እኒህ፡አንበሶች፡ እንደ ፡ ሥንዴ ፡ ይፈጩኝ ፡ ዘንድ ፡ ነፍሴ ወደደች፡የክብር፡ባለቤት፡ወደ፡ሆነ፡ጌታዬ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ልትሔድ፡ ነፍሴ ፡ ሽታለችና።

፴፩፤ ንጉሡም ፡ ቃሉን ፡ ሰምቶ ፡ አደነቀ፡ ድንጋጤም፡አድሮበት፡እንዲህ፡አለ፡የክርስቲያኖች፡ትዕግሥታቸው፡ምን፡ይበዛ፡ስለ፡ አምልኮት ፡ ከአረማውያን ፡ በእንዲህ ፡ ያለ ፡ ሥቃይ፡ላይ፡የሚታገሥ፡ማን፡ነው፡አለ። እነዚያ ፡ አንበሶችም ፡ ወደ ፡ ቅዱሱ ፡ ቀረብ ፡ ብለው ፡ ደንግጠው ፡ ቆሙ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አንዱ ፡ አንበሳ ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ አንገቱን ፡ ያዘው፡በዚያንም፡ጊዜ፡ደስ፡ብሎት፡ነፍሱን፡ በፈጣሪው ፡ ክርስቶስ ፡ እጅ ፡ ሰጠ ፡ ልመናውንም፡ፈጸመለት።

፴፪፤ ለእነዚያ፡ አንበሶችም፡ ሥጋውን ፡ ይዳስሡት፡ ዘንድ ፡ አልተቻላቸውም ፡ የክብር፡ባለቤት፡ክርስቶስ፡ዳግመኛ፡እስከሚመጣ፡የተጠበቀ፡ሆነ፡እንጂ፡ከዚህም፡ በኋላ፡በክብር፡በምስጋና፡ከከተማ፡ውጭ፡ ቀበሩት ፡ እንደዚህም ፡ በክብር ፡ ባለቤት ፡ በጌታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ስም፡ በመልካም፡ተጋድሎ፡ምስክርነቱን፡ፈጸመ፡ለምእመናንም፡ጠቃሚ፡ይሆን፡ዘንድ፡ገድሉን፡ ጻፉ፡የበዓሉንም፡መታሰቢያ፡አደረጉለት።

፴፫፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም፡ በዚህ ፡ ሐዋርያ ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ ዓሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለአግናጥዮስ፡ለእግዚአብሔር፡ኅሩዩ።ዘሰበከ፡ጽድቀ፡ለእለ፡ጌገዩ።አረማውያን፡ላዕሌሁ፡ እንዘ፡ይትዋነዩ።በፍልሐተ፡ቅብዕ፡ወተይ፡አባላቲሁ፡አውዓዩ።ወአፍሐመ፡እሳት፡ካዕበ፡ላዕሌሁ፡ ወደዩ።

፴፬፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ ፊሎንጎስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘሀገረ፡አንጾኪያ።

፴፭፤ ወዝንቱ፡ቅዱስ፡ቀዳሚ፡አውሰበ፡ብእሲተ፡ ወወለደ፡አሐተ፡ወለተ፡ወእምዝ፡ሞተት፡ ብእሲቱ ፡ ወለብሰ ፡ ልብሰ ፡ ምንኵስና ፡ ወተጸምደ፡በተጋድሎ፡ዐቢይ፡ወበእንተ፡ ተጋድሎቱ፡ወትሩፋቲሁ፡ሠናያት፡ወአሥምሮቱ፡ወተጸምዶቱ፡ወየውሀቱ፡ኅረዮ፡

፴፬፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ የአንጾኪያ ፡ አገር ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት፡የከበረ፡አባት፡ፊሎንጎስ፡አረፈ።

፴፭፤ ይህም፡ቅዱስ፡አስቀድሞ፡ሚስት፡አግብቶ፡ አንዲት ፡ ልጅ ፡ ወለደ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሚስቱ፡ ሞተች ፡ የምንኵስናንም ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ ታላቅ ፡ ተጋድሎን ፡ ተጋደለ ፡ ስለ ፡ ተጋድሎውም፡ስለ፡መልካም፡ትሩፋቱም፡ ለአገልግሎት፡በመጸመዱና፡ስለ፡ቅንነቱ፡

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር፡ ከመ፡ ይኩን፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ ላዕለ፡ሀገረ፡አንጾኪያ።

፴፮፤ ወሶበ ፡ ተሠይመ ፡ ዐቀበ ፡ መርዔቶ ፡ ለክርስቶስ፡ በሠናይ ፡ ተዓቅቦ ፡ እምነ ፡ ተኵላት ፡ አርዮሳውያን፡ወዘመቅዶንዮስ፡ወሰባልዮስ፡ ወሐይወ፡በሢመተ፡ሊቀ፡ጵጵስናሁ፡ከመ፡ ሕይወቶሙ፡ለመላእክት፡ወኢያጥረየ፡፪ተ፡ አልባሳተ፡ወኢ፡ወርቀ፡ወብሩረ፡ወፈጺሞ፡ ገድሎ፡ ወአሥመሮ ፡ለእግዚአብሔር፡ ወእምዝ ፡ አዕረፈ ፡ በሰላም ። ወወደሶ ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ በድርሳናቲሁ ፡ ወከሠተ፡ትሩፋቲሁ፡ወጽድቆ።

፴፯፤ ወስብሐት ፡ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ በጸሎቱ ፡ ይምሐረነ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

በአንጾኪያ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ እንዲሆን፡እግዚአብሔር፡ መረጠው።

፴፮፤ በተሾመም፡ጊዜ፡የክርስቶስን፡ መንጋዎች፡ በበጎ፡ አጠባበቅ፡ ከአርዮሳውያን፡ ከመቅዶንዮስና ፡ ከሰባልዮስ ፡ ነጣቂ ፡ ተኵላዎች ፡ ጠበቀ፡በሊቀ፡ጵጵስናውም፡ሹመት፡እንደ፡ መላእክት፡አኗኗር፡ኖረ። ሁለት፡ልብሶችን፡ ገንዘብ ፡ አላደረገም ፡ ወርቅንና ፡ ብርንም ፡ ቢሆን ፡ አላከማቸም ፡ ገድሉንም ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አገልግሎ ፡ ከዚህ በኋላ፡ በሰላም ፡ አረፈ ። ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅም፡ በድርሳኑ ፡ አመሰገነው ፡ ትሩፋቱንና፡ጽድቁንም፡ገለጠ።

፴፯፤ ለእግዚአብሔርም፡ ምስጋና፡ ይሁን፡ እኛንም፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

<u>አርኬ</u>

ሰላም፡ለፊሎንጎስ፡ለእግዚአብሔር፡ ዘተጸምዶ።ለሰባልዮስ፡ይዝርዎ፡ወለአርዮስ፡ይስድዶ።ግዕዘ፡ መላእክት፡አጥረየ፡እንዘ፡ለንዋይ፡ኢይፈቅዶ።ትሩፋቲሁ፡ነጺሮ፡ወለየውሀቱ፡ፍድፋዶ።አፈ፡ወርቅ፡ ዮሐንስ፡ወደሶ፡ወንዕዶ።

፴፰፤ ወበዛቲ፡ዕለት፡ ኮነ፡ዕረፍቶሙ፡ለጻድቃን፡ ዘከዲህ ፡ በአሐቲ ፡ ዕለት ፡ ከመ ፡ ነገሮሙ ፡ መልአከ፡ እግዚአብሔር ፡ ወተዝካሩ ፡ ለአዝቂር፡ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ወበረከቶሙ ፡ ለጻድቃን ፡ ትብጽሐነ ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፴፰፤ በዚችም፡ቀን፡የእግዚአብሔር፡ መልአክ፡ እንደነገራቸው፡በከዲህ፡ያሉ፡ጻድቃን፡ዕረፍታቸው ፡ በአንዲት ፡ ቀን ፡ ሆነ ። የአዝቂርም ፡ መታሰቢያው ፡ ነው ። ለእግዚአብሔርም፡ ምስጋና፡ይሁን፡የጻድቃንም፡በረከታቸው፡ትድረሰን፡ለዘላለሙ፡አሜን።

<u>አርኬ</u>

ሰላም፡እብል፡ ኪያክሙ፡ጻድቃነ።ዘሀገረ፡ከዲህ፡አጽዋነ።ብዑላን፡አበው፡ዘታብዕሉ፡ምስኪነ። አዕኑገ፡ክብር፡አሠርግዉኒ፡አዕዛነ።ወበኵሕለ፡ፈውስ፡ኰሐሉኒ፡ዐይነ።

፴፱፤ ወበዛቲ፡ዕለት፡ተወልደ፡ብፁዕ፡ወቅዱስ፡ ሐዲስ፡ሐዋርያ፡አቡነ፡ተክለ፡ሃይማኖት፡ በረከተ፡ጸሎቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ አሜን።

፴፱፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የተመሰገነና ፡ የከበረ ፡ አዲስ፡ ሐዋርያ ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት፡ ተወለደ ፡ በጸሎቱ ፡ የምትገኝ ፡ በረከቱ፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡ለእግዚአብሔር፡ ምስጋና፡ይሁን፡አሜን።

<u>አርኬ</u>

ሰላም ፡ ለልደትከ ፡ ድኅረ ፡ ነበረት ፡ መካነ ። ለእምከ ፡ ልባ ፡ ከመ ፡ ቃለ ፡ መልአክ ፡ አምነ ። ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በርትዕ፡እንተ፡ቀነይከ፡አዝማነ። መልአ፡ምድረ፡ትምህርትከ፡እምወሰን፡ወሰነ፡ወሰማያተ፡ ጽድቅከ፡ከደነ።

www.ethiopianorthodox.org

፩፤ በስመ፡ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ፩
አምላክ ፡ አመ ፡ ፳ወ፭ ለታኅሣሥ ፡ በዛቲ ፡
ዕለት፡ አዕረፈ፡ አብ፡ ቅዱስ፡ ዮሐንስ፡ ከማ፡
ዘእምሀገረ፡ ስብራ፡ መንጹ፡ እምብሔረ፡ ፃ፡
ዘደቡብ፡ ግብጽ።

፪፤ ወለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ አበዊሁ ፡ መሃይምናን ፡
ፈራህያነ፡ እግዚአብሔር፡ ወኢኮነ፡ ሎሙ፡
ወልድ፡ ዘእንበሌሁ፡ ወፈቀዱ፡ ከመ፡ ይትፈ
ሥሑ፡ ቦቱ፡ በዝንቱ፡ ዓለም፡ በመርዓሁ፡ ወአ
ስተዋሰብዎ ፡ ወለተ ፡ ድንግለ ፡ ሠናይተ ፡
ላሕይ፡ ዘእንበለ፡ ፈቃዱ።

፫፤ ወበዊአ፡ ውስተ፡ ጽርሕ፡ ሌሊተ፡ ቆመ፡ ከመ፡
ዘወትር ፡ ይጼሊ ፡ ወቀርበ ፡ ኀበ ፡ ይእቲ ፡
ወለት ፡ ወይቤላ ፡ አንቲ ፡ ተአምሪ ፡ ከመ ፡
ዝንቱ፡ ዓለም፡ ኃላፊ፡ ወኵሉ፡ ፍትወቱ፡ ቦኑ፡
ትፈቅዲ ፡ ከመ ፡ ንስነዓው ፡ በበይናቲነ ፡
ወንዕቀብ ፡ ሥጋነ ፡ በንጽሕ ፡ ወይእቲ ፡
አውሥአቶ፡ ወትቤሎ፡ አ፡ እኁየ፡ ሕያው፡
ውእቱ፡ እግዚአብሔር፡ ከመ፡ ለዛቲ፡ ፍት
ወት ፡ ኢሐለይክዋ ፡ ባሕቱ ፡ አገበሩኒ ፡
አበውየ፡ ወአስተዋሰቡኒ፡ ለከ፡ ወይእዜኒ፡
ናሁ ፡ ፈጸመ ፡ ሊተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስእ
ለትየ።

፬፤ ወእምዝ፡ ተሰነዓዉ፡ ፪ሆሙ፡ ከመ፡ ይዕቀቡ፡
ድንግልናሆሙ፡ በንጽሕ፡ ወነበሩ፡ ብዙኀ፡
አዝማነ፡ ኅቡረ፡ እንዘ፡ ይሰክቡ፡ ውስተ፡ ፩
ዐራት ፡ ወመልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይወ
ርድ፡ እምሰማይ፡ ወይከድኖሙ፡ ክነፊሁ።

፭፤ ወበእንተ፡ ብዝኀ፡ ጽድቆሙ፡ አብቈለ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ውስተ ፡ ቤቶሙ ፡ ዐፀ ፡ ወይን ፡
ዘኢዘርዓ፡ ወኢተከላ፡ መኑሂ፡ ወልሕቀት፡
ወዐርገት፡ ወጸለለት፡ መልዕልተ፡ ቤቶሙ፡
ወይእቲ፡ ትኤምር፡ በእንተ፡ ዐቂበ፡ ድንግል
ናሆሙ፡ እስመ፡ ዝንቱ፡ ግብር፡ ይትሌዓል፡
ላዕለ፡ ፍጥረተ፡ ዕጓለ፡ እመሕያው፡ ከመ፡
ይኩኑ፡ ፪ቱ፡ ወራዙት፡ ዘይሰክቡ፡ ኅቡረ፡
ወየዐቅቡ፡ ድንግልናሆሙ፡ ኢይትነሣእኑ፡
ሕሊና፡ ፍትወት፡ ግሙራ፡ መኑ፡ ውእቱ፡
ዘየሐቅፍ፡ እሳተ፡ ወኢይውዒ፡ ሥጋሁ፡ ሶበ፡
አኮ፡ ረድኤተ፡ እግዚአብሔር፡ ኮነት፡ ተዐ
ቅቦ።

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡
በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ታኅሣሥ ፡ ሃያ ፡
አምስት፡ በዚች፡ ቀን፡ ከግብጽ፡ ደቡብ፡ ፃ፡
ከሚባል ፡ አውራጃ ፡ መንጹ ፡ ስብራ ፡
ከምትባል፡ ከተማ፡ የከበረ፡ አባት፡ ዮሐንስ፡
ከማ፡ አረፈ።

፪፤ የዚህም ፡ ቅዱስ ፡ ወላጆቹ ፡ እግዚአብሔርን ፡
የሚፈሩ፡ ምእመናን፡ ከእርሱም፡ በቀር፡ ልጅ፡
የላቸውም ፡ በዚህም ፡ ዓለም ፡ በሠርጉ ፡ ደስ ፡
ይላቸው ፡ ዘንድ ፡ ወደው ፡ ላሕይዋ ፡ ደም፡
ግባቷ፡ ያማረ፡ ድንግል፡ ብላቴና፡ ያለ፡ ፈቃዱ፡
አጋቡት።

፫፤ ወደ ፡ ጫጉላ ፡ ቤትም ፡ በሌሊት ፡ ገብቶ ፡
ዘወትር፡ እንደሚጸልይ ፡ ቆመ ፡ ወደዚያች፡
ብላቴናም፡ ቀረብ፡ ብሎ፡ ይህ፡ ዓለም፡ ፍላጎቱ፡
ኃላፊ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አንቺ፡ ታውቂያለሽ፡
ሥጋችንን፡ በንጽሕና፡ ለመጠበቅ ፡ እርስ ፡
በርሳችን፡ እንስማማ፡ ዘንድ፡ ትፈቅጂአለሽን፡
አላት። እርሷም፡ ወላጆቼ፡ አስገድደው፡ ላንተ፡
አጋቡኝ፡ እንጂ፡ ሥጋዊ፡ ፍትወትን፡ እንዳላሰ
ብኋት፡ ሕያው፡ እግዚአብሔር፡ ምስክሬ፡ ነው፡
አሁንም ፡ እነሆ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልመናዬን
ፈጸመልኝ፡ ብላ፡ መለሰችለት።

፬፤ ከዚህም፡ በኋላ፡ ድንግልናቸውን፡ በንጽሕና፡
ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ሁለቱም ፡ ተስማምተው ፡
በአንድነት፡ በአንድ፡ ዐልጋ፡ ላይ፡ እየተኙ፡
ብዙ ፡ ዘመናት ፡ ኖሩ ፡ የእግዚአብሔርም ፡
መልአክ፡ ከሰማይ፡ በመውረድ፡ ክንፎቹን፡
አልብሷቸው፡ ያድራል።

፭፤ ከጽድቃቸውም፡ ብዛት፡ የተነሣ፡ ማንም፡ ያል
ዘራትንና፡ ያልተከላትን፡ የወይን፡ ተክልን፡
እግዚአብሔር፡ በቤታቸው፡ አበቀለ፡ አድጋ፡
ወጥታ ፡ ከቤታቸው ፡ ጣሪያ ፡ በላይ ፡ ተንሳ
ፈፈች፡ እርሷም፡ የድንግልናቸውን፡ መጠበቅ፡
ታመለክታለች። ይህ፡ ሥራ፡ በሰው፡ ተፈጥሮ፡
ላይ ፡ ይከብዳልና ፡ ሁለት ፡ ወጣቶች ፡ በአን
ድነት ፡ የሚተኙ ፡ ሁነው ፡ ድንግልናቸውን ፡
ጠብቀው፡ ሲገኙ፡ ከቶ፡ የፍላጎት፡ ሐሳብ፡ አይ
ነሣምን፡ እሳትን፡ የሚታቀፍ፡ ሥጋው፡ የማይ
ቃጠል ፡ ማን ፡ ነው ፡ የእግዚአብሔር ፡
ረድኤት፡ የምትጠብቀው፡ ካልሆነች።

www.ethiopianorthodox.org

፮፤ አበዊሆሙ፡ ፡ ሶበ ፡ ርእዩ ፡ እንዘ ፡ ይነብሩ ፡ ብዙኀ፡ መዋዕለ ፡ ወኢወለዱ ፡ ወልደ ፡ መሰሎሙ፡በእንተ፡ውርዛዌሆሙ።

፯፤ ወእምዝ ፡ ይቤላ ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ ከማ ፡ ዘውእቱ ፡ ካም ፡ ብሂል ፡ ኦ ፡ እኅትየ ፡ አንሰ ፡ እፈቱ ፡ ከመ ፡ እሑር ፡ ኀበ ፡ ገዳመ ፡ አስቄጥስ፡ ወእመንኵስ ፡ ወባሕቱ ፡ ኢይትከሃለኒ ፡ እግበር ፡ ምንተኒ ፡ ዘእንበለ ፡ ፈቃድኪ፡ ይእቲኒ ፡ አውሥአቶ ፡ ወትቤሎ ፡ ግበር ፡ ዘትፈቅድ ፡ ወእግዚአብሔር ፡ ይረሲከ ፡ ፍቱሐ ፡ እምእንቲአየ ። ወሶበ ፡ ትቤሎ ፡ ዘንተ፡ ነሥአ፡ ወወሰዳ ፡ ኀበ፡ደብረ ፡ ደናግል፡ ወመንኰሰት ፡ ወኮነት ፡ እመ ፡ ምኔት ፡ ወኮነት ፡ ዘትገብር ፡ ተአምራተ ፡ ወመንክራተ ፡ ወአሥመረቶ ፡ ለእግዚአብሔር ።

፰፤ ወቅዱስሰ ፡ ዮሐንስ ፡ ከማ ፡ ሶበ ፡ ወጽአ ፡ ከመ፡ ይሑር ፡ ኀበ ፡ ገዳመ ፡ አስቄጥስ ፡ አስተርአዮ፡ ብእሲ ፡ በገጽ ፡ ብሩህ ፡ ወተሰአሎ ፡ በእንተ ፡ ጸአቱ ፡ ወይቤሎ ፡ ዮሐንስ ፡ ከማ ፡ ለእመ ፡ ሠምረ ፡ እግዚአብሔር ፡ አነ ፡ እፈቅድ ፡ እኩን፡ መነኮሰ ፡ ወአምከሮ ፡ ወይቤሎ ፡ ውእቱ ፡ ዘገጹ ፡ ብሩህ፡ ሑር ፡ ኀበ ፡ በዓቱ ፡ ለቅዱስ ፡ አባ ፡ ዳሩዲ ፡ ዘደብረ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ ወንበር ፡ ኀቤሁ ፡ ወውእቱ ፡ ያመንኵስከ ፡ ወይምራህከ ፡ ፍኖተ፡ ምንኵስና ፡ ወኮነ ፡ ውእቱ ፡ ዘገጹ ፡ ብሩህ ፡ ዘያንሶሱ ፡ ምስሌሁ ፡ እንዘ ፡ ይናዝዞ ፡ እስከ ፡ አብጽሖ ፡ ኀበ ፡ በዓቱ ፡ ለአባ ፡ ዳሩዲ ።

፱፤ ወዘንቱ ፡ አባ ፡ ዳሩዲ ፡ ተወክፎ ፡ ኀቤሁ ፡ ወአልበሶ ፡ አልባሰ ፡ ምንኵስና ፡ ወመሀሮ ፡ ሕገ ፡ ምንኵስና ፡ ወሥርዓተ ፡ ወቀኖናተ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ አዕረፈ ።

፲፤ ወእምዝ ፡ አዘዞ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአባ ፡ ዮሐንስ ፡ ከማ ፡ ከመ ፡ ይሑር ፡ ኀበ ፡ ምዕራበ ፡ ደብር ፡ ዘአብ ፡ ዮሐንስ ፡ ሐጺር ፡ ወይሕንፅ ፡ ሎቱ ፡ ማኅደረ ፡ በህየ ። ወሶበ ፡ ሖረ ፡ ህየ ፡ ተጋብኡ ፡ ኀቤሁ ፡ ፫ ፻ት ፡ አኃው፡ ወአልበሶሙ ፡ አልባሰ ፡ ምንኵስና ፡ ወሐነፁ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወሎሙ ፡ ማኅደራተ ፡ ውእቱኒ ፡ መሀሮሙ ፡ ሥርዓታተ፡ ወጸሎታተ ፡ ወዝማሬያተ ፡ ወውዳሴሃ ፡ ለእግዝእትነ፡ማርያም ።

፮፤ ወላጆቻቸውም ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ሲኖሩ ፡ ልጅን ፡ እንዳልወለዱ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ጐልማሶች ፡ ስለ ሆኑ፡መሰላቸው።

፯፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የከበረ ፡ ዮሐንስ ፡ ከማ ፡ ይህም ፡ ካም ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ አላት ፡ እኅቴ ፡ ሆይ ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ አስቄጥስ ፡ ገዳም ፡ ሒጄ ፡ እመነኵስ ፡ ዘንድ ፡ እሻለሁ፡ ግን ፡ ያላንቺ ፡ ፈቃድ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ አይቻለኝም ፡ እርሷም ፡ የምትሻውን ፡ አድርግ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከእኔ፡ የተፈታሕ፡ ያድርግህ ፡ አለችው ። ይህንንም በአለችው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ደናግል ፡ ገዳም፡ ወሰዳት ፡ በዚያም ፡ መንኵሳ ፡ እመ፡ ምኔት ፡ ሆነች ፡ ድንቆች ፡ ተአምራቶችንም ፡ የምታደርግ ፡ ሆነች ፡ እግዚአብሔርንም ፡ አገለገለችው ።

፰፤ የከበረ ፡ ዮሐንስ ፡ ከማም ፡ ወደ ፡ አስቄጥስ ፡ ገዳም ፡ ይሔድ ፡ ዘንድ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ፊቱ፡ የሚበራ ፡ ሰው ፡ ተገለጠለትና ፡ ስለ ፡ አወጣጡ ፡ ጠየቀው ፡ ዮሐንስ ፡ ከማም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከፈቀደ ፡ እኔ ፡ መነኮስ ፡ መሆንን ፡ እሻለሁ ፡ አለው ፡ ያም ፡ ፊቱ ፡ የሚበራ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መከረው ፡ ከአባ፡ መቃርስ ፡ ገዳም ፡ ወደ ፡ ሚኖር ፡ ወደ ፡ ከበረ ፡ አባ ፡ ዳሩዲ ፡ በዓት ፡ ሒደህ ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ኑር ፡ እርሱም ፡ ያመንኵስህ፡ የምንኵስናንም፡ ሥርዓት ፡ ያስተምርህ ፡ ያም ፡ ፊቱ ፡ ብሩህ ፡ የሆነ ፡ ወደ ፡ አባ ፡ ዳሩዲ ፡ በዓት ፡ እስከ ፡ አደረሰው ፡ ድረስ ፡ እያጽናናው ፡ አብሮት ፡ ተጓዘ ።

፱፤ ይህ ፡ አባ ፡ ዳሩዲም ፡ ተቀብሎ ፡ አመነኰሰው ፡ እስከ ፡ ዕረፍቱም ፡ ጊዜ ፡ የምንኵስናን ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት ፡ አስተማረው።

፲፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ከአባ ፡ ዮሐንስ ፡ ሐጺር ፡ ገዳም ፡ በስተ ፡ ምዕራብ ፡ ሒዶ ፡ ለራሱ ፡ ከዚያ ፡ ማደሪያ ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘው ፡ ወደዚያም ፡ በሔደ፡ ጊዜ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ። ወደርሱ ተሰበሰቡ ፡ የምንኵስናንም ፡ ልብስ ፡ አለበሳቸው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ለራሳቸውም ፡ ማደሪያዎችን ፡ ሠሩ ። ሥርዓትን ፡ ምስጋናን ፡ የእመቤታችንን ፡የማርያምን ፡ ውዳሴ ፡ አስተማራቸው።

www.ethiopianorthodox.org

፲፩፡ ወበእሑቲ ፡ ዕለት ፡ በጊዜ ፡ መንፈቀ ፡
ሌሊት፡ እንዘ ፡ ይቀውሙ ፡ ወይጼልዩ ፡
ውዳሴሃ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ አስተ
ርአዮ ፡ ቅዱስ፡ አትናቴዎስ ፡ ሐዋርያዊ ፡
ወከሠተ ፡ ሎቱ ፡ ምሥጢራተ ፡ መንፈሳ
ውያተ ፡ ወእምይእቲ፡ ዕለት ፡ ኮኑ ፡ ዘይ
ዜክሩ፡ ስሞ ፡ ለቅዱስ ፡ አትናቴዎስ ፡
በተፍጻሜተ፡ ጸሎተ ፡ ፫ቱ ፡ ደቂቅ ።
፲፪፡ ወእምዝ ፡ በእሑቲ ፡ ዕለት ፡ አስተርአየቶ ፡
እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡
ወትቤሎ ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ መካን ፡ ቤትየ ፡
ውእቱ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡ ወአነሂ ፡ እሄሉ ፡
ምስለ ፡ ውሉድከ ፡ በከመ ፡ ሀሎኩ ፡
ምስሌከ። ወይሰመይ ፡ ስምየ ፡ ላዕለ ፡ ዝንቱ፡
ደብር ፡ እስመ ፡ ይእቲ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
ዘኮነት ፡ በስማ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡
ወላዲተ ፡ አምላክ ።
፲፫፡ ወኮኑ ፡ በላዕላይ ፡ ግብጽ ፡ አድባራት ፡
ወዘውስቴቶሙ ፡ መነኮሳት ፡ ፈተዉ ፡
ከመ፡ ይኩኑ ፡ ታሕተ ፡ ጽላሎቱ ፡ ለቅዱስ ፡
አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ከማ ፡ ወፈነዉ ፡ ኀቤሁ ፡
እንዘ ፡ ይስእልዎ ፡ ከመ ፡ ይብጻሕ ፡
ኀቤሆሙ ፡ ወይምሀሮሙ ፡ ሥርዓተ ፡ ወሕገ፡
ዘዚአሁ ። ውእቱሰ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ከማ ፡
ጸውዖ ፡ ለ፩ እምአርድእቱ ፡ ዘስሙ ፡ ሲኖዳ ፡
ወይቤሎ ፡ እስከ ፡ እገብእ ፡ አነ ፡ ቁም ፡
ለአኃው ፡ ውእቱኒ ፡ ቆመ ፡ በእገሪሁ ፡
ኢኖመ ፡ ወኢሰከበ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ እስከ ፡
ገብአ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ከማ ፡ እምላዕላይ ፡
ግብጽ ።
፲፬፡ ወሶበ ፡ ገብአ ፡ ረከቦ ፡ ቀዊሞ ፡ በእገሪሁ ፡
እስከ ፡ ሐብጣ ፡ ወዕዔ ፡ ይወጽእ ፡ እምኔሆን፡
ወይቤሎ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ከማ ፡ ኦ ፡
ወልድየ፡ ሲኖዳ ፡ ለምንት ፡ ገበርከ ፡ ዘንተ ፡
ወአንሰ ፡ ዘአዘዝኩከ ፡ ትቁም ፡ ለአኃው ፡
ህየንቴየ ፡ ወተሐውጽ ፡ ምግባሮሙ ፡ ወተ
አዝዘሙ ፡ ውእቱኒ ፡ ሰገደ ፡ ታሕተ ፡ እግ
ሪሁ፡ ወይቤሎ ፡ ሰረይ ፡ ሊተ ፡ ኦ ፡ አቡየ፡
እስመ ፡ አነ ፡ ኢገበርኩ ፡ ምንተኒ ፡ እም
ሠናያት ።

፲፭፡ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ቀርበ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ከመ ፡
ይፍልስ ፡ እምፃማ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ኃላፊ ፡

፲፩፡ በአንዲትም ፡ ዕለት ፡ የእመቤታችንን ፡
የማርያምን ፡ ውዳሴዋን ፡ በመንፈቀ ፡
ሌሊት፡ ቆመው ፡ ሲጸልዩ ፡ የከበረ ፡
ሐዋርያዊ ፡ አትናቴዎስ ፡ ተገለጠለትና ፡
የረቀቁ ፡ ምሥጢሮችን ፡ ገለጠለት ፡
ከዚያችም ፡ ዕለት ፡ ወዲህ ፡ በሠለስቱ፡
ደቂቅ፡ ጸሎት ፡ ፍጻሜ ፡ የቅዱስ ፡ አትናቴ
ዎስን ፡ ስም ፡ የሚጠሩ ፡ ሆኑ ።
፲፪፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በአንዲት ፡ ዕለት ፡ እመ
ቤታችን ፡ የከበረች ፡ ድንግል ፡ ማርያም፡
ተገልጣለት ፡ ይህች ፡ ቦታ ፡ ለዘላለሙ ፡ የኔ ፡
ማደሪያ ፡ ናት፡ እኔም፡ ካንተ ፡ ጋር ፡
እንደኖርኩ ፡ ከልጆችህ ፡ ጋር ፡ እኖ
ራለሁ፡ ስሜም ፡ በዚህ፡ ገዳም ፡ ሲጠራ፡
ይኖራል ፡ አለችው ፡ ይህች ፡ ቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ አምላክን ፡ በወለደች፡ በእመቤ
ታችን ፡ ስም፡ የተሠራች ፡ ናትና።
፲፫፡ በላይኛውም ፡ ግብጽ ፡ ገዳማት ፡ አሉ ፡
በውስጣቸውም ፡ የሚኖሩ ፡ መነኰሳት ፡
በእርሱ ፡ ጥላ ፡ ሥር ፡ መሆን ፡ ወደው ፡
ወደርሳቸው ፡ መጥቶ ፡ የርሱን ፡ ሥርዓት፡
ማኅበርና ፡ ሕግ ፡ ያስተምራቸው ፡ ዘንድ ፡
እየለመኑት ፡ ወደርሱ ፡ መልእክትን ፡ ላኩ ፡
እርሱም ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ አንዱን ፡
ስሙ ፡ ሲኖዳ ፡ የሚባለውን ፡ ጠርቶ ፡ እኔ ፡
እስከምመለስ ፡ ለመነኰሳቱ፡ ቁምላቸው ፡
አለው ። እሱም ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ከማ ፡
ከላይኛው ፡ ግብጽ ፡ እስከሚመለስ ፡
በእግሮቹ ፡ ቆመ ፡ አላንቀላፋም ፡ በምድር ፡
ላይም ፡ አልተኛም።
፲፬፡ በተመለሰም ፡ ጊዜ ፡ ቆሞ ፡ እግሮቹም ፡
አብጠው ፡ ተልተው ፡ ከእሳቸው ፡ ትል ፡
ሲወጣ ፡ አገኘው ፡ አባ ፡ ዮሐንስም ፡ ልጄ፡
ሲኖዳ ፡ ሆይ ፡ ለምን ፡ ይህን ፡ አደረግህ ፡ እኔ፡
ቁምላቸው ፡ ብዬ ፡ ያዘዝኩህ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡
ሁነህ ፡ እንድታስተዳድራቸው ፡ ሥራቸ
ውን፡ እንድትቆጣጠር፡ እንድታዝዛቸውም ፡
ነበር ፡ አለው ። እርሱም ፡ ከእግሮቹ ፡ በታች ፡
ሰግዶ ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ ከበጎ፡
ሥራ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ አልሠራሁምና
አለው።
፲፭፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ ከኃላፊው ፡ ዓለም ፡
ድካም ፡ ተለይቶ ፡ በዘላለማዊ ፡ የተድላ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወያዕርፍ ፡ ውስተ ፡ ማኅደረ ፡ ተድላ ፡ ዘለዓለም ፡ ደ.ወየ ፡ ንስቲተ ፡ ወመጠወ ፡ ነፍሶ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ለእግዚአብሔር ።

፲፮፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም ሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

ማደሪያ ፡ የሚያርፍበት ፡ ጊዜ ፡ ሲቀርብ ፡ ጥቂት ፡ ታሞ ፡ ነፍሱን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ አስረከበ ።

፲፮፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ ንም ፡ በዚህ ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

## <u>አርኬ</u>

ሰላም፡ለአጻብዒከ፡ወለአጽፋሪከ፡ዓዲ።ዘአስተርአያ፡በጸሎት፡በአምሳለ፡ማኅቶት፡ነዳዲ።ፈጻሜ፡በፅዓት፡ዮሐንስ፡ከማ፡እንበለ፡ትጕንዲ።ወሰላም፡ካዕበ፡ለአባ፡ዳሩዲ።አርዑተ፡ቅዱሳን፡ዘተበውሐ፡በክሣዱ፡ይውዲ።

፲፯፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፉ ፡ ፫ቱ ፡ ቅዱሳን ፡ መቃብያን ፡ በከዊነ ፡ ስምዕ ፡ በመንግሥተ ፡ ሜዶናውያን ፡ ወሞ፩ባውያን ።

፲፰፤ ወሀሎ ፡ አሐዱ ፡ ንጉሥ ፡ ዘስሙ ፡ ጺሩጻ ይዳን ፡ ፈታዊሃ ፡ ለእኪት ፡ ወቦ ፡ ዘታሕተ ፡ እዴሁ ፡ ጽኑዓን ፡ ሐራ ፡ ወቦ ፡ አማልክት ፡ ዘያመልኮሙ ፶ ፡ በአምሳለ ፡ ዕደው ፡ ወ፳ በአምሳለ ፡ አንስት ፡ ወይሠውዕ ሎሙ ፡ ነግሀ ፡ ወሠርከ ፡ ወለሰብእኒ ፡ ያጌብሮሙ ፡ ከመ ፡ ይሡዑ ፡ ሎሙ ።

፲፱፤ ወሀሎ ፩ ብእሲ ፡ ዘእምሕዝበ ፡ ብንያም ፡ ዘስሙ ፡ መቃቢስ ፡ ወቦቱ ፡ ሠለስቱ፡ ደቂቅ፡ ሠናያን ፡ ወጽኑዓን ፡ ወቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘየሐንቅ ፡ ድበ ፡ ወይቀትል ፡ ከመ ፡ እንተ ፡ ዶርሆ ፡ ወቦ ፡ ዘይቀትል ፡ አንበሳ ፡ በአሐቲ ፡ ዝብጠት ፡ ወቦ ፡ በውስተ ፡ ጸብእ ፡ ዘይ ቀትል፡ በአሐቲ ፡ መሊሐተ ፡ ሰይፍ ፡ ምእተ፡ ብእሴ ። ወከመዝ ፡ አስማቲሆሙ ፡ ሲላ ፡ አብያ ፡ ፈንቶስ ፡ ወእሙንቱ ፡ ሥርግዋን ፡ በስን፡ ወበሞገስ ፡ ወእምኵሉሰ፡ እንተ ፡ ትኄይስ ፡ ስነ ፡ ልቦሙ ፡ እስመ ፡ ያመልክዎ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወኢ.ፈርህዎ፡ ለሞተ ፡ ሥጋ ።

፳፤ ወይቤሎሙ ፡ ንጉሥ ፡ አ ፡ አንትሙ ፡ ዐላ ውያን ፡ እፎኑ ፡ ኢትሰግዱ ፡ ለአማልክትየ፡ ወአውሥእዎ ፡ በ፩ ፡ ቃል ፡ ወይቤልዎ ንሕነ ፡ ኢንሰግድ ፡ ለአማልክቲከ ፡ ርኩሳን አላ ፡ ንሰግድ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘፈጠረ ፡ ኪያነ ፡

፲፯፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡ በሜዶናውያንና ፡ በሞዓባ ውያን ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ የከበሩ፡ አምስቱ ፡ መቃባውያን ፡ በሰማዕትነት ፡ ሞቱ ።

፲፰፤ ከፋትን ፡ የሚወዳት ፡ ስሙ ፡ ጺሩጻይዳን፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ንጉሥ ፡ ነበረ ፡ ከሥል ጣኑም ፡ በታች ፡ የጸኑ ፡ ጭፍሮች ፡ አሉ ፡ የሚያመልካቸውም ፡ ኃምሳ ፡ በወንዶች ፡ ሃያ ፡ በሴቶች ፡ አምሳል ፡ የታሠሩ ፡ ጣዖቶች፡ አሉት ፡ በጥዋትና ፡ በማታ ፡ መሥዋዕትን ፡ ያቀርብላቸዋል ፡ ሰዎችንም፡ እንዲሠዉ ፡ ያስገድዳቸው ፡ ነበር።

፲፱፤ ከብንያም ፡ ወገንም ፡ የሆነ ፡ ስሙ ፡ መቃ ቢስ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ ለርሱም ፣ መልከ ፡ መልካሞች ፡ የጸኑ ፡ ሦስት፡ ልጆች ፣ አሉት ፡ ከእርሳቸውም ፡ ግሥላውን ፡ እንደ ፡ ዶሮ፡ አንቆ ፡ የሚ ገድል፡ አለ ። በአንዲት ፡ ዓመታትም፡ አንበሳ ፡ የሚገድል ፡ አለ ። በአንድ ፡ ጊዜ፡ ሰይፍ ፡ መዘዛም ፡ በሰልፍ ፡ ውስጥ ፡ መቶ ፡ ሰው ፡ የሚገድል ፡ አለ ፡ እነርሱም፡ ውበትንና ፡ ግርማን ፡ የተሸለሙ፡ ናቸው፡ ከሁሉ ፡ የሚሻል ፡ የልብ ፡ ውበትንም ፡ እነርሱ ፡ የሥጋ ፡ ሞትን ፡ ያልፈሩ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያመልኩ ፡ ናቸውና ።

፳፤ ንጉሡም ፡ እናንት፡ ዓመፀኞች ፡ ለአማል ክቶቼ፡ እንዴት ፡ አትሰግዱም ፡ አላቸው ፡ እነሱም ፡ በአንድ ፡ ቃል ፡ እኛ ፡ ለረከሱ ፡ አማልክቶችህ ፡ አንሰግድም ፡ እኛንም ፡ አንተንም ፡ ለፈጠረ፡ ሕዝቡንም ፡ በዕው ነትና፡ በቅንነት ፡ ትጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ ላነገሠህ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወኪያከ፡ ወአንገሥከ፡ ከመ ፡ ትርዓይ ፡ ሕዝቦ ፡
በጽድቅ ፡ ወበርትዕ ፡ አንተሰ ፡ ተዓወርከ ።

፳፩፤ ወእምዝ ፡ አዘዘ ፡ ይስድዱ ፡ ላዕሌሆሙ ፡
አራዊተ ፡ ርኁባነ ፡ ወእሙንቱ ፡ አራዊት ፡
ሰገዱ ፡ ሎሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ወተመይጡሙ ፡
ቀተሉ ፡ እምዐላውያን ፡ ፸ወ፰ተ ፡ ሰብአ ፡
ወበዕፁብ ፡ ግብር ፡ ሜጥዎሙ ፡ ውስተ ፡
ማኅደሮሙ ፡ ወለእሉሰ ፡ ቅዱሳን ፡ ወደ
ይዎሙ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ፡ ወመጽኡ ፡
ካልአን ፡ ክልኤቱ ፡ አኃዊሆሙ ፡ ወተደመሩ ፡
ምስሌሆሙ ፡ ወንጉሥኒ ፡ ርእዮሙ ፡ ለ፰ቱ ፡
አኃው ፡ ተምዐ ፡ ጥቀ ፡ ወአዘዘ ፡ ይውር
ውዎሙ ፡ ውስተ ፡ እቶነ ፡ እሳት ፡ ዘይነድድ ፡
ወመጠዉ ፡ ነፍሶሙ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ እግዚአ
ብሔር ።

፳፪፤ ወእምዝ ፡ አዘዘ ፡ ካዕበ ፡ ያውዕዩ ፡ ሥጋሆሙ ፡
ለቅዱሳን ፡ እስከ ፡ ኮነ ፡ ሐመደ ፡ ወኢለከፎሙ ፡
እሳት ፡ ግሙራ ፡ ወዓዲ ፡ አዘዘ ፡ ይእሥሩ ፡
ውስተ ፡ ሥጋሆሙ ፡ አዕባነ ፡ ክቡዳነ ፡ ወያስጥ
ምዎሙ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ ወአልቦ ፡
ዘውሕጠሙ ፡ ውሒጠ ፡ ወአዘዘ ፡ ይግድ
ፍዎሙ ፡ ለአራዊተ ፡ ገዳም ፡ ወለአዕዋፈ ፡
ሰማይ ፡ ወነበሩ ፡ ፲ወ፬ተ ፡ መዋዕለ ፡ እንዘ ፡
ይጼልልዎሙ ፡ ወይከድንዎሙ ፡ አዕዋፍ ፡
በክነፊሆሙ ፡ ወበረቀ ፡ ሥጋሆሙ፡ ከመ ፡
እግረ ፡ ፀሐይ ፡ ወእምዝ ፡ አዘዘ ፡ ይቅብ
ርዎሙ ።

፳፫፤ ወእምዝ ፡ አስተርአይዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ረሲዕ ፡
ንጉሥ ፡ እሉ ፡ ቅዱሳን ፡ ሌሊተ ፡ እንዘ ፡ ስኩብ ፡
ዲበ ፡ ዐራቱ ፡ ወሰይፍ ፡ ውስተ ፡ እደዊሆሙ ፡
ወቆሙ ፡ ቅድሜሁ ፡ ቀኑጡዓነ ። ወነቂሖ ፡
ፈርሀ ፡ ወርዕደ ፡ እስመ፡ መሰሎ ፡ ዘይትቤ
ቀልዎ ።

፳፬፤ ወይቤልዎ ፡ እሉ ፡ ቅዱሳን ፡ ሰማዕታት ፡
ንሕነሰ ፡ ኢንፈድየከ ፡ እኩየ ፡ በእንተ ፡ ዘገ
በርከ ፡ እኩየ ፡ ላዕሌነ ፡ ባሕቱ ፡ ሀሎ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ አምላክነ ፡ ዘይፈድየከ ፡ ወበእንተ ፡
ሕጸጸ ፡ አእምሮትከ ፡ ወጽማዌ ፡ ልብከ ፡
ተግህድነ ፡ ለከ ፡ ወለነሰ ፡ እንዘ ፡ ይመስለከ ፡
ዘቀተልከነ ፡ አስተዳሎከ ፡ ለነ ፡ ሕይወተ ፡
አንተሰ ፡ ወገነውተ ፡ አማልክቲከ ፡ ትወርዱ ፡
ውስተ ፡ ገሀነም ፡ ዘአልቦ ፡ ሙፃእ ፡ ወእምዝ ፡
ተሠወሩ ፡ እምኔሁ ።

አንተ ፡ ግን ፡ ቸለል ፡ ብለህ ፡ ለዘነጋኸው ።
ዚአብሔር ፡ እንሰግዳለን ፡ እንጂ ፡ ብለው ፡
መለሱለት ።

፳፩፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡የተራቡ ፡ አራዊትን ፡ በላ
ያቸው ፡ እንዲሰዱ ፡ አዘዘ ፡ እነዚያም ፡
ለቅዱሳን ፡ ሰግደው ፡ ተመልሰው ፡ ከከሀ
ድያን ፡ ሰባ ፡ አምስት ፡ ሰዎችን ፡ ገደሉ ፡
በጭንቅም ፡ ወደማደሪያቸው ፡ መለሱ
አቸው። አሊህንም ፡ ቅዱሳን ፡ ወደ ፡ ወህኒ ፡
ቤት ፡ ጨመሩአቸው ፡ ሌሎች ፡ ሁለት ፡ ወንድ
ሞቻቸውም ፡ መጥተው ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ተቀ
ላቀሉ ። ንጉሡም ፡ አምስቱን ፡ ወንድማ
ማቾች ፡ አይቶ ፡ እጅግ ፡ ተቆጥቶ ፡ ከሚነድ ፡
እሳት ፡ ውስጥ ፡ ይጨምሩአቸው ፡ ዘንድ ፡
አዘዘ ፡ ነፍሳቸውንም ፡ በእግዚአብሔር ፡
እጅ ፡ አስረከቡ ።

፳፪፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የቅዱሳኑን ፡ ሥጋ ፡ አመድ ፡
እስከሚሆን ፡ ያቃጥሉ ፡ ዘንድ ፡ ዳግመኛ ፡
አዘዘ ፡ እሳቱም ፡ ከቶ ፡ አልነካቸውም ፡ ዳግ
መኛም ፡ ከባዶች ፡ ደንጊያዎችን ፡ ከሥ
ጋቸው ፡ ጋር ፡ አሥረው ፡ ከባሕር ፡ ውስጥ ፡ ያሰ
ጥሟቸው ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ ባሕሩም ፡
አልዋጣቸው ፡ ለዱር ፡ አራዊትና ፡ ለሰማይ ፡
ወፎች ፡ እንዲጥሏቸው፡ አዘዘ ፡ አዕዋፍም ፡
ክንፎቻቸውን ፡ ጋርደውላቸው ፡ ዐሥራ ፡
አራት ፡ ቀኖች ፡ ኖሩ ፡ ሥጋቸውም ፡ እንደ ፡
ፀሐይ ፡ አበራ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይቀብሩአቸው ፡
ዘንድ ፡ አዘዘ።

፳፫ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ያንን ፡ የእግዚ
አብሔርን ፡ ሕግ ፡ የዘነጋ ፡ ንጉሥ ፡ ሌሊት ፡
በዐልጋው ፡ ላይ ፡ ተኝቶ ፡ ሳለ ፡ እሊህ ፡
ቅዱሳን፡ ተቆጥተው ፡ ሰይፋቸውን ፡ መዝ
ዘው ፡ በፊቱ ፡ ቁመው ፡ ታዩት ፡ በነቃም ፡ ጊዜ ፡
የሚበቀሉት ፡ መስሎታልና ፡ ፈርቶ ፡ ተንቀ
ጠቀጠ።

፳፬፤ እነዚያም ፡ የከበሩ ፡ ሰማዕታት ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡
ስላደረግህብን ፡ እኛስ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ አንከፍ
ልህም ፡ በነፍስ ፡ ፍዳ ፡ የሚያመጣ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ነውና ፡ ፍዳንስ ፡ የሚከፍልህ ፡ ፈጣሪ
ያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ አለ። ነገር ፡ ግን ፡ ስለዕ
ውቀትህ ፡ ማነስና ፡ ስለ ፡ ልቡናህ ፡ ድንቁርና ፡
እኛ ፡ ደኅነኞች ፡ እንደሆን ፡ ተገልጠን ፡
ታየንህ ፡ እኛንስ ፡ የገደልከን ፡ መስሎህ ፡
ድኅነትን ፡ አዘጋጀህልን ። የጣዖቶችህ ፡
ካህናትና ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ለዘላለሙ ፡ መውጫ ፡
ወደሌለባት ፡ ወደ ፡ ገሀነም ፡ ትወርዳላችሁ ፡
አሉት ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከርሱ ፡ ተሠወሩ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፫፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ፡በጸሎቶሙ፡ለቅዱሳን፡ሰማዕት፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም፡አሜን።

፳፫፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ ንም ፡ በከበሩ ፡ ሰማዕታት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ እብል ፡ ለመቃብያን ፡ ኃምስቱ ። ተንሢአሙ ፡ ሶቤ ፡ እምድኅረ ፡ በእሳት ፡ ሞቱ ። ለዘቀ ተሎሙ፡ንጉሥ፡ይቢልዎ፡ሎቱ።ይኩነነ፡ረብሐ፡ነፍስ፡ህየንተ፡ሞትነ፡ዝንቱ።በእግዚአብሔር፡እመነ፡ ወተወከል፡ቦቱ።

፳፬፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ካዕበ ፡ ተዘካሮሙ ፡ ለቅ ዱሳን፡ ኒቆላዎስ ፡ መኰንን ፡ ወብእሲቱ ፡ ወዳንኤል፡ንኡስ፡መነኰስ፡መስተጋድል።

* * *

፩፤ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፳ወ፬፡ ለታኅሣሥ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት፡ኮነት፡ሰማዕተ፡ቅድስት፡አንስጣስያ፡ እምሀገረ፡ሮሜ።

፪፤ወለይእቲ፡ቅድስት፡አቡሃ፡ዘያመልክ፡ጣዖተ፡ እማሰ ፡ ክርስቲያናዊት ፡ ይእቲ ፡ ወሶበ ፡ ወለደታ ፡ ለዛቲ ፡ ቅድስት ፡ አጥመቀታ ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ በኅቡእ ፡ ዘእንበለ ፡ ያእምር፡አቡሃ፡ሶበሰ፡አእምረ፡አቡሃ፡እምኢ ተክህላ ፡ አጥምቆታ ፡ ወእምዝ ፡ ሐፀንታ ፡ በሠናይ ፡ ተሐፅኖ ፡ ወመሀረታ ፡ ትምህርተ ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን ፡ እስከ ፡ አጽንዓታ ፡ በሃይ ማኖት ፡ ርትዕት ፡ ወኢተክህሎ ፡ ለመኑሂ ፡ ይወልጥ፡ግዕዛ።

፫፤ ወሶበ ፡ ልሕቀት ፡ ወወርዘወት ፡ አስተዋሰባ ፡ አቡሃ ፡ ለብእሲ፡ ከሀዲ ፡ ዘከማሁ ፡ ይእቲሰ ፡ ጸልአቶ፡ፈድፋደ፡ወኢፈቀደት፡ትትራከብ፡ ምስሌሁ፡ግሙራ፡ወኮነት፡ዘታመከኒ፡በምክ ንያተ ፡ አንስት ፡ ዘይከውን ፡ ላዕሌሆን ፡ ወምዕረ፡ በደዌ ፡ ወትለብስ ፡ አልባሳተ ፡ ርሱሐተ ፡ ወኅሱራተ ፡ ከመ ፡ ይጽልአ ፡ በዝንቱ፡ወይትፈለጥ፡እምኔሃ።

፬፤ ወሶበ ፡ ይወጽእ ፡ ምታ ፡ ውስተ ፡ ወፍሩ ፡ ወይእቲ፡ ትወጽእ ፡ ወትወፍር ፡ ለሐውጾ ፡ ሙቁሐን ፡ ዘበእንተ ፡ ሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ወትትለአኮሙ፡ወትሁቦሙ፡መፍቅዶሙ።

፭፤ወሶበ፡አእመረ፡ምታ፡ዘትገብር፡ዘንተ፡ዐጸዋ፡ ውስተ፡ቤት፡ከመ፡ኢትጻእ፡አፍአ፡ወኮነት፡

፳፬፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ ደግሞ ፡ የከበሩ ፡ የመኰንኑ ፡ የኒቆላዎስና ፡ የታማኝ ፡ ሚስቱ ፡ ተገዳይ ፡ የሆነ፡የታናሽ፡መነኰስ፡የዳንኤል፡መታሰ ቢያቸው፡ነው።

* * *

፩፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ታኅሣሥ ፡ ሃያ ፡ ስድስት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ከሮሚ ፡ አገር ፡ የከበረች፡ አንስጣስያ፡በሰማዕትነት፡ሞተች።

፪፤ የዚችም ፡ ቅድስት ፡ አባቷ ፡ ጣዖትን ፡ የሚያ መልክ፡ ነው ፡ እናቷ ፡ ግን ፡ ክርስቲያን ፡ ናት ፡ ይቺንም፡ቅድስት፡በወለደቻት፡ጊዜ፡አባቷ፡ ሳያውቅ ፡ የክርስትና ፡ ጥምቀትን ፡ በሥውር ፡ አጠመቀቻት፡አውቆ፡ቢሆን፡ማጥመቅ፡ባል ተቻላትም ፡ ነበር። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በበጎ ፡ አስ ተዳደግ ፡ አሳደገቻት ፡ በቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ እስከ፡አጸናቻት፡ድረስ፡የቤተ፡ክርስቲያንን፡ ትምህርት አስተማረቻት ፡ ጠባይዋን ፡ መለ ወጥ፡ለማንም፡አልተቻለውም።

፫፤ አድጋ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ በአደረሰችም ፡ ጊዜ፡ አባቷ፡እንደርሱ፡ላለ፡ከሀዲ፡ሰው፡አጋባት፡ እርሷ፡ግን፡እጅግ፡ጠላችው፡ልትገናኘውም፡ አልፈለገችም ፡ በሴቶች ፡ ላይ ፡ በሚሆነው ፡ ግዳጅና ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በደዌ ፡ የምታ መካኝ ፡ ሆነች ፡ እንዲጠላትና ፡ ከእርሷ ፡ እንዲለይ ፡ ያደፈና ፡ የቆሸሸ ፡ የተጐሳቈለ ፡ ልብስ፡ትለብስ፡ነበር።

፬፤ባሏም፡ወደ፡ሥራው፡ወጥቶ፡በተሰማራ፡ጊዜ፡ እርሷም ፡ ስለ ፡ ቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ የታሠሩ ፡ እስረኞችን ፡ ትጐበኝ ፡ ዘንድ ፡ ትሰማራለች ፡ ታገለግላቸውና፡የሚሹትን፡ትሰጣቸዋለች።

፭፤ባሏም፡ይህን፡የምትሠራውን፡በአወቀ፡ጊዜ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ እንዳትወጣ ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ ዘጋባት ፡ እርሷም ፡ ከእጁ ፡ ያወጣት ፡ ዘንድ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ዘትስእል ፡ ኀበ፡ እግዚአብሔር ፡ ወትረ ፡ በብካይ፡መሪር፡ከመ፡ይፍትሓ፡እምእዴሁ፡ ወሰምዐ ፡ እግዚእነ ፡ ስእለታ ፡ አጥፍአ ፡ ለውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ወተፈሥሐት ፡ ይእቲ ፡ በሞቱ ፡ ወእምዝ ፡ ወሀበት ፡ ኵሎ ፡ ንዋያ ፡ ለነዳያን ፡ ወለምስኪናን ፡ ወለሙቁሐን ፡ ተአማንያን፡በእንተ፡ሃይማኖት፡ርትዕት።

፮:ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ዜናሃ ፡ መኰንነ ፡ ሀገረ ፡ ሮሜ ፡ ፈነወ፡ላእካነ፡ወአብጽሓ፡ኀቤሁ፡ወተሰአላ፡ በእንተ ፡ ሃይማኖታ ፡ ወተአመነት ፡ በቅድሜሁ ፡ ከመ ፡ ይእቲ ፡ ክርስቲያናዊት ፡ ወተናገራ ፡ ወተወካየዳ ፡ ኪዳናተ ፡ ወኢተክህሎ ፡ ከመ፡ያጽንና፡እምክራ፡ሠናይ።

፯ ፡ ወሶቢሃ ፡ ኰነና ፡ በብዙኅ ፡ መክፈልተ ፡ ኵነኔ ፡ ወእምዝ ፡ አዘዘ ፡ ያስጥምዋ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ ወአዕረጋ ፡ ባሕር ፡ ሕያውታ ፡ ወአዘዘ ፡ ካዕበ ፡ ከመ ፡ ያስክብዋ ፡ ማዕከለ ፡ ፬ ፡ መታክል ፡ ወይእሥርዋ ፡ ሰፊሐሙ ፡ ወይቅሥፍዋ ፡ መቅሠፍተ ፡ ዐቢየ ፡ ወማሕመሜ ፡ ወገብሩ ፡ ባቲ ፡ በከመ ፡ አዘዘ ፡ መኰንን ፡ ወባሕቱ ፡ ኢበጽሓ ፡ ምንተኒ ፡ እምእኩይ ፡ ወእምዝ ፡ አዘዘ ፡ ይደይዋ ፡ ውስተ ፡ እቶነ ፡ እሳት ፡ ዘአስተዳለዉ ፡ ላቲ ፡ ወሶበ ፡ ወደይዋ ፡ መጠወት ፡ ነፍሳ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወነሥአት ፡ አክሊለ ፡ ስምዕ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት።

፰ ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎታ ፡ ወበረከታ ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

አዘውትራ ፡ በመረረ ፡ ልቅሶ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የምትለምን ፡ ሆነች ፡ ጌታችንም ፡ ልመናዋን ፡ ሰምቶ ፡ ያንን ፡ ሰው ፡ አጠፋው ። እርሷም ፡ በሞቱ ፡ ደስ ፡ አላት ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ለድኆችና ፡ ለምስኪኖች ፡ ስለ ፡ ቀናች ፡ ሃይማኖትም ፡ በመታመን ፡ ለታሠሩ ፡ እሥረኞች ፡ ገንዘቧን ፡ ሁሉ ፡ ሰጠች።

፯ ፡ የሮሜ ፡ አገረ ፡ ገዢም ፡ ዜናዋን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ መልእክተኞችን ፡ ልኮ ፡ ወደርሱ ፡ አስመጣት ፡ ስለ ፡ ሃይማኖቷም ፡ ጠየቃት ፡ ክርስቲያን ፡ እንደሆነች ፡ በፊቱ ፡ ታመነች ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ በመግባትም ፡ ተናገራት ፡ ከበጎ ፡ ምክርዋ ፡ አውጥቶ ፡ ወደ ፡ ክህደት ፡ ሊያዘነብላት ፡ አልቻለም።

፰ ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ በብዙ ፡ በተለያየ ፡ ሥቃይ ፡ አሠቃያት ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ያሠጥሟት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ ባሕሩም ፡ በሕይወቷ ፡ ተፋት ፡ ዳግመኛም ፡ በአራት ፡ ካስማ ፡ መካከል ፡ አስተኝተው ፡ ዘርግተው ፡ አሥረው ፡ ታላቅና ፡ ጽኑዕ ፡ የሆነ ፡ ግርፋትን ፡ ይገርፋዋት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ መኰንኑም ፡ እንዳዘዘ ፡ አደረጉባት ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ምን ፡ ጉዳት ፡ አልደረሰባትም ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አዘጋጁላት ፡ የእሳት ፡ ማንደጃ ፡ ውስጥ ፡ ይጨምርዋት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ በጨመርዋትም ፡ ጊዜ ፡ ነፍሷን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ሰጠች ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያትም ፡ የሰማዕትነት ፡ አክሊልን ፡ ተቀበለች።

፰ ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በጸሎቷ ፡ ይማረን ፡ በረከቷም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ይኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለአንስጣስያ ፡ ጣዖተ ፡ አቡሃ ፡ መኒና ። እንተ ፡ ተለወት ፡ ፍጹመ ፡ ሃይማኖተ ፡ እማ ፡ ክርስትና ። እስከ ፡ መኰንን ፡ ዕልው ፡ በዋዕየ ፡ እሳት ፡ አርሰና ። ወሰላም ፡ ካዕበ ፡ ለብፅዕት ፡ ዮልያና ። ዘተሳተፈት ፡ ክብረ ፡ ሰማዕት ፡ አሐደ ፡ ከዊና።

፩ ፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካራ ፡ ለቅድስት ፡ ዮልያና ፡ ሰማዕት ። ወተዝካሩ ፡ ለአቦሊ ፡ ጻድቅ ፡ በረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

፩ ፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ የከበረች ፡ የሰማዕት ፡ ዮልያና ፡ መታሰቢያዋ ፡ ነው ፡ የጻድቁ ፡ አቦሊም ፡ መታሰቢያው ፡ ነው ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

## አርኬ

ሰላም፡ለአቦሊ፡እንተ፡ጸለየ፡ጸሎተ። በእንተ፡ሲሳዩ፡ወአራዙ፡እንዘ፡ኢይሔሊ፡ምንተ። ወዲበ፡ዝኒ፡ ወሰከ፡ዲበ፡ሥጋሁ፡መቅሠፍተ። ወይዌግር፡ርእሶ፡ውስተ፡ቀላየ፡ባሕር፡መትሕተ። እንዘ፡እገሪሁ፡የዓሥር፡ ዲበ፡ዕፅ፡መልዕልተ።

* * *

፩ ፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አሐዱ ፡ አምላክ ፡ አመ ፡ ፳ወ፯ ለታኅሣሥ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ አብሳዲ፡ኤጲስቆጶስ።

፪፡አሜሃ፡ሶበ፡ሰምዐ፡ዜናሆሙ፡ዲዮቅልጥያኖስ፡ ንጉሥ ፡ ለኤጲስቆጶሳት ፡ ዐቢያን፡ አባ ፡ አብ ሳዲ፡ወአባ፡አላኒቆስ፡ዘላዕላይ፡ግብጽ፡ከመ፡ እሙንቱ፡ ያጸንዕዎሙ፡ለሕዝበ፡ክርስቲያን፡ ውስተ፡ሃይማኖት፡ርትዕት፡ዘእግዚእነ፡ኢየ ሱስ፡ክርስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት፡ወይሥዕሩ፡ አምልኮ፡አማልክት፡ወፈነወ፡ላእካነ፡ወአብ ጽሐሙ፡ኀቤሁ፡ወኰነኖሙ፡ኮነኔ፡ዐቢየ፡ ወቅዱስ፡አባ፡አብሳዲ፡ሰአሎሙ፡ለላእካን፡ ከመ፡ይትዓገሥዎ፡አሐተ፡ዕለተ፡ወሠርዐ፡ ቅዳሴ ፡ ቍርባን ፡ ወመጠዎሙ ፡ ለሕዝቡ ፡ ምሥጢረ ፡ ቅድሳት ፡ ወመሀሮሙ ፡ ከመ ፡ ይጽንዑ ፡ ውስተ ፡ ሃይማኖት ፡ ርትዕት ። ወእምዝ ፡ ተአምኆሙ ፡ ወወጽአ ፡ እምኀ ቤሆሙ፡ወገደፈ፡ነፍሶ፡ውስተ፡እደ፡እግዚአ ብሔር፡ወሖረ፡ምስለ፡ላእካን፡ወወሰድዎ፡ ኀበ፡አርያኖስ፡መኰንነ፡እንዴናው።

፫፡ወሶበ፡ርእየ፡መኰንን፡ገጾ፡ለአባ፡አብሳዲ፡ አንከረ፡እምአርአያሁ፡ወግርማሁ፡ወተራ ኅርኀ፡ሎቱ፡ወይቤሎ፡አንተ፡ብእሲ፡ክቡር፡ ወግሩም፡መሐክ፡ነፍሰከ፡ወስማዕ፡ቃሎ፡ ለንጉሥ።

፬፡ወአውሥአ፡ቅዱስ፡አብሳዲ፡ወይቤ፡አንሰ፡ ኢይሰምዕ፡ትእዛዘ፡ንጉሥ፡ወኢይዌልጥ፡ መንግሥተ፡ሰማያት፡በሕይወተ፡ዝ፡ዓለም፡ ኃላፊ፡ ወኮነ፡ ማዕከሎሙ፡ ብዙኅ፡ ተዋሥ ኦት፡ ወሶበ፡ ኢተመይጠ፡ እምክሩ፡ ሠናይ፡ አዘዘ፡መኰንን፡ከመ፡ይኰንንዎ፡በመንኰ ራኵር፡ ወይደይዎ፡ ውስተ፡ እቶነ፡ እሳት፡ ወዘንተ፡ ኵሎ፡ ተዓገሠ፡ ወእግዚአብሔር፡ አንሥኦ፡ጥዑየ፡ዘእንበለ፡ሙስና፡ወእምዝ፡ አዘዘ ፡ ከመ ፡ ይምትሩ ፡ ርእሶ ፡ በሰይፍ ፡ ወሰሚዖ ፡ አባ ፡ አብሳዲ ፡ ተፈሥሐ ፡ ዐቢየ ፡

* * *

፩ ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ታኅሣሥ ፡ ሃያ ፡ ሰባት፡በዚች፡ቀን፡የከበረ፡ኤጲስቆጶስ፡አባ፡ አብሳዴ፡በሰማዕትነት፡ሞተ።

፪፡ያን፡ጊዜ፡ታላላቆች፡የሆኑ፡የላይኛው፡ግብጽ፡ ኤጲስቆጶሳት፡አባ፡አብሳዲና፡አባ፡አላኒቆስ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ የጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክር ስቶስ፡በሆነች፡በቀናች፡ሃይማኖት፡ሕዝቡን፡ እንደሚያጸኑአቸው ፡ የአማልክትንም ፡ አም ልኮ ፡ እንደሚሽሩ ፡ ዜናቸውን ፡ ዲዮቅልጥ ያኖስ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡መልእክተኞችን ፡ ልኮ ፡ ወደርሱ፡አስመጥቶ፡ታላቅ፡ሥቃይን፡አሠቃ ያቸው። የከበረ፡አባ፡አብሳዲ፡ግን፡አንዲት፡ ቀን ፡ እንዲታገሡት ፡ መልእክተኞችን ፡ ለመ ናቸውና፡የቍርባን፡መሥዋዕትን፡አዘጋጅቶ፡ ቅዳሴ፡ቀድሶ፡ለሕዝቡ፡ሥጋውንና፡ደሙን፡ አቀበላቸው ። በቀናች ፡ ሃይማኖትም ፡ እንዲ ጸኑ ፡ አስተማራቸው ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በሰላ ምታ ፡ ተሰናብቷቸው ፡ ከእርሳቸው ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ፡ ሰውነቱንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ጥሎ ፡ ከመልእክተኞች ፡ ጋር ፡ ሔደ ፡ ወደ ፡ እንዴናው፡ገዥ፡ወደ፡አርያኖስ፡ወሰዱት።

፫፡መኰንኑም፡የአባ፡አብሳዲን፡ገጽ፡በአየ፡ጊዜ፡ ከአርአያውና ፡ ከግርማው ፡ የተነሣ ፡ አደነቀ ፡ ራራለትም ፡ እንዲህም ፡ አለው ፡ አንተ፡ የከበ ርክና፡የምታስፈራ፡ሰው፡ለነፍስህ፡እዘን፡የን ጉሥንም፡ቃል፡ሰማ።

፬፡አባ፡አብሳዲም፡እንዲህ፡ብሎ፡መለሰ፡እኔ፡ የንጉሥን ፡ ቃል ፡ ሰምቼ ፡ በዚህ ፡ በኃላፊው ፡ ዓለም፡ሕይወት፡መንግሥተ፡ሰማያትን፡አል ለውጥም ፡ በመካከላቸውም ፡ ብዙ ፡ የነገር ፡ ምልልስ ፡ ሆነ ፡ ከበጎ ፡ ምክሩ ፡ ባለተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ በመንኰራኵር ያሠቃዩትና ፡ ከእ ሳት ፡ ማንደጃ ፡ ውስጥም ፡ ይጨምሩት ፡ ዘንድ፡መኰንኑ፡አዘዘ፡ይህን፡ሁሉ፡ታገሠ፡ እግዚአብሔርም ፡ ያለ ፡ ጉዳት ፡ በጤና ፡ አስነሣው። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ራሱን ፡ ይቆርጡት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ አባ ፡ አብሳዲም ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሌሆሙ ፡ ወፈርሁ ፡ ዐቢየ ፡ ፍርሀተ ። ወይ
ቤሎሙ ፡ መልአክ ፡ ኢትፍርሁ ፡ እስመ ፡ ናሁ ፡
እዜንወክሙ ፡ ዐቢየ ፡ ዜና ፡ ፍሥሓ ፡ ዘይከውን ፡
ለክሙ ፡ ወለኵሉ ፡ ዓለም ።

፭፤ እስመ ፡ ተወልደ ፡ ለክሙ ፡ ዮም ፡ መድኀን ፡
ዘውእቱ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእ ፡ ቡሩክ ፡ በሀገረ ፡
ዳዊት ። ወከመዝ ፡ ትእምርቱ ፡ ለክሙ ፡ ትረ
ክቡ ፡ ሕፃነ ፡ እሡረ ፡ መንኰብያቲሁ ፡ ወጥ
ብሉለ ፡ በአጽርቅት ፡ ወስኩበ ፡ ውስተ ፡ ጎል ።

፮፤ ወግብተ ፡ መጽኡ ፡ ምስለ ፡ ውእቱ ፡ መልአክ ፡
ብዙኃን ፡ ሐራ ፡ ሰማይ ፡ እንዘ ፡ ይሴብሕዎ ፡ ለእ
ግዚአብሔር ፡ ወይብሉ ፡ ስብሐት ፡ ለእግዚአ
ብሔር ፡ በሰማያት ፡ ወሰላም ፡ በምድር ፡ ሥም
ረቱ ፡ ለሰብእ ።

፯፤ ወእምዝ ፡ ዐሪጎሙ ፡ መላእክት ፡ እምኅቤሆሙ ፡
ውስተ ፡ ሰማይ ፡ ይቤሉ ፡ እሙንቱ ፡ ሰብእ ፡
ኖሎት ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ንዑ ፡ ንሑር ፡ እስከ ፡
ቤተ ፡ ልሔም ፡ ወናእምር ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡ ዘአር
አየነ ፡ እግዚአብሔር ።

፰፤ ወሖሩ ፡ ፍጡነ ፡ ወረከብዎሙ ፡ ለማርያም ፡
ወለዮሴፍ ፡ ወለሕፃንኒ ፡ ይሰክብ ፡ ውስተ ፡
ጎል ። ወርእዮሙ ፡ አእመሩ ፡ ከመ ፡ በእንተ ፡
ውእቱ ፡ ሕፃን ፡ ዘነገርዎሙ ። ወአንከሩ ፡
ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ሰምዑ ፡ ዘነገርዎሙ ፡ ኖሎት ።

፱፤ ወኖሎት ፡ ሰገዱ ፡ ለሕፃን ፡ ወተመይጡ ፡ እንዘ ፡
ይሴብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡ መካኖሙ ።

፲፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለዘሐወጸነ ፡ ወተ
ሣሃለነ ፡ በተሠግዎቱ ፡ እምዘመድነ ፡ ለዓለመ ፡
ዓለም ፡ አሜን ።

ብርሃን ፡ በላያቸው ፡ በራ ፡ ታላቅ ፡ ፍርሀትንም ፡
ፈሩ ፡ መልአኩም ፡ ለእናንተና ፡ ለመላው ፡
ዓለም ፡ ደስታ ፡ የሚሆን ፡ ታላቅ ፡ የምሥራች ፡
እነግራችኋለሁና ፡ አትፍሩ ፡ አላቸው ።

፭፤ እነሆ ፡ ዛሬ ፡ በዳዊት ፡ አገር ፡ መድኀን ፡ የሆነ ፡
ጌታ ፡ ክርስቶስ ፡ ተወልዶላችኋልና ። ለእና
ንተም ፡ ምልክቱ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ሕፃኑ ፡
አውራ ፡ ጣቱን ፡ ታሥሮ ፡ በጨርቅ ፡ ተጠቅ
ልሎ ፡ በበረት ፡ ውስጥ ፡ ተኝቶ ፡ ታገኙታ
ላችሁ ፡ አላቸው ።

፮፤ ድንገትም ፡ ከዚያ ፡ መልአክ ፡ ጋር ፡ ብዙ ፡
የሰማይ ፡ ሠራዊት ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያመ
ሰገኑ ፡ በሰማይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡
ይሁን ፡ በምድርም ፡ ሰላም ፡ ለሰው ፡ በጎ ፡
ፈቃድ ፡ እያሉ ፡ መጡ ።

፯፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ መላእክት ፡ ከእነርሱ ፡ ዘንድ ፡
ባረጉ ፡ ጊዜ ፡ እነዚያ ፡ እረኞች ፡ ሰዎች ፡ እርስ
በርሳቸው ፡ ኑ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ ሔደን ፡
ይህን ፡ እግዚአብሔር ፡ የገለጠልንን ፡ ነገር ፡
እንወቅ ፡ አሉ ።

፰፤ ፈጥነውም ፡ ሔዱ ፡ ማርያምንና ፡ ዮሴፍን ፡
ሕፃኑንም ፡ በበረት ፡ ውስጥ ፡ ተኝቶ ፡ አገ
ኟቸው ። አይተውም ፡ የነገሩዋቸው ፡ ስለዚህ ፡
ሕፃን ፡ እንደሆነ ፡ አወቁ ፡ እረኞች ፡ የነገሩዋ
ቸውን ፡ የሰሙ ፡ ሁሉ ፡ አደነቁ ።

፱፤ እረኞችም ፡ ለሕፃኑ ፡ ሰግደው ፡ እግዚአብሔርን ፡
እያመሰገኑ ፡ ወደ ፡ ቦታቸው ፡ ተመለሱ ።

፲፤ ከወገናችን ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡ ለጐበኘንና ፡ ይቅር ፡
ላለን ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ ለዘ
ላለሙ ፡ አሜን ።

<u>አርኬ</u>

ሰላም ፡ ለበዓለ ፡ ጌና ፡ ዘኢኮነ ፡ ንትጋ ። እምልደተ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰዓተ ፡ ጸጋ ። እስመ ፡ አልጸቀት ፡ ወበጽሐት ፡ ከመ ፡ ትለዶ ፡ በሥጋ ። ዮም ፡ ለተጽሕፎ ፡ ምስለ ፡ ብዙኃን ፡ እንግልጋ ። ሀገረ ፡ ዳዊት ፡ ማርያም ፡ ዐሪጋ ።

፲፩፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ካዕበ ፡ ኮኑ ፡ ሰማዕተ ፡ ፪ወ፶
ዕደው ፡ ፸ወ፬ አንስት ፡ እምሰብአ ፡ ሀገረ ፡
እንጼናው ።

፲፪፤ ወእሉ ፡ ቀዳሚ ፡ ከሀድያን ፡ ወሶበ ፡ ኮነ ፡
መኰንነ ፡ እንጼናው ፡ ይኄንኖ ፡ ለቅዱስ ፡
ጳውሎስ ፡ ሶርያዊ ፡ ወሀለዉ ፡ እሙንቱ ፡
ሰብእ ፡ ወይሬእይዎ ፡ እንዘ ፡ ይኴንንዎ ፡

፲፩፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡ ደግሞ ፡ ከእንጼናው ፡ አገር ፡
ሰዎች ፡ መቶ ፡ ሃምሳ ፡ ወንዶች ፡ ሃያ ፡ አራት ፡
ሴቶች ፡ በሰማዕትነት ፡ ሞቱ ።

፲፪፤ እሊህም ፡ ቀድሞ ፡ ከሀድያን ፡ ነበሩ ፡ የእን
ጼናው ፡ መኰንን ፡ የከበረ ፡ ሶርያዊ ፡ ጳው
ሎስን ፡ በሚያሠቃየው ፡ ጊዜ ፡ ከዚያ ፡ ነበሩ ፡
ሲአሠቃየውም ፡ ይመለከቱ ፡ ነበር ፡ መኰ

www.ethiopianorthodox.org

ወአዘዘ ፡ መኰንን ፡ ከመ ፡ ያርስኑ ፡ ቅንዋተ፡ ኀፂን፡ውስተ፡እሳት፡ወቦቱ፡ይምልሑ፡አዕ ይንቲሁ፡ለቅዱስ፡ጳውሎስ። ወሶበ፡ገብሩ፡ ዘንተ ፡ ተመልሐ ፡ አዕይንቲሁ ፡ ወገደፍዎ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ። ወበሳኒታ ፡ በጽሑ ፡ እሉ ፡ ሰብእ ፡ ከመ ፡ ይርአይዎ ፡ ወረከብዎ ፡ ጥዑየ፡ ዘእንበለ ፡ ሙስና ፡ እስመ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ አሕ የዎ።

፲፫፤ ወርእዮሙ ፡ ዘንተ ፡ መንክረ ፡ አንከሩ ፡ ፈድ ፋደ፡ ወለበዉ ፡ ከመ ፡ ጣዖታቲሆሙ ፡ ኢይ ክሉ ፡ ምንተኒ ፡ ገቢረ ፡ ወአእመሩ ፡ ከመ ፡ አምላኮሙ፡ለክርስቲያን፡ውእቱ፡አምላክ፡ ዘበአማን ። ወእምዝ ፡ ሖሩ ፡ ኀበ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ፡ወሰገዱ፡ሎቱ፡ታሕተ፡እገሪሁ፡ ወሰአልዎ ፡ ከመ ፡ ይጸሊ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ውእ ቱኒ፡ባረኮሙ፡ወይቤሎሙ፡እግዚአብሔር፡ ይትወከፍ፡አሚኖተክሙ፡ወይጐልቌክሙ፡ ምስለ፡ሰማዕታት።

፲፬፤ ወእምዝ፡ቀርቡ፡ኀበ፡መኰንን፡ወተአመኑ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብ ሐት፡ወአዘዘ፡መኰንን፡ከመ፡ይምትሩ፡አር እስቲሆሙ ፡ በሰይፍ ፡ ወመተርዎሙ ፡ ወነ ሥኡ ፡ አክሊለ ፡ ስምዕ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት።

፲፭፤ ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ኪያነኒ፡ይምሐ ረነ፡በጸሎቶሙ፡ለሰማዕት፡ለዓለመ፡ዓለም፡ አሜን።

ንኑም ፡ ችንካሮችን ፡ በእሳት ፡ አግለው፡ ዐይኖቹን፡እንዲአወልቁ፡አዘዘ። ይህንንም፡ ባደረጉበት፡ጊዜ፡ዐይኖቹ፡ወለቁ፡ከወህኒ፡ ቤትም ፡ ጣሉት ። በማግሥቱም ፡ እሊህ ፡ ሰዎች፡ ሊያዩት፡በሔዱ፡ጊዜ፡ያለ፡ምንም፡ ጉዳት፡ድኖ፡ጤነኛ፡ሁኖ፡አገኙት፡የክብር፡ ባለቤት፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡አድኖ ታልና።

፲፫፤ ይህንንም፡ድንቅ፡ተአምር፡አይተው፡እጅግ፡ አደነቁ፡ጣዖቶቻቸውም፡ምንም፡መሥራት፡ እንደማይችሉ፡አስተዋሉ። የክርስቲያኖች፡ አምላክ፡እርሱ፡እውነተኛ፡አምላክ፡እንደ ሆነ፡አወቁ፡ወደከበረ፡ጳውሎስ፡ሒደው፡ ሰገዱለት፡እንዲጸልይላቸውም፡ለመኑት፡እር ሱም ፡ ባረካቸው ፡ እግዚአብሔር፡ እምነታ ችሁን፡ተቀብሎ፡ከሰማዕታት፡ጋር፡ይቍጠ ራችሁ፡አላቸው።

፲፬፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ መኰንኑ ፡ ቀርበው ፡ በክብር ፡ ባለቤት ፡ በጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ታመኑ፡መኰንኑም፡ራሶቻቸውን፡ ቍረጡ፡ብሎ፡አዘዘና፡ቈረጧቸው፡በመን ግሥተ፡ሰማያትም፡የሰማዕትነት፡አክሊልን፡ ተቀበሉ።

፲፭፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ ንም፡በሰማዕታት፡ጸሎት፡ይማረን፡ለዘላለሙ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለክሙ፡ማኅበራነ፡ዕደው፡ወአንስት። ዘኮንክሙ፡ስምዐ፡ዘበሃይማኖት። ነጺረክሙ፡ገሀደ፡ ግብረ፡ጳውሎስ፡ሰማዕት። እምድኅረ፡መልሕዎ፡ዐይኖ፡በዓውደ፡መኰንን፡መስሕት። ከመ፡ኀብረ፡ገጹ፡ ብሩህ፡ወዐይኑ፡ክሡት።

፲፮፤ ወበዛቲ፡ዕለት፡ተዝካረ፡አበዊነ፡አብርሃም፡ ይስሐቅ ፡ ወያዕቆብ ፡ ወስብሐት፡ ለእግዚአ ብሔር፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፲፮፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ የአባቶቻችን ፡ የአብርሃም ፡ የይስሐቅ፡የያዕቆብ፡መታሰቢያ፡ነው፡ለእግ ዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለክሙ፡ክቡራን፡ዕደው። እምዕጓለ፡እመሕያው። አብርሃም፡ይስሐቅ፡ወያዕቆብ፡ዘዝክርሙ፡ ፍትው። እምሥጋክሙ፡መዋቲ፡ከመ፡ሥጋ፡ኵሉ፡አበው። በሀገረ፡ዳዊት፡ዮም፡ተወልደ፡ሕያው።

www.ethiopianorthodox.org

ወውእቱ፡የሐውር፡በመዓልት፡ወይትኀባእ፡
በሌሊት። ወሶበ፡ይትራከቡ፡ምስለ፡ሰብእ፡
ይትኀባእ ፡ ወሶበ ፡ ይቀውሙ ፡ ይትከሠት ፡
ሎሙ፡በካልዕ፡ገጽ።

፯ ወውእቶሙ ፡ ሶበ ፡ በጽሑ ፡ ኢየሩሳሌም ፡
ተኀብአ፡እምኔሆሙ፡ውእቱ፡ኮከብ፡ወኀዘኑ፡
ፈድፋደ፡ወኢያእመሩ፡ዘይገብሩ። ወእምዝ፡
ቦኡ ፡ ውስተ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወተሰአሉ ፡
በእንተ፡ዘተወልደ፡ወኍልቆሙ፡ለእሙንቱ፡
ሰብእ፡ሠለስቱ፡እልፍ፡ወነገሥታቲሆሙ፡
ሠለስቱ፡ወለለአሐዱ፡ንጉሥ፡ቦ፡በበእልፍ፡
ሠራዊት።

፰ ወሰሚዖ ፡ ሄሮድስ ፡ ንጉሥ ፡ ደንገፀ ፡ ወተ
ሐውከ፡ወኵላ፡ኢየሩሳሌም፡ምስሌሁ።ወአስ
ተጋብአሙ፡ለኵሎሙ፡ሊቃነ፡ካህናት፡ወለጸ
ሐፍተ፡ሕዝብ፡ወተሰአሎሙ፡ወይቤሎሙ፡
በአይቴ፡ይትወለድ፡ ክርስቶስ።የይቤልዎ፡
በቤተ፡ ልሔም ፡ ዘይሁዳ ፡ እስመ ፡ ከማሁ ፡
ጽሑፍ፡በነቢይ።

፱ ወአንቲኒ፡ቤተ፡ልሔም፡ምድረ፡ኤፍራታ፡
ኢትቴሐቲ ፡ እምነገሥተ ፡ ይሁዳ ፡ እስመ ፡
እምኔኪ፡ይወጽእ፡ንጉሥ፡ዘይርዕዮሙ፡ለሕዝ
ብየ፡እስራኤል።

፲ ወእምዝ፡ጸውዖሙ፡ሄሮድስ፡ለሰብአ፡ሰገል
ጽሚተ፡ወተጠየቀ፡እምኔሆሙ፡መዋዕሊሁ፡
በዘአስተርአዮሙ፡ኮከብ።

፲፩ ወፈነዎሙ፡ኀበ፡ቤተ፡ልሔም፡ወይቤሎሙ፡
ሐዊረክሙ ፡ ተሰአሉ ፡ ጥዩቀ ፡ በእንተ ፡
ውእቱ ፡ ሕፃን ፡ ወእምከመ ፡ ረከብክምዎ ፡
ግብኡ ፡ ኀቤየ ፡ ወዜንዉኒ ፡ ከመ ፡ እምጻእ ፡
አነሂ ፡ ወእስግድ ፡ ሎቱ ። ወሰሚዖሙ፡ እም
ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ሖሩ ፡ ወናሁ ፡ ኮከብ ፡ ዘርእዩ፡
እምሥራቅ፡ይመርሖሙ፡እስከ፡ሶበ፡አብጽ
ሖሙ፡ቤተ፡ልሔም፡ወቆመ፡መልዕልተ፡
በዓት፡ኀበ፡ሀሎ፡ሕፃን።

፲፪ ወርእዮሙ፡ኮከበ፡ተፈሥሑ፡ዐቢየ፡ፍሥሓ፡
ወበዊኦሙ፡ውስተ፡ቤት፡ረከብዎ፡ ለሕፃን፡
ምስለ፡ ድንግል፡ማርያም እሙ፡ወወድቁ፡
ወሰገዱ፡ሎቱ፡ወአርኀዉ፡መዛግብቲሆሙ፡
ወአብኡ ፡ ሎቱ ፡ አምኃ ፡ ወርቀ ፡ ከርቤ ፡
ወስሂነ።

፲፫ ወበፈቃደ፡ እግዚአብሔር ፡መጽኡ፡ዮሴፍ፡
ወእግዝእትነ፡ ቅድስት፡ድንግል፡ማርያም፡

ይመስላል ፡ እርሱም ፡ በቀን ፡ ይጓዛል ፡
በሌሊትም፡ይሠወራል፡ከሰውም፡ሲገናኙ፡
ይሠወርና፡ሲቆሙ፡በሌላ፡አንጻር፡ይገለጥላ
ቸዋል።

፯ እነርሱም፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡ሲደርሱ፡ያ፡
ኮከብ፡ተሠወራቸው፡እጅግ፡አዘኑ፡የሚያድ
ረጉትንም፡አላወቁም፡ከዚህም፡በኋላ፡ወደ፡
ኢየሩሳሌም ፡ ከተማ ፡ ገብተው ፡ ስለተወ
ለደው፡ ንጉሥ ፡ ጠየቁ ። የእሊህም ፡ ሰዎች ፡
ቍጥራቸው፡ሠላሳ፡ሽህ፡ነው፡ነገሥታቱ፡
ሦስት ፡ ናቸው ፡ ለየእያንዳንዱ ፡ ንጉሥ ፡
ዐሥር፡አሥር፡ሽህ፡ሠራዊት፡አለው።

፰ ንጉሡ፡ሄሮድስም፡በሰማ፡ጊዜ፡ደነገጠ፡ኢየ
ሩሳሌምም ፡ በመላዋ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ደነገ
ጠች። የካህናት ፡ አለቆችና ፡ የሕዝቡን ፡ ጸሐ
ፊዎች፡ሁሉ፡ሰብስቦ፡ ክርስቶስ፡በየት፡ይወለ
ዳል፡ብሎ፡ጠየቃቸው።በይሁዳ፡ዕፃ፡በቤተ፡
ልሔም፡ነው፡አሉት፡በነቢይ፡እንዲህ፡ተብሎ፡
ተጽፏልና።

፱ የኤፍራታ ፡ ዕፃ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ አንቺም ፡
ከይሁዳ፡ነገሥታት፡አታንሺም፡ወገኖቼ፡እስ
ራኤልን፡የሚጠብቅ፡ንጉሥ፡ካንቺ፡ይወዳ
ልና።

፲ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሄሮድስ ፡ ሰብአ ፡ ሰገልን ፡
በጭልታ፡ጠርቶ፡ኮከቡ፡የታየበትን፡ዘመን፡
ከነሱ፡ተረዳ።

፲፩ ሒዳችሁ፡የዚያን፡ሕፃን፡ነገር፡እርግጡን፡
መርምሩ፡ያገኛችሁትም፡እንደሆነ፡እኔም፡
መጥቼ ፡ እሰግደለት ፡ ዘንድ ፡ በኔ ፡ በኩል ፡
ተመልሳችሁ ፡ ንገሩኝ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡
ልሔም ፡ ሰደዳቸው ። የነገራቸውንም ፡ ሰም
ተው ፡ ከንጉሡ ፡ ሔዱ ፡ እነሆ ፡ በምሥራቅ፡
ያዩት፡ኮከብ፡ወደ፡ቤተ፡ልሔም፡እስኪያደ
ርሳቸው ፡ ይመራቸው ፡ ነበር ፡ ሕፃኑ ፡
ካለበትም፡ዋሻ፡ላይ፡ደርሶ፡ቆመ።

፲፪ ኮከቡንም፡ባዩ፡ጊዜ፡እጅግ፡ደስ፡አላቸው፡
ወደ፡ቤትም፡በገቡ፡ጊዜ፡ ሕፃኑን ከእናቱ፡
ከድንግል ፡ ማርያም ፡ ጋር ፡ አገኙት ፡
ወድቀውም ፡ ሰገዱለት ፡ ሣጥናቸውንም ፡
ከፍተው፡ወርቅ፡ከርቤ፡ዕጣን፡እጅ፡መንሻ፡
አቀረቡለት።

፲፫ በእግዚአብሔርም ፡ፈቃድ ፡ ዮሴፍ ፡ እመቤ
ታችን፡ ቅድስት፡ድንግል፡ማርያም፡ሕፃኑ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወሕፃንኒ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡በይእቲ፡ዕለት፡በእንተዝ፡ረከብዎሙ፡ሰብአ፡ሰገል፡እስመ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት፡ኢተሐፅነ፡ዘእንበለ፡በናዝሬት፡ወኮነ፡ሎቱ፡መዋዕሊሁ፡እምዘተወልደ፡ክልኤቱ፡ዓመት።

፲፬፡ወርቀ፡አብኡ፡በእንተ፡መንግሥቱ፡ወዕጣነ፡አብኡ፡ሎቱ፡እስመ፡አምላክ፡ውእቱ፡ወሎቱ፡ክህነትኒ፡ወከርቤ፡አብኡ፡ትእምርተ፡ሞቱ፡ማሕየዊ።

፲፭፡ወነገሮሙ፡በሕልም፡ከመ፡ኢይግብኡ፡ኀበ፡ኄሮድስ፡ወእንተ፡ካልዕ፡ፍኖት፡ገብኡ፡ወአተዉ፡ብሔሮሙ።ወኮኑ፡ሰባክያነ፡ወዓዋድያነ፡በእንተ፡አስተርእዮቱ፡ለአምላክ፡በሥጋ።

፲፮፡ ወዛቲ፡ዕለት፡ዘበእንቲአሃ፡ተነበየ፡ኢሳይያስ፡ነቢይ፡እንዘ፡ይብል፡ናሁ፡ድንግል፡ትፀንስ፡ወትወልድ፡ወልደ፡ወትሰምዮ፡ዐማኑኤል፡ዘበትርጓሜሁ፡እግዚአብሔር፡ምስሌነ።

፲፯፡ወበእንተ፡ዛቲ፡ቅድስት፡ድንግል፡ተነበየ፡ሕዝቅኤል፡ነቢይ፡እንዘ፡ይብል፡ወይቤለኒ፡እግዚአብሔር፡ዛቲ፡አንቀጽ፡ዕፁታ፡ትነብር፡ወኢትትረኃው፡ወአልቦ፡ዘይበውእ፡እንተ፡ህየ፡እስመ፡እግዚአብሔር፡አምላከ፡እስራኤል፡ይበውእ፡ውስቴታ፡ትነብር፡ዕፁታ።

፲፰፡ወዳንኤልኒ፡ነቢይ፡ይቤ፡ወርኢኩ፡በራእየ፡ሌሊት፡ወናሁ፡መጽአ፡ዐቢይ፡በደመና፡ሰማይ፡ከመ፡ወልደ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡ወበጽሐ፡ኀበ፡ብሉየ፡መዋዕል፡ወአቅረብዎ፡ቅድሜሁ።ወተውህበ፡ሎቱ፡ምኵናን፡ዘለዓለም፡ወክብር፡ወመንግሥት፡ወሥልጣን፡ወኵሎሙ፡አሕዛብ፡ወሕዝብ፡ወበሐውርት፡ወነገድ፡ወነገሥት፡ይትቀነዩ፡ሎቱ፡ወምኵናኑኒ፡ምኵናን፡ዘለዓለም፡ወመንግሥቱ፡ዘኢየኀልቅ፡ወኢይማስን።

፲፱፡ ወካዕበ፡ይቤ፡ኢሳይያስ፡እስመ፡እግዚአብሔር፡አስተርአየ፡ሊተ፡ወአንጦልዐ፡መንጦላዕተ፡ሥጋ፡ዘከማየ።ወካዕበ፡ይቤ፡ሀለወኒ፡እግበር፡ሰማየ፡ሐዲሰ፡ወምድረ፡ሐዳሰ።ወይቤ፡ካዕበ፡ትወጽእ፡በትር፡

ጌታ፡ኢየሱስም፡በዚያች፡ዕለት፡ወደ፡ቤተ፡ልሔም፡መጡ፡ስለዚህም፡ሰብአ፡ሰገል፡አገኙአቸው፡የክብር፡ባለቤት፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ያለ፡ናዝሬት፡በሌላ፡ቦታ፡አላደገምና፡ከተወለደም፡ዕድሜው፡ሁለት፡ዓመት፡ሁኖት፡ነበር።

፲፬፡አምላክ፡ነውና፡ስለ፡መንግሥቱ፡ወርቅን፡ገበሩለት፡ክህነትም፡ገንዘቡ፡ነውና፡ዕጣንን፡ገበሩለት፡ማሕየዊ፡ለሆነ፡ሞቱ፡ምልክትም፡ከርቤን፡ገበሩለት።

፲፭፡ወደ፡ኄሮድስም፡እንዳይመለሱ፡በሕልም፡ነገራቸው፡በሌላ፡መንገድም፡ወደ፡አገራቸው፡ተመልሰው፡ገቡ።አምላክ፡በሥጋ፡ስለመገለጡ፡ዓዋጅ፡ነጋሪዎችና፡ሰባኪዎች፡ሆኑ።

፲፮፡ይችም፡ዕለት፡ነቢዩ፡ኢሳይያስ፡ትንቢት፡ስለርሷ፡የተናገረላት፡ናት፡እንዲህ፡ብሎ፡እነሆ፡ድንግል፡ፀንሳ፡ወንድ፡ልጅን፡ትወልዳለች፡ስሙንም፡ዐማኑኤል፡ትለዋለች፡ትርጓሜውም፡እግዚአብሔር፡ከእኛ፡ጋር፡ማለት፡ነው።

፲፯፡ ስለዚችም፡የከበረች፡ድንግል፡ነቢይ፡ሕዝቅኤል፡እንዲህ፡ብሎ፡ትንቢት፡ተናገረ፡እግዚአብሔርም፡አለኝ፡ይህች፡በር፡ተዘግታ፡ትኖራለች፡አትከፈትም፡የሚገባበትም፡የለም፡የእስራኤል፡ፈጣሪ፡እግዚአብሔር፡እንደተዘጋች፡ይገባባታልና፡ተዘግታ፡ትኑር፡አለ።

፲፰፡ ነቢዩ፡ዳንኤልም፡አለ፡ሌሊት፡በራእይ፡አየሁ፡እነሆ፡ታላቁ፡እንደ፡ሰው፡ልጅ፡በሰማይ፡ደመና፡መጣ፡ዘመኑን፡ወደ፡ሚያስረጅ፡ደረሰ፡ከፊቱም፡አቀረቡት፡የዘላለም፡አገዛዝ፡ጌትነት፡መንግሥት፡ተሰጠው፡ሕዝቡና፡አሕዛቡ፡ሁሉ፡መንደር፡መንድረው፡የሚኖሩትና፡ነገዱም፡ነገሥታቱም፡ሁሉ፡ይገዙለታል፡አገዛዙም፡የዘላለም፡አገዛዝ፡ነው፡መንግሥቱም፡የማያልፍ፡የማይጠፋ፡ነው።

፲፱፡ዳግመኛም፡ኢሳይያስ፡እግዚአብሔር፡እንደ፡እኔ፡የሥጋ፡መጋረጃ፡በመጋረድ፡ተገለጸልኝ፡አለ።አሁኑም፡ደግሞ፡አዲስ፡ሰማይ፡አዲስ፡ምድር፡እሠራ፡ዘንድ፡አለኝ፡አለ፡ሁለተኛም፡ከዕሴይ፡ሥር፡በትር፡ትወጣ

www.ethiopianorthodox.org

ገዳም ፡ ለእስራኤል ፡ ወበከመ ፡ ሠረፀት ፡ በትረ፡አሮን፡ይብስት፡ወፈረየት፡፡ወበከመ፡ ውኅዘ ፡ ማይ ፡ እመንሰከ ፡ አድግ ፡ ኅቱም ፡ ውስተ፡እደ፡ሶምሶን፡፡

፳፪፡ ከማሁ ፡ ልደቱ ፡ ለእግዚእነ ፡ በኅቱም ፡ ድንግልና፡፡

፳፫፡ ወበከመ፡ነደት፡እሳት፡ውስተ፡ዕፀ፡ጳጦስ፡ ወኢውዕየት ፡ ከማሁ ፡ ኢያውዓያ ፡ እሳተ ፡ መለኮት፡ለድንግል፡፡

፳፬፡ ወሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወሰጊድ ፡ ወክብር ፡ ወአኰቴት፡ምስለ፡አቡሁ፡ኄር፡ወመንፈስ ቅዱስ፡ ማሕየዊ፡ዘዕሩይ፡ምስሌሁ፡ለዓለም፡ ዓለም፡አሜን፡፡

የደረቀች ፡ የአሮን ፡ በትርም ፡ እንደለመለ መችና፡እንደ፡አፈራች፡፡በሶምሶንም፡እጅ፡ ውስጥ ፡ ከአህያ ፡ መንጋጋ ፡ ዐጥንት ፡ ውኃ፡ እንደ፡ፈሰሰ፡፡

፳፪፡ እንዲሁ ፡ የጌታችን ፡ ልደት ፡ በኅቱም ፡ ድንግልና፡ሆነ፡፡

፳፫፡ በዕፀ ፡ ጳጦስ ፡ ውስጥ ፡ እሳት ፡ እንደ ፡ ነደ ደች፡ዕፂቱም፡እንዳልተቃጠለች፡እንዲሁ፡ የመለኮቱ ፡ እሳት ፡ ድንግልን ፡ አላቃጠ ላትም፡፡

፳፬፡ ለርሱም፡ከቸር፡አባቱ፡ከማሕየዊ፡መንፈስ ቅዱስ ፡ ጋር ፡ ጌትነት ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ሰጊድ፡ከርሱ፡ጋር፡በትክክልነት፡ይገባል፡ ለዘላለሙ፡አሜን፡፡

## አርኬ

ሰላም ፡ ለልድትከ ፡ እግዚአ ፡ ምሕረት ፡ ወሣህል ፡፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረት ፡ ወላዕለ ፡ እስራኤል፡፡ እንዘ ፡ ይትፌሣሕ ፡ አፉየ ፡ በጽድቀ ፡ ዝንቱ ፡ በዓል፡፡ ለኂሩትከ ፡ አኰቴት ፡ ያወሥእ ፡ በቃል፡፡ ወለመንግሥትከ ፡ ስብሐት፡ይብል፡፡

ሰላም፡ለልደትከ፡ጥንተ፡ኖኅያት፡አልፋ፡፡በከርሠ፡ማርያም፡ድንግል፡ርስሐተ፡ዓለም፡ዘኢለከፋ፡፡ እምኂሩትከ፡መዋዒት፡ዘኢይትረከብ፡ሱታፋ፡፡በገዳመ፡ልብ፡ዘምእምናን፡እምጽንፋ፡እስከ፡ጽንፋ፡፡ምሉዐ ትፍሥሕት፡አኅደርከ፡በተስፋ፡፡

ሰላም፡ለልደትከ፡እሳተ፡መለኮት፡በላዒ፡፡እምልምልምት፡ዕፅ፡እንተ፡ኢትውዒ፡፡ስብሐተ፡ልደትከ፡ ዝንቱ፡ኀበ፡ያስተርኢ፡፡በወይነ፡ማኅሌት፡እንተ፡ይቀድሖ፡ገዛዒ፡፡ትኩዝ፡ይትፌሣሕ፡ ወሕሙም፡ይጥዒ፡፡

ነገሥተ፡ሳባ፡ወዓረብ፡ጋዳ፡ያመጽኡ፡በኃሢሥ፡፡ ወያበውኡ፡አምኃ፡ነገሥተ፡ደስያት፡ወተርሴስ፡፡ ዘትቤ፡ትካት፡በእንተ፡ክርስቶስ፡፡ኀበ፡ወለደት፡ድንግል፡ነአስ፡፡ነዓ፡ነዓ፡ዳዊት፡ንጉሥ፡፡

፴፡ ወበዛቲ ፡ ዕለተ ፡ ተወልደ ፡ ኢያሱ ፡ መስፍን ፡ ዘእምቤተ ፡ ኤፍሬም ፡ ወውእቱ ፡ ዘኮነ ፡ መድ ኃኒቶሙ፡ለደቂቀ፡እስራኤል፡እምጻባዒተ፡ አዕራር፡፡

፴፩፡ ወልደተ ፡ እግዚእነሂ ፡ ኮነ ፡ መድኃኒቶሙ ፡ ለአዳም፡ወለደቂቁ፡፡ወለውእቱ፡ኮነ፡ስሙ፡ ቀዳሚ ፡ ሆሴዕ ፡ ወሶበ ፡ አድኃኖሙ ፡ እምጸ ባዒተ ፡ አማሌቅ ፡ ለእስራኤል ፡ በራፌድ ፡ ተሰምየ፡ኢያሱሃ፡ዘውእቱ፡መድኅን ፡፡

፴፪፡ ወእምድኅረ ፡ ሞቱሂ ፡ ለሙሴ ፡ ኅረዮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወሤሞ ፡ መስፍነ ፡ ለእስ ራኤል ፡ ወአድኃኖሙ ፡ እምቀትለ ፡ አሕዛብ ፡ ነኪራን ፡ ወአስተዋረሶሙ ፡ ርስቶሙ ፡፡ ወእምዝ ፡ አዕረፈ ፡ በሰላም ፡፡

፴፡ በዚችም፡ዕለት፡ከኤፍሬም፡ወገን፡መስፍኑ፡ ኢያሱ ፡ ተወለደ ፡ እርሱም ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች፡ከጠላት፡ሰልፍ፡መድኃኒት፡ሁኖ፡ ያዳናቸው፡ነው፡፡

፴፩፡ የጌታችንም፡መወለድ፡ለአዳምና፡ለልጆቹ፡ መድኃኒት ፡ ሆናቸው ፡፡ የርሱም ፡ የቀድሞ ፡ ስሙ ፡ ሆሴዕ ፡ ነበረ ፡ እስራኤልን ፡ ከአማ ሌቅ፡ጦርነት፡በራፌድ፡በአደናቸው፡ጊዜ፡ ኢያሱ ፡ ተብሎ ፡ ተጠራ ፡ ይህም ፡ አዳኝ ፡ ማለት፡ነው ፡፡

፴፪፡ ሙሴም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ መረጠውና ፡ ለእስራኤል ፡ መስፍን ፡ አድ ርጎ ፡ ሾመው ፡ ልዩ ፡ ከሆኑ ፡ አሕዛብም፡ ጦርነት ፡ አዳናቸው ፡ ርስታቸውንም ፡ አወረሳቸው ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በሰላም ፡ አረፈ ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

፴፫፤ ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ለዓለመ፡ዓለም፡ አሜን።

፴፬፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ያዕቆብ ፡ ወፊሊስ ፡ ወቴዎድሮስ ፡ ሰማዕት ፡ ካልዕ ፡ በረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓ ለመ፡ዓለም፡አሜን።

፴፭፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አቃርዮስ ፡ ንጉሠ ፡ ሮሀ ፡ ወለዝንቱ ፡ ኮነት ፡ መንግሥቱ ፡ በብ ሔረ፡ ሶርያ ፡ ዘትሰመይ ፡ ሰርሜን ፡ እንተ ፡ ይእቲ፡ሀገረ፡ሮሀ።

፴፮፤ ወኮነ ፡ ዘያመልክ ፡ ጣዖተ ፡ ወውእቱ ፡ መፃ ጉዕ፡ ወወሀበ ፡ ንዋዮ ፡ ለዐቀብተ ፡ ሥራይ፡ ወኢክህሉ ፡ ፈውስቶ ፡ ወሰሚዖ ፡ ምግባሮ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ዘይገብር ፡ ተአምራተ ፡ ወመን ክራተ፡ በፈውሶ ፡ ዱያን ፡ ወአውጽኦ ፡ አጋ ንንት ፡ ወከሢተ ፡ አዕይንተ ፡ ዕውራን ፡ ወአ ንሥኦ ፡ ሙታን ፡ ለአከ ፡ ኀቤሁ ፡ እንዘ ፡ ይብል።

፴፯፤ ሰላም፡ለከ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡ዘአስተር አይከ ፡ በሥጋ ፡ ሰብእ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ወሰ ላም ፡ ለአቡከ ፡ ኄር ፡ ዘፈነወከ ፡ ታሕተ ፡ እንዘ፡ ኢትትፈለጥ ፡ እምኔሁ ፡ ወሰላም ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘአልኖሰሰ ፡ ውስተ ፡ ሕሊናየ ፡ ከመ ፡ አንተ ፡ መሲሕ ፡ ወመዓርዩ ፡ ወሰላም፡ ለእምከ ፡ዘወለደተከ፡በድንግልና፡ ዘእንበለ፡ዘርአ፡ብእሲ፡ወሰላም፡ለኵሎሙ፡ እለ፡የአምኑ፡ብከ።

፴፰፤ ወአንሰ፡አመንኩ፡ብከ፡ወተመየጥኩ፡እም አምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ከንቱ ፡ ኀበ ፡ አምልኮ ፡ ዚአከ ፡ ነዓ ፡ ኀቤየ ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ ንጉሠ ፡ ላዕሌየ ፡ ወትባርክ ፡ ሀገርየ ፡ ወትፈውሰኒ ፡ እምደዌየ ፡ ወታንጽሐኒ ፡ እምርስሐትየ ፡ አ፡ እግዚእየ ፡ ለምንት ፡ ለከ ፡ ነቢር ፡ ውስተ ፡ ኢየ ሩሳሌም ፡ እንዘ ፡ ሕዝበ ፡ አይሁድ ፡ ይጸልኡ ፡ ስመከ ፡ ቅዱሰ ፡ ወትፃሙ ፡ በከ ፡ እስመ ፡ ሕዝብ ፡ ህጉላነ ፡ ምክር ፡ እሙንቱ ፡ ቀዳሚኒ ፡ ዘኢአምኑ ፡ ብከ ፡ አመ ፡ አውጻእኮሙ ፡ እም ብሔረ ፡ ግብጽ ፡ በገቢረ ፡ ተአምራት ፡ ወመ ንክራት ፡ ወሴሰይኮሙ ፡ በገዳም ፡ መና ፡ ፵ ፡ ዓመተ ፡ ሚ ፡ መጠን ፡ ዘአንጐርጐሩ ፡ ላዕሌከ ፡ እስከ ፡ ረሰይኮሙ ፡ ለተሀጕሎ ፡ እፎኬ ፡ ሶበ ፡

፴፫፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ ለዘላለሙ፡አሜን።

፴፬፤ በዚችም፡ዕለት፡የከበሩ፡የያዕቆብ፡የፊሊስ፡ የሌላው ፡ ሰማዕት ፡ የቴዎድሮስ ፡ መታሰቢ ያቸው ፡ ነው ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

፴፭፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡ የሮሀ ፡ ንጉሥ ፡ አቃርዮስ ፡ አረፈ ፡ የርሱም ፡ ግዛቱ ፡ በሶርያ ፡ አገር ፡ ሰርሜን፡በምትባል፡ክፍል፡ነው፡እርሷም፡ ሮሀ፡ናት።

፴፮፤ ጣዖትን ፡ የሚያመልክ ፡ ሆኖ ፡ ኖረ ፡ መፃጉዕም፡ ነበረ ፡ ለባለ ፡ መድኃኒቶችም ፡ ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ ሰጥቶ ፡ ሊአድኑት ፡ አል ቻሉም ። የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ ኢየ ሱስ፡ክርስቶስ፡በሽተኞችን፡በማዳን፡አጋን ንትን፡በማስወጣት፡የዕውሮችን፡ዐይኖች፡ በመግለጥ ፡ ሙታንን ፡ በማስነሣት፡ የሚሠ ራውን፡ድንቅ፡ተአምራቱን፡በሰማ፡ጊዜ፡ እንዲህ፡ሲል፡ወደርሱ፡ላከ።

፴፯፤ የሰውን፡ሥጋ፡ለብሰህ፡በኢየሩሳሌም፡የተገ ለጥክ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ምስጋና ፡ ይድረስህ ፡ ከእርሱ ፡ ሳትለይ ፡ ወደታች ፡ ለላከህ ፡ ለቸር ፡ አባትህም ፡ ምስጋና ፡ ይድረሰው ፡ አንተ ፡ የምትስተካከለው ፡ ክር ስቶስ ፡ እንደሆንክ ፡ በሕሊናየ ፡ ለገለጠልኝ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ። ያለወንድ፡ዘር፡በድንግልና፡ለወለደችህም፡ እናትህ ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ ለሚያምኑብህ ፡ ሁሉ፡ሰላምታ፡ይድረሳቸው።

፴፰፤ እኔም ፡ በአንተ ፡ አምኜ ፡ ከንቱ ፡ ጣዖትን ፡ ከማምለክ ፡ አንተን ፡ ወደ ፡ ማምለክ ፡ ተመለስኩ ፡ በኔ ፡ ላይም ፡ ንጉሥ ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ሀገሬንም ፡ ትባርክ ፡ ዘንድ ፡ ከበሽ ታዬም ፡ ታድነኝ ፡ ዘንድ ፡ ከኃጢአቴም ፡ ታነጻኝ ፡ ዘንድ ፡ ወደኔ ፡ ና ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ የከበረ፡ስምህን፡አይሁድ፡ሲጠሉ፡ለአንተ፡ በኢየሩሳሌም፡መኖር፡ምን፡ያደርግልሃል። በከንቱ፡ለምን፡ትደክማለህ፡መካር፡ያጡ፡ ወገኖች ፡ ናቸውና ፡ በቀድሞ ፡ ዘመንም ፡ ድንቆች ፡ ተአምራቶችን ፡ በማድረግ ፡ ከግ ብጽ ፡ አገር ፡ በአወጣኻቸው ፡ ጊዜ ፡ አላመኑ ብህም ፡ በበረሀም፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ መናውን ፡ በመገብካቸው ፡ ጊዜ ፡ ተቆጥተህ ፡ ለጥፋት ፡

www.ethiopianorthodox.org

ይኔጽሩከ ፡ በለቢሰ ፡ ሥጋ ፡ ምድራዊ ፡ ዘይ
ርኅብ፡ወይጸምዕ፡ይመስለከኑ፡ሕሊናሆሙ፡
ዘይትበዓድ፡እምዝንቱ፡እስመ፡አንተ፡ማእ
ምረ ፡ ኅቡአት ፡ እምትካት ፡ ወዘንተ ፡ ወዘይ
መስሎ፡ፈነወ፡ኀቤሁ፡ክታበ።

፴፱፡ ወሶበ ፡ በጽሑ ፡ ላእካኒሁ ፡ ለንጉሥ ፡ ኀበ ፡
እግዚእነ፡አእመረ፡ዘአምጽኡ፡ሎቱ፡መል
እክተ ፡ እምቅድመ ፡ ይንግርዎ ፡ ወነሥአ፡
ልብሰ፡ፀዓዳ፡ወመዝመዘ፡ቦቱ፡ገጾ፡ወገብአ፡
መልክዑ፡ውስተ፡ልብስ። ወፈነወ፡ሎቱ፡
ምስለ ፡ ታዴዎስ ፡ ረድኡ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡
ንሣእ፡ዘንተ፡ሥዕለ፡መልክዕየ፡ወውእቱ፡
ይፌጽም ፡ ለከ ፡ ኵሎ ፡ መፍቅደከ ፡ ወይፌ
ውሰከ ፡ እምደዌከ ፡ ወይባርክ ፡ ሀገረከ ፡
ወያረትዕ ፡ መንግሥተከ ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡
ሥዕል ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ ፍትኖ ፡ በእሳት ፡
ወማይ፡ለእመ፡ይትዌለጥ።

፵፡ ወበጺሐሙ፡ለእካን፡ኀበ፡አቃርዮስ፡ንጉሥ፡
መጠውዎ፡ውእተ፡ሥዕለ፡ውእቱኒ፡ፈተኖ፡
በእሳት፡ወማይ፡ወኢበጽሖ፡ምንትኒ፡እሙ
ስና ፡ ወአምኑ ፡ ሰብአ ፡ ሀገረ ፡ ሮሀ ፡ ምስለ ፡
ንጉሦሙ፡በሥልጣነ፡መለኮቱ፡ለእግዚእነ።
ወገብረ፡ተአምረ፡ወመንክረ፡ብዙኀ፡ዘአልቦ፡
ኍልቍ ፡ ወለንጉሥኒ ፡ ፈወሶ ፡ እምደዌሁ ፡
ውእቱ ፡ ሥዕል ፡ ወእምዝ ፡ መዋዕሊሁ ፡
ፈጺሞ፡አዕረፈ፡ንጉሥ፡በዛቲ፡ዕለት።

፵፩፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለዓለመ ፡
ዓለም፡አሜን።

እስከ ፡ አደረስካቸው ፡ በአንተ ፡ ላይ ፡ ምን ፡
ያህል ፡ አጕረመረሙብህ ፡ በሚራብና ፡
በሚጠማ ፡ ምድራዊ ፡ ሥጋማ ፡ ሲያዩህ ፡
እንዴት ፡ ነዋ ፡ ኀሳባቸው ፡ ከዚህ ፡ የተለየ ፡
ይመስልሃልን፡አንተ፡ከጥንት፡ጀምሮ፡የተ
ሠወረውን፡ታውቃለህና።ይኸንንና፡ይህን፡
የመሰለውን፡ጽፎ፡ደብዳቤ፡ወደርሱ፡ላከ።

፴፱፡ የንጉሥ ፡ መልክተኞችም ፡ ወደ ፡ ጌታችን ፡
በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ሳይነግሩት ፡ ያመጡለትን ፡
መልእክት ፡ አውቆ ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ አነሥቶ ፡
ፊቱን ፡ አሸበት ፡ የፊቱም ፡ መልክ ፡ ወደ ፡
ልብሱ ፡ ገባ ፡ ከደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ከታዴ
ዎስ፡ጋር፡እንዲህ፡ብሎ፡ላከለት፡ይህን፡የኔ፡
መልክ ፡ የሆነውን ፡ ሥዕል ፡ ተቀበል ፡ እር
ሱም ፡ የምትሻውን ፡ ሁሉ ፡ ይፈጽምልሃል ፡
ከበሽታህም፡ይፈውስሃል፡ሀገርህንም፡ይባ
ርካል ፡ መንግሥትህንም ፡ ያጸናል ፡ ይህ ፡
ሥዕል ፡ እኔን ፡ ነውና ፡ ይለወጥ ፡ እንደሆነ ፡
በውኃ፡በእሳት፡ፈትነው።

፵፡ መልክተኞችም ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ አቃርዮስ ፡
በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ያንን ፡ ሥዕል ፡ ሰጡት ፡ በእ
ሳትና ፡ በውኃም ፡ ፈተነውና ፡ ምንም ፡ ምን ፡
ጥፋት ፡ አልደረሰበትም ፡ የሮሀ ፡ አገር ፡
ሰዎችም ፡ ከንጉሣቸው ፡ ጋር ፡ በጌታችን ፡
የመለኮት ፡ ሥልጣን ፡ አመኑ ፡ ይህ ፡ ሥዕል ፡
ቍጥር፡የሌለው፡ብዙ፡ድንቅ፡ተአምራትን፡
አደረገ ፡ ንጉሡንም ፡ ከበሽታው ፡ ፈውሰው ፡
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ዕድሜውን ፡ ሲፈጽም ፡
በዚች፡ዕለት፡አረፈ።

፵፩፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ ለዘ
ላለሙ፡አሜን።

<u>አርኬ</u>

ሰላም፡ለአቃርዮስ፡እንተ፡ደለዎ፡...እይ።እንበለ፡ቀለም፡በልብስ፡ሥዕለ፡አዶናይ።ውእቱ፡ሥዕል፡
ገባሬ፡ዕበይ።ኢተደምሰሰ፡ወኢውዕየ፡በቅድመ፡ጉባኤ፡ሠናይ።ሶበ፡ፈተንዎ፡በእሳት፡ወማይ።

፵፪፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ ቅዱስ ፡ ቆሪል ፡
ገመላዊ፡እምሀገረ፡ሰምኑድ።

፵፫፡ ወውእቱ ፡ ጽሙድ ፡ በጾም ፡ ወበጸሎት ፡
ወወሀቦ፡እግዚአብሔር፡አእምሮ፡ምሥጢ
ራት፡ሥውራት፡ወቦቱ፡ሠለስቱ፡አግማል፡
ዘይትጌበር፡ቦሙ፡ወይጽዕን፡ቦሙ፡እምገ
ራህት፡ተለቤ።

፵፪፡ በዚችም፡ዕለት፡ሰምኑድ፡ከሚባል፡አገር፡
ገመላዊው ፡ ቅዱስ ፡ ቆሪል ፡ አረፈ።

፵፫፡ እርሱም፡በጾም፡በጸሎት፡ተወስኖ፡የሚኖር፡
ነው፡እግዚአብሔርም፡የተሰወሩ፡ምሥጢ
ራት፡ማወቅን፡ሰጠው፡የሚገለገልባቸው፡
ከማሳም ፡ ተልባ ፡ የሚጭንባቸው ፡ ሦስት ፡
ግመሎች፡አሉት።

www.ethiopianorthodox.org

፶፬፤ ወሀሎ ፡ ፩ ፡ ብእሲ ፡ እምሀገረ ፡ ፊራጉን ፡ ዘኮነ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ዘመርጡለ ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ወባቲ ፡ ብዙኀ ፡ ንዋይ ፡ ዘወሀብዋ ፡ በበ ጊዜሁ ፡ ነገሥት ፡ ወመኳንንት ፡ ወይነብር ፡ ውእቱ ፡ ንዋይ ፡ ውስተ ፡ መዝገብ ፡ ኀቡእ ፡ ኀበ ፡ ውእቱ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ወየአምር ፡ ኤጲስ ቆጶስ ፡ ኍልቈ ፡ ውእቱ ፡ ንዋይ ፡ ወውእቱ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ እምታሕቴሁ ፡ ለኤጲስቆጶስ ። ወእምዝ ፡ ሞተ ፡ ውእቱ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ በግ ብት ፡ ዘእንበለ ፡ ይንግር ፡ ለወልዱ ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፡ መዝገብ ፡ ዘንዋይ ።

፶፭፤ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሞቶ ፡ መጽአ ፡ ኀበ ፡ ይእቲ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወኃሠሠ ፡ ንዋያ ፡ ኀበ ፡ ወልዱ ፡ ወይቤሎ ፡ ውእቱ ፡ ወልድ ፡ ኢያእመርኩ ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፡ መዝገብ ፡ ወኢነገረኒ ፡ አቡየ ፡ እስመ ፡ ነሥአ ፡ እደ ፡ ሞት ፡ ግብተ ፡ ወሰሚዖ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ተምዐ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወፈቀደ ፡ ይሣቅዮ ፡ ውእቱኒ ፡ ወልድ ፡ ሰአሎ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ወይቤሎ ፡ ጽንሐኒ ፡ እስከ ፡ አኃሥሥ ፡ ማኅደረ ፡ መዝገብ ፡ ወሶበ ፡ ኢረከብኩ ፡ ትሬስየኒ ፡ ዘፈቀድከ ፡ ውእቱኒ ፡ ወሀቦ ፡ ዕድሜ ።

፶፮፤ ወበዊአ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ ነገራ ፡ ለብእሲቱ ፡ ኵሎ ፡ ትካዞ ፡ ወትቤሎ ፡ ይእቲ ፡ ተአመን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ወሑር ፡ ኀበ ፡ አበው ፡ መነ ኮሳት ፡ ዘደብረ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ ወኅሥሥ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወእምአግዋሪሆሙ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ይነግሩከ ። ወበጺሖ ፡ ህየ ፡ ሰአሎሙ ፡ ለመነኮሳት ፡ ከመ ፡ ይሥልጡ ፡ ትካዞ ፡ ወነጥአ ፡ ዘይነግሮ ፡ ወቀብጸ ፡ ተስፋ ፡ ወቀጸቦ ፡ አሐዱ ፡ ባሕታዊ ፡ ወይቤሎ ፡ ሑር ፡ ኀበ ፡ መካን ፡ ዘይብልዎ ፡ ሰምኑድ ፡ ወተሰአል ፡ በእንተ ፡ ቁሪል ፡ ገመላዊ ፡ ወኅድር ፡ ኀቤሁ ፡ ወውእቱ ፡ ይዜንወከ ።

፶፯፤ ወበጺሖ ፡ ሀገረ ፡ ሰምኑድ ፡ ተሰአለ ፡ በእንቲአሁ ፡ ወነገርዎ ፡ ሰብእ ፡ ወአመርዎ ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፡ ወሐዊሮ ፡ ረከቦ ፡ ውስተ ፡ ማኅ ደሩ ፡ ወሠለስቱ ፡ አግማሊሁ ፡ ምስሌሁ ፡ ውእቱኒ ፡ አእመረ ፡ ኃሢሦቶ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወአብአ ፡ ውስተ ፡ ማኅደሩ ፡ ወአ ቀረበ ፡ ሎቱ ፡ መብልዐ ፡ ወይቤሎ ፡ አ ፡

፶፬፤ ፊራጉን ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ ለእመቤታችን ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያ ኒቱም ፡ ነገሥታትና ፡ መኳንንት ፡ በየጊዜው ፡ የሰጧት ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አላት ፡ በሊቀ ፡ ካህናቱም ፡ ዘንድ ፡ የዕቃው ፡ ሣጥን ፡ በሥ ውር ፡ ይኖር ፡ ነበር ፡ የዚያንም ፡ ዕቃ ፡ ቍጥር ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ ያውቃል ፡ ያ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ በእርሱ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ነበርና ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የዕቃው ፡ ሣጥን ፡ ያለበትን ፡ ለልጁ ፡ ሳይነግር ፡ ያ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ በድንገት ፡ ሞተ ።

፶፭፤ ኤጲስቆጶሱም ፡ የሊቀ ፡ ካህናቱን ፡ ሞት ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ወደዚያች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መጥቶ ፡ ከልጁ ፡ ገንዘቧን ፡ ፈለገ ፡ ያም ፡ ልጅ ፡ አባቴ ፡ በድንገተኛ ፡ ሞት ፡ ስለተነጠቀና ፡ ስለ ፡ አልነገረኝም ፡ ዕቃው ፡ ያለበትን ፡ አላወ ቅሁም ፡ አለው ። ኤጲስቆጶሱም ፡ ሰምቶ ፡ ተቆጣ ፡ ሊአሠቃየውም ፡ ፈለገ ፡ ያም ፡ ልጅ ፡ ኤጲስቆጶሱን ፡ ዕቃው ፡ ያለበትን ፡ ቦታ ፡ እስ ከምፈልግ ፡ ድረስ ፡ ቆየኝ ፡ ባላ ገኘሁትም ፡ ጊዜ ፡ የወደድከውን ፡ ታደርግብኛለህ ፡ ብሎ ለመነው ፡ እርሱም ፡ ጊዜ ፡ ሰጠው ።

፶፮፤ ወደ ፡ ቤቱም ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ችግሩን ፡ ሁሉ ፡ ለሚስቱ ፡ ነገራት ። እርሷም ፡ በእግዘአ ብሔር ፡ ታምነህ ፡ በአባ ፡ መቃርስ ፡ ገዳም ፡ ወዳሉ ፡ አባቶች ፡ መነኰሳት ፡ ወደ ፡ ጎረቤቶ ቻቸውም ፡ ሒድ ፡ እነርሱ ፡ ይነግሩሃልና ፡ አለችው ። ወደዚያም ፡ ሲደርስ ፡ ችግሩን ፡ ይፈጽሙለት ፡ ዘንድ ፡ ለመነኰሳቱ ፡ ነገ ራቸው ፡ የሚነግረውም ፡ አጥቶ ፡ ተስፋ ፡ ቆረጠ ። አንድ ፡ ባሕታዊም ፡ ጠቀሰውና ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ ሰምኑድ ፡ ወደሚሉት ፡ አገር ፡ ሒደህ ፡ ስለ ፡ ባለ ፡ ገመሉ ፡ ቆሪል ፡ ጠይቅ ፡ በእርሱም ፡ ዘንድ ፡ እደር ፡ እርሱም ፡ ይነግርሃል ፡ አለው ።

፶፯፤ ወደ ፡ ሰምኑድ ፡ መንደርም ፡ ደርሶ ፡ ስለርሱ ፡ ስለቆሪል ፡ ጠየቀ ፡ ሰዎችም ፡ ነገሩት ፡ ያለበ ትንም ፡ አመለከቱት ፡ በሔደ ፡ ጊዜም ፡ ከመ ኖሪያው ፡ አገኘው ፡ ሦስቱ ፡ ግመሎቹም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ነበሩ ፡ አባ ፡ ቆሪልም ፡ ፍላጎቱን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አውቆ ፡ ወደ ፡ ማደሪያው ፡ አስገብቶ ፡ መብልን ፡ አቀረበ

www.ethiopianorthodox.org

አቡየ ፡ አንሰ ፡ ኢይበልዕ ፡ ዘእንበለ ፡ ትፌ
ጽም ፡ ሊተ ፡ ትካዝየ ፡ ወይቤሎ ፡ ቆሪል፡
ትካዝከስ ፡ ይትፌጸም ፡ በጊዜሁ ፡ ወይእዜኒ ፡
ብላዕ።

፺፰፡ ወእምድኅረ ፡ ድራር ፡ ኖሙ ፡ ለለማኅደ
ሮሙ ፡ ወከዊኖ ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ ርእዮ ፡
ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ለቆሪል ፡ ቀዊሞ ፡ ምስለ ፡
አግማሊሁ ፡ወሶበ ፡ ይሰግድ ፡ ይሰግዱ ፡ ምስ
ሌሁ ፡ ወሶበሂ ፡ ይቀውም ፡ ይቀውሙ ።
ወጸቢሖ ፡ ነሥአሙ ፡ ውስተ ፡ ገራህት ፡ ከመ ፡
ይጽዓን ፡ ተለቤ ፡ ውእቱኒ ፡ ብእሲ ፡ ሖረ ፡
ምስሌሁ ፡ ከመ ፡ ይትራድኦ ፡ ወበጺሖሙ ፡
ውስተ ፡ ገራህት ፡ አኀዘ ፡ ቆሪል ፡ ይጽዓን ፡
ዲበ ፡ ገመል ፡ ወውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ነሥአ ፡
ካልአ ፡ ገመለ ፡ ወአከበደ ፡ ቦቱ ፡ ዘእንበለ ፡
ዓቅሙ ፡ ፆሮ ፡ ወስእነ ፡ ተሐውሶ ፡ እስመ ፡
ከብዶ ፡ ፆሩ ፡ ወፈቀደ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡
ይዝብጦ ፡ ነሥአ ፡ በትረ ፡ ወጸርሐ ፡ ገመል ፡
በልሳነ ፡ ሰብእ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ አ ፡ አቡየ ፡
ቆሪል ፡ ኢትኅድጎ ፡ ለዝንቱ ፡ ብእሲ ፡ ከመ ፡
ኢያሕስም ፡ በላዕሌየ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡
አፆረኒ ፡ ዘእንበለ፡ ድልወትየ ፡ ወመጺአ ፡
ቆሪል ፡ አቀለለ ፡ ሎቱ ፡ ክበደ ፡ ፆሩ ፡ ወይ
ቤሎ ፡ ለውእቱ ፡ ብእሲ ፡ አ ፡ ወልድየ ፡
ለምንት ፡ አፆርኮ ፡ መጠነ ፡ ኢይክል ፡ ፀዊረ ፡
አኮኑ ፡ አንተ ፡ ዘተኀዝን ፡ ሶበ ፡ አምጽኡ ፡
ላዕሌከ ፡ ፆረ ፡ ክቡደ ፡ ዘኢትክል ፡ ፀዊሮቶ ።

፺፱፡ ወእምዝ ፡ሶበ ፡ አተዉ ፡ ውስተ ፡ ማኅደሩ ፡
ሰአሎ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ለአባ ፡ ቆሪል ፡
በእንተ ፡ ትካዙ ፡ ከመ ፡ ይክሥት ፡ ሎቱ ፡
መካነ ፡ መዝገብ ፡ ውእቱኒ ፡ እምድኅረ ፡ አም
ሐሎ ፡ ከመ ፡ ኢይንግር ፡ ለካልዕ ፡ ከሠተ ፡
ሎቱ ፡ ወይቤሎ ፡ ሀሎ ፡ በምሥራቃ፡ ለይእቲ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ታቦት ፡ ንዑስ ፡ ወህየ ፡
ውእቱ ፡ መዝገብ።

፻፡ ወገቢአ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ ነገራ ፡ ለብእሲቱ ፡
ወሖሩ ፡ ኅቡረ ፡ ውስተ ፡ ውእቱ ፡ መካን ፡
ወረከቡ ፡ ውእተ ፡ መዝገበ ፡ ዘአልቦ ፡ ከማሁ ፡
ውስተ ፡ መዛግብተ ፡ ነገሥት ፡ ወእምዝ ፡
ነገሮ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ውእቱኒ ፡ አወፈዮ ፡
ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይዕቀብ ።

፻፩፡ ወዝንቱኒ ፡ ቆሪል ፡ ብእሲ ፡ ጻድቅ ፡ እምድ
ኅረ ፡ ተጋደለ ፡ ተጋድሎ ፡ ብዙኀ ፡ አዕረፈ ፡
ለት ፡ አባቴ ፡ ሆይ፡ ችግሬን ፡ ሳትፈጽምልኝ ፡
እኔ ፡ አልበላም ፡ አለው ፡ ቆሪልም ፡ ችግርህ ፡
በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ ይፈጸማልና ፡ አሁን ፡ ብላ ፡
አለው ።

፺፰፡ ከራትም ፡ በኋላ ፡ በየመኝታቸው ፡ ተኙ ፡
የሌሊቱም ፡ እኩሌታ ፡ ሲሆን ፡ ያ ፡ ሰው ፡
ቆሪልን ፡ ከግመሎቹ ፡ ጋር ፡ ቆሞ ፡ አየው ፡
ሲሰግድ ፡ ይሰግዳሉ ፡ ሲቆምም ፡ ይቆማሉ ።
በነጋ ፡ ጊዜም ፡ ተልባ ፡ ይጭንባቸው ፡
ዘንድ ፡ ወደ ፡ ማሳ ፡ ወሰዳቸው ፡ ያም ፡ ሰው ፡
ሊረዳው ፡ አብሮ ፡ ሔደ ፡ ወደ ፡ ማሳውም ፡
በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ቆሪል ፡ በገመል ፡ ላይ ፡
መጫን ፡ ጀመረ ፡ ያም ፡ ሰው ፡ ሁለተኛውን ፡
ገመል ፡ ወስዶ ፡ ያለ ፡ አቅሙ ፡ ሸክሙን ፡
አክብዶ ፡ ጫነው ፡ ገመሉም ፡ መንቀሳቀስ ፡
ተሳነው ፡ ሊመታው ፡ ፈልጎ ፡ በትር ፡ አነሣ ።
ገመሉም፡አባቴ፡ቆሪል፡ሆይ፡በላዬ፡ጉዳት፡
እንዳያደርስ፡ይህን፡ሰው፡አታሰናብተውም፡
እርሱ፡ያለ፡ችሎታዬ፡አሸክሞኛልና፡ብሎ፡
በሰው ፡ አንደበት ፡ ጮኸ ፡ ቆሪልም ፡ መጥቶ
ሸክሙን ፡ አቀለለት ፡ ያንንም ፡ ሰው ፡ ልጄ ፡
ሆይ ፡ በማይችለው ፡ መጠን ፡ ለምን ፡ አሸከ
ምከው፡አንተ፡የምትአዝነው፡ልትሸከመው
የማትችለውን ፡ ሸክም ፡ በላይህ ፡ ስለ ፡
አመጡብህ፡አይደለምን፡አለው።

፺፱፡ ወደ ፡ ቤትም ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ ሰው ፡
ስለ ፡ ችግሩ ፡ የዕቃውን ፡ ቦታ ፡ ይገለጥለት ፡
ዘንድ ፡ አባ ፡ ቆሪልን ፡ ለመነው ፡ እርሱም ፡
ለሌላ ፡ እንዳይናገር ፡ ከአማለው ፡ በኋላ ፡ ገለ
ጠለት ፡ እንዲህም ፡ አለው ፡ በዚያች ፡ ቤተ ፡
ክርስቲያን ፡በስተምሥራቅ ፡ ታናሽ፡ ዋሻ ፡
አለ ፡ ዕቃውም ፡ በዚያ ፡ አለ ።

፻፡ ወደ ፡ ቤቱም ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ ለሚስቱ ፡
ነገራት ፡ በአንድነትም ፡ ወደዚያ ፡ ቦታ ፡
ሔዱ ፡ ከነገሥታት ፡ መዛግብት ፡ እንኳ ፡ የሚ
መስለው ፡ የሌለ ፡ መዝገብን ፡ አገኙ ፡
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ለኤጲስቆጶሱ ፡ ነገረው ፡
ኤጲስቆጶሱም ፡ ይጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ ለርሱ ፡
ሰጠው ።

፻፩፡ ይህም ፡ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ቆሪል ፡ ብዙ ፡
ተጋድሎን ፡ ከተጋደለ ፡ በኋላ ፡ በመልካም ፡

www.ethiopianorthodox.org

በርሥአን ፡ ጥሉል።
፶፪፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም
ሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ወበረከቱ ፡
ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

ሽምግልና ፡ አረፈ።
፶፪፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ
ንም ፡ በዚህ ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡
በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡
አሜን ።

## አርኬ

ሰላም ፡ እብል ፡ ለብፁዕ ፡ ቄሪል ። በዓለ ፡ ሠለስቱ ፡ አግማል ። ዘምስሌሆሙ ፡ ተንበለ ፡ በጊዜ ፡ ስኢል። እንዘ ፡
ይሰግድ፡ ወይጼሊ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ልዑል ። ርእሰ ፡ ካህናት ፡ ርኢክዎ ፡ ይብል ።

፶፫፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለሰማዕታተ ፡
አክሚም ፡ ወእሙንቱ ፡ እንዘ ፡ ሀለዉ፡
ጉቡአነ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በበዓለ፡
ልደት ፡ ስቡሕ ፡ ወይገብሩ ፡ ቅዳሴ ፡ ቊርባን ፡
ወናሁ ፡ ርእይዎ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ነቢሮ ፡ ዲበ ፡
ታቦት ፡ እንዘ ፡ ይሜጥዎሙ ፡ ለሕዝብ ፡
ምሥጢራተ ፡ ቅድሰት።
፶፬፡ ወእንዘ ፡ ሀለዉ ፡ በዝንቱ ፡ ፍሥሓ ፡ ዐቢይ፡
መጽአ ፡ አርያኖስ ፡ መኰንን ፡ ወአገቶሙ ፡
ወቦአ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡ ወአ
ኀዞሙ፡ ለ፪ቱ ፡ ሊቃውንተ ፡ ሀገር፡ እለ ፡
ስሞሙ ፡ በሕዋፋ ፡ ወወኒን ፡ ወመተረ፡
ርእሶሙ ፡ በሰይፍ፡ ወእምዝ ፡ ቀተለ ፡ ቀሳ
ውስተ ፡ ወዲያቆናተ ፡ ወንፍቀ ፡ ዲያቆናት ፡
ወመምህራነ ፡ ወመገብተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡
ወኢያትረፈ ፡ ምንተኒ ፡ ዕደ፡ ወአንስተ ፡
ወደቂቀ ፡ እስከ ፡ ወጽአ ፡ ደሞሙ ፡ እምአ
ንቀጸ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወውኅዘ ፡ መጠነ ፡
እስራ ፡ ዓመት።
፶፭፡ ወለአባ ፡ ብኑድያኖስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወለዲዮስ
ቆሮስ ፡ ወለሰከላብዮስ ፡ ወለአኃው ፡ እለ ፡
ምስሌሁ ፡ ወወሰዶሙ ፡ አርያኖስ ፡ እንዘ ፡
እሡራን ፡ እሙንቱ ፡ ወናሁ ፡ ጽሑፍ ፡
ተዝካረ ፡ ዕረፍቶሙ ፡ አመ ፡ ፩ለጥር።
፶፮፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም
ሐረነ ፡ በጸሎቶሙ ፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ፡
ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

፶፫፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ የአክሚም ፡ ሰማዕታት፡
መታሰቢያቸው ፡ ነው። እነርሱም ፡ በከበረ ፡
የልደት ፡ በዓል ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ፡
የቊርባን ፡ ቅዳሴ ፡ አድርገው ፡ ተሰብስበው ፡
ሳሉ ፡ እነሆ ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡
ኢየሱስ፡ ክርስቶስን ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡
ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ለሕዝቡ ፡ ሲያቀብ
ላቸው ፡ አዩት።
፶፬፡ በዚህም ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ውስጥ ፡ እያሉ፡
መኰንኑ ፡ አርያኖስ ፡ መጥቶ ፡ ከበባቸው ፡
ወደ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ገብቶ ፡ ስማቸው ፡
በሕዋፋና ፡ ወኒን ፡ የሚባል ፡ ሁለቱን ፡ የሀገር፡
አለቆች ፡ ይዞ ፡ ራሳቸውን ፡ በሰይፍ ፡ ቆረጠ ፡
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ቀሳውስትን፡ ዲያቆናትን ፡
ንፍቀ፡ ዲያቆናትን፡ መምህራንን፡ የቤተ፡
ክርስቲያንን ፡ ሹማምንት ፡ ገደለ፡ ደማቸው ፡
ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ደጃፍ ፡ ወጥቶ ፡ ሃያ ፡
ክንድ ፡ ያህል ፡ እስኪጎርፍ ፡ ወንዶችን ፡
ሴቶችንና ፡ ልጆችንም ፡ ምንም፡ ሳያስቀር ፡
አሳረዳቸው።
፶፭፡ ኤጲስቆጶሱን ፡ አባ ፡ ብኑድያኖስን ፡ ዲዮስቆ
ሮስን ፡ ሰከላብዮስን ፡ ከኤጲስቆጶሱ ጋር ፡
ያሉ፡ መነኰሳትንም ፡ እነርሱን ፡ እንደ
ታሠሩ ፡ አርያኖስ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ወሰዳቸው፡
እነሆ ፡ የዕረፍታቸው ፡ መታሰቢያ ፡ ጥር ፡
አንድ ፡ ቀን ፡ ተፍፎአል።
፶፮፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡
እኛንም፡ በጸሎታቸው ፡ ይማረን ፡ በረከታ
ቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡
አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለደምክሙ ፡ ዘተክዕወ ፡ እንበለ ፡ ምሒክ። እስከ ፡ ተለዓለ ፡ ጥቀ ፡ መጠነ ፡ አብራክ። ሰማዕታተ ፡ አክ
ሚም ፡ ቅቱላን ፡ በበዓለ ፡ ልደት ፡ ቡሩክ ። ምልዑ ፡ ውስተ ፡ ልብየ ፡ ፈሪሆተ ፡ ሕያው ፡ አምላክ። ከመ ፡ ሕይወ
ትየ ፡ ኢይኅልቅ ፡ በበክ።

www.ethiopianorthodox.org

፩፤ በስመ፡ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፴ ሁ ፡ ለታኅሣሥ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ ክቡር ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ አበ፡ምኔት፡ዘገዳመ፡አስቄጥስ፡በደብረ፡አባ፡ መቃርስ።

፪፤ ወሶበ፡ ተሠይመ፡ ዝንቱ፡ አብ፡ በርሀት፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ወኮነ፡ አበ፡ ለብዙኃን፡ ቅዱሳን፡ ወእምኔሆሙ፡ አባ፡ ገዐርጊ፡ ወአባ፡ አብርሃም፡ ከዋክብት ፡ ዓበይት ፡ ወአባ ፡ ሚናስ፡ ኤጲስ ቆጶስ ፡ ዘሀገረ ፡ ተሙዝ ፡ ወአባ ፡ ዘካርያስ ፡ ዘሀገረ፡ ስሐ፡ ወብዙኃን፡ አምሳሎሙ፡ ዘኮኑ፡ መርሶ፡ ለነፍሳተ፡ ብዙኃን፡ ሰብእ።

፫፤ ወሶበ፡ ያቄርብ፡ ቍርባነ፡ ለሕዝብ፡ ይትከሠት፡ ሎቱ፡ ኃጥእ፡ ወጻድቅ፡ ወብዙኀ፡ ጊዜ፡ ርእዮ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወለመላእ ክቲሁ፡ ቅዱሳን፡ በዲበ፡ ምሥዋዕ።

፬፤ ወርእዮ ፡ ለአሐዱ ፡ ቀሲስ ፡ አሐተ ፡ ዕለተ፡ ዘምግባሩ፡ እኩይ፡ ሶበ፡ መጽአ፡ ኀበ፡ ቤተ፡ ክር ስቲያን ፡ ወምስሌሁ ፡ ብዙኃን ፡ መናፍስት ፡ ርኵሳን፡ እንዘ፡ የዐግትዎ፡ ወይገብሩ፡ ውስተ፡ አፉሁ፡ ልጓመ፡ ወእምቅድመ፡ ይባእ፡ ውስተ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ወጽአ፡ መልአከ፡ እግዚአ ብሔር ፡ እምነ ፡ ምሥዋዕ ፡ ወሰደዶሙ ፡ እምኔሁ፡ በሰይፈ፡ እሳት፡ ወበዊአ፡ ውእቱ፡ ቀሲስ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ወለብሰ ፡ ልብሰ ፡ ክህነት ፡ ዘቅዳሴ ፡ ኮነ ፡ ኵለንታሁ ፡ ከመ፡ እሳት፡ ወቀደሰ፡ ቍርባነ፡ ወመጠዎሙ፡ ለሕዝብ፡ ምሥጢረ፡ ቅድሳት።

፭፤ ወሶበ፡ ከልአ፡ እምላዕሌሁ፡ ልብሰ፡ ክህነት፡ ወሠርጐ ፡ ቅዳሴ ፡ ወወጽአ ፡ አፍአ ፡ ወተመ ጠውዎ ፡ ውእቶሙ ፡ መናፍስት ፡ ርኵሳን ፡ ጸሊማን፡ ወገብሩ፡ ቦቱ፡ በከመ፡ ቀዳሚ።

፮፤ ወዘንተ፡ ነገረ፡ ይቤሎሙ፡ አባ፡ ዮሐንስ፡ እንዘ፡ ያጤይቆሙ ፡ ለአኃው ፡ አልቦ ፡ ፍልጠት ፡ ለካህን ፡ ኃጥእ ፡ ወለካህን ፡ ጻድቅ ፡ በጊዜ ፡ መልእክት ፡ ዘቅዳሴ ፡ እስመ ፡ በእንተ ፡ አሚኖቶሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ይከውን ፡ ውእቱ ፡ ኅብስት ፡ ሥጋሁ ፡ ለክርስቶስ፡ ወወይኑሂ ፡ ደሞ፡ ክቡረ።

፩፤ አንድ ፡ አምላካ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ .ዱስ ፡ ስም፡ ታኅሣሥ ፡ ሠላሳ ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ በአባ ፡ መቃርስ ፡ ገዳም ፡ በአስ ቄጥስ፡ አበ፡ ምኔት፡ የሆነ፡ የከበረ፡ አባት፡ አባ፡ ዮሐንስ፡ አረፈ።

፪፤ ይህም ፡ አባት ፡ በተሾመ ፡ ጊዜ ፡ ቤተ ፡ ክርስ ቲያን፡ በራች፡ ለብዙ፡ ቅዱሳንም፡ አባት፡ ሆነ፡ ከእርሳቸውም ፡ ውስጥ ፡ ታላላቅ ፡ ከዋክብት ፡ የሆኑ፡ አባ፡ ገዐርጊና፡ አባ፡ አብርሃም፡ የሀገረ፡ ተሙዝ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አባ ፡ ሚናስ ፡ የሀገር ፡ ስሐ፡ አባ ፡ ዘካርያስ ፡ ለብዙ፡ ሰዎች ፡ ነፍሳት ፡ ወደብ ፡ የሆኑ ፡ እነርሱን ፡ የመሰሉ ፡ ሌሎች ፡ ብዙዎች፡ አሉ።

፫፤ ለሕዝቡ ፡ ቅዱስ ፡ ቍርባንን ፡ በሚያቈርብ ፡ ጊዜ፡ ኃጢአተኞቹና ፡ ጻድቁ ፡ ይገለጥለታል ፡ ከቅዱሳን ፡ መላእክቶቹ ፡ ጋር ፡ ጌታችንን ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስንም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ብዙ፡ ጊዜ፡ አየው።

፬፤ በአንዲትም ፡ ዕለት ፡ ሥራው ፡ የከፋ ፡ አን ዱን ፡ ቄስ ፡ ወደ፡ ቤተክርስቲያን ፡ ሲመጣ ፡ አየው ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ያሉ ፡ ብዙዎች ፡ ርኩሳን ፡ የረቀቁ ፡ አጋንንት ፡ ከበውት ፡ አፉ ፡ ውስጥ ፡ ልጓም ፡ አድርገዋል፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ከመግባቱ ፡ በፊት ፡ የእግዚአ ብሔር ፡ መልአክ ፡ ከመሠዊየው፡ ወ·.·ቶ ፡ በእ ሳት፡ ሰይፍ፡ ከእርሱ፡ ከቄሱ፡ መናፍስትን፡ አሳ ደዳቸው፡ ቄሱም፡ ወደ፡ መቅደስ፡ በገባ፡ ጊዜ፡ መቀደሻውን፡ የክህነት፡ ልብስ፡ ለበሰ፡ ሁለመ ናውም፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ሆነ ፡ ቀድሶም ፡ ለሕ ዝቡ፡ ሥጋውንና፡ ደሙን፡ አቀበላቸው።

፭፤ ልብሰ ፡ ተክህኖውንና ፡ የመቀደሻውን፡ ሽልማት ፡ ከላዩ ፡ አውልቆ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ በወጣ፡ ጊዜ ፡ እነዚያ ፡ የጠቆሩ ፡ መናፍስት ፡ ርኩሳን ፡ ተቀብለው ፡ እንደቀድሞው ፡ አደረ ጉበት።

፮፤ አባ፡ ዮሐንስም ፡ ይህን ፡ ገር ፡ ለመነኰሳቱ ፡ ሲያስረዳ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው፡ በቅዳሴ ፡ አገል ግሎት ፡ ጊዜ ፡ ለኃጢአተኛውና ፡ ለጻድቁ ፡ ቄስ ፡ ልዩነት ፡ የለም ፡ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ እምነት ፡ ያ ፡ ኅብስት ፡ ተለውጦ ፡ የክርስቶስን ፡ ሥጋ ፡ ይሆናልና ፡ ወይኑም ፡ የከበረ ፡ ደሙን ፡ ይሆ ናልና።

www.ethiopianorthodox.org

፯፤ ወይቤሎሙ፡ ዓዲ፡ በምሳሌ፡ ከመ፡ ማኅተመ፡ ንጉሥ፡ ዘየኀትሙ፡ ቦቱ፡ ኅቢነ፡ ወወርቀ፡ ወብሩረ፡ ወማኅተምሰ፡ ኢይትዌለጥ፡ ወከማሁ፡ እምካህናትኒ፡ ኢይትዌለጥ፡ አላ፡ ውእቱ፡ እግዚአቤሔር፡ ይፈድዮ፡ ለኵሉ፡ ለለ፩፡በከመ፡ምግባሩ፡በጊዜሁ።

፰፤ ወለዝንቱ፡ቅዱስ፡ዮሐንስ፡በጽሐ፡ምንደቤ፡ዐቢይ፡ እስመ፡ ዔወውዎ፡ በርበር፡ አረማውያን፡ ወወሰድዎ፡ ኀበ፡ ብሔሮሙ፡ ወአሠርዎ፡ ወነበረ፡ ኀቤሆሙ፡ እንዘ፡ ያመነድብዎ፡ብዙኀ፡አዝማነ። ወእምዝ፡አግብኦ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት፡ውስተ፡ደብሩ።

፱፤ ወእምቅድመ፡ ይፍልስ፡ አእምረ፡ ጊዜ፡ ፍልሰቱ፡ ወአስተጋብአሙ፡ ለአኃው፡ ወአዘዘሙ፡ ከመ፡ ይዕቀቡ፡ ትዕዛዘ፡ ወንጌል፡ ወይሑሩ፡ከመ፡ሖረቶሙ፡ለአበው፡ቅዱሳን፡ ከመ፡ ይንሥኡ፡ ምስሌሆሙ፡ መክፈልተ፡ ወርስተ፡በመንግሥተ፡ሰማያት።

፲፤ ወእምዝ፡ ሐመ፡ ንስቲተ፡ ወርእዮሙ፡ ለማኅበረ፡ ቅዱሳን፡ መጽኡ፡ ከመ፡ ይንሥኡ፡ ነፍሶ፡ወተፈሥሐ፡ዐቢየ፡ፍሥሓ፡ወመጠወ፡ ነፍሶ፡ ውስተ፡ እዴሁ፡ ለእግዚአብሔር፡ ወፆርዎ፡ አኃው፡ ውስተ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ቅድስት፡ ወገነዝዎ፡ በዝማሬ፡ ወበማኅሌት፡ ዐቢይ፡ ወቀበርዎ፡ ወበእንተ፡ አፍቅሮቶሙ፡ ኪያሁ፡ መተሩ፡ እምልብሰ፡ ግንዘቱ፡ ወአንበርዎ፡ ኀቤሆሙ፡ ወኮነ፡ ፈውሰ፡ ለኵሉ፡ ዘይደዊ። መዋዕሊሁሰ፡ ለዝንቱ፡ አብ፡ ፺ዓመት፡ ወማኅደሩኒ፡ ዘይብልዋ፡ በግቢግ፡ ሀለወት፡ እስከ፡ዮም።

፲፩፤ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፡ ኪያነኒ፡ ይምሐረነ፡ በጸሎቱ፡ ለዝ፡ አብ፡ ወበረከቱ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፯፤ ዳግመኛም፡ በምሳሌ፡ እንዲህ፡ አላቸው፡ በብረት፡ በወርቅና፡ በብር፡ ላይ፡ እንደሚቀረጽ፡ እንደ፡ ንጉሥ፡ ማኅተም፡ ነው። ማኅተሙም፡ አይለወጥም፡ እንዲሁ፡ ከካህናትም፡ የክህነት፡ ጸጋ፡ አይለወጥም፡ እርሱ፡ እግዚአብሔር፡ በጊዜው፡ ጊዜ፡ ለሁሉም፡ ለየአንዳዱ፡ እንደሠራው፡ ይከፍለዋል፡ እንጂ።

፰፤ ይህንም፡ የከበረ፡ ዮሐንስ፡ ታላቅ፡ መከራ፡ ደርሶበታል፡ አረማውያን፡ በርበር፡ ማርከው፡ ወደ፡ አገራቸው፡ ወስደው፡ ታልና፡ እያሠቃዩትም፡ በእነርሱ፡ ዘንድ፡ ብዙ፡ ዘመን፡ ታሥሮ፡ ኖረ፡ ከዚህም፡ በኋላ፡ የክብር፡ ባለቤት፡ ጌታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ወደ፡ ገዳሙ፡ መለሰው።

፱፤ ከመሞቱ፡ በፊት፡ የሚሞትበን፡ ጊዜ፡ አውቆ፡ መነኰሳቱን፡ ሰበሰባቸውና፡ የወንጌልን፡ ትዕዛዝ፡ ይጠብቁ፡ ዘንድ፡ በሰማያዊ፡ መንግሥት፡ በሳ፡ ዕድልን፡ ርስትንም፡ ከእርሳቸው፡ ጋር፡ ይቀበሉ፡ ዘንድ፡ እንደ፡ ቅዱሳን፡ አባቶች፡ አካሄድ፡ እንዲጓዙ፡ አዘዛቸው።

፲፤ ከዚህም፡ በኋላ፡ ጥቂት፡ ታመመ፡ ነፍሱን፡ ሊቀበሉ፡ የቅዱሳንን፡ አንድነት፡ ሲመጡ፡ አያቸውና፡ ፈጽሞ፡ ደስ፡ አለው፡ ነፍሱንም፡ በእግዚአብሔር፡ እጅ፡ ሰጠ፡ መነኰሳቱ፡ ወደ፡ ከበረች፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ተሸክመው፡ ወስደው፡ በመዘመርና፡ በታላቅ፡ ምስጋና፡ ገንዘው፡ ቀበሩት፡ እርሱንም፡ ከመውደዳቸው፡ የተነሣ፡ ከተገነዘበት፡ ልብስ፡ ቆርጠው፡ በእነርሱ፡ ዘንድ፡ አኖሩት፡ ለሚታመም፡ ሁሉ፡ የሚፈውስ፡ ሆነ፡ የዚህም፡ አባት፡ ዕድሜ፡ ዘጠና፡ ዓመት፡ ሆነ፡ በግቢግ፡ የሚልዋት፡ መኖሪያው፡ እስከ፡ ዛሬ፡ አለች።

፲፩፤ ለእግዚአብሔርም፡ ምስጋና፡ ይሁን፡ እኛንም፡ በዚህ፡ አባ፡ ጸሎት፡ ይማረን፡ በረከቱም፡ ከእኛ፡ ጋር፡ ትኑር፡ ለዘላለሙ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ ለዮሐንስ፡ ዘተሰምየ፡ ሊቀ። በውስተ፡ አስቄጥስ፡ ይምራሕ፡ ዘለመቃርዮስ፡ ደቀ። ለእመ፡ ገብሩ፡ ጌጋየ፡ ወለእመ፡ ገብሩ፡ ጽድቀ። በማኅተመ፡ ንጉሥ፡ ምሳሌ፡ ግብረ፡ ካህናት፡ አፆቀ። ዘየኀትሙ፡ ቦቱ፡ ኅቢነ፡ ወወርቀ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፪፤ ወበዛቲ፡ዕለት፡ካዕበ፡ኮነ፡ተዝካረ፡ዕረፍቱ፡ ለአባ፡ዮሐንስ፡ብፁዕ፡ወውእቱ፡ መስታ ጋድል ፡ እምአመ ፡ ለብሰ ፡ አልባሰ ፡ ምንኵስና፡ ተውህቦ ፡ ጸጋ ፡ ትንቢት ፡ ወፈውሶ፡ዱያን፡ወተሰምዐ፡ዜናሁ፡ውስተ፡ ኵሉ፡ምድር።

፲፫፤ ወሀሎ ፡ ፩ ፡ መኰንን ፡ ዘይሔውጸ ፡ ወትረ ፡ ለዝንቱ፡አባ፡ዮሐንስ፡ወነበረት፡ብእሲቱ፡ ለመኰንን ፡ እንዘ ፡ ታጌብሮ ፡ ለምታ ፡ ወታምሕሎ ፡ ከመ ፡ ያብጽሓ ፡ ኀበ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ውእቱኒ ፡ ይቤላ ፡ እስመ ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ፡ኢይሬኢ፡ገጸ፡አንስት፡እምአመ፡ ፴፡ ዓመት ፡ ወእምዝ ፡ ሐዊሮ ፡ መኰንን ፡ ነገሮ፡ለአባ፡ዮሐንስ፡ዘትቤሎ፡ብእሲቱ፡ ወይቤሎ፡አባ፡ዮሐንስ፡በሥምረተ፡እግዚአ ብሔር፡እፌጽም፡ላቲ፡ፈቃዳ።

፲፬፤ ወበይእቲ፡ሌሊት፡አስተርአያ፡በሕልም፡ ቅዱስ፡ዮሐንስ፡ለይእቲ፡ብእሲት፡ወይቤላ፡ ሚ ፡ ሊተ ፡ ወሚ ፡ ለኪ ፡ ኦ ፡ ብእሲቶ ፡ ዘኃሠሥኪ ፡ ትርአዪ ፡ ገጽየ ፡ ሊተ ፡ ዘኢኮንኩ፡ ጻድቀ ፡ ወኢነቢየ ፡ ወእምይ እዜሰ፡ኢትድግሚ፡ኃሢሠ፡ገጽየ። ወዘንተ፡ ብሂሎ፡ጸለየ፡ላዕሌሃ፡ወባረካ።

፲፭፤ ወበሣኒታ ፡ ነገረቶ ፡ ለምታ ፡ ዘከመ ፡ ተራከባ ፡ በመንፈስ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ወአመረቶ ፡ አርአያሁ ፡ ወአምሳሊሁ ፡ ወእምዝ ፡ ለአከቶ ፡ ለምታ ፡ ኀበ ፡ ቅዱስ ፡ ዘምስለ፡ተውዳስ፡ወምዝጋና፡ብዙኅ።

፲፮፤ ወሶበ ፡ ርእዮ ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ ለምታ ፡ አክሞሰሰ፡ወይቤሎ፡አኮኑ፡ተፈጸመ፡ላቲ፡ ተምኔታ ፡ ለብእሲትከ ፡ እስመ ፡ ረከበተኒ ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ በሥምረተ፡ እግዚአብሔር፡ ወሰሚዖ፡መኰንን፡አንከረ፡ፈድፋደ፡እም ትሩፋቲሁ፡ወጽድቁ፡ወነበረ፡ዝንቱ፡አባ፡ ዮሐንስ ፡ መጠነ ፡ ፺ ዓመት ፡ በተጋድሎ ፡ ጽፉቅ፡ወእምዝ፡አዕረፈ፡በሰላም።

፲፯ ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡ አሜን።

፲፪፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ ደግሞ ፡ የተመሰገነ ፡ የአባ፡ ዮሐንስ ፡ የዕረፍቱ ፡ መታሰቢያ ፡ ነው ፡ ይህም፡ ተጋዳይ ፡ የምንኵስና ፡ ልብስን ፡ ከለበሰ፡ጀምሮ፡የትንቢትና፡በሽተኞችን፡ የመፈወስ ፡ ሀብት ፡ ተሰጠው ፡ ዜናውም ፡ በሀገሩ፡ሁሉ፡ተሰማ።

፲፫፤ ይህን ፡ አባ ፡ ዮሐንስን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የሚጐበኘው ፡ አንድ ፡ መኰንን ፡ ነበረ ፡ የመኰ ንኑም፡ሚስት፡ወደ፡አባ፡ዮሐንስ፡ዘንድ፡ እንዲወስዳት ፡ ባሏን ፡ ታምለውና ፡ ታስገ ድደው ፡ ነበር ፡ እርሱም ፡ የከበረ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ፡ከአርባ፡ዓመት፡ጀምሮ፡የሴቶችን፡ ፊት ፡ አላየም ፡ አላት ። ከዚህም፡ በኋላ ፡ መኰንኑ፡ሒዶ፡ሚስቱ፡ያለችውን፡ለአባ፡ ዮሐንስ፡ነገረው፡አባ፡ዮሐንስም፡ በእግዚአ ብሔር፡ ፈቃድ ፡ የፈለገችውን ፡ እፈጽምላ ታለሁ፡አለው።

፲፬፤ በዚያችም ፡ ሌሊት ፡ የከበረ ፡ ዮሐንስ ፡ ለዚያች፡ ሴት፡በሕልም፡ተገልጾ፡እንዲህ፡ አላት፡ጻድቅ፡ያልሆንኩ፡ወይም፡ነቢይ፡ የኔን፡ፊት፡ታዪ፡ዘንድ፡የምትሺ፡አንቺ፡ ሴት፡ከእኔ፡ምን፡አለሽ፡እኔስ፡ካንቺ፡ምን፡ አለኝ፡እንግዲህስ፡ፊቴን፡ማየት፡አትሺ፡ ይህንንም፡ብሎ፡በላይዋ፡ጸልዮ፡ባረካት።

፲፭፤ በማግሥቱም ፡ የከበረ ፡ አባ፡ ዮሐንስ ፡ በመንፈስ፡እንደታያት፡ለባሏ፡ ነገረችው ። መልኩንና፡አምሳያውን፡ አመለከተችው፡ ከዚህም፡በኋላ፡ከብዙ፡ሙገሳና፡ምስጋና፡ ጋር፡ባሏን፡ወደ፡አባ፡ዮሐንስ፡ላከችው።

፲፮፤ የከበረ፡ዮሐንስም፡ባሏን፡በአየው፡ጊዜ፡ ፈገግ፡ብሎ፡የሚስትህ፡ምኞቷ፡የተፈጸ መላት፡አይደለምን፡በዚች፡ዕለት፡ በእግዚ አብሔር፡ፈቃድ፡አግኝታኛለችና፡አለው፡ መኰንኑም፡ሰምቶ፡ከትሩፋቱና፡ከደግነቱ፡ የተነሣ ፡ እጅግ ፡ አደነቀ ። ይህም ፡ አባ ፡ ዮሐንስ፡ጭንቅ፡በሆነ፡ተጋድሎ፡ዘጠና፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ኖረ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በሰላም፡አረፈ።

፲፯፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን፡ እኛንም፡ በዚህ፡አባት፡ጸሎት፡ይማረን፡ በረከቱም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡ አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

## አርኬ

ሰላም፡ ለዮሐንስ፡ዘአኀረመ፡ ሕይወቶ።እምነጽሮ፡ አንስት፡ ዘያስሕቶ። ይቤላ፡ በሕልም፡ ለእንተ፡ ጽሕቀት፡ርእዮቶ።ትርአዩ፡ዘተመነይኪ፡ገጽየ፡ከንቶ።ሚ፡ሊተ፡ወለኪ፡ብእሲቶ።

፲፰፡ ወበዛቲ፡ ዕለት፡ ኮኑ፡ ሰማዕተ፡ ቅዱሳን፡ ኮርዮን፡ወፊልሞና፡ዐበይተ፡ሐራሁ፡ለአር ያኖስ፡ መኰንን፡ ወ፵፡ ሐራ፡ እለ፡ ምስሌሆሙ።

፲፱፡ ወምክንያተ፡ ስምዖሙ፡ ሶበ፡ ርእዩ፡ ተአምራተ፡ እምሰማዕታት፡ ዲዮስቆሮስ፡ ወሰከላብዮስ፡ ወብኑድያስ፡ ዐበይተ፡ አክሚም፡ዘተገብረ፡ገደፉ፡ትርሲተ፡ሐራ፡ ወቆሙ፡ ቅድመ፡ አርያኖስ፡ መኰንን፡ ወጸርሑ፡እንዘ፡ይብሉ፡ንሕነ፡ክርስቲያን፡ ገሀደ፡ ወምእመናን፡ በክርስቶስ፡አምላክ፡ ዘበአማን፡ ወአዘዘ፡ መኰንን፡ ይውርውዎሙ፡ውስተ፡እቶነ፡እሳት፡ወብዙኃን፡ ርእይዎሙ፡ እንዘ፡ ይዌርዉ፡ ርእሶሙ፡ ወከመዝ፡ፈጸሙ፡ስምዖሙ።

፳፡ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፡ወበረከቶሙ፡ ለሰማዕት፡ ትብጽሐነ፡ ለዓለመ፡ ዓለም፡ አሜን።

፳፩፡ ወበዛቲ፡ ዕለት፡ ካዕበ፡ አዕረፈ፡ አባ፡ ዘካርያስ፡መስተጋድል።

፳፪፡ ወዝንቱ፡ ቅዱስ፡ እምቅድመ፡ ይመንኵስ፡ እንዘ፡ የሐውር፡ በፍኖት፡ ተንሥኡ፡ ላዕሌሁ፡ በርበር፡ ወአኀዘዎ፡ ወፈቀዱ፡ ይሕርድዎ፡ ወበፈቃደ፡ እግዚአብሐር፡ እንዘ፡ የሐልፍ፡ በይእቲ፡ ፍኖት፡ ሊቀ፡ ምኔት፡ ከልሐ፡ ላዕሌሆሙ፡ ወእሙንቱ፡ ተሐዘቡ፡ከመ፡በጽሐ፡ኀቤሆሙ፡ሠራዊት፡ ወጐዩ፡ፈሪሆሙ፡ወእንዘ፡ይጐይዩ፡ውስተ፡ ባሕር፡ተሰጥሙ።

፳፫፡ ወሶበ፡ ድኅነ፡ ዘካርያስ፡ እምተቀትሎ፡ ነሥአ፡ ንዋዮሙ፡ ወቦአ፡ ውስተ፡ ሀገር፡ ከመ፡ ይሢጥ፡ ወአኀዞ፡ መኰንነ፡ ሀገር፡ ወፈቀደ፡ ይቅትሎ፡ እንዘ፡ ይሔሊ፡ ከመ፡ ውእቱ፡ ሰራቂ፡ ወሰቦ፡ አእመረ፡ ግብሮ፡ ኀደጎ።

፳፬፡ ወእምዝ፡ ሖረ፡ ኀበ፡ ደብረ፡ አባ፡ ጳኩሚስ፡ ወለብሰ፡ አልባሰ፡ ምንኵስና፡ ወተጸምደ፡ በጾም፡ ወበጸሎት፡ እስከ፡ ቀንአ፡ ላዕሌሁ፡

፲፰፡ በዚችም፡ ዕለት፡ የመኰንኑ፡ አርያኖስ፡ የጥፍሮቹ፡ ታላላቆች፡ ኮርዮንና፡ ፊልሞና፡ ከእርሳቸውም፡ ጋር፡ ካሉ፡ አርባ፡ ወታደሮች፡ ጋር፡በሰማዕትነት፡ሞቱ።

፲፱፡የሰማዕትነታቸውም፡ምክንያት፡የአክሚም፡ ታላላቆች፡ ከሆኑ፡ ከሰማዕታት፡ ዲዮስ ቆሮስ፡ ከሰከላብዮስና፡ ከብኑድያስ፡ የተደረ ገውን፡ ተአምራት፡ በአዩ፡ ጊዜ፡ የወታደ ርነት፡ የማዕርግ፡ ሽልማታቸውን፡ ጣሉ፡ በመኰንኑ፡አርያኖስም፡ፊት፡ቁመው፡እኛ፡ በእውነተኛ፡ አምላክ፡ በክርስቶስ፡ የም ናምን፡ በግልጥ፡ ክርስቲያን፡ ነን፡ ብለው፡ ጮኹ። መኰንኑም፡ ከእሳት፡ ማንደጃ፡ ውስጥ፡ ይጥሏቸው፡ ዘንድ፡ አዘዘ፡ ራሳቸ ውንም፡ ሲወረውሩ፡ ብዙዎች፡ አዩአቸው፡ ገድላቸውንም፡እንዲህ፡ፈጸሙ።

፳፡ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ ይሁን፡ የሰማዕ ታትም፡ በከታቸው፡ ትድረሰን፡ ለዘላለሙ፡ አሜን።

፳፩፡ በዚችም፡ ዕለት፡ ተጋዳይ፡ የሆነ፡ አባ፡ ዘካርያስ፡አረፈ።

፳፪፡ ይህም፡ ቅዱስ፡ ከመመንኰሱ፡ በፊት፡ በጐዳና፡ ሲጓዝ፡ አረማውያን፡ በርበር፡ ተነ ሡበትና፡ ያዙት፡ ሊያርዱትም፡ ወደዱ፡ በእ ግዚአብሐርም፡ፈቃድ፡ የገዳሙ፡ አለቃ፡ በዚያች፡ጐዳና፡ሲያልፍ፡በላያቸው፡ጮኸ፡ እነርሱም፡ ሠራዊት፡ እንደደረሰባቸው፡ ተጠራጠሩ፡ ፈርተውም፡ ሸሹ፡ ሲሸሹም፡ ከባሕር፡ገብተው፡ሰጠሙ።

፳፫፡ ዘካርያስም፡ ከመገደል፡ በዳነ፡ ጊዜ፡ ይሸጥ፡ ዘንድ፡ገንዘባቸውን፡ይዞ፡ወደ፡ከተማ፡ገባ፡ የሀገሩም፡ ገዥ፡ ያዘው፡ ሌባ፡ እንደ፡ ሆነ፡ አስቦ፡ ሊገለው፡ ወደደ፡ ግን፡ ሥራውን፡ በአወቀ፡ጊዜ፡ተወው።

፳፬፡ ከዚህም፡ በኋላ፡ ወደ፡ አባ፡ ጳኩሚስ፡ ገዳም፡ ሒዶ፡ የምንኵስናን፡ ልብስ፡ ለበሰ፡ ሰይ ጣንም፡ እስከ፡ ቀናበት፡ ድረስ፡ በጾምና፡

www.ethiopianorthodox.org

ሰይጣን ፡ ወእምዝ፡ ተመሰለ ፡ በአምሳለ ፡ አቡሁ ፡ ወአስተርአዮ፡ በሕልም ፡ ወይቤሎ ፡ እስመ ፡ ቀርበ፡ ፍልሰትየ ፡ ነዓ ፡ ከመ ፡ ትቅብረኒ ፡ ወሐለየ ፡ ዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ከመ ፡ እሙን ፡ ውእቱ ፡ ወሖረ ፡ ኀበ ፡ አቡሁ ፡ ወረከቦ፡ ሕያወ ፡ ወአእመረ ፡ ከመ ፡ ትምይንተ ፡ ሰይጣን ፡ ውእቱ ፡ ወተመይጠ ፡ ውስተ ፡ ማኅደሩ ፡ ወዐፀወ ፡ ኆኅቶ ፡ ወነበረ ፡ እንዘ፡ይትጋደል፡እስከ፡ሞፆ፡ለሰይጣን።

፳፭፤ ወበዕለተ ፡ ሆሣዕና ፡ ሖረ ፡ ኀበ ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ ወሰአሎ ፡ ከመ ፡ ያብሖ ፡ ይሑር ፡ ኀበ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወአብሖ ፡ ወበሣኒታ፡ ረከቦሙ ፡ ለሠለስቱ ፡ ዕደው ፡ ብሩሃን ፡ እንዘ ፡ ይጸንሕዎ፡ወሖረ፡ምስሌሆሙ።

፳፮፤ ወእምዝ ፡ ሖረ ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ ከመ ፡ ይርአይ፡ ማኅደሮ ፡ ለአባ ፡ ዘካርያስ ፡ ወረከቦሙ ፡ ለሠለስቱ፡ተመናት፡ዐበይት፡ወይድህኩ፡ምድረ፡ ወሶበ ፡ ርእዮሙ ፡ ፈርሀ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወእሙንቱ ፡ ጸውዕዎ ፡ በስሙ ፡ ሠለስተ ፡ ጊዜ ፡ ወተመይጠ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ተናገርዎ ፡ በልሳነ ፡ ሰብእ ፡ ወይቤልዎ ፡ አ ፡ አብ ፡ አይቴ ፡ ሖረ ፡ እግዚእነ ፡ ዘካርያስ ፡ ዘይሴስየነ ፡ ዘነበረ ፡ ወሰሚዖ ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ አንከረ ፡ ወወሀቦሙ መብልዐ።

፳፯፤ ወተመይጠ፡አባ፡ዘካርያስ፡ውስተ፡ማኅደሩ፡ ነበረ፡በተጋድሎ፡ብዙኅ፡ወእምዝ፡አዕረፈ፡ በሰላም።

በጸሎት ፡ ተጠመደ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በአ ባቱ፡ ተመስሎ ፡ በሕልም ፡ ታየውና ፡ መሞቻዬ ፡ ጊዜ ፡ ደርሷልና ፡ ትቀብረኝ ፡ ዘንድ ፡ ና ፡ አለው ፡ ቅዱሱም ፡ እውነት ፡ እንደሆነ ፡ አስቦ ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ ሔደ ፡ ግን ፡ በጤንነት፡አገኘው።የሰይጣን፡ተንኰልም፡ እንደሆነ ፡ አውቆ ፡ ወደ ፡ መኖሪያው ፡ ተመለሰ ፡ ሰይጣንንም ፡ ድል ፡ እስከአደ ረገው፡ ድረስ ፡ በሩን ፡ ዘግቶ፡ እየተጋደለ ፡ ኖረ።

፳፭፤ በሆሣዕናም፡ዕለት፡ወደ፡አበ፡ምኔቱ፡ሒዶ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ለመሔድ ፡ ፈቃድ ፡ ለመነው ፡ ፈቀደለትም ፡ በማግሥቱም ፡ ፊታቸው ፡ የሚያበራ ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ ሲጠብቁት ፡ አገኘቻውና ፡ አብሮዋቸው ፡ ሔደ።

፳፮፤ ከዚህም፡በኋላ፡አበ፡ምኔቱ፡የአባ፡ዘካርያስን፡ ቤት ፡ ሊጐበኝ ፡ ሔደ ፡ ሦስት፡ ታላላቅ ፡ ዘንዶ ዎችም፡በምድር፡ላይ፡ሲርመሰመሱ፡አግኝቶ፡ በአያቸው፡ጊዜ፡ፈራቸው፡እነርሱም፡በስሙ፡ ጠሩት፡ወደነርሱም፡ዘወር፡ሲል፡አባት፡ሆይ፡ ሲመግበን፡የነበረ፡ጌታችን፡ዘካርያስ፡ከዚህ፡ ወደየት ፡ ሔደ ፡ ብለው ፡ በሰው ፡ አንደበት ፡ ተናገሩት ። አበ ፡ ምኔቱም ፡ ሰምቶ ፡ አደነቀ ፡ መብልንም፡ሰጣቸው።

፳፯፤ አባ ፡ ዘካርያስም ፡ ወደ ፡ መኖሪያው ፡ ተመልሶ ፡ በብዙ ፡ ተጋድሎ ፡ ኖረ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በሰላም፡አረፈ።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለዘካርያስ ፡ እንተ ፡ ነገደ ፡ እንዘ ፡ ይፃሙ ። አመ ፡ ፍጻሜሃ ፡ ለጾሙ ። ተመናት ፡ ሠለስቱ ፡ ዘይሴስዮሙ።ሶበ፡ጸውዕዎ፡ለአበ፡ምኔት፡በስሙ።እምነ፡መንክሩ፡ደንገጸ፡ወእምኵሉ፡መድምሙ።

፳፰፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ሰብአ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይገብሩ ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለሕፃናት ፡ ቅዱሳን ፡ ወንጹሐን ፡ ዘቀተሎሙ ፡ ኄሮድስ ፡ ወዜናሆሙ ፡ ጽሑፍ ፡ አመ፡፲ለጥር።

፳፰፤ በዚችም ፡ ዕለት ፡ ኄሮድስ ፡ የገደላቸውን ፡ የከበሩና ፡ የነጹ ፡ ሕፃናትን ፡ መታሰቢያቸውን፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰዎች ፡ ያከብራሉ ፡ ዜናቸውም ፡ ጥር፡ሦስት፡ቀን፡ተጽፎአል።

## አርኬ

ሰላም፡እብል፡ለለአሐዱ፡አሐዱ።ዘክልኤ፡ክረምት፡ወዘይውህዱ።በእንተ፡ልደቱ፡ለቃል፡አመ፡በአ ስፍይት፡ተገምዱ።ሕፃናት፡ንጹሐን፡ወጽሩያን፡ነገዱ።ከመ፡እምአንስት፡እሙንቱ፡ተወልዱ።

www.ethiopianorthodox.org

ተፈጸመ፡ምንባብ፡ዘወርኀ፡ታኅሣሥ፡ቡሩክ። ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ወበሣህሉ፡ወም ሕረቱ፡ለአምላክነ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ወበአስተብቍዖቶሙ፡ለብፁዓን፡ወኄ ሩያን፡ነቢያት፡ወሐዋርያት፡ወበስእለቶሙ፡ ለሰማዕታት፡ወጻድቃን፡ወሊቃነ፡ጳጳሳት፡ ወኤጲስቆጶሳት፡ቀሳውስት፡ወዲያቆናት፡ደና ግል፡ወመነኮሳት፡ወቅዱሳን፡መላእክት፡ወፈ ድፋደሰ፡በትንብልናሃ፡ለእግዝእትነ፡ቅድስት፡ ድንግል፡ማርያም፡ይዕቀቦ፡ለርእሰ፡ሊቃነ፡ ጳጳሳት፡አባ፡ጳውሎስ፡ወይዕቀቦሙ፡ለኵ ሎሙ፡ሊቃነ፡ጳጳሳት፡ወለኵልነ፡ውሉደ፡ አሐቲ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ቅድስት፡እንተ፡ ላዕለ፡ኵሉ፡ጉባኤ፡ዘሐዋርያት፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

በተባረከ፡የታኅሣሥ፡ወር፡የሚነበብ፡ንባብ፡ ደረሰ፡ተፈጸመ። ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ ይሁን፡ፈጣሪያችን፡አብ፡ወልድ፡መንፈስ፡ ቅዱስም፡በይቅርታውና፡በምሕረቱ፡በከበሩና፡ በተመረጡ፡ነቢያትና፡ሐዋርያት፡አማላጅነት፡ በሰማዕታት፡በጻድቃን፡በሊቃነ፡ጳጳሳት፡በኤጲ ስቆጶሳት፡በቀሳውስት፡በዲያቆናት፡በደና ግል፡በመነኮሳት፡በቅዱሳን፡መላእክትም፡ ልመና፡ይልቁንም፡በእመቤታችን፡በቅድስት፡ ድንግል፡ማርያም፡አማልጅነት፡ርእሰ፡ሊቃነ፡ ጳጳሳት፡አባ፡ጳውሎስን፡ይጠብቀው። ሊቃነ፡ ጳጳሳቱንም፡ሁሉ፡ይጠብቅ፡ከሁሉ፡በላይ፡ የምትሆን፡ሐዋርያት፡ሰብስበው፡አንድ፡ያደረ ጓት፡የአንዲት፡ቅድስት፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ ልጆች፡የሆን፡ሁላችንንም፡ይጠብቀን፡ለዘላ ለሙ፡አሜን።

www.ethiopianorthodox.org